# ስንክሳር ዘወርኀ ጥር

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩፡ አምላክ ፡ ወርኀ ፡ ጥር ፡ ብሩክ ፡ ፲፡ ሰዓተ ፡ መዓልቱ ፡ ወእምዝ ፡ ይትዌሰክ ፡ ወአመ ፡ ፩ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ፡ሊቀ፡ዲያቆናት፡ወቀዳሜ፡ሰማዕት።

፪፡ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡እስጢፋኖስ፡ኮነ፡ስምዐ፡በእንቲአሁ፡መጽሐፈ፡ግብረ፡ሐዋርያት፡ከመ፡ ውእቱ ፡ ምሉዐ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኃይል፡ ወይገብር ፡ ዐቢየ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ፡በውስተ፡ሕዝብ።

፫፡ወእምዝ፡ቀንኡ፡ላዕሌሁ፡አይሁድ፡ወአቅፀሩ፡ሎቱ፡ዕደወ፡ሰማዕተ፡ሀሰት፡ወመሀርዎሙ፡ ከመ፡ይበሉ፡ሰማዕናሁ፡ለዝ፡ብእሲ፡እንዘ፡ ይነብብ፡ነገረ፡ፅርፈት፡ላዕለ፡ሙሴ፡ወላዕለ ፡ እግዚአብሔር ።

፬፡ ወሆክዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወለረበናት ፡ ወለጸሐፍት፡ወሮድዎ፡ወሰሐብዎ፡ወተባጽሕዎ፡ኀበ፡ዐውድ።

፭፡ወአቀሙ፡ሎቱ፡ሰማዕተ፡ሐሰት፡ወይቤሉ፡ዝ፡ ብእሲ፡አበየ፡ያርምም፡እንዘ፡ይነብብ፡ፅርፈተ፡ዲበ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወዲበ፡ኦሪት፡ወሰማዕናሁ፡እንዘ፡ይብል፡ ኢየሱስ፡ናዝራዊ፡ ይነሥቶ፡ለቤተ፡መቅደስ፡ወይሥዕር፡ኦሪተክሙ፡ዘወሀበክሙ፡ሙሴ።

፮፡ወነጸርዎ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዐውደ ፡ ወርእዩ ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር።

፯፡ወይቤሎ፡ሊቀ፡ካህናት፡አማንኑ፡ከመዝ፡ትቤ፡ ወይቤ ፡ ውእቱ ፡ ስምዑ ፡ አኃዊነ ፡ ወአበዊነ ፡ አምላከ፡ስብሐት፡አስተርአዮ፡ ለአቡነ ፡ አብርሃም ፡እንዘ፡ሀሎ፡በማዕከለ፡አፍላግ፡ዘሶርያ ዘእንበለ ፡ ይፍልስ ፡ ካራን ። ወይቤሎ ፡ ጻእ ፡ እምብሔርከ ፡ ወተፈለጥ ፡ እምአዝማዲከ ፡ ወነዓ፡ውስተ፡ብሔር፡ዘአነ፡አርእየከ።

፰፡ ወእምዝ ፡ ወጺአ ፡ እምከላውዴዎን ፡ ነበረ ፡

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የተባረከ ፡ የጥር ፡ ወር ፡ የመዓልቱ ፡ ሰዓት ፡ ዐሥር ፡ ነው ፡ ከእንግዲህም ፡ ይጨመርለታል ። በዚችም ፡ ጥር፡ አንድ፡ቀን፡የዲያቆናት፡አለቃ፡የሰማዕታት፡ መጀመሪያ፡የሆነ፡የከበረ፡እስጢፋኖስ፡ምስክር፡ሁኖ፡ሞተ።

፪፡ ለዚህም ፡ ለከበረ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የእግዚአብሔርን፡ኃይልና፡ጸጋ፡የተመላ፡ሰው፡እንደነበረና፡በሕዝቡም፡መካከል፡ታላላቅ፡ተአምራትንና፡ድንቅ፡ሥራን፡ይሠራ፡እንደነበረ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ የተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለርሱ፡ምስክር፡ሆነ።

፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አይሁድ ፡ ቀኑበት ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮች፡የሚሆኑ፡ሰዎችንም፡አስነሡበት፡ ይህን፡ሰው፡በሙሴና፡ በእግዚአብሔር ፡ላይ፡ የስድብ ፡ ቃልን ፡ ሲናገር ፡ ሰምተነዋል ፡ እንዲሉ፡ሐሰትን፡አስተማሩአቸው።

፬፡ ሕዝቡንና ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ጸሐፊዎችንም ፡ አነሣሡአቸው፡አዳርሱን፡ብለው፡ከበው፡እየጐተቱ፡ወደ፡ሸንጎ፡ወሰዱት።

፭፡ የሐሰት ፡ ምስክሮችንም ፡ አቆሙበት ፡ እነርሱም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ላይ ፡ በኦሪትም ፡ ላይ ፡ ስድብን ፡ ሲናገር ፡ ተው ፡ ብንለው ፡ እምቢ ፡ አለ ። የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ቤተ፡መቅደሳችሁን፡ያፈርሰዋል፡ሙሴ፡የሰጣችሁን፡ኦሪታችሁንም፡ይሽራል፡ሲል፡ሰምተነዋል፡አሉ።

፮፡በአደባባይ፡ተቀምጠው፡የነበሩት፡ሁሉ፡ተመለከቱት፡ፊቱንም፡ የእግዚአብሔርን፡መልአክ፡ፊት፡ሁኖ፡አዩት።

፯፡ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ እንዲህ ፡ አልክ፡አለው።እርሱም፡እንዲህ፡አለ፡ወንድሞቻችንና፡አባቶቻችን፡ስሙ፡ወደ፡ካራን፡ ከመምጣቱ ፡ አስቀድሞ ፡ በሶርያ ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡ ለአባታችን ፡ለአብርሃም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር፡ ተገለጠለት።ካገርህ፡ውጣ፡ከዘመዶችህም፡ተለይ፡ እኔ፡ወደማሳይህ፡ሀገርም፡ና፡አለው።

፰፡ከዚህም፡በኋላ፡ከከላውዴዎን፡ወጥቶ፡በካራን፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘስሙ ፡ ሳውል ። ወወገርዎ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡
እንዘ፡ይጼሊ፡ወይብል፡እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ተመጠዋ፡ለነፍስየ።
፲፰፡ ወሶበ፡ሰገደ፡ከልሐ፡በዐቢይ፡ቃል፡ወይቤ፡
እ ፡ እግዚእ ፡ ስረይ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ፡ ኃጢአ
ቶሙ ፡ ወኢትረሲ ፡ ቦሙ ፡ ጌጋየ ፡ ወዘንተ ፡
ብሂሎ ፡ ኖመ ። ወመጽኡ ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡
ወነሥኡ፡ ሥጋሁ፡ለእስጢፋኖስ፡ ወቀበርዎ፡
ወለሀውዎ፡ዐቢየ፡ላሀ።
፲፱፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይም
ሐረነ፡በትንብልናሁ፡ለእስጢፋኖስ፡ ሐዋርያ፡
ወሰማዕት ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓ
ለመ፡ዓለም፡አሜን።

ያስጠብቁ፡ ነበር ። ጌታዬ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡
ሆይ፡ ነፍሴን ፡ ተቀበል ፡ እያለ፡ ሲጸልይ፡ እስጢ
ፋኖስን፡ በደንጊያ፡ወገሩት።
፲፰፡ ዘለፍለፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜም ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድ
ርጎ፡አቤቱ፡ይህን፡ኃጢአታቸውን፡ይቅር፡በላ
ቸው ፡ በደልም ፡ አታድርግባቸው ፡ ይህንንም ፡
ብሎ፡አረፈ።ደጋግ፡ሰዎችም፡መጥተው፡የእስ
ጢፋኖስን ፡ ሥጋ ፡ ወስደው ፡ ቀበሩት ፡ ታላቅ ፡
ልቅሶም፡አለቀሱለት።
፲፱፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡
ሐዋርያና፡ሰማዕት፡በሆነ፡በእስጢፋኖስ፡አማ
ላጅነት፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡
ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ በልዎ፡እስመ፡ለክሙ፡ተውህበ፡ለእስጢፋኖስ፡ በዓሎ፡ከመ፡ትግበሩ፡ክዐበ። በዛቲ፡ዕለት፡ እለ፡ጸሐፉ፡ሐሳበ።ቦ፡ዘይቤ፡ባቲ፡ሰከበ።ወቦ፡ዘይቤ፡ዓፅሙ፡ተረክበ።

፳፡ ወበዛቲ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ለውን
ድዮስ፡ በመዋዕሊሁ፡ለመክስምያኖስ፡ንጉሥ፡
ዐላዊ፡ዘእምብሔረ፡ሶርያ።
፳፩፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡ሶበ፡ሰምዐ፡ዜናሁ፡መክስ
ምያኖስ፡ንጉሥ፡ከመ፡ውእቱ፡መስተጋድል፡
ወያመልኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈነወ ፡ ወአብ
ጽሐ፡ኀቤሁ፡ወአቅረበ፡ሎቱ፡ንዋየ፡ብዙኀ፡
ወአኀዘ ፡ ይኂጦ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ሃይማኖቶ ፡
ወያምልክ ፡ አማልክቲሁ ። ወቅዱስሰ ፡ ለውን
ድዮስ፡ ተሣለቀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአስተቃለለ ፡ ሀብ
ታቲሁ ፡ ወአኅሰረ ፡ ክብሮ ፡ ወረገመ ፡ አማል
ክቲሁ፡ርኩሳነ።
፳፪፡ አሜሃ ፡ ተምዐ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡
ይስቅልዎ ፡ ውስተ ፡ መንኰራኵር ፡ ወይኰ
ንንዎ ፡ ዐቢየ ፡ ኵነኔ ። ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡
አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ወእግዚእነሰ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
አውጽኦ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና።
፳፫፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ይዝብጥዎ ፡ በድንቡሳት ፡
ወያፍልሑ፡ቅብዐ፡ወስብሐ፡በጸሕል፡ዐቢይ
ወይደይዎ፡ ለቅዱስ፡ ውስቴቱ፡ ወገብሩ፡ ቦቱ፡
ዘንተ፡ኵሎ፡ኵነኔ፡እስመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ያጸንዖ ፡ ወያስተ
ዔግሦ፡ወያነሥኦ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና።
፳፬፡ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ ኰንኖቶ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡
ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡
በመንግሥተ፡ሰማያት። ወአስተርአዩ፡እምሥ
ጋሁ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡ብዙኃን፡ወተ
ሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድረ ፡ ሶርያ ፡

፳፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በከሀዲው ፡ መክስምያኖስ ፡
ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከሶርያ ፡ አገር ፡ የከበረ ፡
ለውንድዮስ፡ በሰማዕትነት፡ሞተ።
፳፩፡ የዚህንም፡ቅዱስ፡ዜና፡እግዚአብሔርን፡የሚያ
መልክ ፡ ተጋዳይ ፡ እንደሆነ ፡ ንጉሥ ፡ መክስም
ያኖስ፡በሰማ፡ጊዜ፡ልኮ፡ወደርሱ፡አስመጣው፡
ሃይማኖቱንም ፡ ትቶ ፡ አማልክቶቹን ፡ ያመል
ክለት፡ዘንድ፡ብዙ፡ገንዘብ፡አቀረበለትና፡ይሸነ
ግለው ፡ ጀመረ ፡ የከበረ ፡ ለውንድዮስ ፡ ግን ፡
ዘበተበት፡ስጦታውንም፡በማቃለል፡ክብሩን፡
አጐሳቈለ፡የረከሱ፡አማልክቶቹንም፡ረገመ።
፳፪፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቆጥቶ ፡ በመንኰራኵር፡
ውስጥ፡ሰቅለው፡ጽኑዕ፡የሆነ፡ሥቃይን፡እንዲ
አሠቃዩት ፡ አዘዘ ። ንጉሥ ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉ
በት ፡ የክብር ፡ ባለቤት ጌታችን ፡ ግን ፡ ያለ ፡
ጥፋት፡በጤና፡አወጣው።
፳፫፡ ዳግመኛም ፡ በብረት ፡ ዘንጎች ፡ ይደበድቡት ፡
ዘንድ ፡ ቅባትና ፡ ስብንም ፡ በታላቅ ፡ ድስት ፡
አፍልተው ፡ ቅዱስ ፡ ለውንድዮስን ፡ ከውስጡ ፡
ይጨምሩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
ሥቃይንም ፡ አሠቃዩት ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያጸናውና ፡ ያስታ
ግሠው ፡ ያለ ፡ ጉዳትም ፡ በጤና ፡ ያስነሣው ፡
ነበር።
፳፬፡ ማሠቃየቱንም ፡ በደከመው ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡
በሰይፍ፡እንዲቆርጡ፡አዘዘ፡የሰማዕትነት፡አክ
ሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀበለ።
ከሥጋውም፡ድንቆች፡የሆኑ፡ብዙዎች፡ተአም
ራቶች ፡ ተገለጹ ፡ ዜናውም ፡ በሶርያ ፡ አገር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወተሐንፀ፡ሎቱ፡አብያተ፡ክርስቲያን፡ወም
ኔታት። ወበአሐቲ፡እምነ፡አድባራቲሁ፡ተጠ
ምቀ ፡ ባቲ ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ዘአንጾኪያ።
፳፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎተ ፡ ዝንቱ ፡ ሰማዕት ፡ ወበረ
ከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሁሉ ፡ ተሰማ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ገዳ
ማት፡ተሠሩለት፡ከገዳማቱም፡በአንዲቱ፡የአን
ጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የሆነው፡የከበረ፡ሳዊሮስ፡
በሕፃንነቱ፡ተጠመቀባት።
፳፭፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ ፡ ሰማዕት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡
ከኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለለውንድዮስ ፡ ሰማዕተ ፡ ልደቱ ፡ ለቃል። በአብትረ ፡ ኀዊን ፡ ዝቡጥ ፡ ወበመንኰራኲር፡
ቀሡል። ወድኅረ ፡ መተሩ ፡ ርእሶ ፡ በመጥባሕት ፡ ስሑል። እምኔታቲሁ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ መርጡል።
ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ተጠምቀ ፡ ሳዊሮስ ፡ ኀያል።

፳፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡
አባ፡ መቃርስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡
እስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡
ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፷ወ፱ቱ።
፳፯፤ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ዘእ
ምቅድሜሁ ፡ ተጋብኡ ፡ ኤጲስቆጶሳት፡
ወሊቃውንት ፡ ወልሒቃነ ፡ ግብጽ፡ ወዐ
ርጉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኀበ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ፡
ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይሴአሉ ፡ ወየሐትቱ ፡
እምገዳማውያን ፡ ጻድቃን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስተ ፡ ጾማዕት ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዛቲ፡
ሢመት ፡ ክብርት ። ወእምዝ ፡ ነገሮሙ ፡ ፩
ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡
ወይቤሎሙ ፡ ቀሲስ ፡ መቃርዮስ ፡ ዘይነ
ብር፡ በደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ውእቱ፡
ይደሉ ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት።
፳፰፤ ወሶቤሃ ፡ ኃሠሥዎ ፡ ወአኀዝዎ ፡ ዘእንበለ፡
ፈቃዱ ፡ ወወሰድዎ ፡ አሢሮሙ ፡ እንዘ ፡
ይጸርሕ ፡ ወይብል ፡ አነ ፡ አባሲ ፡ ዘኢይ
በቍዕ ፡ ለዛቲ ፡ ግብር ፡ ወኢሰምዑ ፡ እም
ኔሁ ፡ ቃሎ ፡ አላ፡ ሤምዎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት።
፳፱፤ ወእምዝ ፡ አኀዘ ። ይግበር ፡ ግብረ ፡ ሊቀ
ጵጵስና ፡ ወሤመ ፡ ኤጲስቆጶሳተ ፡ ወካህ
ናተ ፡ በኵሉ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ወሐደሰ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙኃተ፡ ወመዋዕ
ሊሁኒ ፡ ዳኅን ፡ ወሰላም ፡ ዘእንበለ፡ ኀዘን ፡
ወነበረ ፡ በሢመቱ ፡ ፳ ወ፯ ዓመተ፡ ወ፴
ወ፩ ዕለተ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ወአዕረፈ ፡ በሰላም።
፴፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበ
ረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፳፮፤ በዚችም ፡ ቀን፡ የእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ፡
ጳጳሳት ፡ የከበረ፡ አባት ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡
አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ ስልሳ ፡ ዘጠነኛ ፡ ነው።
፳፯፤ ከእርሱ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ አባ ፡ ሚካኤልም፡
በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ሊቃ
ውንቱ ፡ የግብጽም፡ ታላላቆች ፡ ሁሉም ፡
ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ወጥተው፡ ለዚች ፡
ለከበረች ፡ ሹመት ፡ ስለሚገባ ፡ ከዋሻ ፡
ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ ደጋጎች ፡ ገዳማውያን፡
ሲጠያየቁና ፡ ሲመረምሩ፡ ኖሩ ። ከዚህም ፡
በኋላ ፡ አንድ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ስለዚህ ፡
አባት ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡
በአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ የሚኖር ፡ ቀሲስ ፡
አባ ፡ መቃርስ ፡ እርሱ ፡ ለዚች ፡ ሹመት ፡
ይገባል።
፳፰፤ በዚያንም ፡ ጊዜ፡ ፈልገው ፡ ያዙት ፡
እርሱም ፡ እኔ ፡ ለዚች ፡ ሥራ ፡ የማል
ጠቅም፡ በደለኛ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ሲጮህ ፡ ያለ፡
ፈቃዱ ፡ አሥረው ፡ ወሰዱት ፡ ሊቀ ፡ ጵጵ
ስና ፡ ሾሙት ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ የሚላቸውን ፡
ቃሉን ፡ አልሰሙትም።
፳፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናውን ፡
ሥራ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡
በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ካህናትን ፡
ሾመ ፡ ብዙዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያና
ትንም ፡ አደሰ ፡ ጊዜውም ፡ ያለ ፡ ኀዘን ፡
የጤንነትና ፡ የሰላም ፡ ጊዜ ፡ ነበር።
ሹመቱም ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከአርባ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ኖረ ፡ እግዚአብሔርንም ፡
አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።
፴፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡
በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡
አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለመቃርዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሤምዎ። አሐዱ ፡ ጻድቅ ፡ ከመ ፡ አቅደመ ፡ ዜንዎ። ዝንቱ ፡ መምህር ፡ ዘእሴፈዎ ። ጕንደ ፡ ጌጋይየ ፡ ለያፍጥን ፡ ሠርዎ። እንዘ ፡ አዕጹቂሁ ፡ ይመትር ፡ ወይመልሕ ፡ ሥርዎ።

፴፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታተ ፡ አክሚም ፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ዜናሆሙ።

፴፪፤ ወሀሎ ፡ ፩ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ አክሚም ፡ መስፈን ፡ ወባዕል ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ወስሙ ፡ አልሲድማልዮስ ፡ ወወለደ ፡ ፪ተ ፡ ውሉደ ፡ ዘስሞሙ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወሰከላብዮስ ፡ ወእሙንቱ ፡ ተሐፅኑ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘምስለ ፡ ጸዊም ፡ ወጸልዮ።

፴፫፤ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሆሙ ፡ ፈተዉ ፡ ምንኵስና ፡ ወአስተርዮሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአሔር ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ ገዳማዊ ፡ ወሐዊሮሙ ፡ ለብሱ፡ በህየ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወነበሩ ፡ በተጋድሎ ፡ ብዙኀ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ።

፴፬፤ ወእምድኅረ ፡ ኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ተሠይመ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ቀሲሰ ፡ ወሰከላብዮስ ፡ ዲያቆነ፡ ወሶበ ፡ ክህደ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ አዘዞ፡ ለአርያኖስ ፡ መኰንነ ፡ እንዴናው ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ኵሎ ፡ ክርስቲያነ ፡ እለ ፡ ኢይሰግዱ፡ለአማልክት።

፴፭፤ ወበጺሐ ፡ አርያኖስ ፡ ሀገረ ፡ አክሚም ፡ አኀዞ ፡ ለአባ ፡ ብኑድያስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወአሠሮ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ። ወአስተርዮሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሚካኤል ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ ወለሰከላብዮስ ፡ ወነገሮሙ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወይንሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ ወእሙንቱ ፡ ሖሩ ፡ አመ ፡ ፰ ወ ፰ ለታኅሣሥ ፡ ከዊኖሙ ፡ እስራ ፡ ወአርባዕተ ፡ መነኰሳተ።

፴፮፤ ወበጺሐሙ ፡ ሀገረ ፡ አክሚም ፡ ረከብዎሙ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጋቢኦሙ ፡ ምስለ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ወደቂቆሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመድኃኒነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ያብዕሉ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ስቡሕ ፡

፴፩፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ የአክሚም ፡ ሰማዕታት ፡ የምስክርነታቸውን ፡ ተጋድሎ ፈጸሙ ፡ ዜናቸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው።

፴፪፤ አክሚም፡ በሚባል፡ አገር ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ ባለጸጋ ፡ ነው ፡ ስሙም ፡ አልሲድማልዮስ ፡ ይባላል ፡ ስማቸው ፡ ዲዮስቆሮስና ፡ ሰከላብዮስ ፡ የሚባል ፡ ሁለት ፡ ልጆችን ፡ ወለደ ፡ እነርሱም ፡ ከመጾምና ፡ ከመጸለይ ፡ ጋር ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፈራት ፡ አደጉ።

፴፫፤ አባታቸውም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ፡ ምንኵስናን ፡ ተመኙ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ተገልጦላቸው ፡ ወደ ፡ ገዳማዊ ፡ አባ ፡ ሙሴ፡ ገዳም ፡ እንዲሔዱ ፡ አዘዛቸው ፡ ሒደውም ፡ በዚያ ፡ መነኰሱ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችንም ፡ እያደረጉ ፡ በብዙ፡ ተጋድሎ ፡ ኖሩ።

፴፬፤ ከጥቂት ፡ ወራትም ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ቅስና ፡ ሰከላብዮስም ፡ ዲቁና ፡ ተሾሙ። ዲዮቅልጥያኖስም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስን ፡ በካደው ፡ ጊዜ፡ ለጣዖታት ፡ የማይሰግዱ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ሁሉ ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ የእንዴናው ፡ ገዥ ፡ አርያኖስን ፡ አዘዘው።

፴፭፤ አርያኖስም፡ አክሚም፡ ከተማ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ አባ ፡ ብኑድያስን ፡ ያዘውና ፡ አሥሮ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ገባ። የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ሚካኤልም ፡ ለዲዮስቆሮስና ፡ ለሰከላብዮስ፡ ተገለጸላቸው ፡ ወደ ፡ መኰንኑም ፡ ሒደው ፡ የምስክርነት ፡ አክሊልን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ነገራቸው ፡ እነርሱም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ መነኰሳት ፡ ሁነው ፡ ሔዱ።

፴፮፤ ወደ፡ አክሚም ፡ ከተማም ፡ ሲደርሱ ፡ በመድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የከበረ ፡ የልደትን ፡ በዓል ፡ ለማክበርና ፡ ስለ፡ ከበረ፡ ስሙም ፡ ይሞቱ ፡ ዘንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖችን ፡ ከሴቶቻ

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ፡ ይሙቱ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ወአባ ፡ ብኑድያስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቦአ ፡ ምስሌሆሙ፡ ወበጣኒታ ፡ ቀደሰ፡ አባ፡ ብኑድያስ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ አግዮስ ፡ ጸርሑ ፡ መላእክት ፡ እንዘ ፡ ይብሉ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ፡ስብሐቲከ።

፴፯፤ አሜሃ ፡ ርእይዎ፡ ቅዱሳን ፡ ለመድኃኒነ፡ ነቢሮ፡ ዲበ ፡ ታቦት ፡ ወመላእክት ፡ ይቀውሙ ፡ ዐውዶ ፡ ወውእቱ ፡ ይነሥእ ፡ ቍርባነ ፡ ወያነብሮ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ካህን ፡ ወያቄርቦሙ ፡ ለጉቡአን።

፴፰፤ ወሶቤሃ ፡ በጽሐ ፡ አርያኖስ ፡ መኰንን ፡ እንዘ ፡ ይትመዐዕ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ወአኀዞሙ ፡ ለ፪ቱ ፡ ሊቃናተ ፡ ሀገር ፡ ዘስሞሙ፡ ብሕዋፋ ፡ ወውኒን ፡ ወመተረ ፡ ርእሶሙ ፡ በሰይፍ ፡ ወድኀረ ፡ እሉ ፡ ቀተለ ፡ ዲያቆናተ ፡ ወንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ወመዘምራነ ፡ ወመገብተ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ **ወኢያትረፈ** ፡ ደቀ ፡ ወአንስተ ፡ እስከ ፡ ወጽአ ፡ ደሞሙ ፡ እምአንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወውኅዘ ፡ መጠነ ፡ እሥራ ፡ በእመት።

፴፱ **ወእምዝ** ነሥአሙ ፡ ለአባ ፡ ብኑድያስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለዲዮስቆሮስ ፡ ወለሰከላብዮስ ፡ ወለአኃው ፡ እለ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወወሰዶሙ ፡ ምስሌሁ ፡ ወኄጠሙ ፡ ከመ ፡ ይስግዱ ፡ ለጣዖት ፡ ወሶበ ፡ አበይዎ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ እስከ ፡ ይትሌለያ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ ወአስተርአዮሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወአሕየዎሙ ፡ ወርእዮሙ፡ ኮርዮን ፡ ወፊልሞና ፡ ዐበይተ ፡ ሐራሁ ፡ ለአርያኖስ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ ወእምሐራሁ ፡ ፹፯ ፡ አምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአዘዘ ፡ ይውርውዎሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ወፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ፡ አመ ፡ ፴ሁ ፡ ለታኅሣሥ ፡ ወብዙኃን ፡ እምጉቡእን ፡ ወረዉ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ርእሶሙ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያጌብሮሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ነአምን ፡

ቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ ተሰብስበው ፡ አገኙአቸው ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ አባ ፡ ብኑድያስም፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር ፡ ገባ። በማግሥቱም ፡ አባ፡ ብኑድያስ ፡ ቀደሰ ፡ አግዮስ ፡ ወደሚለው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መላእክት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ አመሰገኑ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሸናፊ ፡ ፍጹም ፡ የጌትነትህ ፡ ምስጋና ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ የመላ ፡ ነው።

፴፯፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መድኃኒታችንን ፡ በመሠዊያው፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ መላእክትም ፡ በዙሪያው ፡ ቆመው ፡ ቍርባኑን ፡ እያነሣ፡ በካህኑ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ በማድረግ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ሲያቆርባቸው፡ ቅዱሳኑ ፡ አዩት።

፴፰፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ መኰንኑ ፡ አርያኖስ ፡ ደረሰ ፡ ተቆጥቶም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ስማቸው ፡ ብሕዋፋና ፡ ውኒን ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት፡ የሀገር ፡ አለቆችን ፡ ይዞ ፡ ራሳቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጠ ፡ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ ዲያቆናትን ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆናትን ፡ መዘምራንን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹሞችን ፡ ደማቸው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጃፍ ፡ ወጥቶ ፡ ሃያ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ እስቲጎርፍ ፡ ሴቶችና ፡ ልጆችንም ፡ ሳያስቀር፡ አረዳቸው።

፴፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ አባ ፡ ብኑድያስን ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ሰከላብዮስን ፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ መነኰሳትን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰዳቸው ፡ ለጣዖትም ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ሸነገላቸው ፡ እምቢ ፡ በአሉትም ፡ ጊዜ ፡ ዐጥንቶቻቸው ፡ እስከሚለያዩ ፡ ድረስ ፡ ይደበድቧቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ተገልጾላቸው ፡ አዳናቸው ፡ የአርያኖስም ፡ የጭፍሮቹ ፡ ታላላቆች ፡ ኮርዮንና ፡ ፊልሞና ፡ ከጭፍሮችም ፡ አርባ ፡ ሰዎች ይህን ፡ ድንቅ ፡ ተአምር ፡ አይተው ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመኑ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ማንደጃም ፡ እንዲጥሏቸው ፡ አዘዘ። ተጋድሏቸውንም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ፈጸሙ ፡ ከተሰበሰቡትም ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎች ፡ የሚያስገድዳቸው ፡ ሳይኖር ፡ በእውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ቦክርስቶስ ፡ እናምናለን ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ እሳቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ወከመዝ ፡ ፈጸሙ፡ስምዖሙ።

፴፡ ወእምዝ ፡ አመ ፡ ፩ ፡ ለጥር ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ሙቁሐነ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወሰከላብዮስ ፡ አስተርአዮሙ ፡ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወአጥብዖሙ ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ስምዖሙ ፡ ወጸቢሖ ፡ ተናገሮሙ ፡ አርያኖስ ፡ ለቅዱሳን ፡ በእንተ ፡ ሰጊድ ፡ ለአማልክት ፡ ወሶበ ፡ አበይዎ፡ አዘዘ ፡ ይምልሑ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ ወነሥአ ፡ ቅዱስ ፡ አዕይንቲሁ ፡ እለ ፡ ተመልሓ ፡ ወሚጦን ፡ ውስተ ፡ መካኖን ፡ ወርእዮ ፡ ሉክዮስ፡ መኰንን ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ አምነ ፡በእግዚእነ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወወገርዎሙ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ወፈጸሙ ፡ ስምዖሙ።

፴፩፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ አርያኖስ ፡ ይቅትልዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕት ፡ ወእንዘ ፡ ይጼልዩ ፡ አስተርአዮሙ ፡እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ፡ ስብሐት ፡ ወወሀቦሙ ፡ ኪዳነ ፡ ለዘይጼውዕ ፡ ስሞሙ ፡ ወይገብር ፡ ተዝካሮሙ ፡ ወይጽሕፍ ፡ ገድሎሙ ፡ ከመ ፡ ይኈልቈ ፡ ምስለ ፡ ማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ ወእምዝ ፡ ቀርበ ፡ ሐራዊ ፡ ወመተረ ፡ ርእሶ ፡ ለቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወለሰከላብዮስ ፡ መተርዎ ፡ እምሐቌሁ ፡ ወለ፳ወ፬ቱ ፡ መነኰሳት ፡ ሰጠቅዎሙ ፡ እምነ ፡ ቆሞሙ ፡ ወተከለሉ ፡ አመ ፡ ፩ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ወገነዘ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘምአዝማዲሆሙ ፡ ወቀበሮሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተቀደስት ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስቅዱስ ፡ ወለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ ሰማዕታት ፡ በሀገረ ፡ አክሚም ፡ ፹ወ፩፻ወ፴ ፡ ኮነ ፡ ኍልቆሙ።

፴፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ማንደጃ ፡ ራሳቸውን ፡ ወረወሩ ፡ ምስክርነታቸውንም ፡ እንደዚህ ፡ ፈጸሙ።

፴፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጥር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዲዮስቆሮስና ፡ ሰከላልብዮስ ፡ ታሥረው ፡ ሳሉ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ተገለጠላቸውና ፡ ምስክርነታቸውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ አበረታቸው ፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ለአማልክት ፡ ስለ፡ መስገድ ፡ አርያኖስ ፡ ተናገራቸው ፡ አይሆንም ፡ በአሉትም ፡ ጊዜ ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ዐይኖቹን ፡ ያወልቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ቅዱሱም ፡ የወለቁ ፡ ዐይኖቹን ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ቦታቸው ፡ መለሳቸው ፡ መኰንኑ ፡ ሉክዮስም ፡ አይቶ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ አመነ ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ወርውረዋቸው ፡ ምስክርነታቸውንም ፡ ፈጸሙ።

፴፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበሩ ፡ ሰማዕታትን ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ አርያኖስ ፡ አዘዘ ፡ ሲጸልዩም ፡ የክብር ፡ ባቤለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተገለጠላቸው ፡ ስማቸውን ፡ ለሚጠራ ፡ መታሰቢያቸውንም ፡ ለሚያደርግ፡ ገድላቸውንም ፡ ለሚጽፍ ፡ ከቅዱሳን ፡ አንድነት ፡ ይቈጥረው ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጣቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ ቀርቦ ፡ የቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ራስ ፡ ቆረጠ ፡ ሰከላብዮስንም ፡ ከወገቡ ፡ ላይ ፡ ቆረጡት ፡ ሃያ ፡ አራቱን ፡ መንኰሳትም ፡ ከቁመታቸው ፡ ሠነጠቋቸው ፡ በዚች ፡ በጥር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁሉም ፡ ተቆረጡ ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ የሆነ ፡ ሳሙኤልም ፡በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስቅዱስ ፡ ስም ፡ በከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ቀበራቸው ፡ በሀገረ ፡ አክሚም ፡ የተገደሉ ፡ ሰማዕታትም ፡ ቍጥራቸው ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሆነ።

፴፪፡ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በሁሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ ወሰከላብዮስ ፡ አያዩ ። ምስለ ፡ ሰብአ ፡ አክሚም ፡ በስምዕ ፡ እለ ፡ መዊተ ፡ ዐረዩ። ሐራ ፡ አርያኖስ ፡ ለቀትል ፡ እለ ፡ ተረሰዩ። ለአሐዱ ፡ ርእሶ ፡ በመጥባት ፡ አውቀዩ። ወማዕከለ ፡ ሐቌሁ ፡ በሰይፍ ፡ ካልአ ፡ ሌለዩ።

፴፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ዘኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ዘእንበለ ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡ ትማልም ፡ ወዮም ፡ ወዝ ፡

፴፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ በሰማዕትነት ፡ የተገደሉ ፡ አሉ ፡ እሊህም ፡ ዛሬና ፡ ትላንት ፡ ከተ

www.ethiopianorthodox.org

ውእቱ ፡ ዘቀተሎሙ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ወትልቆሙ ፡ ፰፻ካህናት ፡ ፻ወ፴ ዲያቆናት ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ መምህራን ፡ ወ፹መገብተ ፡ ቤተ ፡ ክርስያን ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ መሳፍንት ፡ ፻ወ፶ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ወሕዝባውያን ፡ ፹፻ወ፬፻ት። ወሊቃናቲሆሙ ፡ ልድያኖስ ፡ ወታድሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፪ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አቤል ፡ ጻድቅ ፡ ዘተክዕወ ፡ ደሙ ፡ በዓመፃ ፡ ወውእቱ ፡ በኩረ ፡ ምውታን ፡ ዘቀተሎ ፡ ቃየል ፡ እኁሁ።

፪፤ ምክንያቱሰ ፡ ሶበ ፡ ዐለወ ፡ አዳም ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበልዐ ፡ እምዕፀ ፡ ዘአዘዞ ፡ ከመ ፡ ኢይብላዕ ፡ አሜሃ ፡ ተሠልጠ ፡ ሞት ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ ውሉዱ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ፡ ለኃጢአት ፡ ወተበውሐ ፡ ሰይጣን ፡ ለአስሕቶ ፡ ዓለም ፡ ወእምዝ ፡ ወጺአ ፡ እምገነት ፡ ወረደ ፡ ታሕቲተ ፡ ምድረ ፡ ወነበረ ፡ ፯ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ፡ ወይላሁ ፡ በእንተ ፡ ጌጋዩ ፡ ወበእንተ ፡ ዐሊወ ፡ ትእዛዙ ፡ ለፈጣሪሁ።

፫፤ ወእምዝ ፡ አእመራ ፡ አዳም ፡ ለሔዋን ፡ ወፀንሰት ፡ ወወለደቶሙ ፡ ለቃየል ፡ ወለኤልዩድ ፡ እኅቱ ፡ ወዳግመ ፡ አእመራ ፡ ወወለደቶሙ ፡ ለአቤል ፡ ወለአቅሌማ ፡ እኅቱ ፡ ወሶበ ፡ ወርዘዉ ፡ ይቤላ ፡ አዳም ፡ ለሔዋን ፡ ናሁ ፡ ወርዘዉ ፡ ደቂቅኪ ፡ ለያውስባ ፡ ቃየል ፡ ለአቅሌማ ፡ እኅተ ፡ አቤል ፡ ወአቤል ፡ ያውስባ ፡ ለኤልዩድ ፡ እኅተ ፡ ቃየል።

፬፤ ወይቤላ ፡ ቃየል ፡ ለእሙ ፡ ሔዋን ፡ ይደሉ ፡ ሊተ ፡ እንሣእ ፡ እኅትየ ፡ ዘተወልደት ፡ ምስሌየ ፡ ወአቤልኒ ፡ ይንሣእ ፡ እኅቶ ፡ ዘተወልደት ፡ ምስሌሁ ፡ እስመ ፡ ኤልዩድ ፡ ዘተወልደ ፡ ምስሌሃ ፡ ቃየል ፡ ትሜኒ ፡ ፈድፋደ ፡ እምአቅሌማ ፡ ወትመስል ፡ ሔዋንሃ ፡ እማ።

፭፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አዳም ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ዐዐቦ ፡ ጥቀ ፡ ወይቤሎ ፡ ለቃየል ፡ ኢይደልወከ ፡ ትንሣእ ፡ እኅተከ ፡ ዘተወልደት ፡ ምስሌከ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ አዕርጉ ፡ መሥዋዕተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ ዘሠምረ ፡ መሥዋቶ ፡ ለይኩን።

ገደሉት ፡ ሌላ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ የገደላቸው ፡ ቍጥራቸው ፡ ካህናት ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዲያቆናት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ መምህራን ፡ ኀምሳ ፡ ሦስት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምንት ፡ ሰማንያ ፡ መሳፍንት ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ሕዝባውያን ፡ ስምንት ፡ ሽህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነው ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሁለት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ደሙ ፡ በግፍ ፡ የፈሰሰ ፡ ጻድቁ ፡ አቤል ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ወንድሙ ፡ ቃየል ፡ የገደለው ፡ የሙታን ፡ በኵር ፡ የሆነ ፡ ነው።

፪፤ ምክንያቱም ፡ አዳም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎ ፡ እንዳይበላው ፡ የታዘዘውን ፡ ዕፅ ፡ በላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በእርሱና ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ ሠለጠነ ፡ ለኃጢአትም ፡ ተገዥ ፡ ሆነ ። ሰይጣንም ፡ ሰውን ፡ ለማሳት ፡ ሠለጠነ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አዳም ፡ ከገነት ፡ ወጥቶ ፡ ወደታችኛዋ ፡ ምድር ፡ ወረደ ፡ ስለ ፡ በደሉና ፡ የፈጣሪውንም ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፉ ፡ ፈጽሞ ፡ እያዘነና ፡ እያለቀሰ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ።

፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡ በግብር ፡ አወቃት ፡ ፀንሳ ፡ ቃየልንና ፡ እኅቱን ፡ ኤልዩድን ፡ ወለደች ፡ ሁለተኛም ፡ ዐወቃት ፡ አቤልንና ፡ እኅቱን ፡ አቅሌማን ፡ ወለደቻቸው ፡ አዳምም ፡ ሔዋንን ፡ እነሆ ፡ ልጆችሽ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ አደረሱ ፡ ጕለመሱ ፡ ቃየል ፡ የአቤልን ፡ እኅት ፡ አቅሌማን ፡ ያግባት ፡ አቤልም ፡ የቃየልን ፡ እኅት ኤልዩድን ፡ ያግባት ፡ አለ።

፬፤ ቃየልም ፡ እናቱን ፡ ሔዋንን ፡ እንዲህ ፡ አላት ፡ ለእኔ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ የተወለደች ፡ እኅቴን ፡ ማግባት ፡ ይገባኛል ፡ አቤልም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተወለደች ፡ እኅቱን ፡ ያግባ ፡ ቃየል ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ የተወለደ ፡ ኤልዩድም ፡ እናቷ ፡ ሔዋንን ፡ የምትመስል ፡ እጅግ ፡ የምታምር ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ናትና።

፭፤ አዳምም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ጭንቅ ፡ ሆነበት ፡ ቃየልንም ፡ አብራህ ፡ የተወለደች ፡ እኅትህን ፡ ታገባት ፡ ዘንድ ፡ አይገባህም ፡ አለዚያም ፡ ለእግዚእበሔር ፡ መሥዋዕትን ፡ አቅርቡና ፡ መሥዋዕቱን ፡ ለተቀበለው ፡ ይሁን ፡ አለው።

www.ethiopianorthodox.org

፮፤ ወሶበ ፡ አቅረቡ ፡ መሥዋዕተ ፡ ነጸረ ፡ እግዚአብሔር ፤ ላዕለ ፡ መሥዋዕተ ፡ አቤል ፡ ወኢነጸረ ፡ መሥዋዕቶ ፡ ለቃየል ፡ ወበእንተዝ ፡ ኀዘነ ፡ ወተከዘ ፡ ወተራከቦ ፡ ሰይጣን ፡ ወይቤሎ ፡ ምንት ፡ ያቴክዘከ ፡ ወይቤሎ ፡ ቃየል ፡ እስመ ፡ አቡየ ፡ አዘዘኒ ፡ እኅድግ ፡ እኅትየ ፡ ለእኁየ ፡ አቤል ። ወይቤሎ ፡ ሰይጣን ፡ ስማዕ ፡ እምኔየ ፡ ምዕዳነ ፡ ንሥአ ፡ ለእኁከ ፡ ኀበ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ ወእንዘ ፡ ይሰቲ ፡ ማየ ፡ ዝብጦ ፡ ርእሶ ፡ በዕብን ፡ ወሶበ ፡ ይመውት ፡ ታወሰቦን ፡ ለክልኤሆን ፡ መኑ ፡ ይከልአከ ፡ ወአደሞ ፡ ለቃየል ፡ ምክረ ሰይጣን ፡ አሚሃ ፡ ነደ ፡ ልቡ ፡ በፍትወተ ፡ ዝሙት ፡ ወቀተሎ ፡ ለአቤል ፡ እኁሁ ፡ በከመ ፡ መሀሮ ፡ ሰይጣን ፡ ወሞተ ፡ አቤል ፡ ጻድቅ ፡ በእደ ፡ እኁሁ ፡ በእንተ ፡ ቅንአተ ፡ ብእሲት ፡ ወከመዝ ፡ ቦአ ፡ ሞት ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።

፯፤ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቃየል ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ አቤል ፡ እኁከ ፡ ወይቤሎ ፡ ቃየል ፡ ኢየአምር ፡ ቦኑ ፡ ዐቃቢሁ ፡ አነ ፡ ለአቤል ።

፰፤ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምንተ ፡ ገበርከ ፡ ቃየል ፡ ቃለ ፡ ደሙ ፡ ለአቤል ፡ እኁከ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤየ ፡ እምድር ። ወይእዜኒ ፡ ርግምተ ፡ ትኩን ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ አብቀወት ፡ አፉሃ ፡ ከመ ፡ ትስተይ ፡ ደሞ ፡ ለእኁከ ፡ እምእዴከ ። እስመ ፡ ትትጌበራ ፡ አንተ ፡ ወኢትዌስከ ፡ ከመ ፡ ተሀብከ ፡ ኃይለ ፡ ርዑደ ፡ ውድጉፀ ፡ ኩን ፡ ላዕለ ፡ ምድር ።

፱፤ ወዝንቱ ፡ መርገም ፡ ኮነ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ላዕለ ፡ ቃየል ፡ እስከ ፡ ተደምሰሰ ፡ ዘርዑ ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ።

፲፤ ወእግዚእነሂ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ሶበ ፡ ዘለፎሙ ፡ ለጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ ይቤሎሙ ። ወበእንተዝ ፡ ናሁ ፡ እፌኑ ፡ ኀቤክሙ ፡ ነቢያተ ፡ ወጠቢባነ ፡ ወጸሐፍተ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘትቀትሉ ፡ ወቦ ፡ ዘትሰቅሉ ፡ ወቦ ፡ ዘትቀሥፉ ፡ በመኳርብቲክሙ ፡ ወትሰድድዎሙ ፡ እምሀገር ፡ ለሀገር ።

፲፩፤ ከመ ፡ ይብጻሕ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ደመ ፡ ኵሎሙ ፡ ጻድቃን ፡ ዘተክዕወ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምደመ ፡ አቤል ፡ ጻድቅ ፡ እስከ ፡ ደመ ፡ ዘካርያስ ፡ ወልደ ፡ በራክዩ ፡ ዘቀተልክምዎ ፡ በማዕከለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወምሥዋዕ ።

፮፤ መሥዋዕትንም ፡ በአቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ የአቤልን ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቀበለ ፡ የቃየልን ፡ ግን ፡ አልተቀበለም ፡ ስለዚህም ፡ ቃየል ፡ ፈጽሞ ፡ አዘነ ፡ ሰይጣንም ፡ ተገናኘውና ፡ ምን ፡ ያሳዝንሃል ፡ አለው ፡ ቃየልም ፡ ለወንድሜ ፡ ለአቤል ፡ እኅቴን ፡ እተውለት ፡ ዘንድ ፡ አባቴ ፡ አዘዘኝ ፡ አለው ። ሰይጣንም ፡ ምክርን ፡ ከኔ ፡ ስማ ፡ ወንድምህን ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ይዘኸው ፡ ሒድ ፡ ውኃንም ፡ ሲጣጣ ፡ ራሱን ፡ በደንጊያ ፡ ምታው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱንም ፡ ታገባቸዋለህ ፡ የሚከለክልህ ፡ ማነው ፡ አለው ፡ ለቃየልም ፡ የሰይጣን ፡ ምክር ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ልቡም ፡ በዝሙት ፡ እሳትነት ፡ ነደደ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳስተማረውም ፡ ወንድሙን ፡ አቤልን ፡ ገደለው ፡ ለሴት ፡ ስለ ፡ መቅናትም ፡ ጻድቁ ፡ አቤል ፡ በወንድሙ ፡ እጅ ፡ ሞተ ፡ እንዲህም ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገባ ።

፯፤ እግዚአብሔርም ፡ ቃየልን ፡ ወንድምህ ፡ አቤል ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ አለው ። ቃየልም ፡ አላውቅም ፡ በውኑ ፡ እኔ ፡ የአቤል ፡ ጠባቂው ፡ ነኝን ፡ አለው ።

፰፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ቃየል ፡ ምን ፡ አድርገሃል ፡ የወንድምህ ፡ የአቤል ፡ ደም ፡ ጩኸት ፡ ከምድር ፡ ወደኔ ፡ ደርሷል ። አሁንም ፡ በእጅህ ፡ የፈሰሰውን ፡ የወንድምህን ፡ ደም ፡ ትጠጣ ፡ ዘንድ ፡ አፍዋን ፡ የከፈተች ፡ ምድር ፡ የተረገመች ፡ ትሁን ፡ አንተ ፡ ታርሳታለህና ፡ በረከቷን ፡ ትሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ አትጨምርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፈሪ ፡ ተቅበዝባዥ ፡ ሁን ።

፱፤ ይህም ፡ መርገም ፡ ዘሩ ፡ በጥፋት ፡ ውኃ ፡ ከምድር ፡ ገጽ ፡ እስከ ፡ ሚደመሰስ ፡ በቃየል ፡ ላይ ፡ የበዛ ፡ ሆነ ።

፲፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችንም ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንን ፡ ሲዘልፋቸው ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ስለዚህ ፡ ነቢያትን ፡ ሊቃውንትን ፡ ጥበበኞችን ፡ ወደናንተ ፡ እልካለሁ ፡ ከነርሱ ፡ የምትገድሉት ፡ አለ ፡ የምትሰቅሉትም ፡ አለ ፡ በምኵራባችሁ ፡ የምትገርፉት ፡ አለ ፡ ካንድ ፡ አገር ፡ ወዳንድ ፡ አገር ፡ ታሳድዷቸዋላችሁ ፡፡

፲፩፤ ከጻድቁ ፡ ከአቤል ፡ ጀምሮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ እስከገደላችሁት ፡ እስከ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፡ በዓለም ፡ የፈሰሰው ፡ የጻድቃን ፡ ደም ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ጳውሎስኒ ፡ ይቤ ፡ በተአምኖ ፡ ኀየሰ ፡ መሥዋዕተ ፡ አቤል ፡ እምዘ ፡ ቃየል ፡ ዘአብአ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበእንቲአሁ ፡ ሰማዕተ ፡ ኮኖ ፡ ከመ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ ወሰማዕቱ እግዚአብሔር ፡ በተወክፎ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ወበእንቲሁ ፡ መዊቶ ፡ ዓዲ ፡ ተናገረ።

፲፫፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ኃጥአ ፡ አዳም ፡ ለወልዱ ፡ አቤል ፡ ይቤሎ ፡ ለቃየል ፡ አይቴ ፡ ሀሎ ፡ አቤል ፡ እኁከ ፡ ወአውሥአ ፡ ቃየል ፡ በቍጥዓ ፡ ወይቤ ፡ ኢየአምር ፡ አነኑ ፡ ዐቃቢሁ ፡ ለአቤል ፡ ወሮጸ ፡ አዳም ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ወልዶ ፡ ወረከበ ፡ በኀበ ፡ ፈለግ ፡ በድኖ ፡ ወሐቀፈ ፡ ክሣዶ ፡ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ ቀተለከ ፡ ወወጽአ ፡ ቃል ፡ እምበድኑ ፡ ዘይብል ፡ ቃየል ፡ እኁየ ፡ ቀተለኒ ፡ ወበከዩ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ መጠነ ፡ ፩ቱ ፡ ሱባዔ ፡ ዓመታት ፡ በሞተ ፡ አቤል ፡ ወልዶሙ።

፲፬፤ ወእምዝ ፡ በጽሑ ፡ መላእክት ፡ ኀበ ፡ አዳም ፡ ወይቤልዎ ፡ ኦ ፡ አዳም ፡ አበ ፡ አበወ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ብሥራትከ ፡ ናሁ ፡ ተሣለመ ፡ ወልድከ ፡ አቤል ፡ ዕፀዊሃ ፡ ለገነት ፡ ወዐርገት ፡ ነፍሱ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ መሥዋዕት ፡ ሥሙር።

፲፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፲፪፤ ጳውሎስም ፡ አለ ፡ ቃየል ፡ ካቀረበው ፡ መሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ አቤል ፡ በሃይማኖት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀረበው ፡ መሥዋዕት ፡ ተሻለ ፡ ስለ ፡ እርሱም ፡ ደግ ፡ እንደሆነ ፡ መሰከረለት ፡ መሥዋዕቱንም ፡ በመቀበሉ ፡ ምስክሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ደግ ፡ እንደሆነም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ተናገረ።

፲፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አዳም ፡ ልጁን ፡ በአጣው ፡ ጊዜ ፡ ወንድምህ ፡ አቤል ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ቃየልን ፡ ጠየቀው ፡ ቃየልም ፡ በቁጣ ፡ አላውቅም ፡ እኔ ፡ የአቤል ፡ ጠባቂው ፡ ነውኝን ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ አዳምም ፡ ልጁን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ሮጠ ፡ በወንዝ ፡ ዳርም ፡ በድኑን ፡ አገኘና ፡ አንገቱን ፡ አቅፎ ፡ ማን ፡ ገደለህ ፡ አለው ፡ ከበድኑም ፡ ወንድሜ ፡ ቃየል ፡ ገደለኝ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወጣ። አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ በልጃቸው ፡ በአቤል ፡ ሞት ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ሲያለቅሱ ፡ ኖሩ።

፲፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መላእክት ፡ ወደ ፡ አዳም ፡ መጥተው ፡ የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ አባቶች ፡ አባት ፡ አዳም ፡ የምሥራች ፡ እነሆ ፡ ልጅህ ፡ አቤል ፡ የገነትን ፡ ዛፎች ፡ ተሳለመ ፡ ነፍሱም ፡ እንደ ፡ ተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐረገች ፡ አሉት።

፲፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ የአባቶቻችንም ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአቤል ፡ ዘውክፍት ፡ ምሥዋዐ ። እስመ ፡ ለልዑል ፡ አቅረበ ፡ በኵረ ፡ አባግዐ ። ወበእንተዝ ፡ ተጽሕፈ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡ ስምዐ ። በአምሳሊሁ ፡ በኵረ ፡ እንስሳ ፡ ወሰብእ ፡ ለአምላክ ፡ ያብኡ ። ወበአምሳሊሁ ፡ አበው ፡ ሠርዑ።

፲፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አላኒቆስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ከሀዲ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ይመንኑ ፡ አማልክቲሁ ፡ ፈነወ ፡ ላእካነ ፡ ከመ ፡ የአኀዝዎ ፡ ወይኩንንዎ ፡ ኵነኔ ፡ ዐቢየ።

፲፯፤ ወሰሚዖ ፡ ብፁዕ ፡ አላኒቆስ ፡ ተፈንዎቶሙ ፡ ለላእካነ ፡ ንጉሥ ፡ አስተጋብአሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ዘሀገረ ፡ ሢመቱ ፡ ወቀደሰ ፡ ቍርባነ ፡ ወመጠዎሙ ፡ ምሥጢረ ፡ ቅድሳት ።

፲፮፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ አላኒቆስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ፡ እርሱ ፡ ጣዖታቱን ፡ እንዲአቃልሉ ፡ ለሰዎች ፡ እንደሚያስተምራቸው ፡ ከሀዲው ፡ ንጉሥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይዘው ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይን ፡ ያሠቃዩት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ።

፲፯፤ የንጉሥ ፡ መልክተኞች ፡ መላካቸውን ፡ የተመሰገነ ፡ አላኒቆስ ፡ ሰምቶ ፡ በሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ያሉትን ፡ ሕዝቦች ፡ ሰበሰባቸውና ፡ የቍርባን ፡ ቅዳሴን ፡ ቀድሶ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ አቀበ

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዝ፡ ይቤሎሙ ፡ ጽንዐ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ እምይእዜሰ ፡ ኢትሬ እዩኒ፡ ገጽየ ፡ ወእሙንቱ ፡ በከዩ ፡ ወኢተክ ህሎሙ ፡ ያኅድግዎ ፡ ወወጽአ ፡ ወመጠወ ፡ ርእሶ ፡ ለላእካነ ፡ ንጉሥ ፡ ወእሙንቱ ፡ ነሥ እዎ ፡ ወወሀብዎ ፡ ለመኰንነ ፡ ሀገረ ፡ እንጼ ናው ፡ ወውእቱ ፡ ነሥአ ፡ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ፡እንድኩ፡ወበህየ፡ኰነኖ፡ኵነኔ፡ጽኑዐ፡ ወሶበ፡ደክመ፡እምኰንኖቱ፡አዘዘ፡ይምትሩ፡ ርእሶ፡በሰይፍ፡ወይሥጥቁ፡መታክፍቲሁ። ወአእሚሮ ፡ ከመ ፡ ቀርበ ፡ ፍልሰቱ ፡ እምዓ ለም ፡ አዘዞ ፡ ለአሐዱ ፡ እምኖትያት ፡ መሐይ ምናን ፡ ወይቤሎ ፡ ሶበ ፡ በጻሕክሙ ፡ ውስተ ፡ መርሶ ፡ ረሲ ፡ ሥጋየ ፡ መልዕልተ ፡ ወግር ፡ ውእቱኒ፡ገብረ፡በከመ፡አዘዞ።

፲፰፡ ወእምዝ ፡ መጽኡ ፡ ሰብእ ፡ መሐይምናን ፡ ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ ወገነዝዎ ፡ ወአንበርዎ ፡ ኀቤሆሙ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ፡ ወሐነፁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአንበሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ውስቴታ ፡ ወኮና ፡ እምኔሁ ፡ ተአምራት፡ወመንክራት፡ዐበይት።

፲፱፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረ ከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ላቸው።ከዚህም፡በኋላ፡በቀናች፡ሃይማኖት፡ ጽኑ ፡ ከእንግዲህ ፡ ፊቴን ፡ አታዩኝም ፡ አላ ቸው።እነርሱም፡አለቀሱ፡ሊአስተዉትም፡ አልተቻላቸውም ፡ ወጥቶም ፡ ራሱን፡ ለን ጉሥ ፡ መልክተኞች ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፡ እነርሱም ፡ ወስደው ፡ ለእንጼናው ፡ አገር ፡ መኰንን ፡ ሰጡት ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ሀገረ ፡ እንድኩ ፡ ወስዶ ፡ በዚያ ፡ ጽኑዕ ፡ ሥቃይን ፡ አሠቃየው ፡ ማሠቃየቱም ፡ በሰላቸው ፡ ጊዜ ፡ ትከሻውን ፡ በሰይፍ ፡ ይሠነጥቁ ፡ ዘንድ ፡ ራሱንም ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ፡ አዘዘ ፡ መሞቱን ፡ አውቆ ፡ አማንያን ፡ ከሆኑ ፡ መርከበኞች ፡ አንዱን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡ ወደ ፡ ወደቡ፡ስትደርሱ፡ሥጋዬን፡በኮረብታ፡ላይ፡ አድርግ፡እርሱም፡እንዳዘዘው፡አደረገ።

፲፰፡ከዚህም፡በኋላ፡ምእመናን፡ሰዎች፡መጥተው፡ ሥጋውን ፡ ወስደው ፡ ገነዙት ፡ የስደቱም ፡ ወራት ፡ እስቲያልፍ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ አኖሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሠርተው ፡ ሥጋውን ፡ በውስጧ ፡ አኖሩ ፡ ከእርሱም ፡ ታላላቅ ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶች ፡ ተደረጉ።

፲፱፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአላኒቆስ ፡ ዘሥጡቅ ፡ መትከፉ ። ለመኰንን ፡ በሰይፉ ። ምእመናንሂ ፡ ጽድቀ ፡ እለ ፡ ተሳተፉ ። ከመ፡አዘዞሙ፡እስከ፡ይትሐነፅ፡ምዕራፉ።በመልዕልተ፡ደብር፡ሥጋሁ፡አዕረፉ።

፳ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡ቴዎናስ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስክንድርያ፡ወውእቱ፡እም ኀ ልቆሙ፡ለአበዊ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፲ወ፮ቱ።

፳፩፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ማእምረ ፡ ወጠቢበ ፡ ወጽኑዐ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወሠናይ ፡ በኵሉ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ወያፈቅርዎ ፡ ወይፈ ቅድዎ፡ኵሎሙ፡ሰብእ፡በእንተ፡አእምሮቱ።

፳፪፡ ወበውእቱ፡መዋዕል፡እስመ፡ኢተክህሎሙ፡ ለክርስቲያን፡ክሡተ፡ይጸልዩ፡ወይቀድሱ፡ ዘእንበለ ፡ በበዓታት ፡ በኅቡእ ፡ በእንተ ፡ ፍርሀቶሙ ፡ ለከሀድያን ፡ ወኄጠሙ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ እስከ ፡ ሐነፀ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡

፳፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ቴዎናስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዐሥራ ፡ ስድተኛ ፡ ነው።

፳፩፡ ይህም፡ቅዱስ፡አዋቂ፡ብልህ፡በቀናች፡ሃይማ ኖትም፡የጸና፡በሥራው፡ሁሉ፡ያማረ፡ስለ፡ ዕውቀቱም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚወዱትና ፡ የሚሹት፡ሆነ።

፳፪፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ ከሀድያንን ፡ በመፍራት ፡ በሥውር ፡ ከዋሻ ፡ ውስጥ ፡ በቀር ፡ በግልጥ ፡ ሊጸልዩና፡ሊቀድሱ፡ለክርስቲያኖች፡አልተ ቻላቸውም፡ነበር፡ይህም፡አባት፡አብያተ፡ ክርስቲያናትን ፡ እስከሠሩ ፡ ድረስ ፡ አግባ

www.ethiopianorthodox.org

ወበስማ ፡ ለእግዝእትነ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሐነፁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይተ፡ ወሜጠሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እምከሀድያን ፡ ወአጥመቆሙ፡ጥምቀተ፡ክርስትና።

፳፫፡ ወውእቱ ፡ ዘአጥመቆ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት ፡ በቀዳሚት ፡ ዓመተ ፡ ሢመቱ ፡ ወበ፭ቱ ፡ ዓመተ ፡ ሢመቱ ፡ ሤሞ ፡ አናጉንስጢሰ ፡ ወበ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመተ ፡ ሢመቱ፡ሤሞ፡ቀሲሰ።

፳፬፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ አስተርአየ ፡ በሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ሰባልዮስ ፡ ከሀዲ ፡ ዘይብል ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ገጽ ፡ ወአውገዞ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ወአብጠላ ፡ ለሃይማኖቱ፡እኪት።

፳፭፡ ወበመዋዕሊሁ፡ዓዲ፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡ቀዝሞስ፡ ወድምያኖስ ፡ ወአኃዊሆሙ ፡ ወእሞሙ ፡ ቴዎዳዳ ፡ ወፈጸሞ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ሑረቶ ፡ ሠናየ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወአዕረፈ፡በሰላም።

ባቸው ፡ በእመቤታችንም ፡ በቅድስት ፡ ድንግል፡ማርያም፡ስም፡ያማረች፡ቤተ፡ክርስቲያን ፡ ሠሩ ፡ ከከሀድያንም ፡ ብዙዎችን ፡ መልሶ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትን ፡ አጠመቃቸው።

፳፫፡ በተሾመባት ፡ በመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት ፡ የሆነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጴጥሮስን ፡ ያጠመቀው ፡ እርሱ ፡ ነው ። በተሾመ ፡ በአምስተኛ ፡ ዓመቱም ፡ አናጉንስጢስነት ፡ ሾመው ፡ በዐሥራ ፡ ሁለተኛም ፡ የሹመቱ፡ዓመት፡ቅስና፡ሾመው።

፳፬፡ በዚህም ፡ አባት ፡ ዘመን ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡አንድ፡ገጽ፡ነው፡የሚል፡ከሀዲ፡ ሰባልዮስ ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ተነሣ ፡ ይህም ፡ አባት ፡ አውግዞ ፡ ለየው ፡ የከፋች ፡ ሃይማኖቱንም፡አጠፋት።

፳፭፡ ዳግመኛም ፡ በዘመኑ ፡ ቀዝሞስና ፡ ድሞያኖስ፡ ወንድሞቻቸው፡እናታቸው፡ቴዎዳዳም፡በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ፡ ይህም ፡ አባት ፡ ያመረ ፡ ጉዞውን ፡ በመጓዝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሎ፡በሰላም፡አረፈ።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም፡እብል፡እንዘ፡እንግር፡ጽድቆ።ለሊቀ፡ጳጳሳት፡ቴዎናስ፡ለጴጥሮስ፡እንተ፡አጥመቆ።በበዓታት፡ጸሎተ ፡ ኢይግበሩ ፡ በተራኅቆ ። ውስተ ፡ አሐቲ ፡ አስተጋብአ ፡ ደቂቆ ። በስመ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ማኅፈደ፡ ነዲቆ።

፳፮፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና፡ ለእግዚእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በደብረ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ በረከተ ፡ ጸሎታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፮፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በአባ ፡ ሲኖዳ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ፡ የእመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ የከበረችበት ፡ ነው ፡ በጸሎቷም ፡ የተገኘ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለቅዳሴ ፡ ቤትኪ ፡ እንተ ፡ ተሐንፀት ፡ እንግዳ ። በደብረ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ። ማርያም ፡ አዝዚ ፡ ኢያንጊጊ፡ በፍኖተ ፡ በዳ ። ጽድቅኪ ፡ ወብርሃንኪ ፡ ኪያየ ፡ ይሰዳ ። ውስተ ፡ መቅደስኪ ፡ ዘባሕርይ ፡ ዓምዳ።

፳፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ምስለ ፡ ቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ ፱፻ወ፺፪ነፍስ ፡ ወሳቤላ ፡ ወለተ ፡ ሕርቃስ ፡ ፈካሪተ ፡ ሕልም ፡ ነቢዪት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

፳፯፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ከቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ ጋር፡ ዘጠኝ ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ የሕርቃስ ፡ ልጅ ፡ ሕልምን ፡ የምትተረጉም ፡ ነቢዪት ፡ ሳቤላ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሳቤላ ፡ ፈካሪተ ፡ ራእይ ፡ ለፀሐይ ፡ ውስቴቱ ። ጠቢባነ ፡ ሮም ፡ ላቲ ፡ ሶበ ፡ ሕልሞሙ ፡ ከሠቱ ። እንበለ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ዘበሰማያት ፡ መንግሥቱ ። አኅረመቶሙ ፡ በዝንቱ ፡ ለመኳንንት ፡ ዐበይቱ ። ለንጉሠ ፡ ምድር ፡ መዋቲ ፡ ኢይስግዱ ፡ ሎቱ ።

* * *

፩ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፫ ፡ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተቀትሉ ፡ ሕፃናት ፡ ዘቤተ ፡ ልሔም ፡ ወዘውስተ ፡ ኵሉ ፡ አድያሚሃ ፡ ዘ፪ኤ ፡ ዓመት ፡ ወዘይንእስ ፡ እምኔሁ ፡ በከመ ፡ ሐሳበ ፡ መዋዕል ፡ በከመ ፡ ተጠየቀ ፡ እምኀበ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ።

፪ ፡ ወኍልቆሙ ፡ ለእሉ ፡ ፲ወ፬፼ወ፵፻ ፡ ወእሙንቱ ፡ ንጹሐን ፡ እምአንስት ፡ በከመ ፡ ተወልዱ ።

፫ ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ወእምድኅረ ፡ ኀለፉ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ናሁ ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተንሥእ ፡ ወንሣእ ፡ ሕፃነ ፡ ወእሞ ፡ ወጕየይ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወሀሉ ፡ ህየ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ እነግረከ ፡ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ለኄሮድስ ፡ ይኅሥሥ ፡ ለሕፃን ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ። ወተንሢኦ ፡ ነሥአ ፡ ሕፃነ ፡ ወእሞ ፡ በሌሊት ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ግብጽ ። ወነበረ ፡ ህየ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሞቱ ፡ ለኄሮድስ ፡ ከመ ፡ ይትፌጸም ፡ ዘተብህለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እምግብጽ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለወልድየ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ኄሮድስ ፡ ሐለየ ፡ ከመ ፡ እምእሉ ፡ ይከውን ፡ ፩ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ።

፭ ፡ ወእግዚእነ ፡ ገብረ ፡ ኵሎ ፡ ምግባረ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ወጐየ ፡ እምገጸ ፡ ኄሮድስ ፡ በኪነ ፡ ጥበቡ ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ ረከቦ ፡ ኄሮድስ ፡ ወፈቀደ ፡ ቀቲሎቶ ፡ እምኢተክህሎ ፡ እንበለ ፡ ጊዜሁ ፡ ወይሔልዩ ፡ አብዳን ፡ ሰብእ ፡ ትስብእቶ ፡ ከመ ፡ ምትሐት ፡ ውእቱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጐየ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ። ወካዕበ ፡ ከመ ፡ ይትፌጸም ፡ ትንቢት ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወርድ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ተጽዒኖ ፡ ዲበ ፡ ደመና ፡ ቀሊል ፡ ወይምሀረነ ፡ ለነ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ንኩየይ ፡ እምእኩይ ፡ ወከመ ፡ ያጥፍአሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ግብጽ ።

* * *

፩ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሦስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ኄሮድስ ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፡ እንደ ፡ ተረዳው ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡ ከዚያም ፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ በቤተ ፡ ልሔምና ፡ በአውራጃዋ ፡ ሁሉ ፡ ያሉ ፡ ሕፃናት ፡ ተገደሉ ።

፪ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ከአራት ፡ ሺህ ፡ ነው ፡ እነርሱም ፡ ከሴቶች ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ንጹሐን ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ።

፫ ፡ በከበረ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልም ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡ ኄሮድስ ፡ ሕፃኑን ፡ ሊገድለው ፡ ይሻዋልና ፡ ተነሣ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ሽሽ ፡ ተመለስ ፡ ብዬ ፡ እስከምነግርህም ፡ ከዚያ ፡ ኑር ፡ ብሎ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ በሌሊት ፡ ተነሥቶ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ሔደ ፡ ኄሮድስ ፡ እስቲሞት ፡ ድረስም ፡ በዚያ ፡ ኖረ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ልጄን ፡ ከግብጽ ፡ ጠራሁት ፡ ተብሎ ፡ በነቢይ ፡ የተነገረው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ።

፬ ፡ ከእነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ አንዱ ፡ እንደሚሆን ፡ ኄሮድስ ፡ አስቧልና ።

፭ ፡ ጌታችንም ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ከብቻዋ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ ሠራ ፡ በረቀቀ ፡ ጥበቡም ፡ ከኄሮድስ ፡ ፊት ፡ ሸሸ ፡ ኄድሮስ ፡ አግኝቶት ፡ ሊግድለው ፡ ቢአስብ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ መግደል ፡ ባለተቻለውም ፡ ነበርና ፡ ሰነፎች ፡ ሰዎች ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ምትሐት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በአሰቡ ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ሸሸ ፡ ሁለተኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈጣን ፡ ደመና ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይወርዳል ፡ ተብሎ ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ እንድንሸሽ ፡ ለእኛ ፡ ሊአስተምረን ፡ የግብጽንም ፡ ጣዖታት ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ወእፎ፡ ተክህሎ፡ ለኄሮድስ፡ አስተጋብኦቶሙ፡ ወቀቲሎቶሙ ፡ ለዘመጠነዝ ፡ ብዝኖሙ ፡ ለሕፃናት፡ እስመ፡ ኄሮድስ፡ ጕህላዊ፡ ተመክነየ፡ ወፈነወ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ አህጉር፡ እንዘ፡ ይብል፡ እስመ፡ መጽሐፈ፡ መልእክቱ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቄሣር፡ በጽሐ፡ ኀቤየ፡ ዘይኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ናልሕቅ ፡ ሕፃናተ ፡ ዘክልኤ ፡ ዓመት፡ ወዘይንእስ፡ ወንሥራዕ፡ ሐራ። ሎቱ፡ ወንሁብ፡ ወርቀ፡ ወብሩረ፡ ወአልባሰ፡ ወበእንተዝ፡ ተጋብኡ፡ ምስለ፡እማቲሆሙ፡ አሜሃ፡ አውጽአ፡እምኀቤሁ፡ ፲ወ፪ተ፻ተ፡ ሐራ፡ ወሐረድዎሙ ፡ መልዕልተ ፡ ደብር ፡ ወተፈጸመ ፡ ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ ዘይቤ ፡ ቃል ፡ በራማ፡ ተሰምዐ፡ ብካይ፡ ወሰቆቃው፡ ወገዐር፡ ወሐማም ፡ ብዙኅ ፡ ራኄል፡ እንዘ ፡ ትበኪ ፡ በእንተ፡ ውሉዳ፡ ወአበየት፡ ተናዝዞ፡ ወነጊፈ፡ ላህ ፡ እስመ ፡ ኢኮንዋ ፡ ውሉዳ ፡ ውሉደ ፡ ወኢሀለዉ።

፲፯፡ ዮሐንስኒ ፡ ይቤ ፡ በራእዩ ፡ ወጸርሑ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ወይቤሉ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ፡ እግዚኦ ፡ ቅዱስ፡ ወጻድቅ፡ ኢትትቤቀሎሙኑ፡ ወኢትኳንኖሙ ፡ በእንተ ፡ ደምነ ፡ እምእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ፡ ምድር ። ወወሀብዎሙ፡ አልባሰ ፡ ብሩሀ፡ ለለአሐዱ፡ እምኔሆሙ፡ ወይቤልዎሙ፡ ከመ፡ ያዕርፉ፡ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸሙ፡ እለ፡ ከማሆሙ፡ አግብርተ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኃዊሆሙ ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይትቀተሉ፡ ከማሆሙ ። እስመ፡ ከመዝ፡ ርእየ፡ ነፍሳቲሆሙ፡ ለእሉ፡ ሕፃናት።

፲፰፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወዮኀልዩ ፡ ማኅሌተ ፡ ሐዲሰ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ወቅድመ ፡ እልክቱ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ወእልክቱኒ ፡ ሊቃናት ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ አእምሮታ ፡ ለይእቲ ፡ ማኅሌት ፡ ዘእንበለ ፡ እልክቱ ፡ ፻ወ፵፻ወ፬፻ ፡ እለ፡ተቤዘዉ፡እምነ፡ምድረ፡ግብጽ።

፲፱፡ እለ ፡ ንጹሐን ፡ እሙንቱ ፡ እምአንስት ፡ በከመ ፡ ተወልዱ።

፳፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፡ ይህን፡ ያህል፡ ብዛት፡ ያላቸውን፡ ሕፃናት፡ መሰብሰብና ፡ መግደል ፡ ለኄሮድስ ፡ እንዴት ፡ ተቻለው ፡ ተንኰለኛ ፡ ኄሮድስ ፡ ምክንያት ፡ ፈጥሮ ፡ የሁለት ፡ ዓመትና ፡ ከዚያም ፡ ያነሱ ፡ ሕፃናትን ፡ አሳድገን ፡ ጭፍራ ፡ እንሠራለት ፡ ዘንድ ፡ የሚያዝ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቄሣር ፡ ደብዳቤ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ደርሷል ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ቀለብ ፡ ልብስም ፡ እንሰጣለን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላከ። ስለዚህም ፡ ከእናቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ተሰበሰቡ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሽህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ወታደሮችን፡ አውጥቶ፡ በተራራ፡ ላይ፡ አረዱአቸው። ነቢይ፡ ኤርምያስም ፡ የተናገረው ፡ ተፈጸመ ፡ ራኄል ፡ ስለ፡ ልጆቿ፡ ስታለቅስ፡ ብዙ፡ መከራ፡ ጩኸት፡ ሙሾ ፡ ልቅሶ ፡ ዋይታ ፡ በራማ ፡ ተሰማ፡ ልቅሶ ፡ መተውን ፡ መጽናናትን ፡ እምቢ ፡ አለች ፡ ልጆቿ፡ ልጆችን፡ አልሆኗትምና።

፲፯፡ ዮሐንስም ፡ በራእዩ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በታላቅ ፡ ቃል፡ ጮኹ፡ የተመሰገንህ፡ ውእነተኛ፡ አቤቱ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ደማችን ፡ ተበቅለህ ፡ በምድር፡ ላይ፡ በሚኖሩ፡ ሰዎች፡ አትፈርድባቸውምን፡ አሉ ። ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ ለየአንዳዱ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ሰጥተው ፡ እንግዲህ ፡ ጥቂት ፡ ቀን፡ ዕረፉ፡ አሉዋቸው። እንደነርሱ ፡ ላሉ፡ ለእግዚአብሔር ፡ባለሟሎች፡ እንደነርሱ፡ ይሞቱ፡ ዘንድ፡ ያላቸው፡ ወንድሞቻቸው፡ እስከሚፈጸሙበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንዲህ ፡ የእሊህን ፡ ሕፃናት፡ ነፍሳቸውን፡ አይቷልና።

፲፰፡ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብዙፋኑ ፡ ፊት ፡ በአራቱ ፡ እንስሶችና ፡ በሃያ ፡ አራቱ ፡ አለቆች ፡ ፊት ፡ አዲስ ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከተዋጁ ፡ ከዐሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ አራት ፡ ሽህ ፡ ሕፃናት ፡ በቀር ፡ ያቺን ፡ ምስጋና ፡ ሊያውቃት፡ የሚቻለው፡ የለም።

፲፱፡ እነርሱም ፡ ከሴቶች ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ንጹሐን ፡ የሆኑ፡ ናቸው።

፳፡ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከታቸውም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

አርኬ

ሰላም ፡ለሕፃናት ፡ ዘቀተሎሙ ፡ ኄሮድስ ። እንዘ ፡ ይመስሎ ፡ ምስለ ፡ እሉ ፡ ከመ ፡ ይትረከብ ፡ ክርስቶስ ። ልበ ፡ አበዊሆሙ ፡ ነደ ፡ ወዘእሞሙ ፡ ክርሥ ። ጊዜ ፡ አስተርአየ ፡ በመልዕልተ ፡ ገጸ ፡ ለየብስ ። ሐሊበ ፡ አጥባት ፡ ምስለ፡ ደም፡ ሕውስ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ሊባኖስ ፡ ዘውእቱ ፡ መጣዕ።

፲፪፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ አብርሃም ፡ ወስመ ፡ እሙ ፡ ንግሥት ፡ እስመ ፡ ጥቀ ፡ ብዑላን ፡ እሙንቱ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ በዕለተ ፡ አዕተዊ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ ጸውዖ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ወአውጽኦ ፡ ሌሊተ ፡ እምቤተ ፡ አቡሁ ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ጳኩሚስ፡ወበህየ፡መንኰሰ።

፲፫፡ ወእምዝ ፡ ፈለሰ ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወነበረ፡እንዘ፡ይትጋደል፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡ ወይገብር ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ እስመ ፡ አውጽአ፡እምኰኵሕ፡ማየ፡ወፈወሰ፡ዱያነ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፬፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፩፡ በዚችም ፡ ዕለት · ዳግመኛ ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ የአባ፡ሊባኖስ፡የዕረፍቱ፡መታሰቢያ፡ነው፡ ይኸውም፡መጣዕ፡ነው።

፲፪፡ የዚህ ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ አብርሃም ፡ የእናቱም፡ ስም፡ ንግሥት፡ ነው፡ እነርሱም፡ በወርቅና፡ በብር፡ እጅግ፡ የበለጸጉ፡ ናቸው፡ ለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ሚስትን ፡ በአመጡለት ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ የከበረ ፡ ገብርኤል፡በሌሊት፡ጠርቶ፡ከአባቱ፡ቤት፡ አውጥቶ፡ወደ፡አባ፡ጳኩሚስ፡አደረሰው፡ በዚያም፡መነኰሰ።

፲፫፡ ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ሒዶ፡እየተ ጋደለ፡ብዙ፡ዘመን፡ኖረ፡ድንቅ፡ተአምራ ትንም፡በማድረግ፡ከዐለት፡ውኃን፡አፍል ቋልና፡በሽተኞችንም፡አድኗልና፡የክብር፡ ባለቤት ፡ ጌታችንንም ፡ አገልግሎና ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ፡በሰላም፡አረፈ።

፲፬፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሊባኖስ ፡ እምቤተ ፡ አቡሁ ፡ ዘወጽአ ። ከመ ፡ ቃለ ፡ መልአክ ፡ ሰምዐ ። ኰኵሐ ፡ ዘቢጦ ፡ ማየ ፡ አንቀዐ።ሰላም፡ለአድኃኒ፡ወዓዲ፡አስትዓ።በውስተ፡ገዳም፡ምስሌሁ፡ዘነበሩ፡ስንዐ።

፲፭፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ተዝካሩ፡ ለአባ፡ አሞን፡ ዘነበረ፡እንዘ፡ይጸፍር፡ሥዕርቶን፡ለአንስት፡ ወኢክህለ ፡ ያስጥሞ ፡ ማዕበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፲፭፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሴቶችን ፡ ጠጉር ፡ ሹርባ ፡ ሲሠራ፡የኖረ፡የአባ፡አሞን፡መታሰቢያው፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ሥራም ፡ ሲኖር ፡ የኃጢአት ፡ ማዕበል ፡ ሊአሠጥመው ፡ አልቻለም ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአሞን ፡ ዘዕቁብ ፡ መከየዱ ። እምውግዓተ ፡ ሦክ ፡ በሊሕ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ መንገዱ ። ከመ ፡ ይንግእ ፡ ዐስበ ፡ ወይሣየጥ ፡ ለማዕዱ ። ሥዕርተ ፡ አንስት ፡ እንዘ ፡ ይጸፍር ፡ በእዱ ። ለባሕረ ፡ ኃጢአት ፡ ኢክህለ ፡ ያሥጥሞ፡ሞገዱ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲፪ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ተዝካረ፡ፍልሰቱ፡ለቅዱስ፡ወክቡር፡ሐዋርያ፡ ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ፍቁረ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡አራት፡በዚች፡ ቀን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ የሚወደው ፡ የከበረና ፡ የተመሰገነ ፡ ወንጌልን ፡ የጻፈ ፡ የሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡ የፍልሰቱ፡መታሰቢያ፡ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሶበ ፡ ወጽአ ፡ ዕፃሁ፡ ከመ ፡
ይሑር ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እስያ ፡ ኀዘነ ፡ ፈድፋደ ፡
ወበከየ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡
እሙንቱ ፡ እኩያን ፡ ወዐላውያን ፡ ወግዙፋነ ፡
ክሣድ ፡ ወባሕቱ ፡ ነሥአ ፡ እምእግዚእነ ፡
ኃይለ ፡ ወኑዛዜ ፡ ወጽአ ፡ ኀበ ፡ ክፍሉ ፡ ምስለ ፡
ረድኡ ፡ አብሮ ኮሮስ ፡ ወተጽዕነ ፡ ዲበ ፡
ሐመር፡ እንዘ ፡ ይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡
ሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ወተሰብረ ፡ ሐመር ፡ ወተ
ሰቅሉ ፡ ለለአሐዱ ፡ ዲበ ፡ ጽላተ ፡ ሐመር ፡
ወለረድኡ ፡ አብሮኮሮስ ፡ አብጽሐ ፡ ሞገደ ፡
ባሕር ፡ ኀበ ፡ አሐቲ ፡ ደሴት ፡ ወቅዱስሰ ፡
ዮሐንስ ፡ ነበረ ፡ ማዕከለ ፡ ሞገደ ፡ ባሕር ፡ ፵
መዓልተ ፡ ወ፵ ፡ ሌሊተ።

፲፡ ወእምዝ ፡ ጐሥዖ ፡ ባሕር ፡ ውስተ ፡ የብስ ፡
ኀበ ፡ ይነብር ፡ ረድኡ ፡ አብሮኮሮስ ፡ ወአእ
ኰትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ተራክ
ቦቶሙ ፡ ወተንሥኡ ፡ ሶቤሃ ፡ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡
ሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ወባሕቱ ፡ ኢተክህሎሙ ፡
ከመ ፡ ይስብኩ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስመ ፡
እሙንቱ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ እኩያን ፡ ፈድፋደ ።
ወበእንተዝ ፡ ተመክነዩ ፡ ምክያተ ፡ ወኮነ ፡
ዮሐንስ ፡ ዘያነድድ ፡ እሳተ ፡ ለቤተ ፡ ብለኔ ፡
ለብእሲት፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሮምና ፡ ወአብሮ
ኮሮስ ፡ ረድኡ ፡ ኮነ ፡ ኀፃቢ ፡ ወይእቲ ፡ ብእ
ሲት ፡ ታመነድቦሙ ፡ ዐቢየ ፡ ምንዳቤ ፡ ወታኀ
ሥሮሙ ፡ በእንተ ፡ ፍልሰቶሙ ፡ ወትዘ
ብጦሙ፡ ወትረግሞሙ ፡ ወረሰየቶሙ ፡ ላቲ ፡
አግብርተ፡ እስመ ፡ ጸሐፉ ፡ ላቲ ፡ ስመ ፡ ግብር
ናቶሙ ፡ ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ኀሣር ፡ ዐቢይ ።

፲፩፡ ወእምዝ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ቦአ ፡ ወልደ ፡ መኰ
ንነ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ይትኀፀብ ፡ ወሀሎ ፡ ውስተ ፡
ውእቱ ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ፡ ኃይለ ፡ ሰይጣን፡
እምአመ ፡ ተሐንፀ ፡ ወሐነቆ ፡ ለወልደ ፡
መኰንን ፡ ወቀተሎ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተጋብኡ ፡
ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ይላህውዎ ፡ ለውእቱ ፡
ወሬዛ ፡ ዘሞተ ፡ ወበጽሐ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡
ምስሌሆሙ ፡ ወቆመ ፡ ይርአይ ፡ በከመ ፡
ኵሎሙ ፡ ሰብእ።

፲፪፡ ወሶበ ፡ ርእየቶ ፡ ረገመቶ ፡ ሮምና ፡ ወትቤሎ ፡
አንተሰ ፡ መጸእከ ፡ ዝየ ፡ ትኅለቅ ፡ ላዕሌየ ፡
ወትትፌሣሕ ፡ በሞቱ ፡ ለወልደ ፡ እግዚእየ ፡

፱፡ ለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወደ ፡እስያ ፡ ሀገር ፡ ይሔድ ፡
ዘንድ ፡ ዕጣው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዝኖ፡
አለቀሰ ፡ እነርሱ ፡ ክፉዎች ፡ ከሀዲዎች ፡
ልባቸው ፡ የደነደነ ፡ መሆናቸውን ፡ አውቋ
ልና ፡ ግን ፡ ከጌታችን ፡ ኃይልን ፡ መጽናናትን ፡
አግኝቶ ፡ ከደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ከአብሮኮሮስ ፡
ጋር ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ሔደ ። ወደ፡
ኤፌሶንም ፡ ሊሔድ ፡ ወዶ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡
ተሳፈረ ፡ መርከቡም ፡ ተሰበረ ፡ እየአንዳንዱ ፡
በመርከብ ፡ ስባሪ ፡ ሠሌዳ ፡ ላይ ፡ ተንጠለጠለ ፡
ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ አብሮኮሮስንም ፡ የባሕሩ ፡
ማዕበል ፡ ወደአንዲት ፡ ደሴት ፡ አደረሰው ፡
ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ በባሕሩ ፡ ማዕበል ፡
መካከል ፡ አርባ ፡ መዓልት ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡
ኖረ።

፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ አብሮኮ
ሮስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ ባሕሩ ፡ ተፋው ፡
ስለ ፡ መገናኘታቸውም ፡ እግዘአብሔርን ፡
አመሰገኑት ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ተነሥተው ፡
ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ ገቡ ፡ ግን ፡ በክብር ፡
ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡
ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡ አልተቻላቸውም ፡ እነዚያ ፡
ያገር ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ የከፉ ፡ ናቸውና ።
ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ ፈጥረው ፡ ዮሐንስ ፡
ሮምና ፡ ለምትባል ፡ ሴት ፡ የውሽባ ፡ ቤት ፡
እሳትን ፡ የሚያነድ ፡ ሆነ ፡ ረድኡ ፡ አብሮኮ
ሮስም ፡ አጣቢ ፡ ሆነ ፡ ያቺ ፡ ሴትም ፡ እጅግ ፡
ታሠቃያቸው ፡ ነበር ፡ መጻተኞችም ፡ ስለሆኑ ፡
ታጐሳቁላቸዋለች ፡ ትደበድባቸዋለች ፡ ትረግ
ማቸዋለች ፡ ባሮቿም ፡ እንደሆኑ ፡ ጽፈውላ
ታልና ፡ ለእርሷ ፡ ባሮች ፡ አደረገቻቸው ፡ በዚህ ፡
በታላቅ ፡ ጕስቍልና ፡ ውስጥ ፡ ኖሩ ።

፲፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንዲት ፡ ዕለት ፡ ይታጠብ፡
ዘንድ ፡ የአገረ ፡ ገዥው ፡ ልጅ ፡ ገባ ፡ በዚያም፡
የውሽባ ፡ ቤት ፡ ከተሠራ ፡ ጀምሮ ፡ የሰይጣን፡
ኃይል ፡ አለ ፡ የመኰንኑንም ፡ ልጅ፡ አንቆ ፡
ገደለው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የአገር ፡ ሰዎች ፡
ለዚያ ፡ ለሞተው ፡ ሊያለቅሱለት ፡ ተሰበሰቡ፡
የከበረ ፡ ዮሐንስም ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር ፡
መጥቶ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊያይ ፡ በዚያ ፡
ቆመ ።

፲፪፡ ሮምናም ፡ በአየችው ፡ ጊዜ ፡ ረገመችው ፡
አንተስ ፡ በጌታዬ ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ ደስ ፡ ብሎህ ፡
ልትዘትብኝ ፡ መጣህ ፡ አለችው ፡ ቅዱሱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወቅዱስሰ ፡ይቤላ ፡ በየውሀት ፡ ኢ.ትፍርሂ ፡ ወኢ.ትኀዝኒ ፡ ወዘንቱ ፡ ብሂሎ ፡ ቀርበ ፡ ኀበ ፡ ምውት ፡ ወአተበ ፡ ላዕሌሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ማሕየዊ ፡ ወነፍሐ ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ ወሐይወ ፡ ሶቤሃ ፡ ውእቱ ፡ ምውት ፡ ወተንሥአ ፡ ወደንገፁ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወትቤ ፡ ሮምና ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ አምላክነ ፡ አንተ ፡ ዘይብልዎ ፡እግዚአብሔር ። ወይቤላ ፡ አልቦ ፡ አላ ፡ ገብሩ ፡ ወሐዋርያሁ ፡ ወበከየት ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡ ወሰአለቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ከመ ፡ ይኅድጉ ፡ ላቲ ፡ አበሳሃ ፡ ዘገብረት ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ናዘዝዋ ፡ ወአጽንዕዋ ።

፮፡ ወአምኑ ፡ ብዙኃን ፡ እምሰብአ ፡ ሀገር ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአጥመቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወገብረ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ አምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ በእግዚእነ ፡ ዘእንበለ ፡ ገነውተ ፡ አማልክት ፡ ወእሙንቱ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይቅትልዎ ፡ እስመ ፡ ሰይጣን ፡ የሐውኮሙ ፡ በላዕሌሁ ፡ ባሕቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዐቅቦሙ፡ ለኅሩያኒሁ።

፯፡ እስመ ፡ ዓማ ፡ ዐቢይ ፡ ወምንዳቤ ፡ ዕፁብ ፡ በጽሐ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ እስከ ፡ ሜጠሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡እግዚአብሔር ፡ ወጳውሎስኒ ፡ ብፁዕ ፡ ሐዋርያ ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በእንተ ፡ ግዝፈተ ፡ ልቦሙ ፡ ወበእንተ ፡ አፍቅሮቶሙ ፡ ጣዖታተ ፡ ወእቱሰ ፡ በዓማ ፡ ዐቢይ ፡ አግብአሙ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምዝ ፡ ሤመ ፡ ሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሳተ፡ ወካህናተ ፡ ወዲያቆናተ ።

፰፡ ወእምዝ ፡ ወጽአ ፡ ኀበ ፡ አህጉር ፡ እለ ፡ የዓውድዋ ፡ ለነኪላ ፡ ብሔረ ፡ እስያ ፡ ወመሀሮሙ ፡ ወሜጠሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር።

፱፡ ወሐይወ ፡ ቅዱስ ፡ ውብፁዕ ፡ ዮሐንስ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ፺ ዓመተ ፡ ወልሕቀ ፡ ፈድፋደ ፡ ወኢጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በሰይፍ ፡ ከመ ፡ ካልአኒሁ ፡ ሐዋርያት ፡ በእንተ ፡ ድንግልናሁ ፡ ወንጽሕናሁ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ኵሎሙ ፡ ይኩኑ ፡

ግን ፡ በቅንነት ፡ አይዞሽ ፡ አትዘኝ ፡ አላት ፡ ይህንንም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሞተው ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ አማተበበት ፡ በፊቱም ፡ ላይ ፡ እፍ ፡ አለበት ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የሞተው ፡ ድኖ ፡ ተነሣ ፡ የአገር ፡ ሰዎችም ፡ ደነገጡ ፡ ሮምናም ፡ ወዮልኝ ፡እግዚአብሔር ፡ የሚሉት ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለች ። እርሱም ፡ አይደለሁም ፡ እኔ ፡ አገልጋይ ፡ ሐዋርያው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ አላት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሠራችውን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ይሏት ፡ ዘንድ ፡ መሪር ፡ ልቅሶ ፡ በማልቀስ፡ሐዋርያትን፡ለመነቻቸው፡እነርሱም፡ አረጋጓት ፡ አጽናኗትም ።

፮፡ ከሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አመኑ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትንም ፡ አጠመቃቸው ፡ በፊታቸውም ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ፡ ይህንንም ፡ አይተው ፡ የሀገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ በጌታችን ፡ አመኑ ። ከጣዖታቱ ፡ አገልጋዮች ፡ በቀር ፡ እነርሱም ፡ ሰይጣን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚያነሣሣቸው ፡ ሊገድሉት ፡ ይሹ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምርጦቹን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠበቃቸው።

፯፡ የከበረ ፡ ዮሐንስም ፡ ሁሉንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ እስከመለሳቸው ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ድካምና ፡ ጭንቅ ፡ የሆነ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት ። የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ስለ ፡ ልቡናቸው ፡ ደንዳናነት ፡ ጣዖታትን ፡ ስለመውደዳቸውም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ መስክሮአል። እርሱም ፡ ዮሐንስ ፡ በታላቅ ፡ ድካም፡ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ መለሳቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ቀሳውስትን ፡ ዲያቆናትን ፡ ሾመላቸው።

፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእስያ ፡ በዙርያዋ ፡ ወዳሉ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ወጥቶ ፡ አስተማረ ፡ እግዘአብሔርንም ፡ ወደማወቅ ፡ መለሳቸው።

፱፡ ይህም ፡ የከበረና ፡ የተመሰገነ ፡ ዮሐንስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ እጅግም ፡ ሸመገለ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ባልንጀሮቹ ፡ ሐዋርያት ፡ በመሰየፍ ፡ ሞትን ፡ አልቀመሰም። ስለ ፡ ድንግልናውና ፡ ስለ ፡ ንጽሕ

www.ethiopianorthodox.org

ዕሩያነ ፡ ውስተ ፡ ስብሐት ፡ ወውእቱ ፡ ዘጸ
ሐፈ ፡ ወንጌለ ፡ ወራእየ ፡ ዘይሰመይ ፡ አቡቀለ
ምሲስ ፡ ወሠለስተ ፡ መልእክታተ ።

፲፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘረፈቀ ፡ ዲበ ፡ እንግድዓሁ ፡
ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እንዘ ፡ ይዴረሩ ፡ ወዘ
ቤሎ ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘያገብአከ ።

፲፩፡ ወውእቱ ፡ ዘቆመ ፡ በጊዜ ፡ ስቅለቱ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ምስለ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድን
ግል ፡ ማርያም ፡ ኀበ ፡ መስቀሉ ፡ ወዘይቤላ ፡
ለእሙ ፡ ብእሲቶ ፡ ነዋ ፡ ወልድኪ ፡ ለውእቱኒ ፡
ረድእ ፡ ነያ ፡ እምከ ።

፲፪፡ ወዘይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኪያሁ ፡
ርእዮ ፡ ይቤሎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እግዚኦ ፡
ዝኬ ፡ እፎ ፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
እመኬ ፡ ፈቀድኩ ፡ የሀሉ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ እመ
ጽእ ፡ ሚ ፡ ላዕሌከ ፡ ወአንተሰ ፡ ትልወኒ ።

፲፫፡ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ብፁዕ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመ ፡
ቀርበ ፡ ፍልሰቱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ጸው
ዖሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ጸለየ ፡ ወባረከ ፡ ወፈተተ ፡
ኅብስተ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይጽ
ንዑ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወባረኮሙ ፡
ወናዘዞሙ ።

፲፬፡ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ ለረድኡ ፡ አብሮኮሮስ ፡
ወለ፪ቱ ፡ ካልአን ፡ እምኢኃው ፡ ከመ ፡ ይን
ሥኡ ፡ መክርየ ፡ ወይትልውዎ ፡ ወወጽአ ፡
አፍአ ፡ ሀገር ፡ ዘኤፌሶን ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡
ይክርዩ ፡ ግበ ፡ ወወረደ ፡ ውስቴታ ፡ ወከልአ ፡
አልባሲሁ ፡ ወኢያትረፈ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡
ቀሚስ ፡ ዘሰንዱን ። ወአንሥአ ፡ እዴሁ ፡
ወጸለየ ፡ ወአስተፋነዎሙ ፡ ከመ ፡ ይትመየጡ ፡
ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወአዘዞሙ ፡ ይንግርዎሙ ፡
ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘክር
ስቶስ ፡ ይጽንዑ ፡ ወይግበሩ ፡ ምግባራተ ፡
ሠናያተ ፡ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ከመ ፡
ይፍድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ።

፲፭፡ ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ንጹሕ ፡ አነ ፡ እምደመ ፡
ኵልክሙ ፡ እስመ ፡ ኢኀደጉ ፡ ወኢ ፡ ምንተኒ ፡
እምትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእምኵሉ ፡
ሥርዓቱ ፡ ዘኢነገርኩክሙ ። ወአንትሙሰ ፡

ናው ፡ ይህ ፡ ሆነ ፡ ሁሉም ፡ በክብር ፡ ይስተካ
ከሉ ፡ ዘንድ ፡ እርሱም ፡ ወንጌልን ፡ ቀለም
ሲስ ፡ የሚባለውን ፡ ራእይ ፡ ሦስት ፡ መልእክ
ታትን ፡ የጻፈ ፡ ነው ።

፲፡ ራት ፡ ሲበሉ ፡ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ አጠገብ ፡ የተ
ቀመጠውና ፡ አቤቱ ፡ የሚያሲዝህ ፡ ማነው ፡
ያለው ፡ ይህ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

፲፩፡ ጌታችንም ፡ በተሰቀለ ፡ ጊዜ ፡ ከእመቤ
ታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡
በመስቀሉ ፡ አጠገብ ፡ የቆመ ፡ እናቱንም ፡
እነሆ ፡ ልጅሽ ፡ ያላት ፡ እርሱን ፡ ደቀ ፡ መዝ
ሙሩንም ፡ እነኋት ፡ እናትህ ፡ ያለው ፡ ነው ።

፲፪፡ ጴጥሮስም ፡ እርሱን ፡ ሲከተለው ፡ በአየው ፡
ጊዜ ፡ ስለርሱ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ አቤቱ ፡
ይህስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፡ ጌታ ፡
ኢየሱስም ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ይኖር ፡
ዘንድ ፡ ከወደድኩ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ አለህ ፡
አንተ ፡ ግን ፡ ተከተለኝ ፡ ያለለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲፫፡ የተመሰገነ ፡ ዮሐንስም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚ
ወጣበት ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ በአወቀ ፡
ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ጠራቸው ፡ ጸሎትንም ፡
ጸለየና ፡ ኅብስቱን ፡ ባርኮ ፡ ቆረሰ ፡ ይህም ፡
የጌታችን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ሰጣቸው ፡
በቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲጸኑ ፡ አዘዛቸው ፡
ባረካቸው ፡ አጽናናቸውም ።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ አብሮ
ኮስን ፡ ከወንድሞችም ፡ ሌሎች ፡ ሁለትን ፡
መቆፈሪያ ፡ ይዘው ፡ ይከተሉት ፡ ዘንድ ፡
አዘዘ ። ከኤፌሶንም ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ፡
ጉድጓድ ፡ እንዲቆፍሩም ፡ አዘዘ ፡ ከውስ
ጥዋም ፡ ወርዶ ፡ ቆመ ፡ ልብሱንም ፡ አስ
ወገደ ፡ ከአንድ ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስ ፡ በቀር ፡ አላ
ስቀረም ። እጆቹንም ፡ አንሥቶ ፡ ጸለየና ፡
ወደ ፡ ከተማ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አሰናበ
ታቸው ፡ በክርስቶስም ፡ ሃይማኖት ፡ ይጸኑ ፡
ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይነግሩአቸው ፡ ዘንድ ፡
አዘዛቸው ፡ በጎ ፡ ሥራዎችንም ፡ ይሠሩ ፡
ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡
ይከፍለው ፡ ዘንድ ፡ አለውና ።

፲፭፡ ሁለተኛም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ ከሁላ
ችሁም ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግ ፡ ሳልነግራችሁ ፡
የተውኩት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የለምና ፡ እና

www.ethiopianorthodox.org

እምይእዜሰ፡ኢትሬእዩኒ፡ገጽየ፡ግሙራ።

፲፮፡ ወሶበ ፡ ይቤ ፡ ዘንተ ፡ በከዩ ፡ ወተአምኁ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወኀደግዎ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ወሖሩ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወነገርዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ፡ ወመጽኡ ፡ ወኢረከቡ ፡ መቃብሮ ፡ አላ ፡ ረከቡ ፡ አሣዕኖ ፡ ወልብሰ ። ወአንከሩ ፡ ጥቀ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘአዕረፎ ፡ ለረድኡ ፡ ዮሐንስ ፡ በዝንቱ ፡ ዕረፍት ፡ ሠናይ ።

፲፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ ሐዋርያ፡ ዮሐንስ ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ንተም ፡ ከእንግዲህ ፡ ከቶ ፡ ፊቴን ፡ አታዩኝም ።

፲፮፡ ይህንንም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ አለቀሱ ፡ እጆቹንና ፡ እግሮቹን ፡ ስመው ፡ በጕድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ትተውት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ተመለሱና፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች፡ ነገሩዋቸው፡ ሁሉም ፡ ደንግጠው ፡ መጡ ፡ ግን ፡ ልብስና ፡ ጫማ ፡ እንጂ ፡ መቃብሩን ፡ አላገኙም ፡ እጅግም ፡ አደነቁ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ዮሐንስን ፡ በዚህ ፡ በጎ ፡ ዕረፍት ፡ ያሳረፈው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑት ።

፲፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ በከበረ ፡ አባት ፡ በሐዋርያ ፡ ዮሐንስ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

<u>አርኬ ፡</u>

ሰላም ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘተለዓለ ፡ መጠኑ ። በንሢአ ፡ ጸጋ ፡ ወክብር ፡ እንተ ፡ ኢተውህበት ፡ ለካልአኑ ። ዘሥጋ ፡ ወደም ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ አኮኑ ። አመ ፡ ሰዓሞ ፡ በአፉሁ ፡ ወአመ ፡ አርፈቆ ፡ በሕፀኑ። ለእሳተ፡ መለኮት፡ መፍርህ ፡ ኢውዕየ ፡ በርስኑ ።

፲፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወማርቴና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወታአድራ ፡ ሰማዕት ፡ ወለአባ ፡ ሊቃኖስ ፡ ወለቀውስጦስ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፲፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአባ ፡ ናርዶስ ፡ ዘደብረ ፡ ቢዘን ፡ መስተጋድል ፡ ዘቀተሎ ፡ ለከይሲ ፡ በጽላሎቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይዝብጦ ፡ በበትር ፡ ወውእቱ ፡ ያወትር ፡ ጸልዮ ፡ ወቀዊመ ፡ እስከ ፡ ሐብጣ ፡ እገሪሁ ።

፳፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፲፰፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ የጊዮርጊስ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ማርቴና ፡ የሰማዕት ፡ ታኦድራ ፡ የአባ ፡ ሊቃኖስ ፡ የቀውስጦስ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፲፱፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ተጋዳይ ፡ የሆነ ፡ በበትር ፡ ሳይመታ ፡ በጥላው ፡ ከይሲውን ፡ የገደለ ፡ የደብረ ፡ ቢዘኑ ፡ የአባ ፡ ናርዶስ ፡ የዕረፍቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ እግሮቹ ፡ እስከ ፡ አበጡ ፡ ድረስ ፡ ጸሎትና ፡ መቆምን ፡ ያዘወትር ፡ ነበር ።

፳፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

*　　*　　*

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ቅዱስ ፡ አውስግንዮስ ፡ በከዊነ ፡ ስምዕ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለዑልያኖስ ፡ ከሀዲ።

፪፡ ወዝንቱ፡ ቅዱስ፡ እምውስተ፡ ሐራሁ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ወያመልኮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወይምሕር፡ ነደያነ፡ ወምስኪናነ፡ ወሰበ፡ አስተ

*　　*　　*

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ በከሀዲው ፡ ዑልያኖስ ፡ ዘመን ፡ የከበረ ፡ አውስግንዮስ ፡ ምስክር ፡ ሁኖ ፡ ሞተ።

፪፡ ይህም ፡ ከንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ጭፍሮች ፡ ውስጥ፡ ነው፡ እርሱም፡ እግዚአብሔርን፡ የሚያመልከው ፡ ለድኆችና ፡ ለምስኪኖች ፡ የሚመ

www.ethiopianorthodox.org

ርአዮ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ መስቀል ፡ በሰማይ ፡ አምሳለ ፡ ከዋክብት ፡ እንዘ ፡ ይበርህ ፡ እምቅድመ ፡ አሚኖቱ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወቀርበ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አውስግንዮስ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ዝንቱ ፡ ትእምርቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወበዝንቱ፡ ትመውዕ፡ፀረከ።

፫፡ አሜሃ፡ኢተረክበ፡እምውስተ፡ሠራዊቱ፡ለቈስጠንጢኖስ ፡ ዘይደፍር ፡ ይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለክርስቶስ፡ዘእንበለ፡ዝንቱ፡ቅዱስ።

፬፡ ወሶበ፡ሞዖሙ፡ለጸላዕቱ፡ቈስጠንጢኖስ፡በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ ኮነ ፡ ክርስቲናዌ በአሚን ፡ ወዐቀመ ፡ ቀርነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአልዓለ።

፭፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አውስግንዮስ ፡ ሐይወ፡ እምድኅረ፡ቈስጠንጢኖስ፡ወውሉዱ፡እስከ፡ መዋዕለ ፡ ዑልያኖስ ፡ ከሀዲ ፡ እስከ ፡ ኮኖ ፡ መዋዕሊሁ፡፻ወ፲ተ።

፮፡ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ያንሶሱ ፡ ማዕከለ ፡ መራህብት ፡ በሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ረከቦሙ ፡ ለክልኤቱ፡ ዕደው፡ እንዘ፡ ይትበአሱ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወፈቀደ ፡ ይዕርቆሙ ፡ ወይግበር ፡ ሰላመ ፡ ማእከሎሙ ፡ ወአዕረቆሙ ፡ ወገበሩ ፡ ፍሥሓ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ አረጋዊ ፡ ክቡር።

፯፡ ወእምህየ፡ሖረ፡አሐዱ፡ብእሲ፡እኩይ፡ኀበ፡ዑልያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ወአስተዋደዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አውስግንዮስ ፡ ኮነ ፡ በፈቃዱ ፡ መስፍነ ፡ ወመኰንነ ፡ ወአብጽሖ ፡ ንጉሥ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኀቤሁ ፡ ወገሠጾ ፡ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘሤመከ ፡ መስፍነ ፡ ወመኰንነ።

፰፡ ወአውሥአ፡ቅዱስ፡አውስግንዮስ፡ወይቤሎ፡ ለምንት፡አንተ፡ኀደገ፡አምልኮቶ፡ለእግዚአብሔር፡ዘነፍስከ፡ውስተ፡እዴሁ፡ወሰገድከ፡ ለጣዖታት ፡ ርኩሳን ፡ ወኢተለውኮሙ ፡ ለነገሥት፡እለ፡እምቅድሜከ፡ወአንሰ፡ሖራ፡ ዘከማከ፡ዘነበርኩ፡ምስለ፡ቈስጠንጢኖስ፡፷ ዓመተ፡ወምስለ፡ውሉዱኒ፡ነበርኩ፡ወአልቦ፡ እምኔሆሙ፡እኩየ፡ግዕዝ፡ዘከማከ።

፱፡ ወተምዐ፡ዑልያኖስ፡ ፈድፋደ፡ላዕለ፡ቅዱስ፡

ጸውት ፡ ነው ፡ መስቀልም ፡ እንደ ፡ ከዋክብት፡ በሰማይ፡እያበራ፡ለንጉሥ፡ቈስንጠንጢኖስ፡ በክብር፡ላቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ከማመኑ ፡ በፊት ፡ በተገለጠለት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ አውስግንዮስ ፡ ወደ፡ ንጉሡ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ይህ ፡ ለክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ምልክቱ፡ነው፡ በዚህም፡ጠላቶችህን፡ታሸንፋለህ።

፫፡ ያን፡ጊዜ፡ከቈስጠኖጢኖስ፡ሠራዊት፡ውስጥ፡ ከዚህ፡ቅዱስ፡ሰው፡በቀር፡የክርስቶስን፡ስም፡ ይጠራ፡ዘንድ፡የደፈረ፡የለም።

፬፡ ቈስጠንጦኖስም፡በከበረ፡መስቀል፡ምልክት፡ ጠላቶቹን፡ ድል ፡ በአደረገ ፡ ጊዜ ፡ ዕውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነ ፡ የሃይማኖትንም ፡ ሥልጣን ፡ አቁሞ፡ከፍ፡ከፍ፡አደረገ።

፭፡ ይህም፡ቅዱስ፡አውስግንዮስ፡እድሜው፡መቶ፡ ዐሥር ፡ ዐመት ፡ እስከ ፡ ሆነው፡ ከቈስጠንጢኖስና ፡ ከልጆቹ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ እስከ፡ከሀዲው፡ዑልያኖስ፡ዘመን፡ኖረ።

፮፡ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ በአንጾኪያ ፡ ከተማ ፡ በአደባባይ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲመላለስ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጣሉ ፡ አገኛቷቸው ፡ ሊአስታርቃቸውና ፡ በመካከላቸው፡ ሰላም ፡ ሊያአደርግ ፡ ወዶ ፡ አስታረቃቸው ፡ በመታረቃቸውም ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ፡ እርሱ፡የከበረ፡አረጋዊ፡ሰው፡ነውና።

፯፡ ከዚያም ፡ አንድ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ንግሥ ፡ ዑልያኖስ ፡ ሒዶ ፡ ነገር ፡ ሠራበት ፡ እንዲህም፡ አለው ፡ አወስግንዮስ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ገዥና ፡ ፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ ሆነ ። ንጉሥም ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ወደርሱ ፡ አቅርቦ ፡ ገሥጸው ፡ ገዥና ፡ ፈራጅ ፡ ዳኛ፡አድርጎ፡የሾመህ፡ማነው፡አለው።

፰፡ የከበረ፡አውስግንዮስ፡መልሶ፡ነፍስህ፡በእጁ፡ የተያዘች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምልኮት ፡ ትተህ ፡ አንተ ፡ ለረከሱ ፡ ጣዖታት ፡ ለምን ፡ ሰገድክ፡ከአንተ፡በፊት፡የነበሩ፡ነገሥታትን፡ ለምን ፡ አልተከተልካቸውም ፡ እኔም ፡ እንዳንተ፡ወታደር፡ሁኜ፡ከቈስጠንጢኖስ፡ጋር፡ሃያ ዓመት ፡ ኖርኩ ፡ ከልጆቹም ፡ ጋር ፡ ነበርኩ፡ ከእነርሱ፡ውስጥ፡እንዳንተ፡ያለ፡ጠባየ፡ክፉ፡ የለም፡አለው።

፱፡ ዑልያኖስም ፡ በቅዱስ ፡ አውስግንዮስ፡ ላይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አውስግንዮስ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ ወይደዩ፡መኃትወ፡እሳት፡ውስተ፡ገበዋቲሁ፡ ወገብሩ፡ቦቱ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ውእቱሰ፡ተዓገሠ፡ በእንተ፡ስሙ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ስብሐት፡

፲፡ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ እምኵንኖቱ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ፡ርእሶ፡በሰይፍ፡ወሶበ፡መጽኡ፡ሐራ፡ ከመ፡ይምትሩ፡ርእሶ፡ሰእሎሙ፡ይትዓገሥዎ፡ እስከ ፡ ይጼሊ ፡ ወፈጺሞ ፡ ጸሎቶ ፡ መተርዎ ፡ ርእሶ፡ቅድስተ፡ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመ ንግሥተ፡ሰማያት።

፲፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እጅግ፡ተቆጣ፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡በጐኖቹም፡ ውስጥ፡መብራቶችን፡አስገብተው፡እንዲለበ ልቡት፡አዘዘ፡እርሱም፡ስለ፡ክብር፡ባለቤት፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ይህን ፡ ሁሉ፡ታገሠ።

፲፡ማሠቃየቱንም፡በሰለቸ፡ጊዜ፡ራሱን፡በሰይፍ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ወታደሮችም ፡ ሊቆርጡት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እስኪጸልይ ፡ ይታገሡት ፡ ዘንድ ፡ ለመናቸው ፡ ጸሎቱንም ፡ ሲፈጽም፡የከበረች፡ራሱን፡ቆረጡት፡የምስክ ርነት ፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማ ያት፡ተቀበለ።

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ እኛ ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአውስግንዮስ፡ለምሥጢረ፡መስቀል፡ዘተርጐሞ። አመ፡ቈስጠንጢኖስ፡ርእየ፡ማዕተበ፡ ከዋክብት፡ቀዊሞ። እንበለ፡ያጽዕቆ፡ልሕቅና፡ወእንበለ፡ርሥአን፡ያድክሞ። ምእተ፡ወዐሠርተ፡ዓመተ፡ መዋዕለ፡ሕይወቱ፡ፈጺሞ። በእንተ፡ክርስቶስ፡ተመትረ፡ወከዐወ፡ደሞ።

፲፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንርያ፡ ወውእቱ፡እምኍልቆሙ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡፹ወ፯ቱ።

፲፫፡ወለዝንቱ፡አባ፡ማቴዎስ፡አበዊሁ፡እምነገደ፡ እስራኤል ፡ ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ ወፍጹ ማን ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወስሙ ፡ ለአቡሁ ፡ ስምዖን፡ወስመ፡እሙ፡በርባራ፡ወወሀቦሙ፡ እግዚአብሔር ፡ ፪ተ ፡ ዘርዐ ፡ ወለዘይልሕቅ ፡ ስሙ ፡ ያዕቆብ ፡ ወለዘይንእስ፡ ሰሙ ፡ ማቴ ዎስ።

፲፬፡ወናሁ፡እንዘ፡ሀሎ፡ማቴዎስ፡ውስተ፡ከርሠ፡ እሙ ፡ ረከባ ፡ ለእሙ ፡ አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ዘሀገረ፡አቡፌስ፡ወሶበ፡ርእያ፡ወረደ፡ እምላዕለ፡አድጉ፡ወሰዓመ፡ከርሣ፡ወይቤላ፡ ቡርክት፡አንቲ፡ኦ፡ብእሲቶ፡ወቡሩክ፡ፍሬ፡ ከርሥኪ፡እስመ፡ናሁ፡ይወጽእ፡እምኔኪ፡ ኮከብ ፡ ብሩህ ፡ ዘያበርህ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በስብከቱ፡ከመ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ።

፲፭፡ወሶበ፡ኮኖ፡፲ወ፭ቱ፡ዓመተ፡እምዘተወልደ፡ አባ፡ማቴዎስ፡አዕረፉ፡አበዊሁ፡ወእምዝ፡ ሖረ፡ኀበ፡አባ፡አብርሃም፡ቆሞስ፡ዘደብረ፡ ቅዱስ ፡ አቡፋና ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ያልብሶ ፡

፲፪፡ በዚችም፡ዕለት፡የእስክንድርያ፡አገር፡ሊቀ፡ ጳጳሳት፡የከበረ፡አባት፡አባ፡ማቴዎስ፡አረፈ፡ እርሱም፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ሰማንያ፡ ሰባተኛው፡ነው።

፲፫፡ የዚህም ፡ የአባ ፡ ማቴዎስ ፡ ወላጆቹ ፡ ከእስ ራኤል፡ነገድ፡የሆኑ፡ክርስቶስን፡የሚያምኑ፡ በበጎ፡ሥራዎችም፡ፍጹማን፡የሆኑ፡ናቸው፡ የአባቱም፡ስም፡ስምዖን፡የእናቱም፡በርባራ፡ ይባላል፡እግዚአብሔርም፡ሁለት፡ዘርን፡ሰጣ ቸው፡የታላቁም፡ስም፡ያዕቆብ፡የታናሹም፡ ማቴዎስ፡ነው።

፲፬፡ እነሆ ፡ ማቴዎስም ፡ በእናቱ ፡ ሆድ ፡ ሳለ ፡ የአቡፌስ፡አገር፡ኤጲስቆጶስ፡አባ፡ጴጥሮስ፡ እናቱን፡አገኛት፡በአያትም፡ጊዜ፡ከበቅሎው፡ ላይ፡ወርዶ፡ሆድዋን፡ሳመ፡አንቺ፡ሴት፡የተ ባረክሽ፡ነሽ፡የማሕፀንሽም፡ፍሬ፡የተባረከ፡ ነው፡እነሆ፡እንደ፡ወንጌላዊ፡ማርቆስ፡በትም ህርቱ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያበራ ፡ ብሩህ ፡ ኮከብ፡ካንቺ፡ይወጣልና፡አላት።

፲፭፡ አባ ፡ ማቴዎስም ፡ ከተወለደ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት፡ዓመት፡ሲሆነው፡ወላጆቹ፡አረፉ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በቅዱስ ፡ አቡፋና ፡ ገዳም ፡ ወደአለ፡ቆሞስ፡ወደ፡አባ፡አብርሃም፡ሒደ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልብሰ ፡ ምንኵስና ፡ ውእቱ፤ ፡ ይቤሎ ፡ ተሰነ
ዓው ፡ ምስለ ፡ እኁከ ፡ ዘይልሕቅ ፡ ወሰሚዖ ፡
አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ተመይጠ ፡ እንዘ ፡ ትኩዘ ፡
ልብ፡ወበፍኖት፡ተራከቦ ፡ቅዱስ፡ሚካኤል፡
መልአክ፡በአምሳለ፡መነኰስ፡ወነገሮ፡ከመ፡
ውእቱ፡ ይከውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይከውና ፡
በእደዊሁ፡ተአምራት፡ወመንክራት።

፲፮፡ ወበጺሖ ፡ ኀበ ፡ እኁሁ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰአሎ ፡
ወአገበሮ፡ከመ፡ይኅድጎ፡ከመ፡ይመንኵስ፡
ወሶበ፡አበዮ፡ሖረ፡ኀበ፡ደብረ፡አባ፡አሞኒ፡
ዘደብረ ፡ ቶና ፡ወተማሕፀነ ፡ በቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ወሶበ ፡ ሰአልዎ ፡ መነኮሳት ፡ ለእ
ኁሁ፡ኀደጎ፡ይግበር፡ዘፈቀደ፡ወሶቤሃ፡ሖረ፡
ኀበ፡ደብረ፡ቅዱስ፡አቡፋና፡ወአመንኰሶ፡
አባ፡አብርሃም፡ወአኀዘ፡ይትጋደል፡በጾም፡
ወበጸሎት ፡ እስከ ፡ ተኃየለ ፡ እምኵሎሙ ፡
መነኰሰት።

፲፯፡ ወእምድኅረ ፡ ኮኖ ፡ ፩ ዓመተ ፡ መጽአ ፡ አባ ፡
ጴጥሮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ኀበ፡አባ፡አብርሃም፡
ወርእዮ ፡ ለአባ ፡ ማቴዎስ ፡ ትዕግሥቶ ፡
ወጥበቦ ፡ ሰአሎ ፡ ለአባ ፡ አብርሃም ፡ የሀቦ ፡
ኪያሁ፡ይኩኖ፡ረድአ፡ሎቱ፡ወነሥአ፡ኤጲ
ስቆጶስ፡ምስሌሁ፡ወነበረ፡ዘእንበለ፡ፈቃዱ፡
ወነበረ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ይተግህ ፡ ምልአ ፡
ሌሊተ ፡ እምጊዜ ፡ ዕርበታ ፡ ለፀሐይ ፡ እስከ ፡
ሥርቀታ።

፲፰፡ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ አኀዞ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ ፡ ወሤሞ ፡ ቀሲስ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ።
ወሰይጣንሰ፡ቀንአ፡ላዕሌሁ፡ወቦአ፡ውስተ፡
ልበ ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ላሕዪት ፡ እስከ ፡
አርአየቶ ፡ ገጸ ፡ ወተናገረቶ ፡ ለግብረ ፡ ፍት
ወት ፡ እኩይ ፡ ውእቱሰ ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡በአንብዕ ፡ እስከ ፡ ፈቀደ ፡ መዊተ።
ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወአስ
ተቀኖዖ፡ከመ፡ይፈንዎ፡ኀበ፡ደብሩ።

፲፱፡ ወሶበ ፡ ከልአ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሐዊረ ፡ ቦአ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ወነሥአ ፡ ልብሰ ፡
ክህነት ፡ ዘኤጲስቆጶስ ፡ ዘብዙኅ ፡ ሤጡ ፡ ወመ
ተሮ ፡ በመላፂ ፡ በበንስቲት ፡ ወሜጦ ፡ ኀበ ፡
መካኑ።

የምንኵስና፡ልብስ፡እንዲአለብሰውም፡ለመ
ነው ። እርሱም ፡ ከታላቅ ፡ ወንድምህ ፡
ተስማማ፡አለው፡አባ፡ማቴዎስም፡ሰምቶ፡
በልቡ ፡ እየተከዘ ፡ ተመለሰ ፡ በጐዳናም ፡
የከበረ ፡ መልአክ ፡ ሚካኤል ፡በመነኰስ ፡
አምሳል ፡ ተገናኘው ፡ እርሱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
እንደሚሆን ፡ በእጆቹም ፡ ድንቆች ፡ ተአም
ራቶች፡እንደሚደረጉ፡ነገረው።

፲፮፡ ወደ፡ወንድሙ፡ወደ፡ያዕቆብም፡ደርሶ፡እንዲ
መነኵስ፡ያሰናብተው፡ዘንድ፡ለመነው፡አባ
በለውም ፡ እምቢ ፡ ባለውም ፡ ጊዜ ፡ የአባ ፡
አሞኒ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደቶና ፡ ገዳም ፡ ሒዶ ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ተማጸነ። መነኰ
ሳቱም ፡ ወንድሙን ፡ በለመኑለት ፡ ጊዜ ፡ የወ
ደደውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ተወው ፡ በዚያ
ንም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ አቡፋና ፡ ገዳም ፡
ሒዶ ፡ አባ ፡ አብርሃም ፡ አመነኰሰው ፡ ከመነ
ኰሳት ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ አየለ ፡ ድረስ ፡ በጾምና ፡
በጸሎት፡ተጋደለ።

፲፯፡ አንድ ፡ ዓመትም ፡ ከሆነው ፡ በኋላ ፡ ኤጲስ
ቆጶሱ ፡ አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አብርሃም ፡
መጣ ፡ የአባ ፡ ማቴዎስንም ፡ ትዕግሥቱንና ፡
ብልህነቱን፡አይቶ፡ለርሱ፡ረዳት፡ይሆነው፡
ዘንድ ፡ እንዲሰጠው ፡ አባ ፡ አብርሃምን ፡
ለመነው ፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ ያለ ፡ ውዴታው ፡
ከርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰደው ፡ ፀሐይ ፡ ስትገባ ፡ ጀምሮ ፡
እስከምትወጣ ፡ ድረስ ፡ መላ ፡ ሌሊቱን ፡
እየተጋ፡በኤጲስቆጶሱ፡ዘንድ፡ኖረ።

፲፰፡ ዕድሜውም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡
ሲሆን ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡
ቅስና፡ ሾመው ። ሰይጣንም ፡ ቀናበት ፡
ፊቷንም፡እስካሳየችውና፡ለክፉ፡ፍትወት፡
ሥራ፡እስከተናገረችው፡ድረስ፡በአንዲት፡
ደም ፡ ግባት ፡ ባላት ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ አድሮ ፡
አነሣሣት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሞትን ፡ እስከተ
መኘ፡ድረስ፡በማልቀስ፡ወደ፡ እግዚአሔር፡
ጸለየ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ያሰና
ብተው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ገብቶ ፡
ማለደው።

፲፱፡ ኤጲስቆጶስም፡መሔድን፡በከለከለው፡ጊዜ፡
ወደ፡ዕቃ፡ቤት፡ገብቶ፡ወጋው፡ብዙ፡የሆነ፡
የኤጲስቆጶሱን፡መቀደሻ፡ልብሰ፡ተክህኖ፡
አንሥቶ፡በየጥቂቱ፡በምላጭ፡ቆረጠውና፡
መልሶ፡ከቦታው፡አኖረው።

www.ethiopianorthodox.org

፳፡ወበሣኒታ ፡ ይቤሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለአባ ፡ ማቴዎስ፡አምጽእ፡ሊተ፡ልብሰ፡ክህነት፡ ከመ፡እቀድስ፡ዮም፡ ወሶበ፡አብጽሐ፡ሎቱ፡ ወድቀ፡በቅድሜሁ፡ከመ፡ጽራብ፡ዕፅ፡ወርእዮ፡ ኤጴስቆጶስ፡ተምዐ፡ጥቀ፡ወይቤ፡መኑ፡ገብረ፡ ዘንተ፡ ወይቤሎ፡አባ፡ማቴዎስ፡አነ፡ገበርኩ፡ እመሰ፡ኢፈነውከኒ፡ኅበ፡ደብርየ፡እገብር፡ ዘየዓቢ፡እምዝ፡እምእደቅ፡በዝሙት።

፳፩፡ ወእምዝ፡ፈነዎ፡በመዓት፡ወጸሐፈ፡ግዘተ ለሰብአ፡ደብሩ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ይስግድ፡ በበ ፫፻ በመዓልት፡ወበሌሊት፡ኢይኅድር፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ወበዓት ፡ ወበቤተ ፡ ክርስ ቲያን፡ዘእንበለ፡በጊዜ፡ጸሎት፡ወተወክፈ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ዘንተ ፡ ገድለ ፡ ወተጋደለ፡ መጠነ ፡ ፪ ዓመት፡ ወሰሚዖ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ትዕግሥቶ፡ወየውሀቶ፡ፈነወ፡ሎቱ፡ቃለ፡ ፍትሐት፡ወቡራኬ።

፳፪፡ ወእመዝ፡ወጽአ፡እኁሁ፡ያዕቆብ፡ወመን ኰሰ፡ወተጋደለ፡እስከ፡ሞዖ፡ለሰይጣን።

፳፫፡ወአባ፡ማቴዎስኒ፡ሖረ፡ኀበ፡ደብረ፡አባ፡እን ጦንዮስ፡ወነበረ፡በህየ፡እንዘ፡ይትጋደል፡ ብዙኀ፡ ወሀሎ ፡ በህየ ፡ መነኮስ ፡ ጻድቅ ፡ ዘስሙ፡ያዕቆብ፡ርእየ፡ራእየ፡ከመ፡መጽአ፡ መልአክ፡ ብርሃናዊ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ወተአምኖ፡ወአንበረ፡ወንጌለ፡ዲበ፡ርእሱ፡ ወወሀቦ፡መራኁተ፡ውስተ፡እዴሁ፡ወነ ቂሐ፡አባ፡ያዕቆብ፡ነገሮ፡ለአባ፡ማቴዎስ፡ ዘንተ፡ራእየ።

፳፬፡ወእምአሜሃ፡ኮነ፡አባ፡ማቴዎስ፡ዘየዓውድ፡ እምሀገር ፡ ለሀገር ፡ በጸሊአ ፡ ስብሐት ፡ ብጡል።

፳፭፡ ወአሐተ፡ዕለተ፡እንዘ፡ይትለአክ፡ቅዳሴ፡ ቍርባን፡አባ፡ማቴዎስ፡ርእየ፡ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ነቢሮ፡ዲበ፡ምሥዋዕ፡ ወይሰክብ፡ውስተ፡ጻሕል፡በአምሳለ፡ሕፃን፡ ንኡስ፡ወበጊዜ፡ፈትቶ፡ኅብስት፡ይቀውም፡ ነዋኀ ፡ ሰዓተ ፡ ሰፊሐ ፡ እደዊሁ ፡ እንዘ ፡ ይዴመም፡ወያነክር፡ምስለ፡ዐቢይ፡ብካይ፡ ወበፍርሀት፡ወኢይነግር፡ለመኑሂ፡ዘንተ፡ ራእየ።

፳፡በማግሥቱም፡ኤጲስቆጶሱ፡አባ፡ማቴዎስን፡ መቀደሻዬን፡ልብሰ፡ተክህኖ፡አምጣልኝ፡ ዛሬ፡እቀድስ፡ዘንድ፡አለው ። በአቀረበለ ትም፡ጊዜ፡እንደ፡ዕንጨት፡ጥራቢ፡ሁኖ፡ በፊቱ፡ወደቀ፡ኤጲስቆጶሱም፡ተቆጥቶ፡ ይህን፡የሠራ፡ማነው፡አለ፡አባ፡ማቴዎስም፡ እኔ፡ነኝ፡አሁንም፡ወደ፡ቦታዬ፡ካላሰናበ ትከኝ፡በዚህ፡ቦታ፡በዝሙት፡ከምወድቅ፡ ከዚህ፡የበለጠ፡እሠራለሁ፡አለ።

፳፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በየቀኑ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ መቶ፡ እንዲሰግድ ፡ በሌሊትም ፡ በቤትና በዋሻ፡ውስጥ፡ገብቶ፡እንዳያድር፡በቤተ፡ ክርስቲያንም፡ከጸሎት፡ጊዘ፡በቀር፡እንዳ ይገባ፡ለገዳሙ፡ሰዎች፡ስለርሱ፡የውግዘት፡ ደብዳቤ፡ጽፎ፡በቁጣ፡አሰናበተው ። አባ ማቴዎስም ፡ ይህን ፡ ቅጣት ፡ ተቀብሎ ፡ ሁለት፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተጋደለ ፡ ኤጲስቆ ጶሱም፡ትዕግሥቱንና፡ቅንነቱን፡ሰምቶ፡ የፍተሐትና፡የቡራኬ፡ቃል፡ላከለት።

፳፪፡ ከዚህም፡በኋላ፡ወንድሙ፡ያዕቆብ፡ወደ፡ ገዳም፡ወጥቶ፡መነኰሰ፡ሰይጣንንም፡እስከ አሸነፈው፡ድረስ፡ተጋደለ።

፳፫፡ አባ፡ማቴዎስም፡ወደ፡አባ፡እንጦንዮስ፡ ገዳም ፡ ሒዶ ፡ በዚያ ፡ እየተጋደለ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖረ ፡ ከዚያም ፡ ስሙ ፡ ያዕቆብ ፡ የሚባል፡ጻድቅ፡መነኰስ፡ነበረ፡ብርሃናዊ፡ መልአክ፡ወደ፡አባ፡ማቴዎስ፡መጥቶ፡እጅ፡ ሲነሣው፡በራሱም፡ላይ፡ወንጌልን፡ሲያኖር፡ በእጁም፡መክፈቻን፡ሲሰጠው፡ራእይን፡ አየ፡አባ፡ያዕቆብም፡በነቃ፡ጊዜ፡ይህን፡ ራእይ፡ለአባ፡ማቴዎስ፡ነገረው።

፳፬፡ ከዚያን፡ጊዜም፡ጀምሮ፡ከንቱ፡ውዳሴን፡ በመጥላት፡ከሀገር፡ወደ፡ሀገር፡የሚዘዋወር፡ ሆነ።

፳፭፡በአንዲት፡ዕለትም፡በቍርባን፡ቅዳሴ፡ላይ፡ ሲያገለግል፡ጌታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ በመሠዊያው፡ላይ፡ተቀምጦ፡አየው፡በታ ናሽ፡ሕፃን፡አምሳል፡በፃሕል፡ውስጥ፡ ተኝቶ፡ነበር፡ኅብስቱንም፡በሚፈትትበት፡ ጊዜ፡እጆቹን፡ዘርግቶ፡ከታላቅ፡ልቅሶ፡ጋር፡ ፈጽሞ፡እያደነቀ፡በመፍራትም፡ለረጂም፡ ጊዜ፡ይቆማል፡ይህንንም፡ራእይ፡ለማንም፡ ለማን፡አይናገርም።

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፤ ወሶበ፡ ይሬኢ፡ መምህር፡ ያነክር፡ እምኔሁ፡ በእንተ፡ ቈመቱ፡ ነዊኅ፡ ሰዓተ፡ ወእመዝ፡ ጸለየ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ይክሥት፡ ሎቱ፡ ዘንተ፡ ወአሐተ፡ ዕለተ፡ በከመ፡ ልማዱ፡ ቦአ፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ ከመ፡ ይቀድስ፡ ወተርእየ፡ እግዚነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ለመምህሩ፡ ሰኪቦ፡ ዲበ፡ ጸሕል፡ እንዘ፡ ይተገመድ፡ በእዴሁ፡ ለአባ፡ ማቴዎስ፡ ተመሲሎ፡ ኅብስተ፡ ወአንከረ፡ መምህሩ ወይቤ፡ ስብሐት፡ ለከ፡ ዘወሀብከነ፡ እግዚኦ፡ ዘ'ተ፡ ዐቢየ፡ ጸጋ፡ ለውሉደ፡ ሰብእ፡ ለነ።

፳፯፤ ወሶበ፡ ርእየ፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ ዘንተ፡ አምጽአ፡ ቅንዋተ፡ ዘኀፂን፡ ወለክአ፡ ውስተ፡ ብረኪሁ፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ እስከ፡ ዐጸየ፡ ወወጽአ፡ እምኔሁ፡ ዕጼ።

፳፰፤ ወእምዝ፡ ሖረ፡ ኀበ፡ ደብረ፡ ቍስቋም፡ ወነበረ፡ ህየ፡ እንዘ፡ ይትጋደል፡ ብዙኀ፡ ወኮነ፡ ሶበ፡ ይኔጽር፡ ላዕለ፡ ይሬእየ፡ ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ ነቢሮ፡ በየማነ፡ አበሁ፡ ወሶበሂ፡ ይኔጽር፡ ታሕተ፡ ይሬእየ፡ በውስተ፡ ቀላያት፡ በዕበየ፡ ስብሐቲሁ።

፳፱፤ ወእምዝ፡ ሶበ፡ አዕረፈ፡ አባ፡ ገብርኤል፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ሤምዎ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ዘእንበለ፡ ፈቃዱ፡ ወሶበ፡ አበየ፡ ረሰዩ፡ ላዕሌሁ፡ ዐቀብተ፡ ወበሣኒታ፡ ነገርዎ፡ ኵሎሙ፡ ኤጲስቆጶሳት፡ ዘርእዩ፡ ራእየ፡ ከመ፡ ይደልዎ፡ ሎቱ፡ ሊቀ ጵጵስና፡ ወአእሚሮ፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ ከመ፡ ኢየኀድግዎ፡ ነሥአ፡ መላጼ፡ በኅቡእ፡ ወሰሐባ፡ ለልሳኑ፡ ወመተራ፡ ወበይዕቲ፡ ሌሊት፡ መጽአት፡ እግዝእትነ፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ኀቤሁ፡ ወቀብዓቶ፡ ቅብዐ፡ ፈውስ፡ ወሜጠት፡ ሎቱ፡ ልሳኖ፡ ከመ፡ ቀዳሚ።

፴፤ ወወሰድዎ። ኀበ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ወአመ፡ ሤምዎ፡ ሊቀ፡ ጵጵስና፡ አመ፡ ፲ወ፮ ለነሐሴ፡ በዕለተ፡ በዓላ፡ ለእግዝእትነ፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ወላዲተ፡ አምላክ፡ ተሰምዐ፡ ቃል፡ እምሰማይ፡ ዘይብል፡ ይደልዎ፡ ሠለስተ፡ ጊዜ፡ ወአምጽኡ፡ ርእሶ፡ ለማርቆስ፡

፳፮፤ መምህሩም፡ ለረጂም፡ ሰዓት፡ ሲቆም፡ በአየ፡ ጊዜ፡ ያደንቅ፡ ነበር፡ ይህንንም፡ ይገልጽለት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ጸለየ፡ በአንዲትም፡ ዕለት፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ እንደልማዱ፡ ሊቀድስ፡ ገባ፡ ጌታችንን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ በሕፃን፡ አምሳል፡ በጻሕሉ፡ ውስጥ፡ ተኝቶ፡ ኅብስትንም፡ መስሎ፡ በአባ፡ ማቴዎስ፡ እጅ፡ ሲቈረስ፡ ለመምህሩ፡ ለአበ፡ ምኔቱ፡ ታየው፡ አበ፡ ምኔቱም፡ አደነቀ፡ ለእኛ፡ ለሰው፡ ልጆች፡ ይህን፡ ታላቅ፡ ጸጋ፡ የሰጠኸን፡ አቤቱ፡ ለአንተ፡ ምስጋና፡ ይገባል፡ አለ።

፳፯፤ አባ፡ ማቴዎስም፡ ይህን፡ በአየ፡ ገዜ፡ የብረት፡ ችንካር፡ አመጣ፡ ተልቶ፡ ከእርሱ፡ ትል፡ እስቲወጣ፡ ድረስ፡ በጉልበቱ፡ ውስጥ፡ በዓርብ፡ ቀን፡ ቀረቀረው።

፳፰፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወደ፡ ደብረ፡ ቍስቋም፡ ሒዶ፡ አብዝቶ፡ እየተጋደለ፡ በዚያ፡ ኖረ፡ ወደ፡ ላይ፡ ቀና፡ ብሎ፡ ሲመለከት፡ ጌታችንን፡ የክብር፡ ባለቤት፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ በአባቱ፡ ቀኝ፡ ተቀምጦ፡ የሚያየው፡ ሆነ፡ ወደታችም፡ ሲመለከት፡ በውቅያኖስ፡ ጥልቅ፡ ውስጥ፡ በጌትነቱ፡ ክብር፡ የሚያየው፡ ሆነ።

፳፱፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አባ፡ ገብርኤል፡ በአረፈ፡ ጊዜ፡ ያለ፡ ውዴታው፡ ይህን፡ አባት፡ ሾሙት፡ እምቢ፡ በአላቸውም፡ ጊዜ፡ ጠባቂዎችን፡ በላዩ፡ አደረጉ፡ በማግሥቱም፡ ሊቀ፡ ጵጵስና፡ እንደሚገባው፡ ያዩትን፡ ራእይ፡ ኤጲስቆጶሳቱ፡ ሁሉም፡ ነገሩት፡ አባ፡ ማቴዎስም፡ እንደማይተዉት፡ አውቆ፡ በሥውር፡ ምላጭ፡ ወስዶ፡ ምላሱን፡ ጐትቶ፡ ቆረጣት፡ በዚያችም፡ ሌሊት፡ እመቤታችን፡ የከበረች፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ወደርሱ፡ መጥታ፡ የሚያድን፡ ቅባትን፡ ቀብታ፡ ምላሱን፡ እንደ፡ ቀድሞዋ፡ አድርጋ፡ መለሰችለት።

፴፤ ወደ። እስክንድርያም፡ ወሰዱት፡ በነሐሴ፡ ዐሥራ፡ ስድስት፡ አምላክን፡ በወለደች፡ በእመቤታችን፡ በቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ በበዓልዋ፡ ቀን፡ ሊቀ፡ ጵጵስና፡ በሾሙት፡ ጊዜ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ይገባዋል፡ የሚል፡ ቃል፡ ከሰማይ፡ ተሰማ፡ በክንዱ፡ ላይም፡ ያደርጉ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወንጌላዊ ፡ ከመ ፡ ያንብሩ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ሠረረት ፡ ርእስ ፡ ወሰዐመት ፡ አፉሁ ።

፴፩፡ ወእምአሜሃ ፡ ኢነበረ ፡ ዲበ ፡ አትሮንስ ፡ በጊዜ ፡ ቍርባን ፡ ወኢይበውእ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ውረቡዕ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ መኑሂ ፡ እምሰብእ ።

፴፪፡ ወተነበየ ፡ ከመ ፡ ይነግሥ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ነጊሦ ፡ እኁሁ ፡ ውድም ፡ አስፈሬ ።

፴፫፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ገብረ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ብዙኀ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ በፈውሶ ፡ ዱያን ፡ ወአንሥአ ፡ ሙታን ፡ በሰበን ፡ ዘዲበ ፡ ርእሱ ።

፴፬፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ተሠይመ ፡ መኰንን ፡ እኩይ ፡ እምታሕተ ፡ ሥልጣነ ፡ ምስር ፡ ወአገበሮ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ማቴዎስ ፡ ነሢአ ፡ ጸባሕት ፡ ዘኢነበረ ፡ ቀዳሚ ፡ ወሶበ ፡ አበዮ ፡ ዘበጦ ፡ ዐቢየ ፡ ዝብጠተ ፡ ወወሰድዎ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ፀዊሮሙ ፡ ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ሰአላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ከመ ፡ ትንሣእ ፡ ነፍሶ ፡ እምገዐረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወይእቲ ፡ አስተርአየቶ ፡ ወተናገረቶ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ኢትኅዘን ፡ እምድኅረ ፡ ፫መዋዕል ፡ ተዓርፍ ።

፴፭፡ ወበሣኒታ ፡ ጸውዖሙ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ለኤጲስ ቆጶሳት ፡ ወለቀሳውስት ፡ ወለዲያቆናት ፡ ወለ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወነገሮሙ ፡ ዕረፍቶ ፡ ወመዐዶሙ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ወባረኮሙ ።

፴፮፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጊዜሁ ፡ ወጸንዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሕማም ፡ ነሥአ ፡ ሥዕለ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወጸለየ ፡ ነዋኀ ፡ ሰዓተ ፡ ወተሳለማ ፡ ወሰዓማ ፡ ለሥዕል ፡ ወአተበ ፡ ገጾ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወባረከ ፡ ኵሎ ፡ ሀገረ ፡ እለ ፡ ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ ወአዕረፈ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ።

፴፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎተ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ዘንድ ፡ የወንጌላዊ ፡ ማርቆስን ፡ ራስ ፡ አመጡ ፡ እርሷም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በረረችና ፡ አፉን ፡ ሳመች ።

፴፩፡ ከዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በቍርባን ፡ ጊዜ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ አልተቀመጠም ፡ በዓርብና ፡ በረቡዕ ፡ ቀን ፡ ከሰው ፡ ማንም ፡ ወደርሱ ፡ ቤት ፡ የሚገባ ፡ የለም ።

፴፪፡ ወንድሙ ፡ ውድም ፡ አስፈሬ ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ እንደሚነግሥ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

፴፫፡ ይህም ፡ አባት ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ በሚያደርገው ፡ ቀጸላ ፡ በሽተኞችን ፡ በመፈወስ ፡ ሙታንን ፡ በማስነሣት ፡ በዘመኑ ፡ ብዙ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ።

፴፬፡ በዘመኑም ፡ ከምስር ፡ ሥልጣን ፡ ች ፡ ክፉ ፡ ሹም ፡ ተሾመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ማቴዎስን ፡ አስቀድሞ ፡ የሌለ ፡ ግብርን ፡ ሊቀበለው ፡ ሽቶ ፡ ግድ ፡ አምጣ ፡ አለው ፡ በከለከለውም ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ድብደባን ፡ ደበደበው ፡ ተሸክመውም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰዱት ። በዚያችም ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፃዕር ፡ ታሳርፈው ፡ ዘንድ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ለመናት ፡ እርሷም ፡ ተገልጻ ፡ አትዘን ፡ ከሦስ ንት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ታርፋለህ ፡ ብላ ፡ ተናገረችው ።

፴፭፡ በማግሥቱም ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ኤጲስቆጶሳቱን ፡ ቀሳውስቱንና ፡ ዲያቆናቱን ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ አስጠራቸውና ፡ የዕረፍቱን ፡ ቀን ፡ ነገራቸው ፡ የሃይማኖትንም ፡ ነገር ፡ መከራቸው ፡ ባረካቸውም ።

፴፮፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጊዜው ፡ ደርሶ ፡ ሕማሙ ፡ በጸናበት ፡ ጊዜ ፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ሥዕል ፡ አንሥቶ ፡ ይዞ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጸለየ ፡ ሥዕሊቱንም ፡ ተሳልሞ ፡ ሳማት ፡ ፊቱንም ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ አማተበ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያምኑ ፡ ምእመናን ፡ ያሉበትን ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ፡ ባረከ ፡ በዕሑድ ፡ ቀንም በሰላም ፡ አረፈ ።

፴፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ስንክሳር ዘወርኀ ጥር

## አርኬ

ሰላም ፡ ለማቴዎስ ፡ እምካልዓኒሁ ፡ ዘተበፅዐ ። ሶበ ፡ ክብረ ፡ ዓለም ፡ ጸልአ ። ምክረ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ እንዘ፡ይሰምዕ፡ሰሚዐ።እንተ፡መተረ፡ልሳኖ፡ኀበ፡ህላዌሁ፡አግብአ።አመ፡እምኔሃ፡ቀብዐ፡ፈውስ፡ተቀብዐ።

፴፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለያሬውንዮስ ፡ ወለባልአን ፡ ዕድ ፡ ወአንስት ፡ ወለለንጊኖስ ፡ ዘሮሜ ፡ ወለእስክንድርያ ፡ ዘሐወጸቶ ፡ ለአባ ፡ አርሳኒ፡ወለአውስያ፡ወበረከቶሙ፡ትብጽሐነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፰፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የያሬውንዮስ ፡ የሌሎችም ፡ የሴቶችና፡የወንዶች፡የሮማዊው፡ለንጊኖስ፡ አባ ፡ አርሳኒን ፡ የጐበኘችው ፡ የእለስክን ድርያ፡የአውስያ፡መታሰቢያቸው፡ነው።በረ ከታቸውም፡ትድረሰን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአውስያ፡እንተ፡ተመይጠት፡እምካህዳ።እግዚአብሔር፡ጊዜ፡ፈቀዳ።አመ፡አኀዘዋ፡ላቲ፡ ወአቅረብዋ፡ለፍዳ። ሶበ፡ከልሐ፡ማዕከሎሙ፡ፈረሰ፡ቴዎድሮስ፡ወልዳ።ማኅበረ፡አጋንንት፡ተዘርዉ፡ ወጐዩ፡እምዐውዳ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፯ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ቦአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት ፡ ወፈጸመ ፡ ሕገ ፡ ዘውስተ ፡ ኦሪት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ፡ ልሳነ ፡ ዕፍረት ፡ እስመ፡እግዚእ፡ክርስቶስ፡ተወክፈ፡ግዝረተ፡ በሥጋሁ፡ከመ፡ይፈጽም፡ኪዳነ፡አበው።

፪፡እስመ፡ለብዙኃን፡መሰሎሙ፡ከመ፡እግዚእነ፡ ኢቦአ፡ውስተ፡ቤተ፡ግዝረት፡ወኢተገዝረ፡ ሶበሰ፡ኮነ፡ከመ፡እሙንቱ፡ሐለዩ፡እምኮኑ፡ አይሁድ፡ዘይረክቡ፡ዐቢየ፡ምክንያተ፡አላ፡ ፈጸመ፡እግዚእነ፡ሕገ፡ኦሪት፡ወለነኒ፡ረሰየ፡ ለነ፡ህየንቴሁ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡ወበልዐ ናዕተ ፡ ወረሰየ ፡ ለነኒ ፡ ህየንቴሁ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሞ።

፫፡በከመ፡ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ወአመ፡ተፈጸመ፡ ሰሙን፡ዕለት፡ወሰድዎ፡ለሕፃን፡ከመ፡ይግ ዝርዎ፡ወሰመይዎ፡ስሞ፡ኢየሱስሃ፡በከመ፡ ሰመዮ፡መልአክ፡እምቅድመ፡ትፅንሶ፡ወት ቤሎ ፡ እግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ ወንጽሕት ፡ ማርያም፡ለጻድቅ፡አረጋዊ፡ዮሴፍ፡አምጽእ፡ ሊተ ፡ ገዛሬ ፡ ጠቢበ፡ ከመ ፡ ይግዝሮ ፡ ለወል ድየ ፡ በከመ ፡ ሕግ ፡ ወንስሚ ፡ ስሞ ፡ ወሖረ ፡ ዮሴፍ ፡ ወአምጽአ ፡ ገዛሬ ፡ ጠቢበ ። ወእቱኒ ፡ ገዛሪ ፡ ርእዮ ፡ ለሕፃን ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ እሙ ፡ ንጽሕት ፡

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ግዝረት ፡ በመግባት ፡ የኦሪትን ፡ ሕግ ፡ ፈጸመ ፡ ልሳነ ፡ ዕፍረት ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ጌታ ፡ ክርስ ቶስ ፡ በሥጋው ፡ ግዝረትን ፡ ተቀበለ ፡ ለአባ ቶች ፡ የተሰጠውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ፡ብሎ፡እንደተናገረ።

፪፡ ለብዙዎችም፡ጌታችን፡ወደ፡ቤተ፡ግዝረት፡እን ዳልገባና፡እንዳልተገረዘ፡ይመስላቸው፡ነበር፡ እነርሱ፡እንዳሰቡት፡ሁኖ፡ቢሆን፡ኑሮ፡አይ ሁድ፡ታላቅ፡ምክንያትን፡የሚያገኙ፡በሆኑ፡ ነበር፡ጌታችን፡ግን፡የግዝረትን፡ሕግ፡ፈጸመ፡ ለእኛ ፡ በግዝረት፡ ፈንታ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀ ትን ፡ ሰጠን ፡ የፋሲካውንም ፡ ቂጣ ፡ በላ ፡ በእር ሱም፡ፈንታ፡ሥጋውንና፡ደሙን፡ሰጠን።

፫፡የከበረ፡ወንጌል፡ስምንተኛው፡ቀን፡በተፈጸመ፡ ጊዜም ፡ ሕፃኑን ፡ ሊገዝሩት ፡ ወሰዱት ፡ ሳትፀ ንሰው፡መልአኩ፡እንዳወጣለት፡ስሙን፡ኢየ ሱስ ፡ አሉት ፡ እንዳለ ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን፡ማርያም፡ጻድቅ፡አረጋዊ፡ዮሴ ፍን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ልጄን፡ እንዲገርዘውና ፡ ስሙንም ፡ እንድንሰይመው ፡ ብልህ ፡ የሆነ ፡ ገራዥ ፡ ሰው ፡ አምጣልኝ ፡ አለችው። ዮሴፍም፡ ሒዶ ፡ የሚገርዝ ፡ ባለሙያ ፡ አመጣ ፡ ያ ፡ ባለ ሙያም ፡ ሕፃኑን፡ ጌታችንን፡ ኢየሱስ፡ ክርስ ቶስን ፡ በእናቱ ፡ በንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ማር

www.ethiopianorthodox.org

ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወይቢሎሙ ፡ አኀዝዎ ፡
ለሕፃን፡ጥንቁቀ፡ከመ፡እግዝሮ።
፬፡ወአውሥአ፡ሕፃን፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡
አ፡ጠቢብ፡ገዛሪ፡ትክልኑ፡ትግዝረኒ፡ዘእንበለ፡
ይትከዐው ፡ ደምየ ፡ እስመ፡ ኢይትከዐው ፡
ደምየ፡ ዘእንበለ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ አመ ፡
ይረግዙኒ ፡ ገቦየ ፡ በኲናት ፡ አሜሃ ፡ ይውኅዝ ፡
ደም፡ወማይ፡ወይከውን፡መድኀኒተ፡ለአዳም፡
ወለደቂቁ፡ለእለ፡የአምኑ።
፭፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ውእቱ ፡ ጠቢብ ፡ ነገሮ ፡ ለእግ
ዚእነ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
አንከረ ፡ ወአስተጋብአ ፡ ንዋዮ ፡ ወተንሢአ ፡
ሰገደ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለሕፃን ፡ ወመላፅያ
ቲሁኒ ፡ አሜሃ ፡ ተመስዉ ፡ ላዕለ ፡ እደዊሁ ፡
ወኮኑ፡ ከመ ፡ ማይ ። ወይቤላ ፡ ለእግዝእትነ ፡
ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ቡርክት ፡ አንቲ፡
እምአንስት ፡ ወቡሩክ ፡ ፍሬ ፡ ከርሥኪ፡ እስመ ፡
ዝንቱ ፡ ወልድኪ ፡ ዘተነበዩ፡ ነቢያት ፡ በእን
ቲአሁ፡ወውእቱ፡ወልደ፡አምላክ፡ሕያው።
፮፡ ወአውሥአ ፡ ካዕበ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ ፡ ለውእቱ ፡
ጠቢብ፡አነ፡ውእቱ፡ትገዝረኒኑ፡አው፡አልቦ፡
ወሚመ ፡ እግበር ፡ አነ ፡ በከመ ፡ ገብሩ ፡ አበወ ፡
አበውየ ፡ ወይቤ ፡ ውእቱ፡ ጠቢብ ፡ እለመኑ ፡
አበወ ፡ አበዊከ ። አውሥአ ፡ እግዚእነ ፡ ሕፃን ፡
ወይቤሎ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡
አበዊሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወለእሉ ፡ ዘእምቅድም ፡
ተውህቦሙ ፡ እምኀበ ፡ አቡየ ፡ ዝንቱ ፡ ግዝረት ፡
ወይቤሎ ፡ ጠቢብ ፡ አንሰ ፡ ኢይክል ፡ እትናገር ፡
ምስሌከ ፡ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልው ፡
ውስቴትከ።

፯፡ ወሶቤሃ ፡ አንሥአ ፡እግዚእነ ፡ ሕፃን ፡ አዕይ
ንቲሁ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወይቤ ፡ አ ፡ አባ ፡ ሀበኒ ፡
ዮም ፡ ግዝረተ ፡ ዘወሀብኮሙ፡ ለአብርሃም ፡
ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ እምቀዳሚ ፡ አሚሃ ፡ አስ
ተርአየት ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ፡ ለሕፃን ፡ ዘእንበለ ፡
እደ ፡ ሰብእ ፡ ግዝረት።
፰፡ ወኮነ ፡ ግዝረቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘኢይትዓወቅ ፡
በከመ ፡ ምሥጢረ ፡ ጸአቱ ፡ እምከርሠ ፡
ድንግል፡ እንዘ ፡ ኢይማስን ፡ ድንግልናሃ ፡
ወከማሁ ፡ በአቱ ፡ ወጸአቱ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡
እንዘ ፡ ዕፁው ፡ ጽርሕ ፡ ወከመዝ ፡ ከሠተ ፡
ክሂሎቶ ፡ በዘፈቀደ ፡ እምኪነ ፡ ጥበቡ ፡ እንዘ ፡

ያም ፡ ክንድ ፡ ላይ ፡ አየው ፡ እንድገርዘው፡ ሕፃ
ኑን፡በጥንቃቄ፡ያዙት፡አላቸው።
፬፡ሕፃን፡ጌታ፡ኢየሱስም፡መልሶ፡እንዲህ፡አለው፡
ባለሙያ ፡ ገራዥ ፡ ሆይ ፡ ደሜ ፡ ሳይፈስ ፡ ትገ
ርዘኝ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለህን ፡ በዚያች ፡ ዕለት ፡
ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ደሜ ፡ አይፈስምና ፡ ጐኔን ፡
በጦር ፡ ሲወጉኝ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ውኃና ፡ ደም ፡
ይፈሳል ፡ ለአዳምና ፡ ለሚያምኑ፡ ልጆቹ ፡ መድ
ኃኒት ፡ ይሆናል።
፭፡የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡
የተናገረውን ፡ ያ ፡ ባለሙያ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አደ
ነቀ ፡ ዕቃውንም ፡ ሰብስቦ ፡ ተነሥቶ ፡ ከሕፃኑ ፡
ጌታ ፡ እግር ፡ በታች ፡ ሰገደ ፡ ያንጊዜም ፡ ምላ
ጮቹ፡ በእጆቹ ፡ ላይ ፡ ቀልጠው ፡ እንደ ፡ ውኃ፡
ሆኑ፡ የከበረች፡ ድንግል፡ እመቤታችንን፡ ማርያ
ምን ፡ ከሴቶች ፡ ተለይተሽ ፡ አንቺ ፡ የተባረክሽ ፡
ነሽ ፡ የማሕፀንሽም ፡ ፍሬ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ ይህ ፡
ልጅሽ ፡ ስለርሱ ፡ ነቢያት ፡ ትንቢት፡ የተናገሩ
ለት፡የሕያው፡አምላክ፡ልጅ ፡ ነው፡ አላት።
፮፡ ሕፃኑም ፡ ለዚያ ፡ ባለሙያ ፡ ዳግመኛ ፡ መልሶ ፡
እንዲህ ፡ አለው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ትገዝረኛለህን ፡
ወይስ ፡ ተውክ ፡ ወይም ፡ ያባቶቼ ፡ አባቶች ፡
እንዳደረጉ ፡ እኔ ፡ ላድርግ ፡ ያም ፡ ባለሙያ ፡ የአባ
ቶችህ ፡ አባቶች ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ አለው ፡
ሕፃን ፡ ጌታችንም ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡
ያዕቆብ ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አባቶች ፡ የሆኑ ፡
ናቸው ፡ ለእነርሱም ፡ ይህ ፡ ግዝረት ፡ አስቀ
ድሞ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ተሰጣቸው ፡ ባለሙ
ያውም ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡
አልችልም፡በአንተ፡ህልውና፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
አለና፡አለው።
፯፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሕፃኑ ፡ ጌታችን ፡ ዐይኖቹን፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንቶ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ለአብ
ርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ አስቀድሞ፡
ግዝረትን ፡ የሰጠሃቸው ፡ ያቺን ፡ ግዝረት ፡ ዛሬ፡
ለእኔ፡ስጠኝ፡አለ።ያን፡ጊዜ፡ያለ፡ሰው፡እጅ፡
በሕፃኑ፡ሥጋ፡ላይ፡ግዝረት፡ተገለጠች።
፰፡ ድንግልናዋ ፡ ሳይለወጥ ፡ ከድንግል ፡ ማሕፀን ፡
እንደ ፡ መውጣቱ ፡ የጌታችን ፡ ግዝረቱ ፡ የማይ
መረመር ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡
በተዘጋ፡ አዳራሽ ፡ መግባቱና ፡ መውጣቱ ፡ እን
ደማይመረመር ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡
ከረቀቀ ፡ ጥበቡ ፡ ችሎታውን ፡ በመገረዝ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኢይትመተር ፡ ምንተኒ ፡ እምሥጋሁ፡በግ
ዝረት።

፱፡ወሶበ፡አኮ፡በፈቃዱ፡ደም፡ወማይ፡ዘይውኅዝ፡
እምገቦሁ ፡ በዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ከመ ፡
ያድኅኖሙ ፡ ለአዳም ፡ ወለደቂቁ ፡ ወከመ፡
ይኩን ፡ ውሱከ ፡ ወኢሕፀፀ ፡ በርእሱ ፡ አላ ፡
በፈቃዱ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ሕግ ፡ አዘዘ ፡
ቀዳሚ።

፲፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ውእቱ ፡ ጠቢብ ፡ ገባሬ ፡ ዘንተ ፡
ተአምረ ፡ ወሰምዐ ፡ ነገሮ ፡ ለሕፃን ፡ አንከረ ፡
ፈድፋደ ፡ ወሰገደ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
ወይቤሎ ፡ አማን ፡ አንተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ወንጉሠ፡እስሬኤል።

፲፩፡ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ መካኑ ፡ እንዘ ፡ ይዜኑ ፡
ዘርእየ ፡ ወሰምዐ ፡ እምተአምራቲሁ ፡ ለእግ
ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወሎቱ፡ስብሐት፡
ወአኰቴት፡ወሰጊድ፡ምስለ፡አቡሁ፡ኄር፡
ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ፡ ይእዜኒ ፡
ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ከሥጋው፡ምንም፡ምን፡ሳይቆረጥ፡ገለጠ።

፱፡ አዳምንና ልጆቹን ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡
በፈቃዱ፡ከጐኑ፡በመስቀል፡ላይ፡የሚፈሰው፡
ደምና ፡ ውኃ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ብዙም ፡ ሆነ ፡
ጥቂት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ እርሱ ፡ በፈቃዱ ፡
ሕጉ፡እንዲፈጸም፡አስቀድሞ፡አዘዘ፡እንጂ።

፲፡ያም፡ባለሙያው፡ገራሽር፡ይህን፡ተአምር፡ባየ፡
ጊዜ፡የሕፃኑንም፡ነገር፡በሰማ፡ጊዜ፡እጅግ፡
አደነቀ፡የክብር፡ባለቤት፡ከሆነ፡ከጌታችን፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግር ፡ በታች ፡ ሦስት ፡
ጊዜ፡ ሰገደና ፡ በእውነት ፡ አንተ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ፡
አለው።

፲፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከጌታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ከተአምራቱ ፡ ያየውንና ፡ የሰማውን ፡
እየተናገረ ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ ሔደ ፡ ለእርሱም ፡
ለጌታችን ፡ ከቸር ፡ አባቱ ፡ ጋራ ፡ ማሕየዊ ፡
ከሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ ክብር ፡
ምስጋና ፡ ስግደትም ፡ ይሁን ፡ ዛሬም ፡
ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለግዝረትከ፡በመዋዕል፡ሰሙን።ከመ፡ትፈጽም፡ለሊከ፡ሥርዓተ፡ኪዳን።እንተ፡ወሀብከ፡
እግዚአ፡አመ፡ቀዳሚ፡ዘመን።ግዝረተ፡መጥባሕት፡ለወልደ፡ታራ፡ምእመን።ወበዕብነ፡እዝኅ፡ለአውሴ፡
መስፍን።

፲፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡
ለአቡነ ፡ ኖኅ ፡ ዘውእቱ ፡ ዐሥር ፡ እምአቡነ ፡
አዳም።

፲፫፡ ወውእቱ ፡ እምንእሱ ፡ ኮነ ፡ ዘይኔጽር ፡
ምሥጢረ ፡ አምላካዌ ፡ ከመ ፡ ይበዝኅ ፡
ኃጢአት ፡ ወይመልእ ፡ እከይ ፡ ወይውሕዱ ፡
ጻድቃን ፡ ወይደመሰስ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ በማየ ፡
አይኅ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ዘይላሁ ፡ ወይበኪ ፡
ወይቈጽር፡ገጾ።

፲፬፡ወዐቀበ፡ድንግልናሁ፡፭ተ፡፻ተ፡ዓመተ፡ወነበረ፡
እንዘ ፡ ይትለአክ ፡ ለሥጋ ፡ አቡነ ፡ አዳም ፡
በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡
እግዚእ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ወነገሮ ፡
ከመ ፡ ይደመሰስ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ወአልቦ ፡
ዘይተርፍ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡
ዚአሁ ፡ ወአውሰበ ፡ ብእሲተ ፡ ዘስማ ፡
ሐይከል ፡ ወለተ ፡ አቡዚር ፡ ወቦአ ፡ ኀቢሃ ፡ ፫

፲፪፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ የአባታችን ፡ የኖኅ ፡
የዕረፍቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ከአባ
ታችን፡አዳም፡ዐሥረኛ፡ትውልድ፡ነው።

፲፫፡እርሱም፡ከታናሽነቱ፡ጀምሮ፡ኃጢአት፡እን
ደሚበዛ ፡ ክፋትም ፡ እንደሚመላ ፡ ደጋጎች ፡
እንደሚያንሱ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ፡ በጥ
ፋት፡ ውኃ ፡ እንደሚደመሰስ ፡ አምላካዊ ፡
ምሥጢርን፡የሚያይ፡ሆነ፡ስለዚህም፡ፊቱ፡
የተቋጠረ፡ሁኖ፡ፈጽሞ፡ያለቅስ፡ነበር።

፲፬፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዓመትም ፡ ድንግልናውን ፡
ጠብቆ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ለአባ
ታችን ፡ አዳም ፡ ሥጋ ፡ ሲያገለግል ፡ ኖረ ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሚስት ፡ እንዲያገባ ፡ ጌታ ፡
አዘዘው ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ እንደሚደ
መሰስ ፡ ከርሱ ፡ ዘር ፡ በቀር ፡ የሚተርፍ ፡
እንደሌለ ፡ ነገረው ። የአቡዚር ፡ ልጅ ፡
የሆነች፡ ሐይከል ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ አገባ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ፡ ወወለዶሙ ፡ ለሴም ፡ ወለካም ፡ ወለ ያፌት።

፲፭፡ ወእምዝ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኖኅ ፡ ግዝም ፡ ዕፀወ ፡ እምዝንቱ ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ወግበር፡ ለከ፡ ታቦተ ፡ እንተ ፡ ዕፅ ፡ ርብዕተ ፡ ወትቀብዓ ፡ እንተ ፡ ውስጣ ፡ ወእንተ ፡ አፍአሃኒ፡በፒሳ።

፲፮፡ ወከመዝ፡ትገብራ፡፫፻ተ፡በእመት፡ኑኃ፡ወ፶ በእመት፡ርኅባ፡ወ፴፡በእመት፡ቆማ።

፲፯፡ ወመስኮተ ፡ ግበር ፡ ለይእቲ፡ ታቦት ፡ ወሶበ ፡ በጽሐት፡ለተፈጽሞ፡አሐቲ፡እመት፡እንዘ፡ ትተርፍ ፡ ግበር ፡ ህየ፡ ኖኅተ ፡ ውስተ ፡ ገቦሃ ፡ ወግበር፡ላቲ፡መዓርጋተ፡ተጽራሕ፡ወተሥ ላስ።

፲፰፡ቀዳማይ፡መዓርግ፡ይኩን፡ለአራዊት፡ወለእ ንስሳ ፡ ወዳግማይ ፡ መዓርግ ፡ ለአዕዋፍ ፡ ወለኵሉ፡ዘይትሐወስ፡ወሣልሳይ፡ይኩን፡ ለከ፡ወለወሉድከ፡ምስለ፡አንስትያሆሙ።

፲፱፡ ወካዕበ ፡ ይቤሎ ፡ ንሣእ ፡ ለከ፡ እምነ ፡ ኵሉ፡ መባልዕት፡ዘይሴሰዩ፡ወአስተጋብእ፡ኀቤከ፡ ወይከውነከ ፡ መብልዐ ፡ ለከ ፡ ወለኵሎሙ ፡ አራዊት፡ወእንስሳ።

፳፡ ወእምዝ ፡ ገብረ ፡ ኖኅ ፡ መጥቅዐ ፡ እምዕፅ ፡ ዘኑኁ፡ ፫ በእመት ፡ ወግድሙ ፡ ፩ እመት ፡ ወመንፈቅ ፡ በዘቦቱ ፡ ይጠቅዕ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚ ፡ ነግሀ ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ ፡ መስተገ ብራን፡ለግብር፡ወዳግሙ፡ለበሊዕ፡ወሣልሱ፡ ለአዕርፎ።

፳፩፡ወርእዮሙ፡እንዘ፡ይገብር፡ታቦተ፡በእንተ፡ ድኅነት፡ እማየ ፡ አይኅ ፡ ተሣለቅዎ ፡ ለኖኅ ፡ ደቂቀ ፡ ቃየል ፡ ወይቤልዎ ፡ ዝንቱ ፡ አረጋዊ ፡ አብደ ፡ እፎ ፡ ይብለነ ፡ የዐርጉ ፡ ማያት ፡ መልዕልተ፡አድባር።

፳፪፡ ወእምዝ ፡ ነሥአ ፡ ኖኅ ፡ ሥጋ ፡ አቡነ፡ አዳም፡ ወሜም ፡ ወልዱ ፡ ነሥአ ፡ ወርቀ፡ ወካም ፡ ከርቤ ፡ ወያፌት ፡ ስኂነ ፡ ወአብኡ ፡ ውስተ ፡ ታቦት።

፳፫፡ ወቦአ ፡ ኖኅ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወደቂቁ ፡ ወአን ስትያ ፡ ደቂቁ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ በእንተ፡ማየ፡አይኅ።

ወደርሷም፡ሦስት፡ጊዜ፡ገባ፡ሴምን፡ካምን፡ ያፌትን፡ወለዳቸው።

፲፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኖኅን ፡ እንዲህ፡አለው፡ከዚህ፡ከደብር፡ቅዱስ፡ዕን ጨቶችን ፡ ቊረጥ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ አድር ገህ፡ ላንተ ፡ መርከብን ፡ ሥራ ፡ ውጭዋንና ፡ ውስጧንም ፡ የደሮ ፡ ማርና ፡ ሙጫ ፡ ለቅል ቃት፡አለው።

፲፮፡አቈልቋይዋን፡ሦስት፡መቶ፡ወርዷን፡ኃምሳ፡ ቊመቷን፡ሠላሳ፡ክንድ፡አድርገህ፡ሥራት፡ አለው።

፲፯፡ ለዚያችም ፡ መርከብ ፡ መስኮት ፡ አውጣላት ፡ አንዲት ፡ ክንድ ፡ ስትቀር ፡ ለመጨረስም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የጐን ፡ ደጃፍ ፡ አውጣላት ፡ የአደራሽነትዋ ፡ እርከንን ፡ ሥራላት፡ሦስት፡ክፍል፡አድርገህ፡ሥራት።

፲፰፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ለአራዊትና ፡ ለእንስሳ፡ ይሁን ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ለአዕ ዋፍና ፡ ለተንቀሳቃሽ፡ ሁሉ ፡ ይሁን ፡ ሦስተ ኛውም ፡ ክፍል ፡ ለአንተና ፡ ለልጆችህ ፡ ከሚ ስቶቻቸው፡ጋር፡ይሁን።

፲፱፡ ሁለተኛም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ከሚመገቧ ቸው፡ መብሎች ፡ ሁሉ ፡ አስገባ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ፡አኑር፡ላንተ፡ለአውሬዎችም፡ለእንስ ሶችም፡ሁሉ፡ምግብ፡ይሆንልሃል።

፳፡ከዚህም፡በኋላ፡ኖኅ፡ርዝመቱ፡ሦስት፡ክንድ፡ ጐኑ፡አንድ፡ክንድ፡ተኩል፡የሆነ፡የዕንጨት፡ ደወል፡ሦስት፡ጊዜ፡የሚደውልበትን፡ሠራ፡ በመጀመሪያ ፡ ለሥራ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ሁለተ ኛው ፡ ለመብል ፡ሲሆን ፡ ሦስተኛው ፡ ለዕረ ፍት፡ነው።

፳፩፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ ስለመዳን ፡ መርከብን ፡ ሲሠራ፡ የቃየል ፡ ልጆች ፡ ኖኅን ፡ አይተው ፡ ዘበቱበት ፡ እንዲህም፡ አሉ ፡ ይህ ፡ ሽማግሌ ፡ አብዷል ፡ ውኃዎች ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ራስ፡ ይወጣሉ፡እንዴት፡ይለናል።

፳፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኖኅ ፡ የአባታችን ፡ አዳምን ፡ ሥጋ ፡ ወሰደ ፡ ሤም ፡ ወርቁን ፡ ካም ፡ ከርቤ ውን ፡ ያፌት ፡ ዕጣኑን ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ መር ከብ፡አስገቡ።

፳፫፡ኖኅም፡ወደ፡መርከብ፡ገባ፡ሚስቱ፡ልጆቹና፡ የልጆቹ፡ሚስቶች፡ከጥፋት፡ውኃ፡ለመዳን ከርሱ፡ጋር፡ገቡ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ወእምእንስሳ፡ወአዕዋፍ፡ዘንጹሕ፡ሰብዓተ፡ ሰብዓተ ፡ ትባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ወእምንስሳ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ክልኤተ ፡ ክልኤተ፡ ተባዕተ፡ወአንስተ።

፳፭፡ ወእምዝ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ተሠጥቁ ፡ ኵሉ ፡ ቀላያት፡ወተርኅወ፡አስራበ፡ሰማይ፡ወኮነ፡ ዝናም፡ላዕለ፡ምድር፡፵ዕለተ፡ወ፵ሌሊተ፡ ወመልአ፡ማይ፡ወአልዓላ፡ለታቦት፡ወተለዓለት፡እምድር።

፳፮፡ ወፈድፋደ ፡ በዝኀ ፡ ጥቀ ፡ ማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር፡ ወከደነ ፡ ኵሎ ፡ አድባረ ፡ ነዋኃተ ፡ ዘመትሕተ ፡ ሰማይ ፡ ፲ወ፭ተ ፡ እመተ ፡ ተለዓለ ፡ መልዕልቶሙ ፡ ማይ ፡ ወሞተ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ወዘይትሐወስ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምነ፡ አዕዋፍ ፡ ወእም ፡ እንስሳ ፡ ወእምነ ፡ ኵሉ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ወኵሉ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው።

፳፯፡ ወተለዓለ ፡ ማይ ፡ መልዕልተ ፡ ምድር ፡ ፻ተ፡ ወ፶ ፡ ዕለተ ፡ ወተዘከሮ ፡ እግዚአብሔር፡ ለኖኅ፡ ወለኵሉ ፡ እንስሳ ፡ እለ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ ወአምጽአ ፡ ነፋሰ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወነትገ ፡ ማይ።

፳፰፡ ወተዐጽዉ ፡ አንቅዕተ ፡ ቀላይ ፡ ወአስራበ ፡ ሰማይኒ ፡ ተእኅዘ ፡ ወቆመ ፡ ዝናም ፡ እምሰማይ ፡ ወአኅዘ ፡ ይኅልቅ ፡ ማይ ፡ ወይሑር፡ እምነ ፡ ምድር ፡ ወእምድኅረ ፡ ምእት ፡ ወኃምሳ ፡ ዕለት ፡ ሐፀ ፡ ማይ።

፳፱፡ ወነበረት ፡ ይእቲ ፡ ታቦት ፡ በሳብዕ ፡ ወርኅ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ፡ ወአመ ፡ ፲ወ፯ ፡ ለጽልመት ፡ ላዕለ ፡ ደብረ ፡ አራራት።

፴፡ ማይሰ ፡ የሐጽጽ ፡ ወይነትግ ፡ እስከ ፡ ፲ቱ ፡ ወርኅ ፡ ወአመ ፡ ኮነ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ አውራኅ ፡ አመ ፡ ርእሰ ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ አስተርአዩ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ለአድባር።

፴፩፡ ወእምድኅረ ፡ ፵ ዕለት ፡ አርኃወ ፡ ኖኅ ፡ መስኮታ ፡ ለታቦት ፡ እንተ ፡ ገብረ ፡ ወፈነዎ፡ ለቋዕ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ እመ ፡ ነትገ ፡ ማይ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ ወሖረ ፡ ወኢገብአ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ኀልቀ ፡ ማይ ፡ እምነ ፡ ምድር።

፴፪፡ ወፈነዋ ፡ ለርግብ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ እመ ፡ ነትገ ፡ ማይ ፡ እምገጸ ፡

፳፬፡ ከንጹሐን ፡ እንስሳትና ፡ አዕዋፍ ፡ ተባትዕና ፡ እንስት ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ንጹሐን ፡ ካልሆኑ ፡ እንስሳትም ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሴትና፡ ወንድ ፡ አስገባ።

፳፭፡ ከዚህም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ምንጮች ፡ ሁሉ ፡ ተነደሉ ፡ የሰማይም ፡ መስኮት ፡ ተከፈተ ። በምድር ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ዝናም ፡ ሆነ ፡ ውኃውም ፡ ሞልቶ ፡ መርከቢቱን፡አንሳፈፋት፡ምድርንም፡ለቀቀች።

፳፮፡ ውኃውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ በዛ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ረጃጅም ፡ ተራራዎችን ፡ ሸፈነ ። ውኃውም ፡ በላያቸው ፡ ዐሥራ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ ከአዕዋፍ ፡ ከእንስሳ ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ የሚኖርና ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ሞተ።

፳፯፡ ውኃውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ቀን ፡ አየለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፡ አሰበው ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ እንስሶች ፡ ሁሉ ፡ ነፋስንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አመጣ ፡ ውኃውም ፡ ጐደለ።

፳፰፡ የቀላይ ፡ ምንጮች ፡ ተደፈኑ ፡ የሰማይም ፡ መስኮት ፡ ተዘጋ ፡ ከሰማይ ፡ የሚወርደውም፡ ዝናም ፡ ቆመ ፡ ውኃውም ፡ እያለቀ ፡ ከምድር፡ ይሸሽ ፡ ጀመረ ፡ ከመቶ ፡ ኃምሳ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ውኃው ፡ ጎደለ።

፳፱፡ መርከቢቱም ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥራ፡ ሁለተኛው ፡ ቀን ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛውም ፡ ሠርቀ ፡ ሌሊት ፡ በአራራት ፡ ተራራ ላይ ፡ አረፈች።

፴፡ ውኃው ፡ እስከ ፡ ዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ እየጎደለ ፡ ይሔድ ፡ ነበር ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ወርም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከወሩ ፡ በመጀመሪያው፡ ቀን ፡ የተራራዎች ፡ ራሶቻቸው ፡ ታዩ።

፴፩፡ ከአርባ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኖኅ ፡ የሠራውን ፡ የመርከቢቱን ፡ መስኮት ፡ ከፍቶ ፡ ውኃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ጎድሎ ፡ እንደሆነ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ቁራን ፡ ላከው ፡ ሔደ ፡ ግን ፡ ውኃው፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ አለቀ ፡ ድረስ ፡ አልተመለሰም።

፴፪፡ ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ውኃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምድር። ወኢረከበት ፡ ኀበ ፡ ተዓርፍ ፡ እገሪሃ ፡ ወገብአት ፡ ኀቤሁ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ እስመ ፡ ማይ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ገጸ ፡ ምድር ፡ ወሰፍሐ ፡ እዴሁ ፡ ወነሥአ ፡ ውስተ፡ ታቦት፡ ኀቤሁ።

፴፫፤ ወተዓገሠ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ ካዕበ ፡ ፈነዋ ፡ ለርግብ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ወገብአት ፡ ኀቤሁ ፡ ርግብ ፡ ፍና ፡ ሠርክ ፡ ወባቲ ፡ ውስተ ፡ አፉሃ ፡ ቈጽለ ፡ ዘይት ፡ ወአእመረ ፡ ኖኅ ፡ ከመ ፡ ነትገ ፡ ማይ ፡ እምነ ፡ ምድር።

፴፬፤ ወተዓገሠ ፡ ካዕበ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ ፈነዋ ፡ ለርግብ ፡ ወኢያገመት ፡ ገቢአ ፡ ኀቤሁ።

፴፭፤ ወአመ ፡ ኮነ ፡ ስድስተ ፡ ምእተ ፡ ወአሐደ ፡ ዓመተ ፡ ሕይወቱ ፡ ለኖኅ ፡ አመ ፡ ርእሰ ፡ ሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ቀዳማይ ፡ ኀልቀ ፡ ማይ ፡ እምድር ። ወበካልዕ ፡ ወርኅ ፡ አመ ፡ ፳ወ፯ ፡ ለጽልመት ፡ የብሰት ፡ ምድር።

፴፮፤ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኖኅ ፡ ፃእ ፡ እምነ፡ ታቦት ፡ አንተ ፡ ወብእሲትከ ፡ ወደቂቅከ ፡ ወአንስትያ ፡ ደቂቅከ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሀሎ ፡ ምስሌከ። ወወጽአ ፡ ኖኅ ፡ ወብእሲቱ፡ ወደቂቁ ፡ ወአንስትያ ፡ ደቂቁ ፡ ምስሌሁ ፡ ወኵሉ ፡እንስሳ።

፴፯፤ ወነደቀ ፡ ኖኅ ፡ ምሥዋዐ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወነሥአ ፡ እንስሳ ፡ ወእምነ ፡ አዕዋፍ ፡ ወእምኵሉ ፡ ዘንጹሕ ፡ ወአዕረገ ፡ ቍርባነ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወአጼነወ ፡ እግዚአብሔር፡ መዐዛ፡ ሠናየ ፡ ወይቤ ፡እግዚአብሔር ፡ ሐለይኩ ፡ ከመ ፡ ኢይድግም ፡ ረጊሞታ ፡ ለምድር፡ በእንተ፡ምግባሩ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡ እስመ ፡ ሥዑም ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ። እከይ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ እምንእሶሙ ፡ ወኢይደግም ፡ እንከ፡ አማስኖቶ፡ ለኵሉ፡ ዘሥጋ፡ ዘሕያው፡ በከመ፡ገበርኩ።

፴፰፤ ኵሎ ፡ መዋዕሊሃ ፡ ለምድር ፡ ዘርዕ ፡ ወማእረር ፡ ቍር ፡ ወሐፍ ፡ ወኃጋይ ፡ ወክረምት ፡ መዓልት ፡ ወሌሊት ፡ ኢይትኀደግ።

ጐድሎ ፡ እንደሆነ ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ርግብን ፡ ላካት ። እግርዋንም ፡ የምታሳርፊበት ፡ ቦታ፡ አላገኘችም ፡ ወደርሱ ፡ ወደ ፡ መርከብም ፡ ተመለሰች ፡ ውኃው ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ወደርሱ ፡ ወደመርከብ ፡ አስገባት።

፴፫፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ቆይቶ ፡ ዳግመኛ ፡ ምድርን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ርግብን ፡ ላካት ፡ ርግብም ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ ወደርሱ ፡ ተመለሰች ፡ በአፉዋም ፡ የዘይት ፡ ቅጠል ፡ ይዛ ፡ ነበር ፡ ኖኅም፡ ውኃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጐደለ ፡ ዐወቀ።

፴፬፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ቆይቶ ፡ ዳግመኛ ፡ ርግብን ፡ ላካት ፡ ደግማ ፡ ወደርሱ ፡ አልተመለሰችም።

፴፭፤ የኖኅም ፡ ዕድሜ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያው ፡ የወሩ፡ መባቻ ፡ ውኃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ተቋረጠ ፡ ኖኅም ፡ የሠራውን ፡ የመርከብ ፡ ድፍንት ፡ ገለጠ ። ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ ባደረገችበት ፡ በዐሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ቀን ፡ በሁለተኛው ፡ ወር ፡ ምድር ፡ ደረቀች።

፴፮፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፡ አንተ ፡ ሚስትህም ፡ ልጆችህም ፡ የልጆችህ ፡ ሚስቶችም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ከመርከብ ፡ ውጡ ፡ አለው። ኖኅም ፡ ወጣ ፡ ሚስቱ ፡ ልጆቹም ፡ የልጆቹም ፡ ሚስቶችም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ እንሳሳቱም ፡ ሁሉ ፡ ወጡ።

፴፯፤ ኖኅም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፡ ከእንስሳት ፡ ከአዕዋፍ ፡ ንጹሕ ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ። እግዚአብሔርም ፡ መልካም ፡ መዓዛን ፡ አሸተተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ክፋት ፡ ምድርን ፡ ሁለተኛ፡ እንዳላጠፋ ፡ ተናገርኩ ፡ በሰዎች ፡ ልቡና ፡ ክፋት ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጸንቶ ፡ ኑሮዋልና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳደረግሁት ፡ ሥጋ ፡ የለበሰውን ፡ በሕይወት ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዳግመኛ ፡ አላጠፋም።

፴፰፤ ምድር ፡ ፀንታ ፡ በምትኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ዘር ፡ መከር ፡ ቅዝቃዜና ፡ ሙቀት ፡ በጋና ፡ ክረምት ፡ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፤ ወባረኮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኖኅ ፡ ወለደቂቁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልዕዋ ፡ ለምድር ፡ ወኰንንዋ ፡ ወአቀውም ፡ ኪዳንየ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወኢይመውት፡ እንከ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ በማየ ፡ አይኅ።

፳፤ ቀስትየ ፡ እሠይም ፡ በደመና ፡ ወትከውን ፡ ተአምረ ፡ ለኪዳንየ፡ ማዕከሌየ፡ ወማዕከሌክሙ፡ ወማዕከለ ፡ ምድር።

፳፩፤ ወእምድኅረ ፡ አይኅ ፡ አኀዘ ፡ ኖኅ ፡ ይትገበራ ፡ ለምድር ፡ ወተከለ ፡ ዐፀደ ፡ ወይን ፡ ወሰትየ ፡ እምኔሁ ፡ ወሰክረ ፡ ወተዐርቀ ፡ በውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወርእዮ ፡ ካም ፡ አቡሁ ፡ ለከነአን ፡ ዕርቃነ ፡ አቡሆሙ ፡ ሠሐቀ ፡ ወወጽአ ፡ ወነገሮሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ አኃዊሁ ፡ በአፍኣ።

፳፪፤ ወነሥኡ ፡ ሴም ፡ ወያፌት ፡ ልብሰ ፡ ወወደዩ፡ ላዕለ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ዲበ ፡ ዘባናቲሆሙ ፡ ወሐሩ ፡ ድኅሪተ ፡ ወከደኑ ፡ ዕርቃነ ፡ አቡሆሙ ፡ ወገጾሙ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ አግብኡ ፡ ወኢርእዩ ፡ ዕርቃነ ፡ አቡሆሙ።

፳፫፤ ወሶበ ፡ ጽሕወ ፡ ኖኅ ፡ እምስካረ ፡ ወይኑ ፡ አእመረ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ቦቱ ፡ ወልዱ ፡ ዘይንእስ ፡ ወይቤ ፡ ኖኅ ፡ ርጉመ ፡ ለይኩን ፡ ከነአን ፡ ወገብረ ፡ ወነባሬ ፡ ይኩን ፡ ለአኃዊሁ ፡ ወይቤ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ለሴም ፡ ለያርሕብ ፡ ብሔሮ ፡ ለያፌት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይኅድር ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለሴም ፡ ወይኩን ፡ ከነአን ፡ ገብሮ።

፳፬፤ ወሐይወ ፡ ኖኅ ፡ እምድኅረ ፡ አይኅ ፡ ፫፻ወ፶ ፡ ዓመተ ፡ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለኖኅ ፡ ፱፻ተ፡ ወ፶ ፡ ዓመተ ። ወአዕረፈ ፡ በሰላም፡

፳፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አይቋረጥም።

፲፱፤ እግዚአብሔር ፡ ኖኅንና ፡ ልጆቹን ፡ ባረካቸው ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ ብዙ ፡ ተባዙ ፡ ምድርን ፡ ምሉዋት ፡ ግዟት ፡ ከእናንተ ፡ ጋር፡ ኪዳኔን ፡ አጸናለሁ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ በጥፋት ፡ ውኃ አይሞትም ።

፳፤ በናንተና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ በምድርም ፡ መካከል ፡ ለመሐላዬ ፡ ምልክት ፡ አድርጌ ፡ ቀስቴን ፡ በደመና ፡ ውስጥ ፡ አኖራለሁ።

፳፩፤ ከጥፋትም ፡ በኋላ ፡ ኖኅ ፡ ምድርን ፡ ይቆፍራት ፡ ያርሳትም ፡ ጀመር ፡ የወይን ፡ ተክልን፡ ተከለ ፡ ወይን ፡ ጠጥቶም ፡ ሰክሮ ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ተራቈተ ፡ የከነአን ፡ አባት ፡ ካም ፡ የአባታቸውን ፡ ዕርቃን ፡ አይቶ ፡ ሳቀ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥቶም ፡ ለሁለቱ ፡ ወንድሞቹ ፡ ነገራቸው።

፳፪፤ ያፌትና ፡ ሴም ፡ ልብስ ፡ ወስደው ፡ ሁለቱም ፡ በትከሻቸው ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፡ የኋሊት፡ ሒደው ፡ የአባታቸውን ፡ ዕርቃን ፡ ሸፈኑ፡ ፊታቸውን ፡ ወደኋላ ፡ አዞሩ ፡ የአባታቸውንም ፡ ዕርቃን ፡ አላዩም።

፳፫፤ ኖኅም ፡ ከወይኑ ፡ ስካር ፡ በነቃ ፡ ጊዜ ፡ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ያደረገበትን ፡ ሁሉ ፡ ዐወቀ ፡ ኖኅም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ከነአን ፡ የተረገመ ፡ ይሁን ፡ ለወንድሞቹም ፡ ተገዥ ፡ አገልጋይ፡ ይሁን ። የሴም ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመስገን ፡ እግዚአብሔርም፡ የያፌትን ፡ አገር፡ ያስፋ ። በሴም ፡ ቤትም ፡ ይደር ፡ ከነአንም ፡ አገልጋይ ፡ ይሁን።

፳፬፤ ኖኅም ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መቶ፡ ኃምሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ የኖኅም ፡ መላ ፡ ዕድሜው ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ኃምሳ ፡ ሆነ ፡ በሰላምም ፡ አረፈ።

፳፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለኖኅ ፡ በሕቁ ። ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወደቂቁ ። በገቢረ ፡ ታቦት ፡ ላዕሌሁ ፡ እለ ፡ ተሣለቁ ። በዝናመ ፡ ድምሳሴ ፡ ወበማየ ፡ አይኅ ፡ ኀልቁ ። ውእቱሰ ፡ አምሠጠ ፡ በጽድቁ።

፳፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ተዝካረ ፡ ዕርገቱ ፡ ለኤልያስ ፡ ነቢይ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ በሠ

፳፮፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ነቢዩ ፡ ኤልያስ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በሥጋ ፡ በእሳት ፡ ሠረገላ ፡ ወደ፡

www.ethiopianorthodox.org

ረገላ ፡ እሳት ፡ እኀዘ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡
በሥጋ።
፴፯፤ ወለዝንቱ ፡ ነቢይ ፡ ቀናኢ ፡ ለፈጣሪሁ ፡
ኮነት ፡ ነፍሱ ፡ ትፃሙ ፡ ለለዕለት ፡ በእንተ ፡
ምግባራቲሆሙ ፡ ለንጉሥ ፡ አክአብ ፡ ወስ
ቴርርት ፡ ብእሲቱ ፡ ኤልዛቤል ፡ ወእምዝ ፡
ተቆጥዓት ፡ ነፍሱ ፡ ወይቤሎ ፡ ለአክዓብ ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ኃይል ፡
ወአምላከ ፡ እስራኤል ፡ ዘቆምኩ ፡ ቅድሜሁ፡
ከመ ፡ ኢይረድ ፡ ዝናም ፡ ወጠል ፡ በእሉ ፡
ዓመታት ፡ ዘእንበለ ፡ በቃለ ፡ አፉየ።

፴፰፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ኤልያስ ፡
ቴስብያዊ ፡ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ እምዝየ ፡ መን
ገለ ፡ ጽባሕ ፡ ወተኀባእ ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡
ኮራት ፡ ዘመንገለ ፡ ገጸ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወስተይ ፡
ማየ ፡ እምውእቱ ፡ ፈለግ ፡ ወእኤዝዞሙ ፡
ለቋዓት ፡ ይሴስዩከ።

፴፱፤ ወገብረ ፡ ኤልያስ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ፡ እግዚ
አብሕር ፡ ወሖረ ፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡
ኮራት ፡ ወቋዓት ፡ ያመጽኡ ፡ ሎቱ ፡ በአፈ ፡
ጽባሕ ፡ ኅብስተ ፡ ወፍና ፡ ሠርክ ፡ ሥጋ ፡
ወእምውእቱ ፡ ፈለግ ፡ ይሰቲ ፡ ማየ።
፵፤ ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ የብሰ ፡
ውእቱ ፡ ፈለግ ፡ ወዝናምኒ ፡ ኢዘንመ ፡ ውስተ፡
ምድር ፡ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡
ኤልያስ ፡ ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡
ውስተ፡ ስራጵታ ፡ ዘሲዶና ፡ ወንበር ፡ ህየ ፡
ወናሁ ፡ አዘዝኩ ፡ በህየ ፡ ትሴሲከ ፡ ብእሲት ፡
መበለት።
፵፩፤ ወተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ስራጵታ ፡ ወበጽሐ ፡
ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ሀገር ፡ ወረከበ ፡ በህየ ፡ ብእ
ሲተ ፡ መበለተ ፡ እንዘ ፡ ተሐጥብ ፡ ዕፀወ ፡
ወጸውዓ ፡ እምድኅሬሃ ፡ ኤልያስ ፡ ወይቤላ ፡
አምጽኢ ፡ ሊተ ፡ ሕቀ ፡ ማየ ፡ በግምዔ ፡
ወእስተይ ፡ ወሖረት ፡ ታምጽእ ፡ ወጸውዓ ፡
እምድኅሬሃ ፡ ወይቤላ ፡ ተማልዒ ፡ ሊተ ፡
ምስሌኪ ፡ ፍተ ፡ ኅብስት ፡ በእደኪ።

፵፪፤ ወትቤሎ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ሕያው ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አምላክከ ፡ ከመ ፡ አልብየ ፡ እክል፡
እንበለ ፡ ምልአ ፡ ሕፍን ፡ ሐሪፅ ፡ ውስተ ፡
ቀሱት ፡ ወኅዳጥ ፡ ቅብዕ ፡ ውስተ ፡ ልጕነት ፡

ሰማይ ፡ ያረገበት ፡ የመታሰቢያው ፡ ቀን ፡
ሆነ።
፴፯፤ ለፈጣሪው ፡ ቀናተኛ ፡ የሆነ ፡ የዚህም ፡
ነቢይ ፡ በንጉሡ ፡ በአክአብና ፡ አስጸያፊ ፡
በሆነች ፡ በሚስቱ ፡ በኤልዛቤል ፡ ስለ ፡ ክፉ፡
ሥራቸው ፡ ሰውነቱ ፡ በየዕለቱ ፡ ትደክም ፡
ነበር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መንፈሱ ፡ ተበሳ
ጨች ፡ አክአብንም፡ በእነዚህ ፡ ዓመታት ፡
ከአፌ ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ ዝናብና ፡ ጠል ፡
እንዳይወርድ ፡ በፊቱ ፡ የቆምኩ ፡ የእስራ
ኤልና ፡ የመላእክት ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ሕያው ፡ ነው ፡ አለው ።
፴፰፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያ
ዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጥቶ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ፡
ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሒድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አው
ራጃ ፡ ባለች ፡ በኮራት ፡ ከዚያ ፡ ወንዝ ፡
ተሠወር ፡ ከዚያም ፡ ወንዝ ፡ ውኃን ፡ ጠጣ ፡
በዚያም ፡ ይመግቡህ ፡ ዘንድ ፡ ቁራዎችን ፡
አዛቸዋለሁ ፡ አለው።
፴፱፤ ኤልያስም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው፡
አደረገ ፡ ሒዶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ አንጻር ፡ ባለ፡
በኮራት ፡ ወንዝ ፡ ተቀመጠ ። ቁራዎችም ፡
ጧት ፡ ዳቦን ፡ ማታ ፡ ሥጋን ፡ ያመጡለት ፡
ነበር ፡ ከዚያም ፡ ወንዝ ፡ ውኃን ፡ ይጠጣል።
፵፤ ከብዙ ፡ ወራትም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ወንዝ ፡ ደረቀ ፡
ዝናብም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አልዘነበም ፡ የእግ
ዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ፡
ተነሥተህ ፡ የሲዶና ፡ ክፍል ፡ ወደምትሆን ፡
ወደ ፡ ስራጵታ ፡ ሒደህ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጥ ፡
ድኃ ፡ ሴት ፡ በዚያ ፡ ትመግብህ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ፡
አዝዣለሁ ፡ አለው።
፵፩፤ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ስራጵታ ፡ ሒዶ ፡ ወደ ፡
አገር ፡ አደባባይ ፡ መግቢያ ፡ ሲደርስ ፡
በዚያ ፡ ዕንጨት ፡ ስትለቅም ፡ አንዲት ፡
ድኃ ፡ ሴትን ፡ አገኘ ፡ ኤልያስ ፡ በኋላዋ ፡
ቁሞ ፡ ጠርቶ ፡ ጥቂት፡ ውኃ፡ በማሰሮ፡
አምጭልኝ፡ ልጠጣ፡ አላት ። እሷም ፡
ልታመጣ ፡ ሔደች ፡ ዳግመኛ ፡ ከኋላዋ ፡
ጠርቶ ፡ እግረ ፡ መንገድሽን ፡ በእጅሽ ፡
ቁራሽ ፡ እንጀራን ፡ አምጭልኝ ፡ አላት ።
፵፪፤ ያችም ፡ ሴት ፡ በማድጋ ፡ካለ ፡ እፍኝ ፡ ሙሉ፡
ዱቄት ፡ በማሰሮም ፡ ካለ ፡ ከጥቂት ፡ ዘይት ፡
በቀር ፡ እህል ፡ እንደሌለኝ ፡ ፈጣሪህ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ። እነሆም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወናሁ ፡ አስተጋብእ ፡ ክልኤተ ፡ ዕፀወ ፡ ወአ
ሐውር ፡ ወእገብር ፡ ለከ ፡ ወለደቂቅየ ፡ ወንበ
ልዕ ፡ ወንመውት።
፲፫፡ ወይቤላ ፡ ኤልያስ ፡ ተአመኒ ፡ በእግዚአብሔር፡
ወሑሪ ፡ ወግበሪ ፡ በከመ ፡ ትቤሊ ፡ ወባሕቱ፡
ሊተ ፡ ቅድሚ ፡ ግበሪ ፡ ንስቲተ ፡ ዳፍንተ ፡
እምውስቴቱ ፡ ወአምጽኢ ፡ ሊተ ፡ ለኪሰ ፡
ወለወልድኪ ፡ ትገብሪ ፡ ድኅረ ። እስመ ፡
ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀሡትኪኒ ፡
እንተ ፡ ሐሪጽ ፡ ኢተኀልቅ ፡ ወልጕንትኪኒ ፡
እንተ ፡ ቅብዕ ፡ ኢተኀልቅ ፡ እስከ ፡ ይሁብ ፡
እግዚአብሔር ፡ ዝናመ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡
ወሖረት ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ወገብረት ፡
ወበልዑ ፡ ውእቱ ፡ ወይእቲ ፡ ወወልዳ።
፲፬፡ ወእምድኅረዝ ፡ ደወየ ፡ ወልዳ ፡ ለይእቲ ፡
ብእሲት ፡ ባዕልተ ፡ ቤት ፡ ወከብደ ፡ ደዌሁ፡
እስከ ፡ ወጽአት ፡ ነፍሱ ፡ እምላዕሌሁ ፡ ወት
ቤሎ ፡ ለኤልያስ ፡ ሚ ፡ ሊተ ፡ ወሚ ፡ ለከ ፡
ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጻእከ ፡ ኀቤየ፡
ከመ ፡ ታዘክር ፡ ኃጢአትየ ፡ ወይሙት ፡ ወል
ድየ።
፲፭፡ ወይቤላ ፡ ኤልያስ ፡ ለይእቲ ፡ ብእሲት ፡
ሀብኒዮ ፡ ለወልድኪ ፡ ወነሥኦ ፡ እምሕፅና ፡
ወአዕረጎ ፡ ውስተ ፡ ጽርሕ ፡ ኀበ ፡ የኀድር ፡
ውእቱ ፡ ወአስከቦ ፡ ዲበ ፡ ዐራቱ ፡ ወጸርሐ ፡
ኤልያስ ፡ ወይቤ ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡
ስምዓ ፡ ለዛቲ ፡ መበለት ፡ እስመ ፡ አነሁ ፡
ኀደርኩ ፡ ኀቤሃ ፡ ለዛቲ ፡ መበለት ፡ አሕ
ሰምከ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወቀተልከ ፡ ወልዳ ።
፲፮፡ ወነፍሐ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ሠልሰ ፡
ጊዜያተ፡ ወጸውዖ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወይቤ፡
እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ትግባእ ፡ ነፍሱ፡
ለዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ላዕሌሁ ። ወሰምዐ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ቃሎ ፡ ለኤልያስ ፡ ወገብአት ፡
ነፍሱ ፡ ለውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ላዕሌሁ ፡ ወሐይወ።
ወተብህለ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ከመ ፡
ውእቱ ፡ ዮናስ ፡ ነቢይ።
፲፯፡ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኤልያስ፡
ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ አስተርእዮ ፡ ለአክአብ ፡
ወእሁብ ፡ ዝናመ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወሖረ ፡
ኤልያስ ፡ ኀበ ፡ አክአብ ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡
አክአብ ፡ ለኤልያስ ፡ ይቤሎ ፡ አንተኑ ፡ ዘት
ገፈትዖሙ ፡ ለእስራኤል ። ወይቤሎ ፡ ኤል

ጥቂት ፡ እንጨትን ፡ እለቅማለሁ ፡ ሔጄም ፡
ለልጄና ፡ ላንተ ፡ አዘጋጃለሁ ፡ በልተነውም፡
እንሞታለን ፡ አለችው።
፲፫፡ ኤልያስም፡ ፡እግዚአብሔር፡እመኚ፡ ሒደሽ፡
እንዳልሽ ፡ አድርጊ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለእኔ ፡ አስ
ቀድመሽ ፡ ትንሽ ፡ አምባሻ ፡ ጋግረሽ ፡ አም
ጭልኝ ፡ ለልጅሽና ፡ ላንቺ ፡ ግን ፡ ኋላ ፡
ታደርጊያለሽ ፡ አላት ። እግዚአብሔር ፡እን
ዲህ ፡ ብሏልና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብን ፡
እስቲአዘንብ ፡ ድረስ ፡ በማድጋሽ ፡ ያለ ፡
ዱቄትሽ ፡ በማሰሮሽም ፡ ያለች ፡ ዘይትሽ ፡
አታልቅም ፡ አላት ። ያቺም ፡ ሴት ፡ ሒዳ ፡
አዘጋጀች ፡ እሷና ፡ እሱ ፡ ልጅዋም ፡ በሉ።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የባለቤቷ ፡ የዚያች ፡ ሴት ፡
ልጅ ፡ ታመመ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ እስከ
ምትለይ ፡ በሽታው ፡ ጸናበት ። ያቺም ፡ ሴት፡
ኤልያስን ፡ ኃጢአቴን ፡ አዘክረህ ፡ ልጄ ፡
ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የመጣህ ፡ ነቢየ ፡
እግዚአበሔር ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ምን ፡ አለኝ ፡
አንተስ ፡ ከእኔ ፡ ምን ፡ አለህ ፡ አለችው።
፲፭፡ ኤልያስም ፡ ያንን ፡ ልጅሽን ፡ ስጪኝ ፡ ብሎ፡
ከእቅፍዋ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ እሱ ፡ ወደሚያ
ድርበት ፡ ሰገነት ፡ አውጥቶ ፡ በአልጋው ፡
ላይ ፡ አስተኛው ። ኤልያስም ፡ ወዮልኝ ፡
አቤቱ ፡ እኔ ፡ በዚች ፡ ድኃ ፡ ሴት ፡ ዘንድ ፡
አድሬአለሁና ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ተቈጥተህ ፡
ልጅዋን ፡ ገደልክባት ፡ አቤቱ ፡ የዚችን ፡
ሴት ፡ ጩኸቷን ፡ ስማት ፡ አለ።
፲፮፡ በዚያም ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እፍ ፡
አለበት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አቤቱ ፡ ፈጣ
ሪዬ ፡ የዚህ ፡ ልጅ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ጋር ፡
ትዋሐድ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ የኤልያስን ፡ ልመናውን ፡ ሰማው ፡
የዚያም ፡ ልጅ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ጋር ፡
ተዋሕዳ ፡ ዳነ።ይህም ፡ ሕፃን ፡ ነቢይ ፡
ዮናስ፡ እንደሆነ ፡ ይነገራል።

፲፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኤልያስን ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናምን ፡ አዝንማለሁና ፡
ሒደህ ፡ ለአክአብ ፡ ተገለጥለት ፡ ብሎ ፡ አዘ
ዘው ፡ ኤልያስም ፡ ወደ ፡ አክአብ ፡ ሔደ ።
አክአብም ፡ ኤልያስን ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ እስ
ራኤልን ፡ የምትገለባብጣቸው ፡ አንተ፡

www.ethiopianorthodox.org

ያስ ፡ አንሰ ፡ ኢይገፈትዖሙ ፡ ለእስራኤል ፡
አላ ፡ አንተ ፡ ወቤተ ፡ አቡከ ፡ እለ ፡ ኀደ
ግምዎ፡ለእግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፡ ወሖ
ርክሙ ፡ ወአምለክሙ ፡ አማልክተ ፡ በዓ
ሊም።

፲፰፡ ወይእዜኒ ፡ ለአክ ፡ ኀበ ፡ እስራኤል ፡
ወአስተጋብኦሙ ፡ ኀቤየ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡
ቀርሜሎስ ፡ ወለነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ አርባዕቱ፡
ምእት ፡ ወኃምሳ ፡ ወለነቢያተ ፡ ምሕራ
ማተ ፡ አዕዋም ፡ እለ ፡ ይሴሰዩ ፡ እማዕዳ ፡
ለኤልዛቤል ፡ አርባዕቱ ፡ ምእት።

፲፱፡ ወለአከ ፡ አክአብ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ እስራኤል ፡
ወአስተጋብኦሙ፡ ለኵሎሙ፡ ውስተ፡ ደብረ፡
ቀርሜሎስ፡ ወቀርበ፡ ኤልያስ፡ ኀበ፡ ኵሎሙ፡
ወይቤሎሙ ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ተሐነክሱ ፡
በክልኤሆን ፡ ጌጋያቲክሙ ፡ ለእመ ፡እግዚአ
ብሔር ፡ አምላክ ፡ ኪያሁ ፡ አምልኩ ፡ ወለ
እመ ፡ ቤል ፡ አምላክ ፡ ኪያሁ ፡ ትልዉ ፡
ወአልቦ ፡ ቃል ፡ ዘአውሥእዎ።

፳፡ ወይቤሎሙ ፡ ኤልያስ ፡ ለሕዝብ ፡ አነ ፡
ባሕቲትየ ፡ ተረፍኩ ፡ ነቢየ ፡እግዚአብሔር፡
ወናሁ ፡ ነቢያተ ፡ በዓል ፡ አርባዕቱ፡ ምእት ፡
ወኃምሳ ፡ ብእሲ ፡ ወነቢያተ ፡ ምሕራማተ ፡
ዖም ፡ አራባዕቱ ፡ ምእት ፡ የሀቡነ ፡ ክልኤተ ፡
አልሕምተ ፡ ወይኅረዩ ፡ ሎሙ ፡ እሙንቱ ፡
አሐደ ፡ ወይጥብሕዎ ፡ በበመሌሊቱ ፡
ወይደይዎ፡ መልዕልተ ፡ዕፀው ፡ ወኢያንድዱ፡
እሳተ ። ወአነኒ ፡ እገብር ፡ ካልአ ፡ ላሕመ ፡
ወኢይወዲ ፡ እሳተ ፡ ወይጸውዑ ፡ እሙንቱኒ ፡
አማልክቲሆሙ ፡ ወአነኒ፡እጼውዕ ፡ ስመ ፡እግ
ዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ዘፈ
ነወ፡ እሳተ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወአውሥእዎ ፡
ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወይቤልዎ ፡ ሠናየ ፡ ቃለ ፡
ነበብከ።

፳፩፡ ወእሙንቱ ፡ አቀረቡ ፡ መቅድመ ፡ መሥ
ዋዕተ ፡ ውእተ ፡ ላሕመ ፡ ዘኀረዩ ፡ ለአማልክ
ቲሆሙ ፡ ወባሕቱ ፡ አልቦ ፡ ዘተመጠዎሙ ።
ወሶበ ፡ አቅረበ ፡ ኤልያስ ፡ መሥዋዕቶ ፡ ወረ
ደት ፡ እሳት ፡ እምሰማይ ፡ እምኀበ ፡
ብሔር፡ ወበልዐት፡መሥዋዕቶ፡ወዕፀዊሁኒ፡
ወማዮኒ ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ፡ ወዕበኒሁኒ፡
ወለሐሰት፡መሬቶሂ።

ነህን፡ አለው ። ኤልያስም ፡ ፈጣሪያችሁ፡
እግዚአብሔርን፡ የተዋችሁት፡ ሒዳችሁ ፡
ጣዖታትን ፡ ያመለካችሁ ፡ አንተና ፡ የአባ
ትህ ፡ ወገኖች ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡
እስራኤልን ፡ አልገለባብጣቸውም ፡ አለው።

፲፰፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ እስሬኤል ፡ ልከህ ፡ ከእኔ ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰብስ
ባቸው ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ኃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡
ነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ከኤልዘቤል ፡ ማዕድ ፡
የሚመገቡ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ በዛፉ፡
መስገጃ ፡ የተሾሙ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትንም ፡
ሰብስባቸው ፡ አለው።

፲፱፡ አክአብም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ልኮ ፡
ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰበ
ሰባቸው ። ኤልያስም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡
ሁሉ ፡ ቀርቦ ፡እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪ ፡ ከሆነ፡
እርሱን ፡ አምልኩ ፡ ቤል ፡ አምላክ ፡ ከሆነ ፡
እርሱን ፡ ተከተሉ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡
በሁለቱ ፡ ስሕተቶቻችሁ ፡ ትጠራጠራላችሁ፡
አላቸው።

፳፡ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡የእግዚአብሔር፡ ነቢይ፡
እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቻለሁ ፡ የጣዖቱ፡ ነቢያት ፡
አራት ፡ መቶ ፡ ሃምሣ ፡ በዛፉም ፡ መስገጃ ፡
የተሾሙት ፡ እነሆ ፡ አራት ፡ መቶ፡ ናቸው ።
ሁለት ፡ ወይፈኖችንም ፡ ይስጡን ፡ እነርሳ
ቸውም ፡ አንዱን ፡ መርጠው ፡ አርደው ፡
በየብልቱ ፡ አወራርደው ፡ በዕንጨቶቹ ፡ ላይ፡
ይከምሩት ፡ እሳትን ፡ ግን ፡ አያንድዱ ።እኔም፡
ሁለተኛውን ፡ ወይፈን ፡ አርዳለሁ ፡ እሳ
ትንም፡ አላነድም ፡ እነርሳቸው ፡ የጣዖቶቻ
ቸውን ፡ ስም ፡ ይጥሩ ፡ እኔም ፡የፈጣሪዬን ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጠራለሁ ፡ ከእር
ሳቸው ፡ እሳትን ፡ ከሰማይ፡ ያወረደ ፡ ፈጣሪ ፡
ነው ፡ አላቸው ፡ ሕዝቡም ፡ መልካም፡ ቃል ፡
ተናገርክ፡ብለው፡መለሱለት።

፳፩፡ እነርሱም ፡ የመረጡትን ፡ በሬ፡ ለአማልክቶ
ቻቸው ፡ አስቀድመው ፡ መሥዋትነትን ፡
አቀረቡ ፡ ግን ፡ የተቀበላቸው ፡ የለም ፡ ኤል
ያስም ፡ መሥዋዕቱን ፡ በአቀረበ ፡ ጊዜ፡ከእግ
ዚአብሔር፡ ታዝዛ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ፡
መሥዋዕቱን ፡ ዕንጨቱን ፡ በጕድጓዱ፡ ያለ ፡
ውኃውንም ፡ አቃጠለቸው፡ መሬቱንም ፡
ላሰችው።

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፡ ወይቤሎሙ፡ ኤልያስ፡ ለሕዝብ፡ አኀዝዎሙ፡ ለነቢያተ፡ በዓል፡ ወአልቦ፡ ዘያመሥጠክሙ፡ እምኔሆሙ፡ ወአኀዝዎሙ፡ ለነቢያተ፡ ሐሰት፡ ወአውረዶሙ ፡ ኤልያስ ፡ ውስተ ፡ ፈለገ ፡ ቂሶን፡ ወረገዞሙ፡ በህየ።

፳፫፡ ወእምዝ ፡ ዘንመ ፡ ሎሙ ፡ ዝናም ፡ ወተፈሥሑ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ስቡሕ።

፳፬፡ ወነገራ ፡ አክአብ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ብእሲቱ ፡ ኵሎ፡ ዘገብረ፡ ኤልያስ፡ ወዘከመ፡ ቀተሎሙ፡ ለነቢያተ ፡ ኀፍረት ፡ ወለአከት፡ ኤልዛቤል ፡ ኀበ፡ ኤልያስ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ እመ ፡ አኮ ፡ አንተ ፡ ኤልያስ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ አነ፡ ኤልዛቤል፡ ከመዝ፡ ለይረስዩኒ፡ አማልክትየ፡ ወከመዝ ፡ ለይቅትሉኒ ፡ ከመዝ ፡ ጌሠመ ፡ ዘ ፡ ጊዜ ፡ እሬስያ ፡ ለነፍስከ ፡ ከመ ፡ ነፍሰ ፡ ፩ እምኔሆሙ።

፳፭፡ ወበእንተዝ ፡ ኀዘነ ፡ ኤልያስ ፡ ፈድፋደ ፡ ወይቤ፡ እግዚኦ፡ ነቢያቲከኒ፡ ቀተሉ፡ ምሥዋዒከኒ፡ ነሠቱ፡ ወአነ፡ ባሕቲትየ፡ ተረፍኩ፡ ወየኃሥሡ፡ ይቅትልዋ፡ ለነፍስየ።

፳፮፡ ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር ኢትፍራህ፡ እስመ፡ ሊተ፡ አትረፍኩ፡ ፸፻ተ፡ ዕደወ፡ ዘኢሰገዱ፡ ለበዓል፡ ወለከሰ፡ መኑሂ፡ ኢይክል፡ ነሢአ፡ ነፍስከ፡ ወባሕቱ፡ አነ፡ አዐርገከ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ እንዘ፡ ሕያው፡ አንተ፡ በሥጋከ።

፳፯፡ ወእምድኅረ ፡ ሞተ ፡ አክአብ ፡ አጽረሩ ፡ ሞዓብ፡ ወደወየ፡ አካዝያስ፡ ወሰከበ፡ ውስተ፡ ጽርሑ ፡ በሰማርያ ፡ ወለአከ ፡ ሐዋርያተ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ ተሰአሉ ፡ ሊተ ፡ ኀበ ፡ በዓለ፡ ጽንጽንያ፡ አምላከ፡ አቃሮን፡ ለእመ፡ አሐዩ ፡ እምዛቲ ፡ ደዌየ ፡ ወሐሩ ፡ ይሰአሉ ፡ ሎቱ።

፳፰፡ ወረከቦሙ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይ ፡ ለላእካን ፡ ወይቤሎሙ ፡ በልዎ ፡ ለንጉሥክሙ ፡ ዑቅ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ትመውት ፡ በዝንቱ ፡ ደዌ ፡ ወአእመረ፡ ንጉሥ ፡ ከመ፡ ኤልያስ ፡ ውእቱ። ወፈነወ ፡ መስፍነ ፡ ኀቤሁ ፡ ምስለ ፡ ኃምሳ ፡ ሐራ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ወሐሩ ፡ ወረከብዎ ፡ ይነብር፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ ወይቤሎ ፡

፳፪፡ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ጣዖቱን ፡ የሚያገለግሉ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ያዝዋቸው፡ ከእነርሱም፡ የሚያመልጣችሁ፡ አይኑር ፡ አላቸው ፡ ሕዝቡም ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ያዙ ፡ ኤልያስም ፡ ቂሶን፡ ወደ ሚባል፡ ወንዝ፡ አውርዶ፡ እየወጋ፡ ጣላቸው።

፳፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዝናብ ፡ ዘነበላቸው ፡ ደስ፡ ብሏቸውም ፡ ምስጉን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት።

፳፬፡ አክአብም ፡ ለሚስቱ ፡ ኤልዛቤል ፡ ኤልያስ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ አሳፋሪዎች ፡ ነቢያቶ ችንም ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ እንደ ፡ ገደላቸው ፡ ነገራት ፡ ባልኖርባት ፡ አንተ ፡ ኤልያስ ፡ ኑረህባት ፡ አንተ ፡ ባትኖርባት ፡ እኔ ፡ ኤልዛቤል ፡ ኑሬባት ፡ ነገ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሰውነ ትህን ፡ ከነሳቸው ፡ እንዳዱ ፡ ሰውነት፡ ባላደ ርጋት ፡ የያዘችውን ፡ ጥላ ፡ አማልክቶቼ ፡ እንዲህ፡ ይጣሉኝ ፡ እንዲህም ፡ ይግደሉኝ ፡ ብላ፡ ወደ፡ ኤልያስ፡ ላከች።

፳፭፡ ስለዚህም፡ ኤልያስ፡ እጅግ፡ አዝኖ፡ እንዲህ፡ አለ፡ አቤቱ ፡ ነቢያቶችህን ፡ ገደሉ፡ መሠዊያ ዎችህንም ፡ አፈረሱ ፡ እኔም፡ ብቻዬን ፡ ቀር ቻለሁ፡ ነፍሴንም፡ ሊገድሏት፡ ይሿታል።

፳፮፡ እግዚአብሔርም፡ ለጣዖት ፡ ያልሰገዱ ፡ ለኔ፡ ሰባት ፡ ሽህ ፡ ሰዎችን ፡ አስቀርቻለሁና ፡ አት ፍራ ፡ ያንተንም ፡ ነፍስ ፡ ማንም ፡ ሊወስዳት ፡ የሚችል ፡ የለም ። ነገር፡ ግን ፡ በሥጋህ ፡ ሕያው ፡ እንደሆንክ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አወጣ ሃለሁ፡ አለው።

፳፯፡ አክአብም፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሞአብ ፡ ሰዎች፡ አመፁ፡ አካዝያስም ፡ ታሞ ፡ በሰማርያ ፡ ባለ፡ እልፍኙ ፡ ተኛ ፡ ከዚች ፡ በሽታዬ ፡ እድን ፡ እሞትም ፡ እንደሆነ ፡ ወደ፡ አቃሮን ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ዝንቡ ፡ ካህን፡ ሔዳችሁ ፡ ጠይቁልኝ ፡ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ፡ እነርሱም ፡ ሊጠ ይቁለት ፡ ሔዱ።

፳፰፡ ነቢዩ ፡ ኤልያስም ፡ መልክተኞቹን ፡ በዚህ ፡ ደዌ፡ እንደምትሞት፡ ዕውቅ፡ ብላችሁ፡ ለንጉ ሣችሁ ፡ ንገሩት ፡ አላቸው ። ንጉሡም፡ ኤል ያስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐውቆ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ፡ ከኃምሳ ፡ ወታደሮች ፡ ጋር፡ የኃምሣ ፡ አለቃውን ፡ ላከ ፡ ሒደውም ፡ በተራራው ፡ ራስ፡ ተቀምጦ፡ አገኙት፡ አለቃውም፡ ነቢየ፡

www.ethiopianorthodox.org

መስፍኖሙ፡ብእሴ፡እግዚአብሔር፡ንጉሥ፡
ይጼውዓከ፡ ነዓ ፡ ረድ ፡ ፍጡነ ፡ ወይቤሎ ፡
ለእመ ፡ ኮንኩ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡
ትረድ፡እሳት፡ወታውዒከ፡ምስለ፡እሊአከ፡
ወወረደት፡እሳት፡ወበልዓቶሙ።

፳፱፤ ወደገመ ፡ ንጉሥ ፡ ኀቤሁ ፡ ፈነወ ፡ ፶ ብእሴ፡
ምስለ፡መስፍኖሙ፡ወጸውዖ፡መስፍኖሙ፡
ወይቤሎ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይጼውዓከ፡ንጉሥ፡ፍጡነ፡ረድ። ወይቤሎ፡
ኤልያስ፡እመሰ፡ብእሴ፡እግዚአብሔር፡ አነ፡
ትረድ፡እሳት፡እምሰማይ፡ትብላዕከ፡ለከ፡
ወለኃምሳ፡እለ፡ምስሌከ፡ወወረደት፡እሳት፡
ወበልዐቶሙ።

፴፤ ወእምዝ፡ፈነወ፡ንጉሥ፡ሣልሳየ፡መስፍነ፡፶
ውእቱሰ፡መጽአ፡በትሕትና፡ኀበ፡ነቢይ፡
ኤልያስ፡ወሰገደ፡ሎቱ፡ወይቤሎ፡ብእሴ፡እግ
ዚአብሔር፡ ገነይኩ፡ለከ፡ትክበር፡ነፍስየ፡
ወነፍሶሙ፡ለእሉ፡አግብርቲከ፡በቅድመ፡
አእይንቲከ፡ወተንሥአ፡ኤልያስ። ወወረደ፡
ምስሌሆሙ፡ወሖረ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወተናገሮ፡
ወይቤሎ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ እፎ፡
ለአከ ፡ ኀበ ፡ በዓለ ፡ ጽንጽንያ ፡ አምላከ ፡
አቃሮን ፡ ኢ.ሀሎኑ ፡ አምላከ ፡ እሥራኤል ፡
ከመ፡ ትሰአል ፡ ቃለ፡ አኮኬ ፡ ከማሁ ፡ እምስ
ካብከ፡ዘዲቤሁ፡ሰከብከ፡ኢትትነሣእ፡አላ፡
ሞተ፡ትመውት፡በህየ፡ወሞተ፡በጊዜሃ።

፴፩፤ ወእምዝ ፡ አመ ፡ ያዐርጎ ፡እግዚአብሔር ፡
ለኤልያስ፡ውስተ፡ሰማይ፡ሖሩ፡ኤልያስ፡
ወኤልሳዕ፡እምነ፡ገልገላ፡ወበጽሑ፡ኀበ፡
ዮርዳኖስ፡ ወነሥአ ፡ ኤልያስ ፡ ሐሜለቶ ፡
ወጠወማ፡ወዘበጠ፡ባቲ፡ማየ፡ዮርዳኖስ፡
ወቆመ ፡ ማይ፡ እምለፌኒ ፡ ወእምለፌኒ ፡
ወኀለፉ ፡ ክልኤሆሙ ፡ በየብስ ፡ ወቆሙ ፡
በድወ፡ወጺአሙ።

፴፪፤ ወይቤሎ ፡ ኤልያስ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ሰአለኒ ፡
ዘትፈቅድ፡እግበር፡ለከ፡ዘእንበለ፡እዕርግ፡
እምኀቤከ፡ወይቤሎ፡ኤልሳዕ፡ለኤልያስ፡

እግዚአብሔር፡ ሆይ ፡ ንጉሥ ፡ ይጠራሃል ፡
ፈጥነህ ፡ ውረድ ፡ ና ፡ አለው ፡ ኤልያስም ፡
የእግዚአብሔር፡ ነቢይ ፡ ከሆንኩ ፡ እሳት ፡
ከሰማይ፡ወርዳ፡አንተንና፡ወገኖችህን፡ታቃ
ጥላችሁ፡አለው፡እሳትም፡ወርዳ፡እርሱንና፡
ኃምሳውን፡ወታደሮች፡አቃጠለቻቸው።

፳፱፤ ንጉሡም ፡ ዳግመኛ ፡ ከአለቃቸው ፡ ጋራ ፡
ኃምሳ ፡ ሰዎችን ፡ ወደርሱ ፡ ላከ ፡ አለቃ
ቸውም፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ንጉሥ ፡
ይጠራሃልና ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድ ፡ አለው ፡
ኤልያስም ፡ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡
ከሆንኩ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ ታቃ
ጥልህ፡ከአንተ፡ጋር፡ያሉትን፡ኃምሳውንም፡
አለው፡እሳትም፡ከሰማይ፡ወርዳ፡አቃጠለ
ቻቸው።

፴፤ ከዚህም፡በኋላ፡ንጉሡ፡ሦስተኛ፡የኃምሣ፡
አለቃ ፡ ላከ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡
ኤልያስ፡በትሕትና፡መጥቶ፡ሰገደለት፡የእግ
ዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ሆይ ፡ ተገዛሁልህ ፡
ሰውነቴ ፡ በፊትህ ፡ ትክበር ፡ የእነዚህም ፡
የባሮችህ ፡ ሰውነት ፡ ትክበር ፡ አለው ።
ኤልያስም፡ተነሥቶ፡ወረደ፡ከእሳቸውም፡
ጋር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሔደ ፡ ንጉሡንም ፡
እንዲህ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡እግዚአብሔር፡
እንዲህ፡አለ፡ቃልን፡ከጣዖት፡ትጠይቅ፡
ዘንድ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡የለምን፡ወደ፡
አቃሮን ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ዝንቡ ፡ ካህን ፡
እንዴት፡ላክህ፡ነገሩ፡እንዲህ፡አይደለም፡
በዚያ፡ሞትን፡ትሞታለህ፡እንጂ፡ከተኛ
ህበት፡መኝታህ፡ አትነሣም፡አለው፡ወዲ
ያውኑ፡ሞተ።

፴፩፤ ከዚህም፡በኋላ፡እግዚአብሔር፡ ኤልያስን፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ በሚያወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ኤል
ሳዕና ፡ ኤልያስ ፡ ከገልገላ ፡ ተነሥተው ፡
ሔደው፡ወደ፡ዮርዳኖስ፡ደረሱ፡ኤልያስም፡
መጠምጠሚያውን፡አውርዶ፡ጠቅሎ፡የዮ
ርዳኖስን ፡ ውኃ ፡ መታበት ፡ ውኃውም ፡
ተከፍሎ፡ወዲያና፡ወዲህ፡ቆመ፡ሁለቱም፡
ሁሉ ፡ በደረቅ ፡ ተሻገሩ ፡ ወጥተውም ፡
በምድረ፡በዳ፡ቆሙ።

፴፪፤ ኤልያስ፡ኤልሳዕን፡ካንተ፡ተለይቼ፡ወደ፡
ሰማይ፡ሳልወጣ፡አደርግልህ፡ዘንድ፡የምት
ሻውን ፡ ለምነኝ ፡ አለው ፡ ኤልሳዕም፡

www.ethiopianorthodox.org

ለይኩን፡ካዕበተ፡ላዕሌየ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ ዘዲቤከ።

፳፫፡ ወይቤሎ ፡ ኤልያስ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ዕፁበ ፡ ሰአልከኒ፡ወባሕቱ፡ለእመ፡ርኢከኒ፡እንዘ፡ አዐርግ፡እምኀቤከ፡ለይኩን፡ለከ፡ወእመሰ፡ ኢርኢከኒ ፡ ኢይከውን ፡ ለከ። ወሶቤሃ ፡ መጽአ፡ ሠረገላ፡እሳት፡ወአፍራሰ፡እሳት፡ ወቦአ ፡ ማዕከለ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ወአስተር ኃቆሙ፡ወዐርገ፡ኤልያስ፡በዐውሎ፡ወበድ ልቅልቅ፡ከመዝ፡ውስተ፡ሰማይ። ወርእዮ፡ ኤልሳዕ፡ጸርሐ፡ወይቤ፡አባ፡አባ፡ኃይሎሙ፡ ወጽንዖሙ፡ለእስራኤል፡ወእምዝ፡ኢርእዮ፡ ዳግመ፡ወሰጠጠ፡አልባሲሁ፡ወረሰዮሙ፡ ለክልኤ። ወአውረደ ፡ ሎቱ ፡ ኤልያስ ፡ ለኤልሳዕ፡ሐሜለቶ፡ወወረደ፡ላዕለ፡ርእሱ፡ ለኤልሳዕ ። ወተመክዓበ ፡ መንፈሱ ፡ ለኤልያስ፡ላዕለ፡ኤልሳዕ፡ወዡሎ፡ተአምረ፡ ዘይገብር ፡ ኤልያስ ፡ ገብረ ፡ ኤልሳዕ ፡ ምክብኢተ።

ኤልያስን፡በአንተ፡ያደረ፡ሀብተ፡መንፈስ ቅዱስ፡ዕጥፍ፡ሁኖ፡ይደርብኝ፡አለው።

፳፫፡ ኤልያስም ፡ ኤልሳዕን ፡ ድንቅ ፡ ነገርን ፡ ለመንከኝ፡ነገር፡ግን፡ካንተ፡ተለይቼ፡ወደ፡ ሰማይ፡ሳርግ፡ብታየኝ፡ይሁንልህ፡ባታየኝ፡ ግን ፡ አይሆንልህም ፡ አለው ። በዚያንም ፡ ጊዜ፡ የእሳት ፡ ሠረገላና ፡ የእሳት ፡ ፈረስ ፡ መጣ፡ ወደ ፡ መካከላቸውም ፡ ገብቶ ፡ አራራ ቃቸው ፡ ኤልያስም ፡ እንደዚህ ፡ በንውጽው ጽታና፡በጥቅል፡ነፋስ፡ወደ፡ሰማይ፡ዐረገ። ኤልሳዕም ፡ አይቶ ፡ የእስራኤል ፡ ኃይላ ቸውና፡ጽናታቸው፡አባ፡አባ፡ብሎ፡ጮኸ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ አላየውም ፡ ልብሶ ቹንም ፡ ለሁለት ፡ አድርጎ ፡ ከፈላቸው፡ ኤልያስም፡ለኤልሳዕ፡መጠምጠሚያውን፡ ጣለለት፡በኤልሳዕም፡ራስ፡ላይ፡ወረደ፡የኤ ልያስም፡ሀብተ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በኤልሳዕ፡ ላይ ፡ ዕጥፍ ፡ ሁኖ ፡ አደረ ፡ ኤልያስም ፡ የሠራውን ፡ ተአምራት ፡ ኤልሳዕ ፡ ዕጥፍ፡ አድርጎ፡ሠራ።

፳፬፡ ወለዝንቱ፡ኤልያስ፡ሀለዎ፡ይምጻእ፡በደኃሪ፡ መዋዕል ፡ ምስለ ፡ ሄኖክ ፡ ወይጌሥጽዎ ፡ ለሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቀትሎሙ ፡ ወይነብር፡አብድንቲሆሙ፡ግዱፈ፡ውስተ፡ መርሕብ ፫ መዓልተ፡ወ ፫ ሌሊተ፡ወእምዝ፡ ይትነሥኡ፡ወይከውን፡ትንሣኤ፡ሙታን። ወዝንቱ፡ኤልያስ፡ነቢይ፡ጻድቅ፡ውእቱ፡ ቀዳማዊ፡ወደኃራዊ፡ወበመዋዕለ፡ብሊት፡ ዘነበረ፡ውስተ፡ገዳም።

፳፬፡ ይህም፡ኤልያስ፡በኋላ፡ዘመን፡ከሄኖክ፡ጋር፡ ይመጣ፡ዘንድ፡አለው፡ሐሳዊ፡መሢሕንም፡ ይቃወሙታል ፡ እርሱም ፡ ይገድላቸዋል፡ በድናቸውም፡በአደባባይ፡ተጥሎ፡ሦስት፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ይቆያል ፡ ከዚህም፡ በኋላ ፡ ይነሣሉ ፡ የሙታን፡ ትንሣኤም ፡ ይሆናል ፡ ይህም ፡ ኤልያስ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነቢይ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ በኋላም፡የሚገለጽ፡ነው፡በብሉይ፡ዘመንም፡ ኑሮው፡በበረሀ፡ውስጥ፡ነበር።

፳፭፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡ነቢይ፡ኤልያስ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፳፭፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ ነቢይ ፡ ኤልያስ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለኤልያስ፡እንዘ፡ይነብር ፡በደብር። ሶበ፡ይቤሎ፡ላእከ፡ንጉሥ፡ኅሱር። ነዓ፡ፍጡነ፡ነቢየ፡እግ ዚአብሔር። ለእመ፡አነ፡ነቢየ፡አምላክ፡ክቡር። እሳተ፡ሰማይ፡ወሪዳ፡ታውዒከ፡በምድር።

፳፮፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡አባ፡ወር ክያኖስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡ ወውእቱ፡እምኍልቆሙ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ሳምናይ፡ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ተሠይመ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡እምድኅረ፡ዕርገቱ፡ለእግዚእነ፡

፳፮፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ የእስክን ድርያ፡አገር፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ወርክያኖስ፡ አረፈ፡እርሱም፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ ስምንተኛ ፡ ነው ። ይህም ፡ አባት ፡ የክብር ፡ ባለቤት፡ጌታችን፡ክርስቶስ፡ከዐረገ፡በኋላ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በ፸ ዓመት ፡ ወድኅረ ፡ ምዝባሬሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በ፴ ዓመት ፡ ወነበረ ፡ በሢመቱ ፡ ፱ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወያጸንዖሙ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወለብዙኃን ፡ አረማውያን ፡ ወከሀድያን ፡ ሚጠሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአጥመቆሙ ፡ ጥምቀት ፡ ክርስትና ፡ ወአብርሀ ፡ አልባቢሆሙ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌል ፡ ወሐረ ፡ ሑረተ ፡ ሠናየ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ። ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

በመቶ ፡ ዓመት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ በሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡ ሕዝቡንም ፡ እያስተማረና ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ እያጸና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ ብዙዎች ፡ አረማውያንንና ፡ ከሀድያንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ መለሳቸው ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትንም ፡ አጠመቃቸው ፡ በወንጌል ፡ ትምህርትም ፡ ልቡናቸውን ፡ ብሩህ ፡ አደረገ ፡ መልካም ፡ ጉዞንም ፡ በመጓዝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ በፍቅር ፡ አንድነት ፡ አረፈ ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለወርከያኑ ፡ ሳምናይ ፡ በፍቅድ ። እምኍልቈ ፡ ጳጳሳት ፡ ኄራን ፡ ዘይብልዎሙ ፡ አዕማድ ። አረማውያነ ፡ ይሚጥ ፡ እምፍኖተ ፡ ካህድ ። ወያብዕል ፡ ክርስቲያነ ፡ በጸጋ ፡ ፍድፉድ ። ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድምዐ ፡ ዘነሥአ ፡ እምወልድ ።

፻፺፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ዐቢይ ፡ ወክቡር ፡ ባስልዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘቂሣርያ ።

፻፺፫፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ ኤስድሮስ ፡ ወውእቱ ፡ ቀሲስ ፡ ንጹሕ ፡ ወቅዱስ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወወለደ ፡ ፭ተ ፡ ውሉደ ፡ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ባስልዮስ ፡ ወጎርጎርዮስ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ወኬርዮን ፡ ወመክርዮን ፡ ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳነ ፡ ወፍጹማነ ።

፻፺፬፡ ወመልአ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ወደረሰ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘዕውቅ ፡ በኵሉ ፡ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእደዊሁ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጽሐፈ ፡ ገድሉ ። ወእምኔሆሙ ፡ ፯ቱ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ወ፩ ዜናሁ ፡ ለጴጥሮስ ፡ እኍሁ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ስብስጥያ ፡ ዘከመ ፡ እሮ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ ብእሲት ። ወሐመይዎ ፡ ሕዝብ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ዜናሁ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ከሠተ ፡ ሎሙ ፡ ገድሎ ፡ ወምሥጢረ ፡ ዘምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ደናግል ፡ ወንጹሐን ፡ እምኃጢአት ፡ ወአጠየቆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ እንዘ ፡ ይጼልል ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሶ

፻፺፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረና ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ አባት ፡ የቂሣርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባስልዮስ ፡ አረፈ ።

፻፺፫፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ኤስድሮስ ፡ ይባላል ፡ እርሱም ፡ ከአንጾኪያ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ንጹሕና ፡ ቅዱስ ፡ የሆነ ፡ ቄስ ፡ ነው ፡ አምስት ፡ ልጆችንም ፡ ወልዶአል ፡ እነርሱም ፡ ባስልዮስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኬርዮን ፡ መክርዮን ፡ ናቸው ፡ ሁሉም ፡ ከፍጹማንነት ፡ የደረሱ ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ።

፻፺፬፡ በዚህ ፡ በከበረ ፡ ባስልዮስ ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መልቶበት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀች ፡ ቅዳሴውን ፡ ደረሰ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእጆቹ ፡ ብዙዎች ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አደረገ ፡ በገድሉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈ ። ከእርሳቸውም ፡ ሰባቱ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ አንደኛው ፡ የስብስጥያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የወንድሙ ፡ የጴጥሮስ ፡ ዜና ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ አንዲት ፡ ሚስት ፡ እንደነበረችው ፡ ሕዝቡም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንዳሙት ፡ ወሬውም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ምሥጢሩንና ፡ ገድሉን ፡ እነርሱ ፡ ንጹሐን ፡ ደናግል ፡ እንደሆኑ ፡ ለሕዝቡ ፡ ገለጠላቸው ። የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ በክንፎቹ ፡ ሲጋርዳቸው ፡ እንዳየ ፡ አስረዳቸው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በቅዱስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤሃ ፡ ርእዩ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይጼልል ፡ ላዕሌሆሙ፡ ለቅዱስ፡ ጴጥሮስ፡ ወብእሲቱ፡ ብዕዕት ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ። ወአን ከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወሰገዱ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወሰ አልዎ፡ከመ፡ይኅድግ፡ሎሙ፡አበሳሆሙ።

፹፡ ወዳግማይ፡ ተአምር፡ በእንተ፡ ዜናሃ፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዘነሥእዋ፡ ዓላውያን፡ ንፉቃን፡ ሃይማኖት፡ በዓመፃ፡ ወከመ፡ ኢተከህሎሙ፡ ያርኅዉ ፡ ኆኅታ ፡ እስመ ፡ ዐጸዋ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ፡ በጸሎቱ ፡ ወእምዝ ፡ ተርኅወት ፡ ለመሐይምናን፡ርቱዓነ፡ሃይማኖት፡ወቦኡ።

፹፩፡ ሣልሳይ ፡ ተአምር ፡ ዜናሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ዘይበጽሕ፡እምድር፡እስከ፡ሰማይ፡ወሰምዐ፡ ቃለ ፡ ዘይብል ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘቂሣርያ ፡ ወበጺሖ ፡ ቅዱስ፡ ኤፍሬም፡ ሀገረ፡ ቂሣርያ፡ ርእየ፡ ጽድቆ፡ ወት ሩፋቲሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ወተሠይመ ፡ እምኔሁ ፡ ዲያቆነ ፡ ወዓዲ ፡ ሢመተ ፡ ቅስና ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወረሰዮ ፡ ይትናገር ፡ በል ሳነ፡ዮናኒ።

፹፪፡ ወራብዕ ፡ ተአምር ፡ በእንተ ፡ ሐሳቢ ፡ መሰ ግል ፡ ዘኢይስሕት ፡ ግሙራ ፡ በሐሳቡ ፡ በእንተ፡ ኵሉ፡ ግብር፡ ወሶበ፡ ደወየ፡ ቅዱስ፡ ባስልዮስ ፡ አእመረ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ወጸውዖ ፡ ለውእቱ ፡ በዓለ ፡ ሐሳብ ፡ ወይቤሎ ፡ ማእዜ ፡ እመውት ፡ ወይቤሎ፡ ሐሳቢ ፡ በጊዜ ፡ ሠርክ ፡ ትወጽእ ፡ ነፍስከ ፡ እምሥጋከ ። ወይቤሎ ፡ ቅዱስ፡ ባስልዮስ ፡ ለእመ ፡ ኢሞትኩ ፡ እስከ ፡ ጽባሕ ፡ ትከውንኑ ፡ ክርስቲያናዌ ፡ ወይቤ ውእቱ ፡ ሐሳቢ ፡ እወ ፡ ወሰአሎ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወወሰኮ ፡ ዲበ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ሠለስተ ፡ ዕለታተ ፡ ወአምነ ፡ ውእቱ ፡ ሐሳቢ ፡ ወተጠምቀ ፡ ወኮነ ፡ ክርስቲያናዌ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ።

፹፫፡ ኃምስ ፡ ተአምር ፡ ዜናሁ ፡ ለገብር ፡ ዘክህደ ፡ ክርስትናሁ ፡ ወጸሐፈ ፡ ክህደቶ ፡ በእዴሁ ፡ ወወሀቦ ፡ ለሰይጣን ፡ ወቅዱስኒ ፡ ባስልዮስ ፡ ሞቅሖ ፡ ለገብር ፡ ውስተ ፡ ጸላዕት ፡ ወሰአለ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ፡ እስከ ፡

ጴጥሮስ፡ላይና፡በከበረች፡ሚስቱ፡ላይ፡የእግዚ አብሔር ፡ መልአክ ፡ ክንፎቹን ፡ ሲጋርድ ፡ ሕዝቡ ፡ አዩ ፡ እጅግም ፡ አደነቁ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ አመሰገኑት ፡ በደላቸውንም ፡ ይቅር ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወድቀው ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን፡ለመኑት።

፹፡ ሁለተኛው ፡ ተአምር ፡ ሃይማኖት ፡ ለዋጮች ፡ መናፍቃን ፡ በግፍ ፡ ስለወሰዱዋት ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ በርዋን ፡ መክፈት ፡ እንዳልተቻላቸው ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በጸሎቱ ፡ ዘግቷታልና ፡ ከዚ ህም ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ለቀና ፡ ምእመ ናን ፡ ተከፍታላቸው ፡ ገቡ።

፹፩፡ ሦስተኛ ፡ የቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ ዜና ፡ ነው ፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የሚደርስ ፡ የብርሃን ፡ ምሰሶ ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የቂሣርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ቃልን ፡ ሰማ ። ቅዱስ ፡ ኤፍሬምም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ፡ የቅዱስ ፡ ባስልዮስን ፡ ደግነቱንና ፡ ትሩፋ ቱን ፡ አየ ፡ ከእርሱም ፡ ዲቁና ፡ ደግሞ ፡ ቅስና ፡ ተሾመ ፡ በቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ ላይም ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ጸልዮ ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲናገር ፡ አደረገው።

፹፪፡ አራተኛ ፡ ተአምር ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚቈጥር፡ ጠንቋይ፡ ከቶ፡ በአቈጣጠሩ፡ የማይ ሳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ የሚሞትበትን ፡ ጊዜ ፡ ዐውቆ ፡ ይህን ፡ ጠንቋይ ፡ ጠርቶ ፡ መቼ ፡ እሞታለሁ ፡ አለው ፡ ጠንቋዩም ፡ ማታ ፡ ነፍስህ ፡ ከሥጋህ ፡ ትለያ ለች ፡ አለው ። የከበረ ፡ ባስልዮስም ፡ እስከ ፡ ጥዋት ፡ ካልሞትኩ ፡ ክርስቲያን ፡ ትሆናለህን ፡ አለው፡ ጠንቋዩም፡ አዎን፡ አለ። የከበረ፡ ባስል ዮስም፡ የክብር፡ ባለቤት፡ ጌታችንን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን ፡ ለመነውና ፡ በዕድሜው ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ቀኖችን ፡ ጨመረለት ፡ ያም ፡ ጠንቋይ ፡ አመነ፡ ከቤተ፡ ሰቦቹ፡ ሁሉ፡ ጋር፡ ተጠምቆ፡ ክር ስቲያን፡ሆነ።

፹፫፡ አምስተኛ፡ ተአምር፡ ክርስትናውን፡ ክዶ፡ ክህ ደቱንም፡ ጽፎ፡ ለሰይጣን፡ ስለ፡ ሰጠ፡ ባርያ፡ ዜና፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ባርያ ፡ ዘጋበት ፡ የክህደቱንም ፡ ደብዳቤ ፡ ሰይጣን ፡ እስከ ፡ መለሰለት ፡ ድረስ ፡ ስለርሱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሜጠ፡ሰይጣን፡ውእተ፡መጽሐፈ፡ክህደቱ፡
ለገብር፡ወአድኃኖ፡ለውእቱ፡ገብር።

፳፬፡ ሳድስ፡ተአምር፡ዜናሁ፡ለቀሲስ፡ድንግል፡
ውእቱ ፡ ወብእሲቱ ፡ ዘኮነ ፡ በኀቤሆሙ ፡
ዘይደዊ፡በደዌ፡ቍስል፡ወዘከመ፡አእመረ፡
ቦሙ ፡ ብፁዕ ፡ ባስልዮስ ፡ ወዘከመ ፡ ሰከበ ፡
በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ዘይደዊ ፡
ወሰአሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ፡
ወሐይወ፡ሶቤሃ፡እምደዌሁ።

፳፭፡ ሳብዕ፡ተአምር፡ዜናሃ፡ለብእሲት፡ክብርት፡
ዘጸሐፈት፡ኵሎ፡ኃጣውኢሃ፡ወሐተመታ፡
ውስተ፡ክርታስ፡ወሰአለቶ፡ለቅዱስ፡ከመ፡
ይጸሊ ፡ ላቲ ፡ እስከ ፡ ይደመሰሱ ፡ ኵሉ ፡
ኃጣውኢሃ፡ወጸለየ፡ላቲ፡ቅዱስ፡ባስልዮስ፡
እስከ፡ተደምሰሱ፡ ኃጣውኢሃ ፡ ዘእንበለ ፡
አሐቲ፡ጌጋይ፡ወአዘዛ፡ከመ፡ትሑር፡ኀበ፡
ቅዱስ፡ኤፍሬም፡ውእቱኒ፡ነገራ፡ወይቤላ፡
አፍጥኒ ፡ ወተመየጢ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ባስል
ዮስ፡እምቅድመ፡ያዕርፍ፡እስመ፡ውእቱ፡
ዘየኀድግ፡ለኪ፡ወውእቱ፡ርእሰ፡ካህናት።
ወተመይጣ ፡ ረከበቶ ፡ በዘአዕረፈ ፡ ወይፀ
ውርዎ ፡ በዐራት ፡ ከመ ፡ ይሰድዎ ፡ ኀበ ፡
ይቀብርዎ፡ወበከየት፡ብካየ፡መሪረ፡ወአን
በረት፡ውእተ፡ክርታስ፡ላዕለ፡ሥጋሁ፡ወተ
ደምሰሰት ፡ ላቲ ፡ ወርእዮሙ ፡ ኵሎሙ ፡
ሕዝብ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ ግብረ ፡ አንከሩ ፡
ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ዘይሁብ ፡ ዘንተ ፡ ጸጋ ፡ ዐቢየ ፡ ለእለ ፡ ይፈ
ርህዎ።

፳፮፡ ወዘንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ገብረ ፡ ተአ
ምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ዘእንበለ ፡
ዘጸሐፍነ ፡ ገዘየ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡
ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ወተግሣጻተ ፡ ብዙኃነ ፡
ወትምህርታተ ፡ ለመነኮሳት ፡ ወተርጐመ ፡
ብዙኃተ፡መጻሕፍተ፡መለኮታውያተ፡እምነ፡
ብሊት፡ወሐዲስ፡ወሠርዐ፡ቀኖናተ፡ወእሉ፡
ይትረከቡ፡ውስተ፡ኵሉ፡መካን፡ወእምዝ፡
አዕረፈ፡በሰላም፡ወቀበርዎ፡በክብር፡ብዙኅ።

፳፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበ
ረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ውስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ወደ ፡እግዚአብሔር ፡ ለመነ ፡ ያንንም ፡ ባርያ ፡
አዳነው።

፳፬፡ ስድስተኛ ፡ ተአምር ፡ ድንግል ፡ ስለሆነ ፡ ቄስ ፡
ዜና ፡ እርሱም ፡ ሚስቱም ፡ ከእነርሳቸውም ፡
በቍስል ፡ ደዌ ፡ የታመመ ፡ አለ ፡ የከበረ ፡ ባስ
ልዮስም ፡ እንደ ፡ አወቀባቸው ፡ በዚያችም ፡
ሌሊት ፡ ከታመመው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተኛ ፡
ስለርሱም፡እግዚአብሔርን፡እንደለመነውና፡
ከደዌው፡እንዳዳነው።

፳፭፡ ሰባተኛ ፡ ተአምር ፡ ስለ ፡ አንዲት ፡ የከበረች ፡
ሴት ፡ ዜና ፡ እርሷም ፡ ኃጢአቷን ፡ ሁሉ ፡ ጽፋ ፡
በክርታስ ፡ አሽጋ ፡ ኃጢአቷ ፡ ሁሉ ፡ እስከሚደ
መሰስ ፡ እንዲጸልይላት ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስን ፡
ለመነችው ፡ ከአንዲት ፡ በደል ፡ በቀር ፡
ኃጢአቶቿ ፡ ሁሉ ፡ እስከተደመሰሱ ፡ ድረስ ፡
ጸለየላት ። ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬምም ፡ እንድ
ትሔድ ፡ አዘዛት ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬምም ፡ ወደ ፡
ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ሳይሞት ፡ ፈጥነሽ ፡ ተመ
ለሽ ፡ የካህናት ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ ስለሆነ ፡ የሚደ
መስስልሽ ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ ብሎ ፡ ነገራት ፡
በተመለሰችም ፡ ጊዜ ፡ ሙቶ ፡ በዐልጋ ፡ ተሸ
ክመው ፡ ወደሚቀብሩበት ፡ ሲወስዱት ፡ አገ
ኘችው ፡ መሪር ፡ ልቅሶም ፡ አልቅሳ ፡ ያንን ፡
ክርታስ ፡ ከአስከሬኑ ፡ ላይ ፡ ጣለችው ፡ በደ
ሏም ፡ ተደመሰሰላት ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡
ድንቅ ፡ ሥራ ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡
ለሚፈሩት ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ የሚሰጥ ፡ እግ
ዚአብሔርን፡አመሰገኑት።

፳፮፡ ይህ ፡ የከበረ ፡ ባስልዮስ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡
ውስጥ ፡ ከጻፍነው ፡ ሌላ ፡ ብዙዎች ፡ ድን
ቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አድርጓል ፡ ብዙዎ
ችንም ፡ ተግሣጾችንና ፡ ድርሳናትን ፡ ለመነኰ
ሳትም ፡ ትምህርቶችን ፡ ደርሷል ። ከብሉይና ፡
ከሐዲስም ፡ አምላካውያን ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ መጻ
ሕፍቶችን ፡ ተርጕሟል ፡ ሥርዓቶችንም ፡ ሠራ ፡
እነርሱም ፡ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ይገኛሉ ፡ ከዚህም ፡
በኋላ ፡ በሰላም ፡ አርፎ ፡ በክብር ፡ በብዙ ፡ ምስ
ጋና ፡ ቀበሩት።

፳፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከ
ቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## ስንክሳር ዘወርኀ ጥር

### አርኬ

ሰላም፡እብል፡ብእሴ፡ኀዳፌ።ዘየአምር፡ምሳሌ፡ወሥዋሬ፡ነገር፡ዘተርፌ።ስእለተ፡አሐቲ፡ብእሲት፡ሶበ፡ባስልዮስ፡ተወክፈ።ደምሰሰ፡በሕይወቱ፡ዘኃጣውኢሃ፡መጽሐፈ።ወድኅረ፡ሞቱ፡አሐደ፡ዘተርፈ።

፳፰፤ወበዛቲ፡ዕለት።አዕረፈ፡አባ፡ሙሴ፡ዘነበረ፡ውስተ፡ገዳም፡፰ አክራመ፡ወእምነጽሮቱ፡አልባበ፡ቅዱሳን፡ተደመ፡ወተወለጠ፡ገጹ፡ወኮነ፡ከመ፡ፍሕም፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር።አሜን።

፳፰፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ በበረሀ ፡ ስልሳ ፡ ዘመናት ፡ የኖረ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ አረፈ ። እርሱም ፡ የቅዱሳ ንን፡ልቡና፡ከማየቱ፡የተነሣ፡አደነቀ፡ፊቱም፡ተለውጦ፡እንደ፡እሳት፡ፍም፡ሆነ፡በረከቱም፡ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትሁን ፡ለእግዚአብሔርም ፡ ምስ ጋና፡ይሁን፡አሜን።

### አርኬ

ሰላም፡ለሙሴ፡ ዘነበረ፡ገዳመ።ስሳ፡አክራመ።በዛቲ፡ዕለት፡እንዘ፡ይነውም፡ንዋመ።እስከ፡እምርእዮቱ፡አልባበ፡ቅዱሳን፡ተደመ።ወተውላጠ፡ገጹ፡እንተ፡ኮነ፡ፍሕመ።

***

፩፤በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡ አመ፡፯ለጥር፡በዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ሶል ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ፡ሮሜ።

፪፤ ወለዝንቱ ፡ አብ ፡ በእንተ ፡ ዕበየ ፡ ተጋድሎቱ ፡ ወተጸምዶቱ ፡ ወትሩፋቲሁ ፡ ወአእምሮቱ ፡ ወጽድቁ፡ኀረይዎ፡ወሤምዎ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ላዕለ፡ሀገረ፡ሮሜ፡እምድኅረ፡አዕረፈ፡አባ፡መልጥያኖስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእምቅድሜሁ። ወሶበ፡ነበረ፡ዲበ፡መንበረ፡ጴጥሮስ፡ርእሰ፡ሐዋርያት ፡ አጥመቆ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ፡ወልደ፡ዕሌኒ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡ እስመ፡ውእቱ፡ኢተጠምቀ፡ዓዲ፡በእንተ፡ጸቢኦቶሙ ፡ ለከሀድያን ፡ ወአንሐለ ፡ ኵሎ ፡ አብያተ፡ጣዖታት፡ወሐነፃን፡ለአብያተ፡ክርስቲያናት፡ዘእግዚአብሔር።

፫፤ወገድሉሰ፡ለዝንቱ፡አብ፡ሶል፡ጴጥሮስ፡ኮነ፡ብሩሀ፡ፈድፋደ፡እስመ፡ውእቱ፡ይሜህሮሙ፡ለሕዝብ፡ኵሎ፡አሚረ፡ወያአትት፡እምአልባቢሆሙ፡ኑፋቄ፡ወሕሊና፡እኪተ፡ዘሰይጣን። ወይተረጕም፡ሎሙ፡ምሥጢረ፡መጻሕፍት፡ዘተሠወረ፡እምኔሆሙ፡ወያሌብዎሙ፡ወኮነ፡ወትረ፡ይትዋሥኦሙ፡ለአይሁድ፡ወለዮናና ውያን፡ወሚጠሙ፡ለብዙኃን፡እምኔሆሙ፡ወአብኦሙ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወአጥመቆሙ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡ወኮነ፡ስሙ፡

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ ጥር፡ሰባት፡በዚች፡ቀን፡የከበረ፡አባት፡የሮሜ፡ሀገር፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ሶል፡ጴጥሮስ፡አረፈ።

፪፤ ይህንንም፡አባት፡ስለ፡ተጋድሎው፡ገናናነት፡ስለ፡አገልግሎቱም፡ስለ፡ትሩፋቱ፡ስለ፡አዋቂነቱና፡ስለ፡ደግነቱ፡ከእርሱ፡ገፊት፡የነበረ፡ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ መልጥያኖስ ፡ ከአረፈ ፡ በኋላ፡መርጠው፡ሊቀ፡ጵጵስና፡በሮሜ፡ሀገር፡ላይ፡ሾሙት።በሐዋርያት፡አለቃ፡በጴጥሮስ፡ወንበር፡በተቀመጠ፡ጊዜ፡የዕሌኒ፡ልጅ፡የሆነ፡ንጉሥ፡ቈስጠንጢኖስን፡የክርስትና፡ጥምቀ ትን፡አጠመቀው፡ከከሀድያን፡ጋር፡ስለሚያ ደርገው፡ጦርነት፡ምክንያት፡ገና፡አልተጠ መቀም ፡ ነበርና ፡ የጣዖታትንም ፡ ቤቶች ፡ አፍርሶ፡የእግዚአብሔርን፡ አብያተ፡ክርስቲ ያናት፡ሠራቸው።

፫፤የዚህም፡አባት፡የሶል፡ጴጥሮስ፡ገድሉ፡እጅግ፡ብሩህ፡የሆነ፡ነው፡እርሱ፡ሁል፡ጊዜ፡ሕዝ ቡን፡ያስተምራቸዋልና፡ከልቡናቸውም፡ከሰ ይጣን ፡ የሆነ ፡ ጥርጥርንና ፡ ክፉ ፡ ሐሳብን ፡ ያርቃል።ከእነርሳቸው፡ሥውር፡የሆነውንም፡የመጻሕፍት፡ምሥጢር፡ተርጕሞ፡ያስገነዝባ ቸዋል ። አይሁድንና ፡ ዮናናውያንን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይከራከራቸው ፡ ነበር ፡ ከእርሳቸውም ፡ ብዙዎችን፡መልሶ፡ወደ፡ቀናች፡ሃይማኖት፡አስገባቸው፡የክርስትና፡ጥምቀትንም፡አጠ መቃቸው ፡ ስሙም ፡ በምእመናን ፡ ዘንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

መፍርሀ፡ወግሩመ፡በኀበ፡ምእመናን።

፱፡ ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ብዙኃተ ፡ በእንተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ወበእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ለወልደ፡ እግዚአብሔር።

፲፡ ወበ፯ቱ፡ዓመተ፡ሢመቱ፡ኮነ፡ጉባኤ፡ማኅበረ፡አበው፡ቅዱሳን፡፫፻፲ወ፰ርቱዓን፡ሃይማኖት፡በሀገረ፡ኒቅያ፡በእንተ፡አርዮስ፡ወኮነ፡ዝንቱ፡ሶል ፡ ጴጥሮስ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ፩ዱ ፡ ወረገሞ ፡ ለአርዮስ ፡ ወአውገዞ ፡ ወለኵሎሙ ፡ ተላውያኒሁ።

፲፩፡ ወነበረ፡በሢመቱ፡ዐሠርተ፡ወአሐደ፡ዓመተ፡ወፈጸመ፡ገድሎ፡ሠናየ፡ወአሥመሮ፡ ለእግዚአብሔር፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ፈጽሞ፡የሚያስፈራ፡ሆነ።

፱፡ እግዚአብሔርን፡ስለ፡ማወቅና፡ስለ፡ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ሰው፡መሆን፡ብዙ፡ድርሳናትን፡ደረሰ።

፲፡ በተሾመ ፡ በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ አርዮስ፡በኒቅያ፡ከተማ፡ሃይማኖታቸው፡የቀና፡የሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ የከበሩ ፡ አባቶች፡የአንድነት፡ስብሰባ፡ሆነ፡ይህም፡አባት ፡ ሶል ፡ ጴጥሮስ ፡ ከእርሳቸው ፡ አንዱ ፡ ነበር ፡ አርዮስንም ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ረገመው፡አውግዞም፡ለየው።

፲፩፡ በሹመቱም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ መልካም ፡ ተጋድሎውን ፡ ፈጽሞ ፡ እግዚአብሔርንም፡አገልግሎ፡በሰላም፡አረፈ።

፲፪፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ጴጥሮስ ፡ሶል ። መጥምቀ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ከሣቴ ፡ መስቀል ።መዋዕለ ፡ ዕብሬትከ፡ኮነ፡ዕብሬተ፡ርትዕ፡ወሣህል።እስመ፡ተቀጥቀጠ፡ዳኅን፡ወወድቀ፡ቤል።በከመ፡ቀዳሚ፡ኢሳይያስ፡ይብል።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፲፫፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ኤፍሬም ፡ አብ ። ምሉአ ፡ ጥበብ ። ፈሪሆተ ፡ ክርስቶስ ፡ ምልአኒ ፡ ከመ ፡ ማህየብ ። በአልባቢሆሙ፡ለዘይፈርህዎ፡ሕዝብ።እስመ፡አድኅኖቱ፡ተብህለ፡ለአምላክ፡ቅሩብ።

፲፬፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለሰሎሞን፡ወጎርጎርዮስ ፡ ወማርቆስ ፡ ወአንትያኖስ ፡ ወሉያ ፡ ወመልይን ፡ ወሱስዮስ ፡ ወማርትይ ፡ በረከቶሙ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር፡አሜን

***

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡አመ ፡ ፲፫ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘቅዱስ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ በገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ በእደዊሁ ፡ ለብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ዘእስክንድርያ።

፪፡ ወእምድኅረዝ ፡ በጽሐ ፡ ምንዳቤ ፡ ላዕለ ፡ አባ፡ብንያሚን፡እምነበ፡መቆቅዝ፡መለካዊ፡

፲፬፡ በዚችም፡ቀን፡የሰሎሞን፡የጎርጎርዮስ፡የማርቆስ፡የአትያኖስ ፡ የሉያ ፡ የመልይን የሱስዮስ ፡ የማርትይ ፡ መታሰቢያቸው ነው። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡ስምንት፡በዚች፡ዕለት ፡ በአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ የአባ ፡ መቃርስ ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡በከበረና፡በተመሰገነ፡በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአባ ፡ ብንያሚን ፡ እጅ፡የከበረችበት፡ሆነ።

፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መቆቅዝ ፡ ከሚባል ፡ ዐላዊ ፡ መለካዊ ፡ በአባ ፡ ብንያሚን ፡ ላይ ፡ መከራ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዐላዊ ፡ ወገሥየ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ነበ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ እስከ ፡ ተፍጸሚተ ፡ ፲ ዓመት ፡ ወእምዝ ፡ አጥፍአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለውእቱ ፡ ዐላዊ ፡ መቆቅዝ ፡ ወኮነ ፡ ኅድዓት ፡ ለኵሎን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ። ወተመይጠ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ ወመጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ረበናት ፡ ዘገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወሰአልዎ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወይቀድስ ፡ ሎሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሐዳሰ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዘቅዱስ ፡ አባ፡መቃርስ።

፫፡ ወተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በዐቢይ ፡ ፍሥሓ ፡ ወወጠነ ፡ ጸሎተ ፡ በእንተ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ለቤተ፡ክርስቲያን።

፬፡ ወሶበ ፡ አኀዘ ፡ ይቅባዕ ፡ ምሥዋዐ ፡ በሜሮን ፡ ርእየ ፡ እዴሁ ፡ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እንዘ ፡ ትቀብዕ ፡ ምስሌሁ ፡ ወድቀ ፡ በገጹ ፡ እምነ፡ፍርሃት፡ዐቢይ፡ወአንሥኦ፡አሐዱ፡እም ኪሩቤል ። ወይቤሎ፡ ተንሥእ፡ ወኢትፍራህ ፡ ወጸሐፍ ፡ ቀኖና ፡ ቅዱሰ ፡ ለዝንቱ ፡ መካን ፡እስመ ፡ ውእቱ ፡ ምሥጢሩ ፡ለእግዚአብሔር ፡ ከመ፡ ኢይባእ ፡ መኑሂ ፡ በትዕቢተ ፡ ልብ፡ ወኢ ፡ በህልያን ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተሠይመ ፡ በርትዕ ፡ ውስቴቱ ፡ ወኢይድፍር ፡ ወኢይትናገር፡በውስቴቱ፡ነገረ፡ከንቶ፡እስመ፡ውእቱ፡ ቤተ ፡ ቅድሳቱ ፡ለእግዚአብሔር ፡ ወዝንቱ ፡ ቀኖና ፡ ሥሩዕ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መካን፡ እስከ፡ ለዓለም።

፭፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ሀሎ ፡ መዋዕል ፡ ይመጽእ ፡ ወያማስኑ ፡ ትእዛዛተ ፡ አበው ፡ ወይከውን ፡ ዝንቱ፡መካን፡ቅዱስ፡ከመ፡መካነ፡ሥላቅ።

፮፡ ወይቤ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ዛቲ ፡ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዛቲ ፡ ኆኅታ ፡ ለሰማይ ፡ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ ይትናገር ፡ ምስለ ፡ ኪሩብ ፡ ነጸረ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወርእየ፡ ፩ደ፡ አረጋዌ ፡ ዘሠናይ ፡ አርአያሁ ፡ ወነዊኀ ፡ ጽሕሙ ፡ ወገጹ ፡ ብሩህ ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ መልአክ ፡ ወአደሞ ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ ወይቤ፡ በነፍሱ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ እምኤጲስቆጶሳት ፡ አነ ፡ እሠይሞ ፡ ለዝንቱ ፡ አረጋዊ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ህየንቴሁ ። ወይቤሎ ፡ ኪሩብ ፡ አ ፡ ብንያሚን ፡ ትሬስዮኑ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ መቃርዮስ ፡ ኤጲስ ቆጶሰ ፡ ዘውእቱ ፡ አቡሆሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡

ደረሰበት ፡ አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ሔደ ፡ ዐሥር ፡ ዓመትም ፡ እስ ኪፈጸም ፡ በዚያ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ዓላዊ ፡ መቆቅዝን ፡እግዚአብሔር ፡ አጠፋው ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ጸጥታ ፡ ሰላም ፡ ሁኖ ፡ አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ወደ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ ተመለሰ ፡ የአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ሽማግ ሎችና ፡ መምህራን ፡ ወደርሱ ፡ መጡ፡ ወደርሳ ቸውም ፡ ሒዶ ፡ አዲስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲ አከብርላቸው ፡ ለመኑት ፡ እርሷም ፡ የከበረ ፡ የአባ፡መቃርስ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ናት።

፫፡ በታላቅ ፡ ደስታም ፡ ተነሥቶ ፡ ከእሳቸው ፡ ጋር ፡ ሔደ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኒቱንም ፡ መባረኪያ ፡ ጸሎት፡ጀመረ።

፬፡ መሠዊያውንም ፡ በሜሮን ፡ ሊቀባ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡የጌታችን ፡ እጅ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ስትቀባ ፡ አየ ፡ ከታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ የተነሣ ፡በግምባሩ ፡ ፍግም ፡ ብሎ ፡ ወደቀ ። ከኪ ሩቤልም ፡ አንዱ ፡ አነሣው ፡ እንዲህም ፡ አለው፡ ተነሣ ፡ አትፍራ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ ሥርዓት ፡ ለዚህ ፡ ቦታ ፡ ጻፍ ፡ ይህ ፡የእግዚአብሔር ፡ ምሥጢር ፡ የሚፈጸምበት ፡ ነውና ፡ ማንም ፡ በትዕቢት ፡ ወይም ፡ መማለጃ ፡ በመስጠት ፡ እን ዳይገባ ፡ በውስጡ ፡ በሚገባ ፡ ከሚሾም ፡ በቀር ፡ የማይደፍርና ፡ በውስጡ ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የሚ ናገር ፡ አይኑር ፡የእግዚአብሔር ፡ መመስገኛ፡ ቤቱ ፡ ነውና ፡ ይህም ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ እስከ፡ዘላለሙ፡የተሠራ፡ይሆናል።

፭ እነሆ፡ዘመን፡ይመጣል፡የአባቶችንም፡ትእ ዛዝና ፡ ሥርዓት ፡ ያፈርሳሉ ፡ ይህም ፡ የከበረ፡ ቦታ፡እንደ፡መሣለቂያ፡ቦታ፡ይሆናል።

፮፡ አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ይህች ፡የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሰማይ ፡ ደጅ ፡ ናት ፡ አለ ፡ ይህንንም ፡ ከኪሩብ ፡ ጋር ፡ ሲናገር ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ በስተምሥራቅ ፡ ተመለከተ ፡ አንድ ፡ መልኩ፡ የሚያምር ፡ ጽሕሙ ፡ የረዘመ ፡ ፊቱም ፡ እንደ ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ የሚያበራ ፡ ሽማግሌ ፡ አየ ። ለአባ ፡ ብንያሚንም ፡ ደስ ፡ አሰኘውና ፡ በልቡ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ አንዱ ፡ ቢሞት፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይህን ፡ ሽማግሌ ፡ እሾመዋለሁ። ኪሩብም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ብንያሚን ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ አባት ፡ መቃርዮስን ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ ታደርገዋለህን ። እርሱ ፡ የሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ውእቱ፡በጽሐ፡ዮም፡በመንፈስ፡ከመ፡
ይትፈሣሕ፡ምስለ፡ውሉዱ፡ወኢይትኃጣእ፡
እምውሉዱ፡ሥዩም፡ወኢ፡ሊቅ፡ወኢይተ
ኃጣእ፡እምኔታቲሁ፡ፍሬ፡ዘመንፈስ፡ቅዱስ።

፯፡ ወይቤ፡አባ፡ብንያሚን፡ብፁዓን፡እሙንቱ፡
ውሉዱ፡ወይቤ፡ኪሩብ፡ብፁዓንሰ፡ለእመ፡
ዐቀቡ፡ትእዛዛቲሁ፡ወተለዉ፡ዓሠሮ፡እሙ
ንቱ፡ይከውኑ፡ምስሌሁ፡ውስተ፡ኀበ፡ሀሎ፡
ስብሐት፡ወለእመ፡ተዓደዉ፡ትእዛዛቲሁ፡
ኢይከውኖሙ፡ምስሌሁ፡ርስት።

፰፡ ወይቤሎ፡አባ፡መቃርስ፡ለኪሩብ፡ኢት
ምትር፡እግዚእየ፡ተስፋ፡ላዕለ፡ውሉድየ፡
በዝንቱ፡ነገር፡ዳዕሙ፡ለእመ፡ተርፈት፡
ውስተ፡አስካል፡አሐቲ፡ኀጠት፡እስመ፡
ይሬሲ፡ውስቴታ፡እግዚአብሔር፡በረከቶ፡
ወከማሁ፡ለእመ፡ተርፈ፡ውስቴቶሙ፡ፍቅር፡
አነ፡አአምን፡ከመ፡እግዚአብሔር፡ኢያር
ኅቆሙ፡እመንግሥቱ።

፱፡ ወአንከረ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ብንያሚን፡እምነ፡
ምሕረቱ፡ለአረጋዊ፡አባ፡መቃርስ፡ወጸሐፈ፡
ውእተ፡ቀኖና፡በከመ፡አዘዞ፡ኪሩብ፡ወአን
በሮ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ይኩን፡ተዝ
ካረ፡ዘወትር።

፲፡ ወሰአሎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡
ስብሐት፡ከመ፡ይኩን፡ዕረፍቱ፡በዛቲ፡ዕለት፡
ሶበ፡ይበጽሕ፡መዋዕሊሁ፡ወኮነ፡ሎቱ፡
ከማሁ። ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡
ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

አባታቸው፡ነውና፡ዛሬ፡ከልጆቹ፡ጋር፡ደስ፡
ይለው፡ዘንድ፡መጥቷልና፡ከልጆቹም፡መን
ፈሳዊ፡ሹመት፡የሚሾም፡ወይም፡አለቃ፡
የሚሆን አይታጣም፡ከገዳማቱም፡የመንፈስ፡
ቅዱስ፡ፍሬ፡አይታጣም።

፯፡ አባ፡ብንያሚንም፡ልጆቹ፡ብፁዓን፡ናቸው፡
አለ፡ኪሩብም፡እንዲህ፡አለ፡ብፁዓንስ፡
የሚባሉ፡ትእዛዞቹን፡ጠብቀው፡ፍለጋውን፡
ቢከተሉ፡እነርሱ፡ከእርሱ፡ጋር፡አሁን፡
በአለበት፡ክብር፡ውስጥ፡ይሆናሉ፡ትእዛ
ዞቹን፡ቢተላለፉ፡ግን፡ከእርሱ፡ጋር፡ዕድል፡
ፈንታ፡አይኖራቸውም።

፰፡ አባ፡ብንያሚንም፡ኪሩብን፡እንዲህ፡አለው፡
ጌታዬ፡ሆይ፡በዚህ፡ነገር፡በልጆቹ፡ላይ
ተስፋ፡የሚያስቆርጥ፡ነገር፡አትናገር፡ነገር፡
ግን፡ በሰብል ፡ውስጥ፡አንዲት፡ ቅንጣት፡
የተረፈች፡እንደሆነ፡እግዚአብሔር፡በው
ስጥዋ፡በረከቱን፡ያደርጋል። እንዲሁም፡
የፍቅር፡ቅንጣት፡በውስጣቸው፡የተገኘ፡
እንደሆነ፡እግዚአብሔር፡ከመንግሥቱ፡እን
ደማያርቃቸው፡እኔ፡አምናለሁ።

፱፡ ከአረጋዊው፡አባ፡መቃርስ፡ርኅራኄ፡የተነሣ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ብንያሚን፡አደነቀ፡
መልአኩ፡ኪሩብ፡እንዳዘዘውም፡ያንን፡
ሥርዓት፡ጽፎ፡ለዘወትር፡መታሰቢያ፡ይሆን፡
ዘንድ፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡አኖረው።

፲፡ ዕድሜው፡በደረሰ፡ጊዜ፡ዕረፍቱ፡በዚች፡ቀን፡
ይሆን፡ዘንድ፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ለመነው፡እንዲሁም፡
ሆነለት። ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡
ይሁን፡ እኛንም፡በጸሎቱ፡ይማረን፡በረ
ከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለቅዳሴ፡ቤትከ፡በእደ፡ብንያሚን፡ዘኮነ። የማነ፡አምላክ፡ምስሌሁ፡እንዘ፡ይቀብዕ፡ሜሮነ። ውሳጤ፡መቅደስከ፡ዛቲ፡መቃርዮስ፡አቡነ። ኢይባእ፡በትእግልት፡ኪሩብ፡ወሰነ። ዘቦ፡ትዕቢተ፡ወዘቦ፡ህልያነ።

፲፩፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አባ፡እንድራኒቆስ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡እምኍ
ልቆሙ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፴ወ፯።

፲፪፡ ወኮነ፡ዝንቱ፡አብ፡ማእምረ፡ወመሐሬ፡
እስመ፡ውእቱ፡ተምህረ፡መጻሕፍተ፡ቤተ፡

፲፩፡ በዚችም፡ዕለት፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡
ሠላሳ፡ሰባተኛ፡የሆነ፡የእስክንድርያ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡አባ፡እንድራኒቆስ፡አረፈ።

፲፪፡ ይህ፡አባት፡የሚራራ፡አዋቂ፡ሆነ፡እርሱ፡
የቤተ፡ክርስቲያንን፡መጻሕፍት፡ተምሮ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ፡ ወውእቱ ፡ ወልደ ፡ እኅወ ፡
አቡሁ፡ለመኰንነ፡እስክንድርያ፡ወበእንተ፡
ሢመቱ፡ወዕበየ፡ክብሩ፡ወቤቱ፡ኢየኀድር፡
ውስተ ፡ አድባር ፡ በከመ ፡ ኮኑ ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት፡ ዘእምቅድሜሁ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡
ውስተ፡አድባር፡አላ፡ኮነ፡ዘየኀድር፡ውስተ፡
ቤቱ ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ በኵሉ ፡ መዋ
ዕሊሁ።
፲፫፤ ወተሠይመ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ በ፲ቱ ፡ ዓመተ ፡
መንግሥቱ ፡ ለሕርቃል ፡ ንጉሠ ፡ ሮም ፡ በ፱፻
ወ፴ወ፫ቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለእስክ
ንድር ፡ ንጉሥ ፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡
አብ ፡ ተንሥአ ፡ ክስራን ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡
ዘያመልክ፡ፀሐየ፡ወአስተጋብአ፡ሠራዊቶ፡
ዘኮኑ፡ብዙኃነ፡ወዐገቶሙ፡ለብሔረ፡ሶርያ፡
ወለፍልስጥዔም ፡ ወአመዝበሮሙ ። ወእ
ምዝ፡ አገታ ፡ ለብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወበጽሐ ፡
ኀበ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወኮኑ ፡ በዓውደ ፡
፯፻ት፡አድባራት፡ዘውስቴቶን፡መነኰሳት፡
ወእሉ፡ ምሉዐን፡ እምንዋይ ፡ ወይትፌግዑ ፡
ወበእንተዝ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥል
ጣነ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወአመዝበረ ፡ አድባራ
ቲሆሙ፡ወኪያሆሙኒ፡ቀተሎሙ፡ወአልቦ፡
ዘተርፈ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅዳጣን ፡ እለ ፡ ጐዩ ፡
እምኔሁ ፡ ወአምሠጡ ፡ ወማህረከ ፡ ኵሎ ፡
ንዋዮሙ።
፲፬፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ሰብአ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡
ዘገብረ ፡ ክስራ ፡ ንጉሥ ፡ አርኃዉ ፡ ሎቱ ፡
አንቀጸ ፡ ሀገር ፡ ወርእየ ፡ በሕልሙ ፡ ከመ ፡
ዘይቤሎ ፡ ናሁ ፡ መጠውክዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡
ውስተ ፡ እዴከ ፡ ወኢታንህላ ፡ አላ ፡ ቅት
ሎሙ፡ ለጽኑዓን ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ዓማ
ፅያን ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ ወሶቤሃ ፡
ነሥአ፡ ለንጉሠ ፡ ሀገር ፡ ወዓሠሮ ። ወይ
ቤሎሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ያምጽኡ፡
ሎቱ፡ወራዙተ፡ጽኑዓነ፡እለ፡መዋዕሊሆሙ፡
እምነ ፡ ፲ወ፰ ዓመት ፡ እስከ፡ ፶ ዓመት ፡
ወዘቦ፡ጽንዕ፡እምነ፡፵እስከ ፡ ፶ዓመት ፡
ወአነ፡ እሁቦሙ፡ለለ፩ዱ፡፳ዲናረ፡ወርቅ።

፲፭፤ ወመሰሎሙ፡እሙነ፡ወወጽኡ፡እምኀቤሁ፡

አልና ፡ እርሱም ፡ ለእስክንድርያው ፡ ገዥ ፡
የአጎቱ፡ልጅ፡ነው፡ከእርሱ፡በፊት፡የነበሩ፡
ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በገዳማት ፡ እንደሚኖሩ ፡
ስለ፡ቤቱና፡ስለ፡ክብሩ፡ታላቅነት፡በዘመኑ፡
ሁሉ፡በገዳም፡የሚኖር፡አልሆነም፡በእስክ
ንድርያ፡ከተማ፡ባለው፡ቤቱ፡የሚኖር፡ሆነ፡
እንጂ።

፲፫፤ ይህ ፡ አባት ፡ ሕርቃል ፡ በነገሠ ፡ በዐሥር ፡
ዓመት ፡ ከእስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡
በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡
ተሾመ ፡ በዘመኑም ፡ ፀሐይን ፡ የሚያመልክ ፡
የፋርስ፡ንጉሥ፡ክስራን፡ተነሣ፡ብዙ፡የሆኑ፡
ሠራዊቱንም፡ሰበሰበ፡የሶርያንና፡የፍልስጥ
ኤምን ፡ አገሮች ፡ ከበባቸውና ፡ ዘረፋቸው ።
ከዚህም፡በኋላ፡ግብጽን፡ከበባት፡ወደ፡እስ
ክንድርያም ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡ በዙሪያዋም ፡
ሰባት ፡ መቶ ፡ ገዳማት ፡ አሉ ፡ በውስጣ
ቸውም፡ መነኰሳትን ፡ የተመሉ ፡ ነበሩ ፡
እነርሱም ፡ ገንዘብ፡ ያላቸው ፡ በተድላ ፡ የሚ
ኖሩ፡ናቸው፡ስለዚህም፡በነርሱ፡ላይ፡እግዚ
አብሔር፡ሥልጣንን፡ሰጥቶት፡ገዳማቱን፡
አፈረሰ፡እነርሱንም፡ገደላቸው፡ከእርሱ፡
ሸሽተው፡ ከአመለጡ ፡ ከጥቂቶች ፡ በቀር ፡
የተረፈ ፡ የለም ፡ ገንዘባቸውንም ፡ ሁሉ፡
ማረከ።
፲፬፤የእስክንድርያ፡ሰዎችም፡ንጉሥ፡ክስራ፡ያደ
ረገውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የከተማውን ፡ በር ፡
ከፈቱለት ፡ እርሱም ፡ ይቺን ፡ አገር ፡ በእጅህ ፡
አሳልፌ ፡ ሰጥቻታለሁ ፡ አታፍርሳት ፡ በው
ስጧ ፡ ያሉትን ፡ ብርቱዎች ፡ ግደላቸው ፡
ዓመፀኞች ፡ ናቸውና ፡ እንደሚለው ፡ በሕ
ልሙ ፡ አየ ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የሀገሩን ፡
ንጉሥ ፡ አሠረው ፡ የሀገሩንም፡ሰዎች ፡
እንዲህ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ ሀገሪቱን ፡
ይጠብቋት፡ዘንድ፡በጦር፡ሠራዊት፡አደራጃ
ቸዋለሁና ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከዐሥራ ፡ ስም
ንት፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ የሆኑትን ፡
ወጣቶች ፡ ብርታት ፡ ያላቸው ፡ የአርባና ፡
የሃምሳ ፡ ዓመት ፡ የሆኑትን ፡ እንድትሰበስ
ቡልኝ፡እኔም፡ለየአንዳዱ፡ደመወዙን፡ሃያ፡
ሃያ፡የወርቅ፡ዲናር፡እሰጠዋለሁ፡አላቸው።
፲፭፤እነርሱም፡እውነት፡መሰላቸው፡ከእርሱም፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፭ ዕደው፡ ወአኀዘ፡ ይጽሐፉ፡ ኍልቆሙ፡
ለኵሎሙ፡ ወእሙንቱሰ፡ ይሔልዩ፡ ከመ፡
ይነሥኡ፡ ወርቀ፡ ወሶበ፡ ተፈጸመ፡ ኆል
ቈቶሙ፡ቀተሎሙ፡ለኵሎሙ፡በሰይፍ።

፲፮፡ ወእምዝ፡ ዐርገ፡ ኀበ፡ ላዕለይ፡ ግብጽ፡
ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ኒቅዮስ፡ ወሰምዐ፡ ከመ፡ ቦ፡
በህየ፡ በዓታት፡ ወአድባራት፡ ወመካናት፡
ዘውስቴቶን፡ ፯፻ መነኰሳት፡ እኩያነ፡
ምግባር፡ ለእሉኒ፡ ለኵሎሙ፡ ቀተሎሙ፡
በሰይፍ።

፲፯፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ህርቃል፡ንጉሠ፡ሮሜ፡ዘገብረ፡
ክስራ፡ንጉሠ፡ፋርስ፡አስተጋብአ፡ሠራዊቶ፡
ወሖረ፡ ኀቤሁ፡ ወቀተለ፡ ኵሎ፡ ሠራዊቶ፡
ወአመዝበረ፡ሀገሮ።

፲፰፡ ወገድሉሰ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ እንድራኒቆስ፡
ዘኮነ፡ ሠናየ፡ ፈድፋደ፡ ወነበረ፡ ዲበ፡
መንበረ፡ሢመቱ፡፯ተ፡ዓመተ፡ወአሥመሮ፡
ለእግዚአብሔር፡ ወአዕረፈ፡በሰላም፡በ፫፻፴
ወ፯ዓመተ፡ ሰማዕታት፡ እምቅድመ፡ መን
ግሥተ፡ተንባላት፡በብሔረ፡ግብጽ።

፲፱፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡
ይምሐረነ፡ በጸሎተ፡ ኵሎሙ፡ ቅዱሳን፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዘንድ፡ ስምንት፡ ሺህ፡ ሰዎች፡ ወጥተው፡
የሁሉንም፡ቍጥራቸውን፡ምዝገባ፡ጀመሩ፡
እነርሱ፡ ግን፡ ወርቅ፡ የሚቀበሉ፡ ይመስ
ላቸው፡ ነበር፡ ምዝገባቸውም፡ በተፈጸመ፡
ጊዜ፡ሁሉንም፡በሰይፍ፡ገደላቸው።

፲፮፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወደ፡ ላይኛው፡ ግብጽ፡
ወጥቶ፡ ወደ፡ ኒቅዮስ፡ ደረሰ፡ በዚያም፡
ገዳማት፡ በውስጣቸው፡ ሰባት፡ መቶ፡
ሥራቸው፡ ክፉ፡ የሆነ፡ መነኰሳት፡ በዋሻ
ዎችና፡ በቦታዎች፡ ሁሉ፡ እንዳሉ፡ ሰማ፡
እነርሱን፡ሁሉንም፡በሰይፍ፡ገደላቸው።

፲፯፡ የሮም፡ ንጉሥ፡ ህርቃልም፡ የፋርስ፡ ንጉሥ፡
ክስራ፡ያደረገውን፡በሰማ፡ጊዜ፡ሠራዊቱን፡
ሰብስቦ፡ወደርሱ፡ሔደ፡የክስራን፡ሠራዊት፡
ሁሉንም፡ገደለ፡ሀገሩንም፡አጠፋ።

፲፰፡ የዚህ፡ አባት፡ እንድራኒቆስ፡ ገድል፡ ግን፡
እጅግ፡ ያማረ፡ ነበረ፡እግዚአብሔርንም፡
አገልግሎ፡ በሰላም፡ አረፈ፡ ከዓመተ፡
ሰማዕታት፡ ሦስት፡ መቶ፡ አርባ፡ ሰባት፡
እስላሞች፡በግብጽ፡ከመንገሣቸው፡በፊት፡
በመንበረ፡ሢመቱም፡ሰባት፡ዓመት፡ኖረ።

፲፱፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና።ይሁን፡እኛንም፡
በቅዱሳን፡ ሁሉ፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ ለዘ
ላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ እብል፡ ለእንድራኒቆስ፡ ግሡጽ። በትምህርተ፡ መንፈስ፡ ምሉዕ፡ ወአኮ፡ ሕጹጽ። ሱባዔ፡ ዓመታት፡ ፈጺሞ፡ በዲበ፡ መንበሩ፡ ሕኑጽ። ፈለሰ፡ ዮም፡ እምዓለመ፡ ጽልመት፡ ወዳኅፅ። እምቅድመ፡ ይንግሡ፡ ተንባላት፡ በግብጽ።

፳፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አባ፡
ብንያሚን፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘሀገረ፡ እስክን
ድርያ፡ ወውእቱ፡ እምኍልቆሙ፡ በአበው፡
ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፴ወ፰ቱ።

፳፩፡ ወዝንቱ፡ አብ፡ እምሰብአ፡ ሀገረ፡ እስክን
ድርያ፡ ወባርስጥ፡ እምነ፡ ብዑላኒሃ፡ ለሀገር፡
ወመንኰሰ፡ እምንእሱ፡ ኀበ፡ ፩ ብእሲ፡
ቅዱስ፡ ዘስሙ፡ ቴዎናስ፡ በውስተ፡ ደብር፡
ዘምዕራበ፡ እስክንድርያ፡ ወኮነ፡ ወትረ፡
ይልሕቅ፡ በምግባረ፡ ሠናይ፡ ወተምህረ፡
መጻሕፍተ፡ቤተ፡ክርስቲያን።

፳፪፡ ወበአሐቲ፡ ሌሊት፡ ርእየ፡ ራእየ፡ ዘከመ፡
ይቤሎ፡ ተፈሣሕ፡ አ፡ ብንያሚን፡ እስመ፡

፳፡ በዚችም፡ ዕለት፡ የከበረ፡ አባት፡ የእስክን
ድርያ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ አባ፡ ብንያሚን፡ አረፈ፡
እርሱም፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ሠላሳ፡
ስምንተኛ፡ነው።

፳፩፡ ይህም፡ አባት፡ ከእስክንድርያ፡ ባርስጥ፡
ከምትባል፡መንደር፡ከሀገሪቱ፡ከበርቴዎች፡
ወገን፡ ነው፡ ከእስክንድርያ፡ ምዕራብ፡
ከምትገኝ፡ ገዳም፡ ውስጥ፡ ስሙ፡ ቴዎናስ፡
ከሚባል፡ከአንድ፡ቅዱስ፡ሰው፡ዘንድ፡ከታ
ናሽነቱ፡ጀምሮ፡መነኰሰና፡የቤተ፡ክርስቲ
ያንን፡ መጻሕፍት፡ ተማረ፡ ሁልጊዜ፡ በበጎ፡
ሥራ፡ያድግ፡ነበር።

፳፪፡ በአንዲት፡ ሌሊትም፡ ብንያሚን፡ ሆይ፡ ደስ፡
ይበልህ፡ በሃይማኖት፡ በትር፡የክርስቶስን፡

www.ethiopianorthodox.org

አንተ ፡ ትርዕዮሙ ፡ በበትረ ፡ አሚን ፡ ለመርዔተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወነገሮ ፡ ለመምህሩ ፡ ዘንተ፡ ራእየ፡ ወይቤሎ፡ መምህሩ፡ ተዓቀብ፡ እምሰይጣናት ፡ ከመ ፡ ኢያስሕቱከ ፡ በትዕቢት ፡ ውእቱኒ ፡ ወሰከ ፡ ዲበ ፡ ትሩፋቲሁ፡ ትሩፋተ።

፳፫፤ ወእምዝ ፡ ነሥአ ፡ መምህሩ ፡ ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ እንድራኒቆስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወነገሮ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ ወልዱ ፡ ብንያሚን ፡ ውእቱኒ ፡ ሤሞ ፡ ቀሲስ ፡ ወረሰዮ ፡ መጋቤ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይሜግባ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሠናይ ፡ ምግብና ፡ እስከ፡ አዕረፈ፡ አባ፡ እንድራኒቆስ፡ ወእምዝ፡ ተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዝንቱ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ወበጽሖ ፡ ምንዳቤ ፡ ዐቢይ ፡ በጊዜ፡ሢመቱ።

፳፬፤ ወእምቅድመ ፡ ይብጻሕ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዐቢይ ፡ ምንዳቤ ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአጠየቆ ፡ ኵሎ ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሁ ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይጕየይ ፡ ውእቱ ፡ ወኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ወሶቤሃ ፡ ቀደሰ ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ ወመጠዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ፡ ወአዘዞሙ፡ ከመ ፡ ይጽንዑ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት፡ ርትዕት ፡ ወአጠየቆሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘይከውን ፡ በከመ፡ተጠየቀ፡እምኀበ፡መልአክ።

፳፭፤ ወእምዝ ፡ ፈነወ ፡ መልእክታተ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወኀበ ፡ ሊቃናተ ፡ አድባራት፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይጕየዩ ፡ ወውእቱ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ውስተ፡ ደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወእምህየ ፡ ኀበ፡ላዕላይ፡ግብጽ።

፳፮፤ ወእምድኅረ ፡ ወጽአ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ እምሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ በጽሐ ፡ መኰንን ፡ ዘውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እምኀበ ፡ ሕርቃል ፡ ንጉሠ ፡ ሮም ፡ ወኮነ ፡ ሥሉጠ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኰነኖሙ ፡ ለብዙኃን ፡ መሐይምናን ፡ ወአኀዞ ፡ ለእኀወ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ዘስሙ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ ወኰነኖ ፡ ወአውዓዮ ፡ ውስተ ፡ ገበዋቲሁ ፡ በእሳት ፡ ወእምዝ፡አሥጠሞ፡ውስተ፡ባሕር።

በጎች ፡ ትጠብቃቸዋለህና ፡ የሚለውን ፡ ራእይ፡ አይቶ ፡ ለመምህሩ ፡ ነገረው ። መምህሩም ፡ ሰይጣናት ፡ በትዕቢት ፡ እንዳያስቱህ ፡ ተጠበቅ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ በትሩፋቱ ፡ ላይ ፡ ትሩፋትን ፡ ጨመረ።

፳፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መምህሩ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ አባ ፡ እንድራኒቆስ ፡ ወሰደውና ፡ ልጁ፡ ብንያሚን ፡ ያየውን ፡ ራእይ ፡ ነገረው ፡ እርሱም ፡ ቅስና ፡ ሾመውና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አስተዳዳሪ ፡ አደረገው፡ አባ ፡ እንድራኒቆስም ፡ እስከ ፡ አረፈ ፡ ድረስ ፡ በበጎ ፡ አስተዳደር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን፡ እየአስተዳደረ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜም ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት።

፳፬፤ በእርሱ ፡ ላይም ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ተገልጦ ፡ ከእርሱ ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አስረዳው ፡ እርሱም ፡ እንዲሸሽ ፡ ኤጲስቆጶሳቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንዲሸሹ ፡ አዘዘው ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ቀድሶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ አቀበላቸው ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲጸኑ ፡ አዘዛቸው ፡ እርሱ ፡ ከመልአኩ ፡ እንደተረዳ ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ፡ አስረዳቸው።

፳፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኤኢጲስቆጶሳቱ ፡ ሁሉ፡ ወደ ፡ ገዳማት ፡ አለቆችም ፡ መልእክቶችን ፡ ላከ፡ እንዲሸሹም ፡ አዘዛቸው ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ በረሀ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ሔደ።

፳፮፤ አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከሮም ፡ ንጉሥ ፡ ከሕርቃል ፡ ዘንድ ፡ የተሾመ ፡ መኰንን ፡ መጣ ፡ እርሱም ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ የደረበ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሠለጠነ ፡ ነው ። ብዙዎች፡ ምእመናንንም ፡ አሠቃያቸው ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ ሚናስ፡ የሚባል ፡ የአባ ፡ ብንያሚንንም ፡ ወንድም ፡ ይዞ ፡ አሠቃየው ፡ በጐኖቹም ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ጨምሮ ፡ አቃጠለው፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ አሠጠመው።

www.ethiopianorthodox.org

፺፯፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ርእየ ፡ ሕርቃል ፡ ንጉሥ ፡ በንዋሙ ፡ ከመ ፡ ዘይቤሎ ፡ ናሁ ፡ ይመጽኡ ፡ ላዕሌከ ፡ ሕዝብ ፡ ብዙኃን ፡ ግዙራን ፡ ወይነግሡ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወመሰሎ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ አይሁድ ፡ ወአጠየቆሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ዐርካኒሁ ፡ ዘንተ ፡ ራእየ ፡ ወራእዩሰ ፡ ኮነት ፡ በእንተ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለተንባላት ፡ ወሶቤሃ ፡ በጽሑ ፡ ተንባላት ፡ እምድረ ፡ ያትሮብ ፡ ወነግሡ ፡ በምድረ ፡ ሶርያ ።

፺፰፤ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ መጽአ ፡ ኡመር ፡ ወልደ ፡ አጽ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ወነግሠ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወነበረ ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወአንሀላ ፡ ወአውዓየ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙኃተ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘኮነት ፡ ኀበ ፡ ጽንፈ ፡ ባሕር ፡ ዘዕውቅት ፡ ዘመትሕተ ፡ ምድር ፡ ወከማሁ ፡ አውዓዮሙ ፡ ለአድባራት ፡ ብዙኃት ፡ እለ ፡ የዓውዳሃ ፡ ለሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወማህረከ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮን ፡ ዘውስቴቶን ።

፺፱፤ ወእምዝ ፡ ነሥአ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ አሕማራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ወአብአ ፡ እዴሁ ፡ ውስተ ፡ ሣፁን ፡ ወረከበ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ወአእሚሮ ፡ ከመ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ አንበሮ ፡ በክብር ፡ ውስተ ፡ ሐመር ።

፻፤ ወኡመርሰ ፡ ወልደ ፡ አጽ ፡ ሶበ ፡ አእመረ ፡ ግብሮ ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ ወበእንተ ፡ ምንት ፡ ጐየ ፡ ጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ መልእክተ ፡ ወፈነወ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ነዓ ፡ ወኢትፍራህ ፡ መግቦሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ወለአብያተ ፡ ክርስቲያናቲከ ። ወመጽአ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ እምኀበ ፡ ጐየ ፡ በ፲ቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሕርቃል ፡ ወበ፫ቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለተንባላት ፡ ወአክበሮ ፡ ኡመር ፡ ወልደ ፡ አጽ ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ ክብረ ፡ ዐቢየ ፡ ወአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ የሀብዎ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቲሁ ፡ ወኵሎ ፡ ንዋያቲሆን ፡ ወምድሮሙ ፡ ለካህናቲሁ ።

፻፩፤ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ጸሊ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ አሐውር ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ምዕራብ ፡ ከመ ፡ እንግሥ ፡ ላዕለ ፡ ፭ቱ ፡ አህጉረ ፡ ወሶበ ፡ ገባእኩ ፡ እገብር ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ ዘትፈቅድ ፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡

፺፯፤ በእነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ንጉሥ ፡ ሕርቃል ፡ በሕልሙ ፡ እነሆ ፡ ግዙራን ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ በላይህ ፡ መጥተው ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይነግሣሉ ፡ የሚለውን ፡ ራእይ ፡ አየ ፡ ለንጉሡም ፡ አይሁድ ፡ እንደሆኑ ፡ መስሎት ፡ ነበር ፡ ለወዳጆቹ ፡ ይህን ፡ ራእይ ፡ አስረዳቸው ፡ ራእዩ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እስላሞች ፡ መንግሥት ፡ የሆነች ፡ ናት ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ያትሮብ ፡ ከሚባል ፡ ምድር ፡ መጥተው ፡ በሶርያ ፡ ምድር ፡ ነገሡ ።

፺፰፤ በዚያንም ፡ ወቅት ፡ የአጽ ፡ ልጅ ፡ ኡመር ፡ መጥቶ ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያም ፡ ሒዶ ፡ አፈረሳት ፡ ብዙዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ አቃጠለ ፡ ከታችኛው ፡ ምድር ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ያለች ፡ የታወቀች ፡ የወንጌላዊ ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ እንዲሁም ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ገዳማትን ፡ አቃጠለ ፡ በውስጣቸው ፡ ያለ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ማረከ ።

፺፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃው ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኒቱን ፡ መርከቦች ፡ ወሰደ ፡ እጁንም ፡ ወደ ፡ ሣጥን ፡ አስገብቶ ፡ ሲዳስስ ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ሥጋ ፡ አገኘ ፡ ታላቅ ፡ እንደሆነም ፡ አውቆ ፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ በክብር ፡ አስቀመጠው ።

፻፤ ወልደ ፡ አጽ ፡ ኡመር ፡ ግን ፡ የአባ ፡ ብንያሚንን ፡ ሥራ ፡ ስለምን ፡ እንደሸሸም ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ መልእክትን ፡ ጻፈለት ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ ና ፡ አትፍራ ፡ ወገኖችህን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ አስተዳድራቸው ። አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ሕርቃል ፡ በነገሠ ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ እስላሞች ፡ በነገሡ ፡ በሰባት ፡ ዓመት ፡ ከሸሸበት ፡ ቦታ ፡ መጣ ፡ ወልደ ፡ አጽ ፡ ኡመርም ፡ አባ ፡ ብንያሚንን ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ አከበረው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱንና ፡ ገንዘባቸውንም ፡ የካህናቱንም ፡ ምድራቸውን ፡ እንዲሰጡት ፡ አዘዘለት ።

፻፩፤ በአምስቱ ፡ ሀገሮች ፡ ላይ ፡ እነግሥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አገር ፡ እሔዳለሁና ፡ ሒደህ ፡ ስለእኔ ፡ ጸልይልኝ ፡ በተመለስኩም ፡ ጊዜ ፡ የምትሻውን ፡ ሁሉ ፡ አደርግልሃለሁ ፡ አለው ፡

እግዚአብሔር ፡ ያርትዕ፡ ፍኖተከ ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ፡ዘይከውን፡ላዕሌሁ።

፴፪፤ ወሶቤሃ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያቅርቡ ፡ ሎቱ ፡ አሕማረ ፡ ወይሑር ፡ ወአስተዳለዉ ፡ አሕማራተ፡ውስተ፡መርሶ፡ወለይእቲ፡ሐመር፡ ዘውስቴታ፡ርእሱ፡ለቅዱስ፡ማርቆስ፡ወን ጌላዊ፡ወሰሐብዋ፡በአሕባል፡ወኢወጽአት፡ እመርስ ፡ ወተጋብኡ ፡ ኵሎሙ፡ ኖትያት ፡ ወሰሐብዋ፡ወኢያንቀልቀለት፡እመካና።

፴፫፤ ወፈርሀ ፡ ሊቀ ፡ ሐመር ፡ ወነገሮ ፡ ለኡመር ፡ በእንተ፡ይእቲ፡ሐመር፡ዘውስቴታ፡ርእሱ፡ ለቅዱስ፡ማርቆስ፡ወይቤ፡ኡመር፡ኅድግዋ፡ ወነገሮ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ ዘንተ ፡ ወአስተ ርአዮ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ በሕልም ፡ ወይቤሎ ፡ አስተዳሉ ፡ ሊተ ፡ መካነ።

፴፬፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ተነሥአ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወአጠየቆ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ዘውስተ ፡ ሐመር ፡ ርእሱ ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወእምዝ ፡ ነሥአ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ለርእሰ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ እምውስተ ፡ ሐመር ፡ ወሶቤሃ ፡ ወጽአት ፡ ይእቲ፡ሐመር፡እመርስ፡መኰንንኒ፡ርእዮ፡ ዘንተ ፡ አንከረ ፡ ፈድፋደ ፡ ወወሀቦ ፡ ለአባ ፡ ብንያሚን ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ወአዘዞ፡ ከመ ፡ ይሕንፅ ፡ ሎቱ ፡ ቤተ ፡ክርስቲያን ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ፡ውእቱኒ፡ሐነፀ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ሠናይተ ፡ ወአንበረ ፡ ውስቴታ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ፡ማርቆስ፡ወርእሶ።

፴፭፤ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ብንያሚን ፡ መስተ ጋድለ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ ምህሮ ፡ አረማ ውያን፡ወሚጠሙ፡ለብዙኃን፡እምኔሆሙ፡ ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወአጽንዖሙ።

፴፮፤ ወበመዋዕሊሁ፡ለዝንቱ፡አብ፡አምጽአ፡እግ ዚአብሔር ፡ ረሀበ ፡ ዐቢየ ፡ ጥቀ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ፡ አህጉር ፡ ዘኢኮነ ፡ ከማሁ ፡ እምቅ ድሜሁ፡ወሞቱ፡በረሀብ፡ብዙኃን፡ሰብእ፡ ዘአልቦ፡ኍልቍ፡ወኮኑ፡ ግዱፋነ፡ውስተ፡ መራኅብተ፡ሀገር፡ወምሥያጣት።

፴፯፤ ወእምዝ ፡ ደወየ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ እግሮ ፡ መጠነ ፡ ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡

አባ ፡ ብንያሚንም ፡ እግዚአብሔር ፡ መንገ ድህን፡ያቀናልህ፡አለው፡በእርሱ፡ላይ፡የሚ ሆነውንም፡ሁሉ፡ነገረው።

፴፪፤ በዚያን፡ጊዜም፡መርከቦቹን፡እንዲያቀርቡ ለትና ፡ እንዲሔድም ፡ ፈለገ ፡ በወደቡም ፡ ውስጥ፡ መርከቦችን፡አዘጋጁለት፡ያቺንም፡ የወንጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ ራስ ፡ በውስጧ ፡ ያለበትን ፡ መርከብ፡ በገመድ፡ አሥረው ፡ ጐተቷት ፡ ግን፡ አልወጣችም ፡ መርከበ ኞችም ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ቢስቧት ፡ ከቦታዋ፡አልተንቀሳቀሰችም።

፴፫፤ የመርከቡም፡ሹም፡ፈራ፡በውስጧ፡የቅዱስ፡ ማርቆስ ፡ ራስ ፡ ስለ ፡ አለባት ፡ ስለዚያች ፡ መርከብ ፡ ለኡመር ፡ ነገረው ፡ ኡመርም ፡ ለአባ፡ ብንያሚን ፡ ይህን ፡ ነገረው ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስም፡ ለአባ፡ብንያሚን፡በሕልም፡ተገ ለጠለትና፡ቦታ፡አዘጋጅልኝ፡አለው።

፴፬፤ አባ፡ብንያሚንም፡በሰማ፡ጊዜ፡ተነሥቶ፡ ወደ፡መኰንኑ፡ሔደ፡በመርከቡ፡ውስጥ፡ ያለችው፡የከበረ፡የወንጌላዊው፡ማርቆስ፡ ራስ፡እንደሆነች፡አስረዳው፡ከዚህም፡በኋላ፡ አባ፡ብንያሚን፡የከበረ፡ማርቆስን፡ራስ፡ ከመርከብ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቶ ፡ ወሰዳት ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ መርከቢቱ ፡ ከወደቡ ፡ ወጣች፡ገዥው፡መኰንን፡ኡመርም፡ይህን፡ አይቶ፡እጅግ፡አደነቀ፡ብዙ፡ገንዘብም፡ ሰጥቶ፡ለከበረ፡ማርቆስ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ እንዲሠራለት፡አዘዘው፡ያማረች፡ቤተ፡ክር ስቲያንንም ፡ ሠራ ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ሥጋ፡ራሱንም፡በውስጧ፡አኖረ።

፴፭፤ ይህ፡አባት፡ብንያሚንም፡አረማውያንን፡ ስለማስተማር፡እጅግ፡ታጋይ፡ሆነ፡ከእነርሳ ቸውም፡ብዙዎቹን፡ወደ፡ቀናች፡ሃይማኖት መለሳቸው፡አጸናቸውም።

፴፮፤ በዚህ፡አባት፡ዘመንም፡ከእርሱ፡አስቀድሞ፡ እንደርሱ፡ያልሆነ፡እጅግ፡ታላቅ፡የሆነ፡ ረሀብን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ አመጣ። ቍጥር፡የሌላቸው፡ብዙ፡ሰዎችም። ሞቱ፡በሀገሩ፡ሜዳዎችና፡ገበያዎች፡ውስጥ፡ የወደቁ፡ሆኑ።

፴፯፤ ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡ብንያሚን፡ለሁለት፡ ዓመት፡ያህል፡እግሩን፡ታመመና፡በሰላም፡

www.ethiopianorthodox.org

መዋዕለ፡ሢመቱኒ፡፴ወ፱ዓመት።

፴፫፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም ሐረን፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

አረፈ፡የሹመቱም፡ዘመን፡ሠላሳ፡ዘጠኝ፡ ዓመት፡ነው።

፴፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለብንያሚን፡ዘተምህረ፡መጻሕፍተ።እስመ፡ተኀርየ፡ያድምዕ፡ዘእስክንድርያ፡ሢመተ። ወይቤሎ፡ራእየ፡ዘከመ፡ኮነ፡ከሡተ።እስመ፡ትርእዮሙ፡ለመርዔተ፡ክርስቶስ፡አንተ።ብንያሚን፡ብፁዕ፡ ተፈሣሒ፡ትፍሥሕተ።

፴፱፤ ወበዛቲ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ተዝካሩ ፡ ለሚክያስ ፡ ነቢይ።

፵፤ ወለዝንቱ ፡ ነቢይ ፡ ኮነ ፡ ሑረቱ ፡ ሠናየ ፡ እምንእሱ፡ወኵሉ፡ሕዝብ፡ያነክርዎ፡ወያከ ብርዎ፡በእንተ፡ስነ፡ምግባሩ፡ወጽድቁ፡ወበእ ንተዝ፡ሰመይዎ፡ሚክያስ፡ዘበትርጓሜሁ፡ መልአክ፡እስመ፡አርአያሁኒ፡ሠናይ፡ፈድ ፋደ፡ወኵሉ፡ዘይትናገር፡ትንቢት፡ይከውን፡ ወመልአከ፡እግዚአብሔር፡ያስተርኢ፡ሎቱ፡ ወይትናገሮ ። ወሕዝብሰ ፡ ኢይሬእይዎ ፡ ለውእቱ፡መልአክ፡አላ፡ባሕቱ፡ይሰምዑ፡ ቃሎ፡ወቦ፡እምኔሆሙ፡እለ፡ደለዎሙ፡ይር አይዎ፡በከመ፡ጽሑፍ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ መሳፍንት ፡ ወአዕረፈ ፡ አመ ፡ ውርዛዌሁ ፡ ወተቀብረ ፡ ውስተ ፡ ገራህቱ፡ ዘአበዊሁ ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግ ዚአብሔር፡አሜን።

፴፱፤ በዚችም፡ዕለት፡የነቢይ፡ሚክያስ፡መታሰ ቢያው፡ሆነ።

፵፤ የዚህም ፡ ነቢይ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ አካሔዱ፡ መልካም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ማማርና፡ስለ፡ጽድቁ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡ያደን ቁታል፡ያከብሩታል፡ሚክያስም፡ይሉታል፡ ትርጓሜውም ፡ መልአክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መልኩ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነውና ፡ የሚናገ ረውም፡ትንቢት፡እንደተናገረው፡ይሆናል፡ የእግዚአብሔር፡መልአክም፡ተገልጾለት፡ያነ ጋገረው፡ነበር፡ሕዝቡ፡ግን፡ያንን፡መልአክ፡ አያዩትም፡ድምፁን፡ግን፡ይሰማሉ፡ከእርሳ ቸውም፡ያደላቸው፡የሚያዩት፡አሉ፡በመሳ ፍንት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈ ። በጐልማሳ ነቱም ፡ አርፎ ፡ በአባቶቹ ፡ ቦታ ፡ ተቀበረ ፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይህን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለሚክያስ፡ዘአድምዐ፡ፍቅዶ።ምስለ፡ንዑሳን፡ነቢያት፡እንዘ፡ኢይትፈለጥ፡እምተዋሕዶ። እግዚአብሔር፡አምላክ፡ለእለ፡ይገብሩ፡ፈቃዶ።ይረድእ፡ይብል፡ዘአልቦ፡ተባዕዶ።በከመ፡ወላዲ፡ ይረድእ፡ውሉዶ።

***

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፱ለጥር፡በዛቲ፡ዕለት፡አብ፡ ቅዱስ፡አባ፡አብርሃም፡አዕረፈ።

፪፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ አቡሁ ፡ መሐሬ ፡ ዘያፈቅር፡ነዳያነ።

፫፤ ወበመዋዕሊሁ፡ኮነ፡ረሀብ፡ዐቢይ፡ውስተ፡ ብሔር ፡ ግብጽ ፡ ወወሀበ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለነዳያን፡እስመ፡ውእቱ፡ባዕል፡ፈድፋደ፡ወእ ምብዝኀ፡ጽድቁ፡ወተአምኖቱ፡ያመዓቅቡ፡ ኀቤሁ፡ኵሎ፡ፍሬያተ፡ገራውህ፡ዘኵሎን፡

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡ዘጠኝ፡በዚች፡ ቀን፡የከበረ፡አባት፡አባ፡አብርሃም፡አረፈ።

፪፤ የዚህም፡ቅዱስ፡ሰው፡አባቱ፡ድኆችን፡የሚወ ዳቸውና፡የሚራራላቸው፡ነው።

፫፤ በዘመኑም፡በግብጽ፡አገር፡ታላቅ፡ረሀብ፡ሆነ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለድኆች ፡ ሰጠ ፡ እርሱ ፡ እጅግ፡ ባለጸጋ ፡ ነበርና ፡ ከደግነቱና ፡ ከታማ ኝነት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እርሱ ፡ በአለበት ፡ አገር፡ዙሪያ፡ያሉ፡አገሮች፡ሁሉም፡የምድራ

www.ethiopianorthodox.org

አህጉር፡እለ፡የዓውዱ፡ሀገሮ፡ወሶበ፡ጸንዐ፡ ረሀብ ፡ ወሀበ ፡ ለነዳያን ፡ ኵሎ ፡ ፍሬያተ ፡ እክል፡ ዘሀሎ ፡ ዕቁበ ፡ በኀቤሁ ፡ ወእግዚአ ብሔር፡ረሰዮሙ፡ለኵሎሙ፡ከመ፡ኢይትና ገርዎ ፡ ሕሱመ ፡ ቃለ ፡ በእንተ ፡ ፍሬ ፡ ምድ ሮሙ።

፬፤ ወሶበ ፡ ይፌንዉ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ የኃሥሡ ፡ ፍሬያተ ፡ ምድሮሙ ፡ ዘአንበሩ ፡ በኀቤሁ ፡ ይትነሣእ፡ወየሐውር፡ኀቤሆሙ፡እሙንቱኒ፡ ኢይትናገርዎ ፡ ምንተኒ ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡ ይጽ ሕፉ፡ሎቱ፡ከመ፡በጽሐሙ፡ፍሬ፡ምድሮሙ፡ ለለ፩ዱ፡ዘዘዚአሆሙ።

፭፤ ወእሙኒ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ፈራሂተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መሀይምንት ፡ ወቀንአ ፡ ላዕሌሃ ፡ ሰይጣን ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ፩ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ወአስተዋደያ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ ወእሙንቱ፡ዔወውዋ፡ወወሰድዋ፡ኀበ፡ብሔ ሮሙ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሌሊት ፡ ርእየት ፡ ራእየ ፡ ከመ፡ውእቱ፡ብእሲ፡ዘአስተዋደያ፡እሡር፡ በሰናሰለ፡እሳት፡ውስተ፡ሲኦል፡ወይቤላ፡ ነጸርኪኑ ፡ ዘገብረ ፡ ለኪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ፡ተበቀሎ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘአስተዋ ደየኪ፡ይእቲሰ፡ትቤ፡ኢኮንኩ፡ዘእፈቅድ፡ እግዚእየ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ላዕሌሁ፡ሕማም፡ ወምንዳቤ፡ወይቤላ፡ውእቱ፡ዘአስተርአያ፡ አንቲሰ፡ሀለወኪ፡ከመ፡ትግብኢ፡ውስተ፡ ሀገርኪ፡ወትንበሪ፡ውስተ፡ቤትኪ፡ወኮነ፡ ከመዝ።

፮፤ ወሶበ፡ሞተ፡ምታ፡ወኮነ፡አብርሃም፡ዕቤረ፡ ወይእቲ ፡ እሙ ፡ ሐለየት ፡ ታስተዋስቦ ፡ ብእሲተ፡ወኢፈቀደ፡ውእቱ፡ዘንተ፡ወተፈ ሥሐት፡ቦቱ፡እሙ፡ፈድፋደ።

፯፤ ወሶበ፡ኃሠሠ፡ከመ፡ይሑር፡ወይመንኵስ፡ ኀበ ፡ ደብር ፡ ወጽአት ፡ እሙ ፡ ከመ ፡ ታስተፋ ንዎ ፡ አንሥአት ፡ እደዊሃ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወጸለየት፡ወአማሕፀነት፡ወልዳ፡ኀበ፡እግዚ አብሔር ፡ ወትቤ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ተወከፍ ፡ እምኔየ፡ዘንተ፡ቊርባነ።

፰፤ ወሶቤሃ፡ሖረ፡ወአንሶሰወ፡አባ፡አብርሃም፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ደብረ፡አባ፡መቃርስ፡በመዋዕሊሁ፡ለአባ፡ ዮሐንስ፡አበ፡ምኔት፡ወቦአ፡ኀቤሁ፡ወኮነ፡ ሎቱ፡ወልደ፡ፍቁረ፡ወአኀዘ፡ይትጋደል፡

ቸውን ፡ ፍሬ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ያስቀመጡ፡ነበር፡ረሀቡም፡በጸና፡ጊዜ፡ በእርሱ፡ዘንድ፡በአደራ፡የተቀመጠውን፡ እህል፡ሁሉንም፡ለድኖች፡ሰጠ፡እግዚአብ ሔርም፡ስለ፡ምድራቸው፡ፍሬ፡ሁሉንም፡ ክፉ፡ቃልን፡እንዳይናገሩት፡አደረጋቸው።

፬፤ በእርሱ፡ዘንድ፡ያኖሩትን፡የምድራቸውን፡ ፍሬ ፡ ሽተው ፡ ወደርሱ ፡ በሚልኩ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ፡ወደርሳቸው፡ይሔዳል፡እነርሱም፡ በየራሳቸው፡ለያንዳንዱ፡የምድራቸው፡ፍሬ፡ እንደደረሳቸው ፡ አድርገው ፡ ይጽፉለታል ፡ እንጂ፡ምንም፡ምን፡አይናገሩትም።

፭፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ እናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ፡ምእመን፡ናት፡ሰይጣንም፡ቀና ባት፡በአንድ፡ክፉ፡ሰው፡ልቡና፡አድሮ፡ በፋርስ፡ሰዎች፡ዘንድ፡ነገር፡ሠራባት፡እነ ርሱም፡ማርከው፡ወደ፡አገራቸው፡ወሰድ ዋት፡በአንዲት፡ሌሊትም፡ራዕይን፡አየች፡ ያ፡ነገር፡የሠራባት፡ሰው፡በሲኦል፡ውስጥ፡ በእሳት፡ሰንሰለት፡ታሥሮ፡እግዚአብሔር፡ ያደረገልሽን ፡ ተመለከትሽን ፡ ነገር ፡ የሠራ ብሽን፡ያንን፡ሰው፡ተበቅሎታልና፡ይላታል፡ እርሷ፡ግን፡ጌታዬ፡ሆይ፡መከራና፡ሥቃይ፡ በርሱ፡ላይ፡እንዲደርስ፡አልሻም፡ትላለች፡ያ፡ የሚያሳያትም ፡ አንቺ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አገርሽ ፡ ተመልሰሽ፡በቤትሽ፡ትኖሪ፡ዘንድ፡አለሽ፡ ይላታል፡እንዲሁም፡ሆነ።

፮፤ ባሏም፡በሞተ፡ጊዜ፡አብርሃም፡ድኃ፡አደግ፡ ሆነ፡እርሷም፡እናቱ፡ሚስት፡ልታጋባው፡ አሰበች፡እርሱ፡ግን፡ይህን፡አልወደደም፡ እናቱም፡እጅግ፡ደስ፡ተሰኘችበት።

፯፤ ወደ፡ገዳም፡ሒዶ፡ሊመነኵስ፡በፈለገ፡ጊዜ፡ እናቱ፡ልትሸኘው፡ወጣች፡እጆቿንም፡ወደ፡ ሰማይ፡አንሥታ፡በመጸለይ፡ልጇን፡ወደ፡እግ ዚአብሔር ፡ አደራ ፡ አስጠበቀች ። አቤቱ ፡ ጌታዬ፡ይህን፡ቊርባንን፡አድርገህ፡ተቀበለኝ፡ አለች።

፰፤ በዚያንም፡ጊዜ፡አባ፡አብርሃም፡ሔደ፡በአስ ቄጥስ፡በረሀ፡ውስጥ፡ተጕዞ፡በአባ፡ዮሐንስ፡ አበ፡ምኔትነት፡ዘመን፡ወደ፡አባ፡መቃርስ፡ ገዳም፡ደረሰ፡ወደርሱም፡ወደ፡አባ፡ዮሐንስ፡ ገባ፡ተወዳጅ፡ልጅንም፡ሆነለት።በጎ፡ተጋድ

www.ethiopianorthodox.org

ሠናየ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሌሊት ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡
ወተሠጥቀ ፡ ተድባበ ፡ በዓቱ ፡ ወርእዮ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
ወወረደ፡ኀቤሁ፡እንዘ፡ይነብር፡ዲበ፡ሠረገላ፡
ኪሩቤል ፡ ወእሙንቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ይሴብሕዎ ፡
ውእቱኒ ፡ ፈርሀ ፡ ወርዕደ ፡ ወአፍጠነ ፡ ሰጊደ ፡
ወእግዚእነ ፡ ባረኮ ፡ ወዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡
በዐቢይ፡ስብሐት።
፱፡ ወኮነት ፡ ትእምርተ ፡ ዘተሠጥቀት ፡ ውስተ ፡
ተድባበ፡ቤቱ፡እንተ፡ባቲ፡ወረደ፡እግዚእነ፡
ወእስከ ፡ ይእዜ ፡ ሀለወት ፡ ተዝካረ ፡ ከዊና ፡
ወይእቲ ፡ ቅርብት ፡ ለማኅደረ ፡ አቡሁ ፡ መንፈ
ሳዊ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወይእቲ ፡
ትሰመይ ፡ በግቢግ። ወመልአከ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይሔውጾ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ወይከሥት ፡
ሎቱ፡ምሥጢራተ፡ብዙኃተ፡ወያሌብዎ።
፲፡ ወእምዝ፡ሖረ፡ኀበ፡ደብረ፡ኀርዮን፡ወረከቦ፡
ለአባ ፡ ገዓርጊ ፡ በህየ ፡ ወነሥአ ፡ ምስሌሁ ፡
ውስተ ፡ ገዳመ ፡አስቄጥስ ፡ ወኀደሩ ፡ ውስተ ፡
ይእቲ፡በዓት፡እስከ፡አመ፡ዕረፍቶሙ።

፲፩፡ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አበ ፡
ምኔት ፡ አምጽአ ፡ ሰይጣን ፡ ላዕለ ፡ አባ ፡
አብርሃም ፡ ዐቢየ ፡ ደዌ ፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡
ውእቱ ፡ ደዌ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወቀሪቦ ፡
ዕረፍቱ ፡ ሰአሎሙ ፡ ለአኃው ፡ ከመ ፡ ይመ
ጥውዎ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሞ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወእም
ድኅረ ፡ ተመጠወ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤሁ ፡ አቡሁ ፡
መንፈሳዊ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወይቤሎ ፡ ናሁ ፡
ጸውዓከ፡እግዚአብሔር፡ውስተ፡ዐቢይ፡ከብ
ካብ፡ወእምዝ፡አዕረፈ፡በሰላም፡እንዘ፡መዋ
ዕሌሁ ፡ ፹ዓመት ፡ ወበዓቶሙኒ ፡ ሀለወት ፡
እስከ፡ይእዜ፡ወይእቲ፡ዕውቅት።
፲፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረ
ከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ሎንም፡ጀመረ፡በአንዲት፡ሌሊትም፡ራዕይን፡
አየ ፡ የበዓቱ ፡ ጣሪያ ፡ ተሰነጠቀ ፡ የክብር ፡
ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡በኪ
ሩቤል፡ሠረገላ፡ተቀምጦ፡ወደርሱ፡ሲወርድ፡
አየው ፡ ኪሩቤልም ፡ ያመሰግኑት ፡ ነበር ፡ እር
ሱም፡ፈርቶ፡ተንቀጠቀጠ፡ፈጥኖም፡ሰገደ፡
ጌታችንም፡ባረከውና፡በታላቅ፡ክብር፡ወደ፡
ሰማይ፡ዐረገ።
፱፡ጌታችንም፡የወረደባት፡በቤቱ፡ጣሪያ፡የተሠነ
ጠቀችው፡ምልክት፡ሁና፡እስከ፡ዛሬ፡በመታ
ሰቢያነት፡አለች፡እርሷም፡ለመንፈሳዊ፡አባቱ፡
ለአበ፡ምኔቱ፡አባ፡ዮሐንስ፡መኖሪያ፡ቅርብ፡
ናት፡እርሷም፡በግቢግ፡ትባላለች።የእግዚአብ
ሔርም ፡ መልአክ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይጐበኘዋል፡
ብዙ፡ምሥጢራትንም፡ይገልጥለታል፡ያስገነ
ዝበዋልም።
፲፡ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡አብርሃም፡ወደ፡ደብረ፡
ኀርዮን፡ሔደ፡በዚያም፡አባ፡ገዐርጊን፡አግ
ኝቶት፡ወደ፡አስቄጥስ፡ገዳም፡ከእርሱ፡ጋር፡
ወሰደውና፡እስከ፡ዕረፍታቸው፡ጊዜ፡በዚያች፡
በዓት፡ኖሩ።
፲፩፡ አበ፡ምኔቱ፡አባ፡ዮሐንስም፡በአረፈ፡ጊዜ፡
በአባ፡አብርሃም፡ላይ፡ሰይጣን፡ታላቅ፡ደዌ፡
አምጥቶበት፡ዐሥራ፡ስምንት፡ዓመት፡በዚያ፡
ደዌ፡ውስጥ፡ኖረ፡ዕረፍቱም፡በቀረበ፡ጊዜ፡የጌ
ታችንን፡ሥጋና፡ደም፡ያቀብሉት፡ዘንድ፡ወን
ድሞችን፡ለመናቸው፡ከተቀበለም፡በኋላ፡መን
ፈሳዊ፡አባቱ፡አባ፡ዮሐንስ፡ወደርሱ፡መጥቶ፡
እነሆ፡ወደ፡ታላቅ፡ሠርግ፡እግዚአብሔር፡ጠር
ቶሃል፡አለው።ከዚህም፡በኋላ፡ዕድሜው፡ሰማ
ንያ ፡ ዓመት ፡ ሁኖት ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡ በዓታ
ቸውም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የታወቀች ፡ ሁና ፡
ትኖራለች።
፲፪፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአብርሃም፡ዘተሠጥቀ፡ተድባቡ። ለክርስቶስ፡ይርአዮ፡እንዘ፡ይነብር፡ዲበ፡ኪሩቡ። አዕ
ረፈ፡ዮም፡ለንብረተ፡ዓለም፡እምጻሕቡ።በመንፈስ፡ከመ፡ይቤሎ፡ዮሐንስ፡አቡ።እግዚአብሔር፡ጸውዓከ፡
ለዐቢይ፡ከብካቡ።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ዕለት ፡አዕረፉ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡

፲፫፡ በዚችም፡ዕለት፡የከበሩ፡አባቶች፡ጊዮርጊስ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ፡ወኖስሞስ፡ወዲዮስቅርስ፡ዘሮሜ። ወተዘካሮሙ፡ለአባ፡ኪናፎርያ፡ወበጥሪቃ፡ ወጥምያኒ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ትብጽሐነ ፡ ወስ ብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

ኖስሞስና ፡ የሮሜ ፡ ሰው ፡ ዲዮስቅርስ ፡ አረፉ ፡ የአባ፡ኪናፎርያ፡የበጥሪቃና፡የጥምያኒ፡መታ ሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ትድረሰን ፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዘኮንከ ፡ ለሀገረ ፡ ናዝሬት ፡ ጸወነ ። ህየንተ ፡ ሄሮድስ ፡ ዘይሁዳ ፡ አመ ፡ አርኬላዎስ ፡ ኰነነ ። በከመ ፡ ከሠትከ ፡ እግዚኦ ፡ ባህለ ፡ መጻሕፍት ፡ ክዱነ ። ትስብክ ፡ ነዓ ፡ ለፂዉዋን ፡ ግዕዛነ ። ወለቀ፡ሱላን ፡ ትጸጉ፡ርጢነ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ሠርዑ ፡ አበዊነ ፡ መምህራነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ እለ ፡ ቀደሙነ ፡ ሊቃውንት ፡ ዐበይት ፡ ከመ ፡ ይጹሙ ፡ ኵሎሙ ፡ መሐይምናን ፡ እስከ ፡ ምሴት ፡ እንዘ ፡ ኢይጥዕሙ ፡ ምንተኒ ፡ መባል ዕተ ፡ ወበጊዜ ፡ ሠርክኒ ፡ ኢይጥዓሙ ፡ ጥሉላተ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይትበላዕ ፡ በጾም ፡ ዐቢይ።

፪፡ ወምክንያቱሰ ፡ ለዝንቱ ፡ ጾም ፡ ዘሠርዕዎ ፡ አበው ፡ ከመ ፡ ይጹምዎ ፡ ምእመናን ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ምሴት ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ አበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ ቅዱሳን ፡ አዘዙ ፡ በቀኖና ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወጥምቀት ፡ በዕለተ ፡ ረቡዕ ፡ አው ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ይብልዑ ፡ በጽባሕ ፡ ኵሎሙ ፡ መሐይ ምናን ፡ መብልዐ ፡ ዘይትበላዕ ፡ በበዓለ ፡ ጰንጠ ቈስቴ ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ ክልኤቱ ፡ በዓላቲሁ ፡ ለእ ግዚአብሔር።

፫፡ ወከመ ፡ ኢይምሰሎሙ ፡ ለካልአን ፡ ከመ ፡ ንሕነ ፡ ንትፌጋዕ ፡ በፍሥሓ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወኢንግበር ፡ በዓላቲነ ፡ በመብልዕ ፡ ወመስቴ ፡ በከመ ፡ በዓላቲሆሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ወአረሚ ። ወበእንተዝ ፡ አዘዙነ ፡ አበዊነ ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ ንጹም ፡ እሎንተ ፡ ክልኤተ ፡ ዕለታተ ፡ ዘእም ቅድመ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወበዓለ ፡ ጥምቀት ፡ እስመ ፡ እላ ፡ ዕለታት ፡ ህየንቴሆሙ ፡ ለረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ሶበ ፡ ይከውን ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወጥምቀት ፡ ወበዝንቱ ፡ ይትፌጸም ፡ ለነ ፡ ፪ቱ ፡ ግብር ፡ ግብረ ፡ ጾም ፡ ወግብረ ፡ በዓል ፡ ወከመዝ ፡ ሥሩዕ ፡ ውስተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ ያኖሙ ፡ ለግብጻውያን።

፬፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዕለተ ፡ በይረሙን ፡ ዘውእቱ ፡ አስተርእዮ ፡ በዕለተ ፡ እሁድ ፡ አው ፡ በዕለተ ፡ ሰንበተ ፡ አይሁድ ፡ ይጹሙ ፡ በእለተ ፡ ዓርብ ፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥር ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ መብልን ፡ ሳይቀምሱ ፡ ምእ መናን ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ምሽት ፡ ይጾሙ ፡ ዘንድ ፡ ከእኛ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃ ውንት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ሥር ዓትን ፡ ሠሩ ፡ በምሽትም ፡ ቢሆን ፡ በታላቁ ፡ ጾም ፡ ከሚበላው ፡ በቀር ፡ ጥሉላትን ፡ እንዳይቀምሱ።

፪፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ምእመናን ፡ እስከ ፡ ምሽት ፡ እንዲጾሙት ፡ ያዘዙበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የልደትና ፡ የጥምቀት ፡ በዓል ፡ በረቡዕ ፡ ወይም ፡ በዓርብ ፡ ቀን ፡ ቢሆን ፡ በበዓለ ፡ ኀምሳ ፡ የሚበ ላውን ፡ የጥሉላት ፡ መብል ፡ በጥዋት ፡ በመብ ላት ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ በዓሉን ፡ እንዲአከብሩ ፡ የከበሩ ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ አዝዘዋል ፡ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታላላቅ ፡ በዓላቶቹ ፡ ናቸውና።

፫፡ እኛ ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ የሚለን ፡ ለሌሎች ፡ እንዳይመስ ላቸው ፡ እንደ ፡ አይሁድና ፡ እንደ ፡ አረማውያን ፡ በዓል ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ብቻ ፡ እንዳና ደርግ ፡ ስለዚህ ፡ ከልደትና ፡ ከጥምቀት ፡ በዓል ፡ በዋዜማ ፡ ያሉትን ፡ ሁለቱን ፡ ዕለታት ፡ እንድ ንጾም ፡ አዘዙን ፡ የልደትና ፡ የጥምቀት ፡ በዓል ፡ በረቡዕና ፡ በዓርብ ፡ ላይ ፡ በሚሆን ፡ ጊዜ ፡ በረቡዕና ፡ በዓርብ ፡ ፈንታ ፡ እንድንጾማቸው ፡ ይገባልና ፡ በዚህም ፡ ሁለት ፡ ሥራ ፡ ይፈጸም ልናል ፡ የጾም ፡ ሥራና ፡ የበዓል ፡ ማክበር ፡ ሥራ ፡ ነው። እንዲሁም ፡ በግብጻውያን ፡ አብያተ ፡ ክር ስቲያን ፡ የተሠራ ፡ ነው።

፬፡ በይረሙን ፡ በእሑድ ፡ ወይም ፡ በአይሁድ ፡ ሰንበት ፡ ቀን ፡ ቢሆን ፡ ይህም ፡ ጌታ ፡ የተገለጸ በት ፡ ጥር ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ነው ፡ በዋዜማው ፡

www.ethiopianorthodox.org

እምቅድሜሁ፡እስከ፡ምሴት፡በከመ፡ተናገርነ፡ ቅድመ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወበዓለ ፡ ጥምቀት ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ኢይትከሀል ፡ ከመ ፡ ይጹሙ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ዳዕሙ ፡ ይትዓቀቡ ፡ እምነ፡በሊዕ፡ጥሉላተ።

፭፤ ወበዕለተ ፡ በዓለ ፡ ጥምቀት ፡ ይትነሥኡ ፡ እምቅድመ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ወይጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ ወይጠመቁ ፡ ሕፃናትኒ ፡ ከመ ፡ ኢይግድፉ ፡ በማይ ፡ ሶበ ፡ ይጠመቁ ፡ ወይቀድሱ ፡ ካህናት ፡ ቍርባነ ፡ እምቅድመ ፡ ይኩን፡ ጽባሐ ፡ ወይጻኡ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን፡በጽባሕ፡ፈድፋደ፡በከመ፡አዘዙ፡አጋእዝቲነ፡ሐዋርያት፡በቀኖና፡ቅዱስ።

፮፤ ወሕዝበ ፡ መለካውያንሰ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ መኃትው ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወጥምቀት ፡ በዕለተ ፡ ቀዳሚት ፡ አው ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ይሠርዑ ፡ ቅዳሴ ፡ በጊዜ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ ይበልዑ ፡ አውሎግያ ፡ ወይሰትዩ ፡ ማየ ፡ ለእመ ፡ ፈቀዱ ፡ ወእምዝ፡ይነብሩ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያንወይጼልዩ፡ጸሎተ፡ሰዓታት፡ወያነብቡ፡ትንቢታተ ፡ ነቢያት ፡ ዘይደሉ ፡ ለበዓል ፡ ወይጼልዩ ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ በጊዜ ፡ ሠርክ ፡ በውእቱ፡ዕለት፡አመ፡፲ ፡ለወርኀ፡ጥር። ወዝንቱ ፡ ኢኮነ ፡ በከመ ፡ ትእዛዘ ፡ አበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ እስመ ፡ አዘዙ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ በዓለ ፡ ኤጲፋንያ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ አስተርእዮቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ አመ ፡ ፲ለወርኃ ፡ ካኑን ፡ ዳግማይ፡ወርኀ፡በሮም፡ወዝንቱ፡አመ፡፲ወ፩፡ለወርኀ፡ጥር።

፯፤ እስመ ፡ መለካውያንሰ ፡ ይትዓደዉ ፡ ትእዛዘ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ መምህራነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ ይበልዑ ፡ በዕለተ ፡ ልደት ፡ ወጥምቀት ፡ በጽባሕ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ በረቡዕ ፡ ወዐርብ ፡ ዘእንበለ ፡ ይጹሙ ፡ ቅድመ ፡ ህየንቴሁ።

፰፤ ወንሕነኒ ፡ ንሰአሎ ፡ **ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ**፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ያንጽሐነ ፡ እምኵሉ ፡ አበሳነ ፡ ወይክሥት ፡ ለነ ፡ ስብሐተ ፡ መለኮቱ ፡ ውስተ ፡ አልባቢነ ፡ በከመ ፡ አስተርአየ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እስመ ፡ ሎቱ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ወሰጊድ ፡ ምስለ ፡ **አቡሁ ፡ ኄር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፤ መስተሣህል ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ዐርብ፡እስከ ፡ ምሽት ፡ ይጹሙ ፡ አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ ጥሉላት ፡ አይብሉ ፡ የልደትና፡ የጥምቀት ፡ በዓልም ፡ ሰኞ ፡ ቀን ፡ ቢሆን ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ይጾሙ ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፡ ነገር፡ግን፡ጥሉላትን፡ከመብላት፡ይጠበቁ።

፭፤ በጥምቀትም ፡ ዕለት ፡ ከእኩለ ፡ ሌሊት ፡ በፊት ፡ ተነሥተው ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ይጸልዩና ፡ ይጠመቁ ፡ ሕፃናትም ፡ በሚጠመቁ ፡ ጊዜ ፡ በውኃ ፡ እንዳይገድፉ ፡ ካህናቱም ፡ ከመንጋቱ ፡ በፊት ፡ ቀድሰው ፡ ቍርባኑን ፡ ያሳርጉ ፡ እጅግም ፡ ማልደው ፡ በጥዋት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይውጡ ፡ በከበረ ፡ ሥርዓታቸው ፡ ጌቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ እንዳዘዙ።

፮፤ የመለካውያን ፡ ወገኖች ፡ ግን ፡ የልደትና ፡ የጥምቀት ፡ ዋዜማ ፡ በቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በእሑድ ፡ ቀን ፡ ቢሆን ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ይቀድሳሉ ፡ ከወደዱም ፡ የተባረከ ፡ ኅብስት ፡ ተመግበው ፡ ውኃ ፡ ይጠጣሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ካህናቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሁነው ፡ በየሰዓቱ ፡ በመጸለይ ፡ ለበዓሉ ፡ የሚገባውን ፡ የነቢያትን ፡ ትንቢቶች ፡ ያነባሉ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ በምሽት ፡ ይኸውም ፡ ጥር ፡ ዓሥር ፡ ነው ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ይጸልያሉ ፡ ይህም ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ እንዳዘዙት ፡ አልሆነም ። እርሳቸው ፡ የኤጲፋንያን ፡ በዓል ፡ እንዲአከብሩ ፡ አዘዋል ፡ ይኸውም ፡ መድኃኒታችን ፡ የተገለጠበት ፡ ካኑን ፡ በሚባል ፡ በሮም ፡ ሁለተኛ ፡ ወር ፡ በሰባት ፡ ይህም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ነው።

፯፤ መለካውያን ፡ ግን ፡ የከበሩ ፡ አባቶች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ያዘዙትን ፡ ይተላለፋሉ ፡ በልደትና ፡ በጥምቀት ፡ በዓል ፡ ዓርብም ፡ ረቡዕም ፡ ቢሆን ፡ አስቀድመው ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሳይጾሙ ፡ በጥዋት ፡ ተነሥተው ፡ ይበላሉና።

፰፤ እኛንም ፡ ከበደላችን ፡ ያነጻን ፡ ዘንድ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ወንዝ ፡ እንደ ፡ ገለጸ ፡ የጌትነቱን ፡ ክብር ፡ በልቡናችን ፡ ይገልጥልን ፡ ዘንድ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የሆነ ፡ **ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን**፡ እንለምነው ፡ ጌትነት ፡ ክብር ፡ ስግደት ፡ ለእርሱ ፡ ይገባልና ፡ **ከቸር ፡ አባቱ ፡ ጋር ፡ ይቅር ፡** ባይ ፡ **ከሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም** ፡ ጋር ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለጾመ ፡ ዕለት ፡ ዋሕድ። ዘስሙ ፡ ገሀድ። መምህራነ ፡ ሥርዓት ፡ አቀሙ ፡
ለዘይመጽእ፡ ትውልድ። እመባልዕት ፡ ጥሉላት ፡ ወእምነ ፡ ቅሡም ፡ ማዕድ። አንስት ፡ ይትህረማ ፡
ወይጹሙ ፡ ዕድ።

፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ታውብንጦስ፡
ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ተሐፅነ ፡ እምንእሱ ፡
በቤተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ዘይሰመይ ፡
አባ ፡ ታኡና ፡ ወውእቱ ፡ አልበሶ ፡ አልባሰ ፡
ምንኵስና ፡ ወርእዮ ፡ ዘተውህበ ፡ ሎቱ ፡
ጥበብ ፡ ወኃይል ፡ ረሰዮ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡
ወሊቀ ፡ ዘምኔት ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ እስክን
ድርያ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘስሙ ፡ ጤናዲራን ፡
ወኍልቈ ፡ አኃው ፡ መነኮሳት ፡ ዘታሕተ ፡
እዴሁ ፡ ፯፡ ፻ት።
፲፡ ወእምድኅረዝ ፡ ሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ታውብንጦስ ፡
ኤጲስቆጶስ ፡ ወመክብበ ፡ አኃው ፡ እለ ፡
ምስሌሁ ፡ በበይነ፡ ሀውክ ፡ እምኅበ ፡ ንጉሥ ፡
ዐላዊ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ጕየ ፡ ወሖረ፡
ውስተ፡ ደብረ ፡ ሲሐት ፡ ወኀደረ ፡ ኀበ ፡
አሐቲ ፡ ድንግል ፡ ፈራሂተ ፡ እግዚአብሔር ።
ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ቤታ ፡ ብዙኃተ ፡ አዝማነ፡
ወአመ ፡ ቀዳሚሰ፡ በአቱ ፡ ኀቤሃ ፡ ረከባ ፡
እንዘ ፡ ታመልክ፡ ጣዖተ ፡ በእንተ ፡ ፍርሀተ ፡
ንጉሥ፡ ወሜጣ ፡ እምስሕተት ፡ ኀበ ፡ አሚነ ፡
እግዚእነ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት።

፲፩፡ ወእምህየ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ተርኑጥ ፡
ወደብረ ፡ መርኑስ ፡ እንዘ ፡ ይፈቅድ ፡ ከመ ፡
ይስማዕ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለአብያተ፡ ክርስቲያን፡
ወየኀድር ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ደብር ፡ ሰኑየ ፡
ወሠሉሰ፡ ዕለተ ፡ በኀቡእ ፡ እንዘ ፡ ይትቀነይ፡
በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወበትጋሀ ፡ ሌሊት ፡ ወስ
ምዐ፡ ኮኑ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ አኃው ፡ ከመ ፡
ወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ወገብረ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲበ ፡ እደዊሁ ፡
ተአምራተ፡ ወመንክራተ ፡ እስከ ፡ ሜጠሙ ፡
ለብዙኃን ፡ እምነ ፡ ፈያት፡ ወዓማፅያን ፡
ውስተ ፡ ተቀንዮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወረሰዮሙ ፡
መነኮሳተ።
፲፪፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ረሥአ ፡ ወልሕቀ ፡ አእመረ ፡
ዕለተ ፡ ፍልሰቱ ፡ ወመዓዶሙ ፡ ለደቂቁ ፡
ከመ ፡ ይጽንዑ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡

፱፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ አባ ፡ ታውብንጦስ ፡ አረፈ፡
ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ፡ አባ ፡
ታኡና ፡ በሚባል ፡ በሮሜው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ቤት ፡ አደገ ፡ እርሱም ፡ የምንኵስናን ፡ ልብስ ፡
አለበሰው ። መንፈሳዊ ፡ ዕውቀትና ፡ ኃይል ፡
እንደተሰጠው ፡ አይቶ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡
ውጭ ፡ ስሙ ፡ ጤናዲራን ፡ በሚባል፡ ቦታ ፡
ኤጲስቆጶስነት ፡ ሹሞ ፡ የገዳም ፡ አበ ፡
ምኔት፡ አደረገው ፡ በእርሱ ፡ ሥር፡ ያሉ ፡
መነኮሳትም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ናቸው።
፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር፡ ላሉ ፡
መነኮሳት ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡
ታውብንጦስ ፡ ከከሀዲ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥ
ያኖስ ፡ ስለሆነው ፡ ሁከት፡ በሰማ፡ ጊዜ ፡
ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲሐት ፡ ገዳም ፡ ሒዶ፡
እግዚአብሔርን ፡ ከምትፈራ፡ ከአንዲት፡ ድን
ግል ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጠ ። በእርሷ ፡ ቤትም ፡
ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ኖረ ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ
ርሷ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ ስለ ፡
መፍራት፡ ጣዖትን ፡ ስታመልክ ፡ አገኛትና፡
የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስን ፡
ወደ ፡ ማመን ፡ መለሳት።
፲፩፡ ከዚያም ፡ ተርኑጥና ፡ መርኑስ፡ ወደ ፡
ሚባሉ ፡ ገዳማት ፡ ሔደ ፡ የአብያተ ፡ ክርስ
ቲያናትን ፡ ወሬ ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ ፈልጎ ፡
በጾም ፡ በጸሎት ፡ ሌሊትም፡ በመትጋት ፡
እያገለገለ ፡ በአንዲት ፡ ገዳም፡ ውስጥ ፡
ሁለት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተሠውሮ ፡ ያድር ፡
ነበር ። የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጸጋ ፡ በላዩ ፡
እንዳደረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእጆቹ ፡
ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ እንዳደረገ ፡
ከወንበዴዎችና ፡ ከዓመፀኞች ፡ ብዙዎ
ችን ፡ መነኮሳትን ፡ አድርጎ ፡ ለክርስቶስ ፡
ወደ ፡ መገዛት ፡ እስከ ፡ መለሳቸው ፡ ድረስ ፡
መነኮሳቱ ፡ ሁሉም ፡ መሰከሩለት።
፲፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ በአረጀ ፡ ጊዜ ፡
የሚሞትበትን ፡ ቀን ፡ ዐወቀ ፡ ልጆቹንም ፡
የክርስቶስ ፡ በሆነች ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘክርስቶስ ፡ ወይዕቀቡ ፡ ትእዛዞ ፡ ወበጊዜሃ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም።

፲፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

እንዲጸኑ ፡ ትእዛዙንም ፡ እንዲጠብቁ ፡ አስተማራቸው ፡ ወዲያውኑ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፲፫፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለታውብንጦስ ። ኀበ፡ ደብረ ፡ ሲሐት ፡ ዘሖረ። ከመ ፡ ለጣዖት ፡ ኢይስግድ ፡ ዘበእደ፡ ሰብእ ፡ ተገብረ። ውስተ ፡ ቤተ ፡ ድንግል ፡ አሐቲ ፡ ከመ ፡ ፈላሲ ፡ ኀደረ። እስከ ፡ ሜጠ ፡ ዐማፄ ፡ ወፈያተ ፡ መሀረ። በኃይለ ፡ አምላኩ ፡ ዘገብረ ፡ መንክረ።

፲፬፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለጠምያኒ ፡ ሰማዕት ፡ ወኪናርያ ፡ ወበጥሪቃ ፡ ንግሥት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

፲፬፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሰማዕት ፡ ለጠምያኒ ፡ የኪናርያና ፡ የንግሥት ፡ በጥሪቃ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ጽዕድዋን ፡ አርጋብ። እምነ ፡ ቢረሌ ፡ ወሐሊብ። ካህናት ፡ ኄራን ፡ ፍቁራኒሁ ፡ ለአብ። እስእለክሙ ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ምኅፃብ። ከመ ፡ ታንጽሑኒ ፡ ለብእሲ ፡ ስዑብ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ፡ አመ ፡ ፲ ወ ፩ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ተጠምቀ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እም ዮሐንስ ፡ መጥምቅ።

፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ በዓለ ፡ ኤጲፋንያ ፡ ትሰመይ፡ በልሳነ ፡ ዮናኒ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ አስተርእዮቱ፡ ለመለኮት ፡ እስመ ፡ ባቲ ፡ አስተርአየ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴሁ ፡ ቅድስት፡ እስመ ፡ ጸርሐ ፡ አብ ፡ እምሰማይ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር፡ ዘኪያሁ ፡ ሠመርኩ፡ ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ። ወልድኒ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ለወልድ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ዐዓዳ ፡ በከመ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሶበ ፡ ተጠምቀ ፡ ወወጽአ ፡ እማይ። ወሶቤሃ፡ ተሠጥቀ ፡ ሰማይ ፡ ወወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወነበረ፡ ዲቤሁ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአጥማቂው፡ ዮሐንስ ፡ ዘንድ ፡ በዮርዳኖስ፡ ወንዝ ፡ ውኃ ፡ ተጠመቀ።

፪፡ ይችም ፡ ዕለት ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ኤጲፋንያ ፡ ትባላለች ፡ ትርጓሜውም፡ መለኮት ፡ የተገለጠበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ልዩ ፡ የሆነች ፡ የሦስትነቱን ፡ ምሥጢር ፡ ገልጦባታልና ፡ አብ፡ ከሰማይ፡ ሁኖ ፡ የምወደው ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እርሱን ፡ ስሙት ፡ እያለ ፡ ሲመሰክር ፡ ወልድም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ፡ ቁሞ ፡ ሳለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በነጭ ፡ ርግብ ፡ አምሳል ፡ በወልድ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ ይህ ፡ አጥማቂው ፡ ዮሐንስ ፡ እንደመሰከረ። እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተጠምቆ ፡ ከውኃ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያኑ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ፡ በጌታችን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ከሰማይም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ መጣ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ ዘኪ
ያሁ ፡ ሠመርኩ፡ ወሎቱ ፡ ስምዕዎ።
፫፡ እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አግሀደ ፡ ርእሶ ፡ እግዚ
እነ ፡ እምቅድመ ፡ ዝኒ ፡ ኢያግሀደ ፡ ርእሶ ፡
መጠነ ፡ ፴ ዓመት ፡ ባሕቱ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡
አግሀደ ፡ ርእሶ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወኮነ ፡
ስምዐ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ አግሀዶ ፡
ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ነዋ ፡
በግዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘያእትት ፡ ኃጢ
አተ ፡ ዓለም ፡ ወይቤ ፡ አንሰ ፡ ኢያአምሮ፡
ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ያእምርዎ ፡ እስራኤል፡ በእንተ ፡
ዝንቱ ፡ መጻእኩ ፡ ከመ ፡ አጥምቅ ፡ በማይ።
፬፡ ወበዝንቱ ፡ በዓል ፡ አስተርአየ ፡ ስብሐተ ፡
መለኮቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ወውእቱ፡ በግዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘየአትት ፡
ኃጢአተ ፡ ዓለም ፡ ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡
በዓል ፡ ዐቢየ ፡ ወክቡረ ፡ በኀበ፡ ኵሎሙ ፡
ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይነጽሑ ፡ ቦቱ ፡ በማይ ፡
ቅዱስ ፡ በአምሳለ፡ ጥምቀቱ ፡ ለእግ፡ኢእነ ፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወይነ
ሥኡ ፡ ውስቴቱ ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአቶሙ ፡
ለእመ፡ ነበሩ ፡ በንጽሕና ፡ ዘነሥኡ።

፭፡ ወበእንተዝ ፡ ይደልወነ፡ ከመ ፡ ንትዓቀብ ፡
ወንግነይ ፡ ወንሰብሕ ፡ ለብዝኀ ፡ ጸጋሁ ፡ ለአም
ላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ በእንቲአነ ፡
ወአድኃነነ ፡ እምኃጣውኢነ።
፮፡ ወሎቱ ፡ ስብሐት፡ ወአኰቴት ፡ ወሰጊድ ፡
ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኄር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ማሕየዊ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡
ዓለም ፡ አሜን።

ይህ፡ የምወደው ፡ በእርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡
ልጄ ፡ ነው ፡ እርሱንም ፡ ስሙት።
፫፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ጌታችን ፡ ራሱን ፡ ገልጦ
አልና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት፡ ያህል ፡
ራሱን ፡ አልገለጠም ፡ ነበር፡ ግን ፡ በዚች ፡
ዕለት ፡ ለእስራኤል፡ ልጆች ፡ ራሱን ፡ ገለጠ ፡
እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ የዓለምን ፡ ኃጢ
አት፡ የሚያስወግድ ፡ ብሎ ፡ መጥምቁ ፡
ዮሐንስ ፡ እንደገለጠው ፡ የከበረ ፡ ወንጌል ፡
ምስክር፡ ሆነ ። እኔ ፡ አላውቀውም ፡ ነበር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እስራኤል ፡ ያውቁት ፡ ዘንድ ፡
በውኃ ፡ ላጠምቅ ፡ ስለዚህ ፡ መጣሁ ፡ አለ።
፬፡ በዚህም ፡ በዓል ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የክር
ስቶስ ፡ የጌትነቱ፡ ክብር ፡ ተገልጧል፡ እር
ሱም ፡ የዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ለማስ
ወገድ ፡ የሚሠዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አማናዊ ፡
በግ ፡ ነው። ስለዚህም ፡ ይህ ፡ በዓል ፡
በክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡
የከበረና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ሆነ ፡ በርሱም ፡
የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ በጥምቀቱ ፡ በአከበረው ፡ ውኃ ፡
ይነጹበታል ፡ የተቀበሉትንም ፡ ንጽሕና ፡
ጠብቀው ፡ ቢኖሩ ፡ በውስጡ ፡ የኃጢአታ
ቸውን ፡ ሥርየት፡ ያገኛሉ።
፭፡ ስለዚህም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተጠብቀን፡
የፈጠሪያችንና ፡ የመድኃኒታችንን ፡ የኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የቸርነቱን ፡ ብዛት፡
ልናመሰግን፡ ይገባናል፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡
ሰው ፡ ሁኖ ፡ ከኃጢአታችን፡ አድኖናልና።
፮፡ ለእርሱም ፡ ከቸር ፡ አባቱ ፡ ሕይወት ፡ ከሆነ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋር ፡ ክብር፡ ምስጋና፡
ስግደትም ፡ ይሁን ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም፡
ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጥምቀትከ ፡ በኍልቈ ፡ ክራማት ፡ ሠላሳ ። እምዘወለደተከ ፡ ድንግል ፡ ዘኢተአምር ፡ አበሳ። አመ ፡ ቆምከ ፡ ዮም ፡ እግዚኦ ፡ ለዮርዳኖስ ፡ ማዕከለ ፡ ከርሣ። ለወድሶትከ ፡ ማዕበላቲሃ፡ ተከውሳ። ወባረኩከ፡ አናብርት ፡ ወዓሣ።

ሰላም ፡ ለጥምቀትከ ፡ በዘቦቱ ፡ ይነጽሑ። ኃጣውአ ፡ ሰብእ ፡ ዘዘዚአሁ። አመ ፡ ላዕሌከ ፡ እግዚኦ ፡ አእዳወ፡ ዮሐንስ ፡ ተሰፍሑ ። ሶበ ፡ ርእዩከ ፡ ቀላያት ፡ ደንገፁ ፡ ወፈርሁ። ማያትኒ፡ በርእስከ ፡ ፈልሑ።

በዝንቱ ፡ በዓል ፡ ዘያሜንን ፡ ወይነ። ወዘያረስዕ ፡ ኀዘነ። ንዑ ፡ ንትፌሣሕ ፡ እንዘ ፡ ናረትዕ ፡ ልሳነ። ዘኢያስተርኢ ፡ ኀቡእ ፡ እስመ ፡ አስተርአየ ፡ ለነ። እሳት ፡ በላዒ፡ አምላክነ።

፯፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ እንጣልዮስ ፡ ዘእምሰብአ፡ ፋርስ።

፰፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ተሠይመ፡ ቀዳሚ ፡ መኰንነ ፡ ላዕለ ፡ ሠራዊተ ፡ ሮም ፡ ወነበረ፡ በሢመቱ ፡ ፲ተ ፡ ወ፫ተ ፡ ዓመተ።

፱፤ ወሶበ ፡ ክህደ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ኀረየ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ መንግሥተ፡ ሰማያዊተ ፡ ወመነነ ፡ ክብረ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወመጽአ ፡ ወቆመ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ ዐላዊ ፡ ወፈትሐ ፡ ቅናቶ ፡ ወወገረ ፡ ሎቱ ፡ ወረገመ ፡ ኪያሁ ፡ ወአማልክቲሁ ፡ ርኩሳነ፡ ወደነገፀ፡ ንጉሥ ፡ በእንተ ፡ ድፍረቱ።

፲፤ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምል ሒቃነ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ ሔጦ፡ ወተናገሮ ፡ ነገረ ፡ ሠናየ ፡ ወመጠዎ ፡ ለኅርማኖስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ዮጊ ፡ ለእመ ፡ ይክል ፡ መይጠ ፡ ልቡ ፡ እምሃይማኖተ ፡ እግዚእ ፡ ክርስቶስ ፡ ወሶበ ፡ ኢተክህሎ ፡ ለኅርማኖስ ፡ ከመ ፡ ይወልጥ ፡ ሕሊናሁ ፡ እምአምልኮተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ አግብኦ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወውእቱ ፡ ኰነኖ ፡ በዘዘዚአሁ ፡ ኵነኔ ፡ ወእግዚእነ ፡ ይፌኑ ፡ መል አኮ ፡ ወያጸንዖ ፡ ወይናዝዞ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤሁ ። ወነበረ ፡ እንዘ፡ ይትኴነን፡ ነዋኀ ፡ መዋዕለ ፡ በብዙኀ ፡ መክፈልተ፡ ኵነኔ፡ እስመ ፡ ሰቀልዎ ፡ ብዙኀ፡ ጊዜ ፡ ወእምዝ ፡ ጠብሕዎ ፡ ወዘሐቅዎ ፡ ማዕሶ ፡ ወመተሩ ፡ ልሳኖ ፡ ወወገርዎ ፡ ለአራዊት ፡ መሠጥ ፡ ወገደፍዎ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ጽልመት ፡ ወመጠወ ፡ ነፍሶ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ።

፲፩፤ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ ኰንኖቶ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወመተርዎ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ሰምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት።

፲፪፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ ረነ ፡ በጸሎተ ፡ ዚአሆሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ወበ ረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፯፤ በዚችም፡ ቀን ፡ ከፋርስ ፡ አገር፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ የከበረ፡ እንጣልዮስ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ።

፰፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ አስቀድሞ ፡ በሮም፡ አገር ፡ የሠራዊት፡ አለቃ ፡ መኰንን ፡ ሁኖ ፡ ዐሥራ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ።

፱፤ የክብር ፡ ባለቤት፡ ክርስቶስን ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ በካደው ፡ ጊዜ፡ ይህ፡ ቅዱስ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥትን ፡ መረጠ ፡ የዚህ ፡ የኃላፊውንም ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ ንቆ፡ ተወ ፡ መጥቶም ፡ በከሀዲው ፡ ንጉሥ፡ ፊት፡ በመቆም ፡ እርሱንና ፡ የረከሱ ፡ አማልክቶቹን ፡ ረገመ ፡ ንጉሡም ፡ ስለ ፡ ድፍረቱ፡ ደነገጠ።

፲፤ ከፋርስ ፡ ሰዎችም ፡ ከታላላቆቹ ፡ ወገን ፡ እንደሆነ ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ በሽንገላ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ተናገረው ፡ ምናልባት ፡ ከጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት፡ ልቡን ፡ መመለስ ፡ ቢችል ፡ ብሎ ፡ ለሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ለኅር ማኖስ ፡ ሰጠው ። ኅርማኖስም ፡ ጌታ ፡ ክርስ ቶስን ፡ ከማምለክ ፡ ሐሳቡን ፡ ሊአስለ ውጠው ፡ ባልተቻለው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ፡ መለሰው ፡ እርሱም፡ በየራሱ ፡ በሆነ፡ ሥቃይ ፡ አሠቃየው። ጌታችንም ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ ያጸናውና ፡ ያረጋጋው ፡ ነበር ፡ በብዙ፡ በተለያዩ ፡ ሥቃዮችም ፡ እየተሠቃየ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ሰቅለውታልና ፡ ከዚያም ፡ አርደው ፡ ቆዳውን ፡ ገፈፉት ፡ ምላሱንም ፡ ቆረጡት፡ ለነጣቂዎች ፡ አራዊቶችም ፡ ጣሉት ፡ በጨለማ፡ ቤትም ፡ ዘጉት ፡ ሦስት ፡ ጊዜም፡ ነፍሱን ፡ አሳለፈ፡ እግዚአብሔርም፡ አስነሣው።

፲፩፤ ዲዮቅልጥያኖስም ፡ ማሠቃየቱን፡ በደከመ፡ ጊዜ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆርጡ ፡ አዘ ዘና ፡ ቆረጡት ፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀበለ።

፲፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለእንጣልዮስ ፡ ዘረሰየ ፡ ማኅሠሦ። ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቆ ፡ ወሰማያዊተ ፡ ንግሦ። ጊዜያተ ፡ ሠላሰ ፡ እስከ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ። ድኅረ ፡ አውቀዩ ፡ ልሳኖ ፡ ወዘሐቁ ፡ ማዕሶ። ለፍጻሜ ፡ ስምዑ ፡ በሰይፍ ፡ መተርዎ ፡ ርእሶ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወው እቱ ፡ እምኁልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳ ሳት ፡ ፴ወ፬ቱ።

፲፬፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ እምቅድመ ፡ ይሠየም ፡ ሊቀ፡ ጵጵስና ፡ ኮነ ፡ ነጋዴ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ህንደኬ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ዲበ ፡ ባሕር ፡ በሐ መር ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚሰ ፡ ኮነ ፡ ዲያቆነ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ መርቆ ሬዎስ ፡ ሰማዕት ፡ በሀገረ ፡ ምስር ፡ ወኮነ ፡ ጸሐፌ ፡ ወኀዲጎ ፡ ጽሕፈቶ ፡ ነጋዴ ፡ ኮነ ።

፲፭፤ ወኀረይዎ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወሤምዎ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ አመ ፡ ፬ ለወርኃ ፡ የካቲት ፡ በ፱፻ወ፬ ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ወኮነ ፡ ዘየዐቅብ ፡ መርዔቶ ፡ በሠናይ ፡ ተዓቅቦ ።

፲፮፤ ወኮነ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ብዙኀ ፡ እምቅድመ ፡ ይሠየም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መጠነ ፡ ፳፻ ዲናረ፡ ወርቅ ፡ ወወሀበ ፡ ኵሎ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወለአብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለአድባራት ፡ እስከ ፡ አህለቀ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ እምቅድመ ፡ ዕረፍቱ ።

፲፯፤ ወበመዋዕለ ፡ ሢመቱ ፡ ኢነሥአ ፡ ምንተኒ ፡ አምኃ ፡ እምሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነበረ ፡ በሢመቱ ፡ ፳ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወአዕረፈ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ጥምቀት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ በ፱፻፴ወ፪፡ዓመተ፡ሰማዕታት፡ንጹሐን።

፲፰፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ አሜን።

፲፫፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት፡ የከበረ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሰባ ፡ አራተኛ ፡ ነው ።

፲፬፤ ይህም ፡ አባት ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ከመሾሙ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ በመርከብ፡ እየሔደ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚነ ግድ ፡ ነጋዴ ፡ ሁኖ ፡ ነበር ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በምስር ፡ አገር ፡ በሰማዕቱ ፡ በቅዱስ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጸሐፊነት፡ የሚያገለግል ፡ ዲያቆን ፡ ነው ፡ ጸሐፊነቱንም ፡ ትቶ ፡ የሚነግድ ፡ ሆነ ።

፲፭፤ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አራት ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ የካቲት ፡ አራት ፡ በእሑድ ፡ ዕለት ፡ ኤጲስቆ ጶሳቱ ፡ መርጠው ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሾሙት ፡ በመልካም ፡ አጠባበቅም ፡ መንጋውን ፡ የሚ ጠብቅ ፡ ሆነ።

፲፮፤ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሁኖ ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ ሃያ ፡ ሽህ ፡ ያህል ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ነበረው ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለገዳማትም ፡ ሁሉን፡ ገንዘቡን ፡ ሰጥቶ ፡ ጨረሰ።

፲፯፤ በሹመቱም ፡ ወራት ፡ ከሕዝብ ፡ ምንም ፡ ምን፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አልተቀበለም ፡ በሹመቱም ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ በጥምቀት ፡ በዓል ፡ አረፈ።

፲፰፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

<u>አርኬ ፡</u>

ሰላም ፡ እብል ፡ ለዮሐንስ ፡ ልሒቅ ። በላህበ ፡ ሃይማኖት ፡ ርሱን ፡ ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምውቅ ። እስከነ ፡ ለነዳያን ፡ ዘረወ ፡ ወለምስኪናን ፡ በጽድቅ ። እምነ ፡ እስራ ፡ አእላፍ ፡ ዲናረ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ። ኢተርፈት ፡ ሎቱ ፡ አሐቲ ፡ ጸሪቅ ።

፲፱፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፉ ፡ ቅዱሳን ፡ ዮስጦስ ፡ ወፋይዮስ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአብ ፡ ቅዱስ ፡ ወመስተጋድል ፡ አባ ፡ ወቅሪስ ።

፲፱፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ ዮስጦስና ፡ ፋይ ዮስ፡ አረፉ ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፳፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ ተጋዳይ ፡ ለሆነ ፡ አባት ፡ አባ ፡ ወቅሪስ ፡ የዕረፍቱ ፡ መታሰቢያ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ተሐፅነ ፡ በኀበ ፡ ዐቢይ ፡ አብ ፡ ባስልዮስ ፡ ወውእቱ ፡ ሤሞ ፡ ቀሲሰ ፡ ወውእቱ ፡ ሠናየ ፡ ላሕይ ፡ በስኑ ፡ ወአዳም ፡ ገጹ።

፳፪፡ ወአመ ፡ ቀዳሚ ፡ ግብሩ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ወሬዛ ፡ ፈተወ ፡ ብእሲተ ፡ መኰንን ፡ ወጥቀ ፡ አፍቀራ ፡ ወይእቲኒ ፡ ፈተወቶ ፡ ወተማከሩ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ውስተ ፡ካልዕ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ፍትወቶሙ ፡ ወእንዘ ፡ ያስተ ሐምሙ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ በሕልሙ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ እሡር ፡ ወይቀውም ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ምኵናን ። ወብዙኃን ፡ እሡራን ፡ ምስሌሁ ፡ ወይትኃሠሥዎሙ ፡ ለለ፩በእንተ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወይቤ፡ በልቡ ፡ ምንትኑ ፡ ውእቱ ፡ ማእሠርየ ፡ ቦኑ ፡ በእንተ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘፈቀድኩ ፡ አዐምዖ ፡ ለምታ ፡ ወውእቱ ፡ አስተዋደየኒ ፡ ወአብጽሐኒ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ዐቢይ።

፳፫፡ ወእንዘ ፡ ይትሀወክ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ፩ ብእሲ ፡ በአምሳለ ፡ ፍቁሩ ፡ ዘት ካት፡ ወይቤሎ ፡ ምንትኑ ፡ ማእሠርከ ፡ ወፈ ቀደ ፡ ይኅብአ ፡ እስመ ፡ ኀፈረ ፡ ኃጢአቶ ፡ ወሶበ ፡ አገበሮ ፡ ይቤሎ ፡ ኦ ፡ ፍቁርየ ፡ ከመዝ፡ ገበርኩ ፡ ሊተሰ ፡ ይመስለኒ ፡ ዘአስተዋደየኒ ፡ ዕገሌ ፡ በእንተ ፡ ብእሲቱ ፡ በእንተዝ ፡ እፌ ርህ፡ ወእትሀወክ ። ወይቤሎ ፡ መልአክ ፡ ዘመጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ በአምሳለ ፡ ፍቁሩ ፡ ኦ ፡ ፍቁርየ ፡ መሐል ፡ ሊተ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ኢትግበር ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ወኢት ግባእ፡ ኀቤሁ ፡ ዳግመ ፡ ወአነ ፡ እትሐበየከ ፡ ወመሐለ ፡ሎቱ ፡ በወንጌል ፡ ወሶቤሃ ፡ ነቅሐ፡ እምንዋሙ ፡ ወአእመረ ፡ ከመ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ፡ ዘርእየ ፡ ራእይ ።

፳፬፡ ወበእንተዝ ፡ ኀደገ ፡ ሀገሮ ፡ ወሖረ ፡ እስክን ድርያ ፡ ወረከባ ፡ በህየ ፡ ለአሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ፈራሂተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘስማ ፡ ኄራኒ ፡ ወሶበ ፡ ተዚያነው ፡ ነገራ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡ ልቡ ፡ ወትቤሎ ፡ ኅድግ ፡ እሎንተ ፡ አልባ ሲከ ፡ ሠናያተ ፡ ወልበስ ፡ ልብሰ ፡ ትሕትና ፡ ወተፀመዶ፡ ለእግዚአብሔር።

፳፭፡ ወእምህየ ፡ ሖረ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይሴሰይ ፡ አህማላተ ፡ እስከ ፡ የብሰ ፡

፳፩፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ በባስልዮስ ፡ ዘንድ ፡ አደገ ፡ እርሱም ፡ ቅስና ፡ ሾመው ፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ በደም ፡ ግባቱ ፡ በላሕዩ ፡ ደስ ፡ የሚል፡ ፊቱም ፡ የሚአምር ፡ ነበር።

፳፪፡ በቀደመው ፡ ግብሩ ፡ ወጣት ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ የሹሙን ፡ ሚስት ፡ ተመኛትና ፡ እጅግም ፡ ወደዳት ፡ እርሷም ፡ ወደደችው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሒደው ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ፡ ለዚህም ፡ ነገር ፡ ሲዘጋጁ ፡ በሕልሙ ፡ ራእይን ፡ አየ ። እርሱ ፡ ታሥሮ ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ቁሞ ፡ ነበር ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ እሥረኞች ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አሉ ፡ ስለ፡ በደላቸውም ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ይመረ ምሩአቸው ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ በልቡ ፡ የታሠ ርሁት ፡ በምን ፡ ይሆን ፡ ባሏን ፡ ልነጥ ቀው ፡ ስለፈለግሁ ፡ ስለዚያች ፡ ሴት ፡ ነውን ፡ እርሱ ፡ ከስሶኝ ፡ ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ግዳጅ ፡ ላይ ፡ አደረሰኝን ፡ አለ።

፳፫፡ በዚህም ፡ ነገር ፡ እየተሸበረ ፡ ሳለ ፡ በቀድሞ ፡ ወዳጁ ፡ አምሳል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጣና ፡ የታ ሠርከው ፡ በምንድን ፡ ነው ፡ አለው ፡ ስለ ፡ ኃጢ አቱ ፡ ስለ ፡ አፈረ ፡ ሊሠውረው ፡ ወደደ ፡ ግድ፡ በአለውም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ነገረው ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ዕገሌ ፡ ስለሚስቱ ፡ የከሰሰኝ ፡ ይመስ ለኛል ፡ ስለዚህም ፡ ፈርቼ ፡ እሸበራለሁ፡ በወ ዳጁ ፡ አምሳል ፡ ወደርሱ ፡ የመጣ፡ መልአክም፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ እንዳትሠራ ፡ ወደርሱም ፡ እንዳትመለስ ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ማልልኝ ፡ እኔም ፡ ዋስ ፡ እሆንሃለሁ ፡ አለው ፡ በወንጌልም ፡ ማለለት ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከእን ቅልፉ ፡ ነቃ ፡ ያየው ፡ ራእይም ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ አወቀ ።

፳፬፡ ስለዚህም ፡ አገሩን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ እስክን ድርያ፡ ሔደ ፡ በዚያም ፡ ስሟ ፡ ኄራኒ ፡ የሚባል ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አገኘ፡ በተነጋገሩም ፡ ጊዜ ፡ የልቡን ፡ ሁሉ ፡ ነገራት ፡ እርሷም ፡ እነዚህን፡ ያማሩ፡ ልብሶችህን ፡ ተው ፡ ተርታ፡ ልብስንም፡ ልበስህ ፡ እግዚአብሔርን፡ አገልግለው ፡ አለችው ።

፳፭፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡ ሔደ ፡ ኩበዙ ፡ ተጋድሎ፡ የተነሳ ፡ ሆዱ ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ እስከ፡ ደረቀ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከርሡ ፡ ከመ ፡ ዕብን ፡ እምብዝኀ ፡ ፃማ ፡ ወእ
ግዚእነ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ወፈወሶ።
፳፮፡ ውእቱሰ ፡ ኮነ ፡ ዘይትጋደል ፡ በጾም ፡ ወበጸ
ሎት ፡ እስመ ፡ አጋንንት ፡ ያሜክርዎ ፡ ወያመ
ነድብዎ ፡ ወየኀድር ፡ ቀዊሞ ፡ ዕራቆ ፡ በክረ
ምት ፡ እንዘ ፡ ይወርድ ፡ ዝናም ፡ ላዕሌሁ ፡ ወበ
ኃጋይኒ ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ በመዓልት ፡ ወቊረ ፡
ሌሊት ፡ እስከ ፡ ተውህቦ ፡ ጸጋ ፡ ሰማያዊ ፡
ወመላእክት ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይሴ
ስይዎ ፡ ኅብስተ ፡ ሰማይ ፡ ወያሰትይዎ ፡ ስቴ ፡
ሰማያዌ።
፳፯፡ ወደለዎ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ኅቡአተ ፡ ራእያተ ፡
ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ሠለስተ ፡ አሐዱ ፡
በእንተ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ውስተ ፡ገዳም ፡ ወካ
ልኡ ፡ በእንተ ፡ ማኅበረ ፡ አኃው፡ ወሣልሱ ፡
በእንተ ፡ ካህናት ።
፳፰፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ አሐዱ ፡
ገዳማዊ ፡ ዘስሙ ፡ ቡላ ፡ ወተአምኆ ፡ በበይና
ቲሆሙ ፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ቡላ ፡ አ ፡ እኁየ ፡
ወቅሪስ፡ኢትንበር፡ባሕቲተከ፡አላ፡አንብር፡
ምስሌከ ፡ ኀዳጣነ ፡ አኃወ ፡ ከመ ፡ ይናዝዙከ ፡
ወከመ ፡ ትድኃን ፡ እምጸብአ ፡ ሰይጣን ፡
ወገብረ፡ከማሁ።
፳፱፡ ወበ ፩እመዋዕል ፡ መጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ሠለስቱ ፡
ሰይጣናት ፡ በአምሳለ ፡ ዕልዋነ ፡ ሃይማኖት ፡
አርዮስ ፡ ወንስጥሮስ ፡ ወማኒ ፡ ወተዋሥእዎ ፡
በሃይማኖቶሙ ፡ ወሞዖሙ ፡ ውእቱ ፡ በቃ
ላተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ወበትምህርተ ፡
አበው ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአስተኀ
ፈሮሙ።

፴፡ ወኮነ ፡ ዘይገብር ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡
ብዙኃተ ፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ረከባ ፡ ዕጹተ ፡ ወኃሠሡ ፡
አኃው ፡ መራኁተ ፡ ወኢረከቡ ፡ ወሶበ ፡ አተበ ፡
ላዕለ ፡ አንቀጽ ፡ ተርኅወ ፡ ሎቱ ።

፴፩፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወቅሪስ ፡ ዘተብህለ ፡ በእን
ቲአሁ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ይቤልዎ ፡ አቡከ ፡ ሞተ ፡
ውእቱኒ ፡ ይቤሎሙ ፡ ሐሰውክሙ ፡ አቡየሰ ፡
ሰማያዊ ፡ ኢይመውት ፡ ዜናሁሰ ፡ ሀሎ ፡ ጽሑፈ ፡
ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ገድሉ ፡ ወመጽሐፈ ፡
ዜናሆሙ ፡ ለአበው ።

ድረስ ፡ ቅጠላቅጠል ፡ እየበላ ፡ ኖረ ፡ ጌታችንም ፡
ወደርሱ ፡ መጥቶ ፡ ፈወሰው።
፳፮፡ አጋንንትም ፡ ስለሚፈታተኑትና ፡ ስለሚያሠ
ቃዩት ፡ እርሱ ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ በመ
ጋደል ፡ በክረምት ፡ ዝናብ ፡ እየወረደበት ፡
ራቁቱን ፡ ቁሞ ፡ ያድራል ፡ በበጋም ፡ በቀን ፡
የፀሐይ ፡ ትኩሳት ፡ በሌሊትም ፡ ቊር ፡ ሰማ
ያዊ ፡ ሀብት ፡ እስከተሰጠው ፡ ድረስ ፡ መላእ
ክትም ፡ ወደርሱ ፡ መጥተው ፡ ሰማያዊ ፡ ኅብስ
ትን ፡ ሰማያዊ ፡ መጠጥን ፡ ይመግቡት ፡ ነበር።

፳፯፡ የተሠወሩ ፡ ራእዮችን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡
ተገባው ፡ ሦስት ፡ ድርሰቶችንም ፡ ደረሰ ፡
አንዱ ፡ በበረሀ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሁለተኛው ፡ በአ
ንድነት ፡ ስለሚኖሩ ፡ መነኰሳት ፡ ሦስተ
ኛው ፡ ስለ ፡ ካህናት ፡ ነው ።
፳፰፡ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ ስሙ ፡ ቡላ ፡ የሚባል ፡
ገዳማዊ ፡ ወደርሱ ፡ መጥቶ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡
ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ፡ አባ ፡ ቡላም ፡ እንዲህ ፡
አለው ፡ ወንድሜ ፡ ወቅሪስ ፡ ሆይ ፡ ብቻህን ፡
አትሁን ፡ ጥቂት ፡ ወንድሞችን ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡
አኑር ፡ እንጂ ፡ ያረጋጉህ ፡ ዘንድ ፡ ከሰይጣንም ፡
ጦርነት ፡ እንድትድን ፡ እንዲሁም ፡ አደረገ።
፳፱፡ ከዕለታትም ፡ በአንዱ ፡ ሃይማኖትን ፡
በለወጡ ፡ በአርዮስ ፡ በንስጥሮስና ፡ በማኒ ፡
አምሳል ፡ ሁነው ፡ ሦስት ፡ ሰይጣናት ፡
ወደርሱ ፡ መጥተው ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ተከ
ራከሩት ፡ እርሱም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕ
ፍት ፡ ቃላትና ፡ ሃይማኖታቸው ፡ በቀናች ፡
አባቶች ፡ ትምህርት ፡ ረታቸውና ፡ አሳፈ
ራቸው።
፴፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡
ይሚሠራ ፡ ሆነ ፡ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ተዘግታ ፡
አገኛት ፡ መነኰሳቱም ፡ መክፈቻ ፡ ፈልገው ፡
አላገኙም ፡ በላይዋም ፡ በአማተበ ፡ ጊዜ ፡ በሩ ፡
ተከፈተለት።
፴፩፡ አባትህ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ በነገሩት ፡ ጊዜ ፡ ዋሽ
ታችኋል ፡ አባቴስ ፡ የማይሞት ፡ ሰማ
ያዊ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ ስለርሱ ፡ የሚነገ
ርለት ፡ ወቅሪስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ዜናውም ፡
በገድሉ ፡ መጽሐፍና ፡ የአባቶች ፡ ዜና ፡ በተጻ
ፈበት ፡ መጽሐፍ ፡ አለ።

፴፪፤ ወእምዝ፡ሶበ፡ልሕቀ፡ወረሥአ፡ፈለሰ፡ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ዘአፍቀሮ። ወስብሐት፡ለእግ ዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ በአረጀ ፡ ጊዜ ፡ ወደ፡ ወደደው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔደ። ለእግዚአብ ሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለወቅሪስ፡እንተ፡ርእየ፡በንዋም።እንዘ፡ውእቱ፡እሡረ፡ከዊኖ፡በዓውደ፡ምኵናን፡ቅውም። ሶበ፡ተኀይጠ፡ለብእሲት፡በስነ፡ላሕያ፡አዳም።ከመ፡ያድኅን፡ነፍሶ፡በአውትሮ፡ጸሎት፡ወጾም። ነዋኅ፡ተናከራ፡ለዛቲ፡ዓለም።

ሰላም፡እብል፡በቃለ፡ሐሤት፡ወፍሥሓ።እንዘ፡እጼውዕ፡ስመከ፡ሠርከ፡ወነግሀ።ዮሐንስ፡ሰባኪ፡ ጥምቀተ፡ለንስሓ።ኀፅበኒ፡ወአንጽሐኒ፡እስመ፡አባልየ፡ረስሐ።በማየ፡ዮርዳኖስ፡ዘኰሎ፡አንጽሐ።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ ወ ፪ ለጥር ፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለመልአክ ፡ ክቡር ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ሚካኤል ፡እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ያዕቆብ፡ እስራ ኤል ፡ እንዘ ፡ ይፈርህ ፡ እምእኁሁ ፡ ኤሳው ፡ ወአድኅኖ ፡ እምኔሁ ፡ ወአኀለፎ ፡ ፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወሐረ ፡ ኀበ ፡ ላባ ፡ እኁወ ፡ እሙ ፡ ውእቱኒ፡አስተዋሰቦ፡፪፡አዋልዲሁ፡ልያሃ፡ ወራኄልሃ ፡ ወእምዝ ፡ አግብኦ ፡ ውስተ ፡ ብሔሩ፡ እንዘ ፡ ይጸይሕ ፡ ፍኖቶ ፡ በዳኅና ፡ ወበሰላም፡ምስለ፡ንዋዩ፡ብዙኅ፡ወውልዱ። ኤሳውኒ ፡ እኁሁ ፡ ተቀበሎ ፡ በሰላም ፡ ወበእ ንተዝ፡ኮነ፡ተዝካረ፡በዓሉ፡ለሚካኤል፡ሊቀ፡ መላእክት።

፪፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በትንብልናሁ ፡ ለዝንቱ ፡ መል አክ፡ክቡር፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡ዐሥራ፡ሁለት፡ በዚች፡ቀን፡የከበረ፡መልአክ፡የመላእክት፡ አለቃ፡የሚካኤል፡የበዓሉ፡መታሰቢያ፡ነው፡ በዚች፡ቀን፡እስራኤል፡ወደ፡ተባለ፡ያዕቆብ፡ እግዚአብሔር ፡ ልኮታልና ፡ ከወንድሙ ፡ ከኤሳውም ፡ ፈርቶ፡ ሳለ ፡ አዳነው ። ዮርዳኖ ስንም ፡ አሻግሮት ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ወንድም ፡ ወደ፡ላባ፡ሔደ።እርሱም፡ሁለቱን፡ልጆቹን፡ ልያንና፡ራኄልን፡አጋባው፡ከዚህም፡በኋላ፡ ከብዙ፡ገንዘቡና፡ከልጆቹ፡ጋር፡መንገዱን፡ እየጠረገና፡እያቀና፡በሰላም፡በጤና፡ወደ፡ አገሩ፡ መለሰው ፡ ወንድሙ ፡ ኤሳውም ፡ በፍቅር ፡ በሰላም ፡ ተቀበለው ፡ ስለዚህም ፡ የሊቀ ፡ መላእክት ፡ ሚካኤል ፡ የበዓሉ ፡ መታሰቢያ፡ሆነ።

፪፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ በከበረ ፡ መልአክ ፡ አማላጅነት ፡ ይማረን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ሚካኤል፡አሐዱ።እምነ፡ሊቃናት፡ልዑላን፡ለእግዚአብሔር፡ጸማዱ።አመ፡ተፈኖከ፡ ትኩን፡ረድኤተ፡ቴዎድሮስ፡ጊዜ፡መራዱ።ከመ፡ቈጽል፡እምነፋስ፡ሰብአ፡ቀኑዝ፡ርዕዱ። ሶበ፡መጥባ ሕተከ፡ነጸሩ፡በእዴ።

፲፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ጽኑዕ፡ወኃያል፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ምሥራቃዊ ፡ ወዝንቱ፡መስተጋድል፡ዐቢይ፡እምሰብአ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ እምዘመደ ፡ ሰብአ ፡ መንግሥት፡ወስሙ፡ለአቡሁ፡ሲድራኮስ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ወስማ ፡ ለእሙ ፡

፲፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡የምሥራቅ ፡ ሰው ፡ ጽኑዕ ፡ ኃይለኛ፡የሆነ፡ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስ፡በሰ ማዕትነት፡ሞተ።ይህም፡ታላቅ፡ተጋዳይ፡ከአ ንጾኪያ፡አገር፡ሰዎች፡ከመንግሥት፡ወገን፡ ነው ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ሲድራኮስ ፡ ይባላል ፡ ለንጉሥም፡የጭፍራ፡አለቃ፡ነው፡የእናቱም፡

www.ethiopianorthodox.org

በጥሪቃ፡ዘበትርጓሜሁ፡እግዝእት፡ብሂል።

፬፤ ወሶበ ፡ ሞተ ፡ ኑማርያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ ወዮስጦስ ፡ ወልዱ ፡ ሀሎ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ ወነበረት ፡ መንግሥት ፡ ዘእንበለ ፡ ንጉሥ ፡ ወሲድራኮስ ፡ አቡሁ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ ወፋሲለደስ ፡ ኮኑ ፡ ይሜግቡ ፡ መንግሥተ ፡ እስከ፡አመ፡ነግሠ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ወክህደ፡ ሃይማኖቶ።

፭፤ ወውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ እምላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ ቀዳሚ፡ ወተወሰበት ፡ ሎቱ ፡ ወለቱ ፡ ለኑማርዮስ ፡ ንጉሥ፡እኅቱ፡ለዮስጦስ፡ወረሰዮ፡ንጉሠ።

፮፤ ወቅዱስሰ፡ቴዎድሮስ፡ሶበ፡ልሕቀ፡ኮነ፡ኃያለ፡ ወጽኑአ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ ወዘሎ፡ ጸብእ ፡ ዘየሐውር ፡ ኀቤሁ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይመውዖሙ ፡ ለጸላእቱ ፡ ወያጐይዮሙ ፡ ወኮኑ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡ ሶበ፡ ይቤልዎሙ ፡ ናሁ ፡ መጽአ ፡ ኀቤክሙ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይሰበር ፡ አልባቢሆሙ ፡ ወይገርሩ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ እስመ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አምላኮሙ ፡ ለሮም።

፯፤ ወውእቱ ፡ ዘዔወዎ ፡ ለኒኆሚዶስ ፡ ወልደ ፡ ንጒሠ፡ ቍዝ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ኮነ፡ ምክንያተ ፡ ክህደቱ ፡ ለዲዮቅልጥያኖስ ፡ ሶበ፡ አንበሮ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አጋግዮስ ። አጋግዮስኒ ፡ ነሥኦ ፡ ወርቀ ፡ እምኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ቍዝ፡ በመዳልው ፡ በመጠነ ፡ ክበደ ፡ መድሎቱ ፡ ወሜጦ፡ኀበ፡አቡሁ፡በኀቡእ።

፰፤ ወቅዱስሰ፡ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስ፡ሶበ፡ሀሎ፡ ውስተ ፡ ጸብእ ፡ ኀበ ፡ ፈለግ ፡ ዘይሰመይ፡ ቡናቢስ፡ ወኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዐርክ ፡ ዘስሙ ፡ ለውንድዮስ ። ወእምዝ ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ በአሐቲ ፡ ሌሊት፡ዘከመ፡ሰዋስው፡ዘይበጽሕ፡እምድር፡ እስከ ፡ ሰማይ ። ወዲበ ፡ ውእቱ ፡ ሰዋስው ፡ ይነብር፡እግዚእነ፡ዲበ፡መንበር፡ዐቢይ፡ወየዓውድዎ ፡ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ መላእክት ፡ ወርእየ ፡ ታሕተ ፡ ሰዋስው ፡ ከይሴ ፡ ዐቢየ ፡ ወይቤሎ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስ፡ትፈቅድኑ፡ትኩነኒ፡ ሊተ ፡ ወልድየ ። ወይቤ፡ ቴዎድሮስ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ አነ ፡ ውእቱ፡ኢየሱስ፡ቃለ፡አብ፡ወለከ፡ሀለወከ፡

ስም ፡ በጥሪቃ ፡ ይባላል ፡ ትርጓሜውም ፡ እመቤት፡ማለት፡ነው።

፬፤ ንጉሥ ፡ ኑማርያኖስም ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ዮስጦስም ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ነበር ፡ መንግሥትም ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረች ፡ የቴዎድሮስ ፡ አባት ፡ ሲድራኮስና ፡ ፋሲለደስ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ነግሦ ፡ ሃይማኖቱን፡እስከ፡ካደ፡ድረስ፡የመንግሥቱን፡አስተዳደር፡ይመሩ፡ነበር።

፭፤ እርሱም ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ አስቀድሞ ፡ ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ የሆነ ፡ የዮስጦስ ፡ እኅት ፡ የንጉሥ፡ኑማርዮስ፡ልጅ፡ሚስት፡ሆነችውና፡ አነገሠችው።

፮፤ ቅዱስ፡ቴዎድሮስም፡በአደገ፡ጊዜ፡በጦርነት፡ ውስጥ፡ፈጽሞ፡ኃይለኛ፡ሆነ፡እርሱ፡ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ ፡ በሚሔድበት ፡ ጦርነት ፡ ሁሉ ፡ ጠላቶቹን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያሳድዳቸዋል ፡ የፋርስ ፡ ሰዎችም ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወደእናንተ ፡ መጣ፡ ሲሏቸው ፡ ልባቸው ፡ ይሰበራል ፡ ይገዙ ለታልም ፡ ከእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሮማውያን፡አምላክ፡ነው፡የሚሉ፡አሉ።

፯፤ ለዲዮቅልጥያኖስ፡ክህደት፡ምክንያት፡የሆነ፡ የቍዝ፡ንጉሥን፡ልጅ፡ኒኆሚዶስን፡ሁለት፡ ጊዜ ፡ የማረከው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ከአባ ፡ አጋግዮስም፡ዘንድ፡በአኖረው፡ጊዜ፡ አጋግዮስ፡ በኒኆሚዶስ፡ክብደት፡ልክ፡ወርቅ፡አስመዝኖ፡ ከቍዝ፡ንጉሥ፡ተቀብሎ፡ወደ፡አባቱ፡መልሶታልና።

፰፤ የከበረ፡ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስም፡በጦርነት፡ ቦታ ፡ ቡናቢስ ፡ በሚባል ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ፡ ስሙ ፡ ለውንድዮስ ፡ የሚባል፡ ወዳጁም ፡ ሳለ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንዲት ፡ ሌሊት ፡ ራእይን ፡ አየ ፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የሚደርስ ፡ መሰላል ፡ አለ ። በላዩም ፡ በታላቅ ፡ ዙፋን ፡ ጌታችን ፡ ተቀምጧል ፡ በዙሪያውም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ አእላፍ ፡ መላእክት ፡ ያመሰግናሉ፡ ከበታቹም፡ ታላቅ፡ ከይሲ ፡ ነበረ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ፡ የተቀመጠውም ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ሆይ ፡ ለኔ ፡ ልጄ ፡ ልትሆነኝ ፡ ትወዳለህን ፡ አለው ። ቴዎድሮስም ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አለ ፡ ጌታችንም ፡ እኔ ፡ የአብ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ፡ ለአንተም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ደምህ፡

ከመ ፡ ይትከዐው፡ ደምከ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ፡ ወሶቤሃ ፡ ነሥአ ፡ አሐዱ ፡ እምእለ ፡ ይቀውሙ ፡ ወአጥመቆ ፡ ውስተ ፡ ባሕረ ፡ እሳት ፡ ሠለስተ፡ ጊዜ ፡ ወኮነ፡ ኵለንታሁ ፡ ከመ ፡ እሎንቱ ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡ዓውደ፡መንበሩ።

፱፡ ወይቤሎ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ለእግ ዚእነ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እትፈለጥ ፡ እምዐርክየ ፡ ለውንድዮስ ፡ አውሥአ ፡ እግዚእነ፡ ወይቤሎ ፡ አኮ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ፡ አላ፡ኒቆሮስኒ፡መኰንነ፡ሠራዊተ፡ቀኅዝ፡

፲፡ ወእምዝ፡ርእየ፡ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስ፡ከመ፡ እሙንቱ ፡ መላእክት ፡ መሠጥዎሙ ፡ ለለውን ድዮስ ፡ ወኒቆሮስ ፡ ወአጥመቅዎሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕረ፡እሳት፡ወመጠውዎ፡ኪያሆሙ፡ለቴዎ ድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ወነቂሖ ፡ እምንዋሙ ፡ ነገሮ ፡ ለለውንድዮስ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ ወተ ፈሥሑ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሐ ፡ ወተአምኑ ፡ በበይና ቲሆሙ።

፲፩፡ ወእምዝ ፡ ያረቶሙ ፡ ኃይለ ፡እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘውስቴቱ ፡ ኒቆሮስ ፡ መኰንነ፡ ሠራዊተ ፡ ቀኅዝ ፡ ውእቱኒ ፡ ተቀበሎሙ፡ በፍሥሓ ፡ ወሐቀፎሙ ፡ ወተአምኖሙ ፡ ዘከመ ፡ የአምሮሙ ፡ ወነገሮሙ፡ ዛተ ፡ ራእየ፡ ዘከመ፡እሙንቱ፡ርእዩ፡ወአንከሩ፡ፈድፋደ፡ ወይቤሎ ፡ ኒቆሮስ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ በናድ ሌዎስ ፡ አእምር ፡ አ ፡ እኁየ ፡ ከመ ፡ ኪያየ ፡ ወእኁየ ፡ ለውንድዮስሃ ፡ መጠዉነ ፡ ለከ ፡ ውስተ፡እደዊከ።

፲፪፡ ወእምዝ ፡ ተንሥኡ ፡ ሶቤሃ ፡ ወመጽኡ ፡ ኀበ፡ ሠራዊቶሙ ፡ ወተሰነዓዉ ፡ ከመ ፡ ይክዓዉ ፡ ደሞሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየ ሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

፲፫፡ አሚሃ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ይጸውዖ ፡ ለቴዎ ድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ወይስአሎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገብረ ፡ ሰላመ ፡ ምስለ ፡ ንጉሠ ፡ ቀኅዝ። እስመ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ሶበ ፡ ክህዶ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአምለከ ፡ ጣዖታተ ፡ ተፈሥሐ፡ ፈድፋደ ፡ ሰብአ ፡ ቀኅዝ፡ በእንተ ፡ዝንቱ።

፲፬፡ ወይቤሎሙ ፡ ለሠራዊቱ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ፡ በናድሌዎስ ፡ ዘፈቀደ ፡ ያድኅን ፡ ነፍሶ ፡ እም ሰይፍ ፡ ለይሑር ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡ ወዘሰ ፡ ይፈቅድ፡ ይትጋደል ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግ

ይፈስ፡ዘንድ፡አለህ፡አለው።በዚያንም፡ጊዜ፡ ከቆሙት፡አንዱ፡ወሰደውና፡በእሳት፡ባሕር፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አጠመቀው ፡ ሁለመናውም ፡ በመንበሩ፡ዙሪያ፡እንደቆሙት፡ሆነ።

፱፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስም ፡ ጌታችንን ፡ ከወዳጄ ፡ ከለውንድዮስ ፡ መለየት ፡ አል ሻም፡ አለው ፡ ጌታም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለ ሰለት፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ለቀኅዝ፡ ሠራዊት ፡ መኰንን ፡ የሆነ ፡ ኒቆሮስም ፡ ነው፡ እንጂ።

፲፡ ከዚህም፡በኋላ፡ቴዎድሮስ፡በናድሌዎስ፡አየ፡ እነዚያ ፡ መላእክትም ፡ ለውንድዮስንና፡ ኒቆ ሮስን፡አመጠቋቸው፡ከእሳት፡ባሕር፡ውስጥ፡ አጠመቋቸውና፡እነርሱን፡ለቴዎድሮስ፡በና ድሌዎስ፡ሰጡት፡ከእንቅልፉም፡በነቃ፡ጊዜ፡ ራእይን ፡ እንዳየ ፡ ለለውንድዮስ ፡ ነገረው ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተሳሳሙ።

፲፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቀኅዝ ፡ የሠራዊት ፡ አለቃ፡ ኒቆሮስ፡ወዳለበት፡የእግዚአብሔር፡ኃይል፡ ተሸከመቻቸው ፡ እርሱም ፡ በደስታ፡ ተቀ ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚያውቃቸው ፡ አቅፎ ፡ ሳማቸው ፡ እነርሱም ፡ እንዳዩት ፡ ያንን፡ራእይ፡ነገሩቸው፡እጅግም፡አደነቁ፡ ኒቆሮስም ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስን ፡ እኔ ንና ፡ ወንድሜ ፡ ለወንድዮስን ፡ ለአንተ ፡ በእጅህ፡ እንደሰጡን ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ዕወቅ፡አለው።

፲፪፡ ከዚህም፡በኋላ፡በዚያን፡ጊዜ፡ወደ፡ሠራዊቶ ቻቸው፡መጡ፡በክብር፡ባለቤት፡በጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ስሙ፡ ደማቸውን ሊአፈሱ፡ተስማሙ።

፲፫፡ ከንጉሠ ፡ ቀኅዝ ፡ እንዴት ፡ ዕርቅ ፡ እንዳደረገ፡ ሊጠይቀው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ፡ ወደ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ላከ፡ ዲዮቅልጥ ያኖስ ፡ ጌታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ክዶ ፡ ጣዖታትን ፡ በአመለከ ፡ ጊዜ ፡ ስለዚህ ፡ የቀኅዝ፡ሰዎች፡እጅግ፡ደስ፡ብሏቸዋልና።

፲፬፡ የከበረ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድልዮስም ፡ ሠራ ዊቱን ፡ ነፍሱን ፡ ከሰይፍ ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ፡ ወደ ፡ ፈለገው ፡ ይሒድ ፡ የክብር፡ ባለቤት ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
ይንበር ፡ ምስሌነ ። ወዘሎሙ ፡ ከልሐ ፡ በል
ዑል ፡ ቃል ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ እስመ ፡ ሞተ ፡
ዘትመውት ፡ ቦቱ ፡ ንሕነ ፡ ንመውት ፡ ምስ
ሌከ ፡ ወአምላክከ ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ፡
ወይቤሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ብፁዕ ፡ ቴዎድሮስ ፡
ለእመ ፡ እሙን ፡ ነገርክሙ ፡ ረዱ ፡ ኵልክሙ ፡
ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ፈለግ ፡ ወተጠመቁ ፡ ሠለ
ስተ ፡ ጊዜ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
፲፩ ፡ ወሶቤሃ ፡ አውጽኡ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወወረዱ ፡
ውስተ ፡ ፈለግ ፡ ወተጠምቁ ፡ በከመ ፡
ይቤሎሙ ፡ ወእንዘ ፡ የዐርጉ ፡ እማይ ፡ ሰምዑ ፡
ቃለ ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ጽንዑ ፡ ሰማዕ
ታትየ ፡ ወኩኑ ፡ መዋዕያነ ፡ እስመ ፡ አነ ፡
እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ።
፲፪ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድ
ሌዎስ ፡ ኀበ ፡ ቅሩበ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡
ኀደጎሙ ፡ ለሠራዊቱ ፡ አፍአ ፡ ሀገር ፡ ወቦአ ፡
ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ዐርካኒሁ ፡ ለውንድዮስ ፡
ወኒቆሮስ ፡ ወንጉሥኒ ፡ ተቀበሎ ፡ በክብር ፡
ወተሰአሎ ፡ በእንተ ፡ ዜና ፡ ጾብእ ፡ ወበእንተ ፡
ሠራዊቱ ፡ ውእቱኒ ፡ ነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ።
፲፫ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ዘከረ ፡ በቅድሜሁ ፡ ሰጊዶ ፡
ለአጽሎን ፡ ቅዱስሰ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድ
ሌዎስ ፡ ገሠጾ ፡ ወረገሞ ፡ ለንጉሥ ፡ ወከማሁ ፡
ዐርካኒሁ ፡ ለውንድዮስ ፡ ወኒቆሮስ ፡ ረገምዎ ፡
ለንጉሥ ፡ ውእቱኒ ፡ ተምዐ ፡ ወአዘዘ ፡ ይሰ
ድዎሙ ፡ ለለውንድዮስ ፡ ወኒቆሮስ ፡ ሀገረ ፡
ሚዶን ። ወበህየ ፡ ይኰንንዎሙ ፡ እስመ ፡ ዲዮ
ቅልጥያኖስ ፡ ፈርሀ ፡ እምነ ፡ ሰብአ ፡ ፋርስ ፡
በእንተ ፡ ኒቆሮስ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መኰንነ ፡
ሠራዊተ ፡ ፋርስ ፡ ወሶበ ፡ ኰነንዎሙ ፡ በህየ ፡
ለለውንድዮስ ፡ ወለኒቆሮስ ፡ ቢጾ ፡ ወነሥኡ ፡
አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ለጥር ፡ በዛቲ ፡
ዕለት ።
፲፬ ፡ ወለቅዱስሰ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ አዘዘ ፡
ከመ ፡ ያስክብዎ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀ ፡ ኮሞል ፡ ዐቢይ ፡
ወይቀንውዎ ፡ በ፻ወ፶ወ፲ ቅንዋተ ፡ ኀፂን ፡
ነዋኀት ፡ ወፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሚካ
ኤልሃ ፡ መልአኮ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአጽንዖ ፡ በኵሉ ፡
ምንዳቤሁ ።

ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ግን ፡ መጋደልን ፡ የሚሻ ፡
ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ አላቸው ። ሁሉም ፡
በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ አንተ ፡ የምትሞትበትን ፡
ሞት ፡ እኛ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እንሞታለን ፡ አምላ
ክህም ፡ አምላካችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጮኹ ፡
የተመሰገነ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ዳግመኛ ፡
ነገራችሁ ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ ሁላችሁም ፡
ወደዚህ ፡ ወንዝ ፡ ወርዳችሁ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ሦስት ጊዜ ፡
ተጠመቁ ፡ አላቸው ።
፲፩ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ልብሳቸውን ፡ አውልቀው ፡
ወደ ፡ ወንዙ ፡ ወርደው ፡ እንዳላቸውም ፡
ተጠመቁ ፡ ከውኃውም ፡ ሲወጡ ፡ ከሰማይ ፡
እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃልን ፡ ሰሙ ፡ ምስክሮቼ ፡
በርቱ ፡ ጽኑ ፡ አሸናፊዎችም ፡ ሁኑ ፡ እኔ ፡
ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁና ።
፲፪ ፡ የከበረ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስም ፡ ወደ ፡
አንጾኪያ ፡ ከተማ ፡ አቅራቢያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
ሠራዊቱን ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ትቶ ፡ ከሁለቱ ፡
ወዳጆቹ ፡ ከለውንድዮስና ፡ ከኒቆሮስ ፡ ጋር ፡
ገባ ፡ ንጉሥም ፡ በክብር ፡ ተቀብሎ ፡ ስለ ፡
ጦርነት ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ ሠራዊቱም ፡ ጠየቀው ፡
እርሱም ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ።
፲፫ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለአጵሎን ፡ ስለ ፡ መስገድ ፡
አወሳ ፡ የከበረ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስም
ንጉሡን ፡ ገሠጸው ፡ ዘለፈውም ፡ እንዲሁም ፡
ወዳጆቹ ፡ ለውንድዮስና ፡ ኒቆሮስ ፡ ንጉሡን ፡
ረገሙት ፡ እርሱም ፡ ተቆጣ ፡ ለውንድዮስንና ፡
ኒቆሮስን ፡ ወደ ፡ ሚዶን ፡ አገር ፡ ወስደው ፡
በዚያ ፡ ያሠቃዩአቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።
ኒቆሮስ ፡ የፋርስ ፡ ሀገር ፡ የሠራዊት ፡ አለቃ ፡
መኰንን ፡ ስለነበረ ፡ ከፋርስ ፡ ሰዎች ፡ የተነሣ ፡
ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ፈርቷልና ፡ በዚያም ፡ ለውን
ድዮስንና ፡ ኒቆሮስን ፡ በአሠቃዩአቸው ፡ ጊዜ ፡
በዚች ፡ ቀን ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ የሰማዕ
ትነት ፡ አክሊልን ፡ ተቀበሉ ።
፲፬ ፡ የከበረ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስን ፡ ግን ፡
ኮሞል ፡ በሚባል ፡ ታላቅ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ አስ
ተኝተው ፡ ቊጥራቸው ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡
ሦስት ፡ በሆኑ ፡ በረጃጅም ፡ የብረት ፡ ችን
ካሮች ፡ እንዲቸነክሩት ፡ አዘዘ ። እግዚአብ
ሔርም ፡ መልአኩን ፡ ሚካኤልን ፡ ወደርሱ ፡
ልኮ ፡ በመከራው ፡ ሁሉ ፡ አጸናው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አስተርአዮ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎተ ፡ ስብሐት ፡ ወይቤሎ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡ ኅሩይየ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብፁዕ ፡ እንተ ፡ እስመ ፡ ተዓገሥከ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ሕማመ ፡ በእንተ፡ ስምየ ፡ ትፌቅድኑ ፡ አውጽአሙ ፡ ለእሉ ፡ ኀፃውንት ፡ እምሥጋከ፡ ወአሕዩከ ፡ ከመ ፡ ታስተኃፍሮ ፡ ለዝንቱ ፡ ዕልው ፡ ንጉሥ።

፳፡ ወይቤሎ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ለእግዚእነ፡ እምይእዜሰ ፡ ይኄይሰኒ ፡ መዊት ፡ በእንተ ፡ ስምከ ፡ ቅዱስ።

፳፩፡ ወይቤሎ ፡ ካዕበ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አ ፡ ፍቁርየ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ናሁ ፡ አስተዳለውኩ ፡ ለከ ፡ ፫ተ ፡ አክሊላተ ፡ አሐዱ ፡ በእንተ ፡ ድንግልናከ ፡ ወካልኡ ፡ በእንተ ፡ ዘመነንከ ፡ ክብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወተወክፎትከ ፡ ፃማ ፡ ወሣልሱ ፡ በእንተ ፡ ክዕወተ ፡ ደምከ ፡ በእንተ ፡ ስምየ።

፳፪፡ ወእነ ፡ እሁበከ ፡ ኪዳነ ፡ ለዘይጼውዕ ፡ ስመከ ፡ ወይገብር ፡ ተዝካረከ ፡ ከመ ፡ አድኅኖ ፡ እምኵሎ ፡ ምንዳቤሁ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ፡ ለዘሂ ፡ ወሀበ ፡ ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወለዘአብአ ፡ መባአ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእንቲአከ ፡ ወለዘጸሐፈ ፡ ወአጽሐፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ገድልከ ፡ ወለዘሐነፀ ፡ መርጡለከ ፡ አነ ፡ እሰሪ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ወአወርሶሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። ወእምድኅረ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚእነ ፡ ዘንተ ፡ ኪዳነ ፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወርእየ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሠለስተ ፡ መላእክተ ፡ እንዘ ፡ ይሜጥውዎ ፡ ሠለስተ ፡ አክሊላተ ፡ ወሶቤሃ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ቅድስተ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር።

፳፫፡ ወእምድኅረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ገነውተ ፡ አማልክት ፡ ኀበ ፡ ሠራዊቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ያስግድዎሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ይዑድ ፡ ዓዋዲ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዘያፈቅሮ ፡ ለንጉሥ ፡ ይስግድአ ፡ ለአማልክት ፡ ወከልሐ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ወይቤሉ ፡ አልቦ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

፲፱፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተገለጸለትና ፡ የመረጥኩህ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ይሁንልህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ታግሠሃልና ፡ ብፁዕ ፡ ነህ ፡ ይህን ፡ ከሀዲ ፡ ንጉሥ ፡ ታሳፍረው ፡ ዘንድ ፡ እሊህን ፡ ብረቶች ፡ ከሥጋህ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቼ ፡ እንዳድንህ ፡ ትሻለህን ፡ አለው።

፳፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስም ፡ ጌታችንን ፡ እንግዲህስ ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡ ስምህ ፡ መሞት ፡ ይሻለኛል ፡ አለው።

፳፩፡ ሁለተኛም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዳጄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ ሦስት ፡ አክሊላትን ፡ አዘጋጅቼልሃለሁ ፡ አንደኛው ፡ ስለ፡ ድንግልናህ፡ ሁለተኛው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ ትተህ ፡ መከራ ፡ ስለመቀበልህ ፡ ሦስተኛው ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ደምህን ፡ ስለ ፡ አፈሰስክ ፡ ነው ፡ አለው።

፳፪፡ እኔም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ሰጠሁህ ፡ ስምህን ፡ ለሚጠራና ፡ መታሰቢያህን ፡ ለሚያደርግ ፡ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ አድነው ፡ ዘንድ ፡ ለድኆችም ፡ ምጽዋት ፡ የሰጠውን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባ ፡ ያገባውን ፡ የገድልህን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈውንና ፡ ያጻፈውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንህንም ፡ የሠራውን ፡ ሁሉንም ፡ ኃጢአቱን ፡ ይቅር ፡ ብዬ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አወርሰዋለሁ። ጌታችንም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ሦስቱን፡ አክሊሎች ፡ ሲሰጡት ፡ ሦስቱን ፡ መላእክት ፡ አየ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የከበረች፡ ነፍሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ሰጠ።

፳፫፡ ቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስም ፡ ከአረፈ ፡ በኋላ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ለጣዖታት ፡ ያሰግዱአቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ፡ ሠራዊት ፡ የጣዖታቱን ፡ ካህናት፡ ላከ ፡ ሁለተኛም ፡ ንጉሥን ፡ የሚወድ ፡ ለአማልክት ፡ ይስገድ ፡ እያለ ፡ የሚዞር ፡ ዓዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ አዘዘ። የቴዎድሮስ ፡ በናድሌዎስ ፡ ሠራዊትም ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ የጌቶች ፡ ጌታ ፡ ከሆነ ፡ ከጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር፡

www.ethiopianorthodox.org

ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኄር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ለርሱም ፡ ከቸር ፡ አባቱ ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ከሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋር ፡ ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሑረትከ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ከብካብ ፡ በፍቅር ። ከመ ፡ ታውይን ፡ ማየ ፡ እግዚአብሔር ። ዝንቱ ፡ ኃይልከ ፡ ዘበኀቤነ ፡ መንክር ። ለከሰ ፡ አልቦ ፡ ዘይሰአነከ ፡ ግብር ። እስመ ፡ ገባሪሆሙ ፡ አንተ ፡ ለሰማይ ፡ ወምድር።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ወመንፈስ ፡ቅዱስ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፫ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፉ ፡ ፯ቱ ፡ ደቂቅ ፡ እለ ፡ አስማቲሆሙ ፡ አር ሰሌዳስ፡ዱአሚዶስ፡አውጋንዮስ፡ድሜጥሮስ፡ ብርጥስ፡እስጢፋኖስ፡ኪራኮስ።

፪፡ ወእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ውሉዶሙ ፡ ለዐበይተ ፡ ሀገር፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአስተዋደይዎሙ ፡ ሰብእ፡ኀበ፡ዳኬዎስ፡ንጉሥ፡ዓላዊ፡ከመ፡ክር ስቲያን፡እሙንቱ፡ወአስተባጽሐሙ፡ኀቤሁ፡ ወአገበሮሙ፡ከመ፡ይስግዱ፡ለጣዖት፡ወሶበ፡ ዐበይዎ፡ወሀቦሙ፡ዕድሜ፡ከመ፡ይትማከሩ፡ ምስለ፡ ነፍሶሙ፡ ወሖረ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ተግባሩ።

፫፡ ወእሉ፡ሰብዓቱ፡ደቂቅ፡ቡሩካን፡ሖሩ ውስተ፡ አብያቲሆሙ ፡ ወዘረዉ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወዘተርፈ ፡ ዲና ራተ፡ ለመፍቅዶሙ ፡ ነሥኡ ፡ ወሖሩ ፡ ወተኀብኡ፡ውስተ፡በዓት፡ዘምሥራቀ፡ሀገር፡ ወዱአሚዶስ፡ወሬዛ፡ጠቢብ፡ወለባዊ፡ኮነ፡ ዘይትለአኮሙ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወይሣየጥ ፡ ሲሳዮሙ፡ወይነግሮሙ፡ነገረ፡ዘሰምዐ።

፬፡ ወሶበ ፡ ተመይጠ ፡ ዳኬዎስ ፡ ንጉሥ ፡ እምኀበ፡ ሖረ ፡ ኀሠሦሙ ፡ ለእሉ ፡ ፯ቱ ፡ ደቂቅ፡ ወሶበ ፡ ነገርዎ ፡ ከመ ፡ ሀለዉ ፡ ኀቡአ ፡ ውስተ፡ በዓት ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይድፍኑ ፡ አፈ ፡ በዓት ፡ በአዕባን ፡ ወለእሉሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ነሥአ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ እግዚእነ ፡ ሶበ ፡ ኖሙ ፡ ወረሰዮሙ ፡ ይኑሙ ፡ ፫፻ ፡ ፸፪ ፡ ፸ወ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ ወሀለዉ ፡ እምወ ዓልተ ፡ ንጉሥ ፡ ዘስሞሙ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወመቅ ዶስዮስ ፡ ነሥኡ ፡ ፪ተ ፡ ጽላተ ፡ ዘአረር ፡ ወጸሐፉ፡ ዜናሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ፯ቱ ደቂቅ ፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡ዐሥራ፡ሦስት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ስማቸው ፡ አርሰሌዳስ ፡ ዱአ ሚዶስ ፡ አውጋንዮስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ብርጥስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ኪራኮስ ፡ የተባሉ ፡ ሰባቱ ፡ ደቂቅ፡ አረፉ።

፪፡ እሊህ ፡ ቅዱሳንም ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ለቀና ፡ ለታላላቅ ፡ የሀገር ፡ ሰዎች ፡ ልጆቻቸው ፡ ናቸው፡ እነርሱም ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንደሆኑ ፡ በከሀዲ፡ንጉሥ፡ዳኬዎስ፡ዘንድ፡ሰዎች፡ነገር፡ ሠሩባቸው ፡ ወደርሱም ፡ አስቀርቦ ፡ ለጣዖት ፡ እንዲሰግዱ ፡ ግድ ፡ አላቸው ፡ እምቢ ፡ ባሉ ትም፡ጊዜ፡ከልባቸው፡ጋር፡ይመክሩ፡ዘንድ፡ ቀጠሮ ፡ ሰጣቸውና ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ተግባሩ ፡ ሔደ።

፫፡ እሊህ ፡ የተባረኩ ፡ ሰባቱ ፡ ደቂቅም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው፡ሔዱና፡ገንዘባቸውን፡ለድኆችና፡ ለምስኪኖች ፡ በተኑ ፡ የቀረውንም ፡ ለስን ቃቸው ፡ ይዘው ፡ ሔዱ ፡ ከከተማውም ፡ በስተ ምሥራቅ፡በዋሻ፡ውስጥ፡ተሠወሩ፡ብልህና፡ አስተዋይ፡የሆነ፡ወጣት፡ዱአሚዶስ፡ወደ፡ ከተማ፡ሒዶ፡ምግባቸውን፡በመግዛት፡የሚ ያገለግላቸው፡ሆነ፡የሰማውንም፡ነገር፡ይነግ ራቸዋል።

፬፡ ንጉሥ ፡ ዳኬዎስም ፡ ከሔደበት ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ እሊህን ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ ፈለጋቸው ፡ በዋሻ፡ውስጥ፡ተሸሽገው፡እንዳሉ፡በነገሩት፡ ጊዜ፡የዋሻውን፡አፍ፡በደንጊያ፡እንዲደፍኑ፡ አዘዘ ፡ የእነዚህንም ፡ ቅዱሳን ፡ ነፍሳቸውን ፡ በተኙ፡ጊዜ፡ጌታችን፡ወሰደ።ሦስት፡መቶ፡ ሰባ፡ሁለት፡ዓመትም፡እንዲአንቀላፉ፡አደረ ጋቸው ፡ ከንጉሥ ፡ አሽከሮችም ፡ ስማቸው ፡ ቴዎድሮስና ፡ መቅዶስዮስ ፡ የተባሉ ፡ ሁለት ፡ የእርሳስ ፡ ሠሌዳዎች ፡ ወስደው ፡ የእሊህን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሐሳበ፡መዋዕሊሁ፡ወአንበሩ፡ውስተ፡አፈ፡
በዓት።

፳፫፡ ወእምድኅረዝ ፡ ሞተ ፡ ዳኬዎስ ፡ ወነግሡ ፡
ብዙኃን ፡ ነገሥት ፡ እስከ ፡ መዋዕለ ፡ መን
ግሥቱ፡ለቴዎዶስዮስ፡ንጉሥ፡ኄር፡ወበመዋ
ዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ኄር ፡ ንጉሥ ፡ ተንሥኡ ፡
ሰብእ፡ዕልዋን፡እለ፡ይብሉ፡አልቦ፡ትንሣኤ፡
ሙታን ፡ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጊዜ ፡ ነቂሖቶሙ ፡
አርኃወ፡በዓቶሙ፡አሐዱ፡መኰንን፡እንዘ፡
የኀሥሥ፡አዕባነ፡ከመ፡ያሕንፅ፡ለአባግዒሁ፡
ማኅደረ።

፳፬፡ወነቂሖሙ፡በ፫፻፸ወ፪ቱ፡ዓመት፡እሙንቱ፡
ቅዱሳን ፡ ፈነውዎ ፡ ለዱአሚዶስ ፡ ከመ ፡
ይሣየጥ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ሰብአ ፡
ሀገር፡ዲናረ፡ውስተ፡እዴሁ፡ዘጽሑፍ፡ስመ፡
ዳኬዎስ፡ንጉሥ፡አኀዝዎ፡ወአብጽሕዎ፡ኀበ፡
መኳንንት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ እስመ ፡ መሰ
ሎሙ ፡ ዘረከበ ፡ መድፍነ ፡ ወሶበ ፡ ሐተትዎ ፡
ነገሮሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ፡ ሰብኡ ፡ ደቂቅ ፡
ወሐዊሮሙ ፡ ረከብዎሙ ፡ እንዘ ፡ ይበርህ፡
ገጾሙ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ ወርእየ፡ ኤጲስቆጶስ ፡
ጽላተ ፡ ዘዓረር ፡ ወነሢኦ ፡ አንበበ ፡ ዘጽሑፍ ፡
ዲቤሁ ፡ ዜናሆሙ ፡ ወመዋዕሊሁ ፡ ወሰ
ሚያሙ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ በመዋዕለ ፡ ዳኬዎስ ፡
ኖሙ ፡ ወአንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሐዎ፡ ለእግ
ዚአብሔር።

፳፭፡ ወእምዝ ፡ ለአኩ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎድስዮስ፡
ወበጺሖ ፡ ንጉሥ ፡ ተአምኆሙ ፡ ወተባረከ ፡
እምኔሆሙ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወእምድኅረ፡
ተዚያነዉ ፡ ባረክዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ወሰከቡ፡
ውስተ ፡ ምድር ፡ ወመጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ ውስተ ፡
እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቀበርዎሙ፡ ውስተ ፡
ይእቲ፡በዓት።

፳፮፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡
ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም፡አሜን።

የሰባቱ ፡ ደቂቅን ፡ ዜናቸውንና ፡ የዘመኑን ፡
ቍጥር ፡ ጽፈው ፡ ቀርጸው ፡ ከዋሻው ፡ አፍ ፡
አኖሩት።

፳፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳኬዎስ ፡ ሞተ ፡ እስከደጉ ፡
ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መን
ግሥት ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ነገሡ ፡ በዚህም፡
ደግ፡ንጉሥ፡ዘመን፡ትንሣኤ፡ሙታን፡የለም፡
የሚሉ፡ከሀድያን፡ሰዎች፡ተነሡ፡እሊህም፡
ሰባቱ ፡ ደቂቅ ፡ የሚነቁበት ፡ ጊዜ ፡ ሲቀርብ ፡
ለበጎቹ ፡ ማደሪያ ፡ ሊአሠራ ፡ ሽቶ ፡ ደንጊያ ፡
እየፈለገ፡የዋሻቸውን፡አፍ፡አንድ፡መኰንን፡
ከፈተው።

፳፬፡እሊህ፡ቅዱሳንም፡በሦስት፡መቶ፡ሰባ፡ሁለት፡
ዓመት ፡ በነቁ ፡ ጊዜ ፡ ምግባቸውን ፡ ይገዛ ፡
ዘንድ ፡ ዱአሚዶስን ፡ ላኩት ፡ የአገር፡ ሰዎ
ችም፡ የዳኬዎስ ፡ ስም ፡ የተጻፈበትን ፡ ዲናር ፡
በእጁ ፡ ውስጥ ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ የተሸሸገ ፡ የወርቅ ፡
ሣጥን፡ያገኘ፡መስሎአቸዋልና፡ይዘው፡ወደዳ
ኞቹና፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አቀረቡት ፡ በመረመ
ሩትም ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡
እንደሆኑ ፡ ነገራቸው ። በሔዱም ፡ ጊዜ ፡
ፊታቸው፡እንደ፡ፀሐይ፡ሲበራ፡አገኙአቸው፡
ኤጲስቆጶሱም ፡ የዕርሳስ ፡ ሠሌዳ ፡ አየ ፡
አንሥቶም፡በላዩ፡የተጻፈውን፡ዜናቸውንና፡
የዘመኑን፡ቍጥር፡አነበበ፡በዳኬዎስ፡ዘመን፡
እንዳንቀላፉ ፡ ሕዝቡ ፡ ሰምተው ፡ እጅግ ፡
አደነቁ፡እግዚአብሔርንም፡አመሰገኑት።

፳፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡
ላኩ፡ እርሱ ፡ መጥቶ ፡ እጅ ፡ ነሣቸው ፡ ከእርሳ
ቸውም ፡ ተባረከ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ከተነጋ
ገሩም ፡ በኋላ ፡ ሁሉንም ፡ ባረኳቸውና፡
በምድር፡ላይ፡ተኙ፡ነፍሳቸውንም፡በእግዚአ
ብሔር፡እጅ፡ሰጡ፡በዚያቹም፡ዋሻ፡ውስጥ፡
ቀበሩአቸው።

፳፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡
የእሊህም ፡ ቅዱሳን ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

አርኬ

ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ደቂቀ ፡ ሐሳብ ፡ ሱባዔ ። ዘነበርክሙ ፡ ክቡዳነ ፡ እምንዋመ ፡ ፍርሀት ፡ ወምማዓ ። በላዕለ፡
እምድኅረ፡ሠለስቱ፡ምእት፡ዓመታት፡ዘምስለ፡ሰብዓ፡ወክልኤ።ነቂሖተክሙ፡ሶበ፡ነጸሩ፡ጉባዔ።
ምውታን፡አእመሩ፡ዘይከውን፡ትንሣኤ።

ሰላም፡እብል፡ለኤጲፋንያ፡ሣልሲት።እንተ፡ይጠመቁ፡ባቲ፡ዘኢተጠምቁ፡ትካት።ለእለ፡ኢገብሩ፡
ቀዳሚ ፡ ምስለ ፡ ትዕይንት ። ለአንጽሖ ፡ ነፍስ ፡ አመ ፡ ሠርቀ ፡ ወርኀ ፡ ካልዕት ። ከመ ፡ ፋሲካ ፡ ይግበሩ ፡
ትኤዝዝ፡ኦሪት።

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቃሮስ ፡ ወሰሚኖስ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለም፡ዓለም፡አሜን።

፲፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ፡አባ፡ነካሮ፡ ወዝንቱ፡ ቅዱስ፡ኮነ፡መስተጋድለ፡በኀቡእ፡ዘእንበለ፡ ያእምሮ፡ሰብእ፡ወውእቱ፡ይሬሲ፡አስዋከ፡ ታሕተ፡መንጸፉ፡ከመ፡ኢይኑም፡በጥዒና፡ ወይትግህ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፡ለጸሎት።

፲፩፡ ወእምብዝኀ፡ትሕትናሁ፡ረሰይዎ፡ዓቃቤ፡ ኖኀት ፡ ወሀሎ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ፡ መነኮስ ፡ ባሕታዊ ፡ ዘይሬኢ ፡ ኅቡአተ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወርእየ ፡ በአሐቲ ፡ ሌሊት፡በንዋሙ፡እንዘ፡ይቀውም፡ውስተ፡ መካን ፡ ልዑል ፡ ወመትሕቴሁ ፡ ገነት ፡ ዘዘዚአሁ፡ፍሬሁ፡ወየዓውድዎ፡አፍላግ፡ ወሀሎ ፡ ማዕከሎሙ ፡ አባ ፡ ነካሮ ፡ ወይሰ ቅዮሙ፡በለፌ፡ወለፌ። ወይቤሎ፡ውእቱ፡ መነኮስ፡አ፡እኍየ፡ነካሮ፡ዘመኑ፡ዛቲ፡ ገነት፡አውሥአ፡አባ፡ነካሮ፡ወይቤሎ፡አነ፡ ተከልክዋ ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ መነኮስ ፡ እፈቅድ፡ከመ፡ተሀበኒ፡እምነ፡ፍሬሃ፡ወአባ፡ ነካሮ፡መተረ፡ሠለስተ፡ፍሬያተ፡ሮማን፡ ወመጠዎ፡ወአሠሮ፡ውስተ፡ልብሱ።

፲፪፡ ወሶበ፡ነቅሐ፡እምንዋሙ፡ረከቦሙ፡ለእሉ፡ ፍሬያተ፡ሮማን፡ወበጊዜሃ፡ሖረ፡ኀበ፡አባ፡ ነካሮ፡ወረከቦ፡ቀዊሞ፡ውስተ፡አንቀጽ፡ ወይቤሎ፡አ፡እኍየ፡ነካሮ፡ርኢከኒኑ፡በዛቲ፡ ሌሊት፡ወይቤሎ፡እወ፡ርኢኩከ፡አኮኑ፡ ወሀብኩከ ፡ ሠለስተ ፡ ፍሬያተ ፡ ሮማን ። ወውእተ፡ጊዜ፡ሖረ፡ውስተ፡ምኔት፡ውእቱ፡ መነኮስ፡ነገሮሙ፡ለአበ፡ምኔት፡ወለመነ ኮሳት፡ዘኮነ፡ኵሎ፡ወአርአዮሙ፡እሎንተ፡ ፍሬያተ፡ሮማን፡ወአንከሩ፡አኃው፡እምቅድ ስናሁ፡ለአባ፡ነካሮ፡እስመ፡ኮነ፡አሚሃ፡ ዘመነ፡ኃጋይ፡ወኢኮነ፡ጊዜሁ፡ለሮማን።

፲፫፡ ወኀዘኑ ፡ መነኮሳት ፡ በእንተ ፡ ዘረሰይዎ ፡ ውስተ ፡ ትሑት ፡ መዓርግ ፡ ወፈቀዱ ፡ ያዕ ብይዎ፡ሶበ፡ሐሩ፡ኀቤሁ፡ኃጥእዎ፡ወኀዘኑ፡ ዐቢየ፡ኀዘነ፡ወእምዝ፡ነገርዎሙ፡ፈላስያን፡

፱፡በዚችም፡ዕለት፡የቃሮስና፡የሰሚኖስ፡መታሰ ቢያቸው፡ነው፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

፲፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ አባ ፡ ነካሮ ፡ አረፈ ፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ሳያውቀው ፡ በሥውር ፡ የሚ ጋደል ፡ ሆነ ፡ እርሱም ፡ ከምንጣፉ ፡ በታች ፡ እሾህ ፡ ይጐዘጕዛል ፡ ጤና ፡ አግኝቶ ፡ እንዳ ይተኛ፡ነው፡በቀንና፡በሌሊትም፡ለጸሎት፡ ይተጋ፡ነበር።

፲፩፡ ከትሑትነቱም ፡ የተነሣ ፡ የበር ፡ ጠባቂ፡ አደረጉት ። በዚያም ፡ ገዳም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተሠወሩ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያይ ፡ ባሕታዊ ፡ መነኮስ ፡ አለ ፡ በአንዲትም ፡ ሌሊት፡በሕልሙ፡በከፍታ፡ቦታ፡ላይ፡ቆሞ፡ አየ፡ከበታቹም፡ፍሬው፡በየዓይነቱ፡የሆነ፡ አትክልት ፡ አለ ፡ ወንዞችም ፡ ከበውታል ፡ አባ፡ ነካሮም ፡ በመካከላቸው ፡ ሁኖ ፡ በወዲያና፡በወዲህ፡ያጠጣቸው፡ነበር። ያ፡ መነኮስም ፡ ወንድሜ ፡ ነካሮ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ አትክልት ፡ የማን ፡ ነው ፡ አለው ፡ አባ ፡ ነካሮም ፡ እኔ ፡ የተከልኳት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ መነኰሴውም፡ ከፍሬዋ ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፡ አባ ፡ ነካሮም ፡ ሦስት ፡ የሮማን ፡ ፍሬ ፡ ቆርጦ ፡ ሰጠው፡በልብሱም፡ቋጠረው።

፲፪፡በነቃም፡ጊዜ፡እነዚያን፡የሮማን፡ፍሬዎች፡ አገኛቸው ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ነካሮ ፡ ሔደ፡ ከበር ፡ ቆሞ ፡ አገኘውና ፡ ወንድሜ ፡ ነካሮ፡ሆይ፡በዚች፡ሌሊት፡አይተኸኛልን፡ አለው ፡ እርሱም ፡ አዎን ፡ አይቼሃለሁ ፡ ሦስት፡ የሮማን ፡ ፍሬዎችን ፡ ሰጥቼህ ፡ የለ ምን፡አለው። በዚያንም፡ጊዜ፡ያ፡መነኰሴ፡ ወደ፡ገዳሙ፡ሔዶ፡የሆነውን፡ሁሉ፡ለአበ፡ ምኔቱና ፡ ለመነኮሳቱ ፡ ነገራቸው ፡ እነዚ ያንም፡የሮማን፡ፍሬዎች፡አሳያቸው፡መነ ኮሳቱም፡ከአባ፡ነካሮ፡ቅድስና፡የተነሣ፡ አደነቁ፡ያን፡ጊዜም፡የበጋ፡ወራት፡ነበረና፡ የሮማንም፡ጊዜው፡አልነበረምና።

፲፫፡ በዝቅተኛ ፡ ማዕረግ ፡ ላይ ፡ ስለአደረጉት ፡ መነኮሳቱ ፡ አዘኑ ፡ በከፍተኛም ፡ ማዕረግ ፡ ሊያደርጉት ፡ ሽተው ፡ ወደርሱ ፡ በሔዱ ፡ ጊዜ፡ አጡት ፡ ታላቅ ፡ ኀዘንንም ፡ አዘኑ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ እንዳረፈ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ፡አዕረፈ፡በዛቲ፡ዕለት።
፲፬፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

መጻተኞች፡ነገሩአቸው።
፲፬፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለብፁዕ፡ነካሮ።መልዕልተ፡አስዋክ፡ዘይነውም፡በታሕተ፡መንጸፉ፡ገቢሮ።እንተ፡እምኔሁ፡በሕልም፡ዘነሥአ፡ብእሴ፡አእምሮ።ረከበ፡በጊዜ፡ንቃሑ፡እስከ፡አንከረ፡አንክሮ።ፍሬያተ፡ሮማን፡ሠለስተ፡በልብሱ፡አቍሮ።

***

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፲ ወ፬ ለጥር፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነት ፡ ሰማዕተ ፡ ቅድስት ፡ ወኅሪት ፡ ምህራኤል፡ዘእምሰብአ፡ሀገረ፡ጠምዋህ፡

፪፡ ወለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ አበዊሃ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈራህያነ፡እግዚአብሔር። ወአቡሃ፡ቀሲስ፡ ዘስሙ፡ዮሐንስ፡ወእማኒ፡ኢላርያ፡ኄርት፡ ይእቲ፡ወባሕቲ፡አልቦሙ፡ውሉድ፡ወእን በይነ፡ዝንቱ፡የኀዝኑ፡ወይስእሉ፡ኀበ፡እግዚ አብሔር፡ ወእምድኅረ፡ጕንዱይ፡መዋዕል፡ ተጸገዉ፡ዛተ፡ወለተ፡ቅድስተ፡ወሰመይዋ፡ ስማ፡ምህራኤልሃ።

፫፡ወሶበ፡ኮና፡፲ወ፪ተ፡ዓመተ፡አኀዘት፡ትግበር፡ ተአምራተ፡ወመንክራተ፡በጸጋ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡ዘኀዱር፡ላዕሌሃ።

፬፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተንሥአ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ዕልው ፡ ወጽአት ፡ ውስተ ፡ ጽንፈ ፡ ባሕር፡ወረኪባ፡ሐመረ፡ተጽዕነት፡ዲቤሁ፡ ወሖረት ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ ለስምዕ ፡ ወበጺሖ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እንጽና ፡ ቆመት ፡ ቅድመ፡ መኰንን ፡ ዘስሙ ፡ ፍልፍልያኖስ ወሶበ፡ርእያ፡መሐካ፡በእንተ፡ነዓስ፡አካላ፡ ወፈቀደ፡ይኅድጋ፡ወይእቲ፡አእሚራ፡ከመ፡ ይፈቅድ፡ይኅድጋ፡ረገመቶ፡ኪያሁ፡ወአማል ክቲሁ፡ርኩሳነ፡በተሀብሎ። ወእንበይነዝ፡ ተምዐ፡መኰንን፡ወኰነና፡ጽኑዐ፡ኰነኔ፡ ወሶበ፡ስእነ፡ይሒጣ፡እምሃይማኖታ፡ርት ዕት፡ አዘዞሙ ፡ ለመሠግራን ፡ ያስተጋብኡ፡ አቃርብተ፡ወአፍዖታተ፡ ወአክይስተ፡ ወይደ ይዎሙ፡ውስተ፡ሐሰል፡ወኪያሃኒ፡ይደዩ፡ ውስተ፡ሐሰል፡ምስሌሆሙ፡ወከመዝ፡ገብሩ፡

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥር፡ዐሥራ፡አራት፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ጠምዋህ ፡ ከሚባል ፡ ሀገር ፡ ሰዎች፡የከበረችና፡የተመረጠች፡ምህራኤል፡ በሰማዕትነት፡አረፈች።

፪፡ የዚችም፡ቅድስት፡ወላጆቿ፡እግዚአብሔርን፡ የሚያመልኩ፡ክርስቲያኖች፡ናቸው፡አባቷም፡ ስሙ፡ዮሐንስ፡የሚባል፡ቄስ፡ነው፡እናቷም፡ ኢላርያ፡የምትባል፡ደግ፡ናት። ነገር፡ግን፡ ልጅ፡ስለሌላቸው፡ስለዚህ፡እያዘኑ፡ወደ፡እግ ዚአብሔር፡ ይለምኑ፡ነበር፡ከብዙ፡ዘመንም፡ በኋላ፡ይህችን፡የከበረች፡የተቀደሰች፡ልጅ፡ ተሰጠቻቸው፡ስሟንም፡ምህራኤል፡ብለው፡ ጠርዋት።

፫፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመትም ፡ በሆናት ፡ ጊዜ ፡ በላይዋ፡በአደረ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስጦታ፡ ድንቆች፡ተአምራቶችን፡መሥራት፡ጀመረች።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከሀዲ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥ ያኖስ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ወጣች ፡ መርከብም ፡ አግኝታ ፡ በላዩ ፡ ተሳፈረች፡ለሰማዕትነት፡ከሚሔዱት፡ጋር፡ በመሔድ፡ወደ፡እንጽና፡ከተማ፡በደረሰች፡ ጊዜ፡ስሙ፡ፍልፍልያኖስ፡በሚባል፡መኰ ንን፡ፊት፡ቆመች፡በአያትም፡ጊዜ፡ስለታና ሽነቷ ፡ ራርቶላት ፡ ሊተዋት ፡ ወደደ ። ሊተ ዋትም ፡ እንደወደደ ፡ ዐውቃ ፡ እርሱንና ፡ የረከሱ፡አማልክቶቹን፡በድፍረት፡ረገመች። ስለዚህም፡መኰንኑ፡ተቆጥቶ፡ጽኑዕ፡የሆነ፡ ሥቃይን፡አሠቃያት፡ከቀናች፡ሃይማኖቷ፡ ሽንግሎ፡ይመልሳት፡ዘንድ፡በተሳነው፡ጊዜ፡ ጊንጦችን፡እፉኝቶችንና፡እባቦችን፡ሰብስ በው፡በዳውላ፡ውስጥ፡እንዲጨምሩአቸው፡ እርሷንም ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር ፡ በዳውላ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባቲ፡ሐራ።

፭፡አሜሃ፡አስተርአያ፡መልአከ፡እግዚአብሔር፡ ወአወፈያ ፡ ኪዳነ ፡ ዘተውህባ ፡ እምኀበ ፡ እግዚእነ፡ወእምዝ፡መጠወት፡ነፍሳ፡ወተመ ጠወት ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ ወአውጽእዋ ፡ እምውስተ ፡ ሐሰል ፡ ወቀበርዋ ፡ በይእቲ ፡ መካን።

፮፡ወእምዝ፡ሶበ፡ሰምዑ፡አቡሃ፡ወእማ፡መጽኡ፡ ምስለ ፡ ብዙኀ ፡ ሕዝብ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ሥጋሃ ፡ ወነሥእዋ ፡ ወአፍለስዋ ፡እምህየ ፡ ወገነዝዋ ፡ በክብር፡ዐቢይ፡ወአንበርዋ፡ውስተ፡ንፍቅ፡ ሠናይት፡ወሐነፁ፡ላቲ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ሠናይተ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀቡእ ፡ ወኮኑ ፡ እምኔሃ፡ተአምራት፡ወመንክራት።

፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ውስጥ፡ እንዲጨምሩ ፡ አጥማጆችን ፡ አዘ ዛቸው፡እነርሱም፡እንዲሁ፡አደረጉ።

፭፡ያን፡ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ተገለጸ ላትና፡ከጌታችን፡ዘንድ፡የተሰጣትን፡ቃል፡ ኪዳን፡አስረከባት፡ከዚህም፡በኋላ፡ነፍሷን፡ አሳለፈች፡የምስክርነት፡አክሊልንም፡ተቀበ ለች ፡ ከዳውላውም ፡ ውስጥ ፡ አውጥተው በዚያች፡ቦታ፡ቀበሩዋት።

፮፡ከዚህም፡በኋላ፡አባቷና፡እናቷ፡በሰሙ፡ጊዜ፡ ሥጋዋ፡ወዳለበት፡ከብዙ፡ሕዝብ፡ጋር፡መጡ ከዚያም ፡ ሥጋዋን ፡ አፈለሱና ፡ ወሰዱአት ፡ በታላቅ፡ክብርም፡ገንዘው፡በአማረች፡ሣጥን፡ ውስጥ፡አኖሩዋት፡በሥውር፡ቦታም፡ያማረች፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ሠሩላት፡ከእርሷም፡ድንቆች፡ ተአምራቶች፡ተገለጡ።

፯፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቷ፡ይማረን፡በረከቷም፡ከእኛ፡ጋር፡ ይኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

---

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለብፅዕት፡ምህራኤል።ዘፈጸመት፡ስምዓ፡በውሳጤ፡ሐሰል።ወለእጉትሃ፡ሰላም፡አባ፡ሖር፡ድንግል።በፈቃዱ፡ዘተውህበ፡ለሕማም፡ወገድል።ሶበ፡እምሥጋሃ፡ነጸረ፡ዘይትገበር፡ኃይል።

---

፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ፵፻ ወ፴ወ፬ ሐራ፡ማኅበረ፡ቅዱስ፡ቂርቆስ፡ሕፃን።ወበረ ከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚ አብሔር፡አሜን።

፰፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ የሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ማኅበር፡የሆኑ፡አራት፡ሺህ፡ሠላሳ፡አራት፡ ጭፍሮች ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ። በረከታ ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

---

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡በቃለ፡ማኅሌት፡ነከራ።አርብዓ፡ምእት፡ወሠላሳ፡ዘምስለ፡ራብዕ፡ሐራ።ክሣው ዲሆሙ፡ለእሉ፡ኀበ፡አፍአ፡ሀገር፡ተመትራ።በርእሰ፡ቂርቆስ፡ወእሙ፡ህየንተ፡አፍሐም፡ያራ።ከመ፡ እግረ፡ፀሐይ፡ዘይሠርቅ፡ሶበ፡ርእዩ፡ጌራ።

---

፱፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡መስተ ጋድል፡አርከሌድስ፡ወዝንቱ፡ቅዱስ፡እምል ሒቃነ፡ሀገረ፡ሮሜ፡ወስመ፡አቡሁ፡ዮሐንስ፡ ወስመ ፡ እሙ ፡ ሰንደሊቃ ፡ ወእሉ ፡ ፪ሆሙ ፡ ጻድቃን ፡ ወየሐውሩ ፡ በትእዛዙ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ዘእንበለ፡ነውር።

፲፡ወሶበ፡ኮነ፡መዋዕሊሁ፡ለቅዱስ፡አርከሌድስ፡ ፲ወ፪ተ፡ዓመተ፡አዕረፈ፡አቡሁ፡ወሐለየት፡ እሙ፡ከመ፡ታስተዋስቦ፡ብእሲተ፡ውእቱሰ፡

፱፡ በዚችም፡ቀን፡በገድል፡የተጠመደ፡የከበረ፡ አባት፡አርከሌድስ፡አረፈ።ይህም፡ቅዱስ፡ ከሮሜ ፡ ሀገር ፡ ከታላላቆች ፡ ወገን ፡ ነው ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ዮሐንስ ፡ የእናቱም ፡ ስም ፡ ሰንደሊቃ ፡ ነው ፡ ሁለቱም ፡ ዕውነተኞች ፡ የሆኑ ፡ በእግዚአብሔር፡ሕግ፡ያለ፡ነቀፋ፡ የጸኑ፡ናቸው።

፲፡ ቅዱስ ፡ አርከሌድስም ፡ ዕድሜው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት፡ዓመት፡በሆነው፡ጊዜ፡አባቱ፡ሞተ፡ እናቱም፡ሚስት፡ልታጋባው፡አሰበች፡እርሱ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኢፈቀደ፡ዘንተ፡ግብረ።
፲፩፡ ወእምዝ ፡ አምከረቶ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡
ንጉሥ ፡ ወይንሣእ ፡ ሢመተ ፡ አቡሁ ፡ ወፈ
ነወት ፡ ፪ተ ፡ አግብርተ ፡ ምስሌሁ ፡ ወዓዲ ፡
ወሀበቶ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኃ ፡ ዘይሁቦ ፡ ለንጉሥ ፡
አምኃ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ በሐመር ፡ ማዕከለ ፡
ባሕር ፡ ተንሥአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ነፋስ ፡ አውሎ ፡
ወተለዓለ ፡ ማዕበለ ፡ ባሕር ፡ ወተሰብረ ፡
ሐመር፡ ውእቱኒ፡ ተሰቅለ፡ በአሐቲ፡ ለውህ፡
ስባረ፡ ሐመር፡ ወአብጽሐቶ፡ ኀበ፡ የብስ።

፲፪፡ ወሶበ ፡ ዐርገ ፡ እምባሕር ፡ ረከበ ፡ በድነ ፡
ዘገደፎ፡ ማዕበለ ፡ ባሕር ፡ ወነበረ ፡ ወበከየ ፡
ላዕሌሁ ፡ ወተዘከረ ፡ ኀልፈቶ ፡ ለዓለም ፡
ወኮነ፡ ዘይጌሥጾ፡ ለነፍሱ ፡ ወይብላ ፡ ምንት ፡
ብየ ፡ ወብኪ ፡ ንዋየ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡
ወድኅረ ፡ እመውት ፡ እገብእ ፡ ውስተ ፡
መሬት።
፲፫፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ወጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡
ይመርሖ፡ ፍኖተ፡ ርቱዐ፡ ወእምዝ፡ አንሶሰወ፡
ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ፩ደብር፡ ውስተ፡ ሀገረ፡ ሶርያ፡
ዘተሐንፀት ፡ በስሙ ፡ ለቅዱስ ፡ ሮማኖስ ።
ወወሀቦ፡ ለአበ፡ ምኔት፡ ዘተርፈ፡ ምስሌሁ፡ ፪
፻ተ፡ ዲናረ፡ ወርቅ፡ ወሰአሎ፡ ከመ፡ ያልብሶ፡
አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ እስመ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ፡ አጠየቆ፡ ለአበ፡ ምኔት፡ እምቅድመ፡
ምጽአቱ ፡ ለብፁዕ ፡ አርከሌድስ ። ወሶበ ፡
በጽሐ፡ ኀቤሁ፡ ተፈሥሐ፡ አበ፡ ምኔት፡ ወአስ
ተጋብአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አኃው ፡ ቅዱሳን ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጸለዩ ፡ ላዕለ ፡
ቅዱስ፡ አርከሌድስ፡ ወአልበሶ፡ አበ፡ ምኔት፡
አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወአስኬማ ፡ ወተፈ
ሥሑ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎሙ ፡ አኃው ፡ እስመ ፡ ጸጋ ፡
እግዚአብሔር፡ ኮነት፡ ላዕሌሁ፡ ገሀደ።

፲፬፡ ወእምዝ ፡ ተጸምደ ፡ አርከሌድስ ፡ ብፁዕ ፡
ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ጸባብ ፡ እስመ ፡ ተጋደለ ፡
ገድለ፡ ጽኑዐ፡ ወኮነ፡ ኵሎ፡ ዕለተ፡ ይጸውም፡
በበሱባዔ ፡ ወይጼሊ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡
ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ፈውስ ፡
ወፈወሶሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ድውያን ፡ እለ ፡

ግን፡ ይህን፡ አልወደደም።
፲፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሒዶ ፡ የአባ
ቱን፡ ሹመት ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ መከረችው ፡
ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ አገልጋዮችን ፡
ላከች፡ ለንጉሡም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሚሰ
ጠውን ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠችው ። በመር
ከብም ፡ ተጭኖ ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡
ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ በላዩ ፡ ተነሣ ፡ ማዕበሉም ፡
እጅግ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ብሎ፡ መርከቡ፡ ተሰበረ፡
እርሱም ፡ በአንዲት ፡ የመርከብ ፡ ስባሪ ፡
ሠሌዳ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ አደረ
ሰችው።
፲፪፡ ከባሕሩም ፡ ሲወጣ ፡ ማዕበል ፡ የተፋው ፡
በድን፡ አገኘ ፡ ተቀምጦም ፡ በላዩ ፡ አለቀሰ ፡
የዓለምን፡ ኃላፊነትም ፡ አሰበ ፡ ነፍሱንም ፡
የሚገሥጻትና፡ የዚህ ፡ የኃላፊው ፡ ዓለም ፡
ገንዘብ ፡ ምኔ ፡ ነው ፡ ላንቺስ ፡ ምንሽ ፡ ነው ፡
ከሞትኩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ አፈር፡ እመለሳለሁና፡
የሚላት፡ ሆነ።
፲፫፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ወደሆነ ፡
ወደ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለመነ ፡
የቀና ፡ መንገድን ፡ ይመራው ፡ ዘንድ ፡ ከዚ
ህም፡ በኋላ ፡ ተጓዘ ፡ በቅዱስ ፡ ሮማኖስ ፡ ስም ፡
በሶርያ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ተሠራ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡
ገዳም ፡ ደረሰ ። ከገንዘቡም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር፡
የቀረውን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡
ለአበ ፡ ምኔቱ ፡ ሰጠው ፡ የምንኵስና ፡ ልብስ
ንም ፡ እንዲያለብሰው ፡ ለመነው ። የከበረ ፡
አርከሌድስም ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ለአበ ፡
ምኔቱ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አስረድቶት፡ ነበር፡
ወደርሱም፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ አበ፡ ምኔቱ፡ ደስ፡
አለው፡ የከበሩ፡ መነኰሳትን፡ ሁሉንም፡ ሰበ
ሰባቸውና፡ በቅዱስ፡ አርከሌድስ፡ ላይ፡ ጸለዩ።
አበ ፡ ምኔቱም ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ አስኬ
ማንም ፡ አለበሰው ፡ መነኰሳቱ ፡ ሁሉም ፡
በእርሱ፡ ደስ፡ አላቸው፡ የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡
በላዩ፡ ተገልጾለችና።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ አርከሌድስ ፡ በጠ
ባብ፡ መንገድ፡ ተጠመደ፡ ጽኑ፡ ገድልን፡ ተጋ
ድሏልና ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በየሰባት ፡ ቀን ፡ የሚ
ጾም ፡ ሆነ ፡ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ ይጸልያል ፡
እግዚአብሔርም ፡ ሀብተ ፡ ፈውስን ፡ ሰጥቶት፡
በእምነት፡ ወደርሱ፡ የሚመጡትን፡ ብዙዎች፡

www.ethiopianorthodox.org

ይመጽኡ፡ኀቤሁ፡በአሚን።
፲፭፤ ወተካየደ ፡ ምስለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ገጸ ፡ አንስት ፡
ግሙራ ፡ ወሶበ ፡ ጐንደየ ፡ ዜናሁ ፡ እምእሙ ፡
መጠነ ፡ ፲ወ፪ዓመት ፡ ወኢያእመረት ፡ ዘኮነ ፡
ላዕሌሁ ፡ እስመ ፡ መሰላ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሞተ ፡
ወኀዘነት ፡ ጥቀ።
፲፮፤ ወእምዝ ፡ ሐነፀት ፡ ቤተ ፡ ነግድ ፡ ወፈላስያን ፡
ወረሰየት ፡ ከመ ፡ ይኀድሩ፡ በህየ ፡ ነጋድያን ፡
ወፈላስያን፡ወአሐተ፡ዕለተ፡ሰምዓቶሙ፡ለነ
ጋድያን ፡ እንዘ ፡ ይትናገሩ ፡ በእንተ ፡ ዜናሁ፡
ለብፁዕ ፡ አርከሌድስ ፡ ወቅድስናሁ ፡ ወተጋ
ድሎቶ ፡ ወትእምርታቲሁ ፡ ወስነ ፡ ራእዩ ፡-
ወሰሚዓ ፡ አእመረት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ወልዳ ፡
ወተሰአለቶሙ፡ካዕበ፡ለነጋድያን፡ወነገርዋ፡
ኵሎ ፡ ግብሮ ፡ ወጠየቀት ፡ ከመ ፡ ሕያው ፡
ውእቱ።
፲፯፤ ወተንሥአት ፡ ሶቤሃ ፡ ወሖረት ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡
ቅዱስ፡ሮማኖስ፡ወለአከት፡ኀበ፡ወልዳ፡አር
ከሌድስ ፡ ወትቤ ፡ ናሁ ፡ መጻእኩአ ፡ ኀቤከአ ፡
አነ ፡ እምከ ፡ እፈቅድአ ፡ እርአይከአ ፡ ገጸከአ።
ውእቱኒ ፡ ፈነወ ፡ ኀቤሃ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አንሰ ፡
ተካየድኩ ፡ ምስለ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡
ገጸ ፡ አንስት ፡ ግሙራ ፡ ወኢይትከሀለኒ ፡
አሐሱ ፡ ኪዳነ ፡ ዘምስለ ፡ እግዚእየ ። ወፈነ
ወት ፡ ዳግመ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ለእመ ፡
ኢያርአይከኒ ፡ ገጸከ ፡ አንሰ ፡ አሐውር ፡ ውስተ ፡
ገዳም ፡ ወይበልዑኒ ፡ አራዊት።
፲፰፤ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ቅዱስ ፡ አርከሌድስ ፡ ከመ ፡
ይእቲ ፡ ኢተኀድጎ ፡ ውእቱኒ ፡ ኢይትከሀሎ ፡
ከመ ፡ ያማስን ፡ ኪዳነ ፡ ዘተካየደ ፡ ምስለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሰአለ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ከመ ፡
ይንሣእ ፡ ነፍሶ ፡ ወእምዝ ፡ ይቤሎ ፡ ለዓቃቤ ፡
አንቀጽ ፡ ኅድጋ ፡ ለእምየ ፡ ከመ ፡ ትባእ ፡ ኀቤየ።
ወሶበ ፡ ቦአት ፡ እሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ረከበቶ ፡
በዘመጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ወከልሐት ፡ ወበከየት ፡
በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ወሰአለት ፡ ኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ነፍሳ ፡ ወተወክፈ ፡
ሰእለታ ፡ ወነሥአ ፡ ነፍሳ።
፲፱፤ ወእምዝ ፡ ፈቀዱ ፡ ይፍልጡ ፡ ሥጋሃ ፡ እምሥጋ ፡
ወልዳ ፡ ወይቅብርዋ ፡ ባሕቲታ ፡ ወወጽአ ፡

በሽተኞችን ፡ አዳነቸው።
፲፭፤ የሴቶችንም ፡ ፊት ፡ ከቶ ፡ እንዳያይ ፡ ከጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ገባ ፡ ከእናቱ ፡
ዘንድም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡
ወሬው ፡ መሰማቱ ፡ በዘገየ ፡ ጊዜ ፡ በእርሱም ፡
የሆነውን ፡ አላወቀችም ፡ የሞተ ፡ መስሏ
ታልና ፡ እጅግ ፡ አዘነች።
፲፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእንግዶችና፡ የመጻተኞች ፡
መቀበያ ፡ የሚሆን ፡ ቤትን ፡ ሠራች ፡ መንገደ
ኞችም ፡ እንዲአድሩበት ፡ አደረገች ፡ በአን
ዲትም ፡ ዕለት ፡ የብፁዕ ፡ አርከሌድስን ፡ ዜና ፡
ሲናገሩ ፡ መንገደኞችን ፡ ሰማቻቸው ፡
እነርሱም ፡ ቅድስናውን ፡ ተጋድሎውን ፡ ምል
ክቶቹንም ፡ የመልኩንም ፡ ደም ፡ ግባት ፡
ሰምታ ፡ ልጅዋ ፡ እንደሆነ ፡ አወቀች ፡
ዳግመኛም ፡ መነግደኞችን ፡ ጠየቀቻቸው ፡
ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ነገሩዋት ፡ እርሱ ፡ ሕያው ፡
እንደሆነ ፡ ተረዳች።
፲፯፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡
ሮማኖስ ፡ ገዳም ፡ ሔደች ፡ ወደ ፡ ልጅዋ ፡ ወደ ፡
አርከሌድስም ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ላከች ፡ እነሆ ፡
ፊትህን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ወድጄ ፡ እኔ ፡ እናትህ ፡
መጥቻለሁ ። እርሱም ፡ ከቶ ፡ የሴቶችን ፡ ፊት ፡
እንዳላይ ፡ ከክብር ፡ ባለቤት ፡ ከጌታዬ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ገብቻለሁና ፡ ቃል ፡
ኪዳኔን ፡ ማፍረስ ፡ አይቻለኝም ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡
ወደርሷ ፡ ላከ ። ዳግመኛም ፡ ፊትህን ፡ ካላሰ
የኸኝ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ እሔደለሁ ፡ አራዊ
ትም ፡ ይበሉኛል ፡ ብላ ፡ ወደርሱ ፡ ላከች።
፲፰፤ የከበረ ፡ አርከሌድስም ፡ እርሷ ፡ እንደማት
ተወው ፡ እርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የገባ
ውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ማፍረስ ፡ እንደማይ
ቻለው ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱን ፡ እንዲወስ
ዳት ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ለመነ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
የበሩን ፡ ጠባቂ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡
እናቴን ፡ ተዋት ፡ አለው ። በገባችም ፡ ጊዜ ፡
ሙቶ ፡ አገኘችውና ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡
በመጮህ ፡ አለቀሰች ፡ ነፍሷንም ፡ ይወስድ ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነች ፡ ልመና
ዋንም ፡ ተቀብሎ ፡ ነፍሷን ፡ ወሰደ።
፲፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሥጋዋን ፡ ከልጅዋ ፡ ሥጋ ፡
ለይተው ፡ ለብቻዋ ፡ ሊቀብሩ ፡ ወደዱ ፡ ከከበረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቃል ፡ እምነ ፡ በድኑ ፡ ለቅዱስ ፡ አርከሌድስ ፡ ዘይብል ፡ ኢትፍልጡ ፡ ሥጋሃ ፡ ለእምየ ፡ እምነ ፡ ሥጋየ ፡ እስመ ፡ ኢያሠነይኩ ፡ ልባ፡በሕይወታ፡ከመ፡ትርአየኒ።

፳፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ፡ አንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወቀበርዎሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ ውስተ ፡ ፩ መቃብር ፡ ወከሠተ ፡ እግዚእነ ፡ እምሥጋሆሙ ፡ ዐቢየ ፡ ፈውሰ ፡ ለድውያን።

፳፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ አሜን።

አርከሌድስም ፡ በድን ፡ የእናቴን ፡ ሥጋ ፡ ከሥጋዬ፡ አትለዩ፡ በሕይወቷ፡ ሳለች፡ ታየኝ፡ ዘንድ ፡ ልቧን ፡ ደስ ፡ አላሰኘሁምና ፡ የሚል ፡ ቃል፡ወጣ።

፳፡ ይህንንም፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ፡ አደነቁ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑት ፡ ሁለቱንም ፡ በአንድ ፡ መቃብር ፡ ውስጥ ፡ ቀበሩአቸው ፡ ጌታችንም ፡ ለበሽተኞች ፡ ታላቅ ፡ ፈውስን ፡ ከሥጋው፡ገለጠ።

፳፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአርከሌድስ ፡ በዕለተ ፡ ፈጸምከ ፡ በድረ። ሶበ ፡ ወላዲትከ ፡ ሞተት ፡ እንዘ ፡ ትተልወከ ፡ ድኅረ። ለእለ፡ ሐለዩ፡ ሰብእ፡ እንተ፡ ባሕቲታ፡ ቀቢረ። አስማዕከ፡ እምበድንከ፡ ዘይቤ፡ ነገረ። ምስለ፡ ሥጋ፡ እምየ፡ ይኩን፡ ሥጋየ፡ ኅቡረ።

፳፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነት ፡ ሰማዕተ ፡ ቅድስት ፡ እምራይስ።

፳፫፡ ወዛቲ ፡ ብፅዕት ፡ ኮነት ፡ ወለተ ፡ አበው ፡ ክቡራን ፡ እለ ፡ ጽኑዓን ፡ በሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወተሐፅነት፡በፈሪሀ፡እግዚአብሔር።

፳፬፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ትወርድ ፡ ውስተ ፡ ፈለግ ፡ ከመ ፡ ትቅዳሕ ፡ ማየ፡ ርእየቶሙ ፡ ለሙቁሐን ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእሉ ፡ ጳጳሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወሰአለቶ፡ ለጸሐፊ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፍ፡ ስማ ፡ ምስሌሆሙ ። ወጸሐፉ ፡ ወአብጽሐ ፡ ኀበ ፡ ቍልቍልያኖስ ፡ መኰንን ፡ ዓላዊ ፡ ውእቱኒ ፡ አኀዘ ፡ ይሒጣ ፡ በብዙኅ ፡ ነገር ፡ ከመ ፡ ትስግድ ፡ ለጣዖት ፡ ወሶበ፡ አበየቶ፡ አዘዘ፡ ከመ፡ ይምትሩ፡ ክሣዳ፡ ወፈጸመት፡ ስምዓ፡ ምስለ፡ ማኅበራኒሃ።

፳፭፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ አሜን።

፳፪፡ በዚችም፡ ዕለት፡ የከበረች፡ እምራይስ፡ በሰማዕትነት፡ሞተች።

፳፫፡ ይቺም ፡ ብፅዕት ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ለጸኑ፡ ለከበሩ፡ አባቶች፡ ልጅ፡ ናት፡ ፈሪሀ፡ እግዚአብሔርንም፡ እየተማረች፡ አደገች።

፳፬፡ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ውኃ ፡ ልትቀዳ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ስትወርድ ፡ ስለ፡ ክርስቶስ ፡ የታሠሩ ፡ እሥረኞችን ፡ አየች ፡ እነርሱም ፡ ጳጳሳት ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት፡ ናቸው ፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡ ስሟን ፡ ይጽፍ ፡ ዘንድ ፡ መዘጋቢውን ፡ ለመነችው ፡ መዘገባትም ፡ ወደ ፡ ከሀዲውም ፡ መኰንን ፡ ወደ ፡ ቍልቍልያኖስ ፡ አቀረባት ። እርሱም ፡ ለጣዖት፡ ትሰግድ ፡ ዘንድ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሸነገላት ፡ እምቢ ፡ ባለችውም ፡ ጊዜ ፡ ቸብቸቦዋን፡ ይቆርጡ፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ ከተባባሪዎቿም፡ ጋር፡ ምስክርነቷን፡ ፈጸመች።

፳፭፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ የሰማዕታትም ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለእምራይስ ፡ ዘኀደገት ፡ ቀሱታ ። ዘትቀድሕ ፡ ቦቱ ፡ ማየ ፡ ቀዳሜ ፡ ሕይወታ ። ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ስምዕ፡ ትሑር ፡ ምስለ ፡ ሰማዕታት ፡ ሙቅሕታ ። ሐየለት ፡ እምልሒቃን ፡ ወተለዓለት ፡ በሥርዓታ ። እንዘ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ክረምታ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ ቅዱስ፡ መክሲሞስ፡ እኁሁ፡ ለዱማቴዎስ። ወናሁ፡ ጸሐፍነ፡ ገድሎ፡ ምስለ፡ ገድለ፡ እኁሁ፡ አመ፡ ፲ወ፯ ለዝ፡ ወርኅ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

፳፯፡ በዚችም፡ ቀን፡ የዱማቴዎስ፡ ወንድም፡ የከበረ፡ መክሲሞስ፡ አረፈ። እነሆ፡ ገድሉን፡ ከወንድሙ፡ ገድል፡ ጋር፡ በዚህ፡ ወር፡ በዐሥራ፡ ሰባት፡ ጽፈናል። ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለመክሲሞስ፡ እንዘ፡ ንኡስ፡ ሀሎ። ዘወርዘወ፡ በተጋድሎ። ጊዜ፡ አዕረፈ፡ ኪያሁ፡ እለ፡ መጽኡ፡ ለተቀብሎ። መቃርዮስ፡ ሶበ፡ ነጸረ፡ ማኅበረ፡ ቅዱሳን፡ ኵሎ። ብፁዕ፡ አንተ፡ መክሲሞስ፡ ይቤሎ።

* * *

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩አምላክ፡ አመ፡ ፲ወ፰ለጥር፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ ጻድቅ፡ ነቢይ፡ አብድዩ። ወዝንቱ፡ ነቢይ፡ ወልዱ፡ ለሐናንያ፡ ወተነበየ፡ በመዋዕሊሁ፡ ለኢዮሳፍጥ፡ ንጉሥ። ወነገሮ፡ እግዚአብሔር፡ በቃሉ፡ በእንተ፡ ትንሣኤ፡ ወበእንተ፡ ፍዳ።

፪፡ ወዘይከውን፡ ካዕበ፡ እምደቂቀ፡ እስራኤል፡ እለ፡ ተርፉ፡ እምአሕዛብ፡ ወአጽንዖሙ፡ ወገሠጾሙ፡ ብዙኀ።

፫፡ ወውእቱ፡ መስፍን፡ ሣልሳይ፡ እምዘፈነዎሙ፡ አካዝያስ፡ ንጉሥ፡ ይጸውዕዎ፡ ለኤልያስ፡ ለእሉኒ፡ ፪ቱ፡ መሳፍንት፡ እለ፡ እምቅድሜሁ፡ ወረደት፡ እሳት፡ እምሰማይ፡ በቃለ፡ ኤልያስ፡ ወበልዓቶሙ፡ ምስለ፡ እለ፡ ምስሌሆሙ፡ ሐራ።

፬፡ ዝንቱሰ፡ ሶበ፡ መጽአ፡ ኀበ፡ ኤልያስ፡ ሰገደ፡ ወአስተብረከ፡ በቅድሜሁ፡ ወተጋነየ፡ ሎቱ፡ ወይቤሎ፡ ብእሴ፡ እግዚአብሔር፡ ገነይኩ፡ ለከ፡ ትክበር፡ ነፍስየ፡ ወነፍሰ፡ እሉ፡ አግብርቲከ፡ በቅድሜከ፡ ወተሣሃለ፡ ነቢይ፡ ኤልያስ፡ ላዕሌሁ፡ እስመ፡ ኢተዝኅረ፡ ወኢተዐበየ፡ ላዕለ፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ወወረደ፡ ወሖረ፡ ምስሌሁ፡ ኀበ፡ ንጉሥ።

፭፡ ወአእመረ፡ ዝንቱ፡ አብድዩ፡ በነፍሱ፡ ከመ፡ መልእክቱ፡ ለኤልያስ፡ ተዐቢ፡ እመልእክቱ፡ ለንጉሥ፡ ምድራዊ፡ እስመ፡ መልእክቱ፡ ለኤልያስ፡ ታበጽሕ፡ ኀበ፡ መልእክቱ፡ ለንጉሥ፡ ሰማያዊ፡ በእንተዝ፡ ኀደገ፡ መልእክተ፡ ነገሥት፡ ምድራውያን፡ ወተለዎ፡ ለኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወተልእኮ፡ ወወረደ፡ ላዕሌሁ፡ ጸጋ፡ እግዚአብሔር፡ ተወነበየ፡ ወመዋዕለ፡ ትንቢቱኒ፡

* * *

፩፡ አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ጥር፡ ዐሥራ፡ አምስት፡ በዚች፡ ቀን፡ ዕውነተኛ፡ ነቢይ፡ አብድዩ፡ አረፈ። ይህም፡ ነቢይ፡ የሐናንያ፡ ልጅ፡ ነው፡ በንጉሥ፡ ኢዮሳፍጥም፡ ዘመን፡ ትንቢት፡ ተናገረ፡ እግዚአብሔርም፡ ስለ፡ ትንሣኤና፡ ስለ፡ ፍርድ፡ ቀን፡ በቃሉ፡ ነገረው።

፪፡ ሁለተኛም፡ ከእስራኤል፡ ልጆች፡ የሚሆነውን፡ ከአሕዛብም፡ ለቀሩት፡ አጸናቸው፡ አብዝቶ፡ መከራቸውም፡ ገሠጻቸውም።

፫፡ ይህም፡ ንጉሥ፡ አካዝያስ፡ ይጠሩት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኤልያስ፡ ከላካቸው፡ ሦስተኛ፡ መፍስን፡ ነው፡ ከእርሱ፡ አስቀድመው፡ የመጡ፡ እነዚያን፡ ሁለት፡ መስፍኖች፡ በኤልያስ፡ ቃል፡ እሳት፡ ከሰማይ፡ ወረዳ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋር፡ ካሉ፡ ወታደሮች፡ ጋር፡ በላቻቸው።

፬፡ ይህ፡ ግን፡ ወደ፡ ኤልያስ፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ በፊቱ፡ ተንበርክኮ፡ ሰግዶ፡ ተገዛለት፡ እንዲህም፡ አለው፡ የእግዚአብሔር፡ ሰው፡ ተገዛሁልህ፡ የእሊህ፡ የባሮችህ፡ ሰውነትና፡ የኔ፡ ሰውነት፡ በፊትህ፡ ትክበር፡ በእግዚአብሔር፡ ነቢይ፡ ላይ፡ ፈጽሞ፡ አልታበየምና፡ ነቢዩ፡ ኤልያስም፡ ራራለት፡ ወርዶም፡ ከርሱ፡ ጋር፡ ወደ፡ ንጉሡ፡ ሔደ።

፭፡ ይህም፡ አብድዩ፡ ከምድራዊ፡ ንጉሥ፡ አገልግሎት፡ የኤልያስ፡ አገልግሎት፡ እንደምትበልጥ፡ የኤልያስም፡ አገልግሎት፡ ለሰማያዊ፡ ንጉሥ፡ አገልግሎት፡ ታደርሳለችና፡ ይህን፡ በልቡ፡ ዐወቀ፡ ስለዚህ፡ ምድራውያን፡ ነገሥታትን፡ ማገልገል፡ ትቶ፡ ነቢይ፡ ኤልያስን፡ ተከትሎ፡ አገለገለው፡ በላዩም፡ ከእግዚአብሔር፡ ሀብተ፡ ትንቢት፡ አደረበትና፡ ትንቢትን፡ የሚናገር፡ ሆነ፡ የትንቢቱም፡

እንዘ ፡ እሙንቱ ፡ መዋዕያን ፡ ወእሉስ ፡ ዓላ
ውያን ፡ ኅፉራን ።

፲፡ ወበጺሖ ፡ ኀበ ፡ ርሥእ ፡ ሠናይ ፡ ወአሥመሮ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወናሁ፡
ጸሐፍነ ፡ ንስቲተ ፡ እምገድሉ ፡ አመ ፡ ፳ወ፩
ለዝ ፡ ወርኀ ፡ ወውእቱ ፡ ዕረፍቱ ፡ በግብጻ
ውያን ።

፲፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስ
ሌነ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

አጠፋ ፡ ከተሰበሰቡትም ፡ ጋር ፡ በሰላም ፡
ተመለሰ ፡ እነርሱ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡
እነዚያም ፡ ከሀድያን ፡ በኀፍረት ፡ ሁነው፡
ተመለሱ ።

፲፡ ወደ ፡ መልካም ፡ እርጅና ፡ ደርሶ ፡ እግዚአብሔ
ርንም ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡
አረፈ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ አንድ፡
ቀን ፡ ከገድሉ ፡ ጥቂት ፡ ጽፈናል ፡ ይኸውም ፡
በግብጻውያን ፡ ዕረፍቱ ፡ ነው ።

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጎርጎርዮስ ፡ ስንዕወ ፡ ምግባር ፡ በኵሉ ። ምስለ ፡ ጳጳሳት ፡ ኄራን ፡ በቀኖስጥንጥንያ ፡
መድበሉ ። ለዝንቱ ፡ መዋዒ ፡ መታሬ ፡ ዕልዋን ፡ ሰይፈ ፡ ቃሉ ። ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡ በዘይረትዕ ፡ ወይደሉ።
በዛቲ ፡ ዕለት፡ ሶርያ ፡ ያብዕሉ ።

፲፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ ለጴ
ጥሮስ ፡ ወሶፍያ ፡ ወለአድምራ ፡ ወለይ
ስሐቅ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡
ቂርቆስ ፡ ሕፃን ፡ ወእሙ ፡ ኢየሉጣ፡ ብዕ
ዕት፡ ወዓዲ ፡ ፼ወ፲፻ወ፬ቱ ፡ ማኅበረ ፡ ቅዱስ፡
ቂርቆስ ፡ ሕፃን ።

፲፬፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ስደት ፡
ላዕለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቲሁ ፡ ለክር
ስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በመዋዕለ ፡ እለእስ
ክንድሮስ ፡ መኰንን ።

፲፭፡ ወሀለወት ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡
ኢየሉጣ ፡ ኄርት ፡ ይእቲ ፡ እምንእሳ ፡ ወሰ
ሚዓ ፡ ከመ ፡ ኮነ ፡ ስደት ፡ ነሥአቶ ፡ ለሕፃና፡
ወጐየት ፡ እምፍርሀተ ፡ መኰንን ፡ እምሀ
ገረ፡ ሮም ፡ ወበጽሐት ፡ ሀገረ ፡ ጠርሴስ ፡
ዘኪልቅያ ፡ ወነበረት ፡ ውስተ ፡ በሐውርት።

፲፮፡ ወበጽሐ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ እለእስክን
ድሮስ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ ዘጐየት ፡
እምኔሁ ፡ ወኃሠሥዎሙ ፡ ሐራሁ ፡ ለክርስ
ቲያን፡ ወረከብዋ ፡ ለቅድስት ፡ ኢየሉጣ ፡

፲፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የጴጥሮስና ፡ የሶፍያ ፡ የአ
ድምራና ፡ የይስሐቅም ፡ የዕረፍታቸው ፡
መታሰቢያ ፡ ነው ፡ በረከታቸውም፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡
ይሁን ፡ አሜን።

፲፫፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡
እናቱ ፡ ብፅዕት ፡ ኢየሉጣ ፡ ዳግመኛም ፡
ለከበረ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ማኅበር ፡ የሆኑ ፡
ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ በሰ
ማዕትነት ፡ ሞቱ ።

፲፬፡ በዚያንም ፡ ወራት ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡
የሆነ፡ ክርስቶስን ፡ በሚያምኑ ፡ የክርስ
ቲያን፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ መከራና ፡
ስደት ፡ ሆነ ።

፲፭፡ ስሟ ፡ ኢየሉጣ ፡ የሚባል ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡
ነበረች ፡ እርሷም ፡ ከታናሽነቷ ፡ ጀምራ ፡
ደግ፡ ናት ፡ ስደትም ፡ እንደሆነ ፡ በሰማች ፡
ጊዜ ፡ መኰንኑን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡
ሕፃኗን ፡ ይዛ ፡ ከሮም ፡ ከተማ ፡ ተሰዳ ፡
የኪልቅያ ፡ አውራጃ ፡ ከሆነ ፡ ከጠርሴስ ፡
ደርሳ ፡ ከዚያም ፡ በሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ እየተዘ
ዋወረች፡ ተቀመጠች ።

፲፮፡ ወደዚያች ፡ አገርም ፡ ያ ፡ ከእርሱ ፡ የሸ
ሸችው ፡ መኰንን ፡ እለእስክንድሮስ ፡ መጣ ፡
ጭፍሮቹም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ፈለጓቸው ።
ይቺንም ፡ ቅድስት ፡ ኢየሉጣን ፡ አግኝ

www.ethiopianorthodox.org

ወአኀዘዋ ፡ ወአብጽሕዋ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡
ወነገርዎ ፡ ከመ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ይእቲ ።

፲፯፡ ወይቤላ ፡ መኰንን ፡ አ ፡ ብእሲቶ ፡ ንግሪ ፡
እምአይ ፡ ሕዝብ ፡ አንቲ ፡ ወምንት ፡ ዘመ
ድኪ ፡ ወአይቴ ፡ ሀገርኪ ።
፲፰፡ አውሥአቶ ፡ ቅድስት ፡ ኢየሉጣ ፡ ወትቤሎ፡
ሊተ ፡ ሕዝብየ ፡ ኢሳውሮስ ፡ ርእሶሙ ፡
ለሀገረ ፡ ኢቆንዮን ፡ አንጌቤናይት ፡ አነ ፡
ወበእንቲአከ ፡ ጐየይኩ ፡ ወናሁ ፡ ይእዜሰ ፡
ውስተ ፡ እዴከ ፡ ሀሎኩ ።

፲፱፡ ወይቤላ ፡ መኰንን ፡ ተአምሪኑ ፡ ከመ ፡
ውስተ ፡ እዴየ ፡ ተረከብኪ ፡ ወይእዜኒ ፡
ኀረዪ ፡ ዘይኄይሰኪ ፡ ወንግሪ ፡ ስመኪ ፡
ወአሆ ፡ በልኒ ፡ ወሡዒ ፡ ለአማልክት ፡
ወትቤሎ ፡ ቅድስት ፡ ኢየሉጣ ፡ አንሰ ፡
ኢይሠውዕ ፡ ለአማልክት ፡ ርኩሳን ፡ ወይ
ቤላ ፡ መኰንን ፡ ሀቢ ፡ ወንግሪ ፡ ስመኪ ፡
ወይእቲ ፡ ትቤሎ ፡ ስምየ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይ
ቤላ ፡ መኰንን ፡ አልቦ ፡ ዘይበቍዓኪ ፡ ዝሰ፡
እበድ ፡ ሀቢ ፡ ወንግሪ ፡ ስመኪ ፡ ከመ ፡
ኢትሙቲ ፡ ወአውሥአቶ ፡ ቅድስት ፡ ኢየ
ሉጣ ፡ ወትቤሎ ፡ እብለከ ፡ ከመ ፡ ክርስ
ተያን ፡ ስምየ ፡ ወእመሰ ፡ መዋቴ፡ ስምየ ፡
ትፈቅድ ፡ ዘእምኀበ ፡ ሰብእ፡ ኢየሉጣ ፡
ስምየ ።

፳፡ ወይቤላ ፡ መኰንን ፡ ተንሥኢ ፡ ወሡዒ ፡ ለአ
ማልክት ፡ ዘእንበለ ፡ ያምጽኡ ፡ ላዕሌኪ ፡
ዓቢያተ ፡ ኵነኔያተ ።
፳፩፡ ወትቤሎ ፡ ቅድስት ፡ ኢየሉጣ ፡ እመሰ ፡
ትፈቅድ ፡ ጽድቀ ፡ ትግበር ፡ ፈኑ ፡ውስተ ፡
ሀገር ፡ ይኅሥሡ ፡ ሕፃነ ፡ ዘ፫ቱ ፡ ዓም ፡ ወያ
ምጽእዎ ፡ ኀቤከ ፡ ወይንግረነ ፡ ውእቱ ፡ ለዘ ን
ትቀነይ ፡ ወናመልክ ።

፳፪፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ፈነወ ፡ መኰንን ፡ ሰገራተ ፡
ይኅሥሡ ፡ ወልደ ፡ ፫ቱ ፡ ዓም ፡ ወኢረከቡ፡
እስመ ፡ ደቂቆሙ ፡ ኀብኡ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡
ወወጽኡ ፡ እምህየ ፡ ሰገራት ፡ እምቅጽረ ፡
ሀገር ፡ አፍአ ፡ ውስተ ፡ ሐቅለ ፡ ኤጳውሎስ ፡

ተው፡ ያገዟትና ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ አደረ
ሷት ፡ የክርስቲያን ፡ ወገንም ፡ እንደሆነች ፡
ነገሩት ።
፲፯፡ መኰንኑም ፡ ሴትዮ ፡ ተናገሪ ፡ ከወዴት ፡
ሕዝብ ፡ ወገን ፡ ነሽ ፡ ነገድሽ ፡ ምንድን ፡
ነው ፡ ሀገርሽስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ አላት ።
፲፰፡ የከበረች ፡ ኢየሉጣም ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ መለሰ
ችለት ፡ የአንጌቤን ፡ ሰው ፡ ለሆንኩ ፡ ለእኔ ፡
ወገኖቼ ፡ ለኢቆንዮን ፡ አገር ፡ አለቆች ፡
የሆኑ፡ ኤሳውሮሳውያን ፡ ናቸው ፡ እኔም ፡
በአንተ ፡ ምክንያት ፡ ሸሽቼ ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡
ዛሬ ፡ ግን ፡ በእጅህ ፡ ውስጥ ፡ ነኝ ፡ አለችው ።
፲፱፡ መኰንኑም ፡ በእጄ ፡ ውስጥ ፡ እንደተገኘሽ ፡
ታውቂያለሽን ፡ አላት ፡ አሁንም ፡ የሚሻ
ልሽን ፡ ምረጪ ፡ ስምሽንም ፡ ተናገሪ ፡ እኔ
ንም ፡ እሺ ፡ በይኝና ፡ ለአማልክት ፡ ሠዊ ፡
የከበረች ፡ ኢየሉጣም ፡ ለረከሱ ፡ አማልክት ፡
እኔ ፡ አልሠዋም ፡ አለችው ፡ መኰንኑም ፡
ስምሽን ፡ ስጪ ፡ ተናገሪ ፡ አላት ፡ እርሷም ፡
የኔ ፡ ስም ፡ ክርስቲያን ፡ መባል ፡ ነው ፡
አለችው ። መኰንኑም ፡ ይህስ ፡ ስንፍና ፡
ነው፡ የሚጠቅምሽ ፡ አይደለም ፡ እንዳ
ትሞቺ ፡ ስምሽን ፡ ስጪ ፡ ተናገሪ ፡ አላት ።
የከበረች ፡ ኢየሉጣም ፡ የኔ ፡ ስም ፡ ክርስ
ቲያን ፡ መባል ፡ እንደሆነ ፡ ነገርኩህ ፡ ሞት ፡
የሚሽረው ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የምጠራ
በትን ፡ ከፈለግህ ፡ ስሜ ፡ ኢየሉጣ ፡ ነው፡
ብላ ፡ መለሰችለት ።
፳፡ መኰንኑም ፡ ጽኑ ፡ የሆኑ ፡ ሥቃዮችን ፡ በላ
ይሽ ፡ ሳያመጡ ፡ ተነሥተሽ ፡ መሥዋዕትን ፡
ለአማልክት ፡ አቅርቢ ፡ አላት ።
፳፩፡ የከበረች ፡ ኢየሉጣም ፡ ዕውነት ፡ ነገርን ፡
ለመሥራት ፡ የምትሻ ፡ ከሆነ ፡ ዕድሜው ፡
ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆነ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡
ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ መንደር ፡
ላክ፡ ወዳንተም ፡ ያምጡትና ፡ የምንገዛላ
ትንና ፡ የምናመልከውን ፡ እርሱ ፡ ይንገረን ፡
አለችው ።
፳፪፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡
ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ መኰንኑ ፡ ወታደሮችን ፡
ላከ ፡ የሀገር ፡ ሰዎችም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሠው
ረዋልና ፡ አላገኙም ፡ ከዚያም ፡ ከከተማው ፡
ቅጽር ፡ ውጭ ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወዳ

www.ethiopianorthodox.org

ወረከብዎ ፡ ለወልደ ፡ ኢየሉጣ ፡ ቅድስት ፡ ወተሰአሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ዘእስፍንቱ ፡ ዓም ፡ ዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ዘሠለስቱ ፡ ዓም ፡ ወዝንቱ ፡ ወልዳ፡ ለመበለት ፡ ክርስቲያናዊት ።

፳፫፤ ወነሥእዎ ፡ ለውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ወወሰድዎ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ልሑይ ፡ ውእቱ ፡ ወሠናይ ፡ በራእዩ ፡ ወይቤሎ ፡ በሀ ፡ ፍሡሕ ፡ ሕፃን ፡ አውሥአ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ፡ ሊተሰ ፡ ትብለኒ ፡ ፍሡሕ ፡ እወ ፡ ሠናየ ፡ ትቤ ፡ ወለከሰ ፡ አልብከ ፡ ፍሥሓ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልቦሙ ፡ ፍሥሓ ፡ ለረሲዓን ፡ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ለሕፃን ፡ ዘእንበለ ፡ እሴአለከ ፡ ዘመጠነዝ ፡ ታወሥአኒኑ ፡ ወይቤሎ ፡ ሕፃን፡ ለመኰንን፡ ዓዲ ፡ እምዝ ፡ ዘይበዝኅ ፡ አወሥአከ ።

፳፬፤ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ለሕፃን ፡ መኑ ፡ ስምከ ፡ አውሥአ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ ፡ ነቅዕ ፡ ዘእምዐዘቅት ፡ ንጹሕ ፡ ወእማይ፡ ዘኢይማስን ፡ ክርስቲያን ፡ ስምየ ፡ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ካዕበ፡ ንግረኒ ፡ ስመከ ፡ ከመ ፡ ኢትሙት ። ወይቤሎ ፡ ሕፃን ፡ ቅዱስ ፡ ነገርኩከ ፡ ከመ ፡ ስምየ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእመሰ ፡ ስመ ፡ ሞክሲ፡ ትፈቅድ ፡ ዘሰመየተኒ ፡ እምየ ፡ ቂርቆስ ፡ ውእቱ ።

፳፭፤ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ለሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ አሆ፡ በለኒ ፡ ወሡዕ ፡ ለአማልክት ፡ ወእምከመ ፡ ልሕቀ ፡ ዘበሥጋከ ፡ እሠይመከ ፡ ወአከብረከ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ብዙኅ ። ወይቤሎ ፡ ሕፃን ፡ ረኃቅ ፡ እምኔየ ፡ ላእኩ ፡ ለሰይጣን ፡ ወፀሩ ፡ ለጽድቅ ።

፳፮፤ ወሰሚዖ ፡ መኰንን ፡ ተምዐ ፡ ወአዘዘ ፡ የዐጽርዎ ፡ በአምዕስቲሁ ፡ ወይጥብሕዎ ፡ እስከ ፡ ውኅዘ ፡ ደሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ።

፳፯፤ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ቅድስት ፡ ኢየሉጣ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ወልዳ ፡ አእኰተቶ ፡ ለእግዚአብሔር።

፳፰፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ያምጽኡ ፡ ጼወ ፡ ወሰናፔ ፡ ወይክሥትዎሙ ፡ አእናፊሆሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ ወይደዩ ፡ ውእተ ፡

ለው፡ በረሀ ፡ በኩል ፡ ወጡ ፡ የቅድስት ፡ ኢየሉጣንም ፡ ልጅ ፡ አገኙት ፡ ይህ ፡ ሕፃን ፡ የስንት፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለርሱ ፡ ጠየቁ፡ ሰዎችም ፡ ይህ ፡ ሕፃን ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ የክርስቲያናዊት፡ መበለት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አሏቸው።

፳፫፤ ያንንም ፡ ሕፃን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ ወሰዱት ፡ መኰንኑም ፡ መልኩ ፡ የሚያምርና፡ ደም ፡ ግባት ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ደስተኛ ፡ ሕፃን ፡ ሰላምታ ፡ ይገባሃል ፡ አለው ። ሕፃኑም ፡ እኔን ፡ ደስተኛ ፡ ማለትህ ፡ መልካም ፡ ተናገርክ ፡ ላንተ ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ የለህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዝንጉዎች ፡ ደስታ ፡ የላቸውም፡ ብሏልና ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ መኰንኑም ፡ ሕፃኑን ፡ ሳልጠይቅህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ትመልስልኛለህን ፡ አለው ። ሕፃኑም፡ ገና ፡ ከዚህ ፡ የሚበዛ ፡ ነገርን ፡ እመልስልሃለሁ ፡ አለው ።

፳፬፤ መኰንኑም ፡ ሕፃኑን ፡ ስምህ ፡ማን፡ነው ፡ አለው ፡ ከንጹሕ ፡ ዐዘቅትና ፡ ከማይለወጥ ፡ ከማይጠፋ ፡ ውኃ ፡ የተገኘ ፡ ሕፃን ፡ ስሜ ፡ ክርስቲያን ፡ መባል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። መኰንኑም ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳትሞት ፡ ስምህን፡ ንገረኝ ፡ አለው ፡ የከበረ ፡ ሕፃንም ፡ ስሜ ፡ ክርስቲያን ፡ መባል ፡ እንደሆነ ፡ ነገርኩህ ፡ ሞክሼ ፡ ስም ፡ የምትሻ ፡ ከሆነ ፡ እናቴ ፡ የሰየመችኝ ፡ ቂርቆስ ፡ ነው።

፳፭፤ መኰንኑም ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስን ፡ እሺ ፡ በለኝና ፡ ለአማልክት ፡ ሠዋ ፡ በሥጋህም ፡ ስታድግ ፡ እሾምሃለሁ ፡ በብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብርም ፡ አከብርሃለሁ ፡ አለው ። ሕፃኑም ፡ የሰይጣን ፡ መልእክተኛ ፡ ለዕውነትም ፡ ጠላቷ ፡ የሆንክ ፡ ከእኔ ፡ ራቅ ፡ አለው ።

፳፮፤ መኰንኑም ፡ ሰምቶ ፡ ተቆጣ ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ እስከሚፈስ ፡ ቆዳውን ፡ እንዲጨምቁትና ፡ እንዲገፉት ፡ አዘዘ ።

፳፯፤ የከበረች ፡ ኢየሉጣም ፡ የልጅዋን ፡ ትዕግሥት ፡ በአየች ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነችው ።

፳፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኰንኑ ፡ ጨውና ፡ ሰናፍጭ ፡ አምጡ ፡ አለ ፡ የሁለቱንም ፡ አፍንጮቻቸውን ፡ ከፍተው ፡ ያንን ፡ ጨውና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዬወ ፡ ወሰናፔ ፡ ውስተ ፡ አእናፊሆሙ ፡
አሚሃ ፡ ጸርሐ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤ ፡ ጥዑም ፡
ለጕርዔየ ፡ ነቢብከ ፡ እመዓር ፡ ወሦከር ፡
ጥዕመኒ ፡ ለአፉየ ።
፳፱፤ ወካዕበ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ወይቤ ፡ አም
ጽኡ ፡ ፲ወ፬ተ ፡ ኅፃውንተ ፡ በሊሐተ ፡
ወነዋኃተ፡ ወርሱናነ ፡ ከመ ፡ አፍሐም ፡
ወደዩ ፡ ፯ተ ፡ ውስተ ፡ አባለ ፡ እሙ ፡ ወ፪ተ ፡
ደዩ ፡ ውስተ ፡ ዕዘኒሁ ፡ ለሕፃን ፡ ወ፪ተ ፡
ውስተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወ፪ተ ፡ በአፉሁ ፡
ወአንፉ ፡ ወ፩ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ከመ ፡ እንዘ ፡
ይትወደይ ፡ ይኅርራ ፡ ዕዘኒሁ ፡ ወይዑራ ፡
አዕይንቲሁ ፡ ወየዓይ ፡ ልሳኑ ፡ ወይባእ ፡
ሕማም ፡ ጽኑዕ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ወይሙት ፡
ውእቱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወከማሁ ፡
ለእሙኒ ፡ ግበሩ ፡ ወተወድዩ ፡ ኅፃውንት ፡
ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ።

፴፤ ወበትእዛዙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
ጠፍአ ፡ ወቈረ ፡ ርስነቶሙ ፡ ለኅፃውንት ፡
ወኮነ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ ወኮኑ ፡ ጥዑያነ ።
ወይቤ ፡ መኰንን ፡ ሰድዎሙ ፡ ውስተ ፡
ቤተ፡ ሞቅሕ ፡ ወእሥርዎሙ ፡ ወዕጽውዎሙ፡
በህየ ።
፴፩፤ ወእምዝ ፡ ይቤ ፡ መኰንን ፡ አምጽኡ ፡ ሊተ፡
ነሀቤ ፡ ኀፂን ፡ ከመ፡ አአዝዝ ፡ ይግበር፡
መብዓለ ፡ ኵነኔ ፡ ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ነሀቤ ፡
ኀፂን፡ ቦአ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡
መኰንን ፡ ወፈጸሞ ፡ አፉሁ ፡ ወስእነ ፡
ነቢበ፡ እስመ ፡ አእመረ ፡ ሰይጣን ፡ ከመ ፡
ይጽሕቅ ፡ ሕፃን ፡ ነሢአ ፡ አክሊል ፡ በእን
ተዝ ፡ ረሰዮ ፡ በሐመ፡ ለመኰንን ።
፴፪፤ ወእምዝ ፡ ጸውዖ ፡ ሕፃን ፡ ለነሐቢ ፡
ወይቤሎ ፡ በዘይኴንኑኒ ፡ ሊተ ፡ ወለእምየ ፡
መብዓለ ፡ ኵነኔ ፡ ትክልኑ ፡ ገቢረ ፡ እስመ ፡
ዝኩሰ ፡ መኰንን ፡ አልቦ ፡ ዘየአምር ፡ ምን
ተኒ ። ወይቤሎ ፡ ነሀቢ ፡ በል ፡ ንግረኒ ፡
ዘትፈቅድ ፡ ወአነ ፡ እክል ፡ ገቢረ ፡ በከመ ፡
አዘዝከኒ ።

፴፫፤ ወአኀዘ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ የአዝዝ ፡ ወይቤ ፡
ግብር ፡ ሊተ ፡ ወለእምየ ፡ መላጽያተ ፡
ክልኤተ ፡ ዘስፍሐሙ ፡ ፩ በእመት ፡ ወዓዲ ፡

ሰናፍጭ ፡ እንዲጨምሩባቸው ፡ አዘዘ ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ ሕፃኑ ፡ ትእዛዝህ ፡ ለጕረሮዬ ፡ ጣፋጭ፡
ሆነ ፡ ከማርና ፡ ከስኳርም ፡ ለአፌ ፡ ጣመኝ ፡
ብሎ ፡ ጮኸ ።
፳፱፤ ሁለተኛም ፡ መኰንኑ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
አዘዘ ፡ የረዘሙና ፡ የተሳሉ ፡ በእሳትም ፡
እንደ፡ ፍም ፡ የጋሉ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡
የብረት፡ ችንካሮች ፡ አምጡ ፡ ሰባቱን ፡ በእ
ናቱ ፡ አካላት ፡ ውስጥ ፡ ጨምሩ ፡ በሕፃኑም፡
ሁለት ፡ በጆሮዎቹ ፡ ሁለት ፡ በዐይኖቹ ፡
ሁለት ፡ በአፉና ፡ በአፍንጫው ፡ አንድ ፡
በልቡ ፡ ጨምሩ ፡ እንዲህ ፡ ሲጨመርበት ፡
ጆሮዎቹ ፡ እንዲአሩ ፡ ዐይኖቹም ፡ ይጠፉ ፡
ዘንድ ፡ አንደበቱም ፡ ይቃጠል ፡ ዘንድ ፡
ወደ፡ ልቡም ፡ ጽኑ ፡ ሕማም ፡ ገብቶ ፡ እርሱ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ እንዲለይ ፡ ለእና
ቱም ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ፡ ችንካሮችም ፡
በቅዱሳኑ ፡ በሥጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ተጨመሩ ።
፴፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ በሆነ ፡ በጌታችን ፡ ትእ
ዛዝ፡ የብረቶቹ ፡ ግለት ፡ ጠፍቶ ፡ እንደ ፡
በረዶ ፡ ቀዘቀዘ ፡ ጤነኞችም ፡ ሆኑ ፡ መኰን
ኑም ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ወስዳችሁ ፡ በዚያ ፡
አሥራችሁ ፡ ዝጉባቸው ፡ አለ።

፴፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኰንኑ ፡ የሥቃይ ፡
መሣሪያን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ እንዳዝዘው ፡
ብረትን ፡ የሚያቀልጥ ፡ ሰው ፡ አምጡልኝ ፡
አለ። በአመጡለትም ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን፡ ወደ ፡
መኰንኑ ፡ ልብ ፡ ገብቶ ፡ አንደበቱን ፡ ዘጋ
ውና ፡ መናገር ፡ ተሳነው ፡ ሕፃኑ፡ ፈጥኖ ፡
አክሊልን ፡ ለመቀበል ፡ እንደሚተጋ ፡ ሰይ
ጣን ፡ ስለ ፡ አወቀ ፡ ስለዚህ ፡ ዘጋው ።
፴፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሕፃኑ ፡ ሠራተኛውን ፡
ጠርቶ ፡ እኔንና ፡ እናቴን ፡ የሚያሠቃዩ
በትን፡ የሥቃይ ፡ መሣሪያ ፡ መሥራት ፡
ትችላለህን፡ ይህ ፡ መኰንን ፡ ግን ፡ ምንም ፡
የሚያውቀው፡ ነገር ፡ የለም ፡ አለው ፡ ሠራ
ተኛውም ፡ እንደምትሻው ፡ በል ፡ ንገረኝ ፡
እንደምታዝዠኝ ፡ እኔ ፡ መሥራት ፡ እችላ
ለሁ ፡ አለው ።
፴፫፤ ሕፃን ፡ ቂርቆስም ፡ ሊአዝዝ ፡ ጀመረ ፡ እን
ዲህም ፡ ኰለ ፡ ሁለት ፡ መላጫዎች ፡ ስፋታ
ቸው ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ የሆነ ፡ ለእኔና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግበር ፡ ሊተ ፡ መቅዓነ ፡ ወመስብረ ፡ ርእስ ፡
ወመጽፍረ ፡ ክሣድ ፡ ወመኖሥሠ ፡ ወመ
ውጽኤ ፡ ዐይን ፡ ወመስረፌ ፡ ወመጥውየ ፡
አንፍ ፡ ወሞርቃሔ ፡ ዕዝን ፡ ወፈታሔ ፡
መለያልይ ፡ ወመውቅየ ፡ ልሳመ ፡ ልሳን።
ጉጠተ ፡ ወመኖሥሠ ፡ ወመሰሐስሐ ፡ ወመ
ፍሕቀ ፡ ገበዋት ፡ ወመጥውየ ፡ ወመቅዓነ ፡
ወመስብረ ፡ አብራክ ፡ ወአቍያጽ ፡ ወመ
ውቅየ ፡ አምትንት ፡ ፈታሔ ፡ ወመላሔ ፡
አሥራው ፡ ወግበር ፡ በዛቲ ፡ መቅዓን ፡
መጽፍረ ፡ አምትንት።

፴፬፤ ወግበር ፡ ካዕበ ፡ ረፊአ ፡ መንበረ ፡ ዘብርት ፡
ዘበአርአያ ፡ ላሕም ፡ ወስቀ፡ር ፡ ሠለስተ ፡
ሥቍረታተ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መንበር ፡
ወግበር ፡ ሠለስተ ፡ ቅትራተ ፡ በመጠነ ፡
ቆምየ ፡ ወአርእስተ ፡ ቅትራቲሁ ፡ ግበር ፡
ዘብርት ፡ ወጸሐፍ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘይብል ፡
ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘኢይትሌለይ ፡ ወኢይት
ፈለጥ ፡ እምእለ ፡ ይጼውዕዎ ።
፴፭፤ ወግበር ፡ ዓዲ ፡ ፪ መጥውየ ፡ ሞጠቅ ፡ ወ፪ተ፡
ሞሰርተ ፡ ወ፪ተ ፡ ጤገናተ ፡ ወ፳ደ፡ ጽሕርተ ፡
ዐቢየ ፡ ወውስተ ፡ ውእቱ ፡ ጽሕርት ፡ መን
ኰራኵረ ፡ ወመድኀኔ ፡ ክሣድ ፡ ወመንቅዔ ።
ወግበር ፡ እደ ፡ ዘኀጺን ፡ ዘየሐትት ፡ ንዋየ ፡
ውስጥ ፡ ዘከርሥ ፡ ኅቡአ ፡ ዝውእቱ ፡ በዘእት
ኳነን ፡ ጽዑረ ፡ አነ።

፴፮፤ ወሰሚዖ ፡ ነሀቤ ፡ ኀጺን ፡ አንከረ ፡ ጥቀ ፡ ወአ
ስተጋብአ ፡ ኀቤሁ ፡ ነሀብተ ፡ ሀገር ፡ ምእተ፡
ወአኀዘ ፡ ገቢረ ፡ ወፈጸመ ፡ በ፴ ጽባሕ ።

፴፯፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ እለእስክንድ
ሮስ ፡ ያምጽእዎሙ ፡ ለቂርቆስ ፡ ወለእሙ ፡
ውስተ ፡ ዐውድ ፡ አሚሃ ፡ እስመ ፡ ተፈትሐ ፡
ልሳኑ ፡ ወይቤ ፡ ላጽይዎሙ ፡ ርእሶሙ ፡
ለሕፃን ፡ ወእሙ ፡ ምስለ ፡ ማዕሶሙ ፡ ወደዩ፡
ላዕሌሆሙ ፡ አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ከመ ፡ ይኅ
ርሩ ፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ይትክሉ ፡ ፬ተ ፡ ቅት

ለእናቴ ፡ ሥራ ። ዳግመኛም ፡ የሚያስ
ጨንቅ፡ ራስን ፡ የሚመታና ፡ የሚሰብር ፡
አንገትንም ፡ የሚያሥር ፡ የሚዝቅም ፡ ሹካ፡
ዐይንንም ፡ የሚያወልቅ ፡ አካልንም ፡ የሚ
በሳሳ ፡ አፍንጫንም ፡ የሚያጣምምና ፡ የሚ
ሰብር ፡ ጆሮንም ፡ የሚልጥ ፡ ሕዋሳትን ፡
የሚፈታና ፡ የሚለያይ ፡ እንደ ፡ ልጓም ፡
ሁኖ ፡ ምላስን ፡ የሚቆርጥ ፡ በሰውነትም ፡
ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ቆላፋ፡
ጉጠትን ፡ ጕኖችንም ፡ የሚፍቅና ፡ የሚቆ
ለምም ፡ አስጨናቂ ፡ የሆነ ፡ ጉልበቶችንና ፡
ጭኖችን ፡ የሚሰብር ፡ ጅማቶችንም ፡ የሚ
ቆራርጥ ፡ ሥሮችንም ፡ የሚመዝ ፡ በዚችም፡
አስጨናቂ ፡ መሣሪያ ፡ ጅማቶችን፡ የሚ
ታታ ፡ አድርግ ።

፴፬፤ ዳግመኛም ፡ በላም ፡ አምሳል ፡ ሰፊ ፡
መቀመጫ ፡ ከናስ ፡ ሥራ ፡ ሦስት ፡ ቀዳዳዎ
ችንም ፡ በዚያ ፡ መቀመጫ ፡ ውስጥ ፡ ቅደድ።
በቁመቴም ፡ ልክ ፡ ሦስት፡ ችንካሮችን፡ ሥራ፡
የችንካሮቹንም ፡ ራስ ፡ ከናስ፡ አድርገህ ፡ በው
ስጡ ፡ ከሚጠሩት ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይ
ለይ ፡ ልዩ፡ ሦስት ፡ ብለህ ፡ ጻፍ።

፴፭፤ ዳግመኛም ፡ ጠምዝዞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚያ
ወጣ ፡ ሁለት ፡ መሣሪያ ፡ ሁለት ፡ መጋዞችን ፡
ሁለት ፡ የብረት ፡ ምጣዶችን ፡ ሥራ ፡ አሁ
ንም ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ጋን ፡ ሠርተህ ፡ በው
ስጡ ፡ አንገትን ፡ የሚጠመዝዝና ፡ የሚሠ
ነጥቅ ፡ ተሽከርካሪ ፡ መሣሪያ ፡ አድርግ ።
በውስጥ ፡ የተሸሸገ ፡ የሆድ ፡ ዕቃን፡ የሚመ
ረምር ፡ እጅን ፡ ከብረት ፡ ሥራ፡ እኔ ፡ የጸዕር፡
ሥቃይን ፡ የምሠቃይበት፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።
፴፮፤ ብረት ፡ ሠሪውም ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ፡
የሚረዱትንም ፡ ከሀገር ፡ ውስጥ ፡ መቶ ፡
ሠራተኞችን ፡ ሰብስቦ ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ፡
በአርባ ፡ ቀንም ፡ ጨረሰ ።
፴፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኰንኑ ፡ እለእስክን
ድሮስ ፡ ቂርቆስንና ፡ እናቱን ፡ ወደ ፡ አደባ
ባይ ፡ ያመጡአቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ አንደበቱ ፡ ተፈትቶ ፡ ነበርና ፡
እንዲህም ፡ አለ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡
ከቆዳቸው ፡ ጋር ፡ ራሳቸውን ፡ ላጪአቸውና፡
በላያቸው ፡ የእሳት ፡ ፍሞችን ፡ ጨምሩ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ራተ ፡ እመ ታክፍቲሁ ፡ እስከ ፡ ሰኰናሁ ፡ ወመጽአ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአሰሰለ ፡ እምኔሁ ፡ ሥቃያተ ።

፴፰፤ ወካዕበ ፡ ወደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ መብዓልተ ፡ ሡነኔ ፡ እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ፡ ወስእኑ ፡ አሕምሞቶሙ ።

፴፱፤ ወእምዝ ፡ ወደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ሞጠቅ ፡ ወወሰርዎሙ ፡ ወወደዩ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ውስተ ፡ ጤገን ፡ ወጠገንዎሙ ፡ በቅብዕ ፡ ወዔው ፡ እስከ ፡ ኮኑ ፡ ሐመደ ። ወእግዚእነ ፡ አንሥአሙ ፡ እሞት ፡ ወአሕየዎሙ ።

፵፤ ወሶበ ፡ ቦኡ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ይቤሎሙ ፡ እመሰ ፡ አማን ፡ እሙታን ፡ ተንሣእክሙ ፡ ረስዩ ፡ ይጸእ ፡ አሣዕንየ ፡ እምእገርየ ፡ ወይኩን ፡ ሕያወ፡ ከመ ፡ ቀዲሙ ፡ ወሶበ ፡ ጸለየ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ኮነ ፡ ሶረ ፡ ዐቢየ ፡ ውእቱ ፡ አሣዕን ፡ ወወጽአ ፡ እምክሣዱ ፡ ጠሊ ።

፵፩፤ ወይእተ ፡ ሶቤ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይጥብሕዎሙ ፡ ወያምስሕዎሙ ፡ ለእልፍ ፡ ወዐሡርቱ ፡ ምእት ፡ ወአርባዕቱ ፡ ሰብእ ፡ ወይቤ ፡ እምከመ ፡ አከሎሙ ፡ ወጸግቡ ፡ ወኢፈቀዱ ፡ ካልዐ ፡ እምዝ ፡ ህልው ፡ ኵሉ ፡ ዘተገብረ ።

፵፪፤ ወእምዝ ፡ ጠብሕዎሙ ፡ ወአምስሕዎሙ ፡ ወአትረፉ ፡ እምሥጋ ፡ ጠሊ ፡ ስድስተ ፡ መዛርዐ ፡ ወእምሥጋ ፡ ላሕም ፡ ዐርባዕተ ፡ መዛርዐ ፡ ወርእዮ ፡ መኰንን ፡ ዘተርፈ ፡ ሥጋ፡ አዘዘ ፡ ይውርውዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ።

፵፫፤ መኰንንኒ ፡ ሶበ ፡ ተኀፍረ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ ፡ ልሳኖ ፡ ለሕፃን ፡ ወእግዚእነ ፡ ሜጠ ፡ ሎቱ ፡ ልሳኖ ፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ያፍልሑ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡ ጽሕርት ፡ ዐቢይ ፡ ወይደይዎሙ ፡ ለሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ወለእሙ፡ ኢየሉጣ ፡ ወርእያ ፡ እሙ ፡ ፈርሀት ፡ ወሶበ ፡ ጸለየ ፡ ላቲ ፡ ወልዳ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወወሀባ ፡ ኃይለ ፡ አምላካዌ ፡ ወቦአት ፡ ውስተ ፡ ጽሕርት ፡ ምስለ ፡ ወልዳ ፡ ወኮነ ፡ ቈሪረ ፡ ከመ ፡ አስሐትያ ፡ ወካዕበ ፡ አዘዘ ፡

እርር፡ ብለው ፡ እንዲቃጠሉ ፡ ዳግመኛም ፡ አራት፡ ችንካሮችን ፡ ከትከሻዎቹ ፡ እስከ ፡ ተረከዙ ፡ ድረስ ፡ እንዲተክሉበት ፡ አዘዘ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ ሥቃዮችን ፡ ከርሱ ፡ አራቀ ።

፴፰፤ ዳግመኛም ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ከሥቃይ ፡ መሣሪያዎች ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው፡ አዋሏቸው ፡ ግን ፡ ማሠቃየት ፡ ተሳናቸው ።

፴፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከማምጠቂያው ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው ፡ መገዙአቸውና ፡ አመድ ፡ እስከሆኑ ፡ ከቅባትና ፡ ከጨው ፡ ጋር ፡ በብረት ፡ ምጣድ ፡ ውስጥ ፡ ቆሉአቸው ፡ ጌታችንም ፡ ከሞት ፡ አስነሥቶ ፡ አዳናቸው ።

፵፤ ወደ ፡ መኰንኑም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ በእውነት ፡ ከሙታን ፡ ተለይታችሁ፡ የተነሣችሁ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ጫማዬ ፡ ከእግሬ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሕያው፡ እንዲሆን ፡ አድርጉ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስም ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ጫማ ፡ ታላቅ ፡ በሬ ፡ ሆነ ፡ ከአንገቱም ፡ ፍየል ፡ ወጣ ።

፵፩፤ በዚያንም ፡ ሰዓት ፡ ለዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሽህ ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ በሬውንና ፡ ፍየሉን ፡ አርደው ፡ ምሳ ፡ እንዲአደርጉላቸው ፡ መኰንኑ፡ አዘዘ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ ይህ ፡ በቅቷቸው ፡ ከጠገቡ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ምግብ፡ ካልፈለጉ፡ የተሠራው ፡ ሁሉ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነዋሪ ፡ ነው ።

፵፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አርደው ፡ ምሳ ፡ አደረጉላቸውና ፡ ከፍየሉ ፡ ሥጋ ፡ ስድስት ፡ እንቅብ ፡ ከበሬው ፡ ሥጋ ፡ አራት ፡ እንቅብ ፡ አተረፉ ፡ መኰንኑም ፡ የተረፈውን ፡ ሥጋ ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እንዲጥሉት ፡ አዘዘ ።

፵፫፤ መኰንኑም ፡ ቢያፍር ፡ የሕፃኑን ፡ ምላስ ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ጌታችንም ፡ ምላሱን ፡ መለሰለት ፡ ዳግመኛም ፡ በታላቅ ፡ ጋን ፡ ውኃ ፡ አፍልተው ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስንና፡ እናቱን ፡ ኢየሉጣን ፡ ይጨምሩአቸው፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እናቱም ፡ አይታ ፡ ፈራች ። ልጅዋም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸለየላት፡ ጊዜ ፡ አምላካዊ ፡ ኃይልን ፡ አሳደረባትና ፡ ከልጅዋ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጋኑ ፡ ገባች ። እንደ ፡ ውርጭም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ሆነ ፡ ደግ

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ይደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ጤገን ፡ ዘውስቴቱ ፡ መንኰራኵር ፡ ወይስሐብዎሙ ፡ እስከ ፡ ይትነተፍ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አውጽአሙ ፡ ሕያዋነ ።

፵፬፤ መኰንንሰ ፡ ሶበ ፡ ስእነ ፡ መዊያቶሙ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ክሣውዲሆሙ ፡ በሰይፍ ፡ ወሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዘክሮተ ፡ ስሙ ፡ ሰጊድ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ሰአለኒ ፡ ዘትፈቅድ ፡፡ ወይቤሎ ፡ ሕፃን ፡ ኢይትቀበር ፡ ሥጋየ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወለኵሉ ፡ ዘጸውዐ ፡ ስምየ ፡ ወዘገብረ ፡ ተዝካርየ ፡ ወለዘሐነፀ ፡ መርጡልየ ፡ ወለዘጸሐፈ ፡ ወአጽሐፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ገድልየ ፡ አው ፡ ለዘያነብቦ ፡ ወለዘያበውእ ፡ መባአ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንየ ፡ ወለዘይጼሊ ፡ ውስቴታ ፡ ሀቦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ወስረይ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወኀበ ፡ ተጸውዐ ፡ ስምየ ፡ በዛቲ ፡ መካን ፡ ኢይምጻእ ፡ ሞተ ፡ ላሕም ፡ ወኢብድብድ ፡ በሰብእ ፡ ወኢ ፡ አባረ ፡ እክል ፡ ወሕጸተ ፡ ማይ።

ሞም ፡ በውስጡ ፡ መንኰራኵር ፡ ወዳለበት ፡ የብረት ፡ ምጣድ ፡ እንዲጨምሩአቸውና ፡ ሥጋቸው ፡ እስከሚቦጫጨቅ ፡ እንዲስቡአቸው ፡ አዘዘ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በሕይወት ፡ አወጣቸው።

፵፬፤ መኰንኑም ፡ እነርሱን ፡ ማሸነፍ ፡ በተሳነው ፡ ጊዜ ፡ ቸብቸቢቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለስም ፡ አጠራሩ ፡ ስግደት ፡ የሚገባው ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወረደ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስንም ፡ የምትሻውን ፡ ለምነኝ ፡ አለው። ሕፃኑም ፡ ሥጋዬ ፡ በምድር ፡ አይቀበር ፡ ስሜን ፡ ለሚጠራ ፡ መታሰቢያዬን ፡ ለሚያደርግ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ ለሚሠራ ፡ የተጋድሎዬን ፡ መጽሐፍ ፡ ለሚጽፍና ፡ ለሚያጽፍ ፡ ወይም ፡ ለሚያነበው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኔ ፡ መባ ፡ ለሚያገባ ፡ በውስጧም ፡ ለሚጸልይ ፡ ለሁሉም ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ስጣቸው ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ስሜም ፡ በሚጠራበት ፡ በዚያች ፡ ቦታ ፡ የከብት ፡ ዕልቂት ፡ አይምጣ ፡ በሰውም ፡ ላይ ፡ አባር ፡ ቸንፈር ፡ በእህልም ፡ ላይ ፡ ድርቅ ፡ የውኃም ፡ ማነስ ፡ አይሁን።

፵፭፤ ወይቤሎ ፡ መድኃኒነ ፡ ኵሎ ፡ ዘሰአልከኒ ፡ እሁበከ ፡ ወአንተ ፡ ትሄሉ ፡ ምስሌየ ፡ በየማንየ ፡ ወሥጋከኒ ፡ አነብር ፡ ዲበ ፡ ሠረገላ ፡ ኤልያስ ፡ ወሰሚዖ ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስ ፡ ተፈሥሐ ፡ ጥቀ ፡ ወአእኰቶ ፡ ለእግዚእነ ። ወእምዝ ፡ ተከለለ ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡ በማዕከለ ፡ ሌሊት ፡ ወከለሎ ፡ መድኃኒነ ፡ በአክሊል ፡ ዘኢይማስን ፡ ወነሥአ ፡ ነፍሶሙ ፡ ምስሌሁ ፡ በስብሐት ፡ ዐቢይ።

፵፭፤መድኃኒታችንም ፡ የለመንከኝን ፡ ሁሉ ፡ እስጥሃለሁ ፡ አንተም ፡ በቀኜ ፡ ትኖራለህ ፡ ሥጋህንም ፡ ኤልያስ ፡ በዐረገበት ፡ ሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ አኖራለሁ ፡ አለው ፡ ሕፃን ፡ ቂርቆስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ጌታችንን ፡ አመሰገነው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሌሊቱ ፡ እኩሌታም ፡ ከእናቱ ፡ ጋር ፡ አንገቱን ፡ ተቆረጠ ፡ መድኃኒታችንም ፡ በማይጠፋ ፡ አክሊል ፡ ጋረደው ፡ ነፍሶቻቸውንም ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አሳረገ።

፵፮፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለቂርቆስ ፡ ወኢየሉጣ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፵፮፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቂርቆስና ፡ በኢየሉጣ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

እግዚአብሔር ፡ ሜመ ፡ ረድኤቶ ፡ ለንስእናከ ፡ ዓቃቢ ። ወስምዖ ፡ መጥበቢ ። ፍትወ ፡ ምግባር ፡ ቂርቆስ ፡ ወምዑዘ ፡ ጊናት ፡ እምከርቢ ። ለዘተጽዕረ ፡ በምንዳቤ ፡ ወለዘቈስለ ፡ በጥብጣቤ ። ለአባልከ ፡ ሰላም ፡ እቤ። ሰላም ፡ ለኢየሉጣ ፡ እንተ ፡ ደለዋ ፡ ትለዶ ። ለቂርቆስ ፡ ባህርይ ፡ ዘብርሃነ ፡ አምላክ ፡ የዓውዶ ። ለመንፈስ ፡ ፍርሀት ፡ ዘባቲ ፡ በኃይለ ፡ ጸሎቱ ፡ ዘሰደዶ ። ትፌቅድኑ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ፡ ለፍሬሁ ፡ ተአልዶ ። እንዝ ፡ በእሳት ፡ ታውዒ ፡ ጐንዶ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡
ኮነ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ ዘትር
ጓሜሁ፡መፍቀሬ፡እግዚአብሔር።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡
አበዊሁኒ ፡ ያመልኩ ፡ ላሕመ ፡ ዘስሙ ፡ መረ
ግድ ፡ ወይሴስይዎ ፡ ስንዳሌ ፡ ብሱለ ፡ ዘቱሱሕ ፡
በቅብዐ ፡ ሰሊጥ ፡ ወመዐር ፡ ወይቀብዕዎ ፡ ቅብዓ
ዕፍረት ፡ ፍትወ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ወያ
ሰትይዎ ፡ ሜሰ ፡ ወቦ ፡ ማኅደር ፡ ለክረምት ፡
ወለኃጋይ ፡ ወውስተ ፡ ክሣዱ ፡ ጋጋ ፡ ዘወርቅ ፡
ወሀብለት።

፫፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ ጥቀ ፡ ሠናይ ፡ በአር
አያሁ ፡ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ አበዊሁ ፡
ተናገርዎ ፡ ከመ ፡ ይስግድ ፡ ለውእቱ ፡ ላሕም ፡
ወኢሰምዐ ፡ ቃሎሙ ፡ ሕፃን ፡ ፊላታዎስ ፡
ወእሙንቱ ፡ ኢፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ያኅዝኑ ፡ ልቦ ፡
በእንተ ፡ አፍቅሮቶሙ ፡ ኪያሁ ፡ ኢያገበርዎ።

፬፤ ወቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ አሚሃ ፡ ኢየአምሮ ፡ ለእግ
ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይመስሎ ፡ ፀሐይ
አምላከ ፡ ወቆመ ፡ ቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ወይቤ ፡
እስእለከ ፡ አንተ ፡ ፀሐይ ፡ ለእመ ፡ አምላክ ፡
አንተ ፡ አጠይቀኒ ፡ ወሶቤሃ ፡ መጽአ ፡ ቃል ፡
ኀቤሁ ፡ እምላዕሉ ፡ ዘይብል ፡ ኢኮንኩ ፡
አምላከ፡ አላ ፡ ላእኩ ፡ ለአምላክ ፡ ዘአንተ ፡
ሀለወከ ፡ ታእምሮ ፡ ወይትከዓው ፡ ደምከ ፡
በእንተ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ።

፭፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ጸንዐ ፡ ልቡ ፡ ለሕፃን ፡
ፊላታዎስ ፡ ወዓዲ ፡ ተፈነወ ፡ ኀቤሁ ፡ መልአክ
በይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ወአጠየቆ ፡ ምሥጢረ ፡
አምላክ ፡ ወከሠተ ፡ ልቦ ፡ ከመ ፡ ይለቡ ፡
ዘይቤሎ ፡ ወአኀዘ ፡ ይንግሮ ፡ እምጥንተ ፡
ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ትስብእቱ ፡ ለመድ
ኃኒነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወተፈሥሐ ፡
ጥቀ ፡ በመንፈሱ።

፮፤ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ዘይጸውም ፡ ወይጼሊ ፡
ብዙኀ ፡ ወትረ ፡ ወኢይበልዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅብ
ስት ፡ ወጼው ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይሁብ ፡ ምጽዋተ ፡

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡
ስድስት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የስሙ ፡ ትርጕም ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ የሆነ ፡ የከበረ ፡ ፊላታዎስ ፡
በሰማዕትነት ፡ ሞተ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከአንጾኪያ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡
ወገን፡ ነው ፡ ወላጆቹም ፡ መረግድ ፡ የሚባል ፡
ላም ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ፡ የተፈተገና ፡ የበሰለ ፡
በሰሊጥ ፡ ቅባትና ፡ በማር ፡ የተለወሰ ፡ ስንዴ ፡
ይመግቡታል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡
የተወደደ ፡ የሽቶ ፡ ቅባት ፡ ይቀቡታል ፡
የወይን፡ ጠጅም ፡ ያጠጡታል ፡ ለክረምትና ፡
ለበጋም ፡ ማደሪያ ፡ አለው ፡ በአንገቱም ፡
የወርቅ ፡ ዛንጅርና ፡ ድሪ ፡ አለ።

፫፤ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ፊላታዎስም ፡ መልኩ ፡ እጅግ ፡
የሚአምር ፡ ነበር ፡ ዐሥር ፡ ዓመትም ፡ በሆነው ፡
ጊዜ ፡ ለዚያ ፡ በሬ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ወላጆቹ ፡
ተናገሩት ፡ ሕፃን ፡ ፊላታዎስም ፡ ቃላቸውን ፡
አልሰማም ፡ እነርሱም ፡ እርሱን ፡ ስለሚ
ወዱት፡ ልቡን ፡ ሊያሳዝኑት ፡ ስለአልፈለጉ ፡
አላስገደዱትም።

፬፤ የከበረ ፡ ፊላታዎስም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጌታችንን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አያውቀውም ፡ ነበር ፡
ፀሐይም ፡ አምላክ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፡ በፀ
ሐይም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አንተ ፡
ፀሐይ ፡ አምላክ ፡ ከሆንክ ፡ ታስረዳኝ ፡ ዘንድ ፡
እለምንሃለሁ ፡ አለው ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡
ከወደላይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደርሱ ፡
መጣ ፡ እኔ ፡ አንተ ፡ ልታወቀውና ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡
ስሙ ፡ ደምህ ፡ ይፈስ ፡ ዘንድ ፡ ያለህ ፡ አምላክ ፡
አይደለሁም።

፭፤ ሕፃን ፡ ፊላታዎስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡
ጸና ፡ ዳግመኛም ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ወደርሱ ፡
መልአክ ፡ ተላከ ፡ እርሱም ፡ የአምላክን ፡
ምሥጢር ፡ አስረዳው ፡ የሚነግረውንም ፡
ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ ልቡናውን ፡ ከፈተለት ፡
ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡
መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ እስከሆ
ነበት፡ ድረስ ፡ የሆነውን ፡ ይነግረው ፡ ጀመረ ፡
በልቡናውም ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው።

፮፤ ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አብዝቶ ፡
የሚጾምና ፡ የሚጸልይ ፡ ሆነ ፡ ከብቻው ፡
እንጀራና ፡ ጨው ፡ በቀር ፡ አይበላም ፡ ለድ

ለነዳያን፡ወለምስኪናን።
፯፤ ወእምዝ፡እምድኅረ፡ዓመት፡ሐለዩ፡አበዊሁ፡
ወገብሩ፡ምሳሐ፡ለአብያጺሁ፡ለወልዶሙ፡
ወነሠሡ፡ከመ፡ይውግር፡ዕጣነ፡ለውእቱ፡
ላሕም ፡ መቅድመ ፡ እንበለ ፡ ይብልዑ ፡
ወይስተዩ ፡ ወቆመ ፡ ፊላታዎስ ፡ ሕፃን ፡
ቅድመ፡ ውእቱ፡ላሕም፡ወይቤሎ፡አማንኑ፡
አምላክ፡አንተ፡ዘያመልኩከ፡ሰብእ፡፡አሜሃ፡
ወጽአ፡ቃል፡እምኔሁ፡ዘይብል፡ኢኮንኩ፡
አነ፡ አምላከ፡ አላ፡ ቦአ፡ ሰይጣን፡ ላዕሌየ፡
ወረሰየኒ፡ከመ፡አስሕቶሙ፡ለሰብእ፡ወዘንተ፡
ብሂሎ፡ ተንሥአ፡ ውእቱ፡ ላሕም፡ ወወግ
አሙ፡ በአቅርንቲሁ፡ ለአበዊሁ፡ ለቅዱስ፡
ፊላታዎስ ፡ ወቀተሎሙ ፡ ፊላታዎስኒ፡
አዘዞሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ይቅትልዎ ፡
ለውእቱ፡ ላሕም ፡ ወያውዕይዎ ፡ በእሳት ፡
እስከ፡ ይከውን ፡ ሐመደ ፡ ወይዝርውዎ ፡
በነፋስ፡ወገብሩ፡በከመ፡አዘዞሙ።
፰፤ ለአበዊሁኒ፡አብድንቲሆሙ፡ኮኑ፡ግዱፋነ፡
እስመ፡ወሀቦ፡እግዚአብሔር፡ጸጋሁ፡ወጸለየ፡
ላዕለ ፡ አብድንቲ ሆሙ ፡ ለአበዊሁ ፡ ወገብ
አት፡ነፍሶሙ፡ወተንሥኡ፡ሶቤሃ፡ወነገርዎ፡
ዘከመ፡ርእዩ፡እምኵነኔያት፡ዘውስተ፡ሲኦል።
፱፤ ወእምዝ፡ተጠምቁ፡ቅዱስ፡ፊላታዎስ፡ወአበ
ዊሁኒ፡ ጥምቀተ፡ ክርስትና፡ በስመ፡ አብ፡
ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ወተውህቦ፡ጸጋ
ፈውስ፡ ወኮነ፡ ዘይፌውሶሙ፡ ለድውያን፡
በጸሎቱ።
፲፤ ወተሰምዐ፡ ዜናሁ፡ ኀበ፡ ንጉሥ፡ ዲዮቅልጥ
ያኖስ ፡ ወፈነወ ፡ መላእክተ ፡ ወአብጽሐ ፡
ኀቤሁ ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይውግር ፡ ዕጣነ ፡
ለአጽሎን ፡ ወተካየዶ ፡ ኪዳናተ ፡ ብዙኃተ ።
ወሶበ፡ኢሰምዖ፡አዘዘ፡ከመ፡ይኰንንዎ፡በዘዘ
ዚአሁ፡ኵነኔ፡ወቀሠፍዎ፡በአስዋጥ፡ወአን
በሩ፡ዲበ፡ከርሡ፡አዕባነ፡ክቡዳነ፡ውእቱሰ፡
ጽኑዕ፡በኃይለ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሎቱ፡ስብሐት።
፲፩፤ ወእምዝ፡አኀዘ፡ይርግሞሙ፡ለንጉሥ፡ወለአ
ማልክት፡ርኵሳን፡ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ይዝብ
ጥዎ፡አፉሁ፡ወይምትሩ፡ልሳኖ፡ወይስብሩ፡
ስነኒሁ፡ወእግዚአነ፡ረሰዮ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡
ሙስና።

ኖችና፡ለምስኪኖችም፡ምጽዋት፡ይሰጣል።
፯፤ ከዓመትም ፡ በኋላ ፡ ወላጆቹ ፡ አሰቡ ፡ ለልጅ
ቻው፡ባልንጀሮች፡ምሳ፡አዘጋጁ፡ሳይበሉና፡
ሳይጠጡ፡አስቀድሞ፡ልጃቸው፡ፊላታዎስ፡
ለዚያ፡በሬ፡ዕጣን፡እንዲአሳርግ፡ፈለጉ፡ሕፃኑ
ፊላታዎስም፡በበሬው፡ፊት፡ቁሞ፡ሰዎች፡
የሚያመልኩህ፡አንተ፡በእውነት፡አምላክ፡
ነህን፡አለው ። ያን፡ጊዜ፡ከበሬው፡እንዲህ፡
የሚል፡ቃል፡ወጣ፡እኔ፡አምላክ፡አይደለሁም
ሰይጣን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ ሰዎችን ፡
እንዳስት፡አደረገኝ፡እንጂ፡ይህንንም፡ብሎ፡
ያ፡በሬ፡ተነሥቶ፡የቅዱስ፡ፊላታዎስን፡ወላ
ጆች ፡ በቀንዶቹ ፡ ወግቶ ፡ ገደላቸው ፡ ፊላታ
ዎስም፡ያንን፡በሬ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡አመድ
እስከሚሆንም፡በእሳት፡አቃጥለው፡በነፋስ
ይበትኑት፡ዘንድ፡አገልጋዮቹን፡አዘዛቸው፡
እርሳቸውም፡እንዳዘዛቸው፡አደረጉ።

፰፤ የወላጆቹም፡በድኖቻቸው፡ወድቀው፡ነበር፡
እግዚአብሔርም፡ጸጋውን፡አሳድሮበታልና፡
ቅዱስ፡ፊላታዎስ፡በወላጆቹ፡በድኖች፡ላይ፡
ጸለየ፡ነፍሳቸውም፡ተመልሳ፡በዚያን፡ጊዜ፡
ተነሡ፡በሲኦልም፡ከአዩት፡ሥቃይ፡ነገሩት።
፱፤ ከዚህም፡በኋላ፡ቅዱስ፡ፊላታዎስና፡ወላጆቹ፡
በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ ስም ፥ የክ
ርስትና፡ጥምቀትን፡ተጠመቁ፡ሀብተ፡ፈው
ስም ፡ ተሰጥቶት ፡ በጸሎቱ ፡ በሽተኞችን ፡
የሚፈውስ፡ሆነ።
፲፤ ወሬውም፡በንጉሡ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ዘንድ፡
ተሰማ፡መልከተኞችንም፡ልኮ፡ወደርሱ፡አስ
ቀረበውና፡ለአጵሎን፡ዕጣን፡ያሳርግ፡ዘንድ፡
አዘዘው፡ብዙ፡ቃል፡ኪዳንም፡ገባለት፡ባልሰ
ማውም ፡ ጊዜ ፡ በየአይነቱ ፡ በሆነ፡ ሥቃይ ፡
ያሠቃዩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። በአላንጋዎች ፡
ገረፉት፡በሆዱም፡ላይ፡የሚከብዱ፡ደንጊያ
ዎችን፡አደረጉ፡እርሱ፡ግን፡በክብር፡ባለቤት
ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኃይል፡የጸና፡ነው።

፲፩፤ ከዚህም፡በኋላ፡ንጉሡንና፡የረከሱ፡አማልክ
ቶችን፡ ሊረግማቸው፡ ጀመረ፡ ንጉሡም፡
አፉን ፡ ይመቱት ፡ ዘንድ ፡ ምላሱንም ፡
ይቆርጡ ፤ ጥርሶቹንም ፡ ይሰብሩ ፡ ዘንድ ፡
አዘዘ፡ ጌታችንም ፡ ያለ ፡ ጥፋት ፡ ጤነኛ፡
አደረገው።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፡ ወእምዝ፡አ'ነዘ፡ንጉሥ፡ከመ፡ይሒጦ፡ወይት
ናገሮ፡ቃለ፡ጥዑመ፡ወቅዱስሰ፡ፊላታዎስ፡
ተካየዶ፡እንዘ፡ይሣለቆ፡ከመ፡ይሡዕ፡ለአ
ማክቲሁ ፡ ወተፈሥሐ ፡ ንጉሥ ፡ እስመ ፡
መሰሎ፡እሙነ፡ወአዘዘ፡ከመ፡ያምጽእዎ፡
ለአጽሎን ፡ ወለገነውተ ፡ አማልክት ፡ ወለ
ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ጣዖት ። ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡
ይዑድ፡ዓዋዲ፡ውስተ፡ሀገር፡እንዘ፡ይብል፡
ንዑአ፡ኩልክሙአ፡አሕዛብአ፡ከመ፡ትርአ
ይዎአ ፡ ለፊላታዎስአ ፡ እንዘ ፡ ይሠውዕአ ፡
ለአማልክትአ ፡ ወተጋብኡ ፡ ሶቤሃ ፡
ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ውስተ፡ዐውደ፡ምኵናን።

፲፫፡ ወእንዘ ፡ ያመጽእዎሙ ፡ ለጣዖታት ፡
በውስተ ፡ ፍኖት ፡ ሰአሎ ፡ ለእግዚእነ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ቅዱስ፡
ፊላታዎስ፡ከመ፡ትክሥት፡ምድር፡አፉሃ፡
ወተሐጦሙ፡ለጣዖታት፡ወለገነውቶሙ፡
ወለኵሎሙ፡መጥዓውያን፡ወውህጠቶሙ፡
ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ክላህ ፡ በውስተ ፡ ዐውደ ፡
ምኵናን ። ወርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ መንከረ ፡
ግብረ፡ አምኑ ፡ ብዙኃን ፡ በእግዚእነ ፡
ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወተምዐ፡ንጉሥ፡
ወአዘዘ፡ይምትሩ፡አርእስቲሆሙ፡በሰይፍ፡
ወመተርዎሙ፡ወነሥኡ፡አክሊለ፡ስምዕ፡
ወቦኡ፡ውስተ፡ሕይወት፡ዘለዓለም።

፲፬፡ ወለቅዱስሰ ፡ ፊላታዎስ ፡ ኰንኖቶ ፡ ሶበ ፡
ደክመ ፡ ንጉሥ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡
በሰይፍ ፡ ወመተርዎ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡
ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፲፭፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰማዕት ፡
ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፲፪፡ ከዚህም፡በኋላ፡ንጉሡ፡ይሸነግለው፡ዘንድ፡
መልካም፡ቃል፡ሊናገረው፡ጀመረ፡የከበረ፡
ፊላታዎስ ፡ ግን ፡ ሲዘብትበት ፡ ለጣዖቶቹ ፡
እንደሚሠዋ ፡ ቃል ፡ ገባለት ፡ ንጉሡም ፡
እውነት፡ስለመሰለው፡ደስ፡አለው፡አጵሎ
ንንና ፡ አገልጋዮቹን ፡ ለጣዖትም ፡ የሚገ
ዙትን፡ሁሉንም፡እንዲአመጡአቸው፡አዘዘ፡
ዳግመኛም ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ዓዋጅ ፡
ነጋሪ ፡ ይዞር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡
ሁላችሁ ፡ አሕዛብ ፡ ኑ ፡ ፊላታዎስ ፡ ለአማ
ልክት ፡ ሲሠዋ ፡ ታዩ ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብም ፡
ሁሉ፡ወደ፡ፍርድ፡አደባባይ፡ተሰበሰቡ።

፲፫፡ ጣዖታቱንም ፡ በጐዳና ፡ ውስጥ ፡ ሲያመጡ
አቸው ፡ የከበረ ፡ ፊላታዎስ ፡ የክብር ፡ ባለ
ቤት፡ጌታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ጣዖ
ታቱንና፡አገልጋዮቻቸውን፡ጣዖት፡አምላ
ኪዎችንም ፡ ሁሉንም ፡ ምድር ፡ አፍዋን ፡
ከፍታ፡ትውጣቻው፡ዘንድ፡ለመነው፡ዋጠቻ
ቸውም ። በአደባባዩም ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡
ጭኸትና ፡ ሽብር ፡ ሆነ። ይህንን ፡ ድንቅ ፡
ሥራ፡ አይተው ፡ ብዙዎች ፡ በክብር ፡ ባለ
ቤት፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመኑ ፡
ንጉሡም ፡ ተቆጥቶ ፡ ራሳቸውን ፡ በሰይፍ ፡
እንዲቆርጡ፡አዘዘ፡ቆረጡአቸውም፡የሰማዕ
ትነት ፡ አክሊልንም ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡
ዘላለም፡ሕይወት፡ገቡ።

፲፬፡የከበረ፡ፊላታዎስንም፡ማሠቃየቱን፡ንጉሡ፡
በሰለቸ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጡ ፡
ዘንድ፡አዘዘና፡ቆረጡት፡የሰማዕትነት፡አክ
ሊልንም፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።

፲፭፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም
በዚህ፡ሰማዕት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለፊላታዎስ፡መሥዋዕተ፡አምላክ፡ደሙ።ወመፍቀሬ፡እግዚእ፡ትርጓሜ፡ስሙ።ከመ፡ኢኮነ፡
ፈጣሬ፡እንበለ፡ፍጥረት፡ዳዕሙ።ፀሐይ፡ገሀደ፡ነገሮ፡ለሰማይ፡በፍጹሙ።ወዘያመልክዎ፡ላሕም፡አቡሁ፡
ወእሙ።

፲፮፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡
ጳላድዮስ፡መስተጋድል። ወዝንቱ፡ቅዱስ፡
ነበረ ፡ ፶ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ኢይወጽእ ፡ እምጸ

፲፮፡በዚችም፡ቀን፡የከበረ፡አባት፡ተጋዳይ፡የሆነ፡
ጳላድዮስ፡አረፈ። ይህም፡ቅዱስ፡ከዋሻው፡
ሳይወጣ ፡ የሴቶችን ፡ ፊት ፡ ሳያይ ፡ ሃምሳ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ማዕቱ ፡ ወኢይሬኢ ፡ ገጸ ፡ አንስት ፡ ወተ
ውህቦ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት፡
ወጸጋ፡ትንቢት፡ወተሰምዐ፡ዜናሁ፡ውስተ፡
ኵሉ፡መካን።

፲፯፡ወሀሎ፡፩ነጋዲ፡በሀገረ፡ምስር፡ወሖረ፡ከመ፡
ይንግድ ፡ በሐመር ፡ ወተንሥአ ፡ ላዕሌሁ ፡
ማዕበል ፡ ወበጽሐ ፡ ለተሠጥሞ ፡ ወሶበ ፡
ቀብጸ፡ ተስፋ፡ጸርሐ፡እንዘ፡ይብል፡ተማሕ
ጸንኩ ፡ በጸሎተ ፡ አባ ፡ ጳላድዮስ ፡ ለእመ ፡
ድኅንኩ፡እሞት፡እሁብ፡፻ተ፡ዲናረ፡ሎቱ፡
ወሶቤሃ ፡ ርእዮ ፡ ለአባ ፡ ጳላድዮስ ፡ እንዘ ፡
ይኄድፍ፡ሐመሮ፡በመስቀሉ፡ወአብጽሖ፡
ውስተ፡መርሶ።

፲፰፡ወእምዝ፡ሶበ፡በጽሐ፡ውስተ፡ሀገር፡ውእቱ፡
ነጋዲ ፡ ተዐሰበ ፡ ፈረሰ ፡ ወነሥአ ፡ ውእተ ፡
ምእተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡ወሖረ፡ኀበ፡ጳላደዮስ፡
ወሶበ፡መስየ፡ኀደረ፡ውስተ፡አሐቲ፡ሀገር፡
ውስተ፡ቤተ፡ነግድ፡ወረከበ፡በህየ፡ብእሴ፡
ዘስሙ ፡ ሞሪት ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡
ልቡ ፡ ወይቤሎ ፡ ሞሪት ፡ አነ ፡ አአምር ፡
መካኖ ፡ ወአበጽሐከ ፡ ኀቤሁ ፡ ወበሳኒታ ፡
ሖሩ፡ ክልኤሆሙ ፡ ወበጽሑ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡
ጳላድዮስ ፡ ወበጺሖሙ ፡ ተአምኆዎ ፡ ውእ
ቱኒ፡ ነጋዲ ፡ ወሀቦ ፡ ውእተ ፡ ወርቀ ፡ ዘአም
ጽአ ፡ ሎቱ ፡ ወርእዮ ፡ አባ ፡ ጳላድዮስ ፡ ባረኮ ፡
ወይቤሎ ፡ አልብየ ፡ መፍቅድ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡
ወርቅ ፡ ወባሕቱ ፡ ሑር ፡ ዝርዎ ፡ ለነዳያን ፡ ወለ
ምስኪናን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለከ ፡ ረባሐ ፡
በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱሰ ፡ ነጋዲ ፡
ወድቀ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወአስተ ብቍዖ ፡
ከመ ፡ ይትመጠ ፡ ወነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ንስቲተ ፡
ወይቤሎ ፡ ተመጠውኩ ፡ ለከ ፡ ዘንተ፡ ለበ
ረከት ፡ ወለዘተርፈ ፡ ግበሮ ፡ በከመ ፡ አዘዝ
ኩከ።

፲፱፡ ወተመይጠ ፡ ውእቱ ፡ ነጋዲ ፡ ነሢአ ፡ ወርቀ ፡
ወወረደ ፡ እምደብር ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ፈለግ ፡
ወሶቤሃ፡ቦአ፡ሰይጣን።ውስተ፡ልበ፡ሞሪት፡
ወፈተወ፡ይንሣእ፡ንዋዮ፡ወሠረረ፡ላዕሌሁ፡
በመዓት፡ወቀተሎ፡ወያረ፡በድኖ፡በሌሊት፡
ወገደፎ ፡ ኀበ ፡ ኖኅተ ፡ አባ ፡ ጳላድዮስ ፡
ወበሣኒታ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወነገሮ ፡
በእንተ፡ምውት።

ዓመት ፡ ኖረ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ የማ
ድረግና ፡ የትንቢት ፡ መናገር ፡ ሀብት ፡
ተሰጠው ፡ ዜናውም ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡
ተሰማ።

፲፯፡ በምስር ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ነበር ፡
ይነግድም ፡ ዘንድ ፡ በመርከብ ፡ ተጭኖ ፡ ሔደ ፡
ማዕበልም ፡ ተነሥቶበት ፡ ለመሥጠም ፡
ደረሰ፡ በአባ ፡ ጳላድዮስ ፡ ጸሎት ፡ ተማጽኛ
ለሁ ፡ ከሞት ፡ ከዳንኩ ፡ መቶ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡
ለእርሱ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፡ በዚያንም ፡
ጊዜ ፡ በመስቀሉ ፡ መርከቡን ፡ ሲቀዝፍ ፡ አባ ፡
ጳላድዮስን ፡ አየው ፡ ወደ ፡ ወደብም ፡
አደረሰው።

፲፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በደረሰ ፡
ጊዜ ፡ ያ ፡ ነጋዴ ፡ ፈረስ ፡ ተከራይቶ ፡ ያንን ፡
መቶ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አባ ፡
ጳላድዮስ ፡ ሔደ ፡ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ በአንዲት ፡
አገር ፡ በእንግዳ ፡ ማደሪያ ፡ ውስጥ ፡ አደረ ።
በዚያም ፡ ሞሪት ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አግኝቶ ፡
በልቡ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ምሥጢሩን ፡ ነገ
ረው፡ ሞሪትም ፡ እኔ ፡ ቦታውን ፡ አውቀዋ
ለሁና ፡ ወደርሱ ፡ አደርስሃለሁ ፡ አለው ፡ በማ
ግሥቱም ፡ ሁለቱም ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ጳላድዮስ ፡
ሔዱ ፡ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡት ፡
ነጋዴውም ፡ ያን ፡ ያመጣውን ፡ ወርቅ ፡
ሰጠው ። አባ ፡ ጳላድዮስም ፡ አይቶ ፡ ባረከው ፡
እንዲህም ፡ አለው ፡ ወደዚህ ፡ ወርቅ ፡ ፍላጎት ፡
የለኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ጠቃሚ ፡ እንዲሆንህ ፡ ሒደህ ፡ ለድኆችና ፡
ለችግረኞች ፡ በትነው ፡ አለው ፡ ነጋዴው ፡
ግን፡ ይቀበለው ፡ ዘንድ ፡ ከእግሩ ፡ ሥር ፡
ወድቆ ፡ ማለደው ፡ ጥቂትም ፡ ወሰደለትና ፡
እንዲህ ፡ አለው ፡ ለበረከት ፡ ይህን ፡ ተቀብየ
ሃለሁ ፡ የቀረውን ፡ እንዳዘዝኩህ ፡ አድርገው ፡
አለው።

፲፱፡ ነጋዴውም ፡ ወርቁን ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ፡ ከተራ
ራውም ፡ ወርዶ ፡ ከወንዝ ፡ ደረሰ ፡ በዚያንም ፡
ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ በሞሪት ፡ ልብ ፡ አደረና ፡
ገንዘቡን ፡ ሊወስድ ፡ ወደደ ፡ በአደገኛነትም ፡
በላዩ ፡ ተወርውሮ ፡ ገደለው ፡ በሌሊትም ፡
በድኑን ፡ ተሸክሞ ፡ ወስዶ ፡ ከአባ ፡ ጳላድዮስ ፡
ደጅ ፡ ጣለው ፡ በማግሥቱም ፡ ወደ ፡ አገረ ፡
ገዥ ፡ ሒዶ ፡ ስለ ፡ ሟቹ ፡ ነገረው።

www.ethiopianorthodox.org

፳፡ ወበጺሖ ፡ መኰንን ፡ህየ ፡ አኀዘ ፡ ለአባ ፡ ጳላድዮስ፡ወአሠሮ፡ጽኑዐ፡ወአኀዘ፡ይሕትቶ፡ በእንተ ፡ ምውት ፡ ወውእቱ ፡ ይቤሎ ፡ ለመ ኰንን ፡ አንሰ ፡ ኢቀተልኩ ፡ ወቀሪቦ ፡ ኀበ ፡ ምውት፡አኀዘ፡ንፍቆ፡ወጸለየ፡ነዋኀ፡ጸሎተ። ወይቤ፡እኤዝዘከ፡አ፡በድን፡በስመ፡እግዚአ ብሔር ፡ ከመ ፡ ትትነሣእ ፡ ወትንግር ፡ ከመ ፡ መኑ፡ቀተለከ፡ወበጊዜሃ፡ተንሥአ፡ምውት፡ ወተናገረ ፡ ከመ ፡ ሞሪት ፡ ቀተሎ ፡ በእንተ ፡ ንዋዩ፡ወርእዮ፡መኰንን፡ዘንተ፡መንክረ፡ደ ንገጸ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ለአባ ፡ ጳላድዮስ ፡ ወነስሐ፡በእንተ፡ዘአሕሰመ፡ላዕሌሁ፡ወሶበ፡ ፈቀደ፡መኰንን፡ከመ፡ይቅትሎ፡ለሞሪት፡ አኀደጎ፡አባ፡ጳላድየስ፡ወእምድኅረ፡ብዙኅ፡ ተጋድሎ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አዕረፈ፡በርሥእ፡ሠናይ።

፳፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡ጻድቅ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፡ መኰንኑም፡ወደዚያ፡በደረሰ፡ጊዜ፡አባ፡ጳላድ ዮስን፡ይዞ፡ጽኑ፡እሥራትን፡አሠረውና፡ስለ፡ ሞተው ፡ ሰው ፡ ሊመረምረው ፡ ጀመረ ። እር ሱም ፡ እኔ ፡ አልገደልኩም ፡ አለው ፡ ወደሞ ተውም ፡ ቀርቦ ፡ ቃሬዛውን ፡ ይዞ ፡ ረጅም ፡ ጸሎትን ፡ ጸለየ ፡ በድን ፡ ሆይ ፡ ማን ፡ እንደገ ደለህ፡ ተነሥተህ ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ስም ፡ አዝዝሃለሁ ፡ አለ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሞተው ፡ ተነሥቶ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ሞሪት ፡ እንደ ፡ ገደለው ፡ ተናገረ ፡ መኰንኑም ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡ ተአምር ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ፡ ለአባ፡ጳላድዮስም፡ሰገደለት፡በላዩም፡ክፉ፡ ስላደረገ፡ ተጸጸተ ፡ ሞሪትንም ፡ ሊገድለው ፡ ወደደ፡አባ፡ጳላድዮስም፡አስተወው።ከብዙ፡ ተጋድሎም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ፡አገልግሎ፡በመልካም፡ሽምግልና፡ አረፈ።

፳፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለጳላድዮስ፡ዕጉሠ፡መከራ፡ወሕማም።አመ፡ሐሰወ፡ላዕሌሁ፡ብእሴ፡ሥጋ፡ወደም።በኃይለ፡ ጸሎቱ፡ ቅድስት ፡ እስከ ፡ ተንሥአ ፡ ንዉም ። ሱታፌ ፡ ምግባሩ ፡ ወላእከ ፡ ዚአሁ ፡ ድኩም ። ለቴዎድሮስ ፡ ረድኡ፡ሰላም፡ሰላም።

፳፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ፲፻ ወ፭፻ወ፫ መኳንንት ፡ ማኅበራኒሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ፊላታ ዎስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስ ብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፳፫፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡፲፻ወ፲፻ ወ፬ቱ፡ሠራዊት፡ማኅበረ፡ቅዱስ፡ቂርቆስ፡ በረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእ ግዚአብሔር፡አሜን።

፳፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የቅዱስ ፡ ፊላታዎስ ፡ ማኅበር፡የሆኑ፡ዐሥር፡ሺህ፡አምስት፡መቶ፡ ሦስት፡መኳንንቶችም፡በሰማዕትነት፡ሞቱ። በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአ ብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

፳፫፡ በዚችም፡ዕለት፡ደግሞ፡የቅዱስ፡ቂርቆስ፡ ማኅበር፡የሆኑ፡ዐሥራ፡አንድ፡ሽህ፡አራት፡ ሠራዊት ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ፡ በረከታ ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ዘምስለ ፡ ቂርቆስ ፡ ሰማዕታተ። እልፈ ፡ ወአርባዕተ ፡ ወዐሠርተ ፡ ምእተ። ዘአኮ ፡ እለ ፡ ሞቱ፡ሠናየ፡ሞተ።ኃጥአን፡ አላ፡ዘረውዎሙ፡ዝርወተ።ከመ፡ይዘርዉ፡ተኰላት፡መርዔተ።

ሰላም ፡ ለእልፍ ፡ ወኃምስቱ ፡ ምእት ፡ ሠራዊት። ወለሠለስቱ ፡ መኳንንት። ማኅበራኒሁ ፡ ለኄር ፡ ፊላታዎስ፡ሰማዕት። እስመ ፡ እጸርሕ ፡ ኀቤክሙ ፡ አመ ፡ ሰዐ ፡ ሑረት ፡ ዕፅብት። ከመ ፡ ትቁሙኒ ፡ በይእቲ ፡ ፍኖት።

፳፬፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡ አባ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክን ድርያ፡ወውእቱ፡እምኍልቆሙ፡ለአበው፡ ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፵ወ፰ቱ።

፳፭፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ መነኰሰ ፡ እምንእሱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ መቃ ርስ ፡ ዘገዳመ ፡አስቄጥስ ፡ ወተጋደለ ፡ ተጋ ድሎ፡ዐቢየ፡ወተጸምደ፡በጾም፡ወበጸሎት፡ ወበትጋህ፡ወኀረዮ፡እግዚአብሔር፡ወሤሞ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቀሲሰ ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ፡ ለቅዱስ ፡ ሚናስ ፡ ሰማዕት ፡ ወመጠውዎ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ወምድሮ ፡ ወዘያበውኡ ፡ ውስቴታ ፡ አምኃ ፡ ወብፅዓተ ፡ ወመገቦ ፡ ሠናየ ፡ ምግብና ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተል እከ፡በሰላም።

፳፮፤ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት፡ ዘእምቅድሜሁ ፡ ተጋብኡ ፡ ኤጲስቆ ጶሳት ፡ ወማእምራን ፡ ከመ ፡ ይኅረዩ ፡ ዘይ ሠይሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኀረዩ፡ ብዙኃነ ፡ ወጸሐፉ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ክርታስ ። ወይቤሎሙ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ለምንት ፡ ረሳዕክምዎ ፡ ለዮሐንስ ፡ ቀሲስ ፡ መጋቤ ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘቅዱስ፡ሚናስ፡ሰማዕት፡ ወይቤሉ፡ኵሎሙ፡በአማን፡ይደሉ፡ውእቱ፡ ለዛቲ፡ሢመት።

፳፯፤ ወእምዝ ፡ ጸሐፉ ፡ ስሞ ፡ በክርታስ ፡ ወደ መርዎ ፡ ምስለ ፡ እሉ ፡ ወአንበርዎ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይጼልዩ፡ ወይ ቄድሱ ፡ ፫ተ ፡ ዕለታተ ፡ ወእምዝ ፡ አምጽኡ ፡ ሕፃነ ፡ ወአዘዝዎ ፡ ይንሣእ ፡ አሐደ ፡ ክር ታሰ ፡ ወነሥአ ፡ ለይእቲ ፡ ክርታስ ፡ ዘውስ ቴታ ፡ ስሙ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ወርእዮሙ ፡ ደመርዋ፡ ምስለ ፡ ክርታሳት ፡ ካዕበ ፡ ወአ ምጽኡ ፡ ካልአ፡ ሕፃነ ፡ ውእቱኒ ፡ ነሥአ ፡ ለይእቲ ፡ ክርታስ ፡ ዳግመ ። ወርእዮሙ ፡ ሜጥዋ ፡ ወደመርዋ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ወአ ምጽኡ ፡ ሣልሳየ ፡ ሕፃነ፡ ውእቱኒ ፡ ነሥአ ፡ ለይእቲ ፡ ክርታስ ፡ ዘውስቴታ ፡ ስሙ ፡ ለዝ ንቱ ፡ አብ ፡ ዮሐንስ፡ ወጠየቁ ፡ ከመ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ኅረዮ ፡ ወእምዝ ፡ አንገዝዎ ፡ ወሤ ምዎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ እስክን ድርያ፡ዘእንበለ፡ፈቃዱ።

፳፬፤ በዚቺም፡ዕለት፡የእስክንድርያ፡አገር፡ሊቀ፡ ጳጳሳት፡የከበረ፡አባት፡አባ፡ዮሐንስ፡አረፈ፡ እርሱም፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡አርባ፡ ስምንተኛ፡ነው።

፳፭፤ ይህ፡አባት፡ከታናሽነቱ፡በአስቄጥስ፡ገዳም፡ በአባ፡መቃርስ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡ መንኵሶ ፡ ፍጹም ፡ ተጋድሎን ፡ ተጋደለ ። በጾም ፡ በጸሎት ፡ በመትጋት ፡ የተጠመደ ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ተመርጦ ፡ በሰ ማዕቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሚናስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሚካኤል፡ ቅስና ፡ ሾመው፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ምድሩንም ፡ በውስጧ ፡ የሚገባውን ፡ መባና፡ስዕለቱንም፡አስረከቡት፡መልካም፡ አስተዳደርንም ፡ አስተዳደረ ፡ በሰላም ፡ በፍ ቅርም፡አገለገለ።

፳፮፤ ከእርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ የሚሾሙትን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይመርጡ ፡ ዘንድ ፡ ኤጲስቆጶ ሳቱና ፡ መምህራኑ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ብዙዎ ችንም፡ መርጠው ፡ ስማቸውን ፡ በክርታስ ። ጻፉ ፡ አንድ ፡ ጻድቅ ፡ ሰውም ፡ በሰማዕት ፡ ቅዱስ ፡ ሚናስ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሾ መውን ፡ ቀሲስ ፡ ዮሐንስን ፡ ለምን ፡ ረሳ ችሁት፡አላቸው፡ሁሉም፡በእውነት፡እርሱ፡ ለዚች፡ሹመት፡የተገባ፡ነው፡አሉ።

፳፯፤ ከዚህም፡በኋላ፡ስሙን፡በክርታስ፡ጽፈው፡ ከእነዚያ፡ጋር፡ቀላቀሉት፡በመሠዊያ፡ላይ፡ አድርገው፡ሦስት፡ቀኖች፡ሲጸልዩና፡ሲቀ ድሱ ፡ ኖሩ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሕፃን ፡ አምጥተው፡አንዷን፡ክርታስ፡እንዲአነሣ፡ አዘዙትና፡በውስጧ፡የዚህ፡ቅዱስ፡ስም፡ ያለባትን ፡ ነሣ ፡ አይተውም ፡ መልሰው ፡ ከክር ሶ፡ጋር፡ቀላቀሏት።ሌላ፡ሕፃንም፡ አመጡና፡እርሱም፡ያቺን፡ክርታስ፡ደግሞ፡ አነሣት፡አይተው፡እንደ፡ቀድሞው፡መል ሰው፡ቀላቀሏት።ሦስተኛም፡ሕፃን፡አመጡ፡ እርሱም ፡ የዚህ ፡ አባት ፡ ዮሐንስ ፡ ስም ፡ ያለባትን፡ያቺን፡ክርታስ፡አነሣ፡እግዚአብ ሔርም፡እንደ፡መረጠው፡ተረዱ፡ከዚህም፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ ውዴታው ፡ ይዘው ፡ በእስክን ድርያ፡አገር፡ላይ፡ሊቀ፡ጵጵስና፡ሾሙት።

www.ethiopianorthodox.org

፳፰፤ ወሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ዐቀቦሙ ፡ ለመርዔቱ ፡ በከመ ፡ ሐዋርያት ፡ ወያነብብ ፡ ሎሙ ፡ መጻ ሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኮነ ፡ ዘያጸንዖሙ ፡ በገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ወውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርት ዕት ፡ ወብዙኀ ፡ ምሕረት ፡ ወምጽዋት ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘቦ ፡ ተጽናስ።

፳፱፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ረኃብ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ እስከ ፡ ኮነ ፡ ለ፩መሥፈርተ ፡ ሥርናይ ፡ ሤጡ ፡ ፪ተ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ወይት ጋባኡ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ቤቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ነዳያን ፡ ወምስኪናን ፡ ወብዙኃን ፡ እም ውስተ ፡ ሕዝብ ። ወሤሞ ፡ ለረድኡ ፡ ማርቆስ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ንዋየ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወኮነ ፡ ዘይሁቦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ጽኑሳን ፡ በጽባሕ ፡ ወበምሴት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ አእተተ ፡ መዓቶ ፡ እግዚእነ ፡ እምላዕለ ፡ ሰብእ ፡ ወበእ ንተዝ ፡ ተሰምየ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ዮሐንስሃ ፡ መሐሬ።

፴፤ ወእምዝ ፡ ሐነፀ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአሠርገዎን ፡ በኵሉ ፡ ሠርጕ ፡ ሠናይ።

፴፩፤ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ነገሮሙ ፡ ለካህናት ፡ ዕለተ ፡ ዘየዓርፍ ፡ ባቲ ፡ ወይቤ ሎሙ ፡ አንሰ ፡ ተወለድኩ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ለጥር ፡ ወበይእቲ ፡ ተሰየምኩ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወባቲ ፡ ካዕበ ፡ አአርፍ ፡ ወሶበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ዘንተ ፡ በከዩ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወይቤልዎ ፡ ኦ ፡ አቡነ ፡ መኑ ፡ ዘይሠየም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እምድኅ ሬከ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ቀሲስ ፡ ማርቆስ ፡ ረድእየ ፡ እስመ ፡ ኀረዮ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ለጥር ፡ አዕረፈ ፡ እምድኅረ ፡ ነበረ ፡ በሢመቱ ፡ ፳ወ፫ተ ፡ ዓመተ።

፴፪፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ሞተ ፡ ዳዊት ፡ ዘተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ እስክንድርያ ፡ በግፍዕ ፡ ወተሠይመ ፡ ካዕበ ፡ ካልዕ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘኮነ ፡ እምቅድሜሁ ፡ እምድኅረ ፡ ነበረ ፡ ፲ ፡ ዓመተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ። ወሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጸሐፈ ፡ መል እክተ ፡ ዘበእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተሠይመ ፡ ህየን

፳፰፡ በተሾመም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ አጠባ በቅ ፡ መንጋዎቹን ፡ ጠበቀ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ ሔርም ፡ የሚያደርሱ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ ያነብ ላቸው ፡ ነበር ፡ በበጎ ፡ ሥራና ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያጸናቸው ፡ ሆነ ፡ ችግር ፡ ላለበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አብዝቶ ፡ የሚራራና ፡ የሚመጸውት ፡ ሆነ።

፳፱፡ በዘመኑም ፡ አንድ ፡ መስፈሪያ ፡ ሥንዴ ፡ ዋጋው ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ እስኪሆን ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ታላቅ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ፡ ድኆችና ፡ ችግረኞች ፡ ከሕዝቡም ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ነበር። ረዳቱ ፡ ማርቆስንም ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ገን ዘብ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ሾመው ፡ ጌታችንም ፡ ከሰ ዎች ፡ ላይ ፡ ቍጣውን ፡ እስከ ፡ አራቀ ፡ ድረስ ፡ ለችግረኞች ፡ ሁሉ ፡ በጥዋትና ፡ በማታ ፡ የሚሰ ጣቸው ፡ ሆነ ፡ ስለዚህም ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ዮሐንስ ፡ መሐሪ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ።

፴፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ አባት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያ ናትን ፡ ሠራ ፡ በጌጥ ፡ ሁሉ ፡ አስጌጣቸው።

፴፩፡ ዕረፍቱም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ለካህናቱ ፡ የሚያርፍ ባትን ፡ ቀን ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ተወለድኩ ፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾምኩ ፡ ደግሞ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ አርፋለሁ ። ይህንንም ፡ ሲላቸው ፡ ኤጲስቆጶሳቱ ፡ አለቀሱና ፡ አባታ ችን ፡ ሆይ ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ የሚሾም ፡ ማን ፡ ነው ፡ አሉት። እርሱም ፡ ረዳቴ ፡ ቀሲስ ፡ ማርቆስ ፡ ነው ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ለዚች ፡ ሹመት ፡ መርጦታልና ፡ አላቸው። በሹመቱ ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ አረፈ።

፴፪፡ በዘመኑም ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ በግፍዕ ፡ የተሾመው ፡ ዳዊት ፡ ሞተ ፡ ዳግመ ኛም ፡ ከእርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተባለ ፡ ተሾመ። ይህም ፡ አባት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ መልእክትን ፡ ጻፈ ፡ ጊዮርጊስም ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ስሙ ፡ ኪራ

www.ethiopianorthodox.org

ቴሁ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ዘስሙ ፡ ኪራኮስ ፡ ወጸሐፈ ፡ መልእክተ ፡ ወፈነወ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ውእቱኒ ፡ ተወክፎ ፡ ወተፈሥሐ፡ ቦቱ፡ወፈነወ፡ሎቱ፡ስጣዌ፡መልእክቱ።

፴፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከያንኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኮስ፡የሚባል፡ጻድቅ፡ሰው፡ተሾመ፡መልእክ ትንም ፡ ጽፎ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ላከ ፡ እርሱም ፡ ደስ ፡ ተሰኘበት ፡ የመልእክቱንም ፡ መልስ፡ጽፎ፡ላከለት።

፴፫፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለዮሐንስ፡ከሣቲ።ምሥጢረ፡ዕለት፡ዘትመጽእ፡በቅድመ፡ጉባኤ፡አሐቲ።እንዘ፡ ይብል፡ሰዓተ፡ሞትየ፡በእንታክቲ።ወተወለድኩ፡አንሰ፡በዕለት፡ዛቲ።ወበትረያርከ፡ተሠየምኩ፡ባቲ።

፴፬ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ማር ፡ ዳንኤል ፡ ሶርያዊ ፡ ዘሀገረ ፡ ዓምድ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሁ፡ባዕለ፡ወርቅ፡ወብሩር።

፴፭፡ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሁ ፡ ሐፀኖ ፡ አባ ፡ ዲዮናስዮስ፡ጳጳስ፡ዘሀገረ፡ዓምድ፡ለዝንቱ፡ ቅዱስ፡ ወመሀሮ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ወእምዝ ፡ ሤሞ ፡ ዲያቆነ ፡ ወቀ ሲሰ ፡ ወአልበሶ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወነ በረ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ እንዘ ፡ ኢይበልዕ ፡ እምሰንበት፡እስከ፡ሰንበት፡እስከ፡ተውህቦ፡ ሀብተ፡ፈውስ።

፴፮፡ ወእምዝ ፡ በዕዐ ፡ ብዕዓተ ፡ ከመ ፡ ኢይር አይ፡ግሙራ፡ገጸ፡አንስት፡ወሰሚዓ፡እሙ፡ ዜናሁ፡ መጽአት ፡ ኀቤሁ፡ ወፈቀደት ፡ ትር አዮ ፡ ወለአከት ፡ ወይቤላ ፡ ውእቱ ፡ አንሰ ፡ በፃዕኩ ፡ ብፅዓት፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ገጸ ፡ አንስት ፡ ወትቤሎ ፡ ይእቲኒ ፡ አኮኑ ፡ አነ ፡ እምከ ፡ እፎ ፡ ታስተማስለኒ ፡ ከመ ፡ ባዕዳት ፡ አንስት ፡ ወሶበ ፡ አበያ ፡ ቀልዓት ፡ ግልባቢሃ ፡ ወረገመቶ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርእየኒ ፡ ፪ቲ ፡ አንስት ፡ እንዘ ፡ ይኤጽራከ ፡ ወይትቃጸባከ፡ተአጺፎን፡አሐደ፡ልብሰ።

፴፯፡ ወእምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋዕል፡ወሰደ፡ሎቱ፡ አሐዱ፡ብእሲ፡መሐይምን፡ለማር፡ዳንኤል፡ ፫፻ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ፡ በዓቱ ፡ ለማር ፡ ዳንኤል ፡ በጊዜ ፡ ምሴት ፡ ተንሥአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዐርኩ ፡ ዘም ስሌሁ ፡ ወቀተሎ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሠ ፡ ዓምድ ፡ በእንተ ፡ ምውት ፡ አዘዘ ፡ ያብጽሕዎ ፡ ለአባ ፡ ዳንኤል ። ወሰ

፴፬፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ዓምድ ፡ ከሚባል ፡ አገር፡ የሶርያ፡ሰው፡ሊቅ፡ዳንኤል፡አረፈ፡የዚህም፡ ቅዱስ ፡ አባቱ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ ባለጸጋ ፡ የሆነ፡ነው።

፴፭፡ አባቱም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የሀገረ ፡ ዓምድ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ አሳደገው፡የቤተ፡ክርስቲያንንም፡ትምርት፡ አስተማረው፡ከዚህም፡በኋላ፡ዲቁና፡ቅስና፡ ሾመው፡የምንኵስና፡ልብስንም፡አለበሰው፡ ሀብተ፡ፈውስም፡እስከተሰጠው፡ድረስ፡ከሰ ንበት ፡ እስከ ፡ ሰንበት ፡ ሳይበላ ፡ በጾም ፡ በጸ ሎት፡ጸንቶ፡ኖረ።

፴፮፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሴቶችን ፡ ፊት ፡ እንዳያይ፡ ፈጽሞ፡ስዕለት፡አደረገ፡እናቱም፡ወሬውን፡ በሰማች፡ጊዜ፡ወደርሱ፡መጣች፡ታየውም፡ ዘንድ፡ላከችበት፡እርሱም፡የሴቶችን፡ፊት፡ እንዳላይ ፡ ስዕለትን ፡ ተስያለሁ ፡ አላት ። እር ሷም ፡ እኔ ፡ እናትህ፡አይደለሁምን፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ታስመስለኛለህ ፡ አለችው ፡ እምቢ ፡ በአላትም ፡ ጊዜ፡ክንብ ንቧን፡ገልጣ፡ ሁለት፡ሴቶች፡አንድ፡ልብስ፡ ለብሰው ፡ እያዩህ ፡ ሲጠቃቀሱብህ ፡ እግዚአ ብሔር፡ያሳየኝ፡ብላ፡ረገመችው።

፴፯፡ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ምእመን ፡ ሰው፡ለሊቅ፡ዳንኤል፡ሦስት፡መቶ፡የወርቅ፡ ዲናር ፡ ወሰደለት ፡ በማታም ፡ ጊዜ፡ ከሊቅ ፡ ዳንኤል፡ደጃፍ፡ሲደርስ፡ከእርሱ፡ጋር፡ያለ፡ ወዳጁ፡ስለ፡ገንዘብ፡ፍቅር፡በላዩ፡ተነሥቶ፡ ገደለው ። ስለ ፡ ሟቹም ፡ የዓምድ ፡ ንጉሥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ዳንኤልን ፡ ያቀርቡት ፡ ዘንድ፡አዘዘ፡በውሽባ፡ቤት፡ያሉ፡ሁለት፡

www.ethiopianorthodox.org

ሚያን፡ዜና፡ምጽአቱ፡ለአባ፡ዳንኤል፡፫ቲ፡
አንስት ፡ እለ ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ፡ ወእም
ብዝኀ፡ ጕጕዓቶን፡ወጽአ፡ከመ፡ይርአያሁ፡
ተአጺፎን ፡ አሐዱ፡ ልብሰ ፡ ወሠሐቀ ፡ አባ ፡
ዳንኤል፡ሶበ፡በጽሐ፡ላዕሌሁ፡ነገረ፡እሙ።
፴፰፡ ወሶበ ፡ ሐተቶ ፡ ንጉሥ ፡ ለአባ ፡ ዳንኤል ፡
በእንተ ፡ ምውት ፡ ይቤሎ ፡ ለንጉሥ ፡ አንሰ ፡
ኢቀተልክዎ ፡ ዳዕሙ ፡ ለሊሁ ፡ ይትናገር ፡
ዘቀተሎ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ምውት ፡ በጸ
ሎቱ፡ለአባ፡ዳንኤል፡ወተናገረ፡ቀታሌሁ።
ወርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንተ ፡
መንክረ፡ሰገዱ፡ቅድሜሁ፡ለአባ፡ዳንኤል፡
ወሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ዘይገብር፡መን
ክረ፡በላዕለ፡ቀዱሳኒሁ።
፴፱፡ ወእምዝ፡አምጽአ፡ንጉሥ፡ለአባ፡ዳንኤል፡
አምኃ ፡ ብዙኀ ፡ ወርቀ ፡ ውእቱኒ ፡ አበየ ፡
ነሢአ ፡ እምኔሁ ፡ ወንጉሥ ፡ ሐነፀ ፡ ሎቱ፡
ደብረ፡ወተጋብኡ፡ብዙኃን፡መነኰሳት።

፵፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ርሥእ ፡ ሠናይ ፡
ደወየ ፡ ንስቲተ ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወበረ
ከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአ
ብሔር፡አሜን።

ሴቶች ፡ የአባ፡ ዳንኤልን ፡ መምጣት ፡ ወሬ ፡
በሰሙ፡ ጊዜ ፡ ከችኮላቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡
ያዩት፡ዘንድ፡አንድ፡ልብስ፡ለብሰው፡ወጡ፡
አባ፡ዳንኤልም፡እናቱ፡የተናገረችው፡ስለደረ
ሰበት፡ፈገግ፡ብሎ፡ሣቀ።
፴፰፡ ንጉሡም ፡ ስለ ፡ ሞተው ፡ ሰው ፡ አባ ፡ ዳንኤ
ልን ፡ በመረመረው ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አልገደል
ሁትም፡ነገር፡ግን፡የገደለውን፡ራሱ፡ይናገር፡
አለ። በዚያንም፡ጊዜ፡ሟቹ፡በአባ፡ዳንኤል፡
ጸሎት፡ተነሥቶ፡ገዳዩን፡ተናገረ፡ይህንንም፡
ድንቅ ፡ ተአምር ፡ ንጉሡና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
አይተው ፡ በአባ ፡ ዳንኤል ፡ ፊት ፡ ሰገዱ ።
በቅዱሳኑ፡ላይ፡ድንቅ፡ሥራ፡የሚሠራ፡እግ
ዚአብሔርንም፡አመሰገኑት።
፴፱፡ ከዚህም፡በኋላ፡ለአባ፡ዳንኤል፡እጅ፡መንሻ፡
ንጉሡ ፡ ብዙ ፡ ወርቅን ፡ አመጣ ፡ አባ ፡
ዳንኤልም፡ከርሱ፡መቀበልን፡እምቢ፡ባለ፡
ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ገዳምን ፡ ሠራለትና ፡ ብዙ ፡
መነኰሳት፡ተሰበሰቡ።
፵፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ሽምግልናም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ፡
ጥቂት፡ታመመና፡በሰላም፡አረፈ፡በረከቱም፡
ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡
ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

ሰላም ፡ ለዳንኤል ፡ እንተ ፡ በዕዐ ፡ ብፅዓተ ። ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ አንስተ ። አመ ፡ ንጉሠ ፡ ዓምድ ፡ አኀዘ፡
እንዘ ፡ ይሰምዕ ፡ ውዴተ ። ዜና ፡ ቀታሊሁ ፡ ከመ ፡ ይንግር ፡ ክሡተ ።በኃይለ ፡ ጸሎቱ ፡ አንሥአ ፡ ብእሴ ፡
ምውተ ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩
አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡
ኮነ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወክቡራን ፡ መክ
ሲሞስ ፡ ወዱማቴዎስ ፡ ውሉዱ ፡ ለንጉሠ ፡
ሮሜ ፡ ለውንድዮስ ።
፪፡ ወዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ወፈ
ራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ፡
ፍትሐ ፡ ወርትዐ ፡ ወበእንተዝ ፡ ወሀቦ ፡
እግዚአብሔር ፡ እሎንተ ፡ ክልኤተ ፡ ቅዱ
ሳነ ፡ ወእሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ እምንእሶሙ ፡ ከመ ፡
መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በንጽሕና።

፫፡ ወሐፀኖሙ ፡ በትሕትና ወበፈሪሀ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወኮኑ ፡ ዘይጸውሙ ፡ ወይጼልዩ ፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡
ሰባት ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ለለውንድዮስ ፡
ለሮም፡ ንጉሥ ፡ ልጆቹ ፡ የሆኑ ፡ የከበሩና ፡
የተመሰገኑ ፡ መክሲሞስና ፡ ዱማቴዎስ ፡
መታሰቢያቸው ፡ ሆነ ።
፪፡ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ እግዚ
አብሔርንም ፡ የሚፈራ ፡ በእውነትም ፡ የቀና ፡
ፍርድን ፡ የሚፈርድ ፡ ነበር ፡ ስለዚህም ፡
እሊህን ፡ ሁለት ፡ ቅዱሳን ፡ እግዚአብሔር ፡
ሰጠው ፡ እነርሱም ፡ ከታናሽነታቸው ፡ ጀምሮ ፡
በንጽሕና ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡
ሆኑ ።
፫፡ ትሕትናን ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማስ
ተማር ፡ አሳደጋቸው ፡ የሚጾሙና ፡ የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ወያነብቡ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡
መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

፬፡ ወእምዝ፡ መጽአሙ ፡ ሕሊና ፡ ከመ ፡ ይመን
ንዎ ፡ ለዝንቱ፡ ዓለም ፡ ወይልበሱ ፡ አልባሰ ፡
መላእክት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ልብሰ ፡ ምንኵ
ስና ፡ ወአመክነዩ ፡ ለአቡሆሙ ፡ ከመ ፡ ይፈ
ንዎሙ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ኒቅያ ፡ ወይጸልዩ፡
ኀበ፡ ተጋብኡ ፡ አበው ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ ፡ ርቱዓነ፡
ሃይማኖት ።

፭፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ እምኔሆሙ ፡ ተፈ
ሥሐ፡ ጥቀ ፡ ወፈነዎሙ ፡ ምስለ ፡ ብዙኅ፡
አግብርት ፡ ወሠራዊት ፡ ወበጺሖሙ ፡ ሀገረ ፡
ኒቅያ ፡ ተባረኩ ፡ እመካነ ፡ ቅዱስ ፡
ወሜጥዎሙ ፡ ለሠራዊት ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡
አቡሆሙ ፡ ምስለ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡
ዘይብል ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ ንጉሥ ፡ ንፈቅድ ፡
ከመ ፡ ንንበር ፡ ዝየ ፡ ኀዳጠ ፡ መዋዕለ ።

፮፡ ወእምዝ ፡ ከሠቱ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ለ፩ ፡ ጻድቅ ፡
መነኰስ ፡ ወይቤልዎ ፡ ንፈቅድ ፡ ንልበስ ፡
አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ እምኀቤከ ፡ ውእቱኒ ፡
ይቤሎሙ ፡ አንአ ፡ እፈርህ ፡ እምነ፡ ንጉሥ ፡
አቡክሙ ፡ ባሕቱ ፡ ሑሩ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ፡ ሶርያ ፡
እስመ ፡ ሀሎ ፡ ህየ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ መነ
ኰስ ፡ ካህን ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘስሙ ፡
አጋብዮስ ፡ ወሶበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ዘንተ፡
ተወክፉ ፡ ምክሮ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ፡ ሶርያ ፡
ወበጽሑ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ አጋብዮስ ፡ ወከ
ሠቱ፡ ሎቱ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ተወክ
ፎሙ ፡ ወአልበሶሙ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡
ወነበሩ ፡ ኀቤሁ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ አዕረፈ ።

፯፡ ወእምቅድመ ፡ ዕረፍቱ ፡ ነገሮሙ ፡ ዘርእየ ፡
ራእየ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ከመ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
መቃርስ ፡ ዘየዓቢ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ አገዝዞሙ ፡ ለውሉድከ ፡ መክሲሞስ ፡
ወዱማቴዎስ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤየ፡ ኀበ ፡
ገዳመ፡ አስቄጥስ ፡ ወይኩኑኒ ፡ ሊተ ፡ ውሉደ፡
እምቅድመ ፡ ዕረፍትየ ።

፰፡ ወይቤሎሙ ፡ ካዕበ ፡ አ ፡ ውሉድየ ፡ አንሰ ፡
እፈቱ ፡ ኮንኩ ፡ ከመ ፡ እርአዮ ፡ ለዝንቱ ፡
አባ፡ መቃርስ ፡ በሥጋሁ ፡ ወናሁ ፡ ርኢክዎ ፡

ጸልዩ ፡ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ የብሉይና ፡
የሐዲስ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ የሚያነቡ ፡ ሆኑ ።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ይተዉት ፡
ዘንድ የመላእክትንም ፡ ልብስ ፡ ይለብሱ ፡
ዘንድ ፡ እርሷም ፡ የከበረች ፡ የምንኵስና ፡
ልብስ ፡ ናት ፡ ከዚያም ፡ ኀሳብ ፡ መጣባቸው ፡
ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡
ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ አባቶች ፡ ወደ ፡ ተሰበሰ
ቡባት ፡ ወደ ፡ ኒቅያ ፡ ሂደው ፡ ይጸልዩ ፡
ዘንድ ፡ እንዲአሰናብታቸው ፡ ለአባታቸው ፡
ምክንያት አቀረቡ ።

፭፡ ይህንንም ፡ ከርሳቸው ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡
ደስ ፡ አለው ፡ ከብዙ ፡ አገልጋዮችና ፡ ከብዙ ፡
ሠራዊት ፡ ጋር ፡ አሰናበታቸው ፡ ከኒቅያ ፡
አገርም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ከከበረ ፡ ቦታ ፡
በረከትን ፡ ተቀበሉ ፡ ሠራዊቱንም ፡ ወደ ፡
ንጉሥ ፡ አባታቸው ፡ ጌታችን ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ፡
እኛ ፡ ከዚህ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ መቆየት ፡
እንሻለን ፡ ከሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ጽፈው ፡
ላኩ ።

፮፡ ከዚህም በኋላ ፡ ለአንድ ፡ ጻድቅ ፡ መነኰስ ፡
ኀሳባቸውን ፡ ገለጡ ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፡
ከአንተ ፡ ዘንድ ፡የምንኵስናን ፡ ልብስ፡
እንድንለብስ ፡ እንሻለን ፡ እርሱም ፡ እኔ ፡
ከንጉሥ ፡ አባታችሁ ፡ የተነሣ ፡ እፈራለሁ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሒዱ ፡ ስሙ ፡
አጋብዮስ ፡ የሚባል ፡ ከዚያ ፡ ሃይማኖቱ ፡
የቀና ፡ ካህን ፡ ደግ ፡ መነኰስ ፡ አለ ፡ አላቸው፡
ይህንንም ፡ ሲላቸው ፡ ምክሩን ፡ ተቀብለው ፡
ወደ ፡ ሶርያ ፡ ተጉዘው፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
አጋብዮስ ፡ ደርሰው ፡ ኀሳባቸውን ፡ ገለጡለት ፡
እርሱም ፡ ተቀብሎ ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡
አለበሳቸው ፡ እስከሚአርፍበትም ፡ ቀን ፡ ከእ
ርሱ ፡ ዘንድ ፡ኖሩ ።

፯፡ ከዕረፍቱም ፡ አስቀድሞ ፡ ያየውን ፡ ራእይ፡
ነገራቸው ፡ ታላቁ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወደርሱ፡
እንደመጣና ፡ ልጆችህ ፡ መክሲሞስና ፡ ዱማ
ቴዎስ ፡ ለኔ ፡ ልጆቼ ፡ ይሆኑኝ፡ ዘንድ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ እንዲመጡ ፡
ከመሞቴ ፡ በፊት ፡ እዘዛቸው ፡ አለው ።

፰፡ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ልጆቼ ፡ እኔ ፡
ይህን ፡ ሰው ፡ አባ ፡ መቃርስን ፡ በሥጋው ፡
አየው ፡ ዘንድ ፡ እመኝ ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡

በመንፈስ ፡ ወአንትሙ ፡ እምድኅረ ፡ ዕረፍ
ትየ፡ሑሩ፡ኀቤሁ።

፱፡ ወእምድኅረ ፡ አዕረፈ ፡ ኢሐሩ ፡ አላ ፡ ነበሩ ፡
በህየ ፡ ብሔረ ፡ ሶርያ ፡ ወወሀቦሙ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ጸጋ ፡ ፈውስ ፡ ወኮኑ ፡ ዘይፌው
ስዎሙ ፡ ለድውያን ፡ ወተሰምዐ ፡ ዜናሆሙ ፡
ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ወእምነጋድያን ፡
እለ ፡ የሐውሩ ፡ በባሕር ፡ ወበየብስ ፡ ተምህሩ ፡
ገቢረ ፡ ተድባባተ ፡ ሐመር ፡ ወኮኑ ፡ ዘይሴሰዩ ፡
እምፃማ ፡ እደዊሆሙ ፡ በበንስቲት ፡ ወዘተ
ርፈ ፡ ይሁብዎሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ።

፲፡ ወእምብዝኀ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡
ዘይገብር ፡ እግዚአብሔር ፡በእደዊሆሙ ፡ ኮኑ ፡
ብዙኃን ፡ መናፍስት ፡ ርኵሳን ፡ ሶበ ፡ ይሰ
ምዑ ፡ ስሞሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ መክሲሞስ ፡
ወዱማቴዎስ ፡ ይወጽኡ ፡ እምሰብእ ፡ ወይጐ
ይዩ ፡ ወእሙንቱ ፡ ይትፌወሱ ፡ ሶቤሃ፡
ወይጥዕዩ ፡ በኃይለ ፡ እግዚእ ።

፲፩፡ ወሀሎ ፡ ከይሲ ፡ ዐቢይ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይነብር፡
በጥቃ ፡ ፍኖት ፡ ወአጥፍአ ፡ ብዙኃነ ፡ ሰብአ ፡
ወመጽኡ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ኀበ ፡ ቅዱሳን ፡
መክሲሞስ ፡ ወዱማቴዎስ ፡ ወሰአልዎሙ ፡
ከመ ፡ ያድኅንዎሙ ፡ እምውእቱ ፡ ከይሲ ፡
ወነሥአ ፡ አባ ፡ መክሲሞስ ፡ ክርታሰ ፡
ወጸሐፈ ፡ ከመዝ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው ፡ አምላኩ ፡ ለመቃርዮስ ፡ ብፁዕ ፡
ወለአቡነ ፡ ክቡር ፡ አጋብዮስ ፡ ለባሴ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሶበ ፡ ይበጽሕ ፡ ዝንቱ ፡
ክርታስ ፡ ኀበ ፡ ጥኅተ ፡ በዓትከ ፡ ትጻእ ፡
አንተ ፡ ወትሙት ፡ ወይብልዑከ ፡ አዕዋፈ ፡
ሰማይ ።

፲፪፡ ወነሥአ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ለይእቲ ፡ ክርታስ ፡
ወሖረ ፡ ወአንበራ ፡ ኀበ ፡ ጥኅተ ፡ በዓቱ ፡
ለውእቱ ፡ ከይሲ ፡ ወሶቤሃ ፡ ወጽአ ፡ ወሞተ ፡
ወበልዕዎ ፡ አእዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወአንከሩ ፡
ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ወብዙኀ ፡ ተአምራተ ፡
ወመንክራተ ፡ ገብረ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡
መክሲሞስ፡ ወዱማቴዎስ ።

በመንፈስ ፡ አየሁት ፡ እናንተም ፡ ከሞትኩ ፡
በኋላ ፡ ወደርሱ ፡ ሒዱ ።

፱፡ ከዐረፈም ፡ በኋላ ፡ አልሔዱም ፡ በዚያ ፡
በሶርያ ፡ አገር ፡ ኖሩ ፡ እንጂ ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ሀብተ ፡ ፈውስ ፡ ሰጥቷቸው ፡ በሽ
ተኞችን ፡ የሚፈውሱ ፡ ሆኑ ፡ ወሬያቸውም ፡
በሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተሰማ ፡ በባሕርና ፡ በየብስ ፡
ከሚነግዱ ፡ ነጋድያንም ፡ የመርከብ ፡ መዛነ
ቢያዎችን ፡ መሥራት ፡ ተምረው ፡ ከድካም ፡
ዋጋቸው ፡ በየጥቂቱ ፡ የሚመገቡና ፡ የተረ
ፈውን ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ የሚሰጡ ፡
ሆኑ ።

፲፡ እግዚአብሔርም ፡ በእጆቻቸው ፡ ከሚሠ
ራቸው ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶች ፡ የተነሣ ፡
የቅዱሳን ፡ መክሲሞስንና ፡ ዱማቴዎስን ፡
ስም ፡ መናፍስት ፡ ርኵሳን ፡ በሚሰሙ ፡ ጊዜ ፡
ከሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ይሸሻሉ ፡ ሰዎቹም ፡
ያን፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ኃይል ፡ ይድናሉ ፡ ጤነ
ኞችም ፡ ይሆናሉ ።

፲፩፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ በጐዳና ፡ አጠገብ ፡
የሚኖር ፡ ከይሲ ፡ ነበር ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች
ንም ፡ አጥፍቷል ፡ የአገር ፡ ሰዎችም ፡ ወደ
ከበሩ ፡ መክሲሞስና ፡ ዱማቴዎስ ፡ መጥ
ተው ፡ ከዚያ ፡ ከይሲ ፡ ያድኗቸው ፡ ዘንድ ፡
ለመኗቸው ፡ አባ ፡ መክሲሞስም ፡ ክርታስ ፡
አንሥቶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ፡ የብፁዕ ፡
መቃርዮስ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስንም ፡ በለበሰ ፡ በአባታችን፡ በአጋ
ብዮስ ፡ አምላክ ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡
አካላዊ ፡ ቃል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ስም ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ከዋሻህ ፡
ደጅ ፡ ሲደርስ ፡ አንተ ፡ ወጥተህ ፡ ሙት ፡
የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ይብሉህ ።

፲፪፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ያቺን ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀብሎ ፡
ሔደ ፡ በዚያም ፡ የዘንዶ ፡ ዋሻ ፡ ደጃፍ ፡
አኖራት ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ዘንዶው ፡
ወጥቶ ፡ ሞተ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ በሉት ፡
ሕዝቦችም ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡
እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑት ፡ የክብር ፡
ባለቤት ፡ ጌታችንም ፡ በእሊህ ፡ ቅዱሳን ፡
በመክሲሞስና ፡ በዱማቴዎስ ፡ እጆች ፡
ብዙ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አደረገ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ወጽአ ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ ፡
እመኳንንቲሁ ፡ ለአቡሆሙ ፡ ኀበ ፡ ጽንፈ ፡
ባሕር ፡ ወርእዮ ፡ ዲበ ፡ ተድባበ ፡ ፩ሐመር ፡
እምአሕማራት ፡ ጽሑፈ ፡ ዘይብል ፡ መክሲ
ሞስ ፡ ወዱማቴዎስ ፡ ተስአሎ ፡ ለሊቀ ፡
ሐመር ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወይቤሎ፡ ውእቱ ፡
ጸሐፍኩ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ፪ቱ ፡
አኃው ፡ ቅዱሳን ፡ መነኰሳት ፡ ከመ ፡
ያድኅነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምተሠጥሞ ፡
በጸሎቶሙ ፡ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ ምንተ ፡
ይመስል ፡ አርአያሆሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ነገሮ ፡
ትእምርተ ፡ አርአያሆሙ ፡ ወአእመረ ፡ ከመ ፡
እሙንቱ ፡ ደቂቁ ፡ ለንጉሥ ፡ ወአኀዞ ፡ ለው
እቱ ፡ ነጋዲ ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ፡
አቡሆሙ ፡፡

፲፬፤ ንጉሥኒ፡ ተሰአሎ፡ ለነጋዲ፡ ወአጠየቆ፡ ነጋዲ፡
አምሳሊሆሙ ፡ ወጠየቀ፡ ንጉሥ ፡ ከመ፡
እሙንቱ ፡ ደቂቁ ፡ ወፈነዎን ፡ ለእሞሙ ፡
ወለእኅቶሙ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ምስለ ፡ ብዙኅ ፡
ሠራዊት ፡ ወበጺሖን ፡ ርእያሆሙ ፡ ወከ
ልሓ ፡ ወበክያ ፡ ወተአምኃሆሙ ፡ ወሰአ
ለቶሙ ፡ እሞሙ ፡ ከመ ፡ ይምጽኡ ፡ ምስሌሃ ፡
ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ አቡሆሙ ፡፡ ወእሙንቱ ፡
ይቤልዋ ፡ ለነሰ ፡ ኢይትከሀለነ፡ ናማስን ፡
ኪዳነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ በዓዕነ
ርእሰነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወባሕቱ ፡ ሑሪ ፡
ወንሕነ ፡ ንጼሊ ፡ ለኪ ፡ ወለአቡነ ፡ ከመ ፡
ያድኅንክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኵሉ ፡
መከራ ፡ ወናዘዝዋ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ፡
ወኀደገቶሙ ፡ ወተመይጠት ፡ እንዘ ፡
ተኃዝን ፡ ወትቴክዝ ፡ በእንተ ፡ተፈልጦታ።

፲፭፤ ወሶበ ፡ በጽሐት፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ነገረቶ ፡
ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ ለብ
እሲቱ ፡ ወለአግብርቲሁ፡ ንኅድጎሙ ፡ ከመ ፡
ይኩኑ ፡ ለነ ፡ መዝገበ ፡ ሕይወት ፡ ኀበ ፡
እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ወይበ
ቍዓነ ፡ ጸሎቶሙ ፡ እስመ፡ ኵሉ ፡ ክብር ፡
ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ሕልም ፡
ኃላፊ ፡ እሙንቱሰ ፡ ረብሑ ፡ መንግሥተ ፡
ዘኢየኀልፍ ፡፡

፲፮፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ አዕረፈ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ ዘብሔረ ፡ ሮሜ ፡ ወተጋብኡ ፡ ኤጲስ
ቆጶሳት ፡ ጳጳሳትሂ ፡ ከመ ፡ ይትማከሩ፡ ዘይ

፲፫፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ከአባታቸው ፡
መኳንንቶች ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡
ደረሰ ፡ ከመርከቦችም ፡ በአንዱ ፡ መርከብ ፡
መዛነቢያ ፡ ላይ ፡ መክሲሞስና ፡ ዱማቴ
ዎስ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡
የመርከቡን ፡ ሹም ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም ፡
እንዲህ ፡ አለው ፡ በጸሎታቸው ፡ ከሥጥ
መት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡
የእሊህን ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ የከበሩ
መነኰሳት ፡ ስማቸውን ፡ በመርከቤ፡ ላይ ፡
ጻፍኩ ፡ መኰንኑም ፡ መልካቸው ፡ ምን ፡
ይመስላል ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ የመልካ
ቸውን ፡ ምልክት ፡ ነገረው ፡ የንጉሡ ፡
ልጆች ፡ እንደሆኑ ፡ አውቆ ፡ ያን ፡ ነጋዴ ፡
ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አባታቸው ፡ አደረሰው ፡፡

፲፬፤ ንጉሡም ፡ ጠየቀው ፡ ነጋዴውም ፡ የመልካ
ቸውን ፡ አምሳል ፡ አስረዳው ፡ ንጉሡም ፡
ልጆቹ ፡ እንደሆኑ ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ እናታ
ቸውንና ፡ እኅታቸውን ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡
ጋር ፡ ወደነርሱ ፡ ላከ ፡ ደርሰውም፡ በአዩ
አቸው ፡ ጊዜ ፡ ጩኸው ፡ አለቀሱ ፡ እናታ
ቸውም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አባታቸው ፡
ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ፡ ለመነ
ቻቸው ፡፡ እነርሱም ፡ ራሳችንን፡ ስዕለት ፡
አድርገን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥተናልና ፡
ቃል ፡ ኪዳናችንን ፡ ማፍረስ ፡ አይቻለንም ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ሒጂ ፡ ለአንቺም ፡ ለአባታ
ችንም ፡ ከመከራ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያድናችሁ ፡ ዘንድ ፡ እንጸልይላችኋለን ፡
በዚህም ፡ እነጋገር ፡ አረጋኋት ፡ በመለ
የቷም ፡ ፈጽማ ፡ እያዘነች ፡ ተመለሰች ፡፡

፲፭፤ ወደ ፡ ንጉሥም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሱ ፡
የሆነውን ፡ ነገረችው ፡ ንጉሡም ፡ ለሚስቱና፡
ለባለሟሎቹ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በእግዚአብ
ሔር፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ የሕይ
ወት ፡ ድልብ ፡ ይሆኑን ፡ ዘንድ ፡ እንተ
ዋቸው ፡ ጸሎታቸውም ፡ ይጠቅመናል ፡ በዓ
ለም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡
ሕልም ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነውና ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡
የማያልፍ ፡ መንግሥትን ፡ አተረፉ።

፲፮፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የሮሜ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት ፡ አረፈ ፡ ስለሚሾሙትም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ ይማከሩ ፡ ዘንድ ፡ ኤጲስቆጶሳት፡ ጳጳ

www.ethiopianorthodox.org

ሠይሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወተዘከርዎ ፡ ለብ
ፁዕ ፡ መክሲሞስ ፡ ወተበሀሉ ፡ ኵሎሙ፡
በአማን ፡ ይደሉ ፡ ውእቱ ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት።
እስመ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ዐቢየ ፡
ከመ ፡ ይፈውስ ፡ ዱያነ ፡ ወይግበር ፡ ተአ
ምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወለእ
መኒ ፡ ኮነ ፡ ወሬዛ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ እስመ ፡
ክርስቶስ ፡ ኀደረ ፡ ውስቴቱ ፡ ወውእቱ ፡
ፍጹም ፡ በአእምሮ ፡ ወበምግባር ፡ ሠናይ ፡
ወበኵሉ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን።

፲፪፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ተፈሥሐ ፡ አቡሁ ፡
ወእሙ ፡ ወፈነዉ ፡ መኳንንተ ፡ ወምስ
ሌሆሙ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ መኰ
ንነ ፡ ሀገር ፡ ዘሶርያ ፡ ከመ ፡ ይፈንዎሙ ፡
ኀበ ፡ ሮሜ ፡ ለቅዱሳን ፡ መክሲሞስ ፡
ወዱማቴዎስ ። ወሰሚያሙ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡
ኀዘኑ ፡ ጥቀ ፡ ወተዘከሩ ፡ ዘአዘዘሙ፡ አቡ
ሆሙ ፡ አባ ፡ አጋብዮስ ፡ ወተንሥኡ ፡ ሶቤሃ ፡
ወወለጡ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወአንሶሰዉ ፡ ኀበ፡
ጽንፈ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወኢየአምሩ ፡ ኀበ፡
የሐውሩ ፡ ወሶበ ፡ ይጸምዑ ፡ ማየ ፡ ይዌልጥ ፡
ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሪረ ፡ ማየ ፡ ወይ
ሬስዮ ፡ ጥዑመ ፡ ወይሰትዩ ። ወእምዝ ፡
ፈነወ ፡ ሎሙ ፡ እምኀቤሁ ፡ ኃይለ ፡ ወያ
ረቶሙ ፡ እምብሔረ ፡ ሶርያ ፡ ወአብጽ
ሖቶሙ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወበ
ዊአሙ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ነገርዎ ፡
ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይፈቅዱ ፡ ኀቤሁ ፡ ይን
በሩ ።

፲፫፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡
ጸጋ ፡ መሰሎ ፡ ከመ ፡ ኢይክሉ ፡ ነቢረ ፡
ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወነገሮሙ ፡ ዕፅብና ፡ ዘገ
ዳም፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢትክሉ ፡ ነቢረ ፡ ዝየ፡
ወአውሥእዎ ፡ ወይቤልዎ ፡ አ ፡ አቡነ፡
ኀድገነ ፡ ለእመ ፡ ኢክህልነ ፡ ነቢረ ፡ ዝየ ፡
ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ነሐውር ።

፲፬፡ ወእምዝ ፡ መሀሮሙ ፡ ጸፊረ ፡ ሆሣዕና ፡
ወአርአዮሙ ፡ ፈለገ ፡ ዘይነሥኡ ፡ እምኔሁ ፡
ሆሣዕና ፡ ወረድአሙ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ሐነፁ ፡
ማኅደረ ፡ ወአምጽአ ፡ ሎሙ ፡ ፩ደ ፡ ብእሴ ፡
ሕዝባዌ ፡ ዘይሠይጥ ፡ ሎሙ ፡ ግብረ ፡ እደዊ
ሆሙ ፡ ወያመጽእ ፡ ሎሙ ፡ሲሳዮሙ ። ወነ
በሩ ፡ ከመዝ ፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ፡

ሳትም ፡ ተሰበሰቡ ፡ የከበረ ፡ መክሲሞስንም ፡
አሰቡትና ፡ ሁሉም ፡ ለዚች ፡ ሹመት ፡ እርሱ ፡
በእውነት ፡ ይገባል ፡ ተባባሉ ። በሽተኞችን ፡
ይፈውስ ፡ ዘንድ ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች፡
ተአምራቶችንም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ሰጥቶታልና ፡ በዕድ
ሜውም ፡ ወጣት ፡ ቢሆን ፡ ክርስቶስ ፡ በው
ስጡ ፡ ስለአደረ ፡ በዕውቀትና ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡
ሁሉ፡ፍጹም፡ነው።

፲፪፡ ይህንንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አባቱና ፡ እናቱ፡
ደስ ፡ አላቸው ፡ መኳንንቶችንም፡ ላኩ፡ የከ
በሩ ፡ መክሲሞስንና ፡ ዱማቴዎስን፡ ወደ ፡
ሮሜ ፡ ይሰዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡
አገረ ፡ ገዥ ፡ ደብዳቤ ፡ አብረው ፡ ላኩ ።
እሊህም ፡ ቅዱሳን ፡ ሰምተው ፡ እጅግ ፡
አዘኑ ፡ አባታቸው ፡ አባ ፡ አጋብዮስም ፡
ያዘዛቸውን ፡ አሰቡ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡
ተነሡ ፡ ልብሳቸውንም ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡
ኤርትራ ፡ ባሕር፡ ዳርቻ ፡ ተጓዙ ፡ ወደየ
ትም ፡ እንደሚጓዙ ፡ አያውቁም ፡ ውኃን ፡
በሚጠሙ ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ መራ
ራውን ፡ ውኃ ፡ ለውጦ ፡ ጣፋጭ ፡ አድርጎ
ላቸው ፡ ይጠጣሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእ
ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ረድኤትን ፡ ኃይልን ፡ ላከላ
ቸውና ፡ ከሶርያ፡ አገርም፡ ተሸክማ ፡ ወደ ፡
አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ አደረሰቻቸው ፡ ወደ፡
አባ ፡ መቃርስም ፡ ገብተው ፡ በእርሱ ፡
ዘንድ ፡ መኖርን ፡ እንደሚሹ ፡ ነገሩት ።

፲፫፡ እነርሱም ፡ በጸጋ ፡ የለመለሙ ፡ እንደሆኑ፡
በአየ ፡ ጊዜ ፡ በገዳም ፡ መኖርን ፡ የማይችሉ
መሰለው ፡ በገዳም ፡ ያለውን፡ ችግር ፡ ነገ
ራቸውና ፡ በዚህ ፡ መኖር ፡ አትችሉም ፡ አላ
ቸው ፡ እነርሱም ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ተወን፡
ከዚህ ፡ መኖር ፡ ካልተቻለን ፡ እንሔዳለን ፡
ብለው ፡ መለሱለት ።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰሌን ፡ መሥራትን ፡ አስ
ተማራቸው ፡ ሰሌንም ፡ የሚቆርጡበትን ፡
ወንዝ ፡ አሳያቸው ፡ ማደሪያቸውንም ፡ እስ
ከሚሠሩ ፡ ድረስ ፡ ረዳቸው ፡ የእጅ ፡ ሥራ
ቸውንም ፡ የሚሸጥና ፡ ምግባቸውን ፡ የሚያ
መጣላቸውን ፡ አንድ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሰው ፡
አምጥቶ፡ አገናኛቸው። እንዲህም፡ ሁነው፡

www.ethiopianorthodox.org

፫ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ኢይትራከቡ ፡ ምስለ ፡
ሰብእ ፡ ግሙራ ፡ አላ ፡ ባሕቲ፡ ኮኑ ፡ ዘይ
በውኡ ፡ በጽሙና ፡ ወበአርምሞ ፡ ወይነ
ሥኡ ፡ ምሥጢረ ፡ ቅድሳት ፡ ወይትመየጡ ፡
ኀበ ፡ ማኀደሪሆሙ ። ወአንከረ ፡ ቅዱስ ፡
መቃርስ ፡ አቡሆሙ፡ እምግብሮሙ፡በእንተ፡
ዘኢመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢሐወጽዎ ፡ አም
ጣነ ፡ ሠለስቱ ፡ ዓመት ፡ ወሰአለ፡ ኀበ ፡
እግዚእነ ፡ ይክሥት ፡ ሎቱ ፡ ግብሮሙ፡ ወተ
ንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወእሙንቱ፡ ተፈ
ሥሑ ፡ ቦቱ ፡ ወኀደረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይእተ ፡
ሌሊተ ፡ ወሶበ ፡ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ፡ ርእ
ዮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ መክሲሞስ ፡ ወዱማቴ
ዎስ ፡ ከመ ፡ ሐብለ ፡ እሳት ፡ የዐርግ ፡ እም
አፉሆሙ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወሰይጣናት ፡ የዓ
ውድዎ ፡ ከመ ፡ ጽንጽንያት ፡ ወመልአከ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይሰድዶሙ፡ በሰይፈ፡ እሳት።
ወሶበ ፡ ጸብሐ ፡ አልበሶሙ ፡ አስኬማ፡ ወሖረ፡
እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡ ጸልዩ፡ ሊተ፡
ወእሙንቱ ፡ ሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ወይቤሉ ፡ አ ፡
አቡነ ፡ መፍትው ፡ አንተ ፡ ትጸሊ ፡ ላዕሌነ ፡
ወትባርከነ ።

፳፤ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ገድሎሙ ፡ ፈቀደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያዕርፎሙ ፡ እምፃማ ፡
ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወሐመ ፡ መክሲሞስ ፡ በሕ
ማም ፡ ጽኑዕ ፡ ወኮነ ፡ ሥጋሁ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡
ወፈነወ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ከመ ፡ይምጻእ፡
ኀቤሁ ፡ ወበጺሐ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ረከቦ ፡
እንዘ ፡ ይደዊ ፡ ወይቤሎ ፡ መክሲሞስ ፡ ጸሊ ፡
ላዕሌየ ፡ ወባርከኒ ፡ ውእቱኒ ፡ ባረከ ፡ ላዕሌሁ ።
ወይቤሎ ፡ ኢትፍራህ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ደዌ ፡
ይትአተት፡ እምኔከ ፡ ወይቤሎ ፡ መክሲሞስ ፡
አ ፡ አቡየ፡ አነ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ በዛቲ ፡ ደዌ ፡
እፈልስ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወአንተ ፡ ጸሊ ፡
ላዕሌየ፡ ከመ ፡ እርከብ ፡ ረድኤተ ።

፳፩፤ ወሶበ ፡ ይቤ ፡ ዘንተ ፡ በከየ ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡
ወበይእቲ ፡ ጊዜ ፡ ርእዮሙ ፡ አባ፡ መቃርስ፡
ለማኀበረ ፡ ቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ ወሐዋርያት፡
ወዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ወቈስጠንጢኖስ ፡
ንጉሥ፡ ወእሙንቱ፡ የዓውድዎ፡ ለአባ፡ መክ

ከቶ ፡ ከሰው ፡ ሳይገናኙ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡
ኖሩ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በጭልታና ፡ በዝምታ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገቡና ፡
ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡
ማደሪያቸው ፡ የሚመለሱ ፡ ሆኑ ። ሦስት፡
ዓመት ፡ ያህል ፡ ወደርሱ ፡ ስለአልመጡና ፡
ስለአልጎበኙት ፡ አባታቸው ፡ አባ ፡ መቃ
ርስ ፡ ከሥራቸው ፡ የተነሣ ፡ አደነቀ ፡ ሥራ
ቸውንም ፡ ይገልጥለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌታ
ችን ፡ ለመነና ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ርሳቸው ፡
ሔደ ፡ እነርሱም ፡ በመምጣቱ ፡ ደስ ፡ ተሰ
ኙበት ፡ በዚያች ፡ ሌሊትም ፡ ከርሳቸው ፡
ጋር ፡ አደረ ። ለጸሎትም ፡ በተነሡ፡ ጊዜ ፡
የእሳት፡ ሐብል ፡ ከአፋቸው ፡ ሲወጣና ፡
ወደ፡ ሰማይ፡ ሲደርስ፡ ሰይጣናትም፡ እንደ፡
ዝንቦች፡ ሲከቡት፡ የእግዚአብሔርም፡ መል
አክ፡በእሳት ፡ ሰይፍ፡ ዝንቦቹን ፡ ሲያበር
ራቸው፡ የከበሩ ፡ መክሲሞስንና ፡ ዱማቴ
ዎስን ፡ አያቸው ፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ አስ
ኬማን ፡ ለብሳቸው፡ ጸልዩልኝ፡ ብሏቸ
ውም፡ ሊሔድ፡ ተነሣ ። እነርሱም ፡ ሰገዱ
ለትና ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ በእኛ ፡
ላይ ፡ ትጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ትባርከንም ፡ ዘንድ ፡
የሚገባ ፡ ነው ፡ አሉት።

፳፤ ተጋድሎአቸውንም ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ ሊአ
ሳርፋቸው ፡ ወደደ ፡ መክሲሞስም ፡ በጽኑ ፡
ሕመም ፡ ታመመ ፡ ሥጋውም ፡ እንደ፡ እሳት፡
ጋለ ፡ ወደርሱም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
አባ ፡ መቃርስ ፡ ላከ ። አባ ፡ መቃርስም ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በደዌ ፡ ሲሠቃይ ፡ አገኘው ፡
መክሲሞስም፡ ጸልይልኝ፡ ባርከኝም፡ አለው።
እርሱም ፡ በላዩ ፡ አማትቦ ፡ ይህ ፡ ደዌ ፡
ከአንተ ፡ ይርቃልና ፡ አይዞህ ፡ አለው ፡ መክ
ሲሞስም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በዚች ፡ ደዌ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደምወጣ ፡ እኔ ፡ አውቃ
ለሁ ፡ ረድኤት ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡
ጸልይልኝ ፡ አለው ።

፳፩፤ ይህንንም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ መሪር ፡
ልቅሶን ፡ አለቀሰ ፡ በዚያችም ፡ ጊዜ ፡ አባ፡
መቃርስ ፡ የቅዱሳንን ፡ አንድነት ፡ ነቢያ
ትን ፡ ሐዋርያትን ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስን ፡
ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስንም ፡ አያቸው ። እነ

www.ethiopianorthodox.org

ሲ.ሞስ ፡ ብፁዕ ፡ እስከ ፡ ወጽአት፡ ነፍሱ፡ በክብር ። ወበከየ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወይቤ፡ ብፁዕ፡ አንተ ፡ መክሲ.ሞስ ፡ እኍሁሰ ፡ ዱማ ቴዎስ ፡ ኮነ ፡ ዘይበኪ ፡ ላዕለ፡ እኍሁ ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡ ወይስእሎ ፡ ለአባ፡ መቃርስ፡ ወይ ብሎ ፡ ሰአል ፡ በእንቲአየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከመ ፡ ይንሥእ ፡ ለነፍስየ፡ ወያብ ጽሓ፡ ኀበ፡ እኍየ ።

፳፱፤ ወእምድኅረ ፡ ተቀብረ ፡ አባ ፡ መክሲ.ሞስ ፡ በ፫ቱ ፡ ዕለት ፡ ሐመ ፡ አባ ፡ ዱማቴዎስ ፡ ወነገርዎ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ በእ ንቲአሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ተንሥአ ፡ ከመ ፡ ይሑር፡ ኀቤሁ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ በፍኖት ፡ ርእዮሙ ፡ ለማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ቀዳሚ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ መክሲ.ሞስ ፡ ወነሥኡ ፡ ነፍሶ ፡ ለዱማቴዎስ ፡ ወአዕረግዋ፡ በክብር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ወበጺ.ሖ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ውስተ ፡ በዓቶሙ ፡ ረከቦ ፡ ለዱማቴዎስ ፡ በዘአዕረፈ ፡ ወነሥኦ ፡ ወቀበሮ ፡ በክብር ፡ ምስለ ፡ እኍሁ መክሲ.ሞስ ፡ በ፩ መቃብር ። ወዕረፍቱ ፡ ለመ ክሲ.ሞስ ፡ አመ ፡ ፲ ወ ፬ ለዝ ፡ ወርኀ ፡ ወዕ ረፍቱ ፡ ካዕበ ፡ ለዱማቴዎስ ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ።

፳፫፤ ወአዘዘ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ከመ ፡ ይሰመይ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ፡ በስሞሙ ፡ ወከ ማሁ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ ተሰምየ ፡ ደብረ ፡ በርሞስ ፡ ወኮነ ፡ ሎሙ ፡ ተዝካረ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

፳፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ መክ ሲ.ሞስ ፡ ወዱማቴዎስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ርሱም ፡ ነፍሱ ፡ በክብር ፡ እስከወጣች ፡ ድረስ ፡ በአባ ፡ መክሲ.ሞስ፡ ዙሪያ ፡ ነበሩ ። አባ ፡ መቃርስም ፡ አልቅሶ ፡ መክሲ.ሞስ ፡ ሆይ ፡ የተመሰገንክ ፡ የከበርክ፡ ነህ ፡ አለ ። ዱማቴዎስም ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ በማልቀስ ፡ አባ ፡ መቃርስን ፡ የሚ ለምነው ፡ ሆነ ፡ ነፍሴን ፡ ይወስዳትና ፡ ወደ ፡ ወንድሜም ፡ ያደርሳት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ጸልይ ፡ አለው ።

፳፱፤ አባ ፡ መክሲ.ሞስም ፡ ከተቀበረ ፡ በኋላ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አባ ፡ ዱማቴዎስ፡ ታመመ፡ ስለርሱም ፡ ለአባ ፡ መቃርስ ፡ ነገሩት ፡ አባ ፡ መቃርስም ፡ ወደርሱ ፡ ሊሔድ ፡ ተነሣ ፡ በጉዞ ፡ ላይም ፡ ሳለ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ አባ፡ መክሲ.ሞስ ፡ የመ ጡትን ፡ የቅዱሳን ፡ አንድነት ፡ አየ ፡ የአባ ፡ ዱማቴዎስንም ፡ ነፍስ ፡ ተቀብለው ፡ በክ ብር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሳረጓት ። አባ ፡ መቃ ርስም ፡ ወደ ፡ በዓታቸው ሲ.ደርስ ዱማቴዎስን አርፎ አገኘው ወስዶም ከወንድሙ ከመክ ሲ.ሞስ ፡ ጋር፡ በአንድ ፡ መቃብር ፡ በክብር ፡ ቀበረው ። የመክሲ.ሞስም ፡ ዕረፍት ፡ በዚ.ህ፡ ወር፡ በዐሥራ ፡ አራት ፡ ነው ፡ ዳግመኛ ፡ የዱማቴዎስ ፡ ዕረፍት ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ በዚ.ች ፡ ቀን ፡ ነው ።

፳፫፤ የከበረ ፡ አባ ፡ መቃርስም ፡ ያ ፡ ቦታ ፡ በስማቸው ፡ እንዲ.ጠራ ፡ አዘዘ ፡ እንዲ.ሁም ፡ ደብረ ፡ በርሞስ ፡ ተብሎ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የሚ.ጠራ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለሙም ፡ መታሰቢ ያቸው ፡ ሆነ።

፳፬፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በከበሩ ፡ መክሲ.ሞስና ፡ ዱማቴ ዎስ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

**አርኬ**

ሰላም ፡ ለዱማቴዎስ ፡ ዘዓጽፈ ፡ ትጉሐን ፡ ዐጽፉ። እኀወ ፡ መክሲ.ሞስ፡ በሥጋ ፡ ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ሱታፉ ። ሠራዊተ ፡ ሰይጣን ፡ ቀሪበ ፡ ዘኢ.ክህሉ ፡ ዐውደ ፡ ምዕራፉ ። ቦ ፡ መልአክ ፡ ዘይጼልሎ ፡ በክንፉ። ወቦ፡ መልአክ ፡ ዘይሰድዶሙ ፡ በሰይፉ ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፰ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ውዕየተ ፡ ዓፅሙ ፡ ወዝርወቱ ፡ ለቅዱስ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ በዚ.ች ፡ ቀን ፡ የሰማዕታት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ፡ ሊቀ፡ ሰማዕታት፡ በረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

አለቃ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዐፅሙ፡ ተቃጥሎ ፡ ተደቁሶ ፡ የተበተነበት ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ ለዘላ ለሙ ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ውዕየተ ፡ ዐፅምከ ፡ በነድ ። እንዘ ፡ ታዜምር ፡ጊዮርጊስ ፡ ሃይማኖተከ ፡ በዐውድ ። እንበለ ፡ ወልጦ ፡ ሀበኒ ፡ በረከተከ ፡ ዘልማድ ። ዕብነኑ ፡ ይሁቦ ፡ በእድ ። ኀበ ፡ አቡሁ ፡ ኀብስተ ፡ ሶበ ፡ ይስእል፡ ወልድ ።

፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ወመስተጋድል ፡ ጽሙድ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ወመምህሩ፡ ለቅዱስ ፡ ኤፍሬም ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ልደቱ ፡ ወተ ሐፅኖቱ ፡ በሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ውእቱሰ ፡ ሶርያዊ ፡ ወእምንእሱ ፡ ኀረየ ፡ ለቢሰ ፡ አል ባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወለብሰ ፡ ሠቀ ፡ ጸጕር፡ ወኮነ ፡ ዘይትጋደል ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ በሐሩረ፡ ኃጋይ ፡ ወበ ቍረ ፡ ክረምት ፡ ወኢያወጽእ ፡ ውእተ ፡ ሠቀ ፡ጸጕር ፡ እምላዕለ ፡ ሥጋሁ፡ ግሙራ ፡ ወሲሳዩ ፡ ሠርጸተ ፡ ምድር ፡ ስቴሁኒ ፡ ማየ ዝናም፡ ባሕቲቱ፡ ወበእንተዝ፡ ኮነ፡ ሥጋሁ፡ ብሩህ ፡ ነፍሱሰ ፡ ትበርህ ፡ ፈድፋደ።

፫፡ ወወሀበ ፡እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ወገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ወኮነ፡ ይነግሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዘይከውን ፡ እምቅ ድመ ፡ ይኩን ፡ ወይከውን ፡ ከማሁ።

፬፡ ወተአምራቲሁሰ ፡ ብዙኅ ፡ ፈድፋደ ፡ እስመ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ርእዮን ፡ ለአን ስት ፡ እንዘ ፡ ይትዋነያ ፡ ወይሣለቃ ፡ ኀበ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀፍረት ፡ ወአይበሰ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ ወሥርዕተ ፡ ርእሶን ፡ ረሰየ ፡ ፀዓዳ ፡ ሲበተ ፡ ወሶበ ፡ ነስሐ ፡ ወሰአላሁ ፡ እንዘ ፡ ይሰግዳ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ነቅዓ ፡ ማዮን ፡ ሜጠ ፡ ሎን ፡ ነቅዐ ፡ ማዮን ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሶንሂ ፡ አትረፈ ፡ ፀዐዳ ፡ ከመ ፡ ይትገሠጻ ፡ ወኢይትዓበያ ።

፩፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በገድል ፡ የተጸመደ፡የከበረ፡ አባት ፡ ለቅዱስ ፡ ኤፍሬምም ፡ መምህሩ ፡ የሆነ ፡ የሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ አረፈ ።

፪፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ተወልዶ ፡ ያደገው ፡ በንጽቢን ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሶርያዊ ፡ ነው ፡ ከታናሽነቱም ፡ የምንኵስና፡ ልብስ ፡ መልበስን ፡ መረጠ ፡ ከጠጕር ፡ የተሠራ ፡ ማቅንም ፡ ለበሰ ፡ በጾም ፡ በጸ ሎት፡ ተወስኖ ፡ በቀን ፡ በሌሊት ፡ በበጋ፡ ሐሩር፡ በክረምት ፡ ቍር ፡ የሚጋደል ፡ ሆነ ፡ ያንንም ፡ ማቅ ፡ ከቶ ፡ ከሥጋው ፡ ላይ ፡ አያወጣውም ፡ ነበር፡ ምግቡም ፡ ቅጠላ ቅጠል ፡ ነው ፡ የሚጠጣውም ፡ የዝናብ ፡ ውኃ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ሥጋው ፡ ብሩህ፡ ሆነ ፡ ነፍሱም ፡ እጅግ ፡ በራች ።

፫፡እግዚአብሔርም ፡ ሀብተ ፡ ትንቢትን ፡ ድን ቆች፡ ተአምራቶችንም፡ የመሥራት፡ ጸጋን፡ ሰጠው ፡ ለሰዎችም ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ የሚሆነውን ፡ ይነግራቸውና ፡ እንዲሁም ፡ ይሆናል ።

፬፡ ተአምራቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ በአንዲትም፡ ቀን፡ ሴቶች፡ በውኃ፡ ምንጭ፡ ላይ ፡ ያለማፈር ፡ ሲጫወቱና ሲሣለቁ ፡ አያቸው ፡ የውኃውንም ፡ ምንጭ፡ አደረቀ ፡ የራሳቸውንም ፡ ጠጕር ፡ ነጭ ፡ ሽበትን ፡ አደረገ ፡ በተጸጸቱና ፡ የውኃውን ፡ ምንጭ ፡ እንዲመልስላቸው ፡ እየሰገዱ ፡ በለመኑት ፡ ጊዜ ፡ የውኃቸውን ፡ ምንጭ ፡ መለሰላቸው ፡ እንዳይታበዩም ፡ ይገሠጹ፡ ዘንድ ፡ የራሳ ቸውን ፡ ጠጉር ፡ ነጭ፡ እንደሆነ ፡ ተወው ።

www.ethiopianorthodox.org

፮፤ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ የኀልፍ ፡ በፍኖት፡
ረከቦሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዘአስከብዎ ፡ ለ፩ ብእሲ ፡
ከመ፡ ምውት ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡
ወሰአልዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ መግነዘ ፡
በዘይገንዝዎ ፡ ቦቱ ፡ ውእቱሰ ፡ ረሰዮ ፡ ምውተ ፡
በጸሎቱ ፡ ወሶበ ፡ ተጋብኡ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ ፡
ኀቤሁ ፡ ረከብዎ ፡ ምውተ ፡ ወሰአልዎ ፡ ካዕበ ፡
እንዘ ፡ ይኔስሑ ፡ ያሕዩ ፡ ሎሙ ፡ ወአሕየወ ፡
ሎሙ።

፯፤ ወሶበ፡ተሰምዐ፡ትሩፋቲሁ፡ወጽድቁ፡ኀረይዎ፡
ወሤምዎ፡ኤጲስቆጶሰ፡ላዕለ፡ሀገረ፡ንጽቢን፡
ወዐቀበ፡መርዔቶ፡ለክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡
በሠናይ፡ተዓቅቦ፡እምተኵላት፡አርዮሳውያን።

፰፤ ወሶበ ፡ አስተጋብአሙ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠን
ጢኖስ፡ ለማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ ፡
አበው ፡ በሀገረ ፡ ኒቅያ ፡ ሀሎ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ዝንቱ ፡ አብ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ አውገዞ ፡
ለአርዮስ ፡ ወሰደዶ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ወሠርዐ ፡ ቀኖና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጸሎተ ፡
ሃይማኖት ፡ ዘእምርት ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ መሃይ
ምናን።

፱፤ ወአንሥአ ፡ ምውተ ፡ በውስተ ፡ ጉባኤ ፡ አመ ፡
ብጽሐቱ፡ለቈስጠንጢኖስ፡ንጉሥ።

፲፤ ወአመ ፡ መጽአ ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡
ንጽቢን ፡ ወዓገታ ፡ ወአምጽአ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ፡
ደመና ፡ ዘቆባር ፡ ላዕለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወትንንያ ፡
ወነደፍዎሙ ፡ ለአፍራሲሆሙ ፡ ወለመሐዛ
ቲሆሙ፡ወአቀኍሰልዎሙ፡ወአፍራሲሆሙኒ፡
በተኩ ፡ ማእሠሪሆሙ ፡ ወሮጹ ፡ ወርእዮ ፡
ንጉሠ፡ ፋርስ ፡ ፈርሀ ፡ ዐቢየ ፡ ፍርሀተ ፡
ወተገሥአ፡ወጐየ፡ወገብአ፡ድኅሬሁ።

፲፩፤ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ገድሎ ፡ ሠናየ ፡ ወአብርሃ ፡
ለነፍሱ ፡ ወለነፍሰ ፡ መርዔቱ ፡ አዕረፈ ፡
በሰላም።

፲፪፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረ
ከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፮፤ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ በጐዳና ፡ አልፎ ፡ ሲሔድ ፡
አንዱን ፡ ሰው ፡ እንደሞተ ፡ ሰው ፡ አስተኝተው፡
ሰዎችን ፡ አገኛቸው ፡ መገነዣ ፡ ልብስም ፡
ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ቅዱሱን ፡ ለመኑት ፡ እርሱ ፡
ግን ፡ በጸሎቱ ፡ ሰውዬውን ፡ ምውት ፡ አደረገው፡
ሰዎችም ፡ ወደርሱ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ሙቶ ፡
አገኙት፡ተጸጽተውም፡ሁለተኛ፡ያድንላቸው፡
ዘንድ፡ለመኑት፡አዳነላቸውም።

፯፤ ትሩፋቱና ፡ ደግነቱም ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ መር
ጠው ፡ በሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ላይ ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡
ሾሙት ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የክርስቶስን ፡ መን
ጋዎች ፡ ከአርዮሳውያን ፡ ተኵላዎች ፡ በበጎ ፡
አጠባበቅ፡ጠበቀ።

፰፤ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ የሦስት ፡ መቶ ፡
ዐሥራ ፡ ስምንቱን ፡ የከበሩ ፡ አባቶች ፡ በኒቅያ ፡
ከተማ ፡ በሰበሰባቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አባት ፡
አብሮ ፡ አለ ፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡ አርዮስን ፡
አውግዞ ፡ ከክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ለየው ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ሥርዓትና ፡ በሁሉ ፡
ምእመናን ፡ ዘንድ ፡ የታወቀች ፡ የሃይማኖት ፡
ጸሎትን፡ሠራ።

፱፤ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
የሞተውን ፡ ሰው ፡ በጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ አስነ
ሥቷል።

፲፤ የፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ መጥቶ ፡ ሀገረ ፡ ንጽቢንን ፡
በከበባት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡
የጭጋግ፡ ደመና ፡ በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ አመጣ ፡
ትንኞችም፡ ፈረሶቻቸውንና ፡ ጐበዛዝቶችን ፡
ነደፏቸው ፡ ፈረሶችም ፡ ማሠሪያቸውን ፡ ቆር
ጠው ፡ ፈረጠጡ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ አይቶ፡
ታላቅ ፡ ፍርሀትን ፡ ፈራ ፡ ተነሥቶም ፡ ሸሽቶ ፡
ወደኋላው፡ተመለሰ።

፲፩፤ ነፍሱን ፡ የመንጋዎቹንም ፡ ነፍስ ፡ ጽድልት ፡
ብርሀት ፡ አድርጎ ፡ ገድሉን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
አረፈ።

፲፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረ
ከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለያዕቆብ ፡ በሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ዘተከሥተ ። አምሳለ ፡ ጽዱል ፡ ማኅቶት ፡ እንተ ፡ ያበርህ ፡ ጽልመተ። እንዘ ፡ ይትዋነያ ፡ በማይ ፡ ሶበ ፡ ነጸረ ፡ አንስተ ። በነቅዐ ፡ ማዮን ፡ አርአየ ፡ ይብሰተ ። ወሥዕርተ ፡ ርእሶን፡ጸሊመ፡ረሰየ፡ሲበተ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ከነ ፡ ተዝካሮን ፡ ለማርያ ፡ ወማርታ ፡ አኃቲሁ ፡ ለአልዓዛር ፡ ዘአንሥአ ፡ እግዚእነ ፡ እመቃብር ፡ እምድኅረ ፡ ረቡዕ ፡ መዋዕል ፡ በረከቶን ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

***

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፱ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተረክበ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ አባ ፡ ዝሑራ ፡ ወአባ ፡ ባሱራ ፡ ወእሞሙ ፡ ኔራ ።

፪፤ ወእሉ ፡ ቅዳሳን ፡ መስተጋድላን ፡ እምሀገረ ፡ ሳብሳ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ በመዋዕለ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወኮና ፡ ሥጋቲሆሙ ፡ ንቡራተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሀገረ ፡ ሳብሳ ፡ ወእምድኅረ ፡ ፲፻፯፻ወ፯ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ንጹሐን ፡ ዓገትዋ ፡ ሠራዊተ ፡ አፍርንጊ ፡ ለብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወነሥእዋ ፡ ለሀገረ ፡ ድምያጥ ፡ ወነግሡ ፡ በህየ ፡ ወነሥኡ ፡ ምስሌሃ ፡ አህጉረ ፡ ዐበይተ ፡ እምእለ ፡ የዓውድዋ ።

፫፤ ወንጉሠ ፡ ኮሞል ፡ ዘውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ አስተጋብአ ፡ ሠራዊተ ፡ ብዙኃነ ፡ እምኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወሖረ ፡ ይጽብኦሙ ፡ ለአፍርንጊ ፡ ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ሠራዊቱ ፡ አንሐሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙኃተ ። ወእምኔሆሙ ፡ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሀገረ ፡ ሳብሳ ፡ ዘውስቴታ ፡ ሀሎ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ ወነሥአ ፡ ፩ዱ ፡ እምሠራዊት ፡ ሣፁነ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ እንዘ ፡ ይሔሊ ፡ ከመ ፡ ይረክብ ፡ ውስቴቱ ፡ ንዋየ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘይትፌሣሕ ፡ ቦቱ ። ወሶበ ፡ አርኀዎ ፡ ረከበ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ባህርያተ ፡ ክቡራተ ፡ ወኢያእመረ ፡ ክብሮሙ ፡ ዘረዎሙ ፡ ኀበ ፡ አረፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነሥአ ፡ ሣፁነ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወሜጦ ።

፬፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ተዓጋሢ ፡ ወብዙኀ ፡ ምሕረት ፡ ተዓገሠ ፡ ላዕሌሁ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሠራዊተ ፡ አፍርንጊ ፡ ወሶበ ፡ ተጻብኡ ፡ ተቀትለ ፡ ውእቱ ፡ መቅድመ ፡ ኵሉ ። በከመ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ አብያጺሁ ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ ሶበ ፡ ገብኡ ፡ ኀበ ፡ ብሔሮሙ ፡ ነገሩ ፡ ወሰበኩ ፡

፲፫፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ከአራት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ከመቃብር ፡ ያስነሣው ፡ የአልዓዛር ፡ እኅቶች ፡ የማርያና ፡ የማርታ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ሆነ ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ የአባ ፡ ዝሑራ ፡ የአባ ፡ ባሱራ ፡ የእናታቸውም ፡ የኔራ ፡ ሥጋቸው ፡ ተገኘ ።

፪፤ እሊህ ፡ የከበሩ ፡ ተጋዳዮችም ፡ ጣዖት ፡ በሚመለክበት ፡ ዘመን ፡ ሳብሳ ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ፡ ሥጋዎቻቸውም ፡ በሳብሳ ፡ አገር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሆኑ ፡ ከንጹሐን ፡ ሰማዕታትም ፡ ዘመን ፡ ከዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የአፍርንጊ ፡ ሠራዊት ፡ ግብጽን ፡ ከበቧት ፡ የድምያጥንም ፡ ከተማ ፡ ወስደው ፡ በዚያ ፡ ነገሡ ፡ ከርሷ ፡ ጋርም ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉ ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞችን ፡ ያዙ ።

፫፤ የኮሞል ፡ ንጉሥም ፡ ይህም ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ አፍርንጊያውያንንም ፡ ይወጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሠራዊትን ፡ ሰበሰበ ፡ ሠራዊቱም ፡ ሲጓዙ ፡ ብዙዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አፈረሱ ፡ ከፈረሱትም ፡ ውስጥ ፡ አንዲቷ ፡ የእሊህ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ ሥጋቸው ፡ በውስጧ ፡ ያለባት ፡ ናት ። ከሠራዊቱም ፡ አንዱ ፡ የቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ ሥጋ ፡ ያለበትን ፡ ሣጥን ፡ ወሰደ ፡ በውስጡ ፡ የሚደሰትበትን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚያገኝ ፡ አስቦ ፡ በከፈተው ፡ ጊዜ ፡ ከዕንቍ ፡ የከበረ ፡ የቅዱሳንን ፡ ሥጋቸውን ፡ አገኘ ፡ ክብራቸውን ፡ ግን ፡ አላወቀም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ሥጋቸውን ፡ በትኖ ፡ ሣጥኑን ፡ ወስዶ ፡ ሸጠው ።

፬፤ ምሕረቱ ፡ የበዛ ፡ የሚታገሥ ፡ ልዑል እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ አፍርንጊ ፡ ሠራዊት ፡ እስከሚደርስ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ታገሠ ፡ ጦርነትም ፡ በገጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ ተገደለ ፡ ባልንጀሮቹም ፡ ምስክር ፡ እንደሆኑ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐቲሁ፡ለእግዚአብሔር፡ወይቤሉ፡ተቀ ትለ፡ቀዳሚ፡በሰይፍ፡ወተመትረ፡ርእሶ፡ ወሠዐርዎ፡ገበዋቲሁ፡ወሞተ፡በእኩይ፡ ሞት።

፫፡ ወሥጋሆሙሰ፡ለቅዱሳን፡ሶበ፡ገደፎሙ፡ ውእቱ፡ብእሲ፡ኮነት፡አሐቲ፡ብእሲት፡መሐ ይምንት፡ብእሲቱ፡ለ፩ ቀሲስ፡ትቀውም፡ ወትኔጽር፡ወእምዝ፡ቦአት፡ኀቤሆሙ፡ በጽሚት፡ወነሥአቶሙ፡ወጠብለለቶሙ፡ በዓጽፋ፡በፍሥሓ፡ወበእንተ፡ፍርሀቶሙ፡ ለተንባላት፡አንበረቶሙ፡ውስተ፡ማዕዝነ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡እንዘ፡ጥብሉላን፡በዐጽፋ፡ ከደነቶሙ፡በግንፋል፡ወነበሩ፡ክዱናነ፡ በውእቱ፡ግንፋል፡ውስተ፡ይእቲ፡ማዕዘንት፡ መጠነ፡፷ ዓመት፡ወረሰዓት፡ዜናሆሙ፡ ይእቲ፡ብእሲት፡እምብዝኀ፡መዋዕል።

፬፡ ወሶበ፡ፈቀደ፡እግዚአብሔር፡ ይክሥቶሙ፡ ለበቍዔተ፡ሕዝቡ፡ተዘከርዎሙ፡ካልአን፡ ሰብእ፡በቅድመ፡ይእቲ፡ብእሲት፡ይእቲኒ፡ ሶቤሃ፡ተዘከረቶሙ፡ወነገረቶሙ፡ለካህናት፡ ወለመሐይምናን፡ወአርአየቶሙ፡መካኖሙ። ወቦኡ፡ካህናት፡ወነሥኡ፡ሥጋሆሙ፡ ወገብሩ፡ሎሙ፡ሣፁነ፡ሠናይተ፡ወአንበ ርዎሙ፡ውስቴታ፡በክብር፡ወገብሩ፡ሎሙ፡ በዓለ፡በከመ፡ዛቲ፡ዕለት፡እስመ፡አዘዘ፡አባ፡ ገብርኤል፡ኤጲስቆጶስ፡ዘይእቲ፡ሀገር፡ከመ፡ ይግበሩ፡ሎሙ፡በዓለ፡ወትረ፡ወይጽሐፉ፡አስ ማቲሆሙ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ግጻዌሆሙ፡ ዘበዓላት።

፭፡ ወተከሥታ፡እምአዕፅምቲሆሙ፡ተአምራት፡ ወመንክራት፡ወእምኔሆሙ፡እስመ፡ሀለወት፡ አሐቲ፡ብእሲት፡ዘባቲ፡ወለት፡ዕውርት፡ እምድኅረ፡ቀብጸት፡ተስፋ፡ሶበ፡ተማሕ ጸነት፡ኀበ፡አዕፅምቲሆሙ፡ለቅዱሳን፡ ተከሥታ፡አዕይንቲሃ፡ወርእየት፡ወሰብሐቶ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ ስብሐት፡ዘአክበሮሙ፡ለእሉ፡ሰማዕታት፡ በዝንቱ፡ክብር፡ዐቢይ፡ወበረከቶሙ፡ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

ብሔርን፡ክብር፡ፈጽመው፡ሰበኩ፡እንዲ ህም፡ አሉ፡እርሱ፡አስቀድሞ፡በሰይፍ፡ ተመታ፡ራሱንም፡ተቆረጠ፡ጉኖቹንም፡ሠነ ጣጥቀውት፡በክፉ፡አሟሟት፡ሞተ።

፫፡ የቅዱሳኑን፡ሥጋቸውን፡ያ፡ሰው፡በበተ ናቸው፡ጊዜ፡የአንድ፡ቄስ፡ሚስት፡የሆነች፡ አንዲት፡ምእመን፡ሴት፡ቁማ፡ትመለከት፡ ነበር፡ከዚህም፡በኋላ፡በጭልታ፡ወደር ሳቸው፡ገብታ፡ደስ፡እያላት፡ወስዳ፡በመጐና ጸፊያዋ፡ጠቀለለቻቸው፡እስላሞችንም፡ከመ ፍራቷ፡የተነሣ፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ማዕ ዘን፡ውስጥ፡አኖረቻቸው፡በመጐናጸፊያዋም፡ እንደ፡ ተቀለሉ፡በጥብ፡ሸፈነቻቸው፡በዚ ያም፡ጥብ፡ተሸፍነው፡በዚያች፡ማዕዘን፡ ውስጥ፡ሃያ፡ዓመት፡ያህል፡ኖሩ፡ከቀን፡ ብዛትም፡የተነሣ፡ያቺ፡ሴት፡ወሬያቸውን፡ ረሳች።

፬፡ እግዚአብሔርም፡ ለወገኖቹ፡ጥቅም፡ይገል ጣቸው፡ዘንድ፡በወደደ፡ጊዜ፡በዚያች፡ሴት፡ ፊት፡ሌሎች፡ሰዎች፡አስታወሷቸው፡ እርሷም፡በዚያን፡ጊዜ፡አስታወሰቻቸው፡ለካ ህናቱና፡ለምእመናኑ፡ነግራ፡ቦታቸውን፡አሳ የቻቸው። ካህናቱም፡ገብተው፡ሥጋቸውን፡ አነሡ፡ያማረች፡ሣጥንንም፡ሠርተው፡ በውስጧ፡በክብር፡አኖሩዋቸው፡እንደ፡ ዛሬዪቱም፡ዕለት፡በዓልን፡አደረጉላቸው፡ ሁል፡ጊዜ፡በዚች፡ዕለት፡በዓል፡ያደርጉ ላቸው፡ዘንድ፡ስማቸውን፡በበዓላት፡ግጻዌ፡ መጽሐፍ፡እንዲጽፉ፡የአገሩ፡ኤጲስቆጶስ፡ አባ፡ገብርኤል፡አዝዟልና።

፭፡ ከዐፅሞቻቸውም፡ድንቆች፡ተአምራቶች፡ ተገለጡ፡ከተአምራቶችም፡አንዲት፡ የታወረች፡ልጅ፡ያለቻት፡ሴት፡ነበረች፡ ተስፋ፡ከቆረጠችም፡በኋላ፡ከቅዱሳኑ፡ዐፅም፡ በተማፀነች፡ጊዜ፡ዐይኖቿ፡ተገልጠውላት፡ አየች፡እሊህንም፡ሰማዕታት፡በዚህ፡ክብር፡ ያከበራቸውን፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ አመሰገነችው፡በረከታ ቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር። ለእግዚአብ ሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ ዘሥጋሆሙ፡ርክበተ ፡። ለዝሑራ፡ወባሱራ፡ወለዘወለደት፡እሎንተ። አመ፡ ሣፁኖሙ፡ነሥአ፡እንዘ፡ይመስሎ፡ጥሪተ። ለዘዘረወ፡ሥጋሆሙ፡ፈደይዎ፡ሞተ። ወዘተማሕፀነት፡ቦሙ፡ ፈወሱ፡ዕውርተ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለበርስጢና፤ወያፍቅረነ፡እግዚእ፡ወበረከቶሙ፡ቅድስት፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፳፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የበርስጢናና ፡ የአባ ፤ ያፍቅረነ፡ እግዚእ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ ልዩ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡እብል፡ለዘፈጸመ፡ገድሎ። ያፍቅረነ፡እግዚእ፡ጻድቅ፡ውስተ፡ከተማ፡ደብር፡ተልዒሎ። መጥባሕተ፡እኂዞ፡በእዴሁ፡እንዘ፡ውእቱ፡ይከፍሎ። መልአከ፡ሰማይ፡ከመዝ፡ይቤሎ። እንተ፡ተጋደልከ፡ርኢ፡ወነጽር፡ቅቱሎ።

***

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡አመ፡፳ሁ፡ለጥር፡በዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡ቅዱስ፡አብሮኮሮስ፡ሐዋርያ፡፩ዱ፡እም፸ወ፪፡አርድእት፡ዘኀረዮሙ፡እግዚእነ፡ወፈነዎሙ፡ይስብኩ፡ወንጌለ፡ወይፈውሱ፡ዱያነ።

፪፤ ወሶበ፡ኮነ፡ዝንቱ፡ቅዱስ፡ምስለ፡ሐዋርያት፡በጽርሐ፡ጽዮን፡ተመልአ፡ጸጋ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ጰራቅሊጦስ፡ወለውእቱ፡ኀረይዎ፡ሐዋርያት፡እምኍልቆሙ፡ለ፯ቱ፡ዲያቆናት፡ዘኮነ፡ስምዐ፡በእንቲአሆሙ፡መጽሐፈ፡ግብረ፡ሐዋርያት፡ከመ፡እሙንቱ፡ምሉአነ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ወጥበብ።

፫፤ ወእምዝ፡ኮነ፡ረድአ፡ለቅዱስ፡ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ወሖረ፡ምስሌሁ፡ኀበ፡ብዙኃት፡አህጉር፡ወአንበረ፡ላዕሌሁ፡እዴሁ፡ወሤሞ፡ኤጲስቆጶሰ፡ላዕለ፡ሀገረ፡ኒቆምድያ፡ዘብሔረ፡ቢታንያ፡ውእቱኒ፡ሰበከ፡በውስቴታ፡ሃይማኖተ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት። ወሚጠሙ፡ለብዙኃን፡እምዮናናውያን፡ወአብአሙ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወአጥመቆሙ፡በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ወመሀሮሙ፡ከመ፡ይዕቀቡ፡ትእዛዛተ፡ወንጌል፡ወሐነፀ፡ሎሙ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወሤመ፡ሎሙ፡ቀሳውስተ፡ወዲያቆናተ።

፬፤ ወእምዝ፡ወጽአ፡ውስተ፡አህጉር፡እለ፡የዓውድዋ፡ለይእቲ፡ሀገር፡ወሰበከ፡ውስቴቶሙ፡ወንጌለ፡ቅዱሰ፡ወሚጠሙ፡ለብዙኃን፡እምስሕተት፡ወለአይሁድኒ፡አጥመቆሙ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡ወባሕቱ፡በጽሐ፡ምንዳቤ፡ብዙኅ፡ወስደት፡በእንተ፡ስሙ፡ለክርስቶስ፡ወፈጸሞ፡ተጋድሎቶ፡ወአሥመሮ፡ለእግዚእነ፡አዕረፈ፡በርሥእ፡ጥሉል።

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡ በሽተኞችንም ፡ ይፈውሱ ፡ ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ መርጦ ፡ ከላካቸው፡ከሰብዓ፡ሁለቱ፡አርድእት፡አንዱ፡የከበረ፡ሐዋርያ፡አብሮኮሮስ፡አረፈ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ከሐዋርያት፡ ጋር፡ሁኖ፡ሳለ፡የአጽናኝ፡መንፈስ፡ቅዱስን፡ጸጋ፡ተመላ ። እርሱንም ፡ ሐዋርያት ፡ መርጠውት ፡ ከሰባቱ ፡ ዲያቆናት ፡ ጋር ፡ የተቆጠረ ፡ ሆነ፡እነርሱ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ያደረባቸው፡ዕውቀትም፡ያላቸው፡እንደሆኑ፡የሐዋርያት፡ሥራ፡መጽሐፍ፡ስለርሳቸው፡ምስክር፡ሆነ።

፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለወንጌላዊ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ፡ደቀ፡መዝሙሩ፡ሆነ፡ከእርሱም፡ጋር፡ወደ፡ብዙ፡አገሮች፡ሔደ፡ በቢታንያ፡አገር፡በኒቆምድያ፡ከተማ፡ላይ፡በአንብሮተ፡እድ፡ኤጲስቆጶስነት ፡ ሾመው ። እርሱም ፡ የክብር ፡ ባለቤት፡ የጌታችንን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ሃይማኖት፡ አስተማረ ፡ ከዮናናውያንም ፡ ብዙዎችን ፡ መልሶ ፡ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ አስገባቸው ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ አጠመቃቸው፡የወንጌልንም፡ትእዛዞች፡እንዲጠብቁ፡ አስተማራቸው ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንንም ፡ ሠርቶ ፡ ቀሳውስትን ፡ ዲያቆናትን ፡ ሾመላቸው።

፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያቺን ፡ አገር ፡ ወደሚከቧት ፡ አገሮች ፡ ወጣ ፡ በውስጣቸውም ፡ የከበረ ፡ ወንጌልን ፡ ሰበከ ፡ ብዙዎችንም ፡ ከስሕተት ፡ መለሳቸው፡አይሁድንም፡የክርስትና፡ጥምቀትን ፡ አጠመቃቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ፡ መከራና፡ስደት፡ደረሰበታል፡ስለ፡ክርስቶስ፡ ስም፡ ተጋድሎውንም፡ሲፈጽም፡ጌታችንንም፡አገልግሎ፡በመልካም፡ሽምግልና፡አረፈ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፳፩ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ አብሮኮሮስሃ ፡ ክቡረ ። ዘአድምዐ ፡ በኒቆምድያ ፡ ዘኤጲስቆጶስ ፡ መንበረ ። እንዘ ፡ ይስዕም ፡ አምላክ ፡ ለአፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ምዕረ ። ስምዐ ፡ ኮነ ፡ በሰማይ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነጸረ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ረድእ ፡ ዘይትሉ ፡ መምህረ።

፩ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ አክሎግ ፡ ቀሲስ ፡ እምሀገረ ፡ እልፈንት ፡ ዘብሔረ ፡ ግብጽ።

፩ በዚችም ፡ ቀን ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ እልፈንት ፡ ከሚባል ፡ ከተማ ፡ የከበረ ፡ ቀሲስ ፡ አክሎግ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ።

፪ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወስማ ፡ ለእሙ ፡ አፎምያ ፡ ወእሉ ፡ እምዘመድ ፡ ክቡራን ፡ ወብዑላን ፡ ፈድፋደ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ በአልሕምት ፡ ወአባግዕ ፡ በአፍራስ ፡ ወአግማል ፡ ወባሕቱ ፡ አልቦሙ ፡ ውሉድ ፡ ወበእንተዝ ፡ የኀዝኑ ፡ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይስእልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ወልደ ፡ ወተወክፈ ፡ ስእለቶሙ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ዘንተ ፡ ወልደ ፡ ቡሩከ ፡ ወሰምይዎ ፡ ስሞ ፡ አክሎግሃ ፡ ዝ ፡ ብሂል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ ጥዑመ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር።

፪ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የናቱ ፡ ስም ፡ አፎምያ ፡ ነው ፡ እነርሱም ፡ ከከበሩ ፡ ወገኖች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ ባለሞችና ፡ በበጎች ፡ በፈረሶችና ፡ በግመሎች ፡ እጅግ ፡ የበለጸጉ ፡ ናቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ የላቸውም ፡ ስለዚህም ፡ ያዝኑ ፡ ነበር። ልጅንም ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ። ሲለምኑ ፡ ኖሩ ፡ ልመናቸውንም ፡ ተቀበሎ ፡ ይህን ፡ የተባረከ ፡ ልጅ ፡ ሰጣቸው ፡ ስሙንም ፡ አክሎግ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፡ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው።

፫ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፳ ዓመት ወሀብዎ ፡ ለመምህር ፡ ከመ ፡ ይትመሀር ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተምህረ ፡ ኵሎ ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይሰምዕ ፡ ጸሎታተ ፡ ወስብሐታተ ፡ ወዘንተኒ ፡ ዘይገብር ፡ እምቅድመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ መምህር።

፫ ስምንት ፡ ዓመትም ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይማር ፡ ዘንድ ፡ ለመምህር ፡ ሰጡት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ ተማረ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሔድ ፡ ምስጋናዎችንና ፡ ጸሎቶችን ፡ ይሰማል ፡ ይህንንም ፡ የሚያደርግ ፡ ወደ ፡ መምህር ፡ ከመሔዱ ፡ አስቀድሞ ፡ ነው።

፬ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ወጽአ ፡ እመምህሩ ፡ ከመ ፡ ይሑር ። ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ተጽዒኖ ፡ ፈረሰ ፡ ወይተልውዎ ፡ ፪ቱ ፡ አግብርት ፡ ወርእዮሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ዕደ ፡ ወአንስት ፡ ጉቡአነ ፡ እንዘ ፡ ይኬልሑ ፡ ወቀርበ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ዘኮነ ። ወረከቦ ፡ ለ፩ ሕፃን ፡ ውዱቀ ፡ በማዕከሎሙ ፡ ዘነሰኮ ፡ ከይሲ ፡ ወቀርበ ፡ ለመዊት ፡ ወተዘከረ ፡ ቅዱስ ፡ አክሎግ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘይቤ ፡ ዛቲ ፡ ተአምር ፡ ትተልዎሙ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ በስምየ ፡ በስመ ፡ ዚአየ ፡ አጋንንተ ፡ ያውጽኡ ፡ ወበካልዕ ፡ ልሳን ፡ ይትናገሩ ፡ ሐዲሳተ ፡ ወአራዊተ ፡ ምድር ፡ ይእኀዙ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየሐስሞሙ።

፬ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ከመምህሩ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ሊሔድ ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ሁለት ፡ አገልጋዮችም ፡ ተከትለውት ፡ ሲጓዙ ፡ ብዙ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ተሰብስበው ፡ ሲጮሁ ፡ አያቸው ፡ የሆነውንም ፡ ሊያይ ፡ ወደ ርሳቸው ፡ ቀረበ ። እባብ ፡ የነከሰውና ፡ ለሞትም ፡ የቀረበ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ በመካከላቸው ፡ ወድቆ ፡ አገኘ ። የከበረ ፡ አክሎግም ፡ ይቺ ፡ ምልክት ፡ በስሜ ፡ የሚያምኑትን ፡ ትከተላቸዋለች ፡ በስሜም ፡ አጋንትን ፡ ያስወጣሉ ፡ አዳዲስ ፡ ቋንቋን ፡ ይናገራሉ ፡ የምድር ፡ አራዊቶችን ፡ በእጃቸው ፡ ይይዛሉ ፡ የሚጐዳቸውም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ያለውን ፡ የከበረ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አሰበ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፤ ወሶቤሃ ፡ አኀዘ ፡ እዴሁ ፡ ለሕፃን ፡ ወአተበ ፡
ላዕሌሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ እንዘ ፡
ይብል፡በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡
ቅዱስ፡ ወይቤ፡ለከ፡እብለከ፡ኦ፡ሕፃን፡ከመ፡
ትሕየው ፡ እምነ ፡ ሕምዙ ፡ ለዝንቱ ፡ አርዌ ፡
እኩይ ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ በአፉሁ ፡
ንጹሕ፡ ወጽድቅ ፡ ናሁ ፡ ወሀብኩክሙ ፡
ሥልጣነ ፡ ከመ ፡ ትኪዱ ፡ አክይስተ ፡ ወአቃ
ርብተ ፡ ወኵሎ ፡ ኃይለ ፡ ጸላኢ ፡ ወኢያሐስ
መክሙ፡ምንተኒ፡ወበጊዜሃ፡ሐይወ፡ውእቱ፡
ወልድ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ዘኢበጽሖ ፡ ምንትኒ ፡
እምእኩይ።
፲፩፤ወሶበ፡ርእዩ፡ሕዝብ፡ዘንተ፡ተአምረ፡አንከሩ፡
ፈድፋደ፡ወሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ገባሬ፡
መንክራት፡በላዕለ፡ቅዱሳኒሁ። ወተሰምዐ፡
ዜናሃ ፡ ለይእቲ ፡ ተአምር ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
አህጉር።
፲፪፤ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ፡ ዓመተ ፡ ኀበ ፡
መምህሩ፡አጽንአ፡፬ተ፡ወንጌላተ፡ወግብረ፡
ሐዋርያት፡ ወመልእክታተ ፡ጳውሎስ፡ ፲ተ፡
ወ፬ተ ፡ ወመልእክታተ ፡ ሐዋርያት ፡ ፯ተ ፡
ወራእየ፡ዮሐንስ ፡ ወመዝሙራተ ፡ ዳዊት፡
፪ተ ፡ወ፶ ወመኀልየ ፡ ነቢያት ፡ ወሰሎሞን ፡
ወያነብብ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ በመዓልት ፡
ወበሌሊት ፡ ወበሌሊተ ፡ እሑድ ፡ የኀድር ፡
እንዘ፡ይትቀነይ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ወኵሎ፡አሚረ፡ይጸውም፡ወይጼሊ።

፲፫፤ ወእምድኅረ ፡ አዕረፉ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ሶበ ፡
ርእዩ፡ሰብእ፡ገድሎ፡ሠናየ፡ሰአልዎ፡ለኤጲ
ስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይሢሞ ፡ ሎሙ ፡ ቀሲሰ ፡
ለቅዱስ ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ በእንቲአሆሙ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ዘይጸውም ፡ በበ፪ቱ ፡
ወበበ፫ቱ፡ዕለት፡ወበበሱባዔ፡በኵሉ፡መዋ
ዕሊሁ፡ወይለብስ፡ሠቀ፡ጸጕር፡እምታሕተ፡
አልባሲሁ፡ወጸጋ፡እግዚአብሔር፡ጸውዓቶ፡
ከመ፡ይሠየም፡ቀሲሰ፡ወነሥአ፡ኤጲስቆጶስ፡
ዘእንበለ፡ፈቃዱ። ወሤሞ፡ቀሲሰ፡ወሶበ፡
ተሠይመ፡ሰምዑ፡ሕዝብ፡ቃለ፡እንዘ፡ይጸ
ርሕ፡ወይብል፡ይደልዎ፡ይደልዎ፡ይደልዎ፡
ሢመተ፡ክህነት፡ለአባ፡አክሎግ፡ኢጲስ
ቆስኒ፡ወሕዝብ፡አንከሩ፡ጥቀ፡ወሰብሕዎ፡
ለእግዚአብሔር።

፲፤ በዚያንም፡ጊዜ፡የሕፃኑን፡እጅ፡ይዞ፡በአብ፡
በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ብሎ፡በላዩ፡
በመስቀል፡ምልክቶ፡አማተበና፡ሕፃን፡ሆይ፡
ከዚህ፡ክፉ፡እባብ፡መርዝ፡ትድን፡ዘንድ፡እና
ገርሃለሁ፡ጌታችን፡ንጹሕና፡እውነት፡በሆነ፡
ቃሉ፡እባቡን፡ጊንጡን፡የጠላትን፡ኃይል፡
ሁሉ ፡ ትረግጡ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ ሥልጣን ፡
ሰጠኋችሁ ፡ ምንም ፡ የሚጎዳችሁ ፡ ነገር ፡
የለም፡ብሏልና፡አለ፡ወዲያውኑ፡ያ፡ልጅ፡
ዳነ፡ከክፉ፡ነገርም፡ምንም፡ምን፡እንዳልደረ
ሰበት፡ሆነ።

፲፩፤ ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ተአምር ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡
እጅግ፡ አደነቁ ፡ በቅዱሳኑ ፡ አድሮ ፡ ድንቅ፡
ሥራ፡የሚሠራ፡እግዚአብሔርንም፡ አመሰ
ገኑት፡የዚችም፡ተአምር፡ወሬዋ፡በሀገሩ፡
ሁሉ፡ተሰማ።
፲፪፤ከመምህሩም፡ዘንድ፡ዐሥራ፡ሁለት፡ዓመት፡
በሆነው፡ጊዜ፡አራቱን፡ወንጌሎች፡የሐዋር
ያትን፡ሥራ፡ዐሥራ፡አራቱን፡የጳውሎስን፡
መልእክቶች፡ሰባቱን፡የሐዋርያት፡መልእ
ክታት፡የዮሐንስንም፡ራእይ፡መቶ፡ሃምሳ
ውን፡የዳዊትን፡መዝሙራት፡የነቢያትንና፡
የሰሎሞንን ፡ መኀልይ ፡ ጠንቅቆ ፡ አጠና።
ሁል ፡ ጊዜ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ያነባል ፡
በእሑድ ፡ ሌሊትም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ውስጥ፡እያገለገለ፡ያድራል፡ሁል፡ጊዜም፡
አዘውትሮ፡ይጾማል፡ይጸልያል።
፲፫፤ ወላጆቹም ፡ ከአረፉ ፡ በኋላ ፡ ሰዎች ፡ መል
ካም፡ ተጋድሎውን ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ ስለ፡ እነ
ርሱ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ቅስና ፡ እንዲሾም
ላቸው ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ ለመኑት፡ እርሱ ፡
በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በየሁለት፡ ቀን ፡ በየሦስት ፡
ቀን ፡ በየሱባዔው ፡ ይጾማልና ፡ በልብሱም ፡
ውስጥ ፡ ማቅ ፡ ይለብሳልና ። ቅስና ፡ ይሾም ፡
ዘንድ ፡የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ጠራችውና ፡
ኤጲስቆጶሱም ፡ ወስዶ ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡
ቅስና ፡ ሾመው ፡ በተሾመ ፡ ጊዜም ፡ ለአባ ፡
አክሎግ ፡ የክህነት ፡ ሹመት ፡ ይገባዋል ፡
ይገባዋል፡ይገባዋል፡እያለ፡ሲጮህ፡ሕዝቡ፡
ቃልን ፡ ሰሙ ፡ ኤጲስቆጶሱና ፡ ሕዝቡም ፡
እጅግ፡አደነቁ፡እግዚአብሔርንም፡ አመሰ
ገኑት።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወእምድኅረ፡እማንቱ፡መዋዕል፡ኮነ፡ስደት፡
ዐቢይ፡ወምንዳቤ፡ላዕለ፡ሕዝበ፡ክርስቲያን፡
ውስተ፡ኵሉ፡ምድር፡እምኀበ፡ዲዮቅልጥ
ያኖስ፡ከሀዲ፡ወአንሐለ፡አብያተ፡ክርስ
ቲያን፡ወብዙኃን፡ኮኑ፡ሰማዕተ።
፲፭፡ ወጸውዖ፡እግዚአብሔር፡ለአባ፡አክሎግ፡
ከመ፡ይኩን፡ሰማዕተ፡ውእቱኒ፡አንቃ
ዕደው፡ሰማየ፡ጸርሐ፡ወይቤ፡አ፡እግዚእየ፡
ወአምላኪየ፡ወመድኃንየ፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስ፡አኃዜ፡ኵሉ፡ዓለም፡ግበር፡ምሕረተከ፡
ወሣህለከ፡ወሰላመከ፡ላዕለ፡ሕዝብ፡እለ፡
ውስተ፡ሀገርከ፡ኵለንታሃ፡ከመ፡ትባርኮሙ፡
ወታድኅኖሙ፡እምሰይጣናት፡ወትፌኑ፡ሊተ፡
መልአከከ፡ኄረ፡ከመ፡ያጽንዓኒ፡እስከ፡
እፌጽም፡ተጋድሎትየ፡በእንተ፡ስምከ፡
ቅዱስ፡እስመ፡ለከ፡ስብሐት፡ወኃይል፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፡ ወእምዝ፡ተመይጠ፡ኀበ፡ሰብእ፡እለ፡
የዓውድዎ፡ወይቤሎሙ፡ዘይፈቅድ፡ይም
ጻእ፡ወይሑር፡ምስሌየ፡ወተለውዎ፡ሰብአ፡
ዚአሁ፡ወሰብአ፡ሀገሩ፡፫፻ወ፵፡ወቆሙ፡
ዲበ፡መካን፡ልዑል፡ወጸርሑ፡እንዘ፡ይብሉ፡
ንሕነ፡ክርስቲያን፡ገሀደ፡ወሰሚዖ፡ሊቀ፡
ሐራሁ፡ለንጉሥ፡ኀዘነ። ወአሠሮ፡ለአባ፡
አክሎግ፡ወመጠዎ፡ለአርያኖስ፡መኰንን፡
ውእቱኒ፡ይቤሎ፡ስግድ፡ለአማልክት፡
ወይቤ፡አባ፡አክሎግ፡አንሰ፡ኢይሰግድ፡ለአ
ማልክት፡ርኵሳን፡አላ፡እሰግድ፡ለእግዚእየ፡
ወአምላኪየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡
ስብሐት።
፲፯፡ ወሶቤሃ፡ተምዐ፡አርያኖስ፡ወኰነኖ፡ኵነኔ፡
ጽኑዐ፡ለአባ፡አክሎግ፡ወወደዮ፡ውስተ፡
እቶነ፡እሳት፡ወወረደ፡መልአከ፡እግዚአ
ብሔር፡ወረሰዮ፡ለእሳት፡ከመ፡ጠል፡ቈሪረ፡
ወቆመ፡ቅዱስ፡አክሎግ፡ማዕከለ፡እቶን፡
ወጸለየ።

፲፰፡ ወእምዝ፡ይቤሎሙ፡አርያኖስ፡መኰንን፡
ለእሙንቱ፡፫፻፡ወ፵ ዕደው፡አንትሙኒ፡
ንዑ፡ ስግዱ፡ለአማልክት፡አውሥእዎ፡
ወይቤልዎ፡ንሕነሰ፡ኢንሰግድ፡ለአማ
ልክት፡ርኵሳን፡ዘእንበለ፡ ላእግዚአብሔር፡

፲፬፡ከእነዚያ፡ወራቶችም፡በኋላ፡በሀገሩ፡ሁሉ፡በክ
ርስቲያን፡ወገኖች፡ላይ፡ከከሀዲው፡ዲዮቅ
ልጥያኖስ፡ዘንድ፡ታልቅ፡መከራና፡ስደት፡
ሆነ፡አብያተ፡ክርስቲያናትንም፡አፈረሰ፡
ብዙዎችም፡በሰማዕትነት፡ሞቱ።
፲፭፡ ምስክርም፡ይሆን፡ዘንድ፡አባ፡አክሎግን፡
እግዚአብሔር፡ጠራው፡እርሱም፡ቆመ፡
ወደሰማይም፡ቀና፡በማለት፡እንዲህ፡ብሎ፡
ጸለየ፡ዓለሙን፡ሁሉ፡የያዝክ፡ጌታዬ፡
ፈጣሪዬ፡መድኃኒቴ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሆይ፡በሀገርህ፡በሁለመናዋ፡ላሉ፡ሕዝብ፡
ቸርነትህን፡ይቅርታህንና፡ሰላምህን፡አድ
ርግ። ትባርካቸውም፡ዘንድ፡ከሰይጣናትም፡
ስሕተት፡ታድናቸው፡ዘንድ፡ለእኔም፡ስለ፡
ከበረው፡ ስምህ፡ ተጋድሎዬን፡ እስከም
ፈጽም፡ያጸናኝ፡ዘንድ፡ቸር፡መልአክህን፡
እንድትልክልኝ፡እለምንሃለሁ፡ኃይል፡ክብር፡
ገንዘብህ፡የሆነ፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፲፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡በዙሪያው፡ወዳሉ፡ሰዎች፡
ተመልሶ፡የሚሻ፡ይምጣ፡ከእኔ፡ጋር፡
ይሒድ፡አለ፡የእርሱ፡ሰዎችና፡የሀገሩ፡
ሰዎች፡ሦስት፡መቶ፡አርባ፡ተከተሉት፡
በከፍታ፡ቦታ፡ላይም፡ቁመው፡እኛ፡
በግልጥ፡ክርስቲያን፡ነን፡ብለው፡ጮኹ።
የንጉሡም፡የሠራዊት፡አለቃ፡ሰምቶ፡አዘነ፡
አባ፡አክሎግንም፡አሥሮ፡ለመኰንኑ፡ለአር
ያኖስ፡ሰጠው፡እርሱም፡ለአማልክት፡
ስገድ፡ አለው፡አባ፡አክሎግም፡ለክብር፡
ባለቤት፡ለጌታዬና፡ለፈጣሪዬ፡ ለኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እሰግዳለሁ፡እንጂ፡እኔ፡ለረከሱ፡
አማልክት፡አልሰግድም፡አለ።
፲፯፡ ቢዘያንም፡ጊዜ፡መኰንኑ፡አርያኖስ፡ተቆጣ፡
አባ፡አክሎግንም፡ጽኑ፡ሥቃይን፡አሠቃ
ይቶ፡ከእሳት፡ማንደጃ፡ውስጥ፡ጨመረው፡
ከእግዚአብሔርም፡የታዘዘ፡መልአክ፡ወርዶ፡
እሳቱን፡እንደ፡ጠል፡ቀዝቃዛ፡አደረገው፡
አባ፡አክሎግም፡በእቶኑ፡መካከል፡ቁሞ፡
ጸለየ።
፲፰፡ ከዚህም፡በኋላ፡መኰንኑ፡አርያኖስ፡ሦስት፡
መቶ፡አርባውን፡ሰዎች፡እናንተ፡ኑ፡ለአማ
ልክት፡ስገዱ፡አላቸው፡እነርሱም፡እንዲህ፡
ብለው፡ መለሱለት። እኛስ፡ ከእግዚአ
ብሔር፡በቀር፡ለረከሱ፡አማልክት፡አንሰ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ወአዘዘ ፡ ይምትርዎሙ ፡ በሰይፍ ፡ አርእስ
ቲሆሙ ፡ ወመተርዎሙ ፡ ወነሥኡ ፡ አክ
ሊለ፡ስምዕ።
፲፱፡ ወበውእቱ፡ጊዜ፡ሞተ፡ወልዱ፡ለአርያኖስ፡
መኰንን ፡ ወኀዘነ ፡ ፈድፋደ ፡ ወይቤሎ ፡
ቅዱስ፡አባ፡አክሎግ፡ለአርያኖስ፡እመሰ፡
ገበርኩ፡ላዕሌከ፡ሠናየ፡ወእስእሎ፡ለእግዚ
አብሔር፡አምላኪየ፡ከመ፡ያንሥእ፡ለከ፡
ወልደከ፡ሕያወ፡ምንተ፡ትሁበኒ።ወይቤሎ፡
አርያኖስ፡እሬስየከ፡ሊቀ፡ላዕለ፡፻ሐራ፡ወእ
ፌንወከ ፡ ኀበ ፡ ሀገርከ ፡ በክብር ፡ ዐቢይ ፡
ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አክሎግ ፡ አንሰ ፡ ኢይፈ
ቅድ ፡ ዘንተ ፡ ባሕቲ ፡ መሐል ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡
ትኩንነኒ ፡ ወትቅትለኒ ፡ ወትፈኑ ፡ ሥጋየ ፡
ኀበ ፡ ሀገርየ ፡ ወመኰንንኒ ፡ መሐለ ፡ ሎቱ ።
ወሶቤሃ፡ሰአለ፡ቅዱስ፡አክሎግ፡ኀበ፡እግዚ
አብሔር፡እንዘ፡ይብል፡እስእለከ፡ኦ፡እግዚ
እየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ትስምዓኒ ፡
ስእለትየ፡ዮም፡ወታንሥእ፡ለዝንቱ፡ሕፃን፡
ምውት ፡ ወይሰባሕ ፡ ስምከ ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡
ለከ፡ስብሐት፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፡ ወሶበ፡ይቤ፡ዘንተ፡አተበ፡ላዕለ፡ሕፃን፡በትእ
ምርተ ፡ መስቀል ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡
ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ተንሥአ ፡
ሕፃን፡ወርእዮሙ፡አሕዛብ፡ዘንተ፡መንክረ፡
ከልሑ፡በ፩ዱ፡ቃል፡ኵሎሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡
ንሕነ፡ነአምን፡በአምላኩ፡ለቅዱስ፡አክሎግ።
፳፩፡ ወተምዐ ፡ መኰንን ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ያውጽ
እዎሙ ፡ አፍአ ፡ ሀገር ፡ ወይክርዩ ፡ ሎሙ ፡
ዓዘቅተ ፡ ርሒበ ፡ ወያንድዱ ፡ እሳተ ፡ ወይደ
ይዎሙ ፡ ውስቴቱ ፡ ወገብሩ ፡ ቦሙ ፡ ከማሁ ፡
ወፈጸሙ ፡ ስምዖሙ ፡ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡
፳፻ወ፲፱ቱ ፡ ነፍስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡
ምስሌነ፡ለዓለም፡አሜን።
፳፪፡ ወእምዝ፡አዘዘ፡አርያኖስ፡ከመ፡ይኰንንዎ፡
ለአባ፡አክሎግ፡ኵነኔ፡ጽኑዐ፡ወይሰድዎ፡
ኀበ ፡ ብሔሩ ፡ ወበህየ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡
በሰይፍ፡ወሶበ፡ሰምዐ፡አባ፡አክሎግ፡ዘንተ፡
ተፈሥሐ፡ፈድፋደ፡ወጸለየ፡ቀዊሞ፡እንዘ፡
ይብል ፡ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እስእለከ ፡ አነ ፡ ገብርከ ፡ ከመ ፡ ትረሲ ፡
ምሕረተከ ፡ ላዕለ ፡ ሀገርየ ፡ ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡

ግድም ፡ አሉት ፡ ራሶቻቸውንም ፡ በሰይፍ ፡
እንዲቆርጧቸው ፡ አዘዘና ፡ ቆረጧቸው ፡ የሰ
ማዕትነት፡አክሊልንም፡ተቀበሉ።
፲፱፡ በዚያንም፡ጊዜ፡የመኰንኑ፡የአርያኖስ፡ልጁ፡
ሞተበትና ፡ እጅግ ፡ አዘነ ፡ የከበረ ፡ አባ ፡
አክሎግም ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡
ብሠራ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብለም
ነው ፡ ልጅህን ፡ ቢያስነሣልህ ፡ ምን ፡ ትሰጠ
ኛለህ ፡ አለው ፡ አርያኖስም ፡ የመቶ ፡ አለቃ፡
አድርጌ፡ሹሜ፡በታላቅ፡ክብር፡ወደ፡ሀገርህ፡
እልክሃለሁ ፡ አለው ። የከበረ ፡ አክሎግም ፡
ይህን ፡ አልሻም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንድታሠቃ
የኝና ፡ እንድትገድለኝ ፡ ሥጋዬንም ፡ ወደ ፡
ሀገሬ ፡ እንደትልክ ፡ ማልልኝ ፡ አለው ፡ እር
ሱም ፡ ማለለት ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡
አክሎግ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡
ለመነ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡
ልመናዬን ፡ ትሰማኝ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ይህን ፡
የሞተውን ፡ ሕፃን ፡ ታስነሣው ፡ ዘንድ ፡ የከ
በረ ፡ ስምህም ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ እለምን
ሃለሁ ፡ ምስጋና ፡ ክብር ፡ ያንተ ፡ ነውና ፡
ለዘላለሙ፡አሜን።
፳፡ ይህንንም፡ሲል፡በመስቀል፡ምልክት፡በአብ፡
በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በሕፃኑ ፡
ላይ፡ አማተበ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሕፃኑ ፡ ተነሣ ፡
አሕዛብም፡ይህን፡ድንቅ፡ተአምር፡አይተው፡
ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ በቅዱስ ፡ አክሎግ ፡
አምላክ፡እናምናለን፡ብለው፡ጮኹ።
፳፩፡ መኰንኑም ፡ ተቆጣ ፡ ከከተማም ፡ እንዲአወ
ጧቸውና ፡ ሰፊ ፡ ጉድጓድ ፡ ቆፍረው ፡ እሳት
ንም ፡ አንድደው ፡ በውስጡ ፡ እንዲጨምሩ
ዋቸው፡አዘዘ፡እንዲሁም፡አደረጉባቸውና፡
ምስክርነታቸውን፡ፈጸሙ፡ቍጥራቸውም፡
ስምንት፡መቶ፡ዘጠኝ፡ሆነ፡በረከታቸውም፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፳፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ አክሎግን ፡ ጽኑዕ ፡
ሥቃይን ፡ አሠቃይተው ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡
ወስደው፡በዚያ፡በሰይፍ፡ራሱን፡ይቆርጡ፡
ዘንድ ፡ አርያኖስ ፡ አዘዘ ፡ አባ ፡ አክሎግም ፡
ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡
እንዲህ፡እያለ፡ቁሞ፡ጸለየ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ሆይ፡እኔ፡ባሪያህ፡እለምንሃለሁ፡
ቸርነትህን ፡ በሀገሬ ፡ ላይ ፡ በውስጧም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሰብእ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ። ወባርክ ፡
ግብረ፡እደዊሆሙ፡ወባርክ፡አንስቲያሆሙ፡
ወውሉዶሙ ፡ ወእንስሳሆሙ ፡ ወገራው
ሂሆሙ፡ወአድኅኖሙ፡እምኵሉ፡ምንዳቤ፡
ወሀቦ ፡ ጸጋ ፡ ለሥጋየ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይደዊ ፡
ወይመጽእ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ሥጋየ ፡ ወይጼሊ ፡
ኀቤከ ፡ ይሕየው ፡ እምደዌሁ ፡ እንዘ ፡
ይጼውዕ፡ስመከ፡ቅዱሰ።
፳፫፤ ወለኵሉ ፡ ዘይጽሕፍ ፡ መጽሐፈ፡ ገድልየ ፡
ወይገብር፡ተዝካርየ፡ወለዘይሁብ፡ቍርባነ፡
አው ፡ ዕጣነ ፡ አው ፡ ቅብዐ ፡ አው ፡ ወይነ ፡
ሀቦሙ፡ዐስቦሙ፡ለኵሎሙ፡በመንግሥተ፡
ሰማያት ፡ ወጸሐፍ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡
መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ለዘሂ ፡ ገነዘ ፡ ሥጋየ ፡
በልብስ ፡ ንጹሕ ፡ ክድና ፡ ለነፍሱ ፡ ልብሰ ፡
ብርሃን ፡ ወለከ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፳፬፤ወሶበ፡ይቤ፡ዘንተ፡አባ፡አክሎግ፡ናሁ፡አስተ
ርአዮ፡እግዚእነ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወይቤሎ፡
ሰላም ፡ ለከ ፡ ፍቁርየ ፡ ወፍቁረ ፡ አቡየ ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ መጻእኩ፡ኀቤከ፡ከመ፡
አሀብከ፡ዐስበከ፡ወአዐርፌከ፡ውስተ፡መንግ
ሥትየ፡ወአስተዳሎኩ፡ለከ፡፫ተ፡አክሊላተ፡
፩ዱ፡በእንተ፡ድንግልናከ፡ወካልኡ፡በእንተ፡
ኵነኔከ፡ወሣልሱ፡በእንተ፡ዘመነንከ፡ክብረ፡
ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወእገብር ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡
ዘኀሠሥከ፡እምኔየ፡በዛቲ፡ዕለት፡ህየንተ፡
ዘኰነኑከ ፡ በእንተ ፡ ስምየ ። አነ ፡ እሁበከ ፡
ተድላ ፡ ዘኢየኀልቅ ፡ ወእሬስዮሙ ፡ ለሠራ
ዊተ፡መላእክት፡ይትለአኩከ፡ወትትፌሣሕ፡
ምስለ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳን፡በውስተ፡ማዕድየ፡
ዘሕይወት፡ወለከ፡እብለከ፡ኦ፡ኅሩይየ፡አባ፡
አክሎግ፡እስመ፡ለኵሉ፡ዘይተነብል፡ኀበ፡
ሥጋከ፡ወየኃሥሥ፡ረድኤተ፡ለእመሂ፡ኮነ፡
ውስተ ፡ ምንዳቤ ፡ ወእመሂ ፡ ውስተ ፡ ደዌ ፡
ወኀዘን ፡ አነ ፡ አድኅኖ ፡ ወለኵሉ ፡ ዘይሰሚ ፡
ወልዶ ፡ በስምከ ፡ አነ ፡ እባርኮ ፡ ወአልሕቆ ፡
በሠናይ ፡ ወአዐቅቦ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡
ወለኵሉ ፡ ዘያበውእ ፡ መባአ ፡ ወለዘይሁብ ፡
ምጽዋተ ፡ ለጽኑሳን ፡ እስከ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡
ቈሪር ፡ በስምከ ፡ አነ ፡ እሰሪ ፡ ኃጢአቶ ፡
ወአወርሶ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ። ወለዘሂ ፡

በሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ላይ፡ታደርግ፡ዘንድ፡
የእጃቸውንም ፡ ሥራ ፡ ባርክ ፡ ሴቶቻቸውን ፡
ልጆቻቸውን ፡ እንስሶቻቸውን ፡ እርሻዎቻቸ
ውንም ፡ ባርክ ፡ ከመከራም ፡ ሁሉ ፡ አድና
ቸው፡ለሥጋዬም፡ጸጋህን፡ስጠው፡የታመመ፡
ሁሉ ፡ ሥጋዬ ፡ ወደላበት ፡ መጥቶ ፡ የከበረ ፡
ስምህን ፡ ጠርቶ ፡ ወዳንተ ፡ በሚጸልይ፡ ጊዜ ፡
ከደዌው፡ይዳን።
፳፫፤የተጋድሎዬን ፡ መጽሐፍ ፡ የሚጽፈውን ፡
ሁሉ ፡ መታሰቢያዬንም ፡ ለሚያደርግ ፡ ለቍ
ርባንም፡ሥንዴን፡የሚሰጥ፡ወይም፡ዕጣንን፡
ወይም ፡ ዘይትን ፡ ወይም ፡ ወይንን ፡ ለሚሰጥ ፡
ለሁሉም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዋጋ
ቸውን ፡ ስጣቸው ፡ ስሞቻቸውንም ፡ በሕይ
ወት ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፍላቸው ፡ ሥጋዬንም ፡
በንጹሕ ፡ ልብስ ፡ የሚገንዘውን ፡ ነፍሱን ፡
የብርሃን ፡ ልብስን ፡ ሸፍናት ፡ ለአንተም ፡
ምስጋና፡ክብር፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፳፬፤ አባ ፡ አክሎግም ፡ ይህን ፡ በአለ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡
የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ፡ ተገለጸለትና፡እንዲህ፡አለው።ወዳጄ፡
የምወድህ ፡ የአባቴና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ወዳጅ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ዋጋህን፡
ልሰጥህ፡በመንግሥቴም፡ውስጥ፡ላሳርፍህ፡
መጣሁ ፡ ሦስት ፡ አክሊላትንም ፡ አዘጋጀ
ሁልህ፡አንዱ፡ስለ፡ድንግልናህ፡ሁለተኛው፡
ስለ፡ሥቃይህ፡ሦስተኛው፡የዚህን፡ዓለም፡
ክብር፡ንቀህ፡ስለተውህ፡ነው።በዚች፡ቀን፡
ከእኔ፡የምትሻውን፡ሁሉ፡አደርግልሃለሁ፡
ስለ ፡ ስሜ ፡ ስለአሠቃዩህ ፡ የማያልቅ ፡ ተድ
ላን ፡ እስጥሃለሁ ፡ የመላእክት ፡ ሠራዊትም ፡
እንዲአገለግሉህ ፡ አደርጋለሁ ፡ ዘላለማዊ ፡
ሕይወት፡ባለው፡በማዕዴ፡ውስጥም፡ከሁሉ፡
ቅዱሳን ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይልሃል ። የመረጥኩህ ፡
አክሎግ፡ሆይ፡አንተን፡እነግርሃለሁ፡ሥጋህ፡
ባለበት፡የሚማልደውን፡ሁሉ፡ርዳታ፡የሚሻ
ውንም ፡ በችግር ፡ ውስጥም ፡ ወይም ፡ በደዌ ፡
ውስጥ፡በኀዘንም፡ላይ፡ሁለንም፡እኔ፡አድና
ቸዋለሁ፡ልጁንም፡በስምህ፡የሚሰይመውን፡
ሁሉ፡እኔ፡እባርከዋለሁ፡በበጎ፡አስተዳደግም፡
አሳድገዋለሁ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እጠብቀ
ዋለሁ ፡ በስምህም ፡ መባ ፡ የሚአገባና ፡ ለችግ
ረኞችም ፡ እስከ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ምጽዋት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐት፡ለዓለም፡አሜን።

፬፡ ወሶቤሃ፡ፆረቶ፡ደመና፡ለዮሐንስ፡በትእዛዘ፡
መንፈስ፡ቅዱስ፡እምሀገረ፡ኤፌሶን፡ወአብ
ጽሐቶ፡ኀበ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ወሰገደ፡
ላቲ፡ወቆመ፡ቅድሜሃ፡ወይቤላ፡ሰላም፡ለኪ፡
ተፈሥሒ፡ኦ፡ምልእተ፡ጸጋ፡ዘወለድኪዮ፡
ለእግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እስመ፡አንቲ፡ትወጽኢ፡እም
ዝንቱ፡ዓለም፡በዐቢይ፡ክብር፡ወስብሐት፡
ወተሐውሪ፡ውስተ፡ሕይወት፡ዘለዓለም።
ዝንቱኒ፡እምድኅረ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡
ዘይከሥት፡ላዕሌኪ፡ስቡሕ፡ወቅዱስ፡ስሙ፡
እግዚእነ፡ወአምላክነ።

፭፡ ወሶበ፡ሰምዓት፡ዘንተ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡ተፈሥሐት፡ፈድፋደ፡
ወሰብሐቶ፡ለእግዚአብሔር፡እንዘ፡ትብል፡
ስብሐት፡ለከ፡እግዚእየ፡ወአምላኪየ፡እስመ፡
አንተ፡ወሀብከኒ፡ዘሰአልኩከ፡ወይእዜኒ፡
ጸግወኒ፡በምጽአትከ፡ምስለ፡መላእክቲከ፡
ከመ፡ይንሥእዋ፡ለነፍየ፡ወያዕርግዋ፡ውስተ፡
ሰማይ፡ኀቤከ።

፮፡ ወሶቤሃ፡ተሰምዐ፡ቃል፡ዘይብል፡እምሰማይ፡
ናሁ፡ይበጽሑ፡መላእክት፡ወሐዋርያት፡እምአ
ጽናፈ፡ምድር፡እንዘ፡ይጼዓኑ፡ደመና፡
ወይበጽሑ፡ኀበ፡ቅድስት፡ድንግል፡እሙ፡
ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እግዚአ፡ሰማይ፡ወም
ድር፡ወበጊዜሃ፡በጽሑ፡ኵሎሙ፡ሐዋርያት፡
ወእለኒ፡አዕረፉ፡እመቃብሪሆሙ፡ተንሥኡ፡
ወበጽሑ፡ኀበ፡እግዝእትነ፡ወሰገዱ፡ላቲ፡
ወይቤልዋ፡ተፈሥሒ፡ኦ፡ምልዕተ፡ጸጋ፡
ዘተወልደ፡እምኔኪ፡አምላክነ፡ውእቱ፡
ያወጽአኪ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ወያዐርገኪ፡
ምስሌሁ፡በክብር፡ወበስብሐት፡በከመ፡
ተካየደኪ።

፯፡ ወሶቤሃ፡ነበረት፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ዲበ፡
ዐራታ፡ወትቤሎሙ፡ለሐዋርያት፡ይእዜ፡
አእመርኩ፡ከመ፡አምላኪየ፡ወአምላክክሙ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ይመጽእ፡ወእሬእዮ፡
በከመ፡ርኢክሙ፡ወእወጽእ፡እምዝንቱ፡
ሥጋየ፡ወአሐውር፡ውስተ፡ሕይወት፡ዘለዓለም፡
ወባሕቱ፡እፈቅድ፡ከመ፡ትንግሩኒ፡እምአይቴ፡
አእመርክሙ፡ከመ፡እትፈለጥ፡እምዝንቱ፡

ላንተም፡ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

፬፡ በዚያንም፡ጊዜ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ትእዛዝ፡
ከኤፌሶን፡አገር፡ዮሐንስን፡ደመና፡ተሸክማ፡
ወደ፡እመቤታችን፡ማርያም፡አደረሰችው፡
ሰገደላትና፡በፊቷ፡ቁሞ፡እንዲህ፡አላት፡
ሰላምታ፡ይገባሻል፡ጌታችንን፡ፈጣሪያች
ንንና፡መድኃኒታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡
የወለድሺው፡ጸጋን፡የተመላሽ፡ደስ፡ይበልሽ፡
አንቺ፡ከዚህ፡ዓለም፡ተለይተሽ፡በክብር፡
በምስጋና፡ወደ፡ዘላለም፡ሕይወት፡ትሔጂአ
ለሽና። ይህም፡ስሙ፡ክቡር፡ምስጉን፡የሆነ፡
ጌታችንና፡ፈጣሪያችን፡ድንቆች፡ተአምራ
ቶችን፡በአንቺ፡ላይ፡ከገለጠ፡በኋላ፡ነው።

፭፡ እመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያምም፡
ይህን፡በሰማች፡ጊዜ፡እጅግ፡ደስ፡አላት፡እግ
ዚአብሔርምንም፡እንዲህ፡ብላ፡አመሰገ
ነችው፡ፈጣሪዬ፡ጌታዬ፡ላንተ፡ምስጋና፡
ይሁን፡አንተ፡የለመንኩህን፡ሰጥተኸኛልና፡
አሁንም፡ነፍሴን፡ተቀብለው፡ወደ፡ሰማይ፡
ወደ፡አንተ፡ሊአሳርጓት፡ከሚመጡ፡መላእከ
ቶችህ፡ጋር፡በመምጣትህ፡የምለምንህን፡
ሁሉ፡ስጠኝ።

፮፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ከሰማይ፡እንዲህ፡የሚል፡
ቃል፡መጣ፡እነሆ፡አሁን፡መላእክት፡
ይደርሳሉ፡ሐዋርያትም፡ሁሉ፡ከምድር፡
ዳርቻ፡በደመና፡ተጭነው፡ለሰማይና፡
ለምድር፡ጌታ፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እናቱ፡
ወደ፡ሆነች፡ወደ፡ቅድስት፡ድንግል፡
ይደርሳሉ። ወዲያውኑ፡ሁሉም፡ሐዋርያት፡
የሞቱትም፡ከመቃብራቸው፡ተነሥተው፡
ወደ፡እመቤታችን፡ደርሰው፡ሰገዱላት፡አም
ላካችን፡ከአንቺ፡የተወለደ፡ጸጋን፡የተመላሽ፡
ሆይ፡ደስ፡ይበልሽ፡እርሱ፡ከዚህ፡ዓለም፡
ለይቶ፡ቃል፡ኪዳን፡እንደሰጠሽ፡በክብር፡
በምስጋና፡ከርሱ፡ጋር፡ያሳርግሻልና፡አሏት።

፯፡ በዚያንም፡ጊዜ፡እመቤታችን፡በዐልጋዋ፡ላይ፡
ተቀመጠች፡ሐዋርያትንም፡እንዲህ፡አለቻ
ቸው፡ፈጣሪዬ፡ፈጣሪያችሁ፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስ፡እንደሚመጣ፡እናንተንም፡እንዳየ
ኋችሁ፡እንደማየው፡አሁን፡አውቅሁ፡ከዚህ፡
ከሥጋዬም፡ወጥቼ፡ወደዘላለም፡ሕይወት፡
እሔዳለሁ፡ነገር፡ግን፡ትነግሩኝ፡ዘንድ፡
እሻለሁ፡ከዚህም፡ዓለም፡እንደምለይ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ፡ወይቤልዋ፡ ጴጥሮስ ፡ ወኵሎሙ ፡
ሐዋርያት ፡ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አዘዘነ ፡
ከመ ፡ ንብጻሕ ፡ ኀቤኪ ፡ ወሶበ ፡ ተፅዕነ ፡ ዲበ ፡
ደመና፡በጺሕነ፡ኀቤኪ፡ከመ፡ቅጽበት።

፰፡ ወሶበ ፡ ሰምዐት ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ዘንተ፡
ነገረ ፡ እምነ ፡ ሐዋርያት ፡ አልዓለት ፡ ቃላ ፡
ወትቤ፡እሴብሕ፡ወእዜምር፡ለስምከ፡ቅዱስ፡
ኦ፡እግዚእየ፡ወአምላኪየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
እስመ ፡ አንተ ፡ ርኢከ ፡ ሕማማ ፡ ለአመትከ ፡
ወገበርከ ፡ ላቲ ፡ ኃይለ ፡ ወመንክረ ፡ ወእመይ
እዜሰ፡ያስተበፅዑኒ፡ኵሉ፡ትውልድ።

፱፡ወፈጸማ፡ጸሎታ፡ወስብሐታ፡ትቤሎሙ፡ለሐ
ዋርያት ፡ አምጽኡ ፡ ዕጣነ ፡ ወማዕጠንተ ፡
ወጸውዕዎ ፡ ለእግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ወእሙንቱ ፡ ገብሩ ፡ በከመ ፡ አዘዘቶሙ ።
ወሶቤሃ ፡ መጽአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡እንዘ፡የዓውድዎ፡ወይ
ሴብሕዎ ፡ እልፍ ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡
መላእክት፡ወናዘዛ፡ለእግዝእትነ፡ወአይድዓ፡
ዘአስተዳለወ ፡ ላቲ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ወውእተ ፡
ጊዜ ፡ ኮና ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ብዙ
ኃት፡ እስመ ፡ ዕውራን ፡ ርእዩ ፡ ወሐንካሳን ፡
ረትዑ ፡ ወጽሙማን ፡ ሰምዑ ፡ ወእለ ፡ ለምፅ፡
ነጽሑ ፡ ወአጋንንት ፡ ወጽኡ ፡ እምሰብእ ፡
ወሐሩ፡ወበሐማን፡ነበቡ፡ወኵሉ፡ዘቦ፡ደዌ፡
ወሕማም፡ድኅነ፡ወሶበ፡ይቀረቡ፡ኀበ፡ቤት፡
ዘሀለወት ፡ ቦቱ ፡ እግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ ማር
ያም፡ይትፌወሱ፡እምደዌሆሙ፡ሶቤሃ።
፲፡ወእምዝ፡ትቤሎ፡እግዝእትነ፡ለወልዳ፡ፍቁር፡
ኦ ፡ ወልድየ ፡ ፍቁርየ ፡ እፈርህ ፡ አንሰ ፡ እመላ
እክት፡ግሩማን፡ወመደንግፃን፡እለ፡ዝርዋን፡
ውስተ ፡ አየር ፡ ወእምበሐረ ፡ እሳት ፡ ወይቤላ ፡
እግዚእነ፡አልቦ፡ለመኑሂ፡ሥልጣን ላዕሌኪ፡
እምኔሆሙ።
፲፩፡ወሶበ፡ቀርበ፡ፈሊሶታ፡እምሥጋሃ፡ሰአልዋ፡
ሐዋርያት፡ወደናግል፡እንዘ፡ይበክዩ፡ከመ፡
ትባርኮሙ፡ወአንበረት፡እዴሃ፡ላዕሌሆሙ፡
ወባረከቶሙ ፡ ወሶቤሃ ፡ ነሥአ ፡ ነፍሳ ፡
ንጽሕተ ፡ በእደዊሁ ፡ መለኮታዊት ፡ ወገ
ልበባ፡በብርሃን፡ወአዕረጋ፡ምስሌሁ፡ኀበ፡
ማኅደር ፡ ሉዓላዊ ፡ ወለሥጋሃሰ ፡ አዘዞሙ ፡

ከወዴት፡አወቃችሁ። ጴጥሮስና፡ሐዋርያት፡
ሁሉ ም ፡ወዳንቺ፡እንመጣ፡ዘንድ፡ መንፈስ፡
ቅዱስ ፡ አዘዘን ፡ በደመና ፡ ላይም ፡ በተጫን ፡
ጊዜ ፡ ወዳንቺ ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ ፈጥነን ፡
ደረስን፡አሏት።
፰፡እመቤታችን፡ማርያምም፡ይህን፡ነገር፡ከሐዋ
ርያት፡በሰማች፡ጊዜ፡ድምጿን፡ከፍ፡አድርጋ፡
እንዲህ፡አለች፡ጌታዬና፡ፈጣሪዬ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ክቡር ፡ ምስጉን ፡ የሆነ ፡
ስምህን፡ፈጽሜ፡አመሰግናለሁ።የእኔን፡የአገ
ልጋይህን፡መከራ፡ተመልክተህ፡ድንቅ፡ኃይ
ልን ፡ አድርገህልኛልና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡
ትውልድ፡ሁሉ፡ያከብሩኛል፡ያመሰግኑኛል።
፱፡ ጸሎቷንና ፡ ምስጋናዋን ፡ ስትጨርስ ፡ ሐዋር
ያትን ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ፡ ዕጣን ፡ አምጥ
ታችሁ ፡ በማጠን ፡ የጌታዬን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስን ፡ ስሙን ፡ ጥሩት ፡ እነርሱም ፡ እንዳዘዘ
ቻቸው ፡ አደረጉ ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡
ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እልፍ፡
አእላፋት፡መላእክት፡አጅበው፡እያመሰገኑት፡
መጣና ፡ አረጋጋት ፡ ያዘጋጀላትንም ፡ ተድላ ፡
ደስታ፡ነገራት፡በዚያንም፡ብዙዎች፡ድንቆች፡
ተአምራቶች፡ተደረጉ፡ዕውሮች፡አይታዋልና፡
ሐንካሶች፡ቀንተው፡ሒደዋልና፡ደንቆሮዎች፡
ሰምተዋልና ፡ ለምጻሞች ፡ ነጹ ፡ አጋንንትም ፡
ከሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ሔዱ ፡ ዲዳዎች ፡ ተናገሩ ፡
በሽታና ፡ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ሁሉ ፡ ዳነ ፡ እመቤታ
ችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወዳለችበት ፡ ቤት ፡
በቀረቡ፡ጊዜ፡ከደዌያቸው፡ይፈወሳሉና።

፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡እመቤታችን ፡ ተወዳጅ ፡
ልጅዋን፡እንዲህ፡አለችው፡በአየር፡ውስጥ፡
ተበትነው፡ከሚኖሩ፡ከሚያስደነግጡ፡ግሩማን፡
መላእክት፡የተነሣ፡ከእሳት፡ባሕርም፡እፈራ
ለሁ፡ጌታችንም፡ከእርሳቸው፡ለማንም፡በእ
ንቺ፡ላይ፡ሥልጣን፡የለውም፡አላት።
፲፩፡ ከሥጋዋም ፡ የምትለይበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡
ሐዋርያትና ፡ ደናግል ፡ ትባርካቸው ፡ ዘንድ ፡
እያለቀሱ ፡ ለመኑዋት ፡ እጅዋን ፡ በላያቸው ፡
ዘርግታ ፡ ባረከቻቸው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡
ጌታችን፡ንጽሕት፡ነፍሷን፡ከሥጋዋ፡ለይቶ፡
በመለኮታዊ ፡ እጆቹ ፡ ይዞ ፡ በብርሃን ፡ ልብስ ፡
አገናጽፎ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ መኖሪያ ፡ ከእርሱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለሐዋርያት፡ከመ፡ይግንዝዋ፡በከመ፡ይደሉ፡
ወይፁርዋ፡ኀበ፡ጌቴሴማኒ።

፲፪፡ ወእምቅድመ፡ጻአተ፡ነፍሳ፡ነበረት፡እግዝ
እትነ፡እንዘ፡ትሬኢ፡ብርሃነ፡ዐቢየ፡ዘኢይት
ነገር፡በልሳነ፡ሰብእ። ወይቤላ፡እግዚእነ፡
ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ እምይእዜሰ፡
አፈልስ፡ሥጋኪ፡ኀበ፡ገነተ፡ትፍሥሕት፡
ወዓዲ፡አነሥእ፡ሥጋኪ፡ምስለ፡ነፍስኪ፡
ወእሬስየኪ፡ውስተ፡ማኅደረ፡ተድላ፡ዘአ
ልቦ፡መምስል፡ዘውስቴቱ፡ይሴብሑ፡መላ
እክት፡በቅድሜኪ።

፲፫፡ ወትቤሎ፡እግዝእትነ፡አእኵተከ፡እግዚኦ፡
ዘገበርከ፡ዘንተ፡ኵሎ፡በኪነ፡ጥበብከ፡ወእስ
እለከ፡ካዕበ፡ከመ፡ትስማዕ፡ስእለትየ፡እስመ፡
ለኵሉ፡ዘይስእል፡ኀቤከ፡በስምየ፡ተወከፍ፡
ስእለቶ፡በግህልከ፡ወለኵሉ፡ዘሀሎ፡ውስተ፡
ምንዳቤ፡ወይስእል፡ኀቤከ፡በስምየ፡አድኅኖ፡
እምኵሉ፡ምንዳቤሁ፡እስመ፡አንተ፡ከሀሊ፡
ላዕለ፡ኵሉ፡ግብር፡በሰማይኒ፡ወበምድርኒ፡
ወባርክ፡ላዕለ፡ኵሉ፡መካን፡እለ፡ይገብሩ፡
ውስቴታ፡ ተዝካርየ፡ ወተወከፍ፡ ቍርባ
ኖሙ፡ለኵሎሙ፡እለ፡ያቄርቡ፡በስምየ።

፲፬፡ ወአውሥአ፡እግዚእነ፡ወይቤላ፡ናሁ፡እገብር፡
ለኪ፡ኵሎ፡ዘሰአልክኒ፡ተፈሥሒ፡እስመ፡
ኵሉ፡ጸጋ፡ወክብር፡ወሞገስ፡ተውህበ፡ለኪ፡
እምኀቤየ፡ወእምኀበ፡አቡየ፡ወመንፈስ፡
ቅዱስ፡ እስመ፡ኵሉ፡ዘይስእል፡በስምኪ፡ኢይ
ትሀጐል፡ በዝ፡ ዓለም፡ ወበዘይመጽእኒ፡
ዓለም።

፲፭፡ ወእምድኅረ፡አዕረፈት፡እግዝእትነ፡ገነዝዋ፡
ሐዋርያት፡ ወፆርዋ፡ ዲበ፡ ዐራት፡ ከመ፡
ይሰድዋ፡ ኀበ፡ ጌቴሴማኒ፡ በከመ፡ አዘዘ፡
እግዚእነ። ወሰሚዖሙ፡አይሁድ፡ወጽኡ፡
ከመ፡ ያውዕዩ፡ ሥጋሃ፡ ወአሐዱ፡ እም
ኔሆሙ፡ አኀዘ፡ዐራታ፡ለእግዝእትነ፡ከመ፡
ይገራ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ሶቤሃ፡ ዘበጦ፡
መልአከ፡እግዚአብሔር፡ እደዊሁ፡በሰይፈ፡
እሳት፡ወኮኑ፡ስቁላነ፡ዲበ፡ዐራታ። አሜሃ፡

ጋር፡አሳረጋት፡ሥጋዋን፡ግን፡እንደሚገባ፡
ገንዘው፡ወደ፡ጌቴሴማኒ፡ተሸክመው፡እንዲ
ወስዷት፡ሐዋርያትን፡አዘዛቸው።

፲፪፡ ነፍሷ፡ከሥጋዋ፡ከመውጣቷ፡በፊት፡በሰው፡
አንደበት፡ ይህ፡ ነው፡ ተብሎ፡ የማይነገር፡
ብርሃንን፡ እያየች፡ ነበር፡ የክብር፡ ባለቤት፡
ጌታችን፡ክርስቶስም እንግዲህ፡ሥጋሽን፡
ተድላ፡ ወዳለበት፡ ገነት፡ አፈልሳለሁ፡
ዳግመኛም፡ ሥጋሽን፡ ከነፍስሽ፡ ጋር፡
አዋህጄ፡ አስነሥቼ፡ መላእክት፡ በውስጡ፡
በፊትሽ፡ ሁነው፡ በሚያመሰግኑበት፡ ተመ
ሳሳይ፡ በሌለው፡ ተድላ፡ ደስታ፡ በአለበት፡
ማደሪያ፡አኖርሻለሁ፡አላት።

፲፫፡ እመቤታችንም፡ እንዲህ፡ አለች፡ አቤቱ፡
በረቀቀ፡ ጥበብህ፡ ይህን፡ ሁሉ፡ የሠራህ፡
አመሰግንሃለሁ፡ ሁለተኛም፡ ልመናዬን፡
ትሰማ፡ ዘንድ፡ እለምንሃለሁ፡ በስሜ፡
ወዳንተ፡የሚለምነውን፡ሁሉ፡ልመናውን፡
ተቀበለው፡ በመከራም፡ ውስጥ፡ ሁኖ፡
ስሜን፡ ጠርቶ፡ ወዳንተ፡ የሚለውነውን፡
ከመከራው፡ ሁሉ፡ አድነው፡ በሰማይም፡
በምድርም፡ በሥራው፡ ላይ፡ ሁሉ፡ አንተ፡
ከሀሊ፡ ነህና፡ መታሰቢያዬን፡ በውስጧ፡
የሚያደርጉባትን፡ቦታ፡ሁሉ፡ባርክ፡በእኔ፡
ስም፡የሚያቀርቡትን፡የሁሉንም፡መሥዋዕ
ታቸውን፡ተቀበል።

፲፬፡ ጌታችንም፡እንዲህ፡ብሎ፡መለሰላት፡የለመ
ንሺኝን፡ ሁሉ፡ አደርግልሻለሁ፡ ደስ፡
ይበልሽ፡ከእኔ፡ከአባቴ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡
ዘንድ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ ባለሟልነት፡ ተሰጥቶ
ሻልና፡ስምሽንም፡ጠርቶ፡የሚለምን፡ሁሉ፡
በዚህም፡ ዓለም፡ በሚመጣውም፡ ዓለም፡
አይጠፋም።

፲፭፡ እመቤታችንም፡ከአረፈች፡በኋላ፡ጌታችን፡
እንዳዘዘ፡ ወደ፡ ጌቴሴማኒ፡ ሊወስዷት፡
ሐዋርያት፡ ገንዘው፡ ተሸከሟት። አይሁ
ድም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ሥጋዋን፡ ሊአቃጥሉ፡
ወጡ፡ ከእርሳቸው፡ አንዱ፡ ከምድር፡ ላይ፡
ይጥላት፡ ዘንድ፡ የእመቤታችንን፡ ዐልጋዋን፡
ያዘ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ የታዘዘ፡
መልአክ፡ እጆቹን፡ በእሳት፡ ሰይፍ፡ ቀጣ
ውና፡እጆቹ፡በዐልጋዋ፡ላይ፡ተንጠለጠሉ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አምነ፡በእግዚእነ፡ወሰአለ፡እምኀበ፡እግዝ
እትነ፡በአንብዕ፡እንዘ፡ይብል፡በአማን፡
አንቲ፡ድንግል፡እሙ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡አምላክ፡ዘበአማን፡እስእለኪ፡
ከመ፡ትጣሃሊ፡ላዕሌየ፡ወበእንተ፡ስእለ
ቶሙ፡ለሐዋርያት፡ተመይጡ፡እደዊሁ፡
ከመ፡ቀዳሚ፡ኮኑ፡ድኍናነ።

፲፮፤ ወሶበ፡ቀበርዋ፡ነበሩ፡ህየ፡ሠለስተ፡
መዓልተ፡ወዕረፍታ፡ዘኮነ፡በዕለተ፡እሑድ፡
አመ፡፳ወ፩ ለወርኀ፡ጥር፡በዛቲ፡ዕለት፡
ወፈነወ፡እግዚእነ፡መላእክተ፡ብርሃና
ውያነ፡ወእሙንቱ፡ነሥኡ፡ሥጋሃ፡እመ
ቃብር፡ወአንበርዋ፡ታሕተ፡ዕፀ፡ሕይወት፡
ውሳጤ፡ገነት።

፲፯፤ ወቶማስሰ፡ሐዋርያ፡ኢሀሎ፡አሚሃ፡ወእንዘ፡
ውእቱ፡ይመጽእ፡ተጽዒኖ፡ላዕለ፡ደመና፡
ወረከባ፡ለእግዝእትነ፡እንዘ፡ያዐርግዋ፡
መላእክት፡ወይቤልዎ፡መላእክት፡ነዓ፡
አምኃ፡ለእመ፡አምላክ፡እግዝእትነ፡
ግል፡ማርያም፡ውእቱኒ፡ሰገደ፡ላቲ፡
ወተአምኃ፡ወተባረከ፡እምኔሃ። ወእምዝ፡
በጽሐ፡ኀበ፡ሐዋርያት፡ወእምንቱ፡ነገርዎ፡
በእንተ፡ዕረፍታ፡ወዘከመ፡ቀበርዋ፡ለእግዝ
እትነ፡ማርያም። ወይቤሎሙ፡ቶማስ፡
አንሰ፡ኢየአምን፡እስከ፡እሬኢ፡ሥጋሃ፡
ወሶበ፡አብጽሕዎ፡ኀበ፡መቃብራ፡ከመ፡
ያርእይዎ፡ሥጋሃ፡ኢረከቡ፡ሥጋሃ፡ውስተ፡
መቃብር፡ደንገፁ፡ወአንከሩ፡ውእተ፡ጊዜ፡
ነገሮሙ፡ቶማስ፡ከመ፡ረከባ፡ለእግዝእትነ፡
እንዘ፡**ተዐርግ**፡ሰማየ፡ምስለ፡መላእክት፡
ወሰሚዖሙ፡ሐዋርያት፡ዘንተ፡ኀዘኑ፡
ፈድፋደ፡በእንተ፡ዘኢርእዩ፡ዕርገታ፡ለእግ
ዝእትነ፡ወአለበዎሙ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ከመ፡ኢፈቀደ፡ይኅድግ፡ሥጋሃ፡ውስተ፡
ምድር። ወእምዝ፡ተካየዶሙ፡ወአስ
ፈዎሙ፡እግዚእነ፡ከመ፡ሀለዎ፡ያርእዮሙ፡
ኪያሃ፡ምእረ፡ዳግመ፡ወእሙንቱ፡ነበሩ፡
እስከ፡አመ፡፲ወ፮ለነሐሴ።

፲፰፤ ወኮነ፡መዋዕሊሃ፡ለእግዝእትነ፡፷ወ፬
በቤተ፡አቡሃ፡ወእማ፡፫ተ፡ዓመተ፡

ያን፡ጊዜ፡በጌታችን፡አምኖ፡ወደ፡እመቤ
ታችን፡እያለቀሰ፡እንዲህ፡ብሎ፡ለመነ፡የእ
ውነተኛ፡አምላክ፡የጌታ፡ኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡እናት፡አንቺ፡በእውነት፡ድንግል፡
የሆንሽ፡በእኔ፡ላይ፡ይቅርታ፡ታደርጊ፡
ዘንድ፡እለምንሻለሁ፡በሐዋርያትም፡
ልመና፡እጆቹ፡ተመልሰው፡እንደቀድሞው፡
ደኅነኞች፡ሆኑ።

፲፮፤በቀበሩዋትም፡ጊዜ፡ከዚያ፡ሦስት፡ቀን፡ኖሩ፡
ዕረፍቷም፡የሆነው፡እሑድ፡ቀን፡በጥር፡
ወር፡በሃያ፡አንድ፡በዚች፡ቀን፡ነበረ፡
ጌታችንም፡ብርሃናውያን፡መላእክትን፡ላከ፡
እነርሱም፡ሥጋዋን፡ከመቃብር፡ወስደው፡
በገነት፡ውስጥ፡በዕፀ፡ሕይወት፡ሥር
አኖሩዋት።

፲፯፤ሐዋርያ፡ቶማስ፡ግን፡ያን፡ጊዜ፡አልነበረም፡
በደመና፡ላይ፡ተጭኖ፡እርሱ፡ሲመጣ፡
መላእክት፡ሲአሳርጓት፡እመቤታችንን፡
አገኛት፡መላእክትም፡ለአምላክ፡እናት፡ለእ
መቤታችን፡ድንግል፡ማርያም፡ና፡እጅ፡
ንሣ፡አሉት፡እርሱም፡ሰገደላትና፡
ተሳለማት፡ከእርሷም፡ተባረከ፡ከዚህም፡
በኋላ፡ወደ፡ሐዋርያት፡ደረሰ። እነርሱም፡
እመቤታችንን፡ማርያምን፡እንደ፡አረፈችና፡
እንደ፡ቀበሩዋትም፡ነገሩት፡ቶማስም፡
ሥጋዋን፡እስከማይ፡አላምንም፡አላቸው።
ሥጋዋንም፡ያሳዩት፡ዘንድ፡ወደ፡
መቃብርዋ፡በአደረሱት፡ጊዜ፡በመቃብር፡
ውስጥ፡ሥጋዋን፡አላገኙም፡ደንግጠውም፡
አደነቁ፡ያን፡ጊዜ፡ከመላእክት፡ጋር፡ወደ፡
ሰማይ፡ስታርግ፡እመቤታችንን፡እንዳ
ገኛት፡ቶማስ፡ነገራቸው። ሐዋርያትም፡
ይህን፡በሰሙ፡ጊዜ፡የእመቤታችንን፡
ዕርገቷን፡ስለ፡አላዩ፡እጅግ፡አዘኑ፡ሥጋ
ዋን፡በምድር፡ውስጥ፡ይተው፡ዘንድ፡እንዳ
ልወደደ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡አስገነዘባቸው።
ከዚህም፡በኋላ፡አንድ፡ጊዜ፡ደግሞ፡እር
ሷን፡ያሳያቸው፡ዘንድ፡እንዳለው፡ጌታችን፡
ቃል፡ኪዳን፡በማድረግ፡ተስፋ፡ሰጣቸው፡
እነርሱም፡እስከ፡ነሐሴ፡ዐሥራ፡ስድስት፡
በተስፋ፡ኖሩ።

፲፰፤የእመቤታችንም፡የዕድሜዋ፡ዘመን፡ስሳ፡
አራት፡ዓመት፡ነው፡በአባትና፡እናቷ፡ቤት፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሰብዓተ ፡ አውራኀ ፡ ወበቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ዓመተ ፡ ወበቤተ ፡ ዮሴፍ ፡ ሠላሳ ፡ ወአርባዕተ ፡ ዓመተ ፡ ወሠለስተ ፡ አውራኀ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዐሥርተ ፡ ወአርባዕተ ፡ ዓመተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ።

፲፱፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘወሀበነ ፡ ኪያሃ ፡ እሞ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወት ፡ ወመድኃኒት ፡ ወበጸሎታ ፡ ይዕቀበነ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በዮሴፍም ፡ ቤት ፡ ሠላሳ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ከጌታ ፡ ዕርገት ፡ በኋላ ፡ በወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ ቤት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፱፤ የሕይወት ፡ የድኅነት ፡ አለኝታ ፡ የሆነች ፡ እርሷን ፡ እናቱን ፡ ለሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በጸሎቷም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ይጠብቀን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጸአተ ፡ ነፍስኪ ፡ እንዘ ፡ ድንጋጼ ፡ ሞት ፡ አልባ ። በመዓዛ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕቱ ፡ ዘይጼኑ ፡ እምስሂነ ፡ ሳባ ። ሀበታተ ፡ ጸጋኪ ፡ ማርያም ፡ እስመ ፡ እማንቱ ፡ ተውህባ ። ውዳሴ ፡ ዚአኪ ፡ አህጉራተ ፡ ዓለም ፡ የበባ ። ወስብሐተኪ ፡ ሰማያት ፡ ነበባ ።

ሰላም ፡ ለጸአት ፡ ነፍስኪ ፡ በመዓዛ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተነቅበ ። ወመሰንቆ ፡ ማኅሌት ፡ ሐዋዝ ፡ እንዘ ፡ ያመዓርር ፡ አልባበ ። ሐራ ፡ ሰማይ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ሐሳበ ። እንዘ ፡ ይዜምሩ ፡ ቅድሜኪ ፡ ወመንገለ ፡ ድኅሬኪ ፡ ካዕበ ። ማርያም ፡ ሞትኪ ፡ ይመስል ፡ ከብካበ ።

ግንዘታ ፡ ለማርያም ፡ ድኅረ ፡ ኀቡረ ፡ ሠለጡ ። በትእዘዘ ፡ ወልዳ ከሀሊ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጡ ። ነፍሳ ፡ ባሕርየ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ተውላጡ ። ዮም ፡ መላእክት ፡ መንገለ ፡ አርያም ፡ መሠጡ ። ወበድነ ፡ ሥጋሃ ፡ ሐዋርያት ፡ ጌቴሴማን ፡ ሶጡ ።

ሰላም ፡ እብል ፡ ለዘደብረ ፡ ማሕው ፡ ተርእዮታ ። በዘዮም ፡ ዕለተ ፡ ዕረፍታ ። ማርያም ፡ ድንግል ፡ ኀበ ፡ ይሴባሕ ፡ ምሕረታ ። ትደምር ፡ ነፍሰ ፡ ዚአየ ፡ ምስለ ፡ ጻድቃን ፡ በቤታ ። በእንተ ፡ ጌጋያ ፡ ኢትንበር ፡ ባሕቲታ ።

፳፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ቅድስት ፡ ኢላርያ ፡ ወለተ ፡ ዘይኑን ፡ ንጉሥ ፡ ዘሀገረ ፡ ሮሜ ።

፳፩፤ አቡሃሰ ፡ ለይእቲ ፡ ቅድስት ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ወመፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወወለደ ፡ ክልኤተ ፡ አዋልደ ፡ ዛተኒ ፡ ቅድስተ ፡ ኢላርያሃ ፡ ወካልዕታ ፡ ወአልቦ ፡ ወልድ ፡ ተባእት ፡ ዘእንበሌሆን ።

፳፪፤ ወኮነት ፡ ዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ኢላርያ ፡ ዘትፈቱ ፡ ትልበስ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወአስኬማ ፡ ዘመላእክት ፡ ወወጽአት ፡ እምቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወወለጠት ፡ አልባሲሃ ፡ ወለብሰት ፡ አልባሰ ፡ ዕደው ፡ ወሖረት ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወእምህየ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወበህየ ። ረከበቶ ፡ ለአሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ፍጹም ፡ አረጋዊ ፡ ዘስሙ ፡ አባ ፡ ባውሚን ፡ ወነገረቶ ፡ ሕሊናሃ ፡ ወአጠየቀቶ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ውእቱኒ ፡ ነብአ ፡ ምሥጢራ ፡ ወአብአ ፡ ውስተ ፡ በዓት ፡ ለባሕቲታ ፡ ወይሔውጻ ፡ ወይ

፳፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሮሚ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ የዘይኑን ፡ ልጅ ፡ የከበረች ፡ ኢላርያ ፡ አረፈች ።

፳፩፤ የዚችም ፡ ቅድስት ፡ አባቷ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወድ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ይቺን ፡ ቅድስት ፡ ኢላርያንና ፡ ሁለተኛዋን ፡ እኅቷን ፡ ወለደ ፡ ከእነርሱም ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የለውም ።

፳፪፤ ይቺም ፡ ቅድስት ፡ ኢላርያ ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ የመላእክትንም ፡ አስኬማ ፡ ትለብስ ፡ ዘንድ ፡ የምትመኝ ፡ ሆነች ፡ ከቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ወጥታ ፡ ልብሷን ፡ ለውጣ ፡ የወንድ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡ ሔደች ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ደረሰች ፡ በዚያም ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ ባውሚን ፡ የሚባለውን ፡ ፍጹም ፡ ሽማግሌ ፡ ጻድቅ ፡ ሰውን ፡ አግኝታ ፡ ሐሳቧን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ፡ እርሷ ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ሆነችም ፡ አስረዳችው ፡ እርሱም ፡ ምሥጢርዋን ፡ ሠውሮ ፡ ለብቻዋ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሜህራ ፡ ዘይደልዋ ፡ ትግበር ፡ ወነበረት ፡ ከመዝ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበእንተ ፡ አልባቲ፡ ጽሕም፡ ትመስሎሙ ፡ ለአረጋውያን፡ሕጽወ፡ወይሰምይዋ፡በስመ፡ብእሲ፡ አባ፡ኢላርዮን።

፳፫፡ወካልዕታሰ፡ዘተርፈት፡ኀበ፡አቡሃ፡ተጽዕነ፡ ላዕሌሃ ፡ ሰይጣን ፡ ርኩስ ፡ ወወሀበ ፡ አቡሃ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ለዐቃብያነ ፡ ሥራይ ፡ ከመ፡ ይፈውስዋ ፡ ባሕቱ ፡ ኢተክህሎሙ ፡ ወእምዝ ፡ አምከርዎ ፡ መኳንንቲሁ ፡ ከመ ፡ ይፈንዋ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ኀበ ፡ አረጋውያን፡ቅዱሳን፡እስመ፡ተሰምዐ፡ዜና፡ቅዱስናሆሙ፡ውስተ፡ኵሉ፡በሐውርተ፡ሮም። ወሶቢሃ ፡ ፈነዋ ፡ ኀበ ፡ ቅዱሳን ፡ ምስለ ፡ ብዙኀ ፡ ሠራዊት ፡ ወጸሐፈ ፡ ሎሙ ፡ መልእክተ ፡ ለቅዱሳን ፡ አረጋውያን ፡ እንዘ ፡ ይብል፡አጤይቀክሙ፡አ፡አበውየ፡ቅዱሳን፡ ዘበጽሐኒ ፡ ኀዘነ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸገወኒ፡ክልኤተ፡አዋልደ፡ወአሐቲ፡ጐየት፡ ወኢየአምር፡ኀበ፡አይ፡መካን፡ከመ፡ትሄሉ፡ ወለካልዕታ ፡ ተጽዕነ ፡ ላዕሌሃ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እንዘ ፡ እሔሊ ፡ ከመ ፡ ትከውነኒ ፡ ናዛዚተ ፡ ወይእዜኒ ፡ አንሰ ፡ እስእል ፡ እምነ፡ ቅድስናክሙ ፡ ከመ ፡ ትጼልዩ፡ ለዕሌሃ ፡ ወይፈውሳ፡ እግዚአብሔር፡በጸሎትክሙ።

፳፬፡ወሶበ፡አንበቡ፡ቅዱሳን፡መልእክተ፡ንጉሥ፡ አኀዙ ፡ ከመ ፡ ይጸልዩ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወከልሐ ፡ ሰይጣን ፡ ዘላዕሌሃ ፡ ወይቤ ፡ አልቦ ፡ ዘያወጽአኒ፡ ዘእንበለ ፡ ኢላርዮን ፡ እማኅደርየ ። ወጸውዕዋ ፡ አረጋውያን ፡ ለኢላርያ ፡ ዘይብልዋ ፡ ሕፅወ፡ ወአዘዝዋ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ንሥእ ፡ ለወለተ ፡ ንጉሥ ፡ ወጸሊ ፡ ላዕሌሃ ፡ እስከ ፡ ይፌውሳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትቤሎሙ ፡ ቅድስት ፡ ኢላርያ ፡አንሰ ፡ ብእሲ ፡ አባሲ፡ኢይክል፡ዘንተ፡ግብረ፡ዕፁበ።

፳፭፡ ወሶበ ፡ አገበርዋ ፡ ነሥአታ ፡ ወወሰደታ ፡ ውስተ ፡ በዓታ ፡ ወጸለየት ፡ ላዕሌሃ ፡ ወተፈወሰት፡በኀዳጥ፡መዋዕል፡ሰይጣንኒ፡ኀደጋ፡ ወጐየ፡ወቅድስት፡ኢላርያ፡ተአምር፡ከመ፡

በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አስገባት ፡ ይጐበኛትና ፡ ልትሠራው፡የሚገባትን፡ያስተምራት፡ነበር። እንዲህም ፡ ሁና ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት፡ ኖረች ፡ ጽሕም ፡ ስለሌላትም ፡ ለአረጋውያን ፡ መነኰሳት ፡ ጃንደረባ ፡ ትመስላቸው ፡ ነበር ። በወንድ ፡ ስም ፡ አጠራርም ፡ አባ ፡ ኢላርዮን ፡ ብለው፡ይጠሩዋታል።

፳፫፡ከአባቷ፡ዘንድ፡በቀረችው፡በሁለተኛዋ፡ግን፡ ርኩስ ፡ ሰይጣን ፡ አደረባትና ፡ ያሠቃያት፡ ጀመር ፡ ያድኗትም ፡ ዘንድ ፡ ለባለ፡ መድኃኒቶች ፡ አባቷ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠ ፡ ግን ፡ አልተቻላቸውም ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበሩ ፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳት ፡ ወዳሉበት፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ይልካት ፡ ዘንድ፡ መኳንንቶቹ ፡ መከሩት ፡ የቅድስናቸው ፡ ወሬ፡ በሮም ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተሰምቷልና ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ላካት ፡ ለቅዱሳኑም፡ መልእክትን፡ ጻፈላቸው፡ እንዲህ፡ ሲል፡ የተከበራችሁ ፡ አባቶቼ ፡ ሆይ ፡ የደረሰብኝን ፡ኀዘን፡ አስረዳችኋለሁ፡ እግዚአብሔር፡ ሁለት፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ሰጥቶኝ ፡ ነበር ። አንዲቱ ፡ ከዓለም ፡ ሸሸች ፡ ወደየት ፡ ቦታ ፡ እንደምትኖር፡አላውቅም፡በሁለተኛዪቱም፡ በላይዋ፡ ርኩስ፡ መንፈስ ፡ ተጫነባት፡ እኔ ፡ መጽናኛ፡ትሆነኛለች፡ብዬ፡እያሰብኩ፡ነበር፡ አሁንም ፡ በጸሎታችሁ ፡ እግዚአብሔር ያድናት ፡ ዘንድ ፡ በላይዋ ፡ እንድትጸልዩ ፡ እኔ ፡ ቅድስናችሁን፡እለምናለሁ።

፳፬፡ ቅዱሳን ፡ መነኰሳትም ፡ የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ በአነበቡ ፡ ጊዜ ፡ በላይዋ ፡ ሊጸልዩ ፡ ጀምሩ ፡ በላይዋ፡ያደረ፡ሰይጣንም፡ከኢላርዮን፡በቀር፡ ከማደሪያዬ ፡ የሚያስወጣኝ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። አረጋውያኑም ፡ ጃንደረባ ፡ የሚሏትን ፡ ኢላርያን ፡ ጠርተው ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ አዳናት ፡ ድረስ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ወስደህ ፡ በላይዋ ፡ ጸልይ ፡ አሏት ፡ ቅድስት ፡ ኢለርያም ፡ እኔ ፡ በደለኛ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ይህን ፡ ጭንቅ ፡ የሆነ ፡ ሥራን ፡ መሥራት፡ አልችልም፡ አለቻቸው።

፳፭፡ በአስገደድዋትም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ በዓትዋ ፡ ወስዳ፡ በላይዋ ፡ ጸለየች ፡ ሰይጣንም ፡ ትቷት ፡ ሸሸ ፡ በጥቂት ፡ ቀንም ፡ ዳነች ። ቅድስት ፡ ኢላርያም፡ እኅቷ ፡ እንደሆነች ፡ ታውቃለች ፡ ስለዚህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እኅታ፡ይእቲ፡ወበእንተዝ፡ተሐቅፋ፡ወት ስዕማ፡ወትወጽእ፡አፍአ፡ወትበኪ፡በእ ንተ፡ጽምዐ፡ፍቅራ።

፳፮፤ ወእምዝ፡አብጽሐታ፡ኀበ፡አረጋውያን፡ ቅዱሳን፡ወትቤሎሙ፡ናሁ፡እግዚአብሔር፡ ወሀባ፡ፈውሰ፡በጸሎትክሙ፡ወአግብእዋ፡ ኀበ፡አቡሃ፡እሙንቱሂ፡ተፈሥሑ፡ፈድ ፋደ፡ወአግብእዋ፡ኀበ፡አቡሃ፡ወወሀቡ፡ ስብሐተ፡ለእግዚአብሔር።

፳፯፤ ወሶበ፡በጽሐት፡ሀገረ፡ሮሜ፡ኀበ፡አቡሃ፡ ጥዕይታ፡ተፈሥሑ፡ባቲ፡ጥቀ፡አቡሃ፡ ወእማ፡ወኵሎሙ፡ሰብአ፡ቤተ፡መን ግሥት፡በእንተ፡ድኅነታ፡ወአእኰትዎ፡ለእ ግዚአብሔር።

፳፰፤ ወተሰአላ፡አቡሃ፡ወይቤላ፡እፎ፡ንብረትኪ፡ በገዳም፡ምስለ፡ቅዱሳን፡አበው፡ወነገረቶ፡ እንዘ፡ትብል፡እስመ፡ዝንቱ፡አብ፡አባ፡ ኢላርዮን፡ዘፈወሰኒ፡ያፈቅረኒ፡ብዙኀ፡ወየ ሐቅፈኒ፡ወይስዕመኒ፡ወሰሚዖ፡ንጉሥ፡ ዘንተ፡ነገረ፡ተሀውከ፡በሕሊናሁ፡ፈድፋደ። ወይቤ፡በልቡ፡ይደልዎኑ፡ለመነኰስ፡ ስዒመ፡አንስት፡ወውእተ፡ጊዜ፡ጸሐፈ፡ መልእክተ፡ኀበ፡አረጋውያን፡ቅዱሳን፡ እንዘ፡ይብል፡ፈንውዎ፡ኀቤየ፡ለአባ፡ ኢላርዮን፡ዘፈወሳ፡ለወለትየ፡ከመ፡ይባ ርክ፡ሀገርየ፡ወይጸሊ፡ላዕሌየ።

፳፱፤ ወጸውዕዋ፡አረጋውያን፡ለኢላርያ፡ቅድስት፡ ወአዘዝዋ፡ከመ፡ትሑር፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወይ እቲ፡በከየት፡ብካየ፡ወሰአለቶሙ፡ለአረጋ ውያን፡አበው፡ከመ፡ይኅድግዋ፡ወይቤልዋ፡ እሙንቱ፡እስመ፡ዝንቱ፡ጻድቅ፡ንጉሥ፡ መፍቀሬ፡ክርስቲያን፡ኢይትከሃለነ፡ንትዓ ደው፡ትእዛዞ፡በከመ፡አዘዙነ፡መጻሕፍት፡ ቅዱሳት፡ወእምዝ፡ፈነውዋ፡በአገብሮ።

፴፤ ወሶበ፡በጽሐት፡ኀበ፡ንጉሥ፡ተቀበልዋ፡ ንጉሥ፡ወኵሎሙ፡ሰብአ፡መንግሥት፡ በክብር፡ወተአምኀዋ፡ወእምዝ፡አግኃሥዋ፡ ውሳጤ፡ጽርሕ፡ንጉሥ፡ወንግሥት፡ለባሕ ቲቶሙ፡ወተሰአላ፡ንጉሥ፡ወይቤላ፡አንሰ፡ ተሀወኩ፡በሕሊናየ፡ሶበ፡ሰማዕኩ፡ከመ፡ አንተ፡ትስዕማ፡ለወለትየ፡ወእፈቅድ፡ከመ፡ ትክሥት፡ሊተ፡ዘንተ፡ግብረ፡እስመ፡

አቅፏ፡ትስማት፡ነበር፡ስለ፡ናፍቆቷና፡ስለ፡ ፍቅርዋ፡ወደ፡ውጭ፡ወጥታ፡ታላቅሳለች።

፳፮፤ ከዚህም፡በኋላ፡ወደከበሩ፡አረጋውያን፡አደረ ሰቻትና፡እነሆ፡በጸሎታችሁ፡እግዚአብሔር፡ አድኗታል፡ወደ፡አባቷ፡መልሷት፡አለ ቻቸው።እነርሱም፡እጅግ፡ደስ፡ብሏ ቸው፡ወደ፡አባቷ፡መለሱዋት፡ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡አቀረቡ።

፳፯፤ ወደ፡ሮሜ፡አገርም፡ወደ፡አባቷ፡በደረሰች፡ ጊዜ፡አባትና፡እናቷ፡ስለ፡መዳንዋ፡በእርሷ፡ እጅግ፡ደስ፡አላቸው፡የቤተ፡መንግሥት፡ ሰዎችም፡ሁሉ፡እግዚአብሔርን፡አመሰ ገኑት።

፳፰፤ አባቷም፡በገዳም፡ከቅዱሳን፡አባቶች፡ጋር፡ አኗኗርሽ፡እንዴት፡ነበር፡ብሎ፡ጠየቃት፡ እርሷም፡እንዲህ፡ብላ፡ነገረችው፡ያ፡ያዳነኝ፡ አባ፡ኢላርዮን፡የሚባል፡አባት፡አብዝቶ፡ ይወደኛል፡አቅፎም፡ይስመኛል፡ንጉሡም፡ ይህን፡ሰምቶ፡በልቡ፡ታወከ፡ለመነኰሴ፡ ሴቶችን፡መሳም፡ይገባዋልን፡አለ።በዚያ ንም፡ጊዜ፡በእኔ፡ላይ፡ይጸልይ፡ዘንድ፡ አገሬንም፡ይባርክ፡ዘንድ፡ልጄን፡ያዳናትን፡ አባ፡ኢላርዮንን፡ወደኔ፡ላኩት፡የሚል፡ ደብዳቤ፡ጽፎ፡ወደ፡ቅዱሳን፡አረጋውያን፡ ላከ።

፳፱፤ አረጋውያንም፡ቅድስት፡ኢላርያን፡ጠር ተው፡ወደ፡ንጉሥ፡እንድትሔድ፡አዘዙዋት፡ እርሷም፡ይተዋት፡ዘንድ፡አረጋውያን፡ አባቶችን፡አልቅሳ፡ለመነቻቸው።እነርሱም፡ እንዲህ፡አሉዋት፡ይህ፡ንጉሥ፡ክርስቲያ ኖችን፡የሚወድ፡ጻድቅ፡ነው፡ቅዱ ሳት፡መጻሕፍትም፡እንደሚያዙን፡ትእ ዛዙን፡መተላለፍ፡አይቻለንም፡ይህንንም፡ ብለው፡አስገድደው፡ላኩዋት።

፴፤ ወደ፡ንጉሡም፡በደረሰች፡ጊዜ፡ንጉሡና፡ የቤተ፡መንግሥት፡ሰዎች፡ሁሉም፡በክብር፡ ተቀብለው፡ተሳለሟት፡ከዚህም፡በኋላ፡ ንጉሡና፡ንግሥቲቱ፡ለብቻቸው፡ሁነው፡ወደ፡ ውስጠኛው፡አዳራሽ፡አስገለሉዋትና፡ንጉሡ፡ እንዲህ፡ብሎ፡ጠየቃት፡አንተ፡ልጄን፡እንደም ትስማት፡በሰማሁ፡ጊዜ፡በሐሳቤ፡ታውኬ አለሁ፡መነኰሴ፡ሴትን፡መሳም፡አይገባው

www.ethiopianorthodox.org

ዘኑሲስ ፡ ወናሁ ፡ ጸሐፍነ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለአ ቡሁ፡ወእኁሁ፡አመ፡፮ለወርኀ፡ጥር።

፴፮፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ማእምር ፡ ፈድፋደ፡ወተሠይመ፡ውስተ፡ደሰያት፡ኤጲ ስቆጶሰ ፡ ወናሁ ፡ ጸሐፍነ ፡ ዘኮነ ፡ ንስቲተ ፡ እምገድሉ ፡ ዘአመ ፡ ፲ ወ ፭ ለዝ ፡ ወርኅ ፡ ወተብህለ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ውእቱ፡ሶበ፡ ይቄድስ ፡ መሥዋዕተ ፡ ቍርባን ፡ ኮነ ፡ ዘይኔጽር፡እንዘ፡ይወርድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ ዲበ፡ምሥዋዕ፡ወእምዝ፡ነጸሮ፡ለኪሩብ፡ ወአኀዞ፡ርእሶ፡ወሐቀፎ፡ውስተ፡ሕፅኑ፡ ወአብጽሖ ፡ ውስተ፡ አርምሞ ፡ ወተደሞ ፡ ዲበ፡ ምሥዋዕ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ይመ ስሎሙ፡ከመ፡ውእቱ፡ንውም፡በሥጋ።

፴፯፡ ወሶበ፡ተፈጸማ፡ሎቱ፡፴ወ፫ቱ፡ዓመታት፡ በሢመተ፡ኤጲስቆጶስና፡መጽአ፡ኀቤሁ፡ እኁሁ፡ቅዱስ፡ባስልዮስ፡ከመ፡የሐውጾ፡ እስመ፡ውእቱ፡ኮነ፡ዘይደዊ፡ደዌ፡ዐቢየ፡ እምብዝኀ፡ተጸምዶት፡በጾም፡ወበጸሎት፡ ወተፈሥሐ፡በምጽአቱ፡ለቅዱስ፡ባስልዮስ።

፴፰፡ ወሶበ፡ዐርገ፡ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡ውስተ፡ ምሥዋዕ፡ከመ፡ይቀድስ፡በከመ፡ልማዱ፡አስ ተርአየቶ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ ማርያም፡ወትቤሎ፡ትመጽእ፡ዮም፡ኀቤየ፡ ወፈጺሞ፡ቅዳሴ፡ቍርባን፡ሰአሎ፡ለእኁሁ፡ ባስልዮስ ፡ ከመ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ይጽንዑ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወው እቱ፡ኮነ፡ከመ፡ዘይነውም፡ወሶበ፡አኀዙ፡ ያንቅሕዎ፡ረከብዎ፡በዘአዕረፈ፡ወአዘዞሙ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ሎቱ ፡ ሣዑነ፡ወገነዞ፡በከመ፡ይደሉ፡በጸሎታት፡ ወበዝማሬያት ፡ ወበማኅሌት ፡ ወአንበርዎ ፡ ውስተ፡መቃብር።

፵፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ፍቱ፡መታሰቢያ፡ነው፡እነሆ፡የአባቱንናየወ ንድሙን ፡ መታሰቢያቸውን ፡ በዚህ ፡ ወር፡ ጥር፡ስድስት፡ቀን፡ጽፈናል።

፴፮፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እጅግ ፡ የተማረ ፡ አዋቂ ፡ ነበረ ፡ በደሴቶችም ፡ ላይ ፡ ኤጲስቆጶ ስነት ፡ ተሾመ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ በአሥራ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ የሆነውን ፡ ከገድሉ ፡ ጥቂት፡ እንጽፋለን ። ስለርሱም ፡ እንዲህ ፡ ተባለ ፡ እርሱ፡መሥዋዕቱን፡ለማክበር፡በሚቀድስ፡ ጊዜ፡በመሠዊያው፡ላይ፡ሲወርድ፡መንፈስ ቅዱስን፡የሚያየው፡ሆነ፡ከዚህም፡በኋላ፡ ኪሩብን ፡ አየው ፡ በደረቱም ፡ ውስጥ ፡ አቀፈው፡በመሠዊያውም፡ላይ፡ሳለ፡ወደ፡ ዝምታና፡ተደሞ፡አደረሰው፡ሰዎችም፡ሁሉ፡ ሥጋዊ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያንቀላፋ ፡ ይመስ ላቸው፡ነበር።

፴፯፡ በኤጲስቆጶስነት ፡ ሹመት ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዘመናት ፡ በተፈጸሙለት ፡ ጊዜ ፡ ወንድሙ ፡ ቅዱስ፡ባስልዮስ፡ሊጠይቀው፡መጣ፡እርሱ፡ ከተጋድሎ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ በጽኑ ፡ ደዌ ፡ የሚታመም ፡ ሁኖ ፡ ነበርና ፡ በቅዱስ ፡ ባስል ዮስም፡መምጣት፡ደስ፡አለው።

፴፰፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ሊቀ ድስ ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የከበረች፡ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያም፡ ተገለጸችለትና ፡ ዛሬ ፡ ወደኔ ፡ ትመጣለህ ፡ አለችው፡የቍርባኑንም፡ቅዳሴ፡ሲጨርስ፡ ሕዝቡ ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ፡ይመክራቸውና፡ያስተምራቸው፡ ዘንድ፡ወንድሙን፡ባስልዮስን፡ለመነው፡ እርሱም ፡ እንደሚያንቀላፋ ፡ ሆነ ፡ በቀሰቀ ሱትም፡ጊዜ፡ሙቶ፡አገኙት፡ቅዱስ፡ባስል ዮስም ፡ ሣጥን ፡ እንዲሠሩለት ፡ አዘዛቸው ። ጸሎታትንም፡በመጸለይ፡መዝሙራትንም፡ በመዘመር ፡ በማመስገንም ፡ እንደሚገባ ፡ ገንዞ፡በመቃብር፡ውስጥ፡አኖሩት።

፵፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለጎርጎርዮስ፡በአእዳወ፡ኪሩብ፡ዘተሐቅፈ።ጊዜ፡ያዐርግ፡ለሊሁ፡ቅዳሴ፡ቍርባን፡ወኩፈ። ሶበ፡ትመጽእ፡ኀቤየ፡ትቤሎ፡ማርያም፡አፈ። እንዘ፡ይመስሎሙ፡አርአያ፡ዘይነውም፡ዘልፈ። ሶበ፡አንቅሕዎ፡ተረክበ፡ዕሩፈ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለኒቆላዎስ ፡ ዘጾማዕት፡ዘኮነ፡ስምዐ፡ወአባ፡ፊቅጦር፡ኤጺስቆጶስ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ ጳውሎስ ፡ መኰንን ፡ ወሲላስ ፡ ቀሲስ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለመርቅያን ፡ ዐላዊ ፡ ንጉሥ ፡ ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ጉቡአነ ፡ ውስተ ፡ ጌቴሴማኒ ፡ በበዓለ ፡ ዕረፍታ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ መሐይምናን ፡ መጽአ ፡ ዮልያኖስ፡ከሀዲ፡ወዓገቶሙ፡ወቀተሎሙ፡ወኢያትረፈ፡፩ደ፡እምኔሆሙ፡ወበረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፡ በዚችም፡ዕለት፡በሰማዕትነት፡የሞተ፡በዋሻ፡የሚኖር ፡ የኒቆላዎስና ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ፊቅጦር ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡አሜን።

፴፩፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ በመናፍቁ ፡ ንጉሥ ፡ በመርቅያን፡ዘመን፡መኰንኑ፡ጳውሎስና፡ቀሲስ፡ሲላስ፡ምስክር፡ሁነው፡ሞቱ፡እነርሱም፡በእመቤታችን፡ማርያም፡የዕረፍቷ፡በዓል፡በጌቴሴማኒ ፡ ከሁሉም ፡ ምእመናን ፡ ጋር ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ከሀዲው ፡ ዮልያኖስ ፡ መጥቶ ፡ ከበባቸው፡ከእርሳቸውም፡አንድም፡እንኳን፡ሳያስቀር፡ገደላቸው፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለሰማዕታተ፡ክርስቶስ፡መድኀን። ምስለ፡መኰንን፡ጳውሎስ፡ወሲላስ፡ካህን። በእንተ፡ዘኢነሥኡ፡ቅድመ፡እንዘ፡ሕያዋን። ከመ፡ይትመጠዉ፡እለ፡ተቀትሉ፡ሙታን። እምዐይነ፡ቀሲስ፡ተንበአ፡ቊርባን።

፴፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለኤርምያስ ፡ ነቢይ፡ወቀውስጦስ፡ወዮሐንስ፡ወአባ፡እስክንድር፡ወአስተርአዮታ፡ለእግዝእትነ፡ውስተ፡ደብረ፡ማሕው፡ምስለ፡ዮሐንስ፡መጥምቅ።

፴፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎተ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳን፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፪፡ በዚችም፡ዕለት፡የነቢይ፡ኤርምያስ፡የቀውስጦስ፡የዮሐንስና፡የአባ፡እስክንድር፡እመቤታችንም፡ከመጥምቁ፡ዮሐንስ፡ጋር፡በደብረ፡ማሕው፡የተገለጠችበት፡ሲሆን፡የሁሉም፡መታሰቢያቸው፡ነው።

፴፫፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለኤርምያስ፡ዘተነበየ፡በተግሣጽ። አመ፡እስራኤል፡አፍቀሩ፡አምልኮተ፡ዕብን፡ወዕፀ። ወአስሰለ፡ሎሙ፡በኃይለ፡ጸሎቱ፡ሥርዋጽ። አራዊተ፡ወአናብስተ፡ግሩማነ፡ራእይ፡ወገጽ። ወበእንተዝ፡ይትገበር፡በዓሉ፡በግብጽ።

***

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ ወ ፪ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ዐቢይ ፡ ወክቡር ፡ አብ ፡ ኮከበ ፡ ገዳም ፡ እንጦንዮስ ፡ አቡሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መነኮሳት፡እምሀገረ፡አቅማን፡እምብሔረ፡ግብጽ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ ፡ ንጹሐን ፡ ክርስቲያን ፡ ወለውእቱሰ ፡ እምንእሱ ፡ አልቦ ፡ ጽልሑት ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ወሶበሂ ፡ የሐውር ፡ ምስለ ፡ አበዊሁ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይቄርብ ፡ ቊርባነ ፡ ወኢይሣለቅ ፡ ምስለ ፡

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ በዚች፡ቀን፡በግብጽ፡አገር፡ከአቅማን፡ከተማ፡የከበረና ፡ የገነነ ፡ የመነኰሳት ፡ ሁሉ ፡ አባት በገዳም ፡ ለሚኖሩ ፡ እንደ ፡ ኮከብ ፡ የሚያበራላቸው፡አባት፡እንጦንዮስ፡አረፈ።

፪፡የዚህም፡ቅዱስ፡ወላጆቹ፡ንጹሐን፡ክርስቲያንናቸው ፡ እርሱም ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ተንኰል ፡ ሽንገላ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ የለውም ፡ ከወላጆቹም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሒዶ ፡ በቆረበ ፡ ጊዜ ፡ ከሕፃናት ፡ ጋር ፡ በመ

www.ethiopianorthodox.org

ሕፃናት፡ወኢይዛዋዕ፡ግሙራ።

፫፤ ወሶበ፡ልሕቀ፡ንስቲተ፡ያደንን፡ርእሶ፡ወይት ኤዘዝ፡ሎሙ፡ለአበዊሁ፡ወሶበ፡ኮኖ፡፯ተ፡ ዓመተ፡ተምህረ፡ኵሎ፡መጻሕፍተ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡ወኮነ፡አሜሃ፡መዋዕለ፡ሢመቱ፡ለአባ፡ ቴዎናስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡ ወሰሚዖ፡ዜናሁ፡ለእንጦንዮስ፡ፈነወ፡ላእካነ፡ ወአብጽሖ፡ኀቤሁ፡ወባረኮ፡ወተነበየ፡ሎቱ፡ እንዘ፡ይብል፡እስመ፡ዝንቱ፡ሕፃን፡ይከውን፡ ዐቢየ፡በቅድመ፡እግዚአብሔር፡ወይወጽእ፡ ዜናሁ፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፡ወአንበረ፡እዴሁ፡ ላዕሌሁ፡ወሤሞ፡ዲያቆነ።

፬፤ ወእምዝ፡ሶበ፡ሞቱ፡አበዊሁ፡ኀደጉ፡ሎቱ፡ እኅተ፡ንስቲተ፡ወእምድኅረ፡፯ቱ፡አውራኅ፡ ሐዊሮ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡በከመ፡ ልማዱ፡ቦአ፡ውሰተ፡ልቡ፡ፍቅረ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡ወይቤ፡በነፍሱ፡እሬ፡ኀደጉ፡ ሐዋርያት፡አበዊነ፡ኵሎ፡ግብረ፡ዓለም፡ ወተለውዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወእለሂ፡ሤጡ፡ጥሪቶሙ፡ወአንበሩ፡ሤጦ፡ ታሕተ፡እግረ፡ሐዋርያት፡በከመ፡ጽሑፍ፡ ውስተ፡መጽሐፈ፡ግብረ፡ሐዋርያት፡ሐለየ፡ ወይቤ፡ሚ፡መጠን፡ተስፋሆሙ፡ዘአስተ፡ ዳለወ፡ሎሙ፡እግዚአብሔር፡በሰማያት፡ ወዝንቱ፡ግብር፡ኮነ፡ውስተ፡ልቡ፡ያንሶሱ፡ ኵሎ፡ጊዜ።

፭፤ ወእምዝ፡ሖረ፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ወሰምዐ፡ቃለ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ዘይቤሎ፡ እግዚእነ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ለባዕል፡ለእመ፡ ትፈቅድ፡ትኩን፡ፍጹመ፡ሑር፡ወሢጥ፡ ኵሎ፡ጥሪተከ፡ወሀብ፡ለነዳያን፡ወረስዮ፡ለከ፡ መዝገበ፡በሰማያት፡ወነዓ፡ትልወኒ።

፮፤ ወነሥአ፡ዘንተ፡ሕሊና፡ቅዱሰ፡እምኀበ፡እግዚ አብሔር፡ወሐለየ፡ከመ፡ውእቱ፡ቃል፡ ተነግረ፡በእንቲአሁ፡ወውእተ፡ጊዜ፡ወጽአ፡ እምቤተ፡ክርስቲያን፡ወሀለዎ፡ለአቡሁ፡ ምድር፡ስፉሕ፡ወሠናይ፡ወወሀቦሙ፡ ለሰብአ፡ሀገሩ፡ወጥሪቶሙኒ፡ዘኀደጉ፡ሎቱ፡ ሤጠ፡ወወሀበ፡ለነዳያን፡ወለምስኪናን። ወነሥአ፡ለእኅቱ፡ወአብአ፡ኀበ፡ደብረ፡ ደናግል።

ጫወት፡ከቶ፡አይሳሳቅም፡ነበር።

፫፤ ጥቂት፡በአደገም፡ጊዜ፡ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡ ለወላጆቹ፡ይታዘዝ፡ነበር፡ሰባት፡ዓመትም፡ በሆነው፡ጊዜ፡የቤተ፡ክርስቲያን፡መጻሕ ፍትን፡ተማረ፡ያን፡ጊዜም፡የእስክንድርያ፡ አገር፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ቴዎናስ፡የተሾመ በት፡ዘመን፡ነበር፡የእንጦንዮስንም፡ወሬውን፡ ሰምቶ፡መልእክተኞችን፡ልኮ፡ወደርሱ፡ አስመጣው፡ባረከውና፡ስለርሱ፡እንዲህ፡ብሎ፡ ትንቢት፡ተናገረ፡ይህ፡ሕፃን፡በእግዚአብ ሔር፡ፊት፡ታላቅ፡ይሆናል፡ዜናውም፡ በዓለሙ፡ሁሉ፡ይወጣል፡እጁንም፡በላዩ፡ ጭኖ፡ዲቁና፡ሾመው።

፬፤ ከዚህም፡በኋላ፡ወላጆቹ፡በሞቱ፡ጊዜ፡ታናሽ፡ ብላቴና፡እኅት፡ትተውለት፡ነበር። ከሰባት፡ ወርም፡በኋላ፡እንደ፡ልማዱ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡በሔደ፡ጊዜ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ፍቅር፡ በልቡ፡አደረበትና፡በኅሳቡ፡በዓለም፡የሚሠ ራውን፡ሁሉ፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡ ሁሉን፡የዓለምን፡ሥራ፡ትተው፡ጌታችንን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡እንዴት፡ተከተሉት፡ በሐዋርያት፡ሥራ፡መጽሐፍም፡እንደተጻፈ፡ ጥሪታቸውን፡እየሼጡ፡የሽያጩንም፡ዋጋ፡ በሐዋርያት፡እግር፡ሥር፡ያኖሩትን፡አሰበ፡ እግዚአብሔር፡በሰማያት፡ያዘጋጀላቸው፡ ዋጋቸው፡ምን፡ያህል፡ይሆን፡አለ፡ይህም፡ ኅሳብ፡በልቡ፡ውስጥ፡የሚወጣ፡የሚወርድ፡ ሆነ።

፭፤ ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ሔደ፡ የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡በከበረ፡ወንጌል፡ ለባለጸጋው፡የተናገረውን፡ሰማ፡እንዲህ፡ ሲል፡ፍጹም፡ትሆን፡ዘንድ፡ከወደድክ፡ ሒድ፡ጥሪትህን፡ሁሉ፡ሽጠህ፡ለድኆች፡ስጥ፡ በሰማይም፡ላንተ፡ድልብ፡አድርገው፡ መጥተህም፡ተከተለኝ።

፮፤ ከእግዚአብሔርም፡ዘንድ፡ይህን፡ልዩ፡ኅሳብ፡ አግኝቶ፡ይህ፡ቃል፡ስለርሱ፡እንደተነገረ፡ አሰበ፡በዚያንም፡ጊዜ፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡ ወጣ፡ለአባቱም፡ያማረ፡ሰፊ፡ምድር፡ነበረው፡ ለአገሩም፡ሰዎች፡ሰጣቸው፡ለርሱ፡የተዉለ ትንም፡ጥሪታቸውን፡ሁሉ፡ሸጦ፡ለድኆችና፡ ለችግረኞች፡ሰጣቸው፡እኅቱንም፡ወስዶ፡ ከደናግል፡ገዳም፡አስገባት።

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወበውእቱ፡መዋዕል፡ኢያስተርአየ፡ሥርዓተ፡ምንዙስና፡ዘይፈቅድ፡ይጸመዱ፡ለእግዚአ
ይወጽእ፡አፍአ፡ሀገር፡ንስቲተ፡
ወይነብር፡ባሕቲቶ፡ወይትቀነይ፡በጾም፡ወበጸሎት፡ወቅዱስኒ፡እንጦንዮስ፡ገብረ፡ከማሁ፡ወኮኑ፡ሰይጣናት፡ዘይጻብእዎ፡በሐኬት፡ወበገቢረ፡ኃጢአት፡ወያመጽኡ፡ቦቱ፡በሕልሙ፡ገጸ፡ብእሲት፡ወይረስይዋ፡ከመ፡ዘትሰክብ፡ምስሌሁ።

፰፤ ወእምዝ፡ሖረ፡ኀበ፡መቃብር፡ዘጽንፈ፡ባሕር፡ወኀደረ፡በህየ፡ወተኀየለ፡በተጋድሎ፡በረድኤተ፡እግዚአብሔር፡ዘኀዱር፡ላዕሌሁ፡ወሲሳዮኒ፡ያመጽኡ፡ሎቱ፡እምአዝማዲሁ፡ወርእዮሙ፡ሰይጣናት፡እንዘ፡ይትጋደል፡ከመዝ፡ቀንዑ፡ላዕሌሁ፡ወዘበጥዎ፡ዝብጠተ፡ዐቢየ፡ወኀደግዎ፡ግዱፈ፡ወሶበ፡መጽኡ፡አዝማዲሁ፡ረከብዎ፡ግዱፈ፡ከመ፡ምዉት፡ወፆርዎ፡ወአብጽሕዎ፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወእግዚእነ፡ፈወሶ፡ወሶበ፡ነቅሐ፡ተመይጠ፡ኀበ፡መካኑ፡ወአኀዘ፡ከመ፡ይትጋደል።

፱፤ ወሶቤሃ፡ርእዮሙ፡ለሰይጣናት፡እንዘ፡ይትጋደል፡ይመጽኡ፡ኀቤሁ፡በአምሳለ፡አራዊት፡ቦ፡በአምሳለ፡አናብስት፡ወተኵላት፡ወቦ፡በአምሳለ፡አክይስት፡ወአቃርብት፡ወለ፩፩ይትነሥኡ፡ላዕሌሁ፡ከመ፡ያፍርህዎ፡ወኮነ፡እንጦንዮስ፡ይሣለቅ፡ላዕሌሆሙ፡ወይብሎሙ፡ለእመ፡ኮነ፡ለክሙ፡ሥልጣን፡ላዕሌየ፡፩እምኔክሙ፡ይመውዕኒ፡ወበጊዜሃ፡ተዘርው፡ከመ፡ጢስ፡እስመ፡ወሀቦ፡እግዚአብሔር፡መዊዐ፡ላዕለ፡ሰይጣናት፡ወአዕረፈ፡እምሕማም፡ወመከራ፡ዘሰይጣናት።

፲፤ ወኮነ፡ዘያበስል፡ሲሳዮ፡፪ተ፡ጊዜ፡ለለዓመት፡ወያየብሶ፡በፀሐይ፡ወኢየኀድግ፡መነሂ፡ከመ፡ይባእ፡ኀበ፡በዓቱ፡አላ፡ይቀውም፡አፍአ፡ወይሰምዕ፡ቃሎ፡ወነበረ፡ከመዝ፡እንዘ፡ይጸመድ፡ወይትጋደል፡ገድለ፡ዐቢየ፡፳ዐመተ።

፲፩፤ ወእምዝ፡አዘዞ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ይፃእ፡ወይምሀሮሙ፡ለሰብእ፡ፈሪሀ፡እግዚአብሔር፡ፍጹመ፡ወአምልኮቶ፡ወበእንተዝ፡ሖረ፡ኀበ፡ሀገረ፡ፍዩም፡ወአስተጋብአሙ፡

፯፤ በዚያንም፡ወራት፡የምንኵስና፡ሥርዓት፡አልተገለጸም፡ነበር፡እግዚአብሔርንም፡ለማገልገል፡የሚሻ፡ከመንደር፡ጥቂት፡ወጣ፡ብሎ፡ብቻውን፡በመቀመጥ፡በጾም፡በጸሎት፡ተወስኖ፡ይጋደላል፡የከበረ፡እንጦንዮስም፡እንዲሁ፡አደረገ፡ሰይጣናትም፡በስንፍናና፡በዝሙት፡ጦር፡የሚዋጉት፡ሆኑ፡በሕልሙም፡የሴት፡ገጽ፡በማሳየት፡አብራውም፡እንደምትተኛ፡ያደርጓታል።

፰፤ ከዚህም፡በኋላ፡በባህር፡ዳርቻ፡ወዳለች፡የመቃብር፡ቤት፡ሒዶ፡በዚያ፡የሚኖር፡ሆነ፡በላዩ፡በአደረ፡በእግዚአብሔርም፡ረድኤት፡በተጋድሎ፡በረታ፡ምግቡንም፡ከዘመዶቹ፡ወገን፡ያመጡለት፡ነበር፡ሰይጣናትም፡ሲጋደል፡አይተው፡ቀኑበት፡ታላቅ፡ድብደባንም፡ደብድበው፡ጥለውት፡ሔዱ፡ዘመዶቹም፡ሲመጡ፡እንደ፡ሞተ፡ሁኖ፡ወድቆ፡አገኙት፡ተሸክመውም፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወሰዱት፡ጌታችንም፡አዳነው፡በነቃም፡ጊዜ፡ወደ፡ቦታው፡ተመልሶ፡ይጋደል፡ዘንድ፡ተጋድሎውን፡ጀመረ።

፱፤ በዚያንም፡ጊዜ፡ሰይጣናትን፡ወደርሱ፡ሲመጡ፡አያቸው፡በአራዊት፡አምሳል፡በአንበሶችና፡በተኵላዎች፡የተመሰሉ፡አሉ፡በእባቦችና፡በጊንጦችም፡የተመሰሉ፡አሉ፡ያስፈሩትም፡ዘንድ፡አንዱም፡አንዱ፡በላዩ፡ተነሣሡ፡እንጦንዮስም፡በእኔ፡ላይ፡ለእናንተ፡ሥልጣን፡ካላችሁ፡ከእናንተ፡አንዱ፡ያቸንፈኝ፡ነበር፡ብሎ፡ዘበተባቸው፡ወዲያውኑ፡እንደ፡ጢስ፡ተበተኑ፡በሰይጣናት፡ላይ፡ድልን፡እግዚአብሔር፡ሰጥቶታልና፡ሰይጣናትም፡ከሚያመጡበት፡መከራና፡ሥቃይ፡አረፈ።

፲፤ ምግቡንም፡በየዓመቱ፡ሁለት፡ጊዜ፡ያበስላል፡በፀሐይም፡ያደርቀዋል፡ወደበዓቱም፡ማንም፡እንዲገባ፡አያሰናብትም፡የሚሻውም፡ሁሉ፡በውጭ፡ይቆምና፡ድምፁን፡ይሰማል፡እንዲሃያ፡ዐመትም፡እንዲህ፡ታላቅ፡ተጋድሎን፡እየተጋደለ፡በገደል፡ተጠምዶ፡ኖረ፡።

፲፩፤ ከዚህም፡በኋላ፡ፍጹም፡የሆነ፡እግዚአብሔርን፡መፍራትንና፡አምልኮቱን፡ለሰዎች፡ወጥቶ፡ያስተምር፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡አዘዘው፡ስለዚህም፡ወደ፡ፍዩም፡አገር፡

www.ethiopianorthodox.org

ለብዙኃን ፡ አርድእት ፡ ወመሀሮሙ ፡ ወአጽ
ንዖሙ ፡ በሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኮኑ ፡ ሎቱ ፡
ብዙኃን ፡ አድባራት ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ አርድ
እቲሁ ።

፲፪፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ፡ በእንተ ፡
ሃይማኖት ፡ ፈተወ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሰማዕተ ፡
ወኀደገ ፡ ደብሮ ፡ ወሖረ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡
ወተአመነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሎቱ ስብሐት ፡ ወኢአኅዝዎ ፡ ግሙራ ፡ ወእ
መሂ ፡ ኮነ ፡ ይሔውጾሙ ፡ ለሙቁሓን ፡ እለ ፡ በክ
ርስቶስ ፡ ወይናዝዞሙ ፡ ወያጸንዖሙ ፡ ወሶበ ፡
ርእዮ ፡ መኰንን ፡ ለቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ ከመ ፡
ኢይፈርህ ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ ኢያስተርኢ ፡ ውስተ ፡
ዓውደ ፡ ምኵናን ፡ ውእቱሰ ፡ ኢኀደገ ፡ ተርእ
ዮተ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ወይትናገሮ ፡ ነገረ ፡
ዘያምዕዖ ፡ ለመኰንን ፡ ከመ ፡ ይኰንኖ ፡ ወይ
ኩን ፡ ሰማዕተ ፡ መኰንንኒ ፡ ኢገብረ ፡ እኩየ ፡
ላዕሌሁ ፡ እስመ ፡ ከልአቶ ፡ ኃይል ፡ አምላካዊት ።
፲፫፡ ወሶበ ፡ ኀለፈ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ፡ ወኮነ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት ፡ ጴጥሮስ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት ፡
ወገብአ ፡ ኀበ ፡ ደብሩ ፡ እንጦኒ ፡ ዝንቱኒ ፡ ኮነ ፡
በሥምረተ ፡ አምላክ ፡ ወኮነ ፡ ዘይለብስ ፡
ልብሰ ፡ ሠቅ ፡ ወኢይትኀፀብ ፡ በማይ ፡ አካሎ ፡
በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ ወብዙኃን ፡
ዱያን ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይጼሊ ፡ ላዕ
ሌሆሙ ፡ ወየሐይዉ ።

፲፬፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕዛበ ፡ እንዘ ፡
ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ትምህርቶ ፡
ወኢኀደግዎ ፡ ይንበር ፡ ባሕቲቶ ፡ በከመ ፡
ይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓበይ ፡ በልቡ ፡ ፈርሀ ፡
በእንተ ፡ ዘይትገበር ፡ እምኔሁ ፡ ወሐለየ ፡
በልቡ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡
ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ኢየአምርዎ ፡ ወሖረ ፡
ኀበ ፡ ሐይቀ ፡ ባሕር ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይጸንሕ ፡
ሐመረ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀቤሁ ፡ እምሰማይ ፡
ወይቤሎ ፡ ኦ ፡ እንጦንዮስ ፡ አይቴ ፡ ተሐውር ፡
ወምንተ ፡ ተኃሥሥ ፡ ዝየ ፡ አውሥአ ፡ ውእቱኒ ፡
ወይቤ ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤየ ፡
ወኢተክህለኒ ፡ እንበር ፡ ባሕቲትየ ፡ ዘከመ ፡
እፈቅድ ፡ ወበእንተዝ ፡ ነሠሥኩ ፡ አሑር ፡ ኀበ ፡
ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ አውሥአ ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡

ወጥቶ ፡ ብዙዎች ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ሰብ
ስቦ ፡ አስተማራቸው ፡ በእግዚአብሔርም ፡
ሕግ ፡ አጸናቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቹ ፡ በውስ
ጣቸው ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ብዙዎች ፡ ገዳማት ፡
ተሠሩለት ።
፲፪፡ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ስደት ፡ በሆነበት ፡ ወራት ፡
በሰማዕትነት ፡ መሞትን ፡ ወዶ ፡ ወደ ፡ እስክን
ድርያ ፡ ሀገር ፡ ሔዶ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡
በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ታመነ ፡
ከቶ ፡ አልያዙትም ፡ በክርስቶስም ፡ ስም ፡
የታሠሩ ፡ እሥረኞችን ፡ በመጐብኘት ፡ ቢአረ
ጋጋቸውና ፡ ቢአጽናናቸውም ፡ አልያዙትም ፡
መኰንኑም ፡ እንደማይፈራ ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡
ከፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይታይ ፡
አዘዘው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መታየቱን ፡
አልተወም ፡ እንዲአሠቃየውና ፡ በሰማዕት
ነትም ፡ እንዲሞት ፡ የሚያስቆጣውን ፡ ነገር ፡
ይናገረው ፡ ነበር ፡ መኰንኑም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላደረገም ፡ አምላካዊት ፡
ኃይል ፡ ከልክላዋለችና ።
፲፫፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጴጥሮስ ፡ ለሰማዕታት ፡ ፍጻሜ ፡
ሁኖ ፡ የመከራው ፡ ወራት ፡ ከአለፈ ፡ በኋላ ፡
እንጦኒ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ተመለሰ ፡ ይህም ፡
በአምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ሆነ ፡ የሚለብሰውም ፡
ማቅ ፡ ነበር ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ገላውን ፡ በውኃ ፡
አልታጠበም ፡ ብዙዎች ፡ በሽተኞችም ፡
ወደርሱ ፡ ይመጣሉ ፡ በላያቸውም ፡ ሲጸልይ ፡
ይድናሉ ።
፲፬፡ ብዙዎች ፡ ሕዝቦችም ፡ ትምህርቱን ፡ ሊሰሙ ፡
ወደርሱ ፡ ሲመጡ ፡ በአያቸው ፡ ጊዜ ፡ ብቻው
ንም ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዳልተውት ፡ አይቶ ፡
ከእርሱ ፡ ስለሚደረገው ፡ ነገር ፡ ልቡ ፡ እንዳይ
ታበይ ፡ ፈራ ፡ እነርሱ ፡ ወደማያውቁት ፡ ቦታ ፡
ወደላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡
ወደ ፡ ባሕሩም ፡ ወደብ ፡ ደርሶ ፡ መርከብ ፡
እየጠበቀ ፡ ተቀመጠ ፡ ከሰማይም ፡ ወደርሱ ፡
ቃል ፡ መጣ ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ እንጦንዮስ ፡
ሆይ ፡ ወዴት ፡ ትሔዳለህ ፡ ከዚህስ ፡ ምን ፡
ትሻለህ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ ብዙዎች ፡ ወደእኔ ፡
ስለሚመጡ ፡ እንደምፈልገው ፡ ለብቻ ፡ መኖር ፡
አልተቻለኝም ፡ ስለዚህም ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡
ግብጽ ፡ እሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወደድኩ ፡ አለ ፡ ያም ፡
ቃል ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ፡ለእመ፡ሖርከ፡ኀበ፡ላዕላይ፡ግብጽ፡ ይትመከዓብ ፡ ዓዲ ፡ ፃማከ ፡ ወለእመሰ ፡ ፈቀድከ፡ትንበር፡ባሕቲተከ፡ሑር፡ውሳጤ፡ ገዳም፡መጠነ፡፫ቱ፡መዋዕል።

፲፭፡ ወሶቤሃ ፡ ርእዮሙ ፡ ለሰብአ ፡ ዓረብ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይሑሩ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ፍኖት ፡ ወሖረ፡ኀቤሆሙ፡ወሰአሎሙ፡ከመ፡ይሑር፡ ምስሌሆሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ተወከፍዎ ፡ በፍ ሥሐ ፡ ወሖረ ፡ ሠለስተ ፡ መዓልተ ፡ እስከ ፡ በጽሐ፡ኀበ፡አሐዱ፡ደብር፡ነዊኅ፡ፈድፋደ፡ ወበህየ፡ሀሎ፡ማይ፡ጽሩይ፡ወቈሪር፡ወዓዲ ዕፀው፡በቀልት፡ወተመርት፡ወህለት፡ሀለዋ፡ ጽፉቃተ፡ወእንጦንዮስ፡አፍቀሮ፡ለእውቱ፡ መካን፡ወኮኑ፡ዓረብ፡ያመጽኡ፡ሎቱ፡ሲሳዮ፡ ወሀለው ፡ ብዙኃን ፡ አራዊት ፡ እኩያን ፡ ወበ ጸሎቱ ፡ አግኃሦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢገ ብኡ፡ግሙራ፡ኀበ፡ውእቱ፡መካን።

፲፮፡ ወኮነ ፡ አሐደ ፡ አሐደ ፡ ጊዜ ፡ ይወጽእ ፡ ኀበ ፡ ጽንፈ፡ባሕር፡ወይሔውጾሙ፡ለአርድእቲሁ፡ ወይናገዞሙ፡ወይገብእ፡ኀበ፡መካኑ፡ውሳጤ፡ ገዳም።

፲፯፡ ወእምዝ፡ሶበ፡ተሰምዐ፡ዜናሁ፡ኀበ፡ቈስጠን ጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሐፈ ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተ፡ኀበ፡ቅዱስ፡እንጦንዮስ፡እንዘ፡ ይስእሎ ፡ ከመ ፡ ይዝክሮ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎቱ ፡ ቅዱስሰ ፡ እንጦንዮስ ፡ ኢተመይጠ ፡ ኀበ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክቱ ፡ ለንጉሥ ፡ አላ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለእሊአሁ ፡ ነዋ ፡ መጽሐፉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይትነበብ ፡ በላዕሌነ ፡ ወሰአልዎ ፡ አኃው ፡ ወይቤልዎ ፡ ዝንቱ ፡ ንጉሥ፡ጻድቅ፡መፍቀሬ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ይደሉ፡ከመ፡ትናገሮ፡በመጽሐፈ፡መልእ ክት፡ወእምገ፡ጸሐፈ፡ሎቱ፡እንዘ፡ይናገሮ፡ ወይባርክ፡ላዕሌሁ፡ወላዕለ፡ቤተ፡መንግሥቱ፡ ወሠራዊቱ።

፲፰፡ ወካዕበ፡ሶበ፡ተሰምዐ፡ዜናሁ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ አፍርጊንያ፡ወውእቱ፡ጸሐፈ፡መልእክተ፡ ኀበ፡ቅዱስ፡እንጦንዮስ፡እንዘ፡ይብል፡አንሰ፡ እስእል ፡ ወእሰተበቍዕ ፡ ኀቤከ ፡ በእንተ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ትምጻእ፡ኀቤነ፡ወትባርክ፡ላዕሌነ፡ወላዕለ፡ ሀገርነ፡ወሠራዊትነ።

ግብጽ፡ብትሔድ፡ድካምህ፡ደግሞ፡እጥፍ፡ ይሆናል፡ብቻህን፡መኖር፡ከወደድክ፡ግን፡ የሦስት፡ቀን፡ጐዳና፡ያህል፡ወደ፡ውስጠ ኛው፡በረሀ፡ተጓዝ።

፲፭፡ በዚያንም፡ጊዜ፡በዚያች፡ጐዳና፡ሊጓዙ፡ የሚሹ፡የዓረብ፡ሰዎችን፡አያቸው፡ወደ፡እር ሳቸውም ፡ ሒዶ ፡ አብሮአቸው ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ፡ ለመናቸው ፡ እነርሱም ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ እጅግ ፡ ረጅም ፡ ወደሆነ፡ተራራ፡እስከሚደርስ፡የሦስት፡ቀን፡ ጐዳና፡ተጓዘ፡በዚያም፡የጠራና፡የቀዘቀዘ፡ ውኃ ፡ አለ ፡ ደግሞም ፡ የሰሌን ፡ የተምር ፡ ዕንጨቶች፡መቃዎችም፡በብዛት፡አሉበት፡ እንጦንዮስም፡ያንን፡ቦታ፡ወደደው፡ዓረቦ ችም፡ምግቡን፡የሚያመጡለት፡ሆኑ፡ብዙ ዎች፡የከፉ፡አራዊትም፡ነበሩ፡በጸሎቱም፡ እግዚአብሔር፡አስወገዳቸው፡ወደዚያም፡ቦታ፡ ከቶ፡አልተመለሱም።

፲፮፡ አንዳድ፡ጊዜም፡ወደ፡ባሕሩ፡ዳርቻ፡በመው ጣት፡ደቀ፡መዛሙርቶቹን፡ጐብኝቶና፡አረጋ ግቶ፡በበረሀ፡ውስጥ፡ወደአለው፡ቦታው፡ ይመለሳል።

፲፯፡ ከዚህም፡በኋላ፡በጻድቁ፡ንጉሥ፡ቈስጠ ንጢስ፡ዘንድ፡ዜናው፡በተሰማ፡ጊዜ፡ በጸሎቱ፡ ያስበው ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ እየለ መነው፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈለት ፡ የከበረ ፡ እንጦ ንዮስ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ ዘወር ፡ አላለም፡ለወገኖቹ፡እንዲህ፡አላቸው፡እንጂ፡ የንጉሠ፡ነገሥት፡ ደብዳቤ፡እነሆ፡ በላያችን፡ይነበባል፡ወንድሞችም፡እንዲህ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ የክርስቲ ያንን፡ወገኖች፡የሚወድ፡ጻድቅ፡ሰው፡ነው፡ በደብዳቤ ፡ ጽፈህ ፡ ልታጽናናው ፡ ይገባል ፡ ከዚህም፡በኋላ፡እያጽናናውና፡እየባረከው፡ ቤተ፡መንግሥቱንና፡ሠራዊቱንም፡እየባረከ፡ ጻፈለት።

፲፰፡ ዳግመኛም፡በአፍርንጊያ፡ንጉሥ፡ዘንድ፡ ዜናው፡በተሰማ፡ጊዜ፡ወደ፡ከበረ፡እንጦ ንዮስ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጥተህ፡በእኛ፡ላይ፡በአገራችንና፡በሠራዊ ታችን፡ላይ፡በረከትን፡ታሳድር፡ዘንድ፡ስለ፡ ጌታችን፡ክርስቶስ፡መከራዎች፡እኔ፡ወዳንተ፡ ፈጽሜ፡እማልዳለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ ዘንተ ፡ ኀዘነ ፡ ጥቀ ፡ ወቆመ ፡ ወጸለየ ፡ ወይቤ ፡ እስእለከ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ፈቃድከ ፡ ከመ ፡ እሑር ፡ ብሔረ ፡ በርኪኖን ፡ ዘአፍርንጊያ ፡ ክሥት ፡ ሊተ ፡ ትእምርተ፡ወባሕቱ፡ይኩን፡ፈቃድከ፡ወሶበ፡ ይቤ፡ዘንተ፡ናሁ፡በጽሐት፡ደመና፡ብርህት፡ ፆረቶ ወአብጽሐቶ ኀበ ብሔረ አፍርንጊያ ፡ በይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ወተፈሥሐ ፡ ንጉሥ ፡ ወኵ ሎሙ፡ሕዝቡ፡ወሠራዊቱ፡ወአቀረቡ፡ሎቱ፡ ኵሎ፡ዱያነ፡ወፈወሶሙ፡ለኵሎሙ፡ወነበረ፡ ኀቤሆሙ፡፮ተ፡አውራኀ፡እንዘ፡ይሜህሮሙ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወሕይወት ፡ ወለብዙኃን ፡ አእላፋት፡ረሰዮሙ፡አርድእቲሁ።

፳፤ ወበዕለተ ፡ እሑድ ፡ ትፀውሮ ፡ ይእቲ ፡ ደመና ፡ ብርህት ፡ ወታበጽሖ ፡ ኀበ ፡ ደብሩ ፡ ወይት ረከብ ፡ ምስለ ፡ ውሉዱ ፡ ወይናዝዞሙ ፡ ወበማ ኒታ ፡ካዕበ ፡ ትፀውሮ ፡ ይእቲ ፡ ደመና ፡ ወትመ ይጦ ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡ አፍርንጊያ ፡ ወእምድ ኅረዝ፡ገብአ፡ኀበ፡ደብሩ፡በሥምረተ፡እግዚአ ብሔር፡እንዘ፡ይጼዓን፡በይእቲ፡ደመና።

፳፩፤ ወበአሐቲ፡ዕለት፡መጽአ፡ላዕሌሁ፡ሀኬት፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ዘይቤሎ ፡ ጻእ ፡ ኀበ ፡ አፍአ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ወወጺአ ፡ ርእየ ፡ ለመልአክ ፡ ወላዕሌሁ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወቅናት ፡ ወፊቃር ፡ ዘመስቀል ፡ ወአስኬማ ፡ ውስተ ፡ ሐቌሁ ፡ ወዲበ ፡ ርእሱ ፡ ቆብዕ ፡ አምሳለ ፡ ጌራ ፡ ወውእቱ ፡ ይነብር ፡ እንዘ ፡ ይጸፍር ፡ ሆሣዕና ፡ ወእምዝ ፡ ይትነሣእ ፡ ወይጼሊ ፡ ወካዕበ ፡ ይነብር ፡ ወይጸፍር ፡ ሆሣዕና ፡ ወይገብር ፡ ከመዝ ፡ በበሰዓታት ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ካዕበ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይብል ፡ አ ፡ እንጦንዮስ ፡ ግበር ፡ ከመዝ፡ ወአንተ ፡ ተዓርፍ ፡ እምሀኬት ፡ ወእም ጻብአ ፡ ሰይጣናት ፡ ወነሥአ ፡ ውእተ ፡ አምሳለ ፡ ወኮነ ፡ ዘይገብር ፡ ከመዝ ፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኢመጽአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሀኬት ፡ ወኢ ፡ ጻብአ ፡ ሰይጣናት።

፳፪፤ ወአስተርአዮ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ሰብሐት ፡ ወናዘዞ ፡ ወአጽንዖ ፡ ወይእዜኒ ፡ ይቤሎ ፡ አ ፡ ኅሩይየ ፡ እን ጦንዮስ ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ እስመ ፡ በእንተ ፡

፲፱፤ የከበረ ፡ እንጦንዮስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘነ ፡ ቁሞም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ እለምን ሃለሁ ፡ በአፍርጊያ ፡ ውስጥ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ በርኪኖን፡አገር፡እንድሔድ፡ፈቃድህ፡ከሆነ፡ ምልክትን ፡ ግለጥልኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያንተ ፡ ፈቃድ፡ይሁን፡ይህንንም፡ባለ፡ጊዜ፡ብርህት፡ ደመና፡መጣች፡በዚያችም፡ሰዓት፡ተሸክማ፡ ወደ ፡ አፍርንጊያ ፡ አገር ፡ አደረሰችው ፡ ንጉ ሡም ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ሕዝቡና ፡ ሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ በሽተኞችንም ፡ አቀረቡለትና ፡ ሁሉ ንም፡ፈወሳቸው፡የጽድቅና፡የሕይወትንም፡ መንገድ ፡ እያስተማራቸው ፡ ከእነርሳቸው ፡ ዘንድ፡ስድስት፡ወር፡ኖረ።

፳፤ በእሑድም ፡ ዕለት ፡ ያቺ ፡ ብርህት ፡ ደመና ፡ ተሸክማ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ታደርሰውና ፡ ከል ጆቹ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ያረጋጋቸዋል ፡ በማግ ሥቱም ፡ ዳግመኛ ፡ ተሸክማ ፡ ወደ ፡ አፍር ንጊያ፡አገር፡ትመልሰዋለች።ከዚህም፡በኋላ፡ በእግዚአብሔር፡ ፈቃድ ፡ በደመና ፡ ተጭኖ ፡ ወደ፡ገዳሙ፡አንደኛውን፡ተመለሰ።

፳፩፤ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ ስንፍና ፡ መጣበት ፡ እንዲህ ፡ የሚለውም ፡ ቃል ፡ መጣ ፡ ታይ ፡ ዘንድ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ውጣ ፡በወጣ ፡ ጊዜም ፡ መልአኩን ፡ አየው ፡ በላዩም ፡ የምንኵስና ፡ ልብስ ፡ አለ ፡ መታጠቂያ ፡ ቅናት ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ ያለው ፡ ቀሚስ ፡ በወገቡም ፡ አስኬማ ፡ በራስ ፡ ቍር ፡ አምሳልም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ቆብ ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ ተቀምጦ ፡ ሰሌን ፡ ይታታል ፡ ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ ይጸልያል ፡ ዳግመኛም፡ተቀምጦ፡ሰሌኑን፡ይታታል፡በየ ሰዓቱም ፡ እንዲህ ፡ በማድረግ ፡ ይጸልያል ። ሁለተኛም፡እንዲህ፡የሚል፡ቃል፡ወደርሱ፡ መጣ ፡ እንጦንዮስ ፡ ሆይ ፡ እንደዚህ ፡ ሥራ ፡ አንተም ፡ ከስንፍና ፡ ከሰይጣናት ፡ ጦርነት ፡ ታርፋለህ ፡ ያንን ፡ ያየውንም ፡ ተቀብሎ ፡ እንዲሁ ፡ አስመስሎ ፡ የሚሠራ ፡ ሆነ ፡ ከዚያ ችም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ ስንፍናና ፡ የሰይጣናት ፡ ውጊያ፡አልመጣበትም።

፳፪፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተገልጾ ፡ አረጋግቶታል ፡ አጽንቶታልም ። አሁንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ የመረጥሁህ፡እንጦንዮስ፡ሆይ፡በእውነት፡እነ

ፃማከ ፡ ወተጋድሎትከ ፡ ወተጸምዶትከ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ፡ ባሕቲትከ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ዚአየ ፡ አነ ፡ አዐቢ ፡ ስመከ ፡ ወአሌዕል ፡ ቀርነከ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ።

፳፫፤ ወእሬስዮሙ ፡ ለአድባራት ፡ ወለገዳማት ፡ ከመ ፡ ማኅደሪሆሙ ፡ ለአርጋብ ፡ እንዘ ፡ ምሉዓን ፡ እመነኮሳት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ አደባራት ፡ ዘዚአከ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይነብሩ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዓለም ።

፳፬፤ ወኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ተዝካረከ ፡ ወይሁብ ፡ ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወመባአ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሰምከ ፡ አነ ፡ እደመስስ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአቶ ፡ ወኢይሬእያ ፡ ለደይን ፡ ግሙራ ፡ ወለደብር ፡ ዘቅቡር ፡ ውስቴቱ ፡ ሥጋከ ፡ አሌዕሎ ፡ ፈድፋደ ፡ ወእሬሲ ፡ ውስቴቱ ፡ መነኮሳተ ፡ ጻድቃነ ፡ ዘከመ ፡ መላእክት ፡ ወኢይትኃጣእ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይከውን ፡ ሊቀ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዓለም ፡ ወእሬስዮሙ ፡ ለነገሥተ ፡ ምድር ፡ ወለመሳፍንት ፡ ወለሥዩማን ፡ ከመ ፡ ይፁሩ ፡ አምኃ ፡ ለደብርከ ፡ ወለውሉድከ ፡ መነኮሳት ፡ እለ ፡ ተለው ፡ አሠረከ ፡ ወእምድኅረ ፡ ይቤሎ ፡ ዘንተ ፡ ዐርገ ፡ እግዚእነ ፡ እምኀቤሁ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ በዐቢይ ፡ ስብሐት ። ወተፈሥሐ ፡ አባ ፡ እንጦኒ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሐ ።

፳፭፤ ወእምዝ ፡ ተነበየ ፡ በእንተ ፡ ተመዝብሮታ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ንፉቃነ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሠለጡ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወእምዝ ፡ ትትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ሥርዓታ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወተነበየ ፡ ካዕበ ፡ በእንተ ፡ መነኮሳት ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይበዝኁ ፡ ፈድፋደ ፡ ወየኀድጉ ፡ ገዳማተ ፡ ወአድባራተ ፡ ወይወርዱ ፡ ወየኀድሩ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ ወአዕጻዳት ፡ ማዕከለ ፡ ዓለም ፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዓለም ።

፳፮፤ ወውእቱ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ዘአልበሶ ፡ ለአባ ፡ መቃርስ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወአስኬማ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ረድኡ ፡ ወወልዱ ፡ ወናዘዞ ፡ ወአጽንዖ ፡ ወአጠየቆ ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሁ ።

ግርሃለሁ ፡ እኔን ፡ ስለመውደድህ ፡ በዚች ፡ በረሀ ፡ ውስጥ ፡ ብቻህን ፡ በመጋደልህና ፡ በማገልገልህ ፡ ፡ ስለ ፡ ድካምህ ፡ ስምህን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርጋለሁ ፡ ሥልጣንህንም ፡ በዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ አደርገዋለሁ ።

፳፫፤ ገዳማትንና ፡ አድባራትንም ፡ መነኮሳትን ፡ የተመሉ ፡ ሁነው ፡ ቅኖች ፡ የዋሃን ፡ ጻድቃን ፡ እንደሚኖሩባቸው ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ይልቁንም ፡ ያንተ ፡ ገዳማት ፡ እነርሱ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ይኖራሉ ።

፳፬፤ መታሰቢያህንም ፡ የሚያደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ለድኖች ፡ ምጽዋትን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባ ፡ በስምህ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ኃጢአቱን ፡ ሁሉ ፡ እደመስሳለሁ ፡ ከቶ ፡ ሥቃይን ፡ አያያትም ፡ በውስጡ ፡ ሥጋህ ፡ የሚቀበርበትንም ፡ ገዳም ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገዋለሁ ፡ በውስጡም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ የሆኑ ፡ ደጋጎች ፡ መነኮሳት ፡ እንዲኖሩበት ፡ አደርጋለሁ ፡ ከእርሳቸውም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ አይታጣም ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ መሳፍንትና ፡ ሹማምንት ፡ ለገዳምህና ፡ ፍለጋህን ፡ ለሚከተሉ ፡ ልጆችህም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ተሸክመው ፡ እንዲመጡ ፡ አደርጋለሁ ፡ ጌታችንም ፡ ይህን ፡ ከተናገረው ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ዐረገ ፡ አባ ፡ እንጦኒም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለው ።

፳፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መፍረስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ መናፍቃን ፡ በላይዋ ፡ ይሠለጥናሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደቀድሞ ፡ ሥርዓቷ ፡ ትመለሳለች ፡ ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ መነኮሳት ፡ እነርሱ ፡ እጅግ ፡ እንደሚበዙ ፡ ገዳሞቻቸውንና ፡ አድባራቶችን ፡ በመተው ፡ ወርደው ፡ ከዓለማውያን ፡ መካከል ፡ በከተማዎችና ፡ በቦታዎች ፡ ውስጥ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜም ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

፳፮፤ ይህም ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ አባ ፡ መቃርስን ፡ አስኬማንና ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ ያለበሰው ፡ ያረጋጋውና ፡ ያጽናናው ፡ ከእርሱ ፡ የሚሆነውንም ፡ ያስረዳው ፡ ነው ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩና ፡ ልጁ ፡ ስለሆነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዕለት ፡ ሰማዕተ ፡ ኮነ ፡ ቅዱስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡
ሐዋርያ ፡ ረድኡ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡
መምህረ ፡ አሕዛብ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ልደቱ ፡ ወተሐፅኖቱ ፡
እምሀገረ ፡ ልስጥራን ፡ ወአቡሁ ፡ ዮናናዊ ፡
ዘያመልክ ፡ ከዋክብተ ፡ ወእሙሰ ፡ አይሁ
ዳዊት ፡ ዘታሕተ ፡ ጽላሎታ ፡ ለሕገ ፡ ኦሪት።
፫፡ ወሶበ ፡ሰበከ ፡ ጳውሎስ ፡ ብፁዕ ፡ ሐዋርያ ፡
ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ልስጥራን ፡ሰምዐ ፡ ዝንቱ ፡
ጢሞቴዎስ ፡ ስብከቶ ፡ ወትምህርቶ ፡ ወተአ
ምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ዘይገብር ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ዲበ ፡ እደዊሁ ፡ ለጳውሎስ ፡ ርእዮ ፡
ዘይደንግፅ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለባውያን ፡ ወጠ
ቢባን ፡ ወበእንተዝ ፡ቦአ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡
ጢሞቴዎስ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ወአ
ምነ ፡ ዲበ ፡ እደዊሁ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወተጠምቀ ፡
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡ቅዱስ ፡
ወኮነ ፡ ረድእ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወተ
ለዎ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ብዙኃ ፡ ወፃመወ ፡
ምስሌሁ ፡ ወበጽሐ ፡ ምንደቤ ፡ ዐቢይ ፡ ወኃ
ዘን ፡ ብዙኀ፡ ወሤሞ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡
ኤጴስቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ ዘኤ
ፌሶን።

፬፡ ወሶቤሃ ፡ ቦአ ፡ ውስቴታ ፡ ወሰበከ ፡ ለሰብአ፡
ዚአሃ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት ፡ ወሜጠሙ ፡ ለብዙ
ኃን፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወአጥ
መቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወእምዝ ፡
ሰበከ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ ብዙኃት፡ እለ ፡
የዓውድዋ ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡ ወለዘርኍቃተ ፡
ሀለዋ ፡ አህጉር ፡ ሰበከ ፡ ሎሙ ፡ ወንጌለ ፡
ቅዱሰ።
፭፡ ወጸሐፈ ፡ መንገሌሁ ፡ ሐዋርያ ፡ ብፁዕ ፡
ጳውሎስ ፡ ፪ተ ፡ መጻሕፍተ ፡ በዘይሜህሮሙ፡
ለሕዝብ ፡ ወበዘይትዓቀብ ፡ ለሊሁ ፡ እምነ ፡
ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ወለዘይደልዎ ፡ ከመ፡
ይሠየም ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆነ ፡ ወአዘዞ ፡
ከመ ፡ ኢያንብር ፡ እዴሁ ፡ ላዕለ ፡ ዘኢይ
ደልዎ ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ፡ አው ፡ እምቅ
ድመ ፡ ይፍትኖ። ወሎቱ ፡ ሰመዮ ፡ ለጢሞ

በዚች ፡ ዕለት ፡ አሕዛብን ፡ ለሚያስተምር ፡
ለከበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ የሆነ ፡
የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በሰማዕት
ነት ፡ ሞተ።
፪፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ልደቱና ፡ እድገቱ ፡ ልስጥራን
ከሚባል ፡ አገር ፡ ነው ፡ አባቱም ፡ ከዋክብ
ትን ፡ የሚያመልክ ፡ ዮናናዊ ፡ ነው ፡ እናቱ ፡ ግን ፡
በኦሪት ፡ ሕግ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ያለች ፡ ናት።
፫፡ የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ በልስጥራን ፡
ሀገር ፡ በሰበከ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ጢሞቴዎስ ፡
ስብከቱንና ፡ ትምህርቱን ፡ ሰማ ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ በጳውሎስ ፡ እጅ ፡ የሚያደርጋቸ
ውን ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አይቶ ፡
እሊህም ፡ ተአምራቶች ፡ አስተዋዮችና ፡ ጥበ
በኞች ፡ የሚደነግጡባቸው ፡ ናቸው ፡ ስለ
ዚህም ፡ ወደ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ሒዶ፡
በእርሱ ፡ ትምህርት ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመነ ፡
በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡
ተጠምቆ ፡ የሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዝ
ሙሩ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ አገሮችም ፡ ተከት
ሎት ፡ በመሔድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ደከመ ፡
ታላቅ ፡ መከራና ፡ ብዙ ፡ ኀዘንም ፡ ደርሶበታል፡
ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ በኤፌሶን ፡ ውስጥ ፡
በአንዲት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡
ሾመው።

፬፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወደርሷ ፡ ገብቶ ፡ ለሰዎቿ ፡
በክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ስም ፡ ሰበከ ፡ ብዙዎችንም ፡ ወደ፡
ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ መልሶ ፡ የክርስትና ፡
ጥምቀትን ፡ አጠመቃቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ፡
በዙሪያዋ ፡ ወዳሉ ፡ ብዙዎች ፡ አገሮች ፡
በርቀትም ፡ ለሚገኙ ፡ አገሮችም ፡ የከበረ ፡
ወንጌልን ፡ ሰበከላቸው።

፭፡ የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ሁለት ፡
መጻሕፍቶችን ፡ ጽፎ ፡ ወደርሱ ፡ ልኳል ፡ እር
ሳቸውም ፡ ሕዝቡን ፡ የሚያስተምርባቸው ፡
ራሱም ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ የሚጠበቅ
ባቸው ፡ ቅስና ፡ ወይም ፡ ዲቁና ፡ ሊሾም ፡
የሚገባውንና ፡ የማይገባውን ፡ የሚለይበት ፡
ክህነት ፡ በማይገባው ፡ እጁን ፡ እንዳይጭን ፡
የሚያስጠነቅቁ፡ ናቸው፡ ጢሞቴዎስን፡

www.ethiopianorthodox.org

ቴዎስ ፡ ወልዶ ፡ ወፍቁሮ ፡ ወፈነወ ፡ መል እክታቲሁ ፡ በላዕለ ፡ እዴሁ ፡ ኀበ ፡ አህጉር።

፯፡ ወሶበ ፡ ረዐየ ፡ ወዐቀበ ፡ መርዔቶ ፡ ለክርስ ቶስ፡ ዘተሠይመ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወአብርሀ ፡ አልባቢሆሙ፡ በትምህርታቲሁ፡ ወተግሣ ጻቲሁ፡ ወድርሳናቲሁ፡ ወኮነ ፡ ይጌሥጾሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ወለዮናናውያን ፡ ወእሙንቱ ፡ ቀንኡ ፡ ወተንሥኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ወተጋብኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወቀተልዎ፡ ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ መሀይምናን ፡ ወቀበርዎ፡ በህየ ፡ ወነበረ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ነግሠ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ጻድቅ ፡ ወውእቱ ፡ ሐለየ ፡ በእንተ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአፍ ለሶ ፡ ኀበ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ሀገር፡ አመ ፡ ፳ ወ ፲ ለወርኀ፡ ጥር ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ በዓለ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት።

፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ወበ ረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ደግሞ፡ ለርሱ ፡ ተወዳጅ ፡ ልጁ ፡ አድርጎ ፡ ይጠራዋል፡ መልእክቶቹንም፡ በእርሱ፡ እጅ፡ ወደ ፡ አገሮች ፡ ልኳል።

፯፡ በላያቸው ፡ የተሾመባቸውን ፡ የክርስቶስን ፡ መንጋዎች ፡ ፈጽሞ ፡ በጠበቀ ፡ ጊዜ ፡ በት ምህርቶቹ ፡ በተግሣጾቹና ፡ በድርሰቶቹ ፡ ልቡ ናቸውን ፡ ብሩህ ፡ አደረገ ፡ አይሁድንና፡ ዮናናውያንን ፡ ይገሥጻቸውና ፡ ይዘልፋቸው፡ ነበር ፡ እነርሱም ፡ ቀንተውበት ፡ ሁሉም ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡበት ፡ ተሰብስበውም ፡ ገደሉት ፡ ምእመናንም ፡ ሥጋውን ፡ አንሥ ተው ፡ ቀበሩት ፡ ጻድቅ ፡ ቍስጠንጢኖስም ፡ እስከ ፡ ነገሠ ፡ በዚያው ፡ ኖረ ፡ እርሱም ፡ ስለ ፡ ሥጋው ፡ አስቦ ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ከተማ፡በጥር ፡ ወር ፡ በሃያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ አፈለሰው ፡ በዚያችም ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደ ረገለት።

፰፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በዚህ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ዘተሠይመ ፡ ቀዋሚ። በመልእክተ ፡ ጳውሎስ ፡ መምህረ ፡ ሮሜ። ለዮናናውያን፡ ኮኖሙ ፡ ዘላፌ ፡ ወለአይሁድ ፡ ረጋሚ። እስከ ፡ አድምዐ ፡ በእዴሆሙ ፡ ዘስምዐ ፡ ሞቱ ፡ ፍጻሜ። እንተ ፡ ተወሰነ ፡ ሎቱ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜ።

፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕት ፡ ጌርሎስ ፡ ወአትናቴዎስ ፡ ወን ጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ ቴዎዶስዮስ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

፱፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ ሰማዕታት ፡ የጌርሎስና ፡ የአትናቴዎስ ፡ የጻድቁ ፡ ንጉሥ፡ የቴዎዶስዮስ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረ ከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላ ለሙ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለከ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ብፁዕ። ወንጉሥ ፡ ክሉል ፡ በጌራ ፡ መዊዕ። ኵነኔከ ፡ ጽድቅ ፡ ወፍትሕከ ፡ ርትዕ። ያስተፌሥሕ ፡ እምወይን ፡ ልበ ፡ ብእሲ ፡ ግፉዕ። ወገጸ ፡ ትኩዝ ፡ ዘጸልመ ፡ ያበርህ ፡ እምቅብዕ።

ሰላም ፡ ለክሣውዲክሙ ፡ በአስይፍት ፡ እለ ፡ ተመትራ። ከመ ፡ ትፈጽሙ ፡ በድረ ፡ ተረፈ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወመርቆሬ። ሰማዕታተ ፡ ክርስቶስ ፡ ኄራን ፡ ዕጉሣን፡ ሕማም ፡ ወመከራ ። ምስለ ፡ ሳሙኤል ፡ ወሱራፌ ፡ መልአከ፡ሰማይ፡ሐራ።ዲበ፡ርእስየ፡አንብሩ፡ዘለክሙ፡ጌራ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፬ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ቅድስት ፡ መስተጋድልት፡ ማር ያ ፡ ዘእምልሒቃነ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ከታ ላላቆቿ ፡ ወገን ፡ የሆነች ፡ የከበረች ፡ ተጋ ዳይ ፡ ማርያ ፡ አረፈች።

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ወለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ አበዊሃ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሶበ ፡ ልሕቀት ፡ ሐለዩ ፡ ያስተዋስብዋ ፡ ወይእቲሰ ፡ ኢፈቀደት ፡ ዘንተ ፡ ወሶበ ፡ አዕረፉ ፡ አቡሃ ፡ ወእማ ፡ ወሀበት ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ዘኀደጉ ፡ ላቲ ፡ ለነዳያን ፡ ወቦአት ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ ደብር ፡ እምአድባራተ ደናግል ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወለብሰት ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወተጋደለት ፡ ተጋድሎ ፡ ዐቢየ ፡ ወነበረት ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ትትጋደሎ ፡ ለንዋም ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ሞዐቶ ፡ ወኢትነውም ፡ ግሙራ ፡ ወኮነት ፡ በመጠነ ፡ እሉ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመታት ፡ ትጸውም ፡ ወትረ ፡ እስከ ፡ ምሴት ፡በከመ ፡ ሕገ ፡ ውእቱ፡ ደብር።

፫፤ ወእምዝ ፡ ለብሰት ፡ አስኬማ ፡ ቅዱሰ ፡ አሜሃ ፡ አውጽአት ፡ ዘላዕሌሃ ፡ አልባሳተ ፡ ፀምር ፡ ወለብሰት ፡ ሠቀ ፡ ወሰአለታ ፡ ለእመ ፡ ምኔት፡ ከመ ፡ ታብሓ ፡ ትሞቅሕ ፡ ርእሳ፡ ውስተ ፡ ጾማዕት ፡ እመ ፡ ትክል ፡ አው፡ አልቦ ፡ ወይእቲ ፡ አብሐታ ፡ ወይእተ፡ ጊዜ፡ ዐጸወት ፡ በዓታ ፡ ወሰቈረት ፡ ንስቲተ፡ መስኮተ ፡ በዘትትሜጠው ፡ ሲሳያ ፡ ወባቲ ፡ ትትሜጠ ፡ ምሥጢረ ፡ ቅድሳት። ወነበረት፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ በዓት ፡ ሙቅሕታ ፡ ፳ወ፪ት፡ ዓመተ።

፬፤ ወኮነት ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ መዋዕለ ፡ ትቀውም ፡ ወትጼሊ ፡ ወበጊዜ ፡ ንዋም ፡ ንስቲተ ፡ ትነውም ፡ ወተረፈ ፡ ሌሊትኒ ፡ ትቀውም ፡ ወትጼሊ ፡ እስከ ፡ ጽባሕ።

፭፤ ወኮነት ፡ ዘትጸውም ፡ በበ፪ መዓልት ፡ ወትሴሰይ ፡ ኀብስተ ፡ ይቡሰ ፡ ዘርሑስ ፡ በማይ ፡ ወበጾመ ፡ ፵ዓ ፡ ቅድስት ፡ ኢትበልዕ፡ ኀብስተ ፡ አላ ፡ አተረ ፡ ዘርሑስ ፡ በማይ ፡ እንዘ ፡ ተጸውም ፡ በበ፫ቱ ፡ ዕለት።

፮፤ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ በዓለ ፡ ጥምቀት ፡ ቅድስት ፡ አመ፡ ፲ወ፩ ለጥር ፡ ሰአለት ፡ ከመ ፡ ያምጽኡ ፡ ላቲ ፡ እማይ ፡ ቅዱስ ፡ ወአምጽኡ ፡ ላቲ ፡ ወተኀፀበት ፡ እደዊሃ ፡ ወገጻ ፡ ወተመጠወት ፡ ምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ፡ ወሰትየት ፡ እም ውእቱ ፡ ማይ ፡ ቅዱስ። ወእምዝ ፡ ደወየት ፡

፪፤ የዚችም ፡ ቅድስት ፡ ወላጆቿ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ፡ በአደገችም ፡ ጊዜ ፡ ሊአጋቧት ፡ አሰቡ ፡ እርሷ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ጋብቻ ፡ አልወደደችም ፡ እናትና ፡ አባቷም ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የተወላትን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉንም ፡ ለድኆች ፡ ሰጥታ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ውጭ ፡ ከአሉ ፡ ገዳማት ፡ወደ ፡ አንዱ ፡ ገዳም፡ ገባች ፡ የምንኵስና ፡ ልብስንም ፡ ለብሳ፡ ታላቅ፡ ተጋድሎን፡ ተጋደለች፡ ድል፡ እስካደረገችውም ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍን ፡ ዐሥራ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ስትታገለው፡ ኖረች ፡ ከቶ ፡ አትተኛም ፡ ነበር ፡ እንደዚያ ፡ ገዳም ፡ ሕግ ፡ በእሊህ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ዓመታት ፡ ሁልጊዜ ፡ እስከማታ ፡ ትጾም ፡ ነበር።

፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ እስኬማን ፡ ለበሰች፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከጥጥ ፡ ባዘቶ ፡ የተሠራውን ፡ ልብስ ፡ ከላይዋ ፡ አውልቃ ፡ ማቅ ፡ ለበሰች ፡ ትችል ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ አትችል ፡ እንደሆነ ፡ ራሷን ፡ ትፈትን ፡ ዘንድ ፡ ለመዝጋት ፡ ትፈቅድላት ፡ ዘንድ ፡ እመ ፡ ምኔቷን፡ለመነቻት፡እርሷም፡ፈቀደችላት፡ በዚያንም፡ጊዜ፡በዓቷን፡ዘጋች፡ምግቧን፡ የምትቀበልበት፡ ትንሽ ፡ መስኮት ፡ ቀደደች፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ በዚያው ፡ ትቀበላለች ፡ በዚያችም ፡ በዓት ፡ ውስጥ ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ዘግታ፡ ኖረች።

፬፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዘመን ፡ ቁማ ፡ ትጸልያለች ፡ በመኝታ ፡ ጊዜም ፡ ጥቂት ፡ ትተኛለች ፡ የቀረውንም ፡ ሌሊት ፡ እስቲነጋ ፡ ቁማ ፡ ስትጸልይ ፡ ታድራለች።

፭፤ በየሁለት ፡ ቀን ፡ የምትጾም ፡ ሆነች ፡ የምትመገበውም ፡ በውኃ ፡ የራሰ ፡ ለምለም፡ እንጀራ ፡ ነበር ፡ በከበረችም ፡ በአርባ ፡ ጾም ፡ እንጀራ ፡ አትበላም ፡ በየሦስት ፡ ቀን ፡ እየጾመች ፡ በውኃ ፡ የራሰ ፡ ሽምብራ ፡ ትመገባለች ፡ እንጂ።

፮፤ ጥር ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የከበረ ፡ የጥምቀት ፡ በዓልም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከተባረከው ፡ ውኃ ፡ ያመጡላት ፡ ዘንድ ፡ ለምና ፡ አመጡላት ፡ ፊቷንና ፡ እጆቿን ፡ ታጥባ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ተቀበለች ፡ ከተባረከውም ፡ ውኃ ፡ ጠጣች ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ታመመች ፡

www.ethiopianorthodox.org

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፫ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ብፁዕ ፡ ጴጥሮስ ፡ ጽሙድ። ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ቀዳሚ ፡ መጸብሐዌ ፡ ወውእቱ ፡ ግዙፈ፡ ልብ፡ ዘአልቦ፡ ምሕረት፡ ወይሰምይዎ፡ በዝንቱ፡ ስም፡ እኩይ፡ ዘአልቦ፡ ምሕረት።

፪፡ ወእምዝ ፡ ተሣሃለ ፡ ላዕሌሁ ፡ እግዚእነ ፡ ዘኢይፈቅድ፡ ሞቶ፡ ለኃጥእ፡ ፈነወ፡ ሎቱ፡ ፩ደ፡ ነዳየ፡ ዘይስእል ፡ ምጽዋተ ፡ እምኔሁ ፡ ወሰአሎ፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ በጽሐ ፡ ገብሩ ፡ ፀዊሮ ፡ ኅብስተ፡ ወነሥአ፡ አሐደ፡ ኅብስተ፡ እምላዕለ፡ ርእሰ፡ ገብሩ፡ ወወገረ፡ ሎቱ፡ ለውእቱ፡ ነዳይ፡ ወዘንተኒ ፡ ዘገብረ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ምሕረት፡ አላ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ እምኔሁ ፡ ወኢይግባእ ፡ ኀቤሁ፡ ግሙራ፡ ወነሢአ፡ ውእቱ፡ ምስኪን፡ ሖረ፡ ኀበ፡ ማኅደሩ።

፫፡ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንዘ ፡ ንውም ፡ ውእቱ ፡ ርእየ ፡ በሕልሙ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ ይትሐሰብዎ፡ ይፈቅዱ ፡ ወመዳልው ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ጸሊማን ፡ ዘሕሡም ፡ አርአያሆሙ ፡ ፈድፋደ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ኵሉ፡ ኃጣውኢሁ ፡ ወአንበርዎ ፡ ውስተ ፡ መድሎት፡ ዘፀጋም ፡ ወዓዲ ፡ ብዙኃን ፡ እመላእክት ፡ ብርሃናውያን ፡ ዘሠናይ ፡ አርአያሆሙ ፡ ወአልባሲሆሙ ፡ ፀዓድው ፡ ወእሙንቱ ፡ ይቀውሙ ፡ ወየኀዝኑ ፡ ወይብሉ፡ ምንተ ፡ ናንብር ፡ ውስተ ፡ መድሎት ፡ ዘየማን ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘረከብነ ፡ ምንተኒ ፡ ወሶቤሃ ፡ አምጽአ ፡ አሐዱ ፡ መልአክ፡ እምኔሆሙ ፡ ውእተ ፡ ኅብስተ ፡ ዘወገረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለነዳይ ፡ ወይቤ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ኢረከብኩ ፡ ሎቱ ፡ ካልአ ፡ እምገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ዘእንበለ ፡ ዛቲ ፡ ኅብስት ፡ ወአውሥኡ ፡ አብያጺሁ ፡ መላእክት፡ ወይቤሉ ፡ ምንተ ፡ ትበቍዕ ፡ ዛቲ ፡ በአንጻረ ፡ እሉንቱ ፡ ኃጣውኢሁ፡ ወሶቤሃ ፡ ነቅሐ ፡ እምንዋሙ ፡ እንዘ ፡ ይፈርህ ፡ ወይደነግፅ ፡ ወተንሥአ ፡ እምስካቡ።

፬፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ነስሐ ፡ በእንተ ፡ እኪት ፡ ምግባሩ ፡ ወኮነ ፡ መሐሬ ፡ ፈድፋደ ፡ ወወሀበ ፡ ቤቶ ፡ ወጥሪቶ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወሤጠ ፡ ርእሶ።

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ በገድል ፡ የተጸመደ ፡ የከበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ አረፈ ። ይህም ፡ ቅዱስ ፡ አስቀድሞ ፡ ቀራጭ ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ ልቡ ፡ የደነደነ ፡ ርኅራኄ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ ጨካኝ ፡ ርኅራኄ ፡ የሌለው ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል።

፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የኃጢአተኛን ፡ ሞት ፡ የማይሻ ፡ ጌታችን ፡ ከእርሱ ፡ ምጽዋት ፡ የሚለምነውን ፡ ድኃ ፡ ላከለትና ፡ ለመነው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አገልጋዩ ፡ እንጀራ ፡ ተሸክሞ ፡ ደረሰ ፡ አገልጋዩ ፡ ከተሸከመው ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ለዚያ ፡ ድኃ ፡ ጣለለት ፡ ይህንንም ፡ ያደረገ ፡ ስለ ፡ ርኅራኄ ፡ አይደለም ፡ ከአጠገቡ ፡ እንዲሔድለትና ፡ ከቶ ፡ ወደርሱ ፡ እንዳይመለስ ፡ ነው ፡ ምስኪኑም ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ ሔደ።

፫፡ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ በሕልሙ ፡ እንዲህ ፡ አየ ፡ ብዙዎች ፡ ሊተሳሰቡት ፡ ይሻሉ፡ በእጆቻቸውም ፡ ሚዛኖች ፡ ተይዘዋል፡ ብዙዎችም ፡ መልካቸው ፡ እጅግ ፡ የከፋ ፡ ጥቋቍሮች ፡ ኃጢአቱ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር፡ አለ ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ሚዛን ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት ፡ ደግሞ ፡ ልብሶቻቸው ፡ ነጫጭ ፡ የሆኑ ፡ ከብርሃናውያን ፡ መላእክት ፡ መልካቸው ፡ ያማረ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ፡ እነርሱም ፡ ቆመው ፡ በማዘን ፡ ምንም ፡ ያገኘነው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ በቀኝ ፡ ባለው ፡ ሚዛን፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ እናኖራለን ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከእርሳቸው ፡ አንዱ ፡ መልአክ፡ ጴጥሮስ ፡ ለድኃው ፡ የጣላትን ፡ ያችን፡ እንጀራ ፡ አምጥቶ ፡ ከዚች ፡ እንጀራ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ከበጎ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ አላገኘሁለትም ፡ አለ ፡ ባልንጀሮቹ ፡ መላእክትም ፡ በእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአቶቹ ፡ አንጻር ፡ ይቺ ፡ ምን ፡ ትጠቅማለች ፡ ብለው ፡ መለሱ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ እየፈራና ፡ እየደነገጠ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ ከተኛበት ፡ ተነሣ።

፬፡ ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ ስለቀደመች ፡ ክፉ ፡ ሥራው ፡ ተጸጸተ ፡ እጅግም ፡ የሚራራ ፡ ሆነ ፡ ቤቱንና ፡ ጥሪቱን ፡ ሁሉ ፡ ሸጦ ፡ ለድኆችና ፡ ለምስኪኖች ፡ ሰጠ ፡ ራሱንም ፡ ሸጠ።

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ ይቄድስዎ ፡ ወያነክርዎ ፡ በእንተ ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ እምሠናያት ፡ ገዮየ ፡ እምህየ ፡ ወቦአ ፡ ወስተ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወመንኰሰ ፡ በህየ ፡ ወተጸምደ ፡ በገድል ፡ ዐቢይ ፡ ወአሥመሮ ፡ለእግዚአብሔር ፡ ወአእሚሮ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ጸውዖሙ ፡ ለቅዱሳን፡ አረጋውያን፡ወተአምኆሙ፡ወአዕረፈ፡ሶቤሃ።

፮፡ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን

፭፡ ብዙዎችም ፡ ከበጎ ፡ ሥራዎች ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ሠራ፡ እንደሚአመሰግኑትና ፡ እንደሚያደንቁት ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ በመሸሽ ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ገብቶ ፡ ከአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ በዚያ ፡ መነኰሰ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ተጋድሎም ፡ ተጠምዶ ፡እግዚአብሔርን ፡ አገለገለው ፡ የዕረፍቱን ፡ ጊዜ ፡ አውቆ ፡ የከበሩ ፡ አረጋውያንን፡ጠርቶ፡ተሳለማቸውና፡በዚያን፡ጊዜ፡አረፈ።

፮፡ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጴጥሮስ ፡ እንተ ፡ ፈጸማ ፡ ወሠለጣ ። ለትእዛዘ ፡አብ ፡ ቀዲሙ ፡ ዘዜነወነ ፡በየውጣ ። ለጥሪተ ፡ ክብሩ፡ ወብዕሉ ፡ በሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡ እንዘ ፡ ይሠውጣ ። እምኀበ ፡ ይስእሎ ፡ ለዓይኑ ፡ ኢሜጣ ። እስከ ፡ ለአግአዚት ፡ ነፍሱ ፡ ከመ ፡ ገብር ፡ ሤጣ።

፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ቅዱስ ፡ ስብስትያኖስ ፡ ወልዱ ፡ ለንጉሠ ፡ ሮም ፡ ወውእቱ ፡ ዘተሐፅነ ፡ በተግሣጽ ፡ ወበፈሪሀ ፡እግዚአብሔር።

፰፡ ወእምድኅረ ፡ ሞተ ፡ አቡሁ ፡ ነግሡ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ወመክስምያኖስ ፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሤምዎ ፡ መኰንነ ፡ ወአክበርዎ ፡ ጥቀ ፡ ከመ ፡ አቡሁ።

፱፡ ወውእቱ ፡ የሐውር ፡ በጥበብ ፡ ወበለብዎ፡ ወይፌውስ ፡ ዙሎ ፡ ዱያነ ፡ ወይከሥት ፡ አዕይንተ ፡ ዕውራን ፡ በጸሎቱ ።

፲፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ክህደ ፡ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ዕልው ፡ አገበሮ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስብስትያኖስ ፡ ይስግድ ፡ ለጣዖት። ወሶበ ፡ ኢሰምዖ ፡ አዘዘ ፡ ይእሥርዎ ፡ ምስለ ፡ ዖም ፡ ይቡስ ፡ ወይንድፍዎ ፡ በአሕፃ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ወተሐዘቡ ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ወኀደግዎ ፡ ወበሌሊት ፡ መጽኡ ፡ መሃምናን ፡ ወረከብዎ ፡ ሕያወ ፡ ወፈትሕዎ ፡ ወወሰድዎ ፡ ማዕከለ፡ደሴት፡ወአንበርዎ፡በህየ።

፲፩፡ወሰሚዖ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡አብጽሐ፡ኀቤሁ፡ ወአዘዘ ፡ ይዝብጥዎ ፡ በአብትረ ፡ ኀፂን ፡ ወነበሩ፡እንዘ፡ይዘብጥዎ፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡ ወእምዝ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ወአስተርአያ ፡

፯፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ የከበረ ፡ ስብስትያኖስ፡ ምስክር ፡ ሁኖ ፡ ሞተ ፡እርሱንም፡ በተግሣጽና ፡እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ የአሳደጉት ፡ ነው።

፰፡ አባቱም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዲዮቅልጥያኖስና ፡ መክስምያኖስ ፡ ነገሡ ፡ ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ አገረ ፡ ገዥነት ፡ ሾሙት ፡ እንደ ፡ አባቱም ፡ እጅግ፡አከበሩት።

፱፡ እርሱም ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ ይጓዝ ፡ ነበር፡ በሽተኞችን ፡ ሁሉ ፡ የዕውራንንም ፡ ዐይኖች፡በጸሎቱ፡ከፈተ።

፲፡ከዚህም፡በኋላ፡የክብር፡ባለቤት ፡ክርስቶስን፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ በካደው ፡ ጊዜ ፡ ለጣዖት፡ይሰግድ፡ዘንድ፡ይህን፡ቅዱስ፡ስብስትያኖስን ፡ ግድ ፡ አለው ፡ ባልሰማውም ፡ ጊዜ ፡ ከደረቀ ፡ ግንድ ፡ ጋር ፡ አሠረው ፡ቍጥር ፡ በሌላቸው ፡ ፍላጻዎች ፡ ይነድፉት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እንደሞተም ፡ ጠርጥረው ፡ ትተውት ፡ ሔዱ ፡ ምእመናንም ፡ በሌሊት ፡ ሲመጡ ፡ በሕይወት ፡ አገኙት ፡ ፈትተውም ፡ ወደ ፡ ደሴት፡መካከል፡ወስደው፡በዚያ፡አኖሩት።

፲፩፡ዲዮቅልጥያኖስም፡ሰምቶ፡ወደርሱ፡አስቀረበውና ፡ በብረት ፡ ዘንጎች ፡ ይደበድቡት ፡ ዘንድ፡አዘዘ፡እየደበደቡትም፡ብዙ፡ቀኖች፡ ኖሩ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነፍሱን ፡ አሳለፈ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በሕልም ፡ ለቅድስት ፡ ውሉድስና ፡ ወነገራ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ሥጋሁ ፡ ወሐዊራ ፡ ነሥአቶ ፡ ወቀበረቶ ፡ ኀበ ፡ መቃብረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ። ወእግዚእነ ፡ ወሀቦ ፡ ኪዳነ ፡ ለዘይገብር ፡ ተዝካሮ ፡ ወይጼውዕ ፡ ስሞ ፡ ከመ ፡ ኢይቀርቦ ፡ ሕማመ ፡ ብድብድ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

ለቅድስት ፡ ውሉድስና ፡ በሕልም ፡ ተገልጦ ፡ ሥጋው ፡ ያለበትን ፡ ነገራት ፡ እርሷም ፡ ሒዳ ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ መቃብር ፡ ወስዳ ፡ ቀበረችው ። ጌታችንም ፡ መታሰቢያውን ፡ ለሚያደርግና ፡ ስሙን ፡ ለሚጠራ ፡ የቸነፈር ፡ ሕመም ፡ እንዳይቀርበው ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ሰጠው ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ስብስትያኖስ ፡ ሰማዕተ ፡ ዋሕድ ፡ ወልድ ። ዘንዱፍ ፡ በአሕፃ ፡ ወእሡር ፡ በጕንድ ። ተውላጠ ዝንቱ ፡ ፃማከ ፡ ወሕማምከ ፡ ፍድፉድ ። መጽሐፈ ፡ ገድልከ ፡ በኀበ ፡ ሀሎ ፡ ዐፀድ ። እግዚአብሔር ፡ አሕረመ ኢይባዕ ፡ ብድብድ።

፲፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሩ ፡ ለአስኪላ ፡ ሰማዕት ። ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

፲፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሰማዕት ፡ አስኪላ ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ሰማዕት ፡ አስኪላ ። ለሐረገ ፡ ወይን ፡ አስካላ ። በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኢይመውት ፡ በቃዔ ፡ ተድላ ። ተኖልወኒ ፡ በፍጽም ፡ ወዕቀበኒ ፡ በከዋላ ። ከመ ፡ ታንግፈኒ ፡ እምዘይንዐ ፡ ተኩላ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፯ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ አረጋውያን ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ መነኮሳት ፡ ፵ወ፱ወላእኩ ፡ ለንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ጻድቅ ፡ ወልደ ፡ አርቃዴዎስ ፡ ጻድቅ።

፪፡ ወምክንያተ ፡ ስምዖሙሰ ፡ እስመ ፡ ለንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡ ወፈነወ ፡ ኀበ ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ ዘገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ እንዘ ፡ ይስእሎሙ ፡ ከመ ፡ ይተን ብሉ ፡ ሎቱ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀቦ ፡ ወልደ። ወሀሎ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ፩አረጋዊ ፡ ዐቢይ ፡ ዘስሙ ፡ ቢስዱራ ፡ ወውእቱ ፡ ጸሐፈ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀብከ ፡ ወልደ ፡ ከመ ፡ ኢይደመር ፡ ምስለ ፡ ንፉቃነ ፡ ሃይማኖት ፡ እለ ፡ ይትነሥኡ ፡ እምድኀሬከ ። ወአንቢቦ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ ተፈሥሐ ፡ ንጉሥ ፡ ወአእኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕረፈ ፡ ሕሊናሁ።

፫፡ ወዓዲ ፡ አምከርዎ ፡ ሰብእ ፡ አብዳን ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ካልዕተ ፡ ይለድ ፡ ወልደ ፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የጻድቅ ፡ አርቃዴዎስ ፡ ልጅ ፡ በሆነ ፡ በጻድቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ የሆኑ ፡ የከበሩ ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ ከንጉሥ ፡ መልእክተኛ ፡ ከልጁም ፡ ጋር ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ።

፪፡ የሰማዕትነታቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ልጅ ፡ አልነበረውም ፡ በአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ወደሚኖሩ ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ ልጅን ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲማልዱለት ፡ እየለመናቸው ፡ መልእክትን ፡ ላከ ፡ ከውስጣቸውም ፡ ስሙ ፡ ቢስዱራ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ አረጋዊ ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ከሚነሡ ፡ መናፍቃን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንዳይሆን ፡ ልጅን ፡ ይሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልወደደም። መልእክቱን ፡ በአነበበ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነው ፡ ሃሳቡንም ፡ አሳረፈ።

፫፡ ዳግመኛም ፡ ግብዞች ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ በዙፋኑ ፡ የሚቀ

www.ethiopianorthodox.org

ዘይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ እምድኅሬሁ ፡ አውሥአሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢይገብር ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዞሙ ፡ ለአረጋውያን ፡ ቅዱሳን ፡ ዘገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ እስመ ፡ ዜናሆሙ ፡ በጽሐ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ።

ወፈነወ ፡ ዳግመ ፡ ላእከ ፡ ከመ ፡ ይሰአሎሙ ፡ ለአረጋውያን ፡ በእንተዝ ፡ ወሀለዎ ፡ ለላእከ ፡ ንጉሥ ፡ ወልድ ፡ ወሰአሎ ፡ ለአቡሁ ፡ ከመ ፡ ይሰዶ ፡ ምስሌሁ ፡ ኀበ ፡ አረጋውያን ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ በረከተ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወበጺሖ ፡ ውእቱ ፡ ላእክ ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ ኀበ ፡ አረጋውያን ፡ መጠዎሙ ፡ ክታበ ፡ ለንጉሥ ፡ ወእሙንቱ ፡ አንበብዋ ፡ አሜሃሰ ፡ ኢሀሎ ፡ አባ ፡ ቢስዱራ ፡ እስመ ፡ አዕረፈ ፡ ወአረጋውያን ፡ ነሥእዎ ፡ ለላእከ ፡ ንጉሥ ፡ ወአብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአባ ፡ ቢስዱራ ፡ ወይቤልዎ ፡ ለሥጋሁ ፡ ኦ ፡ አቡነ ፡ ናሁ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤነ ፡ መልእክቱ ፡ ለንጉሥ ፡ ወንሕነ ፡ ኢነአምር ፡ ዘንሰጠዎ ። ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ አባ ፡ ቢስዱራ ፡ አረጋዊ ፡ ወይቤ ፡ ኢይቤለኩ ፡ ኢፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀብከ ፡ ወልደ ፡ በልዎ ፡ ለንጉሥ ። ወይእዜኒ ፡ እመ ፡ አውሰበ ፡ ካልአተ ፡ አንስተ ፡ ኢይሁቦ ፡ ወልደ ፡ ከመ ፡ ኢይርኵሶ ፡ በትድምርተ ፡ ዓላውያን ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተመይጠ ፡ ወሰከበ ።

፫ ፡ ወጸሐፉ ፡ አረጋውያን ፡ ዘንተ ፡ ውስተ ፡ ክርታስ ፡ ወመጠውዎ ፡ ለላእከ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱኒ ፡ ላእክ ፡ ሶበ ፡ ተንሥአ ፡ ይግባእ ፡ ብሔሮ ፡ ሶቤሃ ፡ በጽሑ ፡ በርበር ፡ ወቆመ ፡ አረጋዊ ፡ ዘስሙ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለእሊአሁ ፡ ናሁ ፡ በጽሑ ፡ በርበር ፡ ይቅትሉነ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይኩን ፡ ሰማዕተ ፡ ይቁም ፡ ምስሌየ ፡ ወዘፈርሀሰ ፡ ይትኀባእ ፡ ኀበ ፡ ማኅፈድ ። ወቦ ፡ እለ ፡ ጐዩ ፡ ወእለ ፡ ተርፉ ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ መነኰሳት ፡ አረጋውያን ፡ ወተመይጠ ፡ ወልዱ ፡ ለላእከ ፡ ንጉሥ ፡ እምፍኖት ፡ ወርእዮሙ ፡ ለመላእክት ፡ እንዘ ፡ ያነብሩ ፡ አክሊላተ ፡ ዲበ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ለአረጋውያን ፡ ሰማዕታት ፡ ወስሙ ፡ ለውእቱ ፡ ወሬዛ ፡ ድያስ ፡ ወይቤሎ ፡ ለአቡሁ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እሬኢ ፡ መላእክተ ፡ መንፈሳውያነ ፡ እንዘ ፡ ያነብሩ ፡ አክሊላተ ፡ ዲበ ፡ አርእስ

መጥ ፡ ልጅን ፡ ይወልድ ፡ ዘንድ ፡ መከሩት ፡ እርሱም ፡ የትሩፋታቸው ፡ ዜና ፡ በዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ ደርሷልና ፡ በአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ከሚኖሩ ፡ ከቅዱሳን ፡ አረጋውያን ፡ ትእዛዝ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አላደርግም ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ።

፬ ፡ ስለዚህም ፡ አረጋውያንን ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተኛውን ፡ ዳግመኛ ፡ ላከ ፡ ለንጉሡም ፡ መልእክተኛ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ፡ ልጁም ፡ በረከታቸውን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ አረጋውያን ፡ እንዲወስደው ፡ አባቱን ፡ ለመነው ፡ መልእክተኛውም ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ አረጋውያን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጣቸው ፡ እነርሱም ፡ አነበቧት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አባ ፡ ቢስዱራ ፡ ስለሞተ ፡ አልተገኘም ፡ አረጋውያንም ፡ የንጉሡን ፡ መልእክተኛ ፡ የአባ ፡ ቢስዱራ ፡ ሥጋ ፡ ወዳለበት ፡ ወሰዱትና ፡ አደረሱት ፡ ሥጋውንም ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ የንጉሥ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ደረሰ ፡ እኛም ፡ የምንመልስለትን ፡ አናውቅም ፡ አሉት ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ቢስዱራ ፡ ተነሥቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅን ፡ ሊሰጥህ ፡ አልፈቀደም ፡ አላልኩህምን ፡ አለ ፡ በሉት ፡ ለንጉሥ ፡ አሁንም ፡ ከዓላውያን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ እንዳይረክስ ፡ ሌሎች ፡ ሴቶችንም ፡ ቢአገባ ፡ ልጅን ፡ አይሰጠውም ፡ ይህንንም ፡ ተናግሮ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ።

፫ ፡ አረጋውያንም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በክርታስ ፡ ጽፈው ፡ ለንጉሥ ፡ መልእክተኛ ፡ ሰጡት ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሊመለስ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ የበርበር ፡ አረማውያን ፡ ደረሱ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባል ፡ አረጋዊም ፡ ቁሞ ፡ ወገኖቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ እነሆ ፡ የበርበር ፡ ሰዎች ፡ ይገድሉን ፡ ዘንድ ፡ መጡ ፡ ምስክርነት ፡ የሚሻ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይቁም ፡ የሚፈራ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ግንብ ፡ ሒዶ ፡ ይሠወር ፡ አለ ። የሸሹም ፡ አሉ ፡ ከአባ ፡ ዮሐንስም ፡ ጋር ፡ የቀሩ ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳት ፡ የንጉሥ ፡ መልእክተኛም ፡ ልጅ ፡ ከጐዳና ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡ በአረጋውያን ፡ ሰማዕታት ፡ ራሶች ፡ አክሊላትን ፡ ሲያኖሩ ፡ መላእክትን ፡ አያቸው ፡ የዚያም ፡ ጐልማሳ ፡ ስሙ ፡ ድያስ ፡ ነው ፡ አባቱንም ፡ እነሆ ፡ በአረጋውያን ፡ ራሶች ፡ ላይ ፡ አክሊላ

www.ethiopianorthodox.org

ቲሆሙ ፡ ለአረጋውያን ፡ ወይእዜኒ ፡ አንሰ ፡ አሐውር ፡ እንግእ ፡ አክሊለ ፡ ከማሆሙ ፡ አቡሁኒ ፡ ይቤሎ ፡ አነኒ ፡ አሐውር ፡ ምስሌከ ፡ ኦ ፡ ወልድየ።

፯፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ከሠቱ ፡ ርእሶሙ ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ ለአረማውያን ፡ ወእሙንቱ ፡ ቀተልዎሙ ፡ ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ።

፰፡ ወእምድኅረ ፡ ሖሩ ፡ አረማውያን ፡ ወረዱ ፡ መነኮሳት ፡ እማኅፈድ ፡ ወአስተጋብኡ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ወገነዝዎሙ ፡ ወአንበርዎሙ ፡ ውስተ ፡ በዓት ፡ ወኮኑ ፡ ዘይጼልዩ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኵሎ ፡ ሌሊተ ፡ ወይዜምሩ ፡ ወይትባረኩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወመጽኡ ፡ ሰብእ ፡ ወሰረቁ ፡ ሥጋሁ ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወወሰድዎ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ባታኑን ፡ ወነበረ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ወእምዝ ፡ ነሥእዎ ፡ ቅዱሳን ፡ ወሜጥዎ ፡ ውስተ ፡ መካኑ።

፱፡ ወካልአን ፡ እምሀገረ ፡ ፍዩም ፡ ሰረቁ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወሬዛ ፡ ወሶበ ፡ አብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ፍዩም ፡ መሠጠ ፡ ወሜጠ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ሥጋ ፡ አቡሁ ፡ መነኮሳትኒ ፡ አመከርዎ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ፡ ወኮኑ ፡ ዘይፈልጥዎ ፡ ለሥጋ ፡ ወሬዛ ፡ እምሥጋ ፡ አቡሁ ፡ ወበጽባሕ ፡ ይረክብዎሙ ፡ ኅቡረ ፡ እስከ ፡ ርእየ ፡ ወሰምዐ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይቤሎ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡ ሶበ ፡ ሀሎነ ፡ በሥጋ ፡ ኢተፈለጥነ ፡ በበይናቲነ ፡ ወበኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስኒ ፡ ኢተፈለጥነ ፡ አንትሙ ፡ ለምንት ፡ ትፈልጡነ ፡ በበይናቲነ ፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ አልቦ ፡ ዘፈለጦሙ።

፲፡ ወሶበ ፡ አመዝበሩ ፡ አረማውያን ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ፈርሁ ፡ መነኮሳት ፡ በእንተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወአፍለስዎሙ ፡ እመካኖሙ ፡ ወአንበርዎሙ ፡ በገቦሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘቅዱስ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወሐነፁ ፡ ሎሙ ፡ መካነ ፡ ወበላዕሌሁ ፡ ሐነፅዋ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስሞሙ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለታውዳስዮስ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ሠርዐ ፡ ሎሙ ፡ በዓለ ፡ አመ ፡ ፭ለየካቲት ፡ ዘውእቱ ፡ አስተርእዮተ ፡ ሥጋ

ትን ፡ ሲያኖሩ ፡ ረቂቃን ፡ መላእክትን ፡ አያለሁ ፡ አሁንም ፡ እንደርሳቸው ፡ አክሊልን ፡ ለመቀበል ፡ እኔ ፡ እሔዳለሁ ፡ አለው ፡ አባቱም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እኔም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እሔዳለሁ ፡ አለው።

፯፡ በዚያችም ፡ ጊዜ ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ ለአረማውያን ፡ ተገለጡላቸው ፡ አረማውያንም ፡ ገደሏቸው ፡ የምስክርነት ፡ አክሊልንም ፡ ተቀበሉ።

፰፡ አረማውያንም ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ መነኮሳቱ ፡ ከተሠወሩበት ፡ ግምብ ፡ ወርደው ፡ የሰማዕታትን ፡ ሥጋቸውን ፡ ሰበሰቡ ፡ ገንዘውም ፡ በበዓት ፡ ውስጥ ፡ አኖሩዋቸው ፡ በእርሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ የሚጸልዩና ፡ የሚዘምሩ ፡ ከእርሳቸውም ፡ የሚባረኩ ፡ ሆኑ ፡ የአባ ዮሐንስንም ፡ ሥጋ ፡ ሰዎች ፡ ሰርቀው ፡ ባታኑን ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ወሰዱት ፡ ከእርሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ወደቦታው ፡ መለሱት።

፱፡ ሌሎችም ፡ ከሀገረ ፡ ፍዩም ፡ የጐልማሳውን ፡ ሥጋ ፡ ሰርቀው ፡ ወደ ፡ ፍዩም ፡ አገር ፡ ሲአደርሱት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ነጥቆ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሥጋ ፡ መለሰው ፡ መነኮሳቱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈተኑት ፡ የወጣቱን ፡ ሥጋ ፡ ከአባቱ ፡ ሥጋ ፡ የሚለዩት ፡ ሁነው ፡ ነበር ። በጥዋትም ፡ በአንድነት ፡ ያገኙአቸዋል ፡ ከመነኰሳቱም ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ እስኪያይና ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ። ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለን እርስበርሳችን ፡ አልተለያየንም ፡ በጌታችን ፡ ክርስቶስም ፡ ዘንድ ፡ አልተለያየንም ፡ እናንተ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ለምን ፡ ትለያዩናላችሁ ፡ ከዚያችም ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ የለያቸው ፡ የለም።

፲፡ አረማውያንም ፡ የአስቄጥስን ፡ ገዳም ፡ በአጠፉ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ ሥጋ ፡ መነኮሳቱ ፡ ፈሩ ፡ ከቦታቻውም ፡ አፍልሰው ፡ ወስደው ፡ በከበረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጐን ፡ አኖሩዋቸው ፡ የመቃብር ፡ ቦታም ፡ ሠሩላቸው ፡ በላዩም ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ታውዳስዮስ ፡ ዘመን ፡ በስማቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠሩላቸው ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ብንያሚንም ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የካቲት ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ በዓልን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሆሙ፡ቤተ፡ክርስቲያኖሙ፡ሂ፡ህለወት፡እስከ፡
ይእዜ፡ወዕውቅት፡በልሳነ፡ቅብጥ፡ብህም፡
ብሲት፡ዘ፡ብሂል፡ፃወ፱።

፲፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም
ሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለቅዱሳን፡ሰማዕት፡ወበረ
ከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ሠራላቸው፡ይኸውም፡ሥጋቸው፡የተገለ
ጠበት፡ነው፡ቤተ፡ክርስቲያናቸውም፡እስከ፡
ዛሬ፡አለች፡በቅብጢ፡ቋንቋ፡ብህም፡ብሲት፡
በመባል፡የታወቀች፡ናት፡ይህም፡አርባ፡
ዘጠኝ፡ማለት፡ነው።
፲፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በከበሩ፡ሰማዕታት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከታ
ቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘለለሙ፡
አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ሱቱፋነ፡ፃማ፡ወሕማም።አርባዓ፡ወተሰዓቱ፡አእሩግ፡ገዳም።ምስለ፡ላእከ፡ንጉሥ፡
ወወልዱ፡ዘተከለልክሙ፡ዮም።ለአንስጣስያ፡ቅድስት፡ዓዲ፡ሰላም።ጽንዐ፡ወራዙት፡ዘሞዐት፡በድካም።

፲፩፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈት፡አንስጣስያ፡
ቅድስት፡ወለተ፩፡ዘእምቤተ፡መንግሥት፡
ዐበይት፡ዘሀገረ፡ቍስጥንጥንያ።
፲፪፡ ወይእቲ፡ሠናይተ፡ላሕይ፡ፈድፋደ፡ወኀ
ሠሣ፡ብስጥያኖስ፡ንጉሥ፡ከመ፡ያውስባ፡
ወይእቲሰ፡ኢፈተወት፡ዘንተ፡በልባ፡እስመ፡
ብእሲቱ፡ለንጉሥ፡ሀለወት፡በሕይወታ፡
ወአጠየቀታ፡ለንግሥት፡ብእሲቱ፡ከመ፡
የኃሥሣ፡ንጉሥ፡ወሶቤሃ፡አስተፋነወታ፡
ንግሥት፡በኀቡእ፡በሐመር፡ኀበ፡ሀገረ፡
ግብጽ፡ወሐነፀት፡ላቲ፡ደብረ፡አፍአ፡ሀገረ፡
እስክንድርያ፡ወነበረት፡ህየ፡ወተሰምየ፡
ውእቱ፡ደብር፡በስማ።
፲፫፡ ወሶበ፡አእመረ፡ንጉሥ፡ከመ፡ቅድስት፡አንስ
ጣስያ፡ሀለወት፡ውስተ፡ብሔረ፡ግብጽ፡
ፈነወ፡ላእካነ፡ይኅሥሥዋ፡ወያምጽእዋ፡
ኀቤሁ፡ወጠይቃ፡ዘንተ፡ነገረ፡ተንሥአት፡
ወለብሰት፡አልባሰ፡ዕደው፡ወተመሰለት፡
መስፍነ፡ወሖረት፡ኀበ፡ገዳመ፡አስቄጥስ፡
ወቦአት፡ኀበ፡አባ፡ዳንኤል፡አበ፡ምኔት፡
ወከሠተት፡ሎቱ፡ኵሎ፡ምሥጢራ፡
ወውእቱ፡ወሰዳ፡ውስተ፡በዓት፡ባሕቲታ፡
ወኢያእመረ፡መኑሂ፡ከመ፡ይእቲ፡ብእሲት
ወአዘዞ፡አባ፡ዳንኤል፡ለአሐዱ፡አረጋዊ፡
ጻድቅ፡ከመ፡ይቅዳሕ፡ማየ፡በቀሱት፡
ለለኵሉ፡ሱባዔ፡ወያንብር፡ኀበ፡አንቀጸ፡
ውእቱ፡በዓት፡ወይሑር፡ወኢያእመረ፡ውእ
ቱኒ፡አረጋዊ፡ወነበረት፡ዛቲ፡ቅድስት፡አን
ስጣስያ፡ውስተ፡ይእቲ፡በዓት፡፳ወ፰ተ፡

፲፩፡ በዚችም፡ዕለት፡ከቍስጥንጥንያ፡ቤተ፡
መንግሥት፡ታላላቆች፡የአንዱ፡ልጅ፡የሆ
ነች፡ቅድስት፡አንስጣስያ፡አረፈች።
፲፪፡ እርሷም፡በላሕይዋ፡በደም፡ግባቷ፡እጅግ፡
ያማረች፡ናት፡ንጉሥ፡ብስጥያኖስም፡ሊአ
ገባት፡ፈለገ፡እርሷ፡ግን፡ይህን፡በልቧ፡አል
ወደደችም፡የንጉሡም፡ሚስቱ፡በሕይወት፡
ነበረች፡ንጉሡ፡እንደሚሻትም፡ለንግሥት፡
ሚስቱ፡አስረዳቻት፡በዚያንም፡ጊዜ፡ንግ
ሥቲቱ፡ወደ፡ግብጽ፡በመርከብ፡አሳፍራ፡
በሥውር፡ሸኘቻት፡ከእስክንድርያም፡
ከተማ፡ውጭ፡ገዳም፡አሠራችላት፡በዚያም፡
ኖረች፡ያም፡ገዳም፡በስሟ፡ተጠራ።
፲፫፡ የከበረች፡አንስጣስያም፡በግብጽ፡አገር፡
እንዳለች፡ንጉሥ፡በአወቀ፡ጊዜ፡ፈልገው፡
ወደርሱ፡ያመጡአት፡ዘንድ፡መልክተኞችን፡
ላከ፡ይህንንም፡ነገር፡ተረድታ፡ተነሣች፡
የወንዶችንም፡ልብስ፡ለብሳ፡መስፍንን፡
መሰለች፡ወደ፡አስቄጥስ፡ገዳም፡ሔዳ፡ወደ፡
አበ፡ምኔቱ፡ወደ፡አባ፡ዳንኤል፡ገባች፡ምሥ
ጢርዋን፡ሁሉ፡ገለጠችለት።እርሱም፡
ወስዶ፡በዋሻ፡ውስጥ፡ለብቻዋ፡አኖራት፡
እርሷም፡ሴት፡እንደሆነች፡ማንም፡
አላወቀም፡በየሳምንቱም፡በእንስራ፡ውኃ፡
ቀድቶ፡ከዚያ፡ዋሻ፡ደጃፍ፡እንዲያኖር፡
አንዱን፡ደግ፡አረጋዊ፡አባ፡ዳንኤል፡
አዘዘው፡ያም፡ሽማግሌ፡አያውቅም፡
ይችም፡ቅድስት፡አንስጣስያ፡በጸሎት፡
በጾምና፡በመስገድ፡በመትጋትም፡እየተጋ

www.ethiopianorthodox.org

ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ትትጋደል ፡ በጾም ፡ ወበ
ጸሎት፡ወበሰጊድ፡ወተጊሆት።

፲፬፡ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ ውእቱ ፡ አረጋዊ ፡ ዘኮነ ፡
ይቀድሕ፡ላቲ፡ማየ፡አዘዞ፡አባ፡ዳንኤል፡
ለረድኡ፡ይግበር፡በከመ፡ይገብር፡ውእቱ፡
አረጋዊ ፡ ወኮነት ፡ ቅድስት ፡ አንስጣስያ ፡
ዘትጽሕፍ ፡ ሕሊናሃ ፡ ውስተ ፡ ገልዕ ፡
ወታነብሮ ፡ በአንቀጸ ፡ በዓታ ፡ ወረድኡ ፡
ይወስዶ፡ለአባ፡ዳንኤል፡መምህሩ፡ወኢየ
አምር፡ምንት፡ውእቱ፡ዘትጽሕፍ፡ውእቱ፡
ረድእ።

፲፭፡ወአሐተ፡ዕለተ፡አምጽአ፡ገልዐ፡ዘጸሐፈት፡
ቦቱ፡ወሶበ፡አንበባ፡አባ፡ድንኤል፡በከየ፡
ወይቤሎ፡ለረድኡ፡ተንሥእ፡ኦ፡ወልድየ፡
ንሑር፡ወንቅብር፡ሥጋሁ፡ለዝንቱ፡ቅዱስ፡
እስመ፡ዝንቱ፡ይፈልስ፡እምዝንቱ፡ዓለም።
ወሶበ ፡ ሖሩ ፡ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ በዓታ ፡
ወተባረኩ፡እምኔሃ፡ወይእቲ፡ትቤሎ፡ለአባ፡
ዳንኤል፡ኦ፡አቡየ፡በእንተ፡እግዚአብሔር፡
ኢትግንዘኒ ፡ በምንትኒ ፡ ልብስ ፡ ዘእንበለ ፡
ዝንቱ፡ዘላዕሌየ፡ወእምዝ፡ተነሥኢአ፡ጸለየት፡
አንስጣስያ፡ብፅዕት፡ወትቤ፡አንሰ፡አማዕቀ
ብኩክሙ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ወነበረት፡
ዲበ፡ምድር፡ወአዕረፈት፡ወበከዩ፡ላዕሌሃ፡
ወሐለዩ ፡ ከመ ፡ ይቅብርዋ ፡ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡
ኀቤሃ፡ረድእ፡ከመ፡ይግንዛ፡ነጸረ፡አጥባዕቲሃ፡
ከመ ፡ አቈጽለ ፡ በለስ ፡ ዘየብሳ ፡ እምብዝኀ ፡
ተጸምዶታ ፡ ኮነ ፡ ከመዝ ፡ ወርእየ ፡ አንከረ ፡
አባ፡ዳንኤል፡ወአርመመ።

፲፯፡ ወእምድኅረ ፡ ቀበርዋ ፡ ተመይጡ ፡ ኀበ ፡
በዓቶሙ ፡ ወቀርበ ፡ ረድኡ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡
ለአባ ፡ ዳንኤል ፡ ወሰአሎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንግረኒ ፡ ዜናሃ ፡
ለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ እስመ ፡ ርኢኩ ፡ ከመ ፡
ብእሲት ፡ ይእቲ ፡ ወአባ ፡ ዳንኤል ፡ አኀዘ ፡
ይንግሮ ፡ ዜና ፡ ገድላ ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡
ይእቲ ፡ እምልሒቃነ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡
ዘሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ወወሀበት ፡ ነፍሳ ፡
ለክርስቶስ ፡ ወኀደገት ፡ ክብረ ፡ ዝንቱ ፡
ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ዝንቱኒ ፡ ተግሣጽ ፡ ለነ ፡
ለዕደው፡እምዛቲ፡ብእሲት፡በእንተ፡ዝንቱ፡

ደለች፡ሃያ፡ስምንት፡ዓመት፡ኖረች።ውኃ፡
ሲቀዳላት ፡ የነበረ ፡ ያ ፡ ሽማግሌ፡ በአረፈ ፡
ጊዜ፡አባ፡ዳንኤልም፡ያ፡ሽማግሌ፡ሲሠራ፡
እንደ፡ነበረ፡ይሠራ፡ዘንድ፡ረዳቱን፡አዘዘው
ቅድስት ፡ አንስጣስያም ፡ ሀሳቧን ፡ በገል ፡
ላይ፡እየጻፈች፡በበዓቷ፡ደረጃፍ፡ታኖረው፡
ነበር፡ረድኡም፡ወደ፡መምህሩ፡ወደ፡አባ፡
ዳንኤል፡ ይወስደዋል ። የምትጽፈውንም ፡
ምን፡እንደሆነ፡አያውቅም።

፲፭፡ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ የጻፈችበትን ፡ ገል ፡
አመጣ፡አባ፡ዳንኤልም፡በአነበባት፡ጊዜ፡
አለቀሰ፡ረድኡንም፡ልጄ፡ሆይ፡ተነሥ፡
የዚያን ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ሥጋ ፡ ሒደን ፡
እንቅበር፡እርሱ፡ ከዚህ፡ዓለም፡ይለያልና፡
አለው ። በሔዱም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ በዓቷ ፡
ገብተው፡ከእርሷ፡ተባረኩ፡እርሷም፡አባ፡
ዳንኤልን፡አባቴ፡ሆይ፡ስለ፡እግዚአብሔር፡
ብለህ፡በላዬ፡ካለው፡በቀር፡በምንም፡ልብስ፡
እንዳትገንዘኝ ፡ አለችው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
የከበረች፡አንስጣስያ፡ተነሥታ፡ጸለየች፡እኔ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ አስጠበቅ
ኋችሁ ፡ አለችና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡
አረፈች ፡ በላይዋም ፡ አለቀሱ ፡ ሊቀብሩ
ዋትም፡አሰበው፡ረድኡ፡ይገንዛት፡ዘንድ፡
ሲቀርብ፡እንደ፡በለስ፡ቅጠሎች፡ደርቀው፡
ጡቶቿን፡ተመለከተ።ከተጋድሎ፡ብዛትም፡
የተነሣ፡እንዲህ፡ሁኗልና፡አባ፡ዳንኤልም፡
አይቶ፡በማድነቅ፡ዝም፡አለ።

፲፯፡ ከቀበርዋትም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በዓታቸው ፡
ተመለሱ ፡ ረድኡም ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡
ቀርቦ፡ሰገደለትና፡እንዲህ፡ሲል፡ለመነው፡
ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ የዚችን ፡ ቅድ
ስት፡ዜናዋን፡ንገረኝ፡ሴት፡እንደሆነች፡አይ
ቻለሁና ። አባ ፡ ዳንኤልም ፡ የገድሏን ፡ ዜና ፡
ሊነግረው ፡ ጀመረ ፡ እንዲህም ፡ አለው፡
እርሷ፡ከቍስጥንጥንያ፡አገር፡ከመንግሥት፡
ታላላቅ፡ወገኖች፡ውስጥ፡የሆነች፡ስትሆን፡
ሰውነቷን፡ለክርስቶስ፡ሰጥታ፡የዚህን፡የኃላ
ፊውን፡ዓለም፡ክብር፡ሁሉ፡ተወች። ስይጣ
ንን፡ከተዋጋችበት፡ከዚህ፡ከታላቅ፡ተጋድ

www.ethiopianorthodox.org

ተጋድሎ ፡ ዐቢይ ፡ ዘተጋደሎቶ ፡ ለሰይጣን ፡ ወኀደጎት ፡ እምኔሃ ፡ ድካመ ፡ አንስት ፡ እስከ ፡ ነሥአት ፡ ጽንዖሙ ፡ ለዕደው ፡ ኃያላን ፡ ወአሥመረቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፲፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፲፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ መጥረያስ ፡ ወስርስንዮስ ፡ ሰማዕት ፡ ወዮሴፍ ፡ መፍቀሬ ፡ ነዳያን ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

ሎዋ ፡ ለእኛ ፡ ለወንዶች ፡ መመከሪያ ፡ ሊሆነን ፡ ይገባል ፡ ከእርሷም ፡ የሴቶችን ፡ ደካማነት ፡ አርቃ ፡ የኃይለኞች ፡ ወንዶችን ፡ ብርታት ፡ ገንዘብ ፡ እስከማድረግ ፡ ደርሳ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለገለችው ።

፲፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፲፰፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ መጥረያስ ፡ የስርስንዮስ ፡ ሰማዕት ፡ የመፍቀሬ ፡ ነዳያን ፡ ዮሴፍ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዮሴፍ ፡ ለጠቢት ፡ አምሳሉ ። እስመ ፡ ዘረወ ፡ በምጽዋት ፡ እንበለ ፡ ያትርፍ ፡ ጥሪተ ፡ ብዕሉ ። ትእዛዘ ፡ አምላክ ፡ ዘይቤ ፡ ሰሚዖ ፡ በውስተ ፡ ወንጌሉ ። ዘገበርክሙ ፡ ለአሐዱ ፡ እምነ ፡ ንኡሳን ፡ እሉ ። ይትሔሰብሂ ፡ ወይትሔለይ ፡ ኵሉ ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ ወ ፪ ለጥር ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ እምሀገረ ፡ በብኑዲ ፡ እምደቡብ ፡ ግብጽ ፡ እምደወለ ፡ ምስር ፡ ታሕቲት ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋይ ፡ ወጥሪት ፡ ወእንስሳ ፡ ወውእቱ ፡ መፍቀሬ ፡ ምጽዋት ፡ ብዙኀ ፡ ወከዊኖ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ። ወሰምዐ ፡ ከመ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ መኰንን ፡ የዐውድ ፡ በበአህጉር ፡ ይኀሥሦሙ ፡ ወይኴንኖሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወወጽአ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሀገሩ ፡ ከመ ፡ ይኅሥሦ ፡ ለመኰንን ፡ ወኮኑ ፡ ሎቱ ፡ አዕርክት ፡ ዘስሞሙ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወካልኡ ፡ ሰርማ ፡ ኖላዌ ፡ አባግዕ ፡ ወተለውዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሰራብዮን ። ወሶበ ፡ ረከበ ፡ ለመኰንን ፡ ቆመ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወተአመነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ምስለ ፡ እሊአሁ ፡ መኰንንኒ ፡ ሞቅሖሙ ፡ ለኵሎሙ ።

፫፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ተጋብኡ ፡ ወበጽሑ ፡ ኵሎሙ ፡ ወኮኑ ፡ ትዕይንተ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ እንዘ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይቅትልዎ ፡ ለመኰንን ፡ ወይንሥእዎ ፡ እምእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ ወቅዱስሰ ፡

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥር ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ከግብጽ ፡ ደቡብ ፡ ከታችኛዪቱ ፡ ምስር ፡ አውራጃ ፡ በብኑዲ ፡ ከምትባል ፡ መንደር ፡ የከበረ ፡ ሰራብዮን ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ።

፪፡ ለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ብዙ ፡ የገንዘብ ፡ ጥሪት ፡ እንስሳትም ፡ አሉት ፡ አብዝቶ ፡ መመጽወትንም ፡ የሚወድ ፡ ነው ፡ ስደትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖችን ፡ ፈልጎ ፡ ያሠቃይ ፡ ዘንድ ፡ መኰንኑ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ በየሀገሩ ፡ እንደሚዞር ፡ ሰማ ፡ ለርሱም ፡ ስማቸው ፡ ቴዎድሮስና ፡ ሁለተኛውም ፡ በግ ፡ አርቢ ፡ ሰርማ ፡ የሚባሉ ፡ ወዳጆች ፡ ነበሩት ፡ እነርሱም ፡ ተከተሉት ፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ መኰንኑን ፡ ሊገናኘው ፡ ከሀገሩ ፡ ወጣ ፡ መኰንኑንም ፡ በአገኘው ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ቁሞ ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋር ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታመነ ፡ መኰንኑም ፡ ሁሉንም ፡ አሠራቸው ።

፫፡ የሀገር ፡ ሰዎችም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበሰቡ ፡ መኰንኑን ፡ ገድለው ፡ ቅዱስ ፡ ሰራብዮንን ፡ ከእጁ ፡ ሊወስዱ ፡ ሽተው ፡ የጦር ፡ መግሪያ ፡ በመያዝ ፡ ለጦርነት ፡ የተሰለፉ ፡ ሠራዊት ፡ ሁነው ፡ ደረሱ ፡ ቅዱሱ ፡ ግን ፡ ከለከ

www.ethiopianorthodox.org

ሰራብዮን ፡ ከልአሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አኮኑ ፡ አንሰ ፡ በፈቃድየ ፡ መጻእኩ ፡ ከመ ፡ እክዐው ፡ ደምየ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ እግዚእየ ፡ ወመኰንንኒ ፡ ሐረ ፡ ተጽዒኖ ፡ ዲበ ፡ ሐመር ፡ ወቅዱሳንኒ ፡ ምስሌሁ ፡ ሐሩ።

፬፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይኰንንዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ በመንኰራኵር ፡ ኵነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ ወይደይዎ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ወእምዝ ፡ አፍልሕዎ ፡ ውስተ ፡ ጻሕል ፡ ምስለ ፡ ዝፍት ፡ ወቅጥራን ፡ ወመተሩ ፡ አሥራወ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአስከብዎ ፡ ውስተ ፡ ዐራተ ፡ ኀፂን ፡ ወቀነውዎ ፡ በቅንዋት ፡ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ኵነኔ ፡ ይትዔገሥ ፡ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፀውር ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ኵነኔ።

፭፡ ወእምዝ ፡ ስቀልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ወነደፍዎ ፡ በአኅፃ ፡ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አውረዶ ፡ እምስቅለት ፡ ወአሠሮ ፡ ለመኰንን ፡ ወሰቀሎ ፡ ህየንቴሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ኢትወርድ ፡ እምላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ዕፅ ፡ ዑቅ ፡ እስከ ፡ ታወጽአሙ ፡ ለኵሎ ፡ መቁሐን ፡ እለ ፡ በክርስቶስ ፡ ወትኤዝዝ ፡ ፍጻሜ ፡ ሞቶሙ ፡ ወሶቤሃ ፡ አዘዘ ፡ ያውጽእዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ወይምትሩ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ በአስይፍት ፡ ወመተርዎሙ ፡ ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ዕደው ፡ ፭፻ወ፵ነፍስ።

፮፡ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ ለ፩መኰንን ፡ ከመ ፡ ይንሥእ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ ምስሌሁ ፡ ወይሰዶ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ከመ ፡ ይኰንኖ ፡ በህየ ፡ ወለእመ ፡ ኢተመይጠ ፡ እምክሩ ፡ ከመ ፡ ይምትር ፡ ርእሶ ፡ መኰንንኒ ፡ ነሥአ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ ወከዊኖ ፡ ሌሊተ ፡ በጽሑ ፡ ውስተ ፡ ፩ መርሶ ፡ ወኖሙ ፡ በህየ ፡ ወበፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽሐት ፡ ይእቲ ፡ ሐመር ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ ወሶበ ፡ ነቅሑ ፡ በጽባሕ ፡ ረከቡ ፡ መካነ ፡ ዘተወለጠ ፡ እምሕዋሮሙ ፡ አንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ ሰራብዮን ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡

ላቸው ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ በጌታዬ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ደሜን ፡ አፈስ ፡ ዘንድ ፡ በፈቃዴ ፡ የመጣሁ ፡ አይደለምን ፡ መኰንኑም ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍሮ ፡ ከዚያ ፡ ሔደ ፡ ቅዱሳኑም ፡ አብረውት ፡ ሔዱ።

፬፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ አገርም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ ሰራብዮንን ፡ በመንኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ ጽኑዕ ፡ ሥቃይን ፡ እንዲአሠቃዩት ፡ ወደ ፡ እሳት ማንደጃም ፡ ይጨምሩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከነዳጅ ፡ ድፍድፍና ፡ ቅመማ ቅመም ፡ ጋር ፡ ቢወጭት ፡ ውስጥ ፡ ቀቀሉት ፡ የሥጋውንም ፡ ሥሮች ፡ ቆረጡ ፡ በብረት ፡ ዐልጋ ፡ ላይም ፡ አስተኙትተው ፡ በችንካር ፡ ቸነከሩት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥቃይም ፡ የሚታገሥ ፡ ሆነ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ሥቃዩን ፡ ከላዩ ፡ ይቀበልለት ፡ ነበር።

፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡ በፍላፃዎች ፡ ነደፉት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ እርሱን ፡ ከተሰቀለበት ፡ አውርዶ ፡ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡ መኰነኑን ፡ አሥሮ ፡ ሰቀለው ። የከበረ ፡ ሰራብዮንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ የታሠሩትን ፡ ሁሉንም ፡ እስከምታወጣቸውና ፡ የሞታቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ እስከምታዝዝ ፡ አንተ ፡ ከእዚህ ፡ ከተሰቀልክበት ፡ ዕንጨት ፡ እንደማትወርድ ፡ ዕወቅ ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉንም ፡ አውጥተው ፡ ራሶቻቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘና ፡ ቆረጧቸው ፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀበሉ ፡ የእሊህመ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ነፍስ ፡ ሆነ።

፮፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ ሰራብዮንን ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወስዶ ፡ ያሠቃየው ፡ ዘንድ ፡ ከኀሳቡም ፡ ካልተመለሰ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጥ ፡ ዘንድ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ አንዱን ፡ መኰንን ፡ አዘዘው ። መኰንኑም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡ ወሰደው ፡ ሌሊትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወደብ ፡ ደርሰው ፡ በዚያ ፡ ተኙ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ ያቺ ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ሰራብዮን ፡ አገር ፡ ደረሰች ፡ በጥዋትም ፡ በነቁ ፡ ጊዜ ፡ የመሔጃቸው ፡ አቅጣጫ ፡ ተለውጦ ፡ አገኙ ፡ እጅግም ፡ አደነቁ ፡ ወደ ፡ ሰራብዮንም ፡ እነሆ ፡ ይቺ ፡ ሀገርህ ፡ ናት ፡

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡እንተ፡ረከብከ፡ሞገሰ። ኅቡአተ፡ትፍትን፡ወዘማዕምቅት፡ከርሠ። ሱርያል፡መልአክ፡ እንዘ፡ትስእል፡መንፈሰ።ፍጥረታተ፡ኵሎ፡አመ፡በማየ፡አይኅ፡ደምሰሰ። እግዚአብሔር፡አትረፈ፡ ሰማኒተ፡ነፍሰ።

፲፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን፡ወዝንቱ፡ኮነ፡ድንግለ፡እምንእሱ፡ ወመፈቀሬ፡እግዚአብሔር፡ወመሐሬ፡ነዳ ያን፡ወምስኪናን፡ወመናኔ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ ኃላፊ ።

፲፪፡ወኮነ፡አቡሁ፡እምዘመደ፡ክቡራን፡ወስሙ፡ አንስጣስዮስ፡ወስመ፡እሙ፡ሶስና፡ወእሙ ንቱ፡ክርስቲያን፡መፍቀርያነ፡ምጽዋት፡ ወይገብሩ፡በዓላተ፡ዘእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ወዘእግዝእትነ፡ማርያም፡ድን ግል፡ወዘኵሎሙ፡ሰማዕታት፡በውሂበ፡ ምጽዋት፡ለነዳያን፡ወምስኪናን፡ወንበረ ቶሙኒ፡ውስተ፡ሀገረ፡አውሲም፡እምደወለ፡ ምስር።

፲፫፡ ወወሀቦሙ፡እግዚአብሔር፡ዘንተ፡ወልደ፡ ቡሩከ፡ቢፋሞንሃ፡ዘኮነ፡አርአያሁ፡ሠናየ፡ ፈድፋደ፡ወተፈሥሑ፡ቦቱ፡ወአፈድፈዱ፡ ገቢረ፡ሠናይ፡ወኂሩተ፡ወሶበ፡ልሕቀ፡ ወበጽሐ፡መዋዕሊሁ፡፲ዓመተ፡መጠውዎ፡ ለ፩ ቀሲስ፡ፈራሄ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ ይምህሮ ፡ ውእቱኒ ፡ ነሥኦ ፡ ወመሀሮ ፡ ጽሕፈተ፡ወጥበበ፡ወተግሣጸ፡ወአጽንዖ፡ መጻሕፍተ፡ቤተ፡ክርስቲያነ፡ቅድስት፡ ወኮነ፡ወትረ፡ይጸመድ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡ወይትጋደል፡በጾም፡ወበጸሎት፡ ወበሰጊድ፡በተጊህ፡ጥቀ።

፲፬፡ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር፡ ዲበ፡ እደዊሁ፡ ተአምራተ፡ወመንክራተ፡ብዙኃተ፡ወእም እሉ፡እስመ፡ሀሎ፡፩ ነዳይ፡ዘደወየ፡በደዌ፡ ቍስል፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡ወሰአሎ፡ለቅ ዱስ፡ቢፋሞን፡ምጽዋተ፡ወሶበ፡ሰፍሐ፡ እዴሁ፡የሀቦ፡ሶቤሃ፡ሐይወ፡እምደዌሁ፡ ወኮነ፡ ጥዑየ ፡ ወረትዐ፡ ኵሉ ፡ መለያል ያቲሁ።

፲፭፡ ወካዕበ፡ በካልዕ፡ ጊዜ፡ እንዘ ፡ ይዛዋዕ ፡ በመዝሙረ፡ዳዊት፡ወሀሎ፡ሀየ፡፩ ብእሲ፡

፲፩፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበረ ፡ ቢፋሞን ፡ በሰማዕ ትነት፡ሞተ፡ይህም፡ከታናሽነቱ፡ድንግል፡ የሆነ፡እግዚአብሔርን፡የሚወድ፡ለድኆ ችና፡ለችግረኞች፡የሚመጸውት፡ይህንንም፡ ዓለም፡ንቆ፡የተወ፡ነው።

፲፪፡አባቱም፡ከከበሩ፡ወገኖች፡የሆነ፡ስሙ፡አንስ ጣስዮስ ፡ የእናቱም ፡ ስም ፡ ሶስና፡ ነው። እነርሱም፡መመጽወትን፡የሚወዱ፡ክርስቲ ያኖች፡ናቸው፡የጌታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስ ቶስን፡የእመቤታችንን፡ድንግል፡ማርያምን፡ የከበሩ ፡ ሰማዕታትንም ፡ ሁሉ ፡ በዓላት ፡ ለድኆችና፡ለምስኪኖች፡ምጽዋትን፡በመስ ጠት፡ያከብራሉ፡የሚኖሩትም፡በምስር፡ አውራጃ ፡ አውሲም ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ውስጥ፡ነው።

፲፫፡ እግዚአብሔርም፡መልኩ፡እጅግ፡ያማረ፡ ይህን ፡ የተባረከ ፡ ልጅ ፡ ቢፋሞንን ፡ ሰጣ ቸው፡በእርሱም፡ደስ፡ብሏቸው፡በጎ፡መሥ ራትንና፡ትሩፋትን፡አበዙ፡አድጎ፡ወደ፡ ዘጠኝ፡ዓመትም፡ሲደርስ፡ያስተምረው፡ ዘንድ፡እግዚአብሔርን፡ለሚፈራ፡አንድ፡ ቄስ፡ሰጡት፡እርሱም፡ተቀብሎ፡ወስዶ፡ ጥበብን ፡ ጽሕፈትን ፡ ተግሣጽን ፡ አስተ ማረው፡የቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያንንም፡ መጻሕፍት፡አጠና፡በቤተ፡ክርስቲያንም፡ ሁል፡ጊዜ፡ያገለግላል፡እጅግ፡በመትጋትም፡ በጾም፡በጸሎት፡በመስገድ፡ይጋደል፡ነበር።

፲፬፡ እግዚአብሔርም፡በእጆቹ፡ብዙዎች፡የሆኑ፡ ድንቆች፡ተአምራቶችን፡አደረገ፡ከእሊህ፡ በቍስል፡ ደዌ፡ እጆቹንና ፡ እግሮቹን ፡ የታ መመ፡አንድ፡ድኃ፡ነበረ፡የከበረ፡ቢፋሞንን፡ ምጽዋትን፡ለመነው፡ሊሰጠውም፡እጁን፡ ሲዘረጋ፡በዚያን፡ጊዜ፡ከደዌው፡ድኖ፡ጤነኛ፡ ሆነ፡ሕዋሳቱም፡ሁሉ፡ጠነከሩ።

፲፭፡ ሁለተኛም፡በሌላ፡ጊዜ፡በዳዊት፡መዝሙር፡ ሲያመሰግን፡ ከዚያ ፡ አንድ፡ ጋኔን ፡ የሚጥ

www.ethiopianorthodox.org

ዘያወድቆ ፡ ጋኔን ፡ ከልሐ፡ ወይቤ ፡ ኅድገኒ፡ ከመ፡እጥፋእ፡እምህየ፡ኦ፡ቅዱሱ፡ለእግዚአ ብሔር ወቅዱስኒ ፡ ቢፋሞን፡ ጸለየ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ፡ ወአሕየዎ ፡ ለውእቱ ፡ ዘጋኔን ። ወርእዮ፡ቀሲስ፡መምህሩ፡ወሰከ፡አክብሮቶ፡ ለቢፋሞን፡ እስመ፡ ውእቱ ፡ ኮነ፡ ዘይልሕቅ፡ በገቢረ፡ትሩፋት፡መንፈሳውያት፡ዘእንበለ፡ ጽርዓት ፡ ወኮነ ፡ እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ፡ ሎቱ፡ስብሐት፡ዘያስተርእዮ፡በውስተ፡ ማኅደሩ፡ወቅዱሳን፡መላእክቲሁ፡ምስሌሁ፡ ወእግዝእትነ፡ማርያም፡ድንግል፡ ወላዲተ፡ አምላክ ፡ ኀቡረ ፡ ይናዝዝዎ ፡ ወነበረ ፡ ኀበ፡ ውእቱ፡ቀሲስ፡መምህሩ፡፰ተ፡ዓመተ።

፲፮፡ ወእምዝ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል፡ ወይጸ ውም፡በበሱባዔ፡ወኢ.ይበልዕ፡ዘእንበለ፡በዕ ለተ ፡ ሰንበት ፡ ወተናገርዎ ፡ አበዊሁ ፡ ከመ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ምንት ፡ ብየ፡ምስለ፡ብእሲት፡ነቢር፡ውስተ፡ዝንቱ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወኵሉ ፡ ፍትወቱ ። ወተፈ ሥሑ፡ቦቱ፡አበዊሁ፡ወወሰኩ፡ገቢረ፡ሠናይ፡ ወበ፺አውራኅ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፡ነገር፡አዕ ረፈ፡አቡሁ፡ቅዱስኒ፡ቢፋሞን፡ወሀበ፡ምጽ ዋተ፡ብዙኀ፡ለነዳያን፡ወለምስኪናን፡ወኮነ፡ ዘይጸመድ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይት ጋደል፡ከመ፡ይፈጽም፡ትእዛዛተ፡ወንጌል፡ ቅዱስ።

፲፯፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ተንሥአ ፡ ጸብእ፡ እምሰብአ፡ፋርስ፡ላዕለ፡ሰብአ፡ሮም፡ወተቀ ትለ፡ንጉሠ፡ሮም፡ወነበረት፡መንግሥተ፡ ሮም፡ዘእንበለ፡ንጉሥ፡ወተጋብኡ፡መኳን ንት፡ ወዐበይተ ፡ መንግሥት ፡ ወተማከሩ ፡ ወአዘዙ ፡ ከመ፡ ያስጋብእዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መስተቃትላን፡ ኃያላን ፡ እምኵሉ ፡ አህጉር፡ ወተረክበ፡፩ብእሲ፡ግዙፈ፡ልብ፡እምላዕላይ፡ ግብጽ። ወውእቱ ፡ ኖላዌ ፡ አጣሊ ፡ ዘስሙ ፡ አግሪጳዳ፡ዘኮነ፡ማኅደረ፡ሰይጣን፡እምንእሱ፡ ወወሰድዎ፡ ብሔረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረሰይዎ ፡ ሊቀ፡ላዕለ፡አፍራስ፡ዘቤተ፡መንግሥት።

፲፰፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ክልኤተ ፡ ኅለተ፡ ነሥአ፡ ወአሠሮ፡ ኅቡረ ፡ ወአንዘረ፡ ቦሙ ፡ አሚሃ ፡ ቦአ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ፡ አፍራስ ፡ ወከልሑ ፡

ለው ፡ ሰው ፡ ነበረ፡የእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ፡ተወኝ፡ከዚህ፡ቦታ፡ልጥፋ፡ብሎ፡ጮኸ፡ የከበረ ፡ ቢፋሞንም፡ ወደ፡ ጌታችን ፡ ጸልዮ ፡ ያንን ፡ ጋኔን ፡ ያደረበትን ፡ ሰው ፡ አዳነው ፡ መምህሩም፡አይቶ፡አክብሮትን፡ለቢፋሞን፡ ጨመረ።እርሱ፡ያለ፡ማቋረጥ፡በመንፈሳዊ፡ ትሩፋት፡ሥራ፡የሚያድግ፡ሁኗልና፡የክብር፡ ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ በማደ ሪያው፡ ውስጥ፡የሚገለጥለት፡ሆነ፡ቅዱሳን፡ መላእክቶቹም፡ከርሱ፡ጋር፡አምላክን፡የወ ለደች፡እመቤታችን፡ድንግል፡ማርያምም፡ በአንድነት፡ያጽናኑት፡ነበር፡በመምህሩም፡ ዘንድ፡ስምንት፡ዓመት፡ኖረ።

፲፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡እየተጋደለ፡ኖረ፡በየሰባት፡ ቀንም ፡ በመጾም ፡ ከሰንበት ፡ ቀን፡ በቀር ፡ አይበላም ፡ ወላጆቹ ፡ ሚስት ፡ እንዲአገባ ፡ ጠየቁት ፡ እርሱም ፡ በዚህ ፡ በሚአልፍ፡ ዓለም፡ከሴት፡ጋር፡መኖር፡ለእኔ፡ምኔ፡ነው፡ ፍላጎቱ ፡ ሁሉ ፡ ያልፋልና፡ አላቸው። ወላጆ ቹም ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ በጎ ፡ መሥራ ትንም፡ጨመሩ። ከዚህም፡ነገር፡በኋላ፡በሰ ባተኛው ፡ ወር ፡ አባቱ ፡ አረፈ፡ የከበረ ፡ ቢፋሞንም፡ለድኆችና፡ለጦም፡አዳሪዎች፡ ምጽዋትን፡ አብዝቶ ፡ ሰጠ ፡ ለቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ አገልግሎትም ፡ የተጠመደ ፡ ሆኖ ፡ የከበረ፡የወንጌልን፡ትእዛዞች፡ለመፈጸም፡ ይጋደል፡ነበር።

፲፯፡ በዚያንም፡ወራት፡የፋርስ፡ሰዎች፡በሮም፡ ሰዎች፡ላይ፡ጦርነት፡አስነሥተው፡ነበር፡ የሮም ፡ ንጉሥም ፡ በጦርነት ፡ ሙቶ ፡ መን ግሥት ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ተቀመጠች ፡ መኳን ንቱና ፡ የመንግሥት ፡ ታላላቆች ፡ ተሰብ ስበው፡ ተማከሩ ፡ ከሁሉ ፡ አገሮችም፡ ተዋጊ ዎች ፡ የሆኑ ፡ አርበኞችን ፡ ይሰበስቧቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዙ ። ከላይኛውም ፡ ግብጽ ፡ ልበ ፡ ደንዳና፡የሆነ፡አንድ፡ሰው፡ተገኘ፡እርሱም፡ ስሙ ፡ አግሪጳዳ ፡ የሚባል፡ የሰይጣን ፡ ማደ ሪያ፡የሆነ፡ፍየሎችን፡የሚያረባ፡ነው፡ወደ፡ አንጾኪያ፡ከተማም፡ወስደው፡ለመንግሥት፡ ፈረሶች፡ባልደራስ፡አድርገው፡ሾሙት።

፲፰፡ በአንዲትም፡ ዕለት ፡ ሁለት ፡ ሸምበቆ ፡ አን ሥቶ ፡ በአንድነት ፡ አሥሮ ፡ ዋሽንት ፡ ነፋ ባቸው ፡ በፈረሶች ፡ ሰይጣን ፡ አደረባቸውና ፡

አፍራስ፡ እንዘ፡ ያንፈርዕፁ ፡ ወወለቱሰ ፡
ለንጉሥ፡ ዘሞተ ፡ ነጸረቶ ፡ በመስኮት ፡
ዘጽርሐ፡ መንግሥት ፡ ወአደማ፡ ፈድፋደ፡
እንዘ፡የዓነዝር፡አግሪጳዳ፡ወወደየ፡ሰይጣን፡
ውስተ፡ልባ፡ፍትወተ፡ዝሙት፡ወጸውዓቶ፡
ለአግሪጳዳ ፡ ኀቤሃ ፡ ወተወሰበት፡ ሎቱ ፡
ወሰመየቶ፡ዲዮቅልጥያኖስሃ፡ ወአንገሦቶ፡
ወሶበ፡ርእየት፡እኅታ፡ዘትንእስ፡ዘገብረት፡
እኅታ፡ ዘትልሕቅ፡ ወቀንአት፡ ይእቲኒ ፡
ነሥአቶ፡ለ፩ዱ፡መኰንን፡ዘስሙ፡መክስም
ያኖስ፡ወተወሰበት፡ሎቱ፡ወረሰየቶ፡ንጉሠ፡
ወአልበሰቶ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት፡ ወኮኑ ፡
መክስምያኖስ ፡ ወዲዮቅልጥያኖስ፡ ዕሩያነ፡
በመንግሥት፡በሀገረ፡አንጾኪያ፡ወሮም።

፲፱፡ ወእምዝ ፡ አስተርአዮሙ፡ ሰይጣን ፡ ወይ
ቤሎሙ፡ አነ፡ ውእቱ ፡ ዘወደይኩ፡ ውስተ፡
ልቦን፡ለአዋልደ፡ንጉሥ፡ፍትወተ፡ዝሙት፡
እስከ ፡ ረሰይኩክሙ፡ ነገሥተ፡ ወይእዜኒ ፡
ለእመ፡ ሰማዕክሙ፡ ትእዛዝየ ፡ እሬስዮሙ ፡
ለኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ እለ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡
ውስተ ፡ እደዊክሙ ፡ ወአንትሙ ፡ ስግዱ ፡
ሊተ፡ወግበሩ፡አምሳላተ፡ዘወርቅ፡ወብሩር፡
ወስምይዎሙ፡አማልክተ፡ወጸውዕዎሙ፡አጽ
ሎንሃ ፡ ወአርዳሚስሃ ፡ ወአዝዝዎሙ ፡ ለኵ
ሎሙ፡ ሰብእ፡ ይውግሩ፡ ዕጣነ፡ ለአማልክት፡
ወይስግዱ ፡ ሎሙ ፡ ወዕጽዉ፡ አብ
ያተ፡ ክርስቲያናት ፡ ኵሎን ፡ ወአርኅዉ፡ አብ
ያተ፡ አማልክትየ፡ ለእለሰ፡ ኢይሰምዑ፡ ትእዛ
ዘክሙ ፡ ወኢየሰግዱ ፡ ለአማልክት ፡ ኰንን
ዎሙ ፡ ኵነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ በዘዘዚአሁ ፡ ኵነኔ ፡
ወምትሩ፡አርእስቲሆሙ፡በአስይፍት።

፳፡ ወሰሚያሙ ፡ እሙንቱ ፡ አብዳን ፡ ዲዮቅልጥያ
ኖስ ፡ ወመክስምያኖስ ፡ ሰገዱ ፡ ሎቱ፡ ወይቤ
ልዎ፡ንሕነ፡ንገብር፡ኵሎ፡ትእዛዘከ።

፳፩፡ ወሶቤሃ ፡ ሤሙ፡ ፸ተ፡ መኳንንተ፡ ኀሬኔዎስሃ፡
ወአርያኖስሃ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወአዘ
ዝዎሙ፡ከመ፡ይኰንንዎሙ፡ለኵሎሙ፡እለ፡
ኢይሰግዱ፡ለጣዖት፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡ዜና፡
አባ ፡ ቢፋሞን ፡ ብፁዕ፡ ኀዘነ፡ ፈድፋደ፡
ወተኀብአ፡እስከ፡ይጤይቅ፡ዘኮነ። ወጸውዖ፡
ለዐርኩ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወተዘያነው፡ በበይና

ፈረሶችም ፡ እየጨፈሩ ፡ ያሽካኩ ፡ ጀመር ፡
የሞተውም ፡ ንጉሥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በቤተ ፡
መንግሥት፡አዳራሽ፡ሁና፡በመስኮት፡ሲዘ
ፍንና ፡ ዋሽንት ፡ ሲነፋ ፡ አግሪጳዳን ፡ አይ
ታው፡እጅግ፡አማራት፡ሰይጣንም፡በልቧ፡
የዝሙትን ፡ ፍላጎት ፡ ጨመረ፡ ወደርሷም፡
አስጠራችውና፡አገባችው፡ስሙንም፡ዲዮ
ቅልጥያኖስ፡አሰኘታ፡አነገሠችው። ታናሽ፡
እኅቷም ፡ ታላቂቱ ፡ እኅቷ ፡ ያደረገችውን ፡
በአየች ፡ ጊዜ ፡ ቀናች፡ እርሷም፡ መክስም
ያኖስ፡የሚባል፡አንድ፡መኰንን፡መልምላ፡
አገባች ፡ ልብሰ ፡ መንግሥትም ፡ አልብሳ፡
ንጉሥ ፡ አደረገችው፡ መክስምያኖስና ፡ ዲዮ
ቅልጥያኖስም፡በአንጾኪያና፡በሮም፡ተስተ
ካክለው፡ነገሡ።

፲፱፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰይጣን ፡ ተገለጠላቸውና ፡
እንዲህ፡አላቸው፡ነገሥታት፡እስከአደረግ
ኋችሁ ፡ ድረስ ፡ በንጉሡ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች፡
የዝሙትን፡ፍቅር፡በልባቸው፡የጨመርኩ፡
እኔ፡ነኝ። አሁንም ፡ ትእዛዜን ፡ ከሰማችሁ፡
በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡
በእጆቻችሁ፡ውስጥ፡አደርጋቸዋለሁ፡እናን
ተም ፡ ስገዱልኝ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ምስሎ
ችንም፡ ሥርታችሁ ፡ አማልክት ፡ በሏቸው፡
ስማቸውንም ፡ አጵሎን ፡ አርዳሚስ ፡ ብላ
ችሁ፡ ጥሩአቸው ፡ ሰዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ዕጣን ፡
እንዲአሳርጉላቸው፡እንዲሰግዱላቸውም፡እዘ
ዟቸው፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ሁሉ፡ ዝጉ፡
የአማልክትንም ፡ ቤቶች ፡ ክፈቱ ፡ ትእዛዛ
ችሁን ፡ ሰምተው ፡ ለአማልክት ፡ የማይሰግ
ዱትን ፡ ግን ፡ በየአይነቱ ፡ በሆነ ፡ በጽኑዕ፡
ሥቃይ፡ አሠቃዩአቸው፡ ራሶቻቸውንም፡በሰ
ይፍ፡ቆረጡ።

፳፡ እሊህም ፡ ሰነፎች ፡ ዲዮቅልጥያኖስና ፡ መክስ
ምያኖስ፡በሰሙ፡ጊዜ፡ሰገዱለትና፡እኛ፡የአ
ዘዝከንን፡ሁሉ፡እናደርጋለን፡አሉት።

፳፩፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በግብጽ፡ አገር ፡ ሄሬኔዎ
ስንና፡ አርያኖስን ፡ ሁለቱን ፡ መኳንንቶች ፡
ሾሙ ፡ ለጣዖት ፡ የማይሰግዱትን ፡ ሁሉ ፡ እን
ዲአሠቃዩ ፡ አዘዙአቸው። የከበረ ፡ አባ ፡ ቢፋ
ሞንም ፡ ይህን ፡ ዜና ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ፡
አዘነ ፡ የሆነውንም ፡ እስቲረዳ ፡ ድረስ ፡ ተሠ
ወረ፡ ወዳጁን፡ ቴዎድሮስንም፡ ጠራውና፡ በክ

ቲሆሙ፡ ከመ ፡ ያክዐዉ ፡ ደሞሙ ፡ በእንተ፡ ስሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ ወጸለዩ ፡ ኅቡረ፡ከመ፡ያድኅኖሙ፡እምኵሉ፡እኩይ።

፳፪፤ ወአፈድፈደ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ወተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ በኀበ ፡ ንጉሥ ፡ መክስም ያኖስ ፡ እስመ ፡ ነገርዎ ፡ ከሀድያን ፡ ወይ ቤልዎ ፡ እስመ ፡ ሀሎ ፡ ፩ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ አውሲም ፡ ዘስሙ ፡ ቢፋሞን ፡ ዘእምደወለ ፡ ምስር ፡ ወውእቱ ፡ ይትዓደው ፡ ትእዛዘ ፡ ነገሥት ፡ ወይረግም ፡ አማልክተ ፡ ወይሜንን።

፳፫፤ ወሶቤሃ ፡ ጸሐፈ ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተ ፡ ወፈነወ፡ ኀበ ፡ አርያኖስ ፡ ከመ ፡ ይንሥኦ ፡ ለቅዱስ ፡ ቢፋሞን ወይኰንኖ ፡ እስከ ፡ ይወግር፡ ዕጣነ ፡ ለአማልክት ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይምትር ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወመልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተ ርአዮ ፡ ለአባ ፡ ቢፋሞን ፡ ከመ፡ ይንግሮ ፡ ዘኮነ ፡ ወአጠየቆ ፡ ከመ ፡ ይከውን ፡ ሰማዕተ ፡ ወእሙ ፡ ዘከመ ፡ ትመውት ። ወአረአዮ ፡ አክሊላተ ፡ ዘአ ስተደለወ፡ ሎሙ ፡ እግዚአበሔር ፡ ወአዘዞ ፡ ከመይንሥኦ፡ለገብሩ፡ዲዮጋኖስ፡ምስሌሁ።

፳፬፤ አሜሃ ፡ ተንሥአ ፡ ወቦአ ፡ ኀበ ፡ እሙ ፡ ወነገራ ፡ ኵሎ ፡ ዘርእየ ፡ ወይእቲኒ ፡ ነገረቶ ፡ ዘከመ ፡ ርእየት ፡ ዘንተ ፡ ራእየ ፡ ወተፈሥሐ ፡ ኅቡረ ። ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሩ ፡ ወቆመ ፡ ይጸሊ ፡ እስከ፡ ጽባሕ ፡ ወከዊኖ ፡ ጽባሐ ፡ ፈነወ ፡ ካዕበ ፡ ኀበ፡ ዐርኩ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀቤሁ ፡ ወነ ገሮ ፡ ዘከመ፡ ርእየ ፡ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ ወይቤሎ፡ እምድኅረ ፡ ኀለፈ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት፡ አንተ ፡ ትሠየም ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ወሕንጽ ፡ ሊተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ፡ተፋለጡ፡በተአምኖ።

፳፭፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ በጽሐ፡ አርያኖስ ፡ መኰንን ። ኀበ ፡ ሀገረ ፡ አውሲም ፡ ወአብጽሑሙ ፡ ለልሒቃነ ፡ ሀገር ፡ ወተበ አሎሙ ፡ በእንተ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ እስመ ፡ ስምዐ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይረግም ፡ አማልክተ ፡ ወኀዘኑ ፡ ልሂቃነ ፡ ሀገር ፡ በእንተ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፍቁር ፡ በኀቤሆሙ፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ አባ ፡ ቢፋሞን ፡

ብር ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስ ፡ ስም፡ ደማቸውን ፡ ያፈሱ ፡ ዘንድ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ፡ ከክፉ፡ ነገርም ፡ ሁሉ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ በአ ንድነት ፡ ጸለዩ።

፳፪፤ የከበረ ፡ ቢፋሞንም ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ አብዝቶ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፡ ወሬውም ፡ በንጉሥ ፡ መክሰም ያኖስ ፡ ዘንድ ፡ ተሰማ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ከሀ ዲዎች ፡ ነግረውታልና ፡ በምስር ፡ አውራጅ ፡ በአውሲም ፡ ከተማ ፡ ስሙ ፡ ቢፋሞን ፡ የሚ ባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ የነገሥ ታትን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ አማላክትን ፡ የሚረግምና፡የሚያቃልል፡ነው።

፳፫፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ ቢፋሞንን ፡ ለአማ ልክት ፡ እስከሚዐጥን ፡ ድረስ ፡ እንዲአሠ ቃየው ፡ ያለዚያም ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲ ቆርጥ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አርያኖስ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ፡ ላከ፡የእግዚአብሔርም፡ መልአክ፡የሆነውን፡ ይነግረው ፡ ዘንድ ፡ ለአባ ፡ ቢፋሞን ተገለጠ ለት ፡ በሰማዕትነትም ፡ እንደሚሞት፡ እና ቱም፡ እንደምትሞት ፡ አስረዳው፡ እግዚአብ ሔርም ፡ ያዘጋጀላቸውን ፡ አክሊላት ፡ አሳ የው ፡ አገልጋዩን ፡ ዲዮጋኖስን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር፡ እንዲወስደው፡አዘዘው።

፳፬፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነሣ ፡ ወደ ፡ እናቱም ፡ ገብቶ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ ነገራት ፡ እርሷም ፡ ይህንኑ ፡ ራእይ ፡ እንዳየች ፡ ነገረችው ፡ በአንድነትም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ወደ ፡ ማደሪያውም ፡ ሒዶ ፡ እስቲነጋ ፡ ድረስ ፡ ሊጸልይ ፡ ቆመ ፡ በነጋ ፡ ጊዜ፡ ወደ ፡ ወዳጁ ፡ ቲዎድሮስ ፡ ልኮ ፡ አስመጣው ፡ ራእይንም፡እንዳየ፡ነገረው፡፡ከዚህም፡በኋላ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡ የመከራው ፡ ወራት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ አንተ ፡ ኤጲስቆጶ ስነት ፡ ትሾማለህና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ልኝ ፡ ይህንንም ፡ ነግሮት ፡ ሰላምታ ፡ ተለዋ ውጠው፡ተሳስመው፡ተለያዩ።

፳፭፤ ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አውሲም ፡ ከተማ ፡ መኰንኑ ፡ አርያኖስ ፡ ደረሰ ፡ የሀገር ፡ ታላላቆችንም ፡ አቅርቦ ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡ ቢፋ ሞን፡ ጠየቃቸው ፡ እርሱ ፡ አማልክትን ፡ እንደ ሚረግም ፡ ሰምቷልና ፡ የሀገር ፡ ሽማግሌዎ ችም ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡፡ ቢፍሞን ፡፡ አዘኑ ፡ እርሱ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተወዳጅ ፡ ነውና ። በዚያ ንም ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ቢፋሞን ፡ ተነሥቶ ፡ ረጂም፡

ወጸለየ ፡ ነዋኀ ፡ ጸሎተ ፡ ወተአምኖሙ ፡ ለኵ
ሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ወለብሰ ፡ አልባሰ ፡ ሠና
ያነ ፡ ወተጽዕነ ፡ ዲበ ፡ ፈረስ ፡ ፀዓዳ ፡ ወሖረ ፡
ኀበ ፡ ይነብሩ ፡ ልሒቃነ ፡ ሀገር ፡ ጉቡአነ፡
ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ እሙንቱ ፡ አክበርዎ ፡ ወተአ
ምኅዎ ፡ ወተለዉዎ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ አርያኖስ ፡
መኰንን ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ አርያኖስ፡ ለአባ ፡
ቢፋሞን ፡ ተፈሥሐ ፡ ወተንሥአ ፡ እመንበሩ ፡
ወተአምኆ ፡ ወይቤሎ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ ወተሠ
ጥዎ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ወይቤሎ ፡ ለምንት ፡
ትብለኒ ፡ ሰላመ ፡ እስመ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለሰላም ፡
ፍሥሐ ፡ ሊተሰ ፡ ቦ ፡ ፍሥሐ ፡ በኀበ ፡ አምላ
ኪየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወለከሰ ፡ ወለካል
አኒከ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ለረሲዓን ፡ አል
ብክሙ ፡ ፍሥሐ ፡ በሰማያት ፡ ወይቤሎ ፡ አር
ያኖስ ፡ አንሰ ፡ ኢመጻእኩ ፡ ከመ ፡ ትትናገረኒ ፡
ነገረ ፡ ኀሡመ ፡ አላ ፡ መጻእኩ ፡ በመጽሐፈ ፡
መልእክቱ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡ ትሡዕ ፡ ለአማ
ልክት ፡ አውሥአ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎ ፡ ሐሰ ፡
ርቱዕሰ ፡ ንሡዕ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይደሉ ፡ ወን
ስግድ ፡ ሎቱ ፡ ወአኮ ፡ ለግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ።
እስመ ፡ እሉ ፡ አማልክቀቲክሙ ፡ አፍ ፡ ቦሙ ፡
ወኢይነቡ ፡ ዐይን ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሬእዩ ፡ ዕዝን ፡
ቦሙ ፡ ወኢይሰምዑ ፡ አንፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢያ
ጼንዉ ፡ እድ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይገሡ ፡ እግር ፡
ቦሙ ፡ ወኢየሐውሩ ፡ ወኢይነቡ ፡ በጐራ
ዒቶሙ ፡ ወአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ውስተ ፡ አፉ
ሆሙ ፡ ወገባርያኒሆሙኒ ፡ ለይኩኑ ፡ ኵሎሙ ፡
ከማሆሙ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይሰግድ ፡ ዘእንበለ ፡
ለእግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡
ወምድር ፡ ወኵሉ ፡ ዘውስቴቶሙ ።

፳፯፤ ወሰሚዖ ፡ አርያኖስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ እምአፈ ፡
ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ተምዐ ፡ ጥቀ ፡ ወኰነኖ ፡
ኵነኔ ፡ ዐቢየ ፡ በዘዘዚአሁ ፡ ኵነኔ፡ ወዓዲ ፡
አሠሮ ፡ በዘነበ ፡ ፈረስ ፡ ወሰሐቦ ፡ ኵሎ ፡ ሀገረ ፡
ወበጽሐ ፡ ኵሎሙ ፡ አግብርቲሁ ፡ ወእሙ ፡
ኀቢሁ፡ ሎሙኒ ፡ መሀሮሙ ፡ እምቃለ ፡ ወን
ጌል፡ ቅዱስ ፡ ወገሠጾሙ ፡ ወሶቢሃ ፡ ጸርሑ ፡
ኵሎሙ ፡ ወይቤሉ ፡ ንሕነ ፡ ክርስቲያን ፡ ገሀደ ፡
ወገፍትዑ ፡ መንበሮ ፡ ለመኰንን ፡ ወአዘዘ ፡
መኰንን ፡ ከመ ፡ ይክርዩ፡ ሎሙ ፡ ዐዘቅተ ፡
ወያንድዱ ፡ እሳተ ፡ ወይውርውዎሙ ፡ ውስ

ጸሎትን ፡ ጸለየ ፡ ፡ ቤቱ ፡ ሰቦቹንም ፡ ሁሉ ፡ ተሰ
ናበታቸው ፡ ያማሩ ፡ ልብሶችንም ፡ ለብሶ ፡
በነጭ ፡ ፈረስ ፡ ተቀመጠ ፡ የአገር ፡ ሽማግ
ሌዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ወዳሉበትም ፡ ሔደ ፡
እነርሱም ፡ በአዩት ፡ ጊዜ ፡ አክብረው ፡ ሰላ
ምታ ፡ ሰጡት ፡ ተከትለውትም ፡ ወደ ፡
መኰንኑ ፡ ወደ ፡ አርያኖስ ፡ ሔደ ፡ አርያኖስም ፡
አባ ፡ ቢፋሞንን ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ፡
ከወንበሩም ፡ ተነሥቶ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡
ብሎ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠው ። አባ ፡ ቢፋሞንም ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ለምን ፡ ሰላም ፡
ትለኛለህ ፡ የሰላም ፡ ትርጓሜው ፡ ደስታ ፡
ነውና ፡ ለእኔ ፡ ግን ፡ በጌታዬ ፡ በፈጣሪዬ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ደስታ ፡ አለኝ ፡
ለአንተና ፡ ለባልንጀሮችህ ፡ በሰያማያት ፡
ደስታ፡ የላችሁም ፡ ብሏል ፡ መጽሐፍ ። ፡ አርያ
ኖስም ፡ እኔ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንድትነግረኝ ፡ አል
መጣሁም ፡ ለአማልክት ፡ እንድትሠዋ ፡ በን
ጉሡ ፡ ደብዳቤ ፡ ታዝዤ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ ፡
አለው ፡ ቅዱሱም ፡ መልሶ ፡ ይህ ፡ አይገባም ፡
ትክክለኛውስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንድንሠዋ፡
ለእርሱም ፡ እንድንሰግድ ፡ ይገባል ፡ እሊህ ፡
አማልክቶቻችሁ ፡ አፍ ፡ አላቸው ፡ አይናገሩም፡
ዓይን ፡ አላቸው ፡ አያዩም ፡ ጆሮ ፡ አላቸው ፡
አይሰሙም ፡ አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱም ፡
እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳስሱም ፡ እግር ፡ አላቸው ፡
አይሔዱም ፡ በአንደበታቸውም ፡ አይናገሩም ፡
በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ትንፋሽ ፡ የለምና ፡ የሠሩአ
ቸውም ፡ እንደነርሱ ፡ ይሁኑ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ሰማ
ይና ፡ ምድርን ፡ በውስጣቸው ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
ከፈጠረ ፡ ከጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፡
ለሌላ ፡ አልሰግድም ፡ አለው ።

፳፯፤ አርያኖስም ፡ ከቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ አፍ ፡ ይህን ፡
ነገር ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ተቆጣ ፡ በየዓይነቱም ፡
ታላቅ ፡ ሥቃይን ፡ አሠቃየው ፡ ዳግመኛም ፡ በፈ
ረስ ፡ ጅራት ፡ አሥሮ ፡ መላ ፡ ከተማውን ፡ አስጐ
ተተው ፡ እናቱና ፡ አገልጋዮቹም ፡ ሁሉ ፡ ወደ
ርሱ ፡ መጡ ፡ እነርሱንም ፡ ከከበረ ፡ የወንጌል ፡
ቃል ፡ አስተማራቸው ፡ ገሠጻቸውም ፡ በዚያ
ንም ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ነን ፡
ብለው ፡ ጮኹ ፡ የመኰንኑን ፡ ወንበር ፡ ገለ
በጡ ፡ መኰንኑም ፡ ጕድጓድ ፡ እንዲቆፍሩላ
ቸውና ፡ እሳትንም ፡ አንድደው ፡ በውስጡ ፡

ቴቱ ፡ ሕያዋኒሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ወገብሩ ፡ ቦሙ፡በከመ፡አዘዘ፡ወኍልቆሙ፡፳፻ት።

፳፯፡ ወኮነ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ያጸንዖሙ ፡ ወያስተ ፄግሦሙ፡እስከ፡ፈጸሙ፡ስምዖሙ፡ወእሙኒ፡ ሰአልቶ ፡ ለወልዳ ፡ ቢፋሞን ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ላዕሌሃ ፡ ውእቱኒ ፡ አተበ ፡ ላዕሌሃ ፡ በትእም ርተ ፡ መስቀል ፡ ወይቤላ ፡ ሑሪ ፡ በሰላም ፡ በሶቢሃ ገደፈት ፡ ነፍሳ ፡ ውስተ ፡ እሳት ወነሥአት፡አክሊለ፡ስምዕ፡ምስሌሆሙ።

፳፰፡ ወለቅዱስሰ ፡ ቢፈሞን ፡ ፈነዎ ፡ አርያኖስ ፡ ኀበ ፡ መክስሞያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ አንተኑ ፡ ቢፋሞን ፡ መሠርይ ፡ ዘትት ዓደው ፡ ትእዛዘ ፡ ነገሥት ፡ ወኢትሰግድ ፡ ለአ ማልክት ፡ አውሥአ ፡ ቅዱስ፡ ወይቤሎ ፡ ሥራ ይሰ ፡ አልብየ ፡ ወኢይሰግድ ፡ ለአማልክት ፡ ርኩሳን ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ወአማልክቲከ ፡ ኀቡረ ፡ ትወርዱ ፡ ውስተ ፡ እሳተ ፡ ገሀነም ፡ ወተምዐ ፡ ንጉሥ ወኰነኖ ፡ ኵነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ እምኰንኖቱ ፡ ፈነዎ ፡ ኀበ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ ውእቱኒ ፡ ፈነዎ ፡ ኀበ ፡ አርያኖስ ፡ ወቅዱስኒ፡ ኢጥዕመ ፡ ምንተኒ ፡ በእላ ፡ መዋ ዕል።

፳፱፡ ወነሥአ ፡ አርያኖስ ፡ ወቀነዎ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ በቅንዋተ ፡ ኀፂን ፡ ወለእመ ፡ ኢሰገድከ ፡ አጠፍአከ ፡ ቅዱስሰ ፡ጸረፈ ፡ ላዕ ሌሁ፡ወላዕለ፡አማላክቲሁ፡ወረገሞሙ፡ወእ ምገ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይስሐብዎ ፡ ውስተ ፡ ኵላ ፡ ፍኖተ ፡ ሀገር ፡ ወያውዕይዎ ፡ በእሳተ ፡ አፍኣ ፡ ሀገረ ፡ እንደ፡ናው ፡ ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ወእግዚእነ ፡ አውጽኦ ፡ እምእ ሳት፡ዘእንበለ፡ሙስና፡ወሶበ፡ኮነ፡ይቀውም፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ቅዱስ፡ ቢፋሞን፡ውኀዘ፡እም እገሪሁ ፡ ደም ፡ ብዙኅ ፡ ወሀሎ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ዘይቀውም፡ምስለ፡ሕዝብ፡ወውእቱ፡ዕውር፡ ወልሙጽ ፡ ሥጋሁ፡ወነሥአ፡እምደም፡ወቀ ብዐ፡አዕይንቲሁ። ወርእየ፡ሶቢሃ፡ወነጽሐ፡ እምለምጹሂ፡ወአሚሃ፡ጸርሐ፡እንዘ፡ይብል፡ ክርስቲያናዊ፡አነ፡ዘእትአመን፡በእግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ስብሐት፡ወአዘዘ፡ መኰንን፡ይምትሩ፡ርእሶ፡በሰይፍ፡ወነሥአ፡ አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

በሕይወት፡ሳሉ፡እንዲወረውሩአቸው፡አዘዘ፡ እንደአዘዘውም ፡ አደረጉባቸው ፡ ቍጥራቸ ውም፡አምስት፡መቶ፡ነው።

፳፯፡ ምስክርነታቸውንም ፡ እስኪፈጽሙ ፡ የከበረ፡ ቢፋሞን ፡ ያጽናናቸውና ፡ ያስታታግሣቸው ፡ ነበር ፡ እናቱም ፡ ልጅዋ ፡ ቢፋሞንን ፡ በላይዋ ፡ እንዲጸልይ፡ለመነችው፡እርሱም፡በመስቀል፡ ምልክት ፡ በላይዋ ፡ አማተበና ፡ በሰላም፡ ሒጂ ፡ አላት ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቷን ፡ በእሳት ፡ ውስጥ፡ጣለች።ከእነሱ፡ጋርም፡የሰማዕትነት፡ አክሊልን፡ተቀበለች።

፳፰፡ የከበረ ፡ ቢፍሞንን ፡ ግን ፡ አርያኖስ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ፡ መክስምያኖስ ፡ ሰደደው ፡ ንጉሡም ፡ የነገሥታትን ፡ ትእዛዝ ፡ የምትተላለፍ ፡ ለአማ ልክት፡ የማትሰግድ ፡ ሥራየኛው ፡ ቢፋሞን ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ። ቅዱሱም ፡ ሥራይን ፡ ግን፡አላውቅም፡ለረከሱ፡አማላክትም፡አልሰ ግድም ፡ አንተና ፡ አማላክቶችህ ፡ በአንድነት ፡ ወደ፡ገሀነም፡እሳት፡ትወርዳላችሁና፡አለው፡ ንጉሡም ፡ ተቆጥቶ ፡ ጽኑዕ ፡ ሠቃይን ፡ አሠቃየው ፡ ከማሠቃየትም ፡ በሰለቸ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኄሬኔዎስ ፡ ሰደደው ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ አርያኖስ ፡ ሰደደው ፡ በእነዚያ፡ ቀኖችም ፡ ምንም፡አልበላም።

፳፱፡ አርያኖስም ፡ ወስዶ ፡ በብረት ፡ ችንካሮች ፡ ቸነከረውና ፡ ለአማልክት ፡ ካልሰገድክ ፡ አጠፋ ሃለሁ ፡ አለው ፡ ቅዱሱም ፡ እርሱንና ፡ አማልክ ቶቹን ፡ ዘለፈ ፡ ረገማቸውም ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በከተማዪቱ፡ሁሉ፡መንገድ፡እንዲጎትቱትና፡ ከእንደ፡ናው ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡ እንዲአ ቃጥሉት ፡ መኰንኑ ፡ አዘዘ ፡ ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ አደረጉበት ፡ ጌታችንም ፡ ያለ ፡ ጥፋት ፡ በጤና ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ አወጣው ፡ የከበረ ፡ ቢፋ ሞንም፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ከእግሮቹ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡ ከሕዝብ ፡ ጋር ፡ የቆመ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ ለም ጻምና ፡ ዕውር ፡ ነበር ፡ ከደሙም ፡ ወስዶ ፡ ዓይኖቹን ፡ ቀባ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አየ ፡ ከለምጹም ፡ ነጻ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የምታመን ፡ ክርስቲየን ፡ ነኝ ፡ ብሎ፡ ጮኸ ፡ ራሱንም ፡ እንዲቆርጡ ፡ መኰንኑ ፡ አዘዘና፡ቆረጡት፡የሰማዕትነት፡አክሊልንም፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፡ ወለቅዱስኒ ፡ አባ ፡ ቢፋሞን ፡ አዘዘ ፡ አርያኖስ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወአዘዞ ፡ ቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ለገብሩ ፡ ዲዮጋኖስ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ሥጋሁ ፡ በኅቡእ ፡ ወይንሣእ ፡ ደሞ ፡ በሰንዱን ፡ ወይንግር ፡ ገድሎ ፡ ለመሃይምናን ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ አውሲም ፡ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ይኅልፍ ፡ መዋዕለ ፡ ምንዳቤ ፡ ወእምዝ ፡ አተበ ፡ ገጾ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ እንዘ ፡ ይብል በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ወቀርበ ፡ ኀበ ፡ ሐራ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ግበሩ ፡ ዘተአዘዝክሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ነሥእዎ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ባሕቲቶ ፡ ወመተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰ ይፍ ፡ ወውኅዘ ፡ ደም ፡ ብዙኅ ፡ እምክሣዱ ፡ ወዲ ዮጋኖስ ፡ ገብሩ ፡ ሰፍሐ ፡ ሰንዱነ ፡ ዘኀቤሁ ፡ ወተቀበለ ፡ ቦቱ ፡ ደሞ ፡ ለቅዱስ ፡ ቢፋሞን ፡ ወመልአ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ጼና ፡ ጥዑም ፈድፋደ ፡ እስከ ፡ አንከሩ ፡ ሐራ ፡ ወደንገፁ ፡ ወወረደ ፡ ላዕሌሆሙ፡ ፍርሀት ፡ ዐቢይ ፡ ወጐዩ ፡ እምዝንቱ ፡ መካን ።

